## ክፍል አንድ

## ህገ መንግስት፣ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ መንግስት መመስረት፣

## ሰንደቅ አላማ እና ብሄራዊ መዝሙር

## አዋጅ ቁጥር 1/1987

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት በሥራ ላይ መዋሉን ለማሳወቅ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መርጠው በላኳቸው ተወካዮቻቸው አማካይነት ኅዳር 29 ቀን 1987 ዓ.ም. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥትን ያጸደቁ በመሆኑ የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አዋጅ ቁጥር 1/1987" ዓ.ም. ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ሕገ መንግሥቱ በሥራ ላይ ስለመዋሉ**

   የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ከነሐሴ 15 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ ሙሉ በሙሉ በሥራ ላይ ውሏል፡፡

3. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ አዋጅ ከነሐሴ 15 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 15 ቀን 1987 ዓ.ም.**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## መግቢያ

እኛ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች፦

በሀገራችን ኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ ሰላም፣ ዋስትና ያለው ዴሞክራሲ እንዲሰፍን፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እድገታችን እንዲፋጠን፣ የራሳችን ዕድል በራሳችን የመወሰን መብታችንን ተጠቅመን፣ በነፃ ፍላጎታችን፣ በሕግ የበላይነት እና በራሳችን ፈቃድ ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ ለመገንባት ቆርጠን በመነሳት፤

ይህን ዓላማ ከግብ ለማድረስ፣ የግለሰብና የብሔር/ብሔረሰብ መሰረታዊ መብቶች መከበራቸው፣ የፆታ እኩልነት መረጋገጡ፣ ባሕሎችና ሃይማኖቶች ካለ አንዳች ልዩነት እንዲራመዱ የማድረጉ አስፈላጊነት ጽኑ እምነታችን በመሆኑ፤

ኢትዮጵያ ሀገራችን የየራሳችን አኩሪ ባሕል ያለን፣ የየራሳችን መልክዓ ምድር አሰፋፈር የነበረንና ያለን፣ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በተለያዩ መስኮችና የግንኙነት ደረጃዎች ተሳስረን አብረን የኖርንባትና የምንኖርባት ሀገር በመሆንዋ፤ ያፈራነው የጋራ ጥቅምና አመለካከት አለን ብለን ስለምናምን፤

መጪው የጋራ ዕድላችን መመስረት ያለበት ከታሪካችን የወረስነውን የተዛባ ግንኙነት በማረምና የጋራ ጥቅማችንን በማሳደግ ላይ መሆኑን በመቀበል፤

ጥቅማችንን፣ መብታችንና ነፃነታችንን በጋራ እና በተደጋጋፊነት ለማሳደግ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ የመገንባቱን አስፈላጊነት በማመን፤

በትግላችንና በከፈልነው መስዋዕትነት የተገኘውን ዴሞክራሲና ሰላም ዘላቂነቱን ለማረጋገጥ፤

ይህ ሕገመንግሥት ከዚህ በላይ ለገለጽናቸው ዓላማዎችና እምነቶች ማሰሪያ እንዲሆነን እንዲወክሉን መርጠን በላክናቸው ተወካዮቻችን አማካይነት በሕገ መንግሥት ጉባዔ ዛሬ ኅዳር 29 ቀን 1987 አጽድቀነዋል።

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 1

### የኢትዮጵያ መንግሥት ስያሜ

ይህ ሕገመንግሥት ፌዴራላዊና ዴሞክራሲያዊ የመንግሥት አወቃቀር ይደነግጋል፡፡ በዚህ መሰረት የኢትዮጵያ መንግሥት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በሚል ስም ይጠራል፡፡

### አንቀጽ 2

## የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን

የኢትዮጵያ የግዛት ወሰን የፌዴራሉን አባሎች ወሰን የሚያጠቃልል ሆኖ በዓለም አቀፍ ስምምነቶች መሰረት የተወሰነው ነው፡፡

## አንቀጽ 3

## የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ

1. የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሐል ቢጫ፣ ከታች ቀይ ሆኖ በመሐሉ ብሔራዊ ዓርማ ይኖረዋል፡፡ ሦስቱም ቀለማት እኩል ሆነው በአግድም ይቀመጣሉ፡፡
2. ከሰንደቅ ዓላማው ላይ የሚቀመጠው ብሔራዊ ዓርማ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች እና ሃይማኖቶች በእኩልነትና በአንድነት ለመኖር ያላቸውን ተስፋ የሚያንጸባርቅ ይሆናል፡፡
3. የፌዴራሉ አባሎች የየራሳቸው ሰንደቅ ዓላማና ዓርማ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ዝርዝሩን በየራሳቸው ምክር ቤት ይወስናሉ።

## አንቀጽ 4

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር

የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር የሕገ መንግሥቱን ዓላማዎችና የኢትዮጵያ ሕዝቦች በዴሞክራሲ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን እምነት፣ እንዲሁም የወደፊት የጋራ ዕድላቸውን የሚያንጸባርቅ ሆኖ በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 5

## ስለ ቋንቋ

1. ማናቸውም የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በእኩልነት የመንግሥት እውቅና ይኖራቸዋል፡፡
2. አማርኛ የፌዴራሉ መንግሥት የሥራ ቋንቋ ይሆናል፡፡
3. የፌዴሬሽኑ አባሎች የየራሳቸውን የሥራ ቋንቋ በሕግ ይወስናሉ።

## አንቀጽ 6

## ስለ ዜግነት

1. ወላጆቹ/ወላጆቿ ወይም ከወላጆቹ/ከወላጆቿ አንደኛቸው ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት የሆነ/የሆነች የኢትዮጵያ ዜጋ ነው/ናት፡፡
2. የውጭ ሀገር ዜጎች የኢትዮጵያ ዜግነት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡
3. ዜግነትን በሚመለከት ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 7

## የፆታ አገላለጽ

በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የሕገ መንግሥቱ መሰረታዊ መርሆዎች

## አንቀጽ 8

## የሕዝብ ሉዓላዊነት

1. የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የኢትዮጵያ ሉዓላዊ ሥልጣን ባለቤቶች ናቸው፡፡
2. ይህ ሕገ መንግሥት የሉዓላዊነታቸው መግለጫ ነው፡፡
3. ሉዓላዊነታቸውም የሚገለጸው በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት በሚመርጧቸው ተወካዮቻቸውና በቀጥታ በሚያደርጉት ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ አማካይነት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 9

## የሕገ መንግሥት የበላይነት

1. ሕገ መንግሥቱ የሀገሪቱ የበላይ ሕግ ነው፡፡ ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሠራር፣ እንዲሁም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን ውሳኔ ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር የሚቃረን ከሆነ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡
2. ማንኛውም ዜጋ፣ የመንግሥት አካላት፣ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ሌሎች ማኅበራት እንዲሁም ባለሥልጣኖቻቸው፣ ሕገ መንግሥቱን የማስከበርና ለሕገ መንግሥቱ ተገዥ የመሆን ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3. በዚህ ሕገ መንግሥት ከተደነገገው ውጭ በማናቸውም አኳኋን የመንግሥት ሥልጣን መያዝ የተከለከለ ነው፡፡
4. ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የሀገሪቱ ሕግ አካል ናቸው፡፡

## አንቀጽ 10

## ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች

1. ሰብዓዊ መብቶችና ነፃነቶች ከሰው ልጅ ተፈጥሮ የሚመነጩ የማይጣሱና የማይገፈፉ ናቸው፡፡
2. የዜጎች እና የሕዝቦች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ይከበራሉ፡፡

## አንቀጽ 11

## የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት

1. መንግሥትና ሃይማኖት የተለያዩ ናቸው፡፡
2. መንግሥታዊ ሃይማኖት አይኖርም፡፡
3. መንግሥት በሃይማኖት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡ ሃይማኖትም በመንግሥት ጉዳይ ጣልቃ አይገባም፡፡

## አንቀጽ 12

## የመንግሥት አሠራርና ተጠያቂነት

1. የመንግሥት አሠራር ለሕዝብ ግልጽ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት፡፡
2. ማንኛውም ኃላፊና የሕዝብ ተመራጭ ኃላፊነቱን ሲያጓድል ተጠያቂ ይሆናል፡፡
3. ሕዝብ በመረጠው ተወካይ ላይ እምነት ባጣ ጊዜ ከቦታው ለማንሳት ይችላል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## መሰረታዊ መብቶችና ነፃነቶች

## አንቀጽ 13

## ተፈጻሚነትና አተረጓጎም

1. በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራል መንግሥትና የክልል ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚ እና የዳኝነት አካሎች በዚህ ምዕራፍ የተካተቱትን ድንጋጌዎች የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታ አለባቸው፡፡
2. በዚህ ምዕራፍ የተዘረዘሩት መሰረታዊ የመብቶችና የነፃነቶች ድንጋጌዎች ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ሕጋጋት፣ ዓለም አቀፍ የሰብዓዊ መብቶች ስምምነቶችና ዓለም አቀፍ ሠነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማሉ፡፡

## ክፍል አንድ

## ሰብዓዊ መብቶች

## አንቀጽ 14

## የሕይወት፣ የአካል ደህንነትና የነፃነት መብት

ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ በመሆኑ የማይደፈርና የማይገሰስ በሕይወት የመኖር፣ የአካል ደህንነትና፣ የነፃነት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 15

## የሕይወት መብት

ማንኛውም ሰው በሕይወት የመኖር መብት አለው፡፡ ማንኛውም ሰው በሕግ በተደነገገ ከባድ የወንጀል ቅጣት ካልሆነ በስተቀር ሕይወቱን አያጣም፡፡

## አንቀጽ 16

## የአካል ደህንነት መብት

ማንኛውም ሰው በአካሉ ላይ ጉዳት እንዳይደርስበት የመጠበቅ መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 17

## የነፃነት መብት

1. በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ማንኛውም ሰው ወንድም ሆነ ሴት ነፃነቱን/ቷን አያጣም/አታጣም፡፡
2. ማንኛውም ሰው በሕግ ከተደነገገው ሥርዓት ውጭ ሊያዝ፣ ክስ ሳይቀርብበት ወይም ሳይፈረድበት ሊታሰር አይችልም፡፡

## አንቀጽ 18

## ኢሰብዓዊ አያያዝ ስለመከልከሉ

1. ማንኛውም ሰው ጭካኔ ከተሞላበት፣ ኢሰብዓዊ ከሆነ ወይም ክብሩን ከሚያዋርድ አያያዝ ወይም ቅጣት የመጠበቅ መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም ሰው በባርነት ወይም በግዴታ አገልጋይነት ሊያዝ አይችልም፡፡ ለማንኛውም ዓላማ በሰው የመነገድ ተግባር የተከለከለ ነው፡፡
3. ማንኛውም ሰው በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት ማንኛውንም ሥራ እንዲሠራ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 "በኃይል ተገዶ ወይም ግዴታን ለማሟላት" የሚለው ሐረግ የሚከተሉትን ሁኔታዎች አያካትትም፤

ሀ/ ማንኛውም እስረኛ በእስራት ላይ ባለበት ጊዜ በሕግ መሰረት እንዲሠራ የተወሰነውን ወይም በገደብ ከእስር በተለቀቀበት ጊዜ የሚሠራውን ማንኛውም ሥራ፣

ለ/ ማንኛውም ወታደራዊ አገልግሎት ለመስጠት ሕሊናው የማይፈቅድለት ሰው በምትክ የሚሰጠውን አገልግሎት፣

ሐ/ የማኅበረሰቡን ሕይወት ወይም ደህንነት የሚያሰጋ የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም አደጋ በሚያጋጥምበት ጊዜ የሚሰጥ ማንኛውንም አገልግሎት፣

መ/ በሚመለከተው ሕዝብ ፈቃድ በአካባቢው የሚፈጸመውን ማንኛውም ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ የልማት ሥራ፡፡

## አንቀጽ 19

## የተያዙ ሰዎች መብት

1. ወንጀል ፈጽመዋል በመባል የተያዙ ሰዎች የቀረበባቸው ክስና ምክንያቶቹ በዝርዝር ወዲያውኑ በሚገባቸው ቋንቋ እንዲነገራቸው መብት አላቸው፡፡
2. የተያዙ ሰዎች ላለመናገር መብት አላቸው፣ የሚሰጡት ማንኛውም ቃል ፍርድ ቤት በማስረጃነት ሊቀርብባቸው እንደሚችል መረዳት በሚችሉት ቋንቋ እንደተያዙ ወዲያውኑ ማስገንዘቢያ እንዲሰጣቸው መብት አላቸው፡፡
3. የተያዙ ሰዎች በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ፍርድ ቤት የመቅረብ መብት አላቸው፡፡ ይህም ጊዜ ሰዎቹ ከተያዙበት ቦታ ወደ ፍርድ ቤት ለመምጣት አግባብ ባለው ግምት የሚጠይቀውን ጊዜ አይጨምርም፡፡ ወዲያውኑ ፍርድ ቤት እንደቀረቡ በተጠረጠሩበት ወንጀል ለመታሰር የሚያበቃ ምክንያት ያለ መሆኑ ተለይቶ እንዲገለጽላቸው መብት አላቸው፡፡
4. የያዛቸው የፖሊስ መኮንን ወይም የሕግ አስከባሪ በጊዜው ገደብ ፍርድ ቤት በማቅረብ የተያዙበትን ምክንያት ካላስረዳ፣ ፍርድ ቤቱ የአካል ነፃነታቸውን እንዲያስከብርላቸው የመጠየቅ ሊጣስ የማይችል መብት አላቸው፡፡ ሆኖም ፍትሕ እንዳይጓደል ሁኔታው የሚጠይቅ ከሆነ ፍርድ ቤቱ የተያዘው ሰው በጥበቃ ስር እንዲቆይ ለማዘዝ ወይም ምርመራ ለማካሄድ ተጨማሪ ጊዜ ሲጠየቅ አስፈላጊ በሆነ መጠን ብቻ ሊፈቅድ ይችላል፡፡ የሚያስፈልገውን ተጨማሪ የምርመራ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ሲወስን ኃላፊ የሆኑት የሕግ አስከባሪ ባለሥልጣኖች ምርመራውን አጣርተው የተያዘው ሰው በተቻለ ፍጥነት ፍርድ ቤት እንዲቀርብ ያለውን መብት የሚያስከብር መሆን አለበት፡፡
5. የተያዙ ሰዎች በራሳቸው ላይ በማስረጃነት ሊቀርብ የሚችል የእምነት ቃል እንዲሰጡ ወይም ማናቸውንም ማስረጃ እንዲያምኑ አይገደዱም፡፡ በማስገደድ የተገኘ ማስረጃ ተቀባይነት አይኖረውም፡፡
6. የተያዙ ሰዎች በዋስ የመፈታት መብት አላቸው፡፡ ሆኖም በሕግ በተደነገጉ ልዩ ሁኔታዎች ፍርድ ቤት ዋስትና ላለመቀበል ወይም በገደብ መፍታትን ጨምሮ በቂ የሆነ የዋስትና ማረጋገጫ እንዲቀርብ ለማዘዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 20

## የተከሰሱ ሰዎች መብት

1. የተከሰሱ ሰዎች ክስ ከቀረበባቸው በኋላ ተገቢ በሆነ አጭር ጊዜ ውስጥ በመደበኛ ፍርድ ቤት ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ችሎት የመሰማት መብት አላቸው፡፡ ሆኖም የተከራካሪዎቹን የግል ሕይወት፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታና የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ ሲባል ብቻ ክርክሩ በዝግ ችሎት ሊሰማ ይችላል፡፡
2. ክሱ በቂ በሆነ ዝርዝር እንዲነገራቸው እና ክሱን በጽሑፍ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
3. በፍርድ ሂደት ባሉበት ጊዜ በተከሰሱበት ወንጀል እንደ ጥፋተኛ ያለመቆጠር፣ በምስክርነት እንዲቀርቡም ያለመገደድ መብት አላቸው፡፡
4. የቀረበባቸውን ማናቸውንም ማስረጃ የመመልከት፣ የቀረቡባቸውን ምስክሮች የመጠየቅ፣ ለመከላከል የሚያስችላቸውን ማስረጃ የማቅረብ ወይም የማስቀረብ እንዲሁም ምስክሮቻቸው ቀርበው እንዲሰሙላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡
5. በመረጡት የሕግ ጠበቃ የመወከል ወይም ጠበቃ ለማቆም አቅም በማጣታቸው ፍትሕ ሊጓደል የሚችልበት ሁኔታ ሲያጋጥም ከመንግሥት ጠበቃ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
6. ክርክሩ በሚታይበት ፍርድ ቤት በተሰጠባቸው ትእዛዝ ወይም ፍርድ ላይ ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አላቸው፡፡
7. የፍርዱ ሂደት በማይገባቸው ቋንቋ በሚካሄድበት ሁኔታ በመንግሥት ወጪ ክርክሩ እንዲተረጎምላቸው የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 21

## በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች መብት

1. በጥበቃ ስር ያሉና በፍርድ የታሰሩ ሰዎች ሰብዓዊ ክብራቸውን በሚጠብቁ ሁኔታዎች የመያዝ መብት አላቸው፡፡
2. ከትዳር ጓደኞቻቸው፣ ከቅርብ ዘመዶቻቸው፣ ከጓደኞቻቸው፣ ከሃይማኖት አማካሪዎቻቸው፣ ከሐኪሞቻቸው እና ከሕግ አማካሪዎቻቸው ጋር ለመገናኘትና እንዲጎበኟቸውም ዕድል የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 22

## የወንጀል ሕግ ወደኋላ ተመልሶ የማይሠራ ስለ መሆኑ

1. ማንኛውም ሰው የወንጀል ክስ ሲቀርብበት የተከሰሰበት ድርጊት በተፈጸመበት ጊዜ ድርጊቱን መፈጸሙ ወይም አለመፈጸሙ ወንጀል መሆኑ በሕግ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር ሊቀጣ አይችልም፡፡ እንዲሁም ወንጀሉን በፈጸመበት ጊዜ ለወንጀሉ

ተፈጻሚ ከነበረው የቅጣት ጣሪያ በላይ የከበደ ቅጣት በማንኛውም ሰው ላይ አይወሰንም፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ቢኖርም፣ ድርጊቱ ከተፈጸመ በኋላ የወጣ ሕግ ለተከሳሹ ወይም ለተቀጣው ሰው ጠቃሚ ሆኖ ከተገኘ ከድርጊቱ በኋላ የወጣው ሕግ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 23

## በአንድ ወንጀል ድጋሚ ቅጣት ስለመከልከሉ

ማንኛውም ሰው በወንጀል ሕግና ሥርዓት መሰረት ተከሶ የመጨረሻ በሆነ ውሳኔ ጥፋተኛነቱ በተረጋገጠበት ወይም በነፃ በተለቀቀበት ወንጀል እንደገና አይከሰስም ወይም አይቀጣም፡፡

## አንቀጽ 24

## የክብርና የመልካም ስም መብት

1. ማንኛውም ሰው ሰብዓዊ ክብሩና መልካም ስሙ የመከበር መብት አለው፡፡
2. ማንኛውም ሰው የራሱን ስብዕና ከሌሎች ዜጎች መብቶች ጋር በተጣጣመ ሁኔታ በነፃ የማሳደግ መብት አለው፡፡
3. ማንኛውም ሰው በማንኛውም ስፍራ በሰብዓዊነቱ እውቅና የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 25

## የእኩልነት መብት

ሁሉም ሰዎች በሕግ ፊት እኩል ናቸው፤ በመካከላቸውም ማንኛውም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግ በሕግ እኩል ጥበቃ ይደረግላቸዋል፡፡ በዚህ ረገድ በዘር፣ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በቀለም፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ፣ በማኅበራዊ አመጣጥ፣ በሀብት፣ በትውልድ ወይም በሌላ አቋም ምክንያት ልዩነት ሳይደረግ ሰዎች ሁሉ እኩልና ተጨባጭ የሕግ ዋስትና የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 26

## የግል ሕይወት የመከበርና የመጠበቅ መብት

1. ማንኛውም ሰው የግል ሕይወቱ፣ ግላዊነቱ፣ የመከበር መብት አለው፡፡ ይህ መብት መኖሪያ ቤቱ፣ ሰውነቱና ንብረቱ ከመመርመር እንዲሁም በግል ይዞታው ያለ ንብረት ከመያዝ የመጠበቅ መብት ያካትታል፡፡
2. ማንኛውም ሰው በግል የሚጽፋቸውና የሚጻጻፋቸው፣ በፖስታ የሚልካቸው ደብዳቤዎች፣ እንዲሁም በቴሌፎን፣ በቴሌኮሙኒኬሽንና በኤሌክትሮኒክ መሣሪያዎች የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች አይደፈሩም፡፡
3. የመንግሥት ባለሥልጣኖች እነዚህን መብቶች የማክበርና የማስከበር ግዴታ አለባቸው፡፡ አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲፈጠሩና ብሔራዊ ደህንነትን፣ የሕዝብን ሰላም፣ ወንጀልን በመከላከል፣ ጤናንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ በመጠበቅ ወይም የሌሎችን መብትና ነፃነት በማስከበር ዓላማዎች ላይ በተመሰረቱ ዝርዝር ሕጎች መሰረት ካልሆነ በስተቀር የእነዚህ መብቶች አጠቃቀም ሊገደብ አይችልም፡፡

## <u>አንቀጽ 27</u>

## <u>የሃይማኖት፣ የእምነትና የአመለካከት ነፃነት</u>

1. ማንኛውም ሰው የማሰብ፣ የሕሊና እና የሃይማኖት ነፃነት አለው፡፡ ይህ መብት ማንኛውም ሰው የመረጠውን ሃይማኖት ወይም እምነት የመያዝ ወይም የመቀበል፣ ሃይማኖቱንና እምነቱን ለብቻ ወይም ከሌሎች ጋር በመሆን በይፋ ወይም በግል የማምለክ፣ የመከተል፣ የመተግበር፣ የማስተማር ወይም የመግለጽ መብትን ያካትታል፡፡
2. በአንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የሃይማኖት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችሏቸው የሃይማኖት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት ማቋቋም ይችላሉ፡፡
3. ማንኛውንም ሰው የሚፈልገውን እምነት ለመያዝ ያለውን ነፃነት በኃይል ወይም በሌላ ሁኔታ በማስገደድ መገደብ ወይም መከልከል አይቻልም፡፡
4. ወላጆችና ሕጋዊ ሞግዚቶች በእምነታቸው መሰረት የሃይማኖታቸውንና የመልካም ሥነ ምግባር ትምህርት በመስጠት ልጆቻቸውን የማሳደግ መብት አላቸው፡፡
5. ሃይማኖትንና እምነትን የመግለጽ መብት ሊገደብ የሚችለው የሕዝብን ደህንነት፣ ሰላምን፣ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የሕዝብን የሞራል ሁኔታ፣ የሌሎች ዜጎችን መሰረታዊ መብቶች፣ ነፃነቶች እና መንግሥት ከሃይማኖት ነፃ መሆኑን ለማረጋገጥ በሚወጡ ሕጎች ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 28

## በስብዕና ላይ ስለሚፈጸሙ ወንጀሎች

1. ኢትዮጵያ ባጸደቀቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶችና በሌሎች የኢትዮጵያ ሕጎች በሰው ልጅ ላይ የተፈጸሙ ወንጀሎች ተብለው የተወሰኑትን ወንጀሎች፤ የሰው ዘር የማጥፋት፣ ያለፍርድ የሞት ቅጣት እርምጃ የመውሰድ፣ በአስገዳጅ ሰውን የመሰወር፣ ወይም ኢሰብዓዊ የድብደባ ድርጊቶችን በፈጸሙ ሰዎች ላይ ክስ ማቅረብ በይርጋ አይታገድም፡፡ በሕግ አውጪው ክፍልም ሆነ በማንኛውም የመንግሥት አካል ውሳኔዎች በምሕረት ወይም በይቅርታ አይታለፉም፡፡
2. ከዚህ በላይ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱትን ወንጀሎች ፈጽመው የሞት ቅጣት ለተፈረደባቸው ሰዎች ርዕሰ ብሔሩ ቅጣቱን ወደ ዕድሜ ልክ ጽኑ እስራት ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ዴሞክራሲያዊ መብቶች

## አንቀጽ 29

## የአመለካከት እና ሀሳብን በነፃ የመያዝና የመግለጽ መብት

1. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት የመሰለውን አመለካከት ለመያዝ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ያለማንም ጣልቃ ገብነት ሀሳቡን የመግለጽ ነፃነት አለው፡፡ ይህ ነፃነት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጭ ወሰን ሳይደረግበት በቃልም ሆነ በጽሑፍ ወይም በሕትመት፣ በሥነ ጥበብ መልክ ወይም በመረጠው በማንኛውም የማሰራጫ ዘዴ፣ ማንኛውንም ዓይነት መረጃና ሀሳብ የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት ነፃነቶችን ያካትታል፡፡
3. የፕሬስና የሌሎች መገናኛ ብዙኃን፣ እንዲሁም የሥነ ጥበብ ፈጠራ ነፃነት ተረጋግጧል፡፡ የፕሬስ ነፃነት በተለይ የሚከተሉትን መብቶች ያጠቃልላል፤

   ሀ/ የቅድሚያ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ መሆኑን፣

   ለ/ የሕዝብን ጥቅም የሚመለከት መረጃ የማግኘት ዕድልን፡፡
4. ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች፣ ሀሳቦችና አመለካከቶች በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ ሲባል ፕሬስ በተቋምነቱ የአሠራር ነፃነትና የተለያዩ አስተያየቶች የማስተናገድ ችሎታ እንዲኖረው የሕግ ጥበቃ ይደረግለታል፡፡

5. በመንግሥት ገንዘብ የሚካሄድ ወይም በመግሥት ቁጥጥር ሥር ያለ መገናኛ ብዙሃን የተለያዩ አስተያየቶችን ለማስተናገድ በሚያስችለው ሁኔታ እንዲመራ ይደረጋል፡፡
6. እነዚህ መብቶች ገደብ ሊጣልባቸው የሚችለው የሀሳብና መረጃ የማግኘት ነፃነት በአስተሳሰባዊ ይዘቱና ሊያስከትል በሚችለው አስተሳሰባዊ ውጤት ሊገታ አይገባውም በሚል መርህ ላይ ተመስርተው በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል፡፡ የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም ለመጠበቅ ሲባል ሕጋዊ ገደቦች በነዚህ መብቶች ላይ ሊደነገጉ ይችላሉ፡፡ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎች በሕግ የሚከለከሉ ይሆናሉ፡፡
7. ማንኛውም ዜጋ ከላይ በተጠቀሱት መብቶች አጠቃቀም ረገድ የሚጣሉ ሕጋዊ ገደቦችን ጥሶ ከተገኘ በሕግ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል፡፡

## አንቀጽ 30

## የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. ማንኛውም ሰው ከሌሎች ጋር በመሆን መሣሪያ ሳይዝ በሰላም የመሰብሰብ፣ ሰላማዊ ሰልፍ የማድረግ ነፃነትና፣ አቤቱታ የማቅረብ መብት አለው፡፡ ከቤት ውጭ የሚደረጉ ስብሰባዎችና ሰላማዊ ሰልፎች በሚንቀሳቀሱባቸው ቦታዎች በሕዝብ እንቅስቃሴ ላይ ችግር እንዳይፈጥሩ ለማድረግ ወይም በመካሄድ ላይ ያለ ስብሰባ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ሰላምን፣ ዴማክራሲያዊ መብቶችንና የሕዝብን የሞራል ሁኔታ እንዳይጥሱ ለማስጠበቅ አግባብ ያላቸው ሥርዓቶች ሊደነገጉ ይችላሉ፡፡
2. ይህ መብት የወጣቶችን ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስምን ለመጠበቅ፣ የጦርነት ቅስቀሳዎች እንዲሁም ሰብዓዊ ክብርን የሚነኩ የአደባባይ መግለጫዎችን ለመከላከል ሲባል በሚወጡ ሕጎች መሰረት ተጠያቂ ከመሆን አያድንም፡፡

## አንቀጽ 31

## የመደራጀት መብት

ማንኛውም ሰው ለማንኛውም ዓላማ በማኅበር የመደራጀት መብት አለው፡፡ ሆኖም አግባብ ያለውን ሕግ በመጣስ ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን በሕገ ወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሰረቱ ወይም የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምዱ ድርጅቶች የተከለከሉ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 32

## የመዘዋወር ነፃነት

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወይም በሕጋዊ መንገድ ሀገሪቱ ውስጥ የሚገኝ የውጭ ዜጋ በመረጠው የሀገሪቱ አካባቢ የመዘዋወርና የመኖሪያ ቦታ የመመስረት፣ እንዲሁም በፈለገው ጊዜ ከሀገር የመውጣት ነፃነት አለው፡፡
2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ወደ ሀገሩ የመመለስ መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 33

## የዜግነት መብቶች

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት ከፈቃዱ/ከፈቃዷ ውጭ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን/ዜግነትዋን ሊገፈፍ ወይም ልትገፈፍ አይችልም/አትችልም፡፡ ኢትዮጵያዊ/ኢትዮጵያዊት ዜጋ ከሌላ ሀገር ዜጋ ጋር የሚፈጽመው/የምትፈጽመው ጋብቻ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን/ዜግነትዋን አያስቀርም፡፡
2. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የኢትዮጵያ ዜግነት በሕግ የሚያስገኘውን መብት፣ ጥበቃና ጥቅም የማግኘት መብት አለው፡፡
3. ማንኛውም ዜጋ ኢትዮጵያዊ ዜግነቱን የመለወጥ መብት አለው፡፡
4. ኢትዮጵያ ከአጸደቃቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ጋር በማይቃረን መንገድ በሚወጣ ሕግ እና በሚደነገግ ሥርዓት መሰረት የኢትዮጵያ ዜግነት ለውጭ ሀገር ሰዎች ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 34

## የጋብቻ፣ የግልና የቤተሰብ መብቶች

1. በሕግ ከተወሰነው የጋብቻ ዕድሜ የደረሱ ወንዶችና ሴቶች በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ ወይም በሃይማኖት ልዩነት ሳይደረግባቸው የማግባትና ቤተሰብ የመመስረት መብት አላቸው፡፡ በጋብቻ አፈጻጸም፣ በጋብቻው ዘመንና በፍቺ ጊዜ እኩል መብት አላቸው፡፡ በፍቺም ጊዜ የልጆችን መብትና ጥቅም እንዲከበር የሚያደርጉ ድንጋጌዎች ይደነገጋሉ፡፡
2. ጋብቻ በተጋቢዎች ነፃና ሙሉ ፈቃድ ላይ ብቻ ይመሰረታል፡፡
3. ቤተሰብ የኅብረተሰብ የተፈጥሮ መሰረታዊ መነሻ ነው፡፡ ከኅብረተሰብና ከመንግሥት ጥበቃ የማግኘት መብት አለው፡፡

4. በሕግ በተለይ በሚዘረዘረው መሰረት በሃይማኖት፣ በባሕል የሕግ ሥርዓቶች ላይ ተመስርተው ለሚፈጸሙ ጋብቻዎች እውቅና የሚሰጥ ሕግ ሊወጣ ይችላል፡፡
5. ይህ ሕገ መንግሥት የግል እና የቤተሰብ ሕግን በተመለከተ በተከራካሪዎች ፈቃድ በሃይማኖቶች ወይም በባሕሎች ሕጎች መሰረት መዳኘትን አይከለክልም፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 35

## የሴቶች መብት

1. ሴቶች ይሕ ሕገ መንግሥት በአረጋገጣቸው መብቶችና ጥበቃዎች በመጠቀም ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡
2. ሴቶች በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሰረት በጋብቻ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡
3. ሴቶች በበታችነትና በልዩነት በመታየታቸው የደረሰባቸውን የታሪክ ቅርስ ከግምት ውስጥ በማስገባት ይህ ቅርስ እንዲታረምላቸው በተጨማሪ የድጋፍ እርምጃዎች ተጠቃሚ የመሆን መብት አላቸው፡፡ በዚህ በኩል የሚወሰዱት እርምጃዎች ዓላማ በፖለቲካዊ፣ በማኅበራዊና በኢኮኖሚያዊ መስኮች እንዲሁም በመንግሥት እና በግል ተቋሞች ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት ተወዳዳሪና ተሳታፊ እንዲሆኑ ለማድረግ እንዲቻል ልዩ ትኩረት ለመስጠት ነው፡፡
4. ሴቶች ከጎጂ ባሕል ተጽዕኖ የመላቀቅ መብታቸውን መንግሥት ማስከበር አለበት፡፡ ሴቶችን የሚጨቁኑ ወይም በአካላቸው ወይም በአዕምሮአቸው ላይ ጉዳት የሚያስከትሉ ሕጎች፣ ወጎችና ልማዶች የተከለከሉ ናቸው፡፡
5. ሀ/ ሴቶች የወሊድ ፈቃድ ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የማግኘት መብት አላቸው፡፡ የወሊድ ፈቃድ ርዝመት ሴቷ የምትሠራውን ሥራ ሁኔታ፣ የሴቷን ጤንነት፣ የሕፃኑንና የቤተሰቡን ደህንነት ከግምት ውስጥ በማስገባት በሕግ ይወሰናል፡፡

   ለ/ የወሊድ ፈቃድ በሕግ በሚወሰነው መሰረት ከሙሉ የደመወዝ ክፍያ ጋር የሚሰጥ የእርግዝና ፈቃድን ሊጨምር ይችላል፡፡
6. ሴቶች በብሔራዊ የልማት ፖሊሲዎች ዕቅድና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም፣ በተለይ የሴቶችን ጥቅም በሚነኩ ፕሮጀክቶች ሀሳባቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

7. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣ የማስተዳደር፣ የመቆጣጠር፣ የመጠቀምና የማስተላለፍ መብት አላቸው፡፡ በተለይ መሬትን በመጠቀም፣ በማስተላለፍ፣ በማስተዳደርና በመቆጣጠር ረገድ ከወንዶች ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡ እንዲሁም ውርስን በሚመለከት በእኩልነት የመታየት መብት አላቸው፡፡
8. ሴቶች የቅጥር፣ የሥራ ዕድገት፣ የእኩል ክፍያና ጡረታን የማስተላለፍ እኩል መብት አላቸው፡፡
9. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህርት፣ መረጃ እና አቅም የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ 36

## የሕፃናት መብት

1. ማንኛውም ሕፃን የሚከተሉት መብቶች አሉት፤
   ሀ/ በሕይወት የመኖር፣
   ለ/ ስምና ዜግነት የማግኘት፣
   ሐ/ ወላጆቹን ወይም በሕግ የማሳደግ መብት ያላቸውን ሰዎች የማወቅና የእነሱንም እንክብካቤ የማግኘት፣
   መ/ ጉልበቱን ከሚበዘብዙ ልማዶች የመጠበቅ፣ በትምህርቱ፣ በጤናውና በደህንነቱ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሥራዎች እንዲሠራ ያለመገደድ ወይም ከመሥራት የመጠበቅ፣
   ሠ/ በትምህርት ቤቶች ወይም በሕፃናት ማሳደጊያ ተቋሞች ውስጥ በአካሉ ከሚፈጸም ወይም ከጭካኔና ኢሰብዓዊ ከሆነ ቅጣት ነፃ የመሆን፡፡
2. ሕፃናትን የሚመለከቱ እርምጃዎች በሚወሰዱበት ጊዜ በመንግሥታዊ ወይም በግል የበጎ አድራጎት ተቋሞች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በአስተዳደር ባለሥልጣኖች ወይም በሕግ አውጪ አካላት የሕፃናት ደህንነት በቀደምትነት መታሰብ አለበት፡፡
3. ወጣት አጥፊዎች፣ በማረሚያ ወይም በመቋቋሚያ ተቋሞች የሚገኙ፣ በመንግሥት እርዳታ የሚያድጉ ወጣቶች፣ በመንግሥት ወይም በግል እጓለ ማውታን ተቋሞች ውስጥ የሚገኙ ወጣቶች ከአዋቂዎች ተለይተው መያዝ አለባቸው፡፡
4. ከጋብቻ ውጭ የተለወዱ ሕፃናት በጋብቻ ከተወለዱ ሕፃናት ጋር እኩል መብት አላቸው፡፡

5. መንግሥት ለእንስሳ ማውታን ልዩ ጥበቃ ያደርግላቸዋል፡፡ በጉዲፈቻ የሚያድጉበትን ሥርዓት የሚያመቻቹና የሚያስፋፉ እንዲሁም ደህንነታቸውንና ትምህርታቸውን የሚያራምዱ ተቋሞች እንዲመሰረቱ ያበረታታል፡፡

## አንቀጽ 37

## ፍትሕ የማግኘት መብት

1. ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት ወይም ለሌላ በሕግ የዳኝነት ስልጣን ለተሰጠው አካል የማቅረብና ውሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተውን ውሳኔ ወይም ፍርድ፤
   ሀ/ ማንኛውም ማኅበር የአባላቱን የጋራ ወይም የግል ጥቅም በመወከል፣
   ለ/ ማንኛውንም ቡድን ወይም ተመሳሳይ ጥቅም ያላቸውን ሰዎች የሚወክል ግለሰብ ወይም የቡድን አባል የመጠየቅና የማግኘት መብት አለው፡፡

## አንቀጽ 38

## የመምረጥና የመመረጥ መብት

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በቀለም፣ በዘር፣ በብሔር፣ በብሔረሰብ፣ በፆታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፖለቲካ ወይም በሌላ አመለካከት ወይም በሌላ አቋም ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግበት የሚከተሉት መብቶች አሉት፤
   ሀ/ በቀጥታ እና በነፃነት በመረጣቸው ተወካዮች አማካኝነት በሕዝብ ጉዳይ አስተዳደር የመሳተፍ፣
   ለ/ ዕድሜው 18 ዓመት ሲሞላ በሕግ መሰረት የመምረጥ፣
   ሐ/ በማናቸውም የመንግሥት ደረጃ በየጊዜው በሚካሄድ ምርጫ የመምረጥና የመመረጥ፡፡ ምርጫው ሁሉ አቀፍ፣ በሁሉም እኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልጽበት ዋስትና የሚሰጥ መሆን አለበት፡፡
2. በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሠራተኞች፣ በንግድ፣ በአሠሪዎችና በሙያ ማኅበራት ለተሳትፎ ድርጅቱ የሚጠይቀውን ጠቅላላና ልዩ የአባልነት መስፈርት የሚያሟላ ማንኛውም ሰው በፍላጎቱ አባል የመሆን መብቱ የተከበረ መሆን አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 በተመለከቱት ድርጅቶች ውስጥ ለኃላፊነት ቦታዎች የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ይፈጸማሉ፡፡

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 3 ድንጋጌዎች የሕዝብን ጥቅም ሰፋ ባለ ሁኔታ የሚነኩ እስከሆነ ድረስ በሕዝባዊ ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## አንቀጽ 39

## የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መብት

1. ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ዕድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል ያለው መብቱ በማናቸውም መልኩ ያለ ገደብ የተጠበቀ ነው፡፡
2. ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ በቋንቋው የመናገር፣ የመጻፍ፣ ቋንቋውን የማሳደግ እና ባሕሉን የመግለጽ፣ የማዳበርና የማስፋፋት እንዲሁም ታሪኩን የመንከባከብ መብት አለው፡፡
3. ማንኛውም የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ ራሱን የማስተዳደር ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት ብሔሩ፣ ብሔረሰቡ፣ ሕዝቡ በሰፈረበት መልክዓ ምድር ራሱን የሚያስተዳድርበት መንግሥታዊ ተቋማት የማቋቋም እንዲሁም በክልልና በፌዴራል አስተዳደሮች ውስጥ ሚዛናዊ ውክልና የማግኘት መብትን ያጠቃልላል፡፡
4. የብሔር፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት ከሥራ ላይ የሚውለው፤

   ሀ/ የመገንጠል ጥያቄ በብሔር፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ የሕግ አውጪ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ የድምፅ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ፣

   ለ/ የፌዴራሉ መንግሥት የብሔር፣ የብሔረሰቡ ወይም የሕዝቡ ምክር ቤት ውሳኔ በደረሰው በሦስት ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠያቂው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፣

   ሐ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝበ ውሳኔው በአብላጫ ድምፅ ሲደገፍ፣

   መ/ የፌዴራሉ መንግሥት መገንጠሉን ለመረጠው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ምክር ቤት ሥልጣኑን ሲያስረክብ፣

   ሠ/ በሕግ በሚወሰነው መሰረት የንብረት ክፍፍል ሲደረግ ነው፡፡
5. በዚህ ሕገ መንግሥት ውስጥ "ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ" ማለት ከዚህ ቀጥሎ የተገለፀውን ባህርይ የሚያሳይ ማኅበረሰብ ነው፡፡ ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባሕል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው፡፡

## አንቀጽ 40

## የንብረት መብት

1. ማንኛውም የኢትዮጵያ ዜጋ የግል ንብረት ባለቤት መሆኑ/መሆኗ ይከበርለታል/ ይከበርላታል፡፡ ይህ መብት የሕዝብን ጥቅም ለመጠበቅ በሌላ ሁኔታ በሕግ እስካልተወሰነ ድረስ ንብረት የመያዝና በንብረት የመጠቀም ወይም የሌሎችን ዜጎች መብቶች እስካልተቃረነ ድረስ ንብረትን የመሸጥ፣ የማውረስ ወይም በሌላ መንገድ የማስተላለፍ መብቶችን ያካትታል፡፡
2. ለዚህ አንቀጽ ዓላማ "የግል ንብረት" ማለት ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ወይም ሕጋዊ ሰውነት በሕግ የተሰጣቸው ኢትዮጵያዊ ማኅበራት ወይም አግባብ በአላቸው ሁኔታዎች በሕግ በተለየ በጋራ የንብረት ባለቤት እንዲሆኑ የተፈቀደላቸው ማኅበረሰቦች በጉልበታቸው፣ በመፍጠር ችሎታቸው ወይም በካፒታላቸው ያፈሩት ተጨባጭ የሆነና የተጨባጭነት ጠባይ ሳይኖረው ዋጋ ያለው ውጤት ነው፡፡
3. የገጠርም ሆነ የከተማ መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ባለቤትነት መብት የመንግሥትና የሕዝብ ብቻ ነው፡፡ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት ነው፡፡
4. የኢትዮጵያ አርሶ አደሮች መሬት በነፃ የማግኘትና ከመሬታቸው ያለመነቀል መብታቸው የተከበረ ነው፡፡ አፈጻጸሙን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ይወጣል፡፡
5. የኢትዮጵያ ዘላኖች ለግጦሽም ሆነ ለእርሻ የሚጠቀሙበት መሬት በነፃ የማግኘት፣ የመጠቀምና ከመሬታቸው ያለመፈናቀል መብት አላቸው፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ ይወሰናል፡፡
6. የመሬት ባለቤትነት የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ መንግሥት ለግል ባለሀብቶች በሕግ በሚወሰን ክፍያ በመሬት የመጠቀም መብታቸውን ያስከብርላቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
7. ማንም ኢትዮጵያዊ በጉልበቱ፣ ወይም በገንዘቡ በመሬት ላይ ለሚገነባው ቋሚ ንብረት ወይም ለሚያደርገው ቋሚ መሻሻል ሙሉ መብት አለው፡፡ ይህ መብት የመሸጥ፣ የመለወጥ፣ የማውረስ፣ የመሬት ተጠቃሚነቱ ሲቋረጥ ንብረቱን የማንሳት፣ ባለቤትነቱን የማዛወር ወይም የካሳ ክፍያ የመጠየቅ መብትን ያካትታል፡፡ ዝርዝር አፈጻጸሙ በሕግ ይወስናል፡፡

8. የግል ንብረት ባለቤትነት መብት እንደተጠበቀ ሆኖ፣ መንግሥት ለሕዝብ ጥቅም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ተመጣጣኝ ካሳ በቅድሚያ በመክፈል የግል ንብረትን ለመውሰድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 41

## የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የባሕል መብቶች

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ በሀገሪቱ ውስጥ በማንኛውም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመሰማራትና ለመተዳደሪያው የመረጠውን ሥራ የመሥራት መብት አለው፡፡
2. ሁሉም ኢትዮጵያዊ መተዳደሪያውን፣ ሥራውንና ሙያውን የመምረጥ መብት አለው፡፡
3. የኢትዮጵያ ዜጎች ሁሉ በመንግሥት ገንዘብ በሚካሄዱ ማኅበራዊ አገልግሎቶች በእኩልነት የመጠቀም መብት አላቸው፡፡
4. መንግሥት የጤና፣ የትምህርትና ሌሎች የማኅበራዊ አገልግሎቶችን ለሕዝብ ለማቅረብ በየጊዜው እየጨመረ የሚሄድ ሀብት ይመድባል፡፡
5. መንግሥት የአካል እና የአዕምሮ ጉዳተኞችን፣ አረጋዊያንንና ያለወላጅ ወይም ያለአሳዳጊ የቀሩ ሕፃናትን ለማቋቋምና ለመርዳት የሀገሪቱ የኢኮኖሚ አቅም በፈቀደው ደረጃ እንክብካቤ ያደርጋል፡፡
6. መንግሥት ለሥራ አጦችና ለችግረኞች ሥራ ለመፍጠር የሚያስችል ፖሊሲ ይከተላል፤ እንዲሁም በሚያካሂደው የሥራ ዘርፍ ውስጥ የሥራ ዕድል ለመፍጠር የሥራ ፕሮግራሞችን ያወጣል፣ ፕሮጀክቶችን ያካሂዳል፡፡
7. መንግሥት ዜጎች ጠቃሚ ሥራ የማግኘት ዕድላቸው እየሰፋ እንዲሄድ ለማድረግ አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
8. ገበሬዎችና ዘላን ኢትዮጵያውያን በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ኑሮ ለመኖር የሚያስችላቸውና ለምርት ካደረጉት አስተዋጽኦ ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ተገቢ ዋጋ ለምርት ውጤቶቻቸው የማግኘት መብት አላቸው፡፡ መንግሥት የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲዎችን በሚተልምበት ጊዜ በዚህ ዓላማ መመራት አለበት፡፡
9. መንግሥት የባሕልና የታሪክ ቅርሶችን የመንከባከብና ለሥነጥበብና ለስፖርት መስፋፋት አስተዋፅኦ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

## አንቀጽ 42

## የሠራተኞች መብት

1. ሀ/ የፋብሪካና የአገልግሎት ሠራተኞች፣ ገበሬዎች፣ የእርሻ ሠራተኞች፣ ሌሎች የገጠር ሠራተኞች፣ ከተወሰነ የኃላፊነት ደረጃ በታች ያሉና የሥራ ጠባያቸው የሚፈቅድላቸው የመንግሥት ሠራተኞች የሥራና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን ለማሻሻል በማኅበር የመደራጀት መብት አላቸው፡፡ ይህ መብት የሠራተኛ ማኅበራትንና ሌሎች ማኅበራትን የማደራጀት፣ ከአሠሪዎችና ጥቅማቸውን ከሚነኩ ሌሎች ድርጅቶች ጋር የመደራደር መብትን ያካትታል፡፡

   ለ/ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) የተመለከቱት የሠራተኛ ክፍሎች ሥራ ማቆምን ጨምሮ ቅሬታቸውን የማሰማት መብት አላቸው፡፡

   ሐ/ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) መሰረት እውቅና ባገኙት መብቶች ለመጠቀም የሚችሉት የመንግሥት ሠራተኞች በሕግ ይወሰናሉ፡፡

   መ/ ሴቶች ሠራተኞች ለተመሳሳይ ሥራ ተመሳሳይ ክፍያ የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

2. ሠራተኞች በአግባቡ የተወሰነ የሥራ ሰዓት ዕረፍት፣ የመዝናኛ ጊዜ፣ በየጊዜው ከክፍያ ጋር የሚሰጡ የዕረፍት ቀኖች፣ ደመወዝ የሚከፈልባቸው የሕዝብ በዓላት እንዲሁም ጤናማና አደጋ የማያደርስ የሥራ አካባቢ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

3. እነዚህን መብቶች ተግባራዊ ለማድረግ የሚወጡ ሕጎች በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት እውቅና ያገኙትን መብቶች ሳይቀንሱ የተጠቀሱት ዓይነት የሠራተኛ ማኅበራት ስለሚቋቋሙበትና የጋራ ድርድር ስለሚካሄድበት ሥርዓት ይደነግጋሉ፡፡

## አንቀጽ 43

## የልማት መብት

1. የኢትዮጵያ ሕዝቦች በአጠቃላይም ሆነ በኢትዮጵያ ያሉ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች በተናጠል የኑሮ ሁኔታቸውን የማሻሻልና የማያቋርጥ እድገት የማግኘት መብታቸው የተጠበቀ ነው፡፡

2. ዜጎች በብሔራዊ ልማት የመሳተፍ በተለይም አባል የሆኑበትን ማኅበረሰብ የሚመለከቱት ፖሊሲዎችና ፕሮጀክቶች ላይ ሀሳባቸውን እንዲሰጡ የመጠየቅ መብት አላቸው፡፡

3. መንግሥት በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚገባቸው ስምምነቶችም ሆኑ የሚያደርጋቸው ግንኙነቶች የኢትዮጵያን የማያቋርጥ ዕድገት መብት የሚያስከብሩ መሆን አለባቸው፡፡
4. የልማት እንቅስቃሴ ዋና ዓላማ የዜጎችን እድገትና መሰረታዊ ፍላጎቶች ማሟላት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 44

## የአካባቢ ደህንነት መብት

1. ሁሉም ሰዎች ንጹህና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት አላቸው፡፡
2. መንግሥት በሚያካሂዳቸው ፕሮግራሞች ምክንያት የተፈናቀሉ ወይም ኑሮአቸው የተነካባቸው ሰዎች ሁሉ በመንግሥት በቂ ዕርዳታ ወደ ሌላ አካባቢ መዘዋወርን ጨምሮ ተመጣጣኝ የሆነ የገንዘብ ወይም ሌላ አማራጭ ማካካሻ የማግኘት መብት አላቸው፡፡

# ምዕራፍ አራት

# የመንግሥት አወቃቀር

## አንቀጽ 45

## ሥርዓተ መንግሥት

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሥርዓተ መንግሥት ፓርላሜንታዊ ነው፡፡

## አንቀጽ 46

## የፌዴራል ክልሎች

1. የፌዴራሉ መንግሥት በክልሎች የተዋቀረ ነው፡፡
2. ክልሎች የሚዋቀሩት በሕዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነት እና ፈቃድ ላይ በመመስረት ነው፡፡

## አንቀጽ 47

## የፌዴራል መንግሥት አባላት

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባላት የሚከተሉት ናቸው፣
    1) የትግራይ ክልል
    2) የአፋር ክልል

3) የአማራ ክልል
4) የኦሮሚያ ክልል
5) የሱማሌ ክልል
6) የቤንሻንጉል/ጉሙዝ ክልል
7) የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል
8) የጋምቤላ ሕዝቦች ክልል
9) የሐረሪ ሕዝብ ክልል

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱት ክልሎች ውስጥ የተካተቱት ብሔሮች፣ ብሔሰቦች፣ ሕዝቦች በማንኛውም ጊዜ የየራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት አላቸው፡፡
3. የማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ የራሱን ክልል የመመስረት መብት ሥራ ላይ የሚውለው፤
   ሀ/ የክልል መመስረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝቡ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥና ጥያቄው በጽሑፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፤
   ለ/ ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሳኔ ሲያደራጅ፤
   ሐ/ ክልል የመመስረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ሕዝበ ውሳኔ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፤
   መ/ የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣኑን ለጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሲያስረክብ፤
   ሠ/ በሕዝበ ውሳኔ የሚፈጠረው አዲስ ክልል ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል ሲሆን ነው፡፡
4. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባላት እኩል መብትና ሥልጣን አላቸው፡፡

## <u>አንቀጽ 48</u>

## <u>የአከላለል ለውጦች</u>

1. የክልሎችን ወሰን በሚመለከት ጥያቄ የተነሳ እንደሆነ ጉዳዩ በሚመለከታቸው ክልሎች ስምምነት ይፈጸማል፡፡ የሚመለከታቸው ክልሎች መስማማት ካልቻሉ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የሕዝብን አሰፋፈርና ፍላጎት መሰረት በማድረግ ይወስናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የቀረበ ጉዳይ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

## አንቀጽ 49

## ርዕሰ ከተማ

1. የፌዴራሉ መንግሥት ርዕሰ ከተማ አዲስ አበባ ነው፡፡
2. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ራሱን በራሱ የማስተዳደር ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
3. የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ተጠሪነቱ ለፌዴራሉ መንግሥት ይሆናል፡፡
4. የአዲስ አበባ ነዋሪዎች በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው መሰረት በፌዴራሉ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይወከላሉ፡፡
5. የኦሮሚያ ክልል፣ የአገልግሎት አቅርቦት ወይም የተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀምንና የመሳሰሉትን ጉዳዮች በተመለከተ፣ እንዲሁም አዲስ አበባ በኦሮሚያ ክልል መሀል የሚገኝ በመሆኑ የሚነሱ ሁለቱን የሚያስተሳስሩ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ ያለው ልዩ ጥቅም ይጠበቅለታል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## የሥልጣን አወቃቀር እና ክፍፍል

## አንቀጽ 50

## ስለ ሥልጣን አካላት አወቃቀር

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ በፌዴራል መንግሥትና በክልሎች የተዋቀረ ነው፡፡
2. የፌዴራሉ መንግሥትና ክልሎች የሕግ አውጪነት፣ የሕግ አስፈጻሚነትና የዳኝነት ሥልጣን አላቸው፡፡
3. የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የሥልጣን አካል የፌዴራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡ ተጠሪነቱም ለሀገሪቱ ሕዝብ ነው፡፡ የክልል ከፍተኛ የሥልጣን አካል የክልሉ ምክር ቤት ነው፤ ተጠሪነቱም ለወከለው ክልል ሕዝብ ነው፡፡
4. ክልሎች፤ በክልልነትና ክልሎች አስፈላጊ ሆነው በሚያገኙአቸው የአስተዳደር እርከኖች ይዋቀራሉ፡፡ ሕዝቡ በዝቅተኛ የአስተዳደር እርከኖች በቀጥታ ይሳተፍ ዘንድ ለዝቅተኛ እርከኖች በቂ ሥልጣን ይሰጣል፡፡

5. የክልል ምክር ቤት በክልሉ ሥልጣን ስር በሆኑ ጉዳዮች የክልሉ የሕግ አውጪ አካል ነው፡፡ ይህንን ሕገ መንግሥት መሰረት በማድረግ የክልሉን ሕገ መንግሥት ያዘጋጃል፣ ያጸድቃል፣ ያሻሽላል፡፡
6. የክልል መስተዳድር የክልሉ ከፍተኛ የሕግ አስፈጻሚ አካል ነው፡፡
7. የክልል የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡
8. የፌዴራሉ መንግሥትና የክልሎች ሥልጣን በዚህ ሕገ መንግሥት ተወስኗል፡፡ ለፌዴራሉ መንግሥት የተሰጠው ሥልጣን በክልሎች መከበር አለበት፡፡ ለክልሎች የተሰጠው ሥልጣን በፌዴራሉ መንግሥት መከበር አለበት፡፡
9. የፌዴራሉ መንግሥት በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 51 ከተሰጡት ሥልጣን እና ተግባሮች እንዳስፈላጊነቱ ለክልሎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 51

## የፌዴራል መንግሥት ሥልጣንና ተግባር

1. ሕገ መንግሥቱን ይጠብቃል፤ ይከላከላል፡፡
2. የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፤ ያስፈጽማል፡፡
3. የጤና፣ የትምህርት፣ የባሕልና ታሪካዊ ቅርስ፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሀገር አቀፍ መመዘኛዎችና መሰረታዊ የፖሊሲ መለኪያዎችን ያወጣል፤ ያስፈጽማል፡፡
4. የሀገሪቱን የፋይናንስ፣ የገንዘብ፣ የውጭ ኢንቨስትመንት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን ያወጣል፤ ያስፈጽማል፡፡
5. የመሬት፣ የተፈጥሮ ሀብትና የታሪክ ቅርሶች አጠቃቀምና ጥበቃን በተመለከተ ሕግ ያወጣል፡፡
6. የሀገርና የሕዝብ የመከላከያና የደህንነት እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት የፖሊስ ኃይል ያደራጃል፤ ይመራል፡፡
7. ብሔራዊ ባንክን ያስተዳድራል፤ ገንዘብ ያትማል፤ ይበደራል፤ የውጭ ምንዛሪና የገንዘብ ልውውጥን ይቆጣጠራል፡፡ ክልሎች ከውስጥ ምንጮች ስለሚበደሩበት ሁኔታ ሕግና መመሪያ ያወጣል፡፡
8. የውጭ ግንኙነት ፖሊሲን ይወስናል፤ ፖሊሲውንም ያስፈጽማል፤ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ይዋዋላል፤ ያጸድቃል፡፡

9. የአየር፣ የባቡር፣ የባሕር መጓጓዣ፤ የፖስታና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች እንደዚሁም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን የሚያገናኙ አውራ መንገዶችን ያስፋፋል፤ ያስተዳድራል፤ ይቆጣጠራል፡፡
10. ለፌዴራሉ መንግሥት በተሰጡት የገቢ ምንጮች ክልል ግብርና ቀረጥ ይጥላል፤ ያስተዳድራል፤ የፌዴራል መንግሥት በጀት ያረቃል፤ ያጸድቃል፤ ያስተዳድራል፡፡
11. ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ክልሎችን የሚያስተሳስሩ ወይም ድንበር ተሻጋሪ የሆኑ ወንዞችና ሀይቆችን አጠቃቀም ይወስናል፤ ያስተዳድራል፡፡
12. በክልሎች መካከል የሚደረግን የንግድ ግንኙነትና የውጭ ንግድን ይመራል፤ ይቆጣጠራል፡፡
13. በፌዴራል መንግሥት ገንዘብ የተቋቋሙ አንድ ወይም ከአንድ ክልል በላይ የሚሸፍኑ የአገልግሎት ተቋሞችን ያስተዳድራል፤ ያስፋፋል፡፡
14. ከክልል አቅም በላይ የሆነ የጸጥታ መደፍረስ ሲያጋጥም በክልሉ መስተዳድር ጥያቄ መሰረት የሀገሪቱን የመከላከያ ኃይል ያሰማራል፡፡
15. በዚህ ሕገ መንግሥት የተረጋገጡትን የፖለቲካ መብቶች ለማስፈጸም አስፈላጊ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችን እንዲሁም ምርጫን በሚመለከት ሕጎች ያወጣል፡፡
16. በሀገሪቱ በአጠቃላይም ሆነ በተወሰኑ የሀገሪቱ ክፍሎች የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፤ አዋጁን ያነሳል፡፡
17. የዜግነት ጥያቄ ይወስናል፡፡
18. የኢምግሬሽንና የፓስፖርት፤ ወደ ሀገር የመግቢያና የመውጫ ጉዳዮችን፤ ስለስደተኞችና ስለ ፖለቲካ ጥገኝነት ይወስናል፤ ይመራል፡፡
19. የፈጠራና የድርሰት መብቶችን ይፈቅዳል፤ ይጠብቃል፡፡
20. አንድ ወጥ የመለኪያ ደረጃዎችና የጊዜ ቀመር ያወጣል፡፡
21. የጦር መሣሪያ ስለመያዝ ሕግ ያወጣል፡፡

## አንቀጽ 52

## የክልል ሥልጣንና ተግባር

1. በሕገ መንግሥቱ ለፌዴራሉ መንግሥት በተለይ ወይም ለፌዴራሉ መንግሥትና ለክልሎች በጋራ በግልጽ ያልተሰጠ ሥልጣን የክልል ሥልጣን ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የክልሎች ሥልጣንና ተግባር የሚከተሉትን ያጠቃልላል፤

ሀ/ ራስን በራስ ማስተዳደርን ዓላማ ያደረገ ክልላዊ መስተዳድር ያዋቅራል፤ የሕግ የበላይነት የሰፈነበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ይገነባል፤ ይህን ሕገ መንግሥት ይጠብቃል፤ ይከላከላል፤

ለ/ የክልል ሕገ መንግሥትና ሌሎች ሕጎችን ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤

ሐ/ የክልሉን የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲ፣ ስትራቴጂና ዕቅድ ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤

መ/ የፌዴራሉ መንግሥት በሚያወጣው ሕግ መሰረት መሬትና የተፈጥሮ ሀብትን ያስተዳድራል፤

ሠ/ ለክልሉ በተወሰነው የገቢ ምንጭ ክልል ግብርና ታክስ ይጥላል፤ ይሰበስባል፤ የክልሉን በጀት ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤

ረ/ የክልሉን መስተዳድር ሠራተኞች አስተዳደርና የሥራ ሁኔታዎች በተመለከተ ሕግ ያወጣል፤ ያስፈጽማል፤ ሆኖም ለአንድ የሥራ መደብ የሚያስፈልጉ የትምህርት፣ የሥልጠናና የልምድ መመዘኛዎች ከአጠቃላይ የሀገሪቱ መመዘኛዎች ጋር የተቀራረቡ መሆናቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት ይኖርበታል፡፡

ሰ/ የክልሉን የፖሊስ ኃይል ያደራጃል፣ ይመራል፣ የክልሉን ሰላምና ጸጥታ ያስጠብቃል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## ስለፌዴራሉ መንግሥት ምክር ቤቶች

### አንቀጽ 53

### የፌዴራል መንግሥት ምክር ቤቶች

የፌዴራሉ መንግሥት ሁለት ምክር ቤቶች ይኖሩታል፤ እነዚህም የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ናቸው፡፡

## ክፍል አንድ

## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

### አንቀጽ 54

### የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት፤ ሁሉ አቀፍ፣ ነፃ፣ ቀጥተኛ፣ ትክክለኛ በሆነና ድምጽ በሚስጥር በሚሰጥበት ሥርዓት በየአምስት ዓመቱ በሕዝብ ይመረጣሉ፡፡

2. የምክር ቤቱ አባላት በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሌሎች ተወዳዳሪዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ በሚሆንበት የምርጫ ሥርዓት ይመረጣሉ፡፡ የተለየ ውክልና ያስፈልጋቸዋል ተብሎ የታመነባቸው አናሳ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በምርጫ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ይሆናሉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
3. የምክር ቤቱ አባላት ቁጥር የሕዝብ ብዛትንና በልዩ ትኩረት ውክልና የሚሰጣቸው አናሳ ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን ቁጥር መሰረት በማድረግ ከ550 የማይበልጥ ሆኖ ከዚህ ውስጥ አናሳ ብሔረሰቦች ከ20 የማያንስ መቀመጫ ይኖራቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይደነገጋል፡፡
4. የምክር ቤቱ አባላት የመላው ሕዝብ ተወካዮች ናቸው፡፡ ተገዥነታቸውም፤

   ሀ/ ለሕገ መንግሥቱ፤

   ለ/ ለሕዝቡ፤ እና

   ሐ/ ለሕሊናቸው

   ብቻ ይሆናል፡፡
5. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል በምክር ቤቱ ውስጥ በሚሰጠው ድምፅ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፡፡ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፡፡
6. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፤ በወንጀልም አይከሰስም፡፡
7. ማንኛውም የምክር ቤቱ አባል የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣበት ጊዜ በሕግ መሰረት ከምክር ቤት አባልነቱ ይወገዳል፡፡

## አንቀጽ 55

## የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት ለፌዴራሉ መንግሥት በተሰጠው የሥልጣን ክልል ሕጎችን ያወጣል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ዝርዝር ሕግ ያወጣል፤

   ሀ/ የመሬትና የተፈጥሮ ሀብት፤ እንዲሁም ድንበር ተሻጋሪ ወይም ከአንድ ክልል በላይ የሚያስተሳስሩ ወንዞችና ሀይቆች አጠቃቀምን በተመለከተ፤

   ለ/ በክልሎች መካከል የሚኖረውን የንግድ ልውውጥ፤ እንዲሁም የውጭ ንግድ ግንኙነትን በተመለከተ፤

ሐ/ የአየር፣ የባቡርና የባሕር መጓጓዣ፤ የፖስታና የቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎቶችን እንዲሁም ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ክልሎችን የሚያገናኙ አውራ መንገዶችን በተመለከተ፤

መ/ በዚህ ሕገ መንግሥት የተደነገጉትን የፖለቲካ መብቶች አፈጻጸምን እንዲሁም ምርጫን በተመለከተ፤

ሠ/ የዜግነት መብትን፤ የኢምግሬሽን፤ የፓስፖርትን፤ ወደ ሀገር የመግቢያና የመውጫ ጉዳዮችን እንዲሁም የስደተኞችና የፖለቲካ ጥገኝነት ጉዳዮችን በተመለከተ፤

ረ/ አንድ ወጥ የመጠን መለኪያ ደረጃና የጊዜ ቀመርን በተመለከተ፤

ሰ/ የፈጠራና የሥነጥበብ መብቶችን በተመለከተ፤

ሸ/ የጦር መሣሪያ መያዝን በተመለከተ፡፡

3. የሠራተኛ ጉዳይ ሕግ ያወጣል፡፡
4. የንግድ ሕግ (ኮድ) ያወጣል፡፡
5. የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ያወጣል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሎች በፌዴራሉ መንግሥት የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ በግልጽ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ሕግ የማውጣት ሥልጣን ይኖራቸዋል፡፡
6. አንድ የኢኮኖሚ ማኀበረሰብን ለመፍጠር ሲባል በፌዴራል መንግሥት ሕግ እንዲወጣላቸው የሚያስገድዱ ለመሆናቸው በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የታመነባቸው የፍትሐብሔር ሕጎችን ያወጣል፡፡
7. የፌዴራል መንግሥት፤ የሀገርና የሕዝብ መከላከያ፤ የደህንነትና የፖሊስ ኃይል አደረጃጀትን ይወስናል፡፡ በሥራ አፈጻጸማቸው ረገድ የሚታዩ መሠረታዊ የዜጎችን ሰብዓዊ መብቶችና የሀገርን ደህንነት የሚነኩ ጉዳዮች ሲከሰቱ ያጣራል፤ አስፈላጊ እርምጃዎች እንዲወስዱ ያደርጋል፡፡
8. በአንቀጽ 93 በተመለከተው መሰረት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፤ የሕግ አስፈጻሚው የሚያወጣውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ተመልክቶ ይወስናል፡፡
9. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያቀርብለት የሕግ ረቂቅ መሰረት የጦርነት አዋጅ ያውጃል፡፡
10. የሀገሪቱን አጠቃላይ የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊ፣ የልማት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጂዎችን፤ የፋይናንስና የገንዘብ ፖሊሲን ያጸድቃል፤ ገንዘብን፤ የብሔራዊ

ባንክ አስተዳደርን፣ የውጭ ምንዛሪንና ልውውጥን በተመለከተ ዝርዝር ሕግ ያወጣል፡፡

11. ለፌዴራል መንግሥት በተከለለው የገቢ ምንጭ ክልል ግብርና ታክስ ይጥላል፡፡ የፌዴራል መንግሥት በጀት ያጸድቃል፡፡

12. የሕግ አስፈጻሚው አካል የሚዋዋላቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ያጸድቃል፡፡

13. የፌዴራል መንግሥት ፍርድ ቤት ዳኞችን፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላትን፣ የኮሚሽነሮችን፣ የዋናው ኦዲተርን እንዲሁም የሌሎች ሹመታቸው በምክር ቤቱ መጽደቅ ያለበትን ባለሥልጣኖች ሹመት ያጸድቃል፡፡

14. የሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ያቋቁማል፣ ሥልጣንና ተግባሩን በሕግ ይወስናል፡፡

15. የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋምን ያቋቁማል፣ ተቋሙን የሚመሩ አባላትን ይመርጣል፣ ይሰይማል፡፡ ሥልጣንና ተግባሩን በሕግ ይወስናል፡፡

16. በማንኛውም ክልል ሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱና ክልሉ ድርጊቱን ማቆም ሳይችል ሲቀር፣ በራሱ አነሳሽነትና ያለ ክልሉ ፈቃድ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤትና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ ጥያቄ ያቀርባል፣ በተደረሰበት ውሳኔ መሰረት ለክልሉ ምክር ቤት መመሪያ ይሰጣል፡፡

17. ምክር ቤቱ ጠቅላይ ሚኒስትሩን እና ሌሎች የፌዴራሉ መንግሥት ባለሥልጣናትን ለጥያቄ የመጥራትና የሕግ አስፈጻሚውን አካል አሠራር የመመርመር ሥልጣን አለው፡፡

18. ለሕግ አስፈጻሚው አካል በተሰጠ ማንኛውም ሥልጣን ላይ የምክር ቤቱ አባላት በአንድ ሦስተኛ ድምጽ ሲጠይቁ ምክር ቤቱ ይወያያል፡፡ ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ የመመካከርና አስፈላጊ መስሎ የታየውን እርምጃ የመውሰድ ሥልጣን አለው፡፡

19. ምክር ቤቱን የሚመሩ አፈጉባዔና ምክትል አፈጉባዔ ይመርጣል፣ ለምክር ቤቱ ሥራ የሚያስፈልጉትን ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያዋቅራል፡፡

## አንቀጽ 56

## የፖለቲካ ሥልጣን

በምክር ቤቱ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች የፌዴራሉን መንግሥት የሕግ አስፈጻሚ አካል ያደራጃል/ያደራጃሉ፣ ይመራል/ይመራሉ፡፡

## አንቀጽ 57

## ስለሕግ አጸዳደቅ

ምክር ቤቱ መክሮ የተስማማበት ሕግ ለሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ለፊርማ ይቀርባል፤ ፕሬዚዳንቱ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ይፈርማል፡፡ ፕሬዚዳንቱ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ካልፈረመ ሕጉ በሥራ ላይ ይውላል፡፡

## አንቀጽ 58

## የምክር ቤቱ ስብሰባና የሥራ ዘመን

1. ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይኖራል፡፡
2. የምክር ቤቱ የሥራ ጊዜ ከመስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ከሰኞ እስከ ሰኔ ሠላሳ ነው፤ በመካከሉም ምክር ቤቱ በሚወስነው ጊዜ የአንድ ወር ዕረፍት ይኖረዋል፡፡
3. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚመረጠው ለአምስት ዓመታት ነው፤ የሥራ ዘመኑ ከማብቃቱ ከአንድ ወር በፊት አዲስ ምርጫ ተካሂዶ ይጠናቀቃል፡፡
4. ምክር ቤቱ ዕረፍት ላይ በሚሆንበት ጊዜ የምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡ ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቁ አፈ-ጉባዔው ስብሰባ የመጥራት ግዴታ አለበት፡፡
5. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስብሰባዎች በግልጽ ይካሄዳሉ፤ ሆኖም በምክር ቤቱ አባላት ወይም በፌዴራል የሕግ አስፈጻሚ አካል በዝግ ስብሰባ እንዲደረግ ከተጠየቀና ከምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ከደገፉት ዝግ ስብሰባ ሊደረግ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 59

## የምክር ቤቱ ውሳኔዎችና የሥነ-ሥርዓት ደንቦች

1. በዚህ ሕገ መንግሥት በግልጽ በተለይ ካልተደነገገ በስተቀር ማናቸውም ውሳኔዎች የሚተላለፉት በምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምጽ ነው፡፡
2. ምክር ቤቱ ስለ አሠራሩና ስለ ሕግ አወጣጥ ሂደት ደንቦችን ያወጣል፡፡

## አንቀጽ 60

## ስለምክር ቤቱ መበተን

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ በምክር ቤቱ ፈቃድ ምክር ቤቱ እንዲበተን ለማድረግ ይችላል፡፡
2. በጣምራ የመንግሥት ሥልጣን የያዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራነታቸው ፈርሶ በምክር ቤቱ የነበራቸውን አብላጫነት ያጡ እንደሆነ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተበትኖ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ ጣምራ መንግሥት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለመመስረት እንዲቻል ፕሬዚዳንቱ የፖለቲካ ድርጅቶችን ይጋብዛል፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶቹ አዲስ መንግሥት ለመፍጠር ወይም የነበረውን ጣምራነት ለመቀጠል ካልቻሉ ምክር ቤቱ ተበትኖ አዲስ ምርጫ ይደረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 መሰረት ምክር ቤቱ የተበተነ እንደሆነ ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ መደረግ አለበት፡፡
4. ምርጫው በተጠናቀቀ በሠላሳ ቀናት ውስጥ አዲሱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሥራውን ይጀምራል፡፡
5. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተበተነ በኋላ ሀገሪቱን የሚመራው ሥልጣን ይዞ የነበረው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራ የዕለት ተዕለት የመንግሥት ሥራ ከማከናወንና ምርጫ ከማካሄድ በስተቀር አዲስ አዋጆችን፣ ደንቦችንና ድንጋጌዎችን ማውጣት ወይም ነባር ሕጎችን መሻርና ማሻሻል አይችልም፡፡

## ክፍል ሁለት

## የፌዴሬሽን ምክር ቤት

### አንቀጽ 61

### የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት

1. የፌዴሬሽን ምክር ቤት በፌዴራሉ መንግሥት አባል ክልሎች የሚገኙት ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የሚልኩዋቸው አባላት የሚወከሉበት ምክር ቤት ነው፡፡
2. እያንዳንዱ ብሔር፣ ብሔረሰብ ሕዝብ ቢያንስ አንድ ተወካይ ይኖረዋል፤ በተጨማሪም የብሔር ወይም ብሔረሰቡ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ አንድ ተጨማሪ ወኪል ይኖረዋል፡፡
3. የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት በክልል ምክር ቤቶች ይመረጣሉ፤ የክልል ምክር ቤቶች በራሳቸው ወይም በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጡ በማድረግ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል እንዲወከል ያደርጋሉ፡፡

## አንቀጽ 62

## የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. ምክር ቤቱ ሕገ መንግሥቱን የመተርጎም ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን ያደራጃል፡፡
3. የብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብትን በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በሕገ መንግሥቱ መሰረት ይወስናል፡፡
4. በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው የሕዝቦች እኩልነትና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት ስር እንዲሰድና እንዲዳብር ያደርጋል፡፡
5. ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በጣምራ የተሰጡትን ሥልጣኖች ያከናውናል፡፡
6. በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሄ ይፈልጋል፡፡
7. የክልሎችና የፌዴራሉ መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን፤ እንዲሁም የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች ድጎማ የሚሰጥበትን ቀመር ይወስናል፡፡
8. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ይለያል፡፡
9. ማንኛውም ክልል ይህን ሕገ መንግሥት በመጣስ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌዴራሉ መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ያዛል፡፡
10. የምክር ቤቱን የተለያዩ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፡፡
11. ምክር ቤቱ የራሱን አፈጉባዔና ምክትል አፈጉባዔ ይመርጣል፤ የራሱን የሥራ አፈጻጸምና የውስጥ አስተዳደር ደንብ ያወጣል፡፡

## አንቀጽ 63

## የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት መብት

1. ማንኛውም የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በሚሰጠው አስተያየት ወይም ድምጽ ምክንያት አይከሰስም፤ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፡፡
2. ማንኛውም የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፤ በወንጀልም አይከሰስም፡፡

## አንቀጽ 64

## ውሳኔዎችና የሥነ ሥርዓት ደንቦች

1. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ምልዓተ ጉባዔ የሚኖረው ከአባላቱ ሁለት ሦስተኛው የተገኙ እንደሆነ ነው፡፡ ማናቸውም ውሳኔ የሚያልፈው ስብሰባ ላይ ከተገኙት የምክር ቤቱ አባላት ከግማሽ በላይ ድምፅ ሲደገፍ ብቻ ነው፡፡
2. አባላት ድምፅ መስጠት የሚችሉት በአካል ሲገኙ ብቻ ነው፡፡

## አንቀጽ 65

## ስለ በጀት

የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በጀቱን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በማቅረብ ያስወስናል፡፡

## አንቀጽ 66

## የምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ ሥልጣን

1. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አፈ ጉባዔ የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፡፡
2. ምክር ቤቱን በመወከል ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን ይመራል፡፡
3. ምክር ቤቱ በአባሎቹ ላይ የወሰነውን የዲስፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል፡፡

## አንቀጽ 67

## ስብሰባና የሥራ ዘመን

1. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፡፡
2. የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 68

## በሁለቱም ምክር ቤቶች አባል መሆን የማይቻል ስለመሆኑ

ማንኛውም ሰው በአንድ ጊዜ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል ሊሆን አይችልም፡፡

# ምዕራፍ ሰባት

# ስለ ሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት

## አንቀጽ 69

## ስለ ፕሬዚዳንቱ

ፕሬዚዳንቱ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ርዕሰ ብሔር ነው፡፡

## አንቀጽ 70

## የፕሬዚዳንቱ አሰያየም

1. ለፕሬዚዳንትነት እጩ የማቅረብ ሥልጣን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡
2. የቀረበው እጩ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት የጋራ ስብሰባ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ከተደገፈ ፕሬዚዳንት ይሆናል፡፡
3. የምክር ቤት አባል ፕሬዚዳንት ሆኖ ከተመረጠ የተወከለበትን ምክር ቤት ወንበር ይለቃል፡፡
4. የፕሬዚዳንቱ የሥራ ዘመን ስድስት ዓመት ይሆናል፡፡ አንድ ሰው ከሁለት ጊዜ በላይ ለፕሬዚዳንትነት ሊመረጥ አይችልም፡፡
5. የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ምርጫ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ከጸደቀ በኋላ ሥራውን ከመጀመሩ በፊት የጋራ ስብሰባው በሚወስነው ጊዜ ስብሰባው ፊት ለሕገ መንግሥቱና ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ያለውን ታማኝነት በሚቀጥሉት ቃላት ይገልጻል፡፡

   "እኔ ………….. በዛሬው ዕለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት በመሆን ሥራዬን ስጀምር የተጣለብኝን ከፍተኛ ኃላፊነት በታማኝነት ለመፈጸም ቃል እገባለሁ፡፡"

## አንቀጽ 71

## የፕሬዚዳንቱ ሥልጣንና ተግባር

1. የሕዝብ ተወካዮችን ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑን ምክር ቤት ዓመታዊ የጋራ ስብሰባ ይከፍታል፡፡
2. በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያጸደቃቸውን ሕጎችና ዓለም አቀፍ ስምምነቶች በነጋሪት ጋዜጣ ያውጃል፡፡
3. ሀገሪቷን በውጭ ሀገሮች የሚወክሉትን አምባሳደሮችና ሌሎች መልዕክተኞች በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት ይሾማል፡፡
4. የውጭ ሀገር አምባሳደሮችንና የልዩ መልዕክተኞችን የሹመት ደብዳቤ ይቀበላል፡፡
5. በሕግ መሰረት ኒሻኖችና ሽልማቶችን ይሰጣል፡፡
6. በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕግ በተወሰነው መሰረት ከፍተኛ የውትድርና ማዕረጎችን ይሰጣል፡፡
7. በሕግ መሰረት ይቅርታ ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## የሕግ አስፈጻሚ አካል

### አንቀጽ 72

### ስለ አስፈጻሚነት ሥልጣን

1. የኢትዮጵያ ፌዴራል መንግሥት ከፍተኛ የአስፈጻሚነት ሥልጣን የተሰጠው ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡
2. ጠቅላይ ሚኒስትሩና የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪዎች ናቸው፡፡ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላት በመንግሥት ተግባራቸው በጋራ ለሚሰጡት ውሳኔ የጋራ ኃላፊነት አለባቸው፡፡
3. በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት በሌላ አኳኋን ካልተወሰነ በስተቀር የጠቅላይ ሚኒስትሩ የሥራ ዘመን የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሥራ ዘመን ነው፡፡

### አንቀጽ 73

### የጠቅላይ ሚኒስትሩ አሰያየም

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት መካከል ይመረጣል፡፡
2. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አብላጫ መቀመጫ ያገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ያገኙት የፖለቲካ ድርጅቶች የመንግሥት ሥልጣን ይረከባል/ይረከባሉ፡፡

### አንቀጽ 74

### የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሥልጣንና ተግባር

1. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሀገሪቱ ርዕሰ መስተዳድር፣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰብሳቢና የጦር ኃይሎች ጠቅላይ አዛዥ ነው፡፡
2. ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባሎችን ከሁለቱ ምክር ቤቶች አባላት ወይም ለሥራው ብቃት ካላቸው ሌሎች ግለሰቦች መካከል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በእጩነት አቅርቦ ሹመታቸውን ያስጸድቃል፡፡
3. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያወጣቸው ሕጎች፣ ፖሊሲዎች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል፡፡
4. የሚኒስትሮች ምክር ቤትን ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይወክላል፡፡
5. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ያወጣቸውን ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና ውሳኔዎች ተፈጻሚነት ይከታተላል፡፡
6. የሀገሪቱን የውጭ ፖሊሲ በበላይነት ያስፈጽማል፡፡

7. ኮሚሽነሮችን፣ የማዕከላዊ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንትን እና ዋና ኦዲተርን መርጦ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሹመታቸውን ያስጸድቃል፡፡
8. የመስተዳድሩን ሥራ አፈጻጸምና ብቃት ይቆጣጠራል፣ አስፈላጊ የሆኑ የእርምት እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡
9. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 እና 7 ከተዘረዘሩት ውጭ የሆኑ ከፍተኛ የመንግሥት የሲቪል ሹመቶችን ይሰጣል፡፡
10. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ሕግ ወይም በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት ኒሻኖችንና ሽልማቶችን ለፕሬዝዳንቱ አቅርቦ ያሰጣል፡፡
11. ስለ ሀገሪቱ ሁኔታ፣ በመንግሥት ስለተከናወኑ ተግባራትና ስለወደፊት ዕቅዶች ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በየወቅቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
12. በዚህ ሕገ መንግሥትና በሌሎች ሕጎች የተሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡
13. ሕገ መንግሥቱን ያከብራል፤ ያስከብራል፡፡

## አንቀጽ 75

## ስለ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር

1. ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፣

   ሀ/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ ተለይተው የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፣

   ለ/ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶት ይሠራል፡፡
2. ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 76

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት፤ ጠቅላይ ሚኒስትር፣ ምክትል ጠቅላይ ማኒስትር፣ ሚኒስትሮችና በሕግ በሚወሰን መሰረት ሌሎች አባሎች የሚገኙበት ምክር ቤት ነው፡፡
2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ነው፡፡
3. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለሚወስነው ውሳኔ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ ነው፡፡

## አንቀጽ 77

## የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣንና ተግባር

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የወጡ ሕጎችና የተሰጡ ውሳኔዎች በሥራ መተርጎማቸውን ያረጋግጣል፣ መመሪያዎችን ይሰጣል፡፡
2. የሚኒስቴሮችንና በቀጥታ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑ ሌሎች የመንግሥት አካላትን አደረጃጀት ይወስናል፣ ሥራቸውን ያስተባብራል፣ ይመራል፡፡
3. የፌዴራሉን መንግሥት ዓመታዊ በጀት ያዘጋጃል፣ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊነቱን ያረጋግጣል፡፡
4. የገንዘብና የፋይናንስ ፖሊሲን ተግባራዊነት ያረጋግጣል፣ ብሔራዊ ባንክን ያስተዳድራል፣ ገንዘብ ያትማል፣ ከሀገር ውስጥና ከውጭ ይበደራል፣ የውጭ ምንዛሪና የገንዘብ ልውውጥን ይቆጣጠራል፡፡
5. የፈጠራና የኪነ ጥበብ መብቶችን ያስጠብቃል፡፡
6. የኢኮኖሚያዊ፣ የማኅበራዊና የልማት ፖሊሲዎች እና ስትራቴጂዎችን ይነድፋል፣ ያስፈጽማል፡፡
7. አንድ ወጥ የመለኪያ ደረጃዎችንና የጊዜ ቀመር ያወጣል፡፡
8. የሀገሪቱን የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ያወጣል፣ ያስፈጽማል፡፡
9. ሕግና ሥርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፡፡
10. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ያውጃል፤ በዚህ ሕገ መንግሥት በተደነገገው የጊዜ ወሰን ውስጥ፣ የታወጀውን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል፡፡
11. የጦርነት ጉዳዮችን ጨምሮ በማናቸውም ጉዳዮች ላይ የሕግ ረቂቅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
12. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና ጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡
13. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚሰጠው ሥልጣን መሰረት ደንቦችን ያወጣል፡፡

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ስለፍርድ ቤቶች አወቃቀርና ሥልጣን

### አንቀጽ 78

### ስለ ነፃ የዳኝነት አካል

1. ነፃ የዳኝነት አካል በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፡፡
2. የፌዴራሉ መንግሥት ከፍተኛ የዳኝነት አካል የፌዳራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይሆናል፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የፌዴራል ከፍተኛ

ፍርድ ቤትም ሆነ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሀገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲደራጅ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ሊወስን ይችላል፡፡ ጉዳዩ በዚህ አኳኋን ካልተወሰነ የፌዴራል ከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ሥልጣን ለክልል ፍርድ ቤቶች ተሰጥቷል፡፡

3. ክልሎች፤ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች፣ የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችና የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ይኖራቸዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
4. የዳኝነት ሥልጣንን ከመደበኛ ፍርድ ቤቶች ወይም በሕግ የመዳኘት ሥልጣን ከተሰጠው ተቋም ውጭ የሚያደርግ፣ በሕግ የተደነገገን የዳኝነት ሥርዓት የማይከተል ልዩ ፍርድ ቤት ወይም ጊዜያዊ ፍርድ ቤት አይቋቋምም፡፡
5. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የክልል ምክር ቤቶች በአንቀጽ 34 ንዑስ አንቀጽ 5 መሰረት የሃይማኖትና የባሕል ፍርድ ቤቶችን ሊያቋቁሙ ወይም እውቅና ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ይህ ሕገ መንግሥት ከመጽደቁ በፊት በመንግሥት እውቅና አግኝተው ሲሰራባቸው የነበሩ የሃይማኖቶችና የባሕል ፍርድ ቤቶች በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት እውቅና አግኝተው ይደራጃሉ፡፡

## አንቀጽ 79

## የዳኝነት ሥልጣን

1. በፌዴራልም ሆነ በክልል የዳኝነት ሥልጣን የፍርድ ቤቶች ብቻ ነው፡፡
2. በየትኛውም ደረጃ የሚገኝ የዳኝነት አካል ከማንኛውም የመንግሥት አካል፣ ከማንኛውም ባለሥልጣን ሆነ ከማንኛውም ሌላ ተጽዕኖ ነፃ ነው፡፡
3. ዳኞች የዳኝነት ተግባራቸውን በሙሉ ነፃነት ያከናውናሉ፡፡ ከሕግ በስተቀር በሌላ ሁኔታ አይመሩም፡፡
4. ማንኛውም ዳኛ ከዚህ በታች በተመለከቱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር በሕግ ከተወሰነው የጡረታ ዕድሜ ከመድረሱ በፊት ከፈቃዱ ውጭ ከዳኝነት ሥራው አይነሳም፤

   ሀ/ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በዳኞች የዲሲፕሊን ሕግ መሠረት ጥፋት ፈጽሟል ወይም ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና አንሶታል ብሎ ሲወስን፣ ወይም

   ለ/ በህመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ብሎ ሲወስን፣ እና

   ሐ/ የጉባዔው ውሳኔ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወይም በክልል ምክር ቤቶች ከግማሽ በላይ ድምፅ ሲጸድቅ፡፡

5. የማንኛውም ዳኛ የጡረታ መውጫ ጊዜ አይራዘምም፡፡
6. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራሉን መንግሥት የዳኝነት አካል የሚያስተዳድርበትን በጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤ ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል፡፡
7. የክልል የዳኝነት አካሎች በጀት በየክልሉ ምክር ቤቶች ይመደባል፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፌዴራሉን የከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የዳኝነት ሥልጣን ደርበው ለሚሠሩት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶችና የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች የበጀት ማካካሻ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 80

## የፍርድ ቤቶች ጣምራነትና ሥልጣን

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል ጉዳዮች ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
2. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በክልሉ ጉዳይ ላይ የበላይና የመጨረሻ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪ የፌዴራል የከፍተኛ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተጠቀሰው ቢኖርም፤
   ሀ/ የፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን ማናቸውንም የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
   ለ/ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሰረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት ያለበትን በክልል ጉዳዮች የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ለማረም በሰበር ችሎት የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡
4. የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በክልሉ ከሚኖረው የዳኝነት ሥልጣን በተጨማሪ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡
5. የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣኑ መሰረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፡፡
6. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በፌዴራል የዳኝነት ሥልጣኑ በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርበው ይግባኝ በፌዴራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይታያል፡፡

## አንቀጽ 81

## ስለዳኞች አሿሿም

1. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትና ምክትል ፕሬዚዳንት በፌዴራል መንግሥት ጠቅላይ ሚኒስትር አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
2. ሌሎች የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞችን በተመለከተ በፌዴራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የቀረቡለትን እጩዎች ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለሕዝብ ተወካዮች ምክርት ቤት አቅርቦ ያሾማል፡፡
3. የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤትና የክልል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡ የክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የዳኞችን ሹመት ለምክር ቤቱ ከማቅረቡ በፊት የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ በእጩዎቹ ላይ ያለውን አስተያየት መጠየቅና አስተያየቱን ከራሱ አስተያየት ጋር በማያያዝ ለክልሉ ምክር ቤት የማቅረብ ኃላፊነት አለበት፡፡ የፌዴራሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አስተያየቱን በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ካላቀረበ የክልሉ ምክር ቤት ሹመቱን ያጸድቃል፡፡
4. የክልል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች በክልሉ የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ አቅራቢነት በክልሉ ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
5. በየትኛውም ደረጃ የሚገኑ ዳኞች የዲሲፕሊንና የዝውውር ጉዳይ በሚመለከተው የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 82

## የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አወቃቀር

1. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በዚህ ሕገ መንግሥት ተቋቁሟል፡፡
2. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አሥራ አንድ አባላት ይኖሩታል፡፡ አባላቱም የሚከተሉት ናቸው፤

   ሀ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ሰብሳቢ፤

   ለ/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ሰብሳቢ፤

   ሐ/ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅራቢነት በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚሾሙ በሙያ ብቃታቸውና በሥነ ምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች፤

   መ/ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል የሚወክላቸው ሦስት ሰዎች፡፡

3. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሥራ ቅልጥፍናን ለማረጋገጥ የሚያስችለው መዋቅር ሊዘረጋ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 83

## ሕገ መንግሥቱን ስለመተርጎም

1. የሕገ መንግሥታዊ ክርክር ጉዳይ ሲነሳ በፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ውሳኔ ያገኛል፡፡
2. የፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ በሚያቀርብለት ሕገ መንግሥታዊ ጉዳይ ላይ በሠላሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

## አንቀጽ 84

## የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ሥልጣንና ተግባር

1. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን ይኖረዋል፡፡ በሚያደርገው ማጣራት መሰረት ሕገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለፌዴሬሽን ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡
2. በፌዴራሉ መንግስትም ሆነ በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ ሕጎች ከዚህ ሕገ መንግሥት ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳና ጉዳዩም በሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም በባለ ጉዳዩ ሲቀርብለት መርምሮ ለመጨረሻ ውሳኔ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ያቀርባል፡፡
3. በፍርድ ቤቶች የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሲነሳ፣
   ሀ/ ሕገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሳያገኘው ሲቀር ጉዳዩን ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ይመልሳል፤ በአጣሪ ጉባዔው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለጉዳይ ቅሬታውን ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
   ለ/ የትርጉም ጥያቄ መኖሩን ያመነበት እንደሆነ በጉዳዩ ላይ የሚሰጠውን ሕገ መንግሥታዊ ትርጉም ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ለመጨረሻ ውሳኔ ያቀርባል፡፡
4. የሚመራበትን ሥነ ሥርዓት አርቅቆ ለፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ አሥር

## የብሔራዊ ፖሊሲ መርሆዎችና ዓላማዎች

### አንቀጽ 85

### ዓላማዎች

1. ማንኛውም የመንግሥት አካል ሕገ መንግሥቱን፣ ሌሎች ሕጎችንና ፖሊሲዎችን ሥራ ላይ ሲያውል በዚህ ምዕራፍ በተመለከቱት መርሆዎችና ዓላማዎች ላይ መመስረት አለበት፡፡
2. በዚህ ምዕራፍ ውስጥ "መንግሥት" ማለት እንደየሁኔታው የፌዴራል መንግሥት ወይም የክልል መስተዳድሮች ማለት ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 86

### የውጭ ግንኙነት መርሆዎች

1. የኢትዮጵያን ሕዝቦች ጥቅም የሚያስጠብቅና የሀገሪቱን ሉዓላዊነት የሚያስከብር የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ ማራመድ፡፡
2. የመንግሥታትን ሉዓላዊነትና እኩልነት ማክበር፣ በሌሎች ሀገሮች ጉዳዮች ውስጥ ጣልቃ አለመግባት፡፡
3. የሀገሪቱ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን እንዲሁም በዓለም አቀፍ ደረጃ የሚደረጉ ስምምነቶች የኢትዮጵያን ጥቅም የሚያስከብሩ መሆናቸውን ማረጋገጥ፡፡
4. የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት የሚያስከብሩና የሕዝቦቿን ጥቅም የማይፃረሩ ዓለም አቀፍ ሕጎችና ስምምነቶችን ማክበር፡፡
5. ከጎረቤት ሀገሮችና ከሌሎችም የአፍሪካ ሀገሮች ጋር በየጊዜው እያደገ የሚሄድ ኢኮኖሚያዊ ኅብረትና የሕዝቦች ወንድማማችነትን ማጎልበት፡፡
6. በሀገሮች መካከል የሚነሱ ግጭቶች ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ጥረት ማድረግ፡፡

### አንቀጽ 87

### የመከላከያ መርሆዎች

1. የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት የብሔሮች፣ የብሔረሰቦች እና የሕዝቦችን ሚዛናዊ ተዋፅዖ ያካተተ ይሆናል፡፡
2. የመከላከያ ሚኒስትር ሆኖ የሚሾመው ሲቪል ይሆናል፡፡

3. የመከላከያ ሠራዊት የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ከመጠበቅ በተጨማሪ በዚህ ሕገ መንግሥት መሰረት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የሚሰጡትን ተግባሮች ያከናውናል፡፡
4. የመከላከያ ሠራዊቱ በማናቸውም ጊዜ ለሕገ መንግሥቱ ተገዢ ይሆናል፡፡
5. የመከላከያ ሠራዊቱ ተግባሩን ከፖለቲካ ድርጅቶች ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን ያከናውናል፡፡

## አንቀጽ 88

## ፖለቲካ ነክ ዓላማዎች

1. መንግሥት በዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ላይ በመመስረት ሕዝቡ በሁሉም ደረጃዎች ራሱን በራሱ የሚያስተዳድርበትን ሁኔታ ማመቻቸት አለበት፡፡
2. መንግሥት የብሔሮችን፣ የብሔረሰቦችን፣ የሕዝቦችን ማንነት የማክበርና በዚሁ ላይ በመመርኮዝ በመካከላቸው እኩልነት፣ አንድነትና ወንድማማችነትን የማጠናከር ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 89

## ኢኮኖሚ ነክ ዓላማዎች

1. መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያውን የሀገሪቱ የተጠራቀመ ዕውቀትና ሀብት ተጠቃሚዎች የሚሆኑበትን መንገድ የመቀየስ ኃላፊነት አለበት፡፡
2. መንግሥት የኢትዮጵያውያንን የኢኮኖሚ ሁኔታዎች ለማሻሻል እኩል ዕድል እንዲኖራቸው ለማድረግና ሀብት ፍትሐዊ በሆነ መንገድ የሚከፋፈሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለበት፡፡
3. የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ አደጋ እንዳይደርስ መከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጎጂው እርዳታ በወቅቱ እንዲደርስ ማድረግ፡፡
4. በእድገት ወደ ኋላ ለቀሩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች መንግሥት ልዩ ድጋፍ ያደርጋል፡፡
5. መንግሥት መሬትንና የተፈጥሮ ሀብትን በሕዝብ ስም በይዞታው ስር በማድረግ ለሕዝቡ የጋራ ጥቅምና እድገት እንዲውሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡
6. የሀገር ልማት ፖሊሲዎችና ፕሮግራሞች በሚዘጋጁበት ወቅት መንግሥት ሕዝቡን በየደረጃው ማሳተፍ አለበት፡፡ የሕዝብንም የልማት እንቅስቃሴዎች መደገፍ አለበት፡፡
7. መንግሥት በሀገር ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ልማት እንቅስቃሴ ውስጥ ሴቶች ከወንዶች ጋር በእኩልነት የሚሳተፉበትን ሁኔታ የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት፡፡

8. መንግሥት የሠራተኛውን ሕዝብ ጤንነት፣ ደህንነትና የኑሮ ደረጃ ለመጠበቅ መጣር አለበት፡፡

## አንቀጽ 90

## ማኅበራዊ ነክ ዓላማዎች

1. የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንጹህ ውሃ፣ የመኖሪያ፣ የምግብና የማኅበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ይደረጋል፡፡
2. ትምህርት በማናቸውም ረገድ ከሃይማኖት፣ ከፖለቲካ አመለካከቶች እና ከባሕላዊ ተፅዕኖዎች ነፃ በሆነ መንገድ መካሄድ አለበት፡፡

## አንቀጽ 91

## ባሕል ነክ ዓላማዎች

1. መንግሥት መሰረታዊ መብቶችንና ሰብዓዊ ክብርን፣ ዲሞክራሲንና ሕገ መንግሥቱን የማይቃረኑ ባሕሎችና ልማዶች በእኩልነት እንዲጎለብቱና እንዲያድጉ የመርዳት ኃላፊነት አለበት፡፡
2. የሀገር የተፈጥሮ ሀብቶችንና የታሪክ ቅርሶችን መጠበቅ የመንግሥትና የሁሉም ኢትዮጵያዊ ግዴታ ነው፡፡
3. መንግሥት አቅም በፈቀደ መጠን ኪነጥበብን፣ ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ 92

## የአካባቢ ደህንነት ጥበቃ ዓላማዎች

1. መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንጹህና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት አለበት፡፡
2. ማንኛውም የኢኮኖሚ ልማት እርምጃ የአካባቢውን ደህንነት የማያናጋ መሆን አለበት፡፡
3. የሕዝብን የአካባቢ ደህንነት የሚመለከት ፖሊሲና ፕሮግራም በሚነደፍበትና ሥራ ላይ በሚውልበት ጊዜ የሚመለከተው ሕዝብ ሁሉ ሀሳቡን እንዲገልጽ መደረግ አለበት፡፡
4. መንግሥትና ዜጎች አካባቢያቸውን የመንከባከብ ግዴታ አለባቸው፡፡

## ምዕራፍ አሥራ አንድ

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 93

### ስለ አስቸኳይ ጊዜ አዋጅ

1. ሀ/ የውጭ ወረራ ሲያጋጥም ወይም ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ሲከሰትና በተለመደው የሕግ ማስከበር ሥርዓት ለመቋቋም የማይቻል ሲሆን፣ ማናቸውም የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት፣ የፌዴራሉ መንግሥት የሚንስትሮች ምክር ቤት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ የመደንገግ ሥልጣን አለው፡፡

   ለ/ የተፈጥሮ አደጋ ሲያጋጥም ወይም የሕዝብን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል በሽታ ሲከሰት የክልል መስተዳድሮች በክልላቸው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ሊያውጁ ይችላሉ፤ ዝርዝሩ ክልሎች ይህን ሕገ መንግሥት መሰረት በማድረግ በሚያወጧቸው ሕገ መንግሥቶች ይወሰናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 (ሀ) መሰረት የሚታወጅ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ፣

   ሀ/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሥራ ላይ ባለ ጊዜ የታወጀ ከሆነ በታወጀ በአርባ ስምንት ሰዓታት ውስጥ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቅረብ አለበት፡፡ አዋጁ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሁለት ሦስተኛ ድምፅ ተቀባይነት ካላገኘ ወዲያውኑ ይሻራል፡፡

   ለ/ ከላይ በንዑስ አንቀጽ (ሀ) ስር የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሥራ ላይ ባልሆነበት ወቅት የሚታወጅ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መቅረብ ያለበት አዋጁ በታወጀ በአሥራ አምስት ቀናት ውስጥ ነው፡፡

3. በሚኒስትሮች ምክር ቤት የተደነገገው የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በምክር ቤቱ ተቀባይነት ካገኘ በኋላ ሊቆይ የሚችለው እስከ ስድስት ወራት ነው፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ አንድን የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በየአራት ወሩ በተደጋጋሚ እንዲታደስ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4. ሀ/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚታወጅበት ጊዜ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣቸው ደንቦች መሰረት የሀገርን ሰላምና ሕልውና፣ የሕዝብን ደህንነት፣ ሕግና ሥርዓትን የማስከበር ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

   ለ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሥልጣን በሕገ መንግሥቱ የተቀመጡትን መሰረታዊ

የፖለቲካና የዴሞክራሲ መብቶችን፣ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጁን ለማወጅ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ ለማስወገድ ተፈላጊ ሆኖ በተገኘው ደረጃ እስከ ማገድ ሊደርስ የሚችል ነው፡፡

ሐ/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ስር የሚያወጣቸው ድንጋጌዎችና የሚወስዳቸው እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ በዚህ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 1፣ 18፣ 25 እና 39 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተቀመጡትን መብቶች የሚገድቡ ሊሆኑ አይችሉም፡፡

5. በሀገሪቱ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ በሚታወጅበት ወቅት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአባላቱና ከሕግ ባለሙያዎች መርጦ የሚመድባቸው ሰባት አባላት ያሉት የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ ያቋቁማል፡፡ ቦርዱ አዋጁ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚጸድቅበት ጊዜ ይቋቋማል፡፡

6. የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ አፈጻጸም መርማሪ ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ኃላፊነቶች አሉት፤

ሀ/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ምክንያት የታሰሩትን ግለሰቦች ስም በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይፋ ማድረግና የታሰሩበትን ምክንያት መግለጽ፡፡

ለ/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ ወቅት የሚወሰዱት እርምጃዎች በማናቸውም ረገድ ኢሰብዓዊ አለመሆናቸውን መቆጣጠርና መከታተል፣

ሐ/ ማናቸውም የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃ ኢሰብዓዊ መሆኑን ሲያምንበት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም የሚኒስትሮች ምክር ቤት እርምጃውን እንዲያስተካክል ሀሳብ መስጠት፣

መ/ በአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እርምጃዎች ኢሰብዓዊ ድርጊት የሚፈጽሙትን ሁሉ ለፍርድ እንዲቀርቡ ማድረግ፣

ሠ/ የአስቸኳይ ጊዜ አዋጅ እንዲቀጥል ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጥያቄ ሲቀርብ ያለውን አስተያየት ለምክር ቤቱ ማቅረብ፡፡

## <u>አንቀጽ 94</u>

## <u>የፋይናንስ ወጪን በሚመለከት</u>

1. የፌዴራሉ መንግሥትና ክልሎች በሕግ የተሰጧቸውን ኃላፊነቶችና ተግባሮች ለማከናወን የሚያስፈልጋቸውን ወጪ በየበኩላቸው ይሸፍናሉ፤ ሆኖም ማናቸውም ክልል በውክልና ለሚፈጽመው ተግባር የሚያስፈልገው ወጪ ሌላ ስምምነት ከሌለ በቀር ውክልናውን በሰጠው ወገን ይሸፈናል፡፡

2. የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች የተመጣጠነ እድገት እንቅፋት ካልሆነ በስተቀር ለአስቸኳይ ጊዜ እርዳታ፣ ለመልሶ ማቋቋምና ለልማት ማስፋፊያ ለክልሎች ብድርም ሆነ እርዳታ ሊሰጥ ይችላል፡፡ የፌዴራሉ መንግሥት ክልሎች ለሚያስፈልጋቸው ወጪ የሚያደርገውን ድጎማ በሚመለከት ኦዲትና ቁጥጥር የማድረግ ሥልጣን ይኖረዋል፡፡

## አንቀጽ 95

## የፋይናንስ ገቢን በሚመለከት

የፌዴራሉ መንግሥትና ክልሎች የሚዋቀረውን የፌዴራል አደረጃጀት የተከተለ የገቢ ክፍፍል ያደርጋሉ፡፡

## አንቀጽ 96

## የፌዴራል መንግሥት የታክስና የግብር ሥልጣን

1. የፌዴራል መንግሥት በወጪና ገቢ ዕቃዎች ላይ የጉምሩክ ቀረጥ፣ ታክስና ሌሎች ክፍያዎች ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
2. በፌዴራል መንግሥትና በዓለም አቀፍ ድርጅቶች ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
3. በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሆኑ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይስ ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
4. በብሔራዊ የሎተሪ እና ሌሎች የዕድል ሙከራ ገቢዎች ላይ ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
5. በአየር፣ በባቡርና በባሕር ትራንስፖርት ገቢዎች ላይ ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
6. በፌዴራል መንግሥት ባለቤትነት ሥር በሚገኙ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ገቢ ላይ ግብር ይጥላል፣ ይሰበስባል፤ ኪራይ ይወስናል፡፡
7. የፌዴራል መንግሥት አካላት ከሚሰጧቸው ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎችን ይወስናል፤ ይሰበስባል፡፡
8. የሞኖፖል ታክስ ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡
9. የፌዴራል የቴምብር ሽያጭ ቀረጥ ይጥላል፣ ይሰበስባል፡፡

## አንቀጽ 97

## የክልል መስተዳድሮች የታክስና የግብር ሥልጣን

1. ክልሎች፣ በክልል መስተዳድርና በድርጅት ተቀጣሪዎች ላይ የሥራ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
2. የመሬት መጠቀሚያ ክፍያ ይወስናሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
3. በግል የሚያርሱና በኅብረት ሥራ ማኅበራት በተደራጁ ገበሬዎች ላይ የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
4. በክልሉ በሚገኙ ግለሰብ ነጋዴዎች ላይ የንግድ ትርፍ ግብርና የሽያጭ ታክስ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
5. በክልሉ ውስጥ በውሀ ላይ ከሚደረግ ትራንስፖርት በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
6. በክልል መስተዳድር በግል ባለቤትነት ስር ካሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች በሚገኝ ገቢ ላይ ግብር ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፤ በባለቤትነታቸው ስር ባሉ ቤቶችና ሌሎች ንብረቶች ላይ ኪራይ ያስከፍላሉ፡፡
7. በክልል መስተዳድር ባለቤትነት ስር በሚገኙ የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና ኤክሳይስ ታክስ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
8. በአንቀጽ 98 ንዑስ አንቀጽ 3 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በማዕድን ሥራዎች ላይ የማዕድን ገቢ ግብር፣ የሮያሊቲና የመሬት ኪራይ ክፍያዎች ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
9. በክልል መስተዳድር አካላት ከሚሰጡ ፈቃዶችና አገልግሎቶች የሚመነጩ ክፍያዎች ይወስናሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
10. ከደን የሚገኝ የሮያሊቲ ክፍያ ይወስናሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡

## አንቀጽ 98

## የጋራ የታክስና የግብር ሥልጣን

1. የፌዴራል መንግሥትና ክልሎች በጋራ በሚያቋቁሟቸው የልማት ድርጅቶች ላይ የንግድ ትርፍ ግብር፣ የሥራ ግብር፣ የሽያጭና የኤክሳይስ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡
2. በድርጅቶች የንግድ ትርፍ ላይ እና በባለ አክሲዮኖች የትርፍ ድርሻ ላይ ግብርና የሽያጭ ታክስ በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡

3. በከፍተኛ የማዕድን ሥራዎችና በማናቸውም የፔትሮሊየምና የጋዝ ሥራዎች ላይ የገቢ ግብርና የሮያሊቲ ክፍያዎች በጋራ ይጥላሉ፣ ይሰበስባሉ፡፡

## አንቀጽ 99

## ተለይተው ስላልተሰጡ የታክስ እና የግብር ሥልጣኖች

በዚህ ሕገ መንግሥት ተለይተው ያልተሰጡ ታክስና ግብር የመጣል ሥልጣኖችን በሚመለከት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤትና የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ይወስናሉ፡፡

## አንቀጽ 100

## የታክስና የግብር አጣጣል መርሆዎች

1. ክልሎችና የፌዴራሉ መንግሥት ታክስና ግብር በሚጥሉበት ጊዜ የሚጠየቀው ታክስና ግብር ከምንጩ ጋር የተያያዘና በአግባቡ ተጠንቶ የተወሰነ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
2. በመካከላቸው የሚኖረውን መልካም ግንኙነት የማይጎዳና ከሚቀርበው አገልግሎት ጋር ተመጣጣኝ መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው፡፡
3. ለትርፍ የቆመ ድርጅት ካልሆነ በስተቀር ክልሎች በፌዴራሉ መንግሥት ንብረት ላይ፣ የፌዴራሉ መንግሥትም በክልሎች ንብረት ላይ ግብር ወይም ቀረጥ የማስከፈል ሥልጣን አይኖራቸውም፡፡

## አንቀጽ 101

## ዋናው ኦዲተር

1. ዋናው ኦዲተር በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማል፡፡
2. ዋናው ኦዲተር የፌዴራሉን የሚኒስቴርና ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ሂሳቦች በመቆጣጠር በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተመደበው ዓመታዊ በጀት፣ በበጀት ዓመቱ ለተሠሩት ሥራዎች በሚገባ መዋሉን መርምሮ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. ዋናው ኦዲተር የመሥሪያ ቤቱን በጀት በቀጥታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስጸድቃል፡፡
4. የዋናው ኦዲተር ዝርዝር ተግባር በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 102

## የምርጫ ቦርድ

1. በፌዴራልና በክልል የምርጫ ክልሎች ነፃና ትክክለኛ ምርጫ በገለልተኝነት እንዲያካሂድ ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ይቋቋማል፡፡
2. የቦርዱ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡ ዝርዝሩ በሕግ ይወሰናል፡፡

## አንቀጽ 103

## የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን

1. የሀገሪቱን የሕዝብ ቁጥር በየጊዜው የሚያጠናና ቆጠራ የሚያካሂድ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ይኖራል፡፡
2. የኮሚሽኑ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ፡፡
3. ኮሚሽኑ ዋና ጸሐፊ፣ አስፈላጊ ባለሙያዎችና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች ይኖሩታል፣
4. የኮሚሽኑ ዓመታዊ በጀት በቀጥታ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ይጸድቃል፡፡
5. የሕዝብ ቆጠራ በየአሥር ዓመቱ ይካሄዳል፡፡ በውጤቱም መሰረት የምርጫ ክልሎችን አከላለል የምርጫ ቦርድ በሚያቀርበው ረቂቅ መሠረት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት ይወስናል፡፡
6. የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፡፡ ስለ ሥራው አፈጻጸም በየጊዜው ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

## አንቀጽ 104

## የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብን ስለማመንጨት

አንድ የሕገ መንግሥት ማሻሻያ ሀሳብ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ የደገፈው፣ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ የደገፈው ወይም ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ውስጥ አንድ ሦስተኛው የክልል ምክር ቤቶች በድምፅ ብልጫ የደገፉት ከሆነ ለውይይትና ለውሳኔ ለመላው ሕዝብና የሕገ መንግሥቱ መሻሻል ለሚመለከታቸው ክፍሎች ይቀርባል፡፡

## አንቀጽ 105

## ሕገ መንግሥቱን ስለማሻሻል

1. በዚህ ሕገ መንግሥት ምዕራፍ ሦስት የተዘረዘሩት መብቶችና ነፃነቶች በሙሉ፣ ይህ አንቀጽ፣ እንዲሁም አንቀጽ 104 ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ብቻ ይሆናል፡፡

   ሀ/ ሁሉም የክልል ምክር ቤቶች የቀረበውን ማሻሻያ በድምፅ ብልጫ ሲያጸድቁት፣

   ለ/ የፌዴራሉ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቀው፣ እና

   ሐ/ የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ማሻሻያውን ሲያጸድቀው ነው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተዘረዘሩት ውጭ ያሉት የሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ሊሻሻሉ የሚችሉት በሚከተለው አኳኋን ብቻ ይሆናል፤

   ሀ/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት በጋራ ስብሰባ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቁት፣ እና

   ለ/ ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ምክር ቤቶች ውስጥ የሁለት ሦስተኛ ክልሎች ምክር ቤቶች በድምፅ ብልጫ የቀረበውን ማሻሻያ ሲያጸድቁት ነው፡፡

## አንቀጽ 106

## የመጨረሻ ሕጋዊ እውቅና ስላለው ቅጂ

የዚህ ሕገ መንግሥት የአማርኛ ቅጂ የመጨረሻው ሕጋዊ እውቅና ያለው ሰነድ ነው፡፡

## አዋጅ ቁጥር 2/1987

## የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መመስረቱን ለማስታወቅ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች መርጠው በላኳቸው ተወካዮቻቸው አማካኝነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስትን ያጸደቁ በመሆኑ፤

በጸደቀው ህገመንግስት በተደነገገው መሰረት የፌደራልመንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌደሬሽን ምክር ቤት አባላት ምርጫ እና ውክልና ተከናውኖ የፌዴሬሽኑ መስራች ጉባዔ የተካሄደ በመሆኑ፤

በህገ መንግስቱ አንቀጽ 55/1 መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መመስረቱን ለማስታወቅ የወጣ አዋጅ ቁጥር 2/1987" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **የፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መመስረት**

   የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ከነሐሴ 15 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ ተመስርቷል፡፡

3. **ስልጣን ስለመረከብ**

   የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ወካዮች ምክር ቤት ከነሐሴ 15 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ የመንግስት ስልጣንን ከሽግግሩ መንግስት ተረክቧል፡፡

4. **ስለተሻሩ ህጎች**

   የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፤

   1. የሽግግር ወቅት ቻርተር፤
   2. የፕሬዚዳንቱን ስልጣን እና ተግባር ለመወሰን የወጣው አዋጅ ቁጥር 1/1983፡፡

5. **ስለነባር ህጎች ተፈጻሚነት**

   በስራ ላይ ያለ ማንኛውም ህግ ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ጋር እስካልተቃረነ ድረስ ተፈጻሚነቱ ይቀጥላል፡፡

6. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ አዋጅ ከነሐሴ 16 ቀን 1987 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 16 ቀን 1987 ዓ.ም.**

**(ዶ/ር) ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 3/1987

## የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣን ማቋቋም በማስፈለጉ፤ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 3/1987" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ መቋቋም**

   1. የፌዴራል የሕግ ጋዜጣ የሆነ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የሚወጣ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
   2. ማናቸውም የፌዴራል መንግሥት ሕግ የሚወጣው በፌዴራሉ ነጋሪት ጋዜጣ ይሆናል፡፡
   3. ማናቸውም የፌዴራል ወይም የክልል ህግ አውጪ፣ አስፈጻሚ እና ተርጓሚ እንዲሁም ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ የሚወጣ ሕግን የመቀበል ግዴታ ይኖርበታል።
   4. የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ የሚታተመው በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች ይሆናል፣ በሁለቱ ቋንቋዎች መካከል የይዘት ልዩነት በሚፈጠርበት ጊዜ የአማርኛው የበላይነት ይኖረዋል።

3. **የተሻረ ሕግ**

   የነጋሪት ጋዜጣ ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1/1934 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

4. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

   ይህ አዋጅ ከነሐሴ 16 ቀን1987 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ16 ቀን 1987 ዓ.ም**

**(ዶ/ር) ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 654/2001

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ

ስለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማ በህገ መንግሥቱ አንቀፅ 3 ንዑስ አንቀፅ /1/ እና /2/ የተደነገገ በመሆኑ፤

ይህንን ህገ መንግሥታዊ ድንጋጌ ተከትለው ቀደም ሲል የወጡትና በስራ ላይ ያሉት ህጎች ሰንደቅ ዓላማን በሚመለከት ያልሸፈንዋቸው እና ያልተመለከትዋቸው ጉዳዮች በመኖራቸው፤

ለሕገመንግሥቱ ድንጋጌ አፈፃፀም ሰንደቅ አላማንና አርማን የሚመለከቱ ዝርዝር ጉዳዮችን የሚወስን እና ቀደም ሲል የነበሩትን የተለያዩ ህጎች በአንድ ላይ የሚያጠቃልል አንድ ራሱን የቻለ ሕግ ማውጣቱ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀፅ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር 654/2001" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

   1. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 47 መሠረት የተቋቋመ የፌዴሬሽኑ አባል ክልልማለት ነው፤
   2. "የከተማ መስተዳደር" ማለት የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳደር ወይም የድሬደዋ ከተማ መስተዳደር ማለት ነው፤
   3. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
   4. "በስተቀኝ" ማለት አንድ ሰው ፊቱን ወደ ተመልካች አቅጣጫ በማድረግ ሰንደቅ ዓላማዎች በሚቆሙበት ወይም በሚሰቀሉበት ወይም ባሉበት መስመር መሀል ሲቆም የሚኖረው የቀኝ እጅ አቅጣጫ ማለት ነው።

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

   ይህ አዋጅ፦

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የግዛት ወሰን ውስጥ የክልል መንግስታትንና የከተማ መተዳደሮችን ጨምሮ፤ እና
2. በውጭ ሀገር በሚገኙ ኢትዮጵያውያን፤ የኢትዮጵያ ኢምባሲዎችና ቆንስላዎች፤ የኢትዮጵያ ንግድ መርከቦችና ጀልባዎች እና አውሮፕላኖች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን

4. **የሰንደቅ ዓላማ ቀን**

ብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን /ከዚህ በኋላ "የብሔራዊ የሰንደቅ ዓላማ ቀን" እየተባለ የሚጠራ/ በየዓመቱ ጥቅምት ወር የመጀመሪያ ሰኞ በአገር አቀፍ ደረጃ ይከበራል፡፡[1]

## ክፍል ሦስት

## ስለ ሰንደቅ ዓላማና ብሔራዊ ዓርማ

5. **የሰንደቅ ዓላማ ምንነት**

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማ (ከዚህ በኋላ "ሰንደቅ ዓላማው" እየተባለ የሚጠራ) የሪፐብሊኩ ሉዓላዊነትና የሕዝቦች በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት መግለጫ ነው።

6. **የሰንደቅ ዓላማው ቀለማትና ቅርፅ**

1. ሰንደቅ ዓላማው ከላይ አረንጓዴ፣ ከመሃልቢጫ፣ ከታች ቀይ ሆኖ በክብ ሰማያዊ መደብ ላይ የተቀረፀ ብሔራዊ ዓርማ ይኖረዋል። ዓርማው በሰንደቅ ዓላማው መሃከል ላይ የሚያርፈው የክቡ ዙሪያ የአረንጓዴውንና የቀዩን ቀለማት ቁመት አጋማሽ አካሎ ይሆናል፡፡
2. ቀለማቱ ብሩህና መሠረታዊ ይሆናሉ።
3. ቀለማቱ አግድም የተዋቀሩና እኩል ስፋት የሚኖራቸው ይሆናሉ፤ የሰንደቅ ዓላማው ወርድ የቁመቱ እጥፍ ይሆናል፡፡
4. የዓርማው ቅርፅ ክብ በሆነ ሰማያዊ መደብ ላይ፦

ሀ/ ከየአቅጣጫው መጥተው የሚገናኙ ቀጥታና እኩል የሆኑ ቢጫ መስመሮች ይኖረዋል፤

ለ/ ቀጥታና እኩል ከሆኑት መስመሮች የተዋቀረ ኮከብ ይኖረዋል፤

[1] በ20/61(2006) አ.863 አንቀጽ 2(1) ተሻሻለ፡፡

ሐ/ ቀጥታና እኩል በሆኑት መስመሮች መተላለፊያ ላይ የማጊፊነጥቅ ቢጫ ጨረር ይኖረዋል።

7. **<u>የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት ትርጉም</u>**

የሰንደቅ ዓላማው ቀለማት የሚከተለው ትርጉም ይኖራቸዋል፡

1. አረንጓዴው የሥራ፣ የልምላሜና የእድገት ምልክት ነው፤
2. ቢጫው የተስፋ፣ የፍትህ እና እኩልነት ምልክት ነው፤
3. ቀዩ ለነፃነትና ለእኩልነት መስፊን የሚደረግ የመስዋዕትነትና የጀግንነት ምልክት ነው።

8. **<u>የዓርማው ትርጉም</u>**

1. ክብ የሆነው ሰማያዊ መደብ ሰላምን ያመለክታል።
2. ቀጥታና እኩል የሆኑት መስመሮች፤ የብሔሮች፣ የብሔረሰቦችና የሕዝቦች እንዲሁም የሀይማኖቶችን እኩልነት ያመለክታሉ።
3. ቀጥታና እኩል ከሆኑት መስመሮች የተዋቀረው ኮከብ፤ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በመፈቃቀድ የመሠረቱትን አንድነት ያመለክታል።
4. ቢጫ ጨረር፤ በመፈቃቀድ አንድነት ለመሠረቱት ብሔር፣ ብሔረሰቦች የፈነጠቀውን ብሩህ ተስፋ ይጠቁማል።

9. **<u>የሰንደቅ ዓላማው ስዕላዊ መልክ</u>**

የሰንደቅ ዓላማው ስዕላዊ መልክ እንደሚከተለው ነው፡-

ስዕሉ እዚህ ይገባል

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የሰንደቅ ዓላማ አሰቃቀልና አጠቃቀም ስነስርዓት</u>

10. **<u>የሰንደቅ ዓላማው መጠን</u>**

በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 6 ንዑስ አንቀፅ /3/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሰንደቅ ዓላማው የሚከተሉት መጠኖች ይኖሩታል።

| ተ/ቁ | የሰንደቅ አላማው ቁመት እና ወርዱ መጠን በሳንቲ ሜትር |
|---|---|
| 1 | 210 x 240 |
| 2 | 150 x 300 |
| 3 | 135 x 270 |

| | |
|---|---|
| 4 | 105 x 210 |
| 5 | 90 x 180 |
| 6 | 21 x 42 |

11.**<u>የሰንደቅ ዓላማው መጠን አጠቃቀም</u>**

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 6/3/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ቦታዎችና ክንዋኔዎች የሰንደቅ ዓላማው መጠን በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 10 በተደነገጉት መጠንን በሚመለከቱት ተራ ቁጥሮች መሠረት ይሆናል፡፡

1. በከፍተኛ አደባባይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር 1 ይሆናል፡፡
2. በመካከለኛ አደባባይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር 2 ይሆናል፡፡
3. በመስሪያ ቤቶች፣ በከፍተኛ የትምህርት ተቋማትና ድርጅቶች አደባባይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር 3 ይሆናል፡፡
4. በትልልቅ የመንግሥት ህንፃዎች ላይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር 3 ይሆናል።
5. በትልልቅ ህንፃዎች ምድር ቤት ውስጥ የሚገኙ ድርጅቶችና የንግድ ቤቶች የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር 4 ይሆናል።
6. በከፍተኛ መርከቦች ላይና በሰልፍ ጊዜ በክብር ዘብ የሚያዘው የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር 4 ይሆናል።
7. ለውጭ ሀገር እንግዳ አቀባበልና ለበዓላት በየመንገዱ ለሚውለበለብ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር 5 ይሆናል።
8. በመካከለኛ መርከቦች ላይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር 5 ይሆናል፡፡
9. በፕሬዝዳንቱ፣ በጠቅላይ ሚኒስትሩና በአምባሳደሮች ፅህፈት ቤት ጠረጴዛ ላይ የሰንደቅ ዓላማው መጠን ተራ ቁጥር 6 ይሆናል።
10. ፕሬዘዳንቱ፣ ጠቅላይ ሚኒስትሩና አምባሳደሮች በሚጓዙበት መኪና ላይ የሚውለበለበው ሰንደቅ ዓላማ የቁመቱና የወርዱ ቅንብር/ሬሾ/ 3 ለ 4 ሆኖ 30 በ40 ሳንቲም ሜትር ነው፡፡

12.**<u>የሰንደቅ ዓላማ አሰቃቀል</u>**

1. የሰንደቅ ዓላማውን መውለብለብ የሚያግድ ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካላጋጠመ በስተቀር፣ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ በሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ ከላይ እስከታች ባሉ የክልል የስልጣን አካላት ፅህፈት ቤቶች፣ በሚኒስቴር

መስሪያ ቤቶች፣ በሌሎች አስፈፃሚ አካላት ፅህፈት ቤቶች፣ በፍርድ ቤቶች፣ በትምህርት ቤቶች፣ በመከላከያ ድርጅቶች፣ በፖሊስና በጠረፍ ጥበቃ ተቋሞች፣ በሪፐብሊኩ ኢምባሲዎችና በአምባሳደሮች መኖሪያ ቤት ሕንፃዎች እንዲሁም የሪፐብሊኩ ንግድ መርከቦች እና ጀልባዎች በየቀኑ ሰንደቅ ዓላማ ይሰቅላሉ።

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ያልተመለከቱ የመንግሥት መስሪያ ቤቶች በብሔራዊ በዓል ቀን ሰንደቅ ዓላማ ይሰቅላሉ።
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ /2/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሰንደቅ ዓላማ የሚሰቀለው በሚከተሉት ስፍራዎች ይሆናል፦

   ሀ/ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በቅጥር ግቢው አደባባይ፤

   ለ/ በፌዴሬሽን ምክር ቤት በቅጥር ግቢው አደባባይ፤

   ሐ/ የሪፐብሊኩ ፕሬዘዳንትና ጠቅላይ ሚኒስትር በፅህፈት ቤቱና በመኖሪያ ቤቱ ሕንፃዎች።
4. የዚህ አንቀጽ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባልነት ለሚካሄድ ምርጫ ሰንደቅ ዓላማው መራጮች በሚመዘገቡበት እና ድምጻቸውን በሚሰጡበት ቦታ ይሰቀላል።
5. ሰንደቅ አላማው ከማናቸውም ኮሌጆች፣ የስፖርት ቡድኖች እና ተቋማትን ጨምሮ ከሌሎች አርማዎች ጋር በሚሰቀልበት ጊዜ ከመሀልና በቁመቱ ልክ ከፍ ብሎ ይውላል፡፡

13.<u>የሰንደቅ ልሣን</u>

የማንኛውም ሰንደቅ ልሣን /ጫፍ/ ግማሽ የክብ አምሳል ይኖረዋል።

14.<u>የሰንደቅ መትከያ ስፍራ</u>

በአደባባይ የሚውለበለብ ሰንደቅ ዓላማ የሚተከለው በተቻለ መጠን ከሚተከልበት ተቋም ሕንፃ ፊት ለፊትና መሀል ለመሀል ይሆናል።

15.<u>ሰንደቅ ዓላማው የሚሰቀልበትና የሚወርድበት ጊዜ</u>

1. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /2/ እና /3/ የተመለከቱት እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 12/1/ በተጠቀሱት መስሪያ ቤቶች እንዲሁም በመርከቦችና ጀልባዎች ላይ ሰንደቅ ዓላማው ከጠዋቱ በ12 ሰዓት ተሰቅሎ ከምሽቱ 12 ሰዓት ይወርዳል። ሆኖም የአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ በታወጀባቸው አካባቢዎች የሚገኙ የመከላከያ ሰራዊት አሀዶች ሁኔታው እስካልተለወጠ ድረስ መደበኛውን ሰዓት ጠብቀው ሰንደቅ ዓላማውን መስቀልና ማውረድ አይገደዱም፡፡

2. በትምህርት ቤቶች ሰንደቅ ዓላማው የሚሰቀለው ጠዋት ተማሪዎች ተሰልፈው ትምህርት ከመጀመሩ በፊት ይሆናል፣ የሚወርደውም ከምሽቱ 12 ሰዓት ይሆናል፡፡
3. በበዓላት ወቅት ሰንደቅ ዓላማው ከዋዜማው እስከ በዓሉ ማግስት የሚሰቀል ሲሆን በነዚህ ቀናትም ጠዋት 12 ሰዓት እየወጣ ከምሽቱ 12 ሰዓት ይወርዳል።

16.<u>ሰንደቅ ዓላማው አንድ ዓይነት ብቻ ስለ መሆኑ</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማ ከዚህ በላይ በተደነገጉት አንቀፆች መሠረት አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይና ከብ ሰማያዊ ቀለማት ኖሮት በመሀከሉ በዚህ አዋጅ የተዘረዘረው ዓርማ ያለው ብቻ ነው፡፡

17.<u>ሰንደቅ ዓላማው ሲሰቀልና ሲወርድ ሊሠጠው ስለሚገባ አክብሮት</u>

1. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ ይህንን የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሰንደቅ ዓላማ የሚገባውን ክብር የመስጠትና የማክበር ኃላፊነትና ግዴታ አለበት፡፡
2. ብሔራዊ የሆነ ታሪካዊ ክስተት ወይም ሁኔታ ጋር ግንኙነት ያላቸው ሰንደቅ ዓላማዎች ታሪክነታቸውን ለመጠበቅ በተዘጋጀ ቤተ መዘክር እንዲቀመጡ ይደረጋል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ሰንደቅ ዓላማው በሚያረጅበት፣ በሚቀደድበት ወይም በማንኛውም መልኩ ሊያገለግል ያልቻለ ሲሆን ተገቢው ክብርና ሥነ-ሥርዓት አፈፃፀም ተሰጥቶት በማቃጠል እንዲወገድ ይደረጋል፡፡

18.<u>ሰንደቅ ዓላማው ከፌዴሬሽኑ አባል ክልሎች ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲሰቀል የሚኖረው የአወጣጥ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከክልል ሰንደቅ ዓላማ ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ በስተቀኝ ይውላል።
2. የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከሁለት ክልሎች ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከመሀል ሆኖ በቁመቱ ልክ ከሁለቱ ሰንደቅ ዓላማዎች ከፍ ብሎ ሲውል የክልሎቹ ሰንደቅ ዓላማዎች ደግሞ በክልሎቹ ስያሜና በአማርኛ ፊደል ተራ መሰረት ቀዳሚው በቀኝ ሌላው በግራ ይውላል፡፡
3. የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከሁለት የበለጡ የክልሎች ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ በስተቀኝ መጨረሻ ሲውል

እሱን ተከትለው የክልሎች ሰንደቅ ዓላማዎች በክልሎቹ ስያሜና በአማርኛ ፊደል ተራ መሰረት ቦታቸውን ይይዛሉ።

19. <u>ሰንደቅ ዓላማው ከሌሎች ሃገራት ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲሰቀል የሚኖረው የአወጣጥ ስነስርዓት</u>

1. የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከሌላ ሃገር ሰንደቅ ዓላማ ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል በስተቀኝ ይውላል።
2. ከሁለት የሌሎች ሃገራት ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ ከመሀል ሆኖ ሌሎቹ ሰንደቅ ዓላማዎች በሃገራቱ ስምና በእንግሊዝኛ ፊደል ተራ መሠረት ቀዳሚው በቀኝ ሌላው በግራ ይውላል።
3. ከሁለት ከበለጡ የሌሎች ሃገራት ሰንደቅ ዓላማዎች ጋር ሲያዝ ወይም ሲሰቀል የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ በላቲን ፊደል ቅደም ተከተል ተራውን ይይዛል፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያ አስተናጋጅ እንጂ የጉዳይ ተካፋይ ካልሆነች የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ በስተቀኝ መጨረሻ ይውላል።
4. በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ 1 እስከ 3 የተደነገጉት እንደየአግባብነታቸው በተባበሩት መንግስታት፣ በአፍሪካ ሕብረት እና በሌሎች አለም አቀፍ ድርጅቶች ሰንደቅ አላማዎች ላይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

20. <u>በሰልፍ ጊዜ የሰንደቅ ዓላማው አያያዝ</u>

ሰንደቅ ዓላማው በሕዝባዊ ሰልፍ እንዲያዝ ሲደረግ የአያያዙ ስነስርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፦

1. ሰንደቅ ዓላማውን የያዘው ሰው ከሰልፈኛው ፊት መሀል ለመሀል አምስት ሜትር ቀድሞ ይሄዳል፣
2. ተሸካሚው ሰንደቁን ከታች በቀኝ እጅ ከላይ በግራ እጁ በሰውነቱ መሀል ለመሀል ቀጥ አድርጎ ይይዛል፣
3. ሰንደቅ ዓላማው ይታጀባል።

21. <u>በተሽከርካሪዎች ላይ ስለሚኖር የሰንደቅ ዓላማ አጠቃቀም ሥነ-ሥርዓት</u>

1. ማንኛውም የውጭ ሀገር ባለስልጣን ወይም የአለም አቀፍ ወይም አህጉር አቀፍ ድርጅት የስራ ኃላፊ ኢትዮጵያ ውስጥ በሚመጣበት ጊዜ የኢትዮጵያ መንግስት በሚመድብለት ተሽከርካሪ የሚጓዝ ከሆነ፤ በማንኛውም ጊዜ በተሽከርካሪው በስተቀኝ የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ የሚቀመጥ ሲሆን በስተግራ በኩል ደግሞ

ባለሥልጣኑ ወይም ኃላፊው የተወከለበት ሀገር ወይም ተቋም ሰንደቅ ዓላማ ይቀመጣል።

2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት እና ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሁም አምባሳደሮች የሚጓዙበት ተሽከርካሪ፣ ባቡር፣ አውሮፕላን፣ መርከብ ወይም ጀልባ ላይ ሰንደቅ ዓላማው ይሰቀላል።

3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ /2/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የሪፐብሊኩን ሰንደቅ ዓላማ በተሽከርካሪ ላይ በመስቀል መጠቀም የሚችሉት የሚከተሉት ብቻ ይሆናሉ፡-

   ሀ/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ፤

   ለ/ የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባኤ፤

   ሐ/ የፌዴራል መንግስቱ ሚኒስትሮች፤

   መ/ የሀገሪቱ የጦር ኃይሎች ኢታማዦር ሹም፤

   ሠ/ የፌዴራል ፍርድ ቤት ፕሬዝዳንቶች፤

   ረ/ የክልል መንግስታት ፕሬዝዳንቶች፡፡

## 22.<u>በብሔራዊ ሀዘን ጊዜ ስለሚኖር የሰንደቅ ዓላማ ስነስርዓት</u>[2]

1. በኃላፊነት ላይ ያለ ወይም ከኃላፊነት የተነሣ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝዳንት ወይም ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ከዚህ ዓለም በሞት የተለየ እንደሆነ የሪፐብሊኩ ሰንደቅ ዓላማ በሚታወጀው ብሔራዊ የሐዘን ቀን ዝቅ ብሎ እንዲውለበለብ ይደረጋል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ ከተመለከቱት ሰዎች ውጪ ብሔራዊ የሀዘን ቀንና ሰንደቅ ዓላማው ዝቅ ብሎ የሚውለበለብባቸው ሁኔታዎች በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በውሳኔ የሚያልፍ ይሆናል።

3. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ድንጋጌ ቢኖርም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በስራ ላይ በማይሆንበት ጊዜ ብሔራዊ የሃዘን ቀንና ሰንደቅ ዓላማው ዝቅ ብሎ የሚውለበለብባቸው ሁኔታዎች በምክር ቤቱ አፈጉባዔ የሚወሰን ይሆናል፡፡

4. በማንኛውም ጊዜ ቢሆን የብሔራዊ ሀዘን ቀኑ በህዝባዊና ሀይማኖታዊ በዓላት በሚውልበት ጊዜ ሰንደቅ ዓላማው ዝቅ ብሎ አይውለበለብም።

---

[2] በ21/61(2006) አ.863 አንቀጽ 2(2) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አዲስ የገባ ሲሆን የቀድሞዎቹ ንዑስ አንቀፅ (3) እና (4) እንደቅደም ተከተላቸው ተሻጋሽገው ንዑስ አንቀጽ (4) እና (5) ሆነዋል፡፡

5. በዚህ አንቀፅ ድንጋጌ መሠረት በሚፈፀም የቀብር ሥነ-ሥርዓት ቀብሩ ከመፈፀሙ በፊት በአስክሬኑ ሣጥን ላይ ያረፈው ሰንደቅ ዓላማ በተገቢው ሥነ-ሥርዓት ተጣጥፎ መነሳት ያለበት ሲሆን በማንኛውም መልኩ መሬት እንዲነካ መደረግ የለበትም፡፡

## ክፍል አምስት

## የተከለከሉና ቅጣት የሚያስከትሉ ተግባራት

### 23.የተከለከሉ ተግባራት

ከዚህ በታች የተመለከቱትን ተግባራት መፈፀም የተከለከለ ነው፦

1. ሰንደቅ ዓላማውን በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ዓርማውን ሳያካትቱ መጠቀም፤
2. ሰንደቅ ዓላማው ላይ ቃላቶችን መፃፍ፣ ሌሎች ምልክቶች ወይም አርማዎችን ወይም ስእሎችን ለጥፎ መገልገል፤
3. ያረጁ፣ የተበላሹ፣ ቀለማቸው የደበዘዘና የተቀደዱ ሰንደቅ ዓላማዎችን መጠቀም ወይም መገልገል፤
4. ሰንደቅ ዓላማው በወጣበት ሰንደቅ /ምሰሶ/ ላይ ማስታወቂያ መለጠፍ፣ ያለአግባብ ሌሎች ሰንደቅ ዓላማዎችን ወይም አርማዎችን ጨምሮ ማውለብለብ ወይም መገልገል፤
5. ህዝብ በተሰበሰበበት ቦታ ሰንደቅ ዓላማውን በፅሁፍ ወይም በቃላት፣ ወይም በድርጊት ወይም በሌላ በማናቸውም አኳኋን መድፈር ወይም ማዋረድ ወይም ጉዳት እንዲደርስበት ማድረግ፤
6. የሰንደቅ ዓላማውን ቀለማት ቅደም ተከተል እንዲሁም የብሄራዊ አርማውን መጠን ሳይጠብቁ ማዘጋጀትና መገልገል፤
7. የሰንደቅ ዓላማውን በዚህ አዋጅ ከተጠቀሰው የማውረጃ ጊዜ በላይ ማቆየት፤
8. በስብሰባ ወይም በማናቸውም መሰል ክንውኖች ሰንደቅ ዓላማውን የጠረጴዛ ሽፋን አድርጎ መጠቀም፤
9. ሰንደቅ ዓላማን የህንፃ ወይም የሌሎች ቁሳቁሶች መሸፈኛ ማድረግ፤
10. ሰንደቅ ዓላማውን በማንኛውም ንግድ ማስታወቂያነት መጠቀም፤
11. ሰንደቅ ዓላማው በሚሰቀልበትና በሚወርድበት ጊዜ ተገቢውን ክብር አለመስጠት፡፡

### 24.ቅጣት

1. በሌላ ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 23 ከንዑስ አንቀፅ /2/ እስከ /11/ የተመለከቱትን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ እስከ ሶስት ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።
2. በሌላ ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 23 ንዑስ አንቀፅ /1/ የተመለከተውን በመተላለፍ ጥፋት የፈፀመ እንደሆነ እስከ አምስት ሺህ ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም አንድ አመት ከስድስት ወር በሚደርስ ፅኑ እስራት ይቀጣል።
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ /2/ የተመለከተውን ጥፋት የፈፀመው በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል እንደሆነ የገንዘብ ቅጣቱ ከሁለት እጥፍ ያላነስ ይሆናል።

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### 25.<u>ደንብ የማውጣት ስልጣን</u>

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆነ ደንብ ለማውጣት ይችላል፡፡

### 26.<u>መመሪያ ስለማውጣት</u>

በዚህ አዋጅ አንቀፅ 25 መሠረት የሚወጣውን ደንብ ተከትለው የሚከተሉት መስሪያ ቤቶች የአፈፃፀም መመሪያዎች ለማውጣትይችላሉ፦

1. የመከላከያ ሠራዊት አህዶችን በሚመለከት የሀገር መከላከያ ሚኒስትር፤
2. የንግድ መርከቦችንና ጀልባዎችን በሚመለከት የትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር፤
3. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ኤምባሲዎችንና ቆንስላዎችን በሚመለከት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር።

### 27.<u>ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች</u>

የሰንደቅ ዓላማና ዓርማ አዋጅ ቁጥር 16/1988 እና የሰንደቅ ዓላማና ዓርማ /እንደተሻሻለ/ አዋጅ ቁጥር 48/1989 በዚህ አዋጅ ተተክተዋል።

### 28.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ነሐሴ 22 ቀን 2001 ዓ.ም.**
**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**
**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 673/2002

## የኢትዮጵያ ብሄራዊ መዝሙር አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ መዝሙር እንደሚኖር በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀፅ 4 የተደነገገ በመሆኑ፤

የብሔራዊ መዝሙሩም ዝርዝር ጉዳዮች በሕግ እንደሚወሰኑ በሕገ-መንግሥቱ በመደንገጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 4 እና አንቀፅ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር አዋጅ ቁጥር 673/2002" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው እስካልሆነ ድረስ፦

   1. "የውጭ ሀገር ባለሥልጣን" ማለት የአንድ የውጭ ሀገር ፕሬዚዳንት፣ ጠቅላይ ሚኒስትር ወይም ሚኒስትር ማለት ነው፤
   2. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት አንቀፅ 47 የተመለከተው ማንኛውም የፌዴሬሽኑ አባል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤
   3. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
   4. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል።

3. **የብሔራዊ መዝሙሩ ምንነት**

   የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ብሔራዊ መዝሙር /ከዚህ በኋላ "ብሔራዊ መዝሙሩ" እየተባለ የሚጠራ/፦

   1. የህገመንግሥት የበላይነትን፤
   2. የኢትዮጵያ ህዝቦች ረጅም የታሪክ ባለቤትነትን፤
   3. የኢትዮጵያ ህዝቦች በዲሞክራሲያዊ ሥርዓት አብረው ለመኖር ያላቸውን ፅኑ እምነት፤

4. የኢትዮጵያ ህዝቦች የወደፊት የጋራ እድላቸው ብሩህ መሆኑን፤ የሚገልፅ ምልክት ነው።

4. <u>**የብሔራዊ መዝሙሩ ግጥምና የሙዚቃ ኖታ**</u>

1. የብሔራዊ መዝሙሩ ግጥም እንደሚከተ ለው ይሆናል፡-

   የዜግነት ክብር በኢትዮጵያችን ፀንቶ፣
   ታየ ሕዝባዊነት ዳር እስከዳር በርቶ፡፡
      ለሰላም፣ ለፍትህ፣ ለሕዝቦች ነፃነት፣
      በእኩልነት፣ በፍቅር፣ ቆመናል በአንድነት፤
      መሠረተ ፅኑ፣ሰብዕናን ያልሻርን፣
      ሕዝቦች ነን፣ ለሥራ፣ በሥራ የኖርን፡፡
   ድንቅ የባህል መድረክ፣ የአኩሪ ቅርስ ባለቤት፣
   የተፈጥሮ ፀጋ፣ የጀግና ሕዝብ እናት፤
   እንጠብቅሻለን፣ አለብን አደራ፣
   ኢትዮጵያችን ኑሪ፣ እኛም ባንቺ እንኩራ!

2. የብሔራዊ መዝሙሩ  የሙዚቃ ኖታ እንደሚከተለው ይሆናል፡-

ኖታው እዚህ ይገባል

5. <u>**ብሔራዊ መዝሙሩ ኢትዮጵያ ውስጥ ባሉ ቋንቋዎች ስለመተርጎሙ**</u>

1. ማንኛውም ክልል በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረት ብሔራዊ መዝሙሩ እንዲዘመር ያደርጋል።
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ክልሎች በህግ በወሰኑት የሥራ ቋንቋ የብሔራዊ መዝሙሩ የግጥም ይዘትና ዜማ እንደተጠበቀ ሆኖ የብሔራዊ መዝሙሩን ዜማና ግጥም በባለሙያ በማስተርጎም መጠቀም ይችላሉ፤ ይህም በሥራ ላይ የሚውለው በየምክር ቤቶቻቸው በሚያፀድቁት የብሔራዊ መዝሙሩ የተረጋገጠ ትርጉም ይሆናል።

## <u>ክፍልሁለት</u>

## <u>የብሔራዊ መዝሙሩ አጠቃቀም</u>

6. <u>**በምክር ቤቶች የመክፈቻ ስብሰባና በቃለ መሀላ ሥነ-ሥርዓቶች ብሔራዊ መዝሙሩ ስለመዘመሩ**</u>

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌዴሬሽን ምክር ቤት ዓመታዊ የጋራ ስብሰባቸውን የሚከፍቱት በሙዚቃ ባንድ በሚታጀብ የብሔራዊ መዝሙር ይሆናል።
2. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት በመሆን የተመረጠ ሰው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በሚፈፀመው የቃለ መሃላ ሥነ-ሥርዓት ብሔራዊ መዝሙር ይዘመራል።
3. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ሚኒስትር በመሆን የሚመረጠው ሥራውን ከመጀመሩ በፊት በሚፈፀመው የቃለ መሃላ ሥነ-ሥርዓት ብሔራዊ መዝሙር ይዘመራል።

7. <u>በብሔራዊ በዓላት</u>

በሕግ በሚወሰነው መሠረት ብሔራዊ መዝሙሩ በብሔራዊ በዓላት ሥነ-ሥርዓት ላይ ይዘመራል።

8. <u>በትምህርትቤቶች</u>

1. በሰንደቅ ዓላማ አዋጅ ቁጥር 654/2001 አንቀፅ 15 /2/ መሠረት በትምህርት ቤቶች የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ የሚሰቀለው ብሔራዊ መዝሙር በመዘመር ይሆናል።
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት ብሔራዊ መዝሙሩ የሚዘመረው በኦዲዮ የተቀረፀውን የብሔራዊ መዝሙሩን ቅጂ በማሰማት ወይም በተማሪዎች የህብረት ዝማሬ መሆን ይኖርበታል።

9. <u>በቴሌቪዥን እና በሬድዮ ስርጭቶች</u>

1. በመገናኛ ብዙሃንና በመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 መሠረት የብሮድካስት ሥራን የሚሰራና ስርጭቱ ከአንድ ክልል በላይ የሆነ ማንኛውም ድርጅት እለታዊ ስርጭቱን ከመጀመሩ በፊት እና ከእለታዊ ስርጭቱ መዝጊያ በፊት ብሔራዊ መዝሙሩ እንዲተላለፈ ያደርጋል።
2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ /1/ የተመለከተው የብሮድካስት ድርጅት ስርጭት ለሃያ አራት ሰዓታት ያለማቋረጥ የሚተላለፍ ከሆነ ብሔራዊ መዝሙሩ የሚተላለፈው ከሌሊቱ በ6 ሰዓት እና ከንጋቱ በ12 ሰዓት ይሆናል።

10. <u>በስፖርታዊ ክንዋኔዎች</u>

የአለም ዓቀፍ የስፖርት ማህበራት ደንቦች እንደተጠበቁ ሆኖ አንድ የኢትዮጵያ ስፖርት ቡድን ሃገሪቱን በመወከል ከሌላ አቻው የውጭ ሃገር የስፖርት ቡድን

ጋር በኢትዮጵያ ውስጥ በሚያደርገው የስፖርታዊ ውድድር ብሔራዊ መዝሙሩ የሚዘመረው የእንግዳው ሃገር ብሔራዊ መዝሙር ከተዘመረ በኋላ ይሆናል፡፡

11.**<u>የውጭ ሃገር ባለሥልጣናት ወደ ኢትዮጵያ በሚመጡበት ጊዜ</u>**

የውጭ ሃገር ባለሥልጣን ወደ ኢትዮጵያ ሲመጣ በሚደረግለት የ"እንኳን ደህና መጣህ" አቀባበል የተወከለበት ሃገር ብሔራዊ መዝሙር በቅድሚያ የሚዘመር ሲሆን በመቀጠልም የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር ይዘመራል፡፡ ዝርዝሩ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ይወሰናል፡፡

12.**<u>በውጭ ሃገራት ባሉ የኢትዮጵያ ኢምባሲዎች እና የቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች</u>**

በውጭ ሃገራት ያሉ የኢትዮጵያ ኢምባሲዎች ወይም የቆንስላ ጽሕፈት ቤቶች የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙርን እና የሌላ ሃገር ብሔራዊ መዝሙርን ለማዘመር ሲወስኑ በቅድሚያ የኢትዮጵያ ብሔራዊ መዝሙር የሚዘመር ሲሆን በማስከተልም የውጭ ሀገሩ ብሔራዊ መዝሙር ይዘመራል፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የሥነ-ሥርዓት ደንቦችና ክልከላዎች</u>

13.**<u>ብሔራዊ መዝሙር በሚዘመርበት ጊዜ የሚጠበቅ ተግባር</u>**

1. ማንኛውም ሰው ብሔራዊ መዝሙሩ በሚዘመርበት እና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ በሚሰቀልበት ጊዜ ፊቱን ወደ ሰንደቅ ዓላማው በማዞር እና እጆቹን ወደታች በመዘርጋት ቀጥ ብሎ መቆም ይጠበቅበታል፡፡
2. ማንኛውም የፖሊስ ወይም የሃገር መከላከያ ሰራዊት አባል የሆነና መለዮ የለበሰ ሰው ብሔራዊ መዝሙሩ በሚዘመርበትና የኢትዮጵያ ብሔራዊ ሰንደቅ ዓላማ በሚሰቀልበት ጊዜ ፊቱን ወደ ሰንደቅ ዓላማው በማዞር ወታደራዊ ሰላምታ በመስጠት የብሔራዊ መዝሙሩ ዝማሬ እስኪያበቃ ድረስ መቆም ይጠበቅበታል፡፡

14.**<u>ጥፋቶች</u>**

1. በዚህ አዋጅና በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሠረት በትምህርት ሚኒስቴር የሚወጣው መመሪያ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ማንኛውም የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሠረት ብሔራዊ መዝሙሩ እንዳይዘመር ያደረገ እንደሆነ፣ እንደአግባብነቱ የትምህርት ቤቱ የበላይ ሃላፊ ወይም ትምህርት ቤቱ በቀላል እሥራት ወይም እስከ 5,000 ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

2. ማንኛውም ሰው ብሔራዊ መዝሙሩን ለንግድ ማስታወቂያነት የተጠቀመ እንደሆነ በቀላል እሥራት ወይም በገንዘብ ይቀጣል።

## **ክፍል አራት**

## **ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች**

15. **ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን**

1. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ለማውጣት ይችላል።
2. የትምህርት ሚኒስቴር እና የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረት የሚወጡ ደንቦችን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጡ ይችላሉ።

16. **ተፈፃሚነት ስለማይኖራቸው ህጎች**

ይህን አዋጅ የሚቃረን ማንኛውም አዋጅ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

17. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም 6 ቀን 2003 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 3/1983

## ስለሰላማዊ ሰልፍና ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ ሥነ ሥርዓት የወጣ አዋጅ

ሐምሌ 15 ቀን 1983 ዓ.ም. በወጣው የኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር ክፍል አንድ አንቀጽ አንድ የዴሞክራሲ መብቶች ያለአንዳች ገደብ ሙሉ በሙሉ መከበራቸው የታወጀ ስለሆነ፤

ሰላማዊ ሰለፍንና ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባን በማያካሂዱ ግለሰቦችና በሌሎች ግለሰቦች መካከል ሊነሣ የሚችል አምባጓሮን በመቆጣጠርና የሕዝብ ሰላምና ፀጥታ የሚያውክን ሁኔታ በማስወገድ የሰላማዊ ሰልፈኞችና ሕዝባዊ የፖለቲካ ተሰብሳቢዎችን መብቶች ለመጠበቅ፤

በዴሞክራሲያዊ መብቶች በመጠቀም በሚደረግ ሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ ሳቢያ በግለሰቦችና በንብረት ላይ ሊደርስ የሚችል ጉዳትና ጥፋትን ለመቆጣጠር፤ እነዚህንም መብቶች በሚገባ ተግባር ላይ እንዲውሉ የኅብረተሰቡን የዕድገት ደረጃና የኑሮ ሥርዓት በማገናዘብ የተመለከቱት ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሕዝብ እንዲጠቀምባቸው ለማድረግ፤

የእነዚህና የሌሎች ሰብአዊ መብቶች አጠቃቀምን በተመለከተ በቅርቡ ተጠንቶ ሌሎች ዝርዝር ሕጐች እስኪወጡ ድረስ ሕዝቡ በዴሞክራሲያዊ መብቱ ካሁኑ መጠቀም እንዲችል በቻርተሩ አንቀጽ ዘጠኝ (መ) መሠረት የተወካዮች ምክር ቤት የሚከተለውን አውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሰላማዊ ሰልፍና ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ ሥነ ሥርዓት አዋጅ ቁጥር 3/1983 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "ሰላማዊ ሰልፍ" ማለት ብዙ ሕዝብ በአደባባይ፣ በመንገድ ወይም በሌላ ለሰላማዊ ሰልፍ ምቹ በሆነ ሥፍራ፣ የጦር መሣሪያ ሳይዙና የኅብረተሰቡን ሰላም ሳያውኩ ሃሳባቸውን በንግግር፣ በዘፈን፣ መፈክርን በማሰማት፣ ጽሑፍን በማንገብ ... ወዘተ በስርዓትና በይፋ የሚገልፁበት ሂደት ነው፤
   2. "ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ" ማለት ብዙ ሕዝብ በቤት፣ በግቢ፣ በአደባባይ ወይም በሌላ ለስብሰባ ምቹ በሆነ ሥፍራ የጦር መሣሪያ ሳይዙና የኅብረተሰቡን ሰላም ሳያውኩ፣ ካስፈለገ በድምጽ ማጉሊያ መሣሪያም ጭምር እየተጠቀሙ

ፖለቲካዊና ፖለቲካ ነክ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በይፋ ውይይት የሚያካሂዱበት ስብሰባ ነው፡፡

3. <u>ሰላማዊ ሰልፍና ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ ስለማድረግ</u>

   1. በኢትዮጵያ የሽግግር ወቅት ቻርተር አንቀጽ አንድ እንደተረጋገጠው ማንኛውም ግለሰብ ሰላማዊ ሰልፍና ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ የማዘጋጀትና በነዚሁ የመሣተፍ መብት አለው፡፡
   2. ማንኛውም ግለሰብ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 3 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን መብት በሥራ ላይ የሚያውለው የሌሎችን ሕጋዊ መብቶች በማይጋፋበት አኳኋን ይሆናል፡፡

4. <u>የማሳወቅ ግዴታ</u>

   1. ሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ የሚያዘጋጅ ማንኛውም ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት የታሰበው ሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ ከሚካሄድበት ጊዜ ቢያንስ ከ48 ሰዓታት በፊት በጽሑፍ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡
   2. የማሳወቂያው ጽሑፍ ሰላማዊ ሰልፉ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ በከተማ ከሆነ የሚደረገው ለከተማው አስተዳደር ጽ/ቤት፤ ከከተማ ውጭ ከሆነ ለአውራጃው አስተዳደር ጽ/ቤት[3] ይሆናል፡፡

5. <u>የጽሑፉ ይዘት</u>

   1. ሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ የሚያዘጋጅ ማንኛውም ግለሰብ፣ ቡድን ወይም ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ለከተማው ወይም ለአውራጃው አስተዳደር ጽ/ቤት የሚያቀርበው ጽሑፍ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ነጥቦች የያዘ ይሆናል፤

      ሀ/ የሰላማዊ ሰልፉ ወይም የሕዝባዊ ፖለቲካ ስብሰባው ዓላማ፤

      ለ/ ሰላማዊ ሰልፉ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባው የሚደረግበት ቦታ፤ ሰላማዊ ሰልፉ ከቦታ ቦታ የሚዘዋወር ከሆነም የሚተላለፍባቸው መንገዶችና አደባባዮች፤

      ሐ/ ሰላማዊ ሰልፉ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባው የሚደረግበት ቀንና ሰዓት፤

---

[3] በዚህ ንዑስ አንቀፅ እንዲሁም በአንቀፅ 5(1) እና በአንቀፅ 6 “የአውራጃ” ተብሎ የተገለፀው አስተዳደራዊ እርከን የሌለ በመሆኑ ሰላማዊ ሰልፉ የሚካሄድበት አግባብ ያለው የአስተዳደር አካል ይተካዋል፡፡

መ/ ሰላማዊ ሰልፉ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባው የሚወስደው ጊዜ ግምትና የተሳታፊው ሕዝብ ብዛትና ማንነት ግምት፤

ሠ/ ሰላማዊ ሰልፉ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባው በሚደረግበት ጊዜ ሰላምና ፀጥታን ለማስጠበቅ ከመንግሥት የሚፈለገው ዕርዳታ፤ እና

ረ/ የሰላማዊ ሰልፉ ወይም የሕዝባዊ ፖለቲካ ስብሰባ አደራጅ ግለሰብ ወይም ቡድን ሙሉ ስም፣ አድራሻና ፊርማ፤ በድርጅት ስም የሚዘጋጅ ከሆነም የድርጅቱ የአመራር አካል ተወካዮች ሶስት ተጠሪዎች ስም፣ አድራሻና ፊርማ፡፡

6. <u>የከተማው ወይም የአውራጃው አስተዳደር ጽ/ቤት ኃላፊነት</u>

1. የከተማው ወይም የአውራጃው አስተዳደር ጽ/ቤት የሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ ጥያቄ በጽሑፍ ሲቀርብለት ሰላምን ከማስፈን፣ ፀጥታን ከማስጠበቅና የሕዝቡን ዕለታዊ ኑሮ እንዳይሰናከል ከማድረግ አንፃር አስፈላጊውን ዝግጅት ሁሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

2. የከተማው ወይም የአውራጃው አስተዳደር ጽ/ቤት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱትን ሁኔታዎች በማገናዘብ ሰላማዊ ሰልፉ ወይም ህዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባው በሌላ ሥፍራ ቢደረግ ይሻላል የሚል አስተያየት ካለው ምክንያቱን በመግለጽ ይህንኑ ጥያቄው በደረሰው በ12 ሰዓት ውስጥ በጽሑፍ ለአዘጋጁ የማሳወቅ ኃላፊነት አለበት፡፡ ሆኖም የከተማው ወይም የአውራጃው አስተዳደር ጽ/ቤት ሰላማዊ ሰልፉ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባው ምን ጊዜም በየትኛውም ቦታ ሊካሄድ አይችልም ማለት አይችልም፡፡

7. <u>የተከለከሉ ሥፍራዎች</u>

1. ማንኛውም ሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ ከዚህ በታች በተዘረዘሩትት ቦታዎች 100 ሜትር ርቀት ውስጥ ሊደረግ አይችልም፤

ሀ/ በኤምባሲዎችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶችተ የሥራ ቦታና የመኖሪያ ቤት፣

ለ/ በቤተክርስቲያን፣ በመስጊድና በመሳሰሉት የጸሎት ቤቶች እንዲሁም በሆስፒታልና በመካነ መቃብር ዙሪያ፤

ሐ/ በኤሌክትሪክ ማመንጫዎች፣ በግድቦችና በመሳሰሉት አደጋ ሊያስከትሉ በሚችሉ ቦታዎች ዙሪያ እና፤

መ/ ገበያ ቀን ሰላማዊ ሰልፎችን ወይንም የሕዝብ ስብሰባዎችን ለማስተናገድ አስቸጋሪ በሚሆኑ የገበያ ቦታዎች፡፡

2. ማናቸውም ሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ በጦር ኃይሎች፣ በጥበቃና የሕዝብን ሰላምና ደኅንነት በሚቆጣጠር የመንግሥት የሥራ ክፍሎች አካባቢ 500 ሜትር ርቀት ውስጥ ሊደረግ አይችልም፡፡

8. <u>የተከለከሉ ሁኔታዎች</u>

1. ማናቸውም ሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ፤

   ሀ/ የዘር፣ የቀለም፣ የሃይማኖት፣ የጾታና የመሳሰሉትን የእኩልነት መብቶችን በሚጻረር ልዩነቶች በማድረግ ላይ የተመሠረተ ዓላማን፤

   ለ/ በብሔር፣ በብሔረሰብና በሕዝቦች በዘረኝነት ላይ የተመሠረተ የጥላቻ አሉባልታንና ዘረኛ ጥርጣሬን ለማራመድና ለማነሳሳት፤ አይፈቀድለትም፡፡

2. የኢሠፓና የደኅንነት አባላት የተወካዮች ምክር ቤቱ ሌላ ውሳኔ እስካልወሰነ ድረስ በማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዳይሳተፉ ታግደዋል፤ ድርጅቶቹም ፀረ-ዴሞክራሲና ወንጀለኛ ድርጅቶች ስለሆኑ ፈርሰዋል፡፡ [4]

9. <u>ሕጋዊ ተጠያቂነት</u>

የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች የጣሰ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተመለከቱትን ለመፈጸም ሙከራ ያደረገ ወይም የፈጸመ ግለሰብ፣ ቡድን ወይም የድርጅት ተጠሪ ወይም ተጠሪዎች እና በሙከራው ወይም በድርጊቱ ተባባሪ የሆኑ ሁሉ ሊደርስ ይችል ለነበረው ወይም ለደረሰው ጥፋት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናሉ፡፡

10. <u>የፀጥታ አስከባሪዎች ኃላፊነት</u>

የግለሰቦችን መብት ለማስከበር፣ በግለሰቦች ላይ ሊደርስ የሚችል የአካልም ሆነ የንብረት ጉዳትና ጥፋት እንዲሁም በኅብረተሰቡ ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ለመጠበቅ የፀጥታ አስከባሪዎች በማናቸውም ሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሕዝባዊ የፖለቲካ ስብሰባ በመገኘት የሕዝብን መብት ሰላምና ደኅንነት የማስከበር ኃላፊነት አለባቸው፡፡

11. <u>የተሻሩ ሕጎች</u>

ይህንን አዋጅ የሚፃረር ማናቸውም ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያና ውሳኔ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

12. <u>ሕጉ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ጊዜ ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

[4] ይህ ንዑስ አንቀፅ ከህግ መንግስቱ ጋር ስለማይጣጣም ተፈፃነት አይኖረውም፡፡

አዲስ አበባ ነሐሴ 6 ቀን 1983 ዓ.ም
መለስ ዜናዊ
የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ፕሬዚዳንት

# አዋጅ ቁጥር 573/2000

## የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ

በሕገመንግሥቱ መሠረት ዜጎች የመደራጀት መብታቸውን ተጠቅመው በሰላማዊና ህጋዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ በመሳተፍ የፖለቲካ ሥልጣን የሚይዙበትን ሁኔታ በህግ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ዜጎች የፖለቲካ ፓርቲ ሲመሰርቱ እና በአባልነት ሲንቀሳቀሱ ስለሚኖራቸው መብትና ግዴታ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎች ሊከተሏቸው የሚገቡ መሠረታዊ መርሆዎችን በመደንገግ ህጋዊ ሰውነት አግኝተው እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የፖለቲካ ፓርቲዎች በመዋሀድ ወይም ግንባር በመፍጠር ወይም ተቀናጅተው ሊንቀሳቀሱ የሚችሉበትን ሁኔታ መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 /1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጉም**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፤

   1. "ቦርድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፣
   2. "የፖለቲካ ፖርቲ" ወይም "የፖለቲካ ድርጅት" ማለት ከሕብረተሰቡ ውስጥ የተወሰኑ ሰዎችን በማሰባሰብ የራሱን የፖለቲካ እምነትና ዓላማ የሚያንፀባርቅበት ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ ማሕበራዊ ተቋም ነው፣
   3. "ህገ መንግስት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ነው፣
   4. "ንግድና ኢንዳስትሪ ሥራዎች" ማለት ለትርፍ ለሚካሄድ የማምረት፣ አገለግሎት የመስጠት ወይም የማከፋፈል ሥራዎችን ይጨምራል፣

5. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግሥት አንቀፅ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ይጨምራል፣
6. "መደበኛ ነዋሪ" ማለት በ1952 ዓ.ም በወጣው የፍትሐብሔር ህግ እንደተደነገገው በመደበኛ የመኖሪያ ቤት የሚኖር ሰው ነው፣
7. "የፖለቲካ ፓርቲ ሃላፊዎች" ማለት እንደሁኔታው የአንድ ፖለቲካ ፓርቲ የሥራ አስፈጻሚ አባላት፣ ወይም በተመሳሳይ የሥልጣን ደረጃ ላይ ያሉ የፖለቲካ ፓርቲ መሪዎች ናቸው፣
8. "ውህደት" ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ በህግ መሠረት ተመዝግበው የነበሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአንድ ላይ ተዋህደው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ የሚመሰርቱበት ሁኔታ ነው፣
9. "ግንባር" ማለት ሁለት እና ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የተናጠል ህጋዊ ህልውናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ የሆነ ስያሜ፣ የፖለቲካ ፕሮግራምና መተዳደሪያ ደንብ ኖሯቸው ለመንቀሳቀስ ሲወስኑ የሚደራጅ አካል ነው፣
10. "መቀናጀት" ማለት ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለጊዜያዊ አላማ በጋራ ለመሥራት እያንዳንዱ አካል ህጋዊ ህልውናውን እንደጠበቀ ለመቀናጀታቸው ጊዜያዊ የምስክር ወረቀት የሚያገኙበት ሁኔታ ነው፣
11. "መተካት" ማለት አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ነባር ስሙንና ፕሮግራሙን በመቀየር አዲስ ስምና ፕሮግራም በማዘጋጀት በዚሁ ስሙ እና ፕሮግራሙ እንዲታወቅ አስፈላጊውን መረጃ ለቦርዱ በማቅረብ በአዲስ የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመዘገብበትና የሚንቀሳቀስበት ሁኔታ ነው፣
12. "የፖለቲካ ፓርቲ አዲተር" ማለት የሞያ ብቃቱ የተረጋገጠ፣ በማናቸውም መንገድ ከሚሾመው የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ግንኙነት የሌለው በፖለቲካ ፓርቲ የሚሾም ሰው ነው፣
13. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በመላው ኢትዮጵያ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የፖለቲካ ፓርቲ አመሰራረት፣ ምዝገባ እና ሰነዶች

## ምዕራፍ አንድ

## የፖለቲካ ፓርቲ አመሰራረት

4. **የፖለቲካ ፓርቲ ስለመመስረት**

   1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 58 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ፓርቲ የማቋቋም ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብት አለው።
   2. የዚህ አዋጅ አንቀፅ 58 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም እድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ በዚህ አዋጅ መሠረት የሃገር አቀፍ ወይም የክልል የፖለቲካ ፓርቲ አባል የመሆን መብት አለው፡፡

5. **አገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲ ስለመመስረት**

   1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በሀገር አቀፍ የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመሰረተው፤
      ሀ/ 1500 መስራች አባላት ሲኖሩት፣
      ለ/ ከነዚህ መስራች አባላት ውስጥ ከአርባ በመቶ /40 በመቶ/ የማይበልጡት የአንድ ክልል መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ፣
      ሐ/ የተቀሩት መስራች አባላት ነዋሪነታቸው በኢትዮጵያ ከሚገኙት ክልሎች ውስጥ ቢያንስ በአራቱ ክልሎች መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑና፣
      መ/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ /ሐ/መሠረት ከየክልሉ ለአገር አቀፍ ፓርቲ መስራችነት ከሚመዘገቡት አባላት በአያንዳንዱ ክልል አስራ አምስት በመቶ /15 በመቶ/

      ሲሆን ነው፡፡
   2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተጠቀሱት መስራች አባላት ድምፅ ለመስጠት መብት ያላቸው ሆነው፣ የፖለቲካ ፓርቲው አባል ለመሆናቸው ስምምነታቸውን በፊርማቸው የገለፁ መሆን አለባቸው።
   3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት መስራች አባላት የፈረሙበት ሰነድ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ሰነድ ነው፡፡

6. **የክልል የፖለቲካ ፓርቲ ስለመመስረት**

   1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በክልል የፖለቲካ ፓርቲነት የሚመሰረተው፤
      ሀ/ 750 መስራች አባላት ሲኖሩት፣
      ለ/ ከነዚህ መስራች አባላት ውስጥ ከስልሳ በመቶ /60 በመቶ/ በላይ የሆኑት የክልሉ መደበኛ ነዋሪዎች ሲሆኑ ነው፡፡
   2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተጠቀሱት መስራች አባላት ድምፅ ለመስጠት መብት ያላቸውና የፖለቲካ ፓርቲው አባል ለመሆናቸው ስምምነታቸውን በፊርማቸው የገለፁ መሆን አለባቸው።

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት መስራች አባላት የፈረሙበት ሰነድ ለሕዝብ ይፋ የሚሆን ሰነድ ነው።

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለ ፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ

7. ስለምዝገባ

   1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በኢትዮጵያ ውስጥ ለመንቀሳቀስ የሚችለው በዚህ አዋጅ መሠረት በቦርዱ ተመዝግቦ የህጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ሲያገኝ ብቻ ነው፡፡
   2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በስሙ ውል መዋዋል፣ መክሰስና መከሰስ፣ የንብረት ባለቤት ወይም ባለይዞታ መሆን፣ መሸጥ፣ መለወጥ በሌላ በማናቸውም ሁኔታ ንብረት ማስተላለፍ ወይም አላማውን ተከትሎ ማናቸውም ሕጋዊ ተግባር ማከናወን ይችላል። እንዲሁም ግዴታውን የመወጣት ኃላፊነት አለበት።

8. ለምዝገባ ስለሚቀርብ ማመልከቻ

   1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የምዝገባ ማመልከቻ በፖለቲካ ፓርቲው መሪ ተፈርሞ ለቦርዱ መቅረብ አለበት።
   2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ ከሚከተሉት ሰነዶች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፤

      ሀ/ በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 13 መሠረት የፖለቲካ ፓርቲ መመስረቻ ፅሁፍ፣

      ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 15 መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው ፕሮግራም፣

      ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 14 መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው የመተዳደሪያ ደንብ፣

      መ/ የፖለቲካ ፓርቲ ኃላፊዎች ስምና አድራሻ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በኃላፊነት ለመስራት የተስማሙ ለመሆናቸው የሚገልፅ በፊርማቸው የተረጋገጠ ሰነድ፣

      ሠ/ መስራቾች የፈረሙበትና ለሕዝብ ይፋ የሆነ ሰነድ፣

      ረ/ የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች በፓርቲው ጠቅላላ ጉባዔ የተመረጡ መሆኑን የሚገልፅ ሰነድ፣

      ሰ/ የፖለቲካ ፓርቲውን ኦዲተር ስም፣ አድራሻ እና በኦዲተርነት ለማገልገል የተስማማበት በፊርማው የተረጋገጠ ሰነድ።

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /2/ የተዘረዘሩት ሰነዶች ከእያንዳንዱ አምስት ቅጂ ከምዝገባ ማመልከቻው ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
4. የምዝገባ ጥያቄ ማመልከቻ ያቀረበ የፖለቲካ ፓርቲ፦
   ሀ/ የምዝገባ የአገልግሎት ክፍያ እና
   ለ/ በየጊዜው ለሚደረጉ የመሠረታዊ ሰነዶች ማሻሻያ ክፍያ
   ይከፍላል።
5. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /4/ /ሀ/ የተደነገገውን ክፍያ የከፈለበት ሰነድ ከምዝገባ መጠየቂያ ማመልከቻው ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል።
6. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /4/ የተደነገገው የክፍያ መጠን በቦርዱ ይወሰናል፡፡
7. በዚህ አንቀፅ መሠረት የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች ለሕዝብ ግልፅ መሆን አለባቸው።

9. <u>የቦርዱ ኃላፊነት</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲዎችን የመመዝገብ ሥልጣን የቦርዱ ነው፡፡
2. በፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ ማመልከቻ ባቀረበ አካል ላይ ተቃውሞ ያለው ማንኛውም ሰው ተቃውሞ ማቅረብ እንዲችል ቦርዱ የምዝገባ ማመልከቻ መቅረቡን በተለያየ ማስታወቂያ ለሕዝብ ይገልፃል።
3. በንዑስ አንቀፅ /2/ መሠረት ተቃውሞ ያለው ሰው ማስታወቂያው በወጣ 14 ቀን ውስጥ ተቃውሞውን ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርበታል። ቦርዱ በዚህ ጊዜ ውስጥ ለአመልካቹ ፈቃድ አይሰጥም።
4. ቦርዱ ለምዝገባ አስፈላጊ የሆኑ ተያያዥ መረጃዎች እንዲቀርብለት እንዲሁም በዚህ አዋጅ መሠረት በሚደረግ እንቅስቃሴ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መረጃ ወይም ማብራሪያ ሊጠይቅ ይችላል፡፡
5. ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 8 መሠረት የሚቀርብለትን ማመልከቻና አባሪ ሰነዶች ተቀብሎ በመመርመር ሰነዶቹ በዚህ አዋጅ በተመለከተው መሠረት የተሟሉ እና ትክክለኛ መሆናቸውን፣ ፓርቲው ህገ መንግሥቱንና ይህን አዋጅ የሚያከብርና የሚያስከብር መሆኑን በማረጋገጥ እንዲሁም የፖለቲካ ፖርቲውን ዋና ጽሕፈት ቤት በመጎብኘት የምዝገባ ማመልከቻውን በተቀበለ በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ የምዝገባውን ፎርማሊቲ አጠናቅቆ የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለአመልካቹ ይሰጠዋል።

6. ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /5/ መሠረት የተመዘገበን የፖለቲካ ፓርቲ አግባብ ሆኖ ባገኘው የብዙኃን መገናኛ ለሕዝብ ያሳውቃል።

7. ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /5/ በተቀመጠው ጊዜ ውስጥ ምላሽ ካልሰጠ የምዝገባ ማመልከቻ ያቀረበውን የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ ህግ መሠረት እንደመዘገበው ይቆጠራል።

8. ቦርዱ የምዝገባ ማመልከቻውን ያልተቀበለው የፖለቲካ ፓርቲው ማሟላት ያለበትን ሳያሟላ በመቅረቱ ከሆነ ይህንኑ በ30 ቀናት እንዲያሟላ በጽሁፍ ለአመልካቹ ያሳውቀዋል።

9. ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲው ያቀረበውን የምዝገባ ማመልከቻ ውድቅ ያደረገው እንደሆነ ይህንኑ ምክንያት ለአመልካቹ በፅሁፍ ያሳውቃል።

10. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /9/ መሠረት ቦርዱ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አካል ጉዳዩ በፅሁፍ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ14 ቀን ውስጥ አቤቱታውን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። አቤቱታ ያቀረበው አካል ለዚህ ጉዳይ አፈፃፀም ሰውነት እንዳለው ተቆጥሮ በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ተመርጦ በምዝገባ ማመልከቻው ላይ ፈርሞ ያቀረበው የፓርቲው መሪ የፓርቲው ህጋዊ ወኪል እንደሆነ ይቆጠራል።

11. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት በፖለቲካ ፓርቲ የቀረበለትን የሰነድ ማሻሻያ መርምሮ መቀበል አለመቀበሉን በ30 ቀናት ውስጥ ለፓርቲው ያሳውቃል።

12. ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /11/ መሠረት የማሻሻያ ሰነዱን መርምሮ ከተቀበለው ይህንኑ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

13. ቦርዱ የማሻሻያ ሰነዱን ካልተቀበለው አመልካቹ የፖለቲካ ፓርቲ አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲያደርግ ትዕዛዝ ይሰጣል፣ እንደሁኔታው በዚህ ህግ መሠረት እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

14. ቦርዱ የፖለቲካ ፓርቲ እንቅስቃሴን ይከታተላል ተገቢውን መረጃ ይይዛል።

15. ቦርዱ በዚህ አዋጅ በክፍል አምስት ድንጋጌ መሠረት የፖለቲካ ፓርቲን የገቢ ምንጭ የወጪ ዝርዝር እና ንብረት ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ህገ ወጥ ድርጊት ተፈጽሞ ሲያገኘውም አስፈላጊውን ህጋዊ እርምጃ ይወስዳል።

16. ቦርዱ፡-

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 50 መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የተደረገ ድጋፍና የድጋፍ አጠቃቀም ዝርዝር እና

ለ/ ስለፖለቲካ ፓርቲ አጠቃላይ እንቅስቃሴ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ወቅታዊ እና ዓመታዊ ሪፖርት ያቀርባል።

17. ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 47 የተደነገገው የኦዲት ሪፖርት እንደደረሰው ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እንዲመረመር ሊያዝ ይችላል፡፡

## 10. <u>መመዝገብ ስለማይችል የፖለቲካ ፓርቲ</u>

ከዚህ በታች የተጠቀሱትን ተግባራት የሚያራምድ ወይም አላማው ያደረገ ማንኛውም ቡድን ወይም አካል በፖለቲካ ፓርቲነት ሊመዘገብ አይችልም፤

1. የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ህገ መንግሥትን በመጣስ በዘር፣ በሃይማኖት እና በመሳሰሉት ልዩነቶች ላይ የተመሠረተ ጥላቻና ጠላትነት በብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና በሕዝቦች መካከል በማስፋፋት ጦርነትና ግጭት መፍጠርን ዓላማ ያደረገ፣
2. የፖለቲካ ዓላማውን በትጥቅ ለማራመድ የተደራጀ፣
3. መንግሥትን በኃይል ጥሎ ሥልጣን ለመያዝ ዓላማ አድርጎ የያዘ፣
4. የውጭ ሀገር ዜጎች አባል የሆኑበት የፖለቲካ ድርጅት፣
5. የህገወጥ አላማ ለማካሄድ የተቋቋመ የፖለቲካ ድርጅት፣ እና
6. ህገ መንግሥታዊ ስርዓቱን በህገወጥ መንገድ ለማፍረስ የተመሠረተ።

## 11. <u>በፖለቲካ ፓርቲነት ለመመዝገብ ስለማይችል ድርጅት ወይም ማህበር</u>

የሚከተሉት ድርጅቶች ወይም ማህበራት በዚህ አዋጅ መሠረት በፖለቲካ ፓርቲነት ሊመዘገቡ አይችሉም፣

1. በንግድ ሕግ ወይም በፍትሐብሔር ሕግ ወይም አግባብ ባላቸው ሌሎች ሕጎች መሠረት፣ የንግድና ኢንዳስትሪ ስራዎችን ለማከናወን የተቋቋሙ ማሕበሮች ወይም ድርጅቶች፣
2. ዓላማቸው ትርፍ ለማግኘት ያልሆነ ወይም ለበጎ አድራጎት ተግባር የተቋቋሙ ማሕበራት ወይም ድርጅቶች፣
3. የብዙሃን የሠራተኛ እና የሙያ ማሕበራት፣
4. የመረዳጃ ማሕበራት፣
5. የሃይማኖት ድርጅቶች፣
6. ዕድርና ዕቁብን የመሳሰሉ ማሕበራዊ ተቋሞች፣

## ምዕራፍ ሶስት

## ስለ ፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች

12.**የፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች**

1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የሚከተሉት ዋና ዋና ሰነዶች ይኖሩታል፤

   ሀ/ የመመስረቻ ፅሁፍ፣

   ለ/ የፖለቲካ ፕሮግራም፣

   ሐ/ የመተዳደሪያ ደንብ፣

   መ/ የሃብትና ንብረት የገቢና የወጪ ሰነዶች፣

2. ከላይ የተጠቀሱ ሰነዶችን ለማሻሻል የፈለገ የፖለቲካ ፓርቲ አስቀድሞ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

13. **ስለፖለቲካ ፓርቲ መመስረቻ ፅሁፍ**

1. የፖለቲካ ፓርቲ መመስረት የሚፈልጉ ግለሰቦች መስራች ሆነው ለማደራጀት የፈለጉትን የፖለቲካ ፓርቲ ማቋቋማቸውን የሚገልጹበት የመመስረቻ ጽሁፍ ይኖራቸዋል።

2. የመመስረቻ ጽሑፍ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ ይሆናል፤

   ሀ/ የፓርቲውን መጠሪያ ሙሉ ስም እና አህፅሮት ስም፣

   ለ/ የፓርቲውን ዓርማ፣

   ሐ/ የፓርቲውን ዓላማ፣

   መ/ የፓርቲውን የገቢ ምንጭ፣

   ሠ/ ፓርቲው የተመሰረተበትን ቀን እና ዓመተ ምህረት

   ረ/ የፓርቲውን ዋና መሥሪያ ቤት እና ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች አድራሻ፣

   ሰ/ የፕሮግራሙን እና የመተዳደሪያ ደንቡን አወጣጥ ስርዓት፣

3. የፓርቲው መመስረቻ ጽሑፍ በመስራች አባላቱ የተፈረመ መሆን አለበት።

14.**ስለፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም**

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ዓላማው አድርጎ የያዘውን የፖለቲካ እምነት የሚቀርጽበት የፖለቲካ ፕሮግራም ይኖረዋል።

2. የፖለቲካ ፓርቲ ፕሮግራም፤

   ሀ/ ፓርቲው የተቋቋመበትን ዓላማ እና

   ለ/ ፓርቲው ዓላማውን ከግብ ለማድረስ የሚንቀሳቀስበትን ስልት የሚገልጽ የተግባር መመሪያ ነው።

15.<u>ስለፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የመተዳደሪያ ደንብ ይኖረዋል። የመተዳደሪያ ደንቡም፤

   ሀ/ አባላቱን የሚቀበልበትን ሁኔታ፣

   ለ/ የአባላቱን መብትና ግዴታ፣

   ሐ/ የፖለቲካ ፓርቲውን ልዩ ልዩ አካላት እና የስራ ኃላፊነታቸውን፣

   መ/ አባላቱ በፓርቲው ሥራ ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎ፣

   ሠ/ የፓርቲውን የስብሰባ እና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት፣

   ረ/ በአባላቱ ላይ ስለሚወሰድ የሥነ ሥርዓት እና የሥነምግባር እርምጃ፣

   ሰ/ የፖለቲካ ፓርቲው የጉባኤ ስብሰባ የሚካሄድበትን ጊዜና ሁኔታ፣

   ሸ/ የፖለቲካ ፓርቲው የሚፈርስበትን ሁኔታ

   ቀ/ ማንኛውም አባል እኩል ድምጽ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ሁኔታን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

2. የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የፖለቲካ ፓርቲው አባል በዜግነቱ የተረጋገጠለትን መብት የሚቀንስ ወይም የተጣለበትን ግዴታ የሚሽር ሊሆን አይችልም።

3. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የዚህን አዋጅ አንቀፅ 16 እና ከአንቀፅ 27 እስከ አንቀፅ 31 የተደነገጉትን ያገናዘበ መሆን አለበት፣

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>የፖለቲካ ፓርቲና የአባላት መብት እና ግዴታ</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>የፖለቲካ ፓርቲ መብት</u>

16.<u>የፖለቲካ ፓርቲ በራሱ ጉዳይ ላይ ስላለው ነፃነት</u>

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፦

1. የፖለቲካ ፕሮግራሙንና የመተዳደሪያ ደንቡን የሚያፀድቅበትንና የሚያሻሽልበትን እንዲሁም ስብሰባ የሚያካሂድበትን ሥነ ሥርዓት በመተዳደሪያ ደንቡ ይወስናል።

2. በመተዳደሪያ ደንቡ በሚወሰነው መሠረት የፖለቲካ ሥራውን የሚመሩ፣ ውሳኔ የሚሰጡ እና የሚያስፈጽሙ የአመራር አካላት ይኖሩታል።

## 17.ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ስለማቋቋም

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የፖለቲካ ሥራውን ለማካሄድ በሀገሪቱ ውስጥ በየትኛውም ቦታ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ሊያቋቁም ይችላል።

## 18.ከገቢ ግብር ነፃ ስለመሆን

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከአባላቱና ከደጋፊዎቹ በሚገኘው ገቢ ላይ ምንም አይነት የገቢ ግብር አይከፍልም።
2. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ቀጥሮ ከሚያሰራቸው ሠራተኞች ደመወዝ ላይ በሕግ በተወሰነው መሠረት የገቢ ግብር ሰብስቦ ለመንግሥት ገቢ ከማድረግ ነፃ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የፖለቲካ ፓርቲ ግዴታ

## 19.ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ

1. ማንኛውም በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ፤
   ሀ/ ቦርዱ ሲጠይቅ በህጉ መሠረት የሚፈለገው የአባላት ቁጥር ያሟላ መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ የማቅረብ፣
   ለ/ ፓርቲዎች ግንባር ለመፍጠር ወይም ለመዋሃድ ወይም ለመቀናጀት ሲፈልጉ ቦርዱ በስብሰባቸው ላይ እንዲገኝ ቢያንስ ከ30 ቀናት በፊት የማሳወቅ፣
   ሐ/ በየዓመቱ ወይም ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ፓርቲው በኦዲተር የተረጋገጠ የሃብትና እዳ ሰነድ በፓርቲው መሪ ፊርማ ለቦርዱ የፅሁፍ ሪፖርት የማቅረብ፣
   መ/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ /ሐ/ የተጠቀሰው ሪፖርት የፖለቲካ ፓርቲውን የገቢ ወይም የሃብቱን ምንጭ የማካተት ግዴታ አለበት፡፡
2. ቦርዱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ /1/ የተደነገገውን ግዴታ ላላሟላ የፖለቲካ ፓርቲ የአንድ ወር ጊዜ ማስጠንቀቂያ ከሰጠ በኋላ በአንቀፅ 39 መሠረት አስፈላጊ እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡
3. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ፓርቲው መሪ በዚህ አንቀፅ መሠረት ለቦርዱ በፅሁፍ ያሳወቀው ሃብትና እዳ ሃሰት ሆኖ ከተገኘ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 39 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ አግባብ ባለው የወንጀል ህግ ይጠየቃል።

4. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀፅ /4/ የተደነገገውን መረጃ ወይም ማብራሪያ ሳይሰጥ የቀረ እንደሆነ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 39 መሠረት ተጠያቂ ይሆናል።
5. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 17 መሠረት ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤት ያቋቋመ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቱን አድራሻ እና የመሥሪያ ቤቱን ሃላፊዎች ወይም ተወካዮች ለቦርዱ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

20.<u>መረጃ የመስጠት ግዴታ</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ የተደነገጉ መረጃዎችን በቦርዱ ሲጠየቅ በሰነድ የተረጋገጠ የጽሁፍ መረጃ የማቅረብ ግዴታ አለበት።
2. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት የተጠየቀውን መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆነ ወይም የሰጠው መረጃ ሃሰት መሆኑን እያወቀ የሰጠ ከሆነ ቦርዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 39 /1/ መ የተደነገገውን እርምጃ ከመውሰዱ በተጨማሪ አግባብ ባለው ህግ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

21.<u>የአመራር አባላትን ስለማሳወቅ</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አዲስ የአመራር አባላትን የመረጠ እንደሆነ ወዲያውኑ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በተለያየ ምክንያት የአመራር አባላቱ የተጓደሉ ከሆነና ቁጥሩም ከ50በመቶ+1 በታች ከሆነ በ30 ቀናት ውስጥ ማሟላት አለበት። ይህንንም ወዲያውኑ ለቦርዱ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።[5]

22.<u>ስለፖለቲካ ፓርቲ ሰነዶች አጠባበቅ</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ ክፍል አምስት ምዕራፍ ሁለት በተመለከቱት ጉዳዮች ማለትም እንደ ሂሳብ መዝገብ፣ የስጦታ ሰርተፊኬት፣ የባለንብረትነት መረጃ ሰነዶች እና የመሳሰሉትን በሚገባ የመጠበቅ ግዴታ አለበት።
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ የተደነገገው ቢኖርም በቦታው መጣበብና በሠራተኛ እጥረት ምክንያት ከ10 ዓመታት ዕድሜ በላይ ያላቸው የሂሳብ ሰነዶች ማስወገድ ይችላል።
3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የፓርቲውን ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ ጠብቆ መያዝ አለበት፡፡

[5] አማርኛው ፶፩+፩ ተብሎ የተገለፀው 50%+1 ለማለት ስለሆነ ከእንግሊዘኛው ጋር ተስተካክሎ መነበብ ይኖርበታል፡፡

## 23.ስለፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በሚመለከተው ህጋዊ አካል የተረጋገጠ የሞያ ብቃት ያለው የውጭ ኦዲተር ይሾማል።
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ የተገለፀው የፖለቲካ ፓርቲው ኦዲተር ሹመት በፓርቲው ህገ ደንብ መሠረት የሚፈፀም ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ መሠረት የተሾመ ኦዲተር ሹመቱን መቀበሉን በፊርማው ማረጋገጥ አለበት፡፡
4. በተለያየ ምክንያት ኦዲተሩ ሥራውን ሲለቅ እና አዲስ ኦዲተር ሲተካ የፖለቲካ ፓርቲው መሪ አዲስ የተሾመውን ኦዲተር በ30 ቀናት ውስጥ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት።

## 24.የፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር መብት

በፖለቲካ ፓርቲ የተሾመ ኦዲተር ማንኛውንም ከፖለቲካ ፓርቲ ሀብትና ንብረት ጋር የተያያዘ ሰነድ በማንኛውም ጊዜ የማግኘት እና የመመርመር መብት አለው፡፡

## 25.የፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር ሆኖ ሊሾም ስለማይችል ሰው

ማንኛውም ሰው የፓርቲው ጠበቃ፣ ተቀጣሪ፣ የቦርድ አባል በመሆን አገልግሎት ወይም እያገለገለ ከሆነ ወይም በማንኛውም መልኩ ከሿሚው የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ግንኙነት ያለው ከሆነ የፖለቲካ ፓርቲው ኦዲተር ሆኖ ሊሾም አይችልም።

## 26.በፖለቲካ ፓርቲ የተሾመ ኦዲተር አሰራር

1. በፖለቲካ ፓርቲ የተሾመ ኦዲተርም ሆነ እርሱ ቀጥሮ ያሰማራቸው ባለሞያዎች ስራቸውን በቅንነት፣ በታማኝነትና በገለልተኝነት ማከናወን አለባቸው።
2. በፖለቲካ ፓርቲ የተሾመ ኦዲተር የኦዲት ሪፖርት በጽሁፍ ሆኖ ለፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊዎች መሰጠት አለበት፡፡
3. የፖለቲካ ፓርቲው ከሚያቀርበው የሂሳብ ሪፖርት ጋር የኦዲተሩ የሞያ ብቃት ሰርተፊኬት ተያይዞ መቅረብ አለበት።

## 27.ስለፖለቲካ ፓርቲ ስያሜና አርማ

1. የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ስያሜ ከተመሳሳይ የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የንግድና ኢንዳስትሪ ሥራዎች ድርጅት ወይም ሌላ ማሕበራዊ ተቋም ወይም ከግለሰብ ስም ጋር የማይመሳሰል ወይም የማያደናግር የፓርቲው ብቸኛ መጠሪያ መሆን አለበት፡፡
2. የፓርቲው ዓርማ እና ሰንደቅ ዓላማ፤

ሀ/ ከሌሎች ፓርቲዎች ዓርማና ሰንደቅ ዓላማ ጋር የማይመሳሰል፣

ለ/ በብሔር፣ ብሔረሰብ፣ በዘር፣ በሃይማኖት መካከል ጥላቻና ግጭትን የማይፈጥር፣

ሐ/ የጦረኝነትን ወይም ሌላ ሕገወጥ ድርጊትን መልዕክት የማያስተላልፍ፣

መ/ ከኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ወይም ዓርማ ወይም ከልዩ ልዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ዓርማና ሰንደቅ ዓላማ ወይም ከሃይማኖት ድርጅቶች ምልክቶች ጋር የማይመሳሰል፣

ሠ/ የሕዝብን ሞራል፣ ሥነ ምግባር እና የመሳሰሉትን የማይነካ መሆን አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መብትና ግዴታ

28. **በፖለቲካ ፓርቲ የመሳተፍ መብት**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ መሠረት በፓርቲው ስብሰባዎች ላይ የመሳተፍ፣ ሐሳቡንና አስተያየቱን በነፃ የመግለፅ፣ ድምፅ የመስጠት እና መምረጥ ወይም የመመረጥ መብት አለው።

29. **ስለአባልነት መዋጮ**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ ወይም የፖለቲካ ፓርቲው በሚወስነው መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲው በየጊዜው የአባልነት መዋጮ ሊከፍል ይችላል፡፡

30. **ከአባልነት ስለመወገድ**

1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ አባል የፖለቲካ ፓርቲው መተዳደሪያ ደንብ በሚወስነው መሠረት ከአባልነት ሊወገድ ይችላል፡፡
2. ከፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ ውጪ ከፓርቲ አባልነት የተወገደ አባል በውሳኔው ላይ ቅሬታ ሲኖረው መወገዱ በተገለጸበት በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡፡

31. **ስለአባልነት**

1. የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባላት መስራቾቹና ከምስረታ በኋላ የፓርቲው አባላት የሆኑትን ያካተተ ነው።
2. የፖለቲካ ፓርቲ አባልነት በውርስም ሆነ በሌላ በማናቸውም መንገድ ለሌላ ተላልፎ የማይሰጥ በአባሉ ላይ ተወስኖ የሚቀር ነው።

3. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በማንኛውም ጊዜ አባልነቱን ሊተው ይችላል።

4. የፖለቲካ ፓርቲ መተዳደሪያ ደንብ የዚህን ምዕራፍ ድንጋጌዎች መቃረን የለበትም።

## ክፍል አራት

## ስለፖለቲካ ፓርቲዎች መዋሀድ፣ ግንባር መፍጠር፣ መቀናጀት፣ መተካት እና መሰረዝ

### ምዕራፍ አንድ

### ስለፖለቲካ ፓርቲዎች መዋሀድ፣ ግንባር መፍጠር መቀናጀት እና መተካት

**32.ስለፖለቲካ ፓርቲ ውህደት**

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ተዋህደው አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለመመስረት ይችላሉ፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለመዋሃድ የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥያቄያቸውን የጠቅላላ ምርጫ ወይም የአካባቢ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ከመውጣቱ ከ30 ቀናት በፊት በፅሁፍ ለቦርዱ ያቀርባሉ፣ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረትም ምዝገባው በቦርዱ ይፈፀማል፡፡
3. ለውህደት የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

   ሀ/ እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በፓርቲው ጉባኤ ውህደቱን የተቀበለ ስለመሆኑ የሚገልፅ ውሳኔ እና

   ለ/ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ ሲዋሃዱ የሚኖረውን አዲስ ስምና በዚህ አዋጅ አንቀፅ 8 የተዘረዘሩ ሰነዶችን፡፡
4. ቦርዱ በዚህ ህግ መሰረት የውህደት ጥያቄውን የተቀበለው ከሆ፤

   ሀ/ ለእያንዳንዱ ለተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች ተሰጥቶ የነበረውን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰርዛል፣ አዲሱ ፓርቲም በዚህ ህግ መሠረት ይመዘገባል፤

   ለ/ ቦርዱ የእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ንብረት፣ ገንዘብና አስፈላጊ ሰነዶች በውህደት ወደ ተመሰረተው የፖለቲካ ፓርቲ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ እንዲተላለፍ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡
5. በውህደት የሚመሠረት የፖለቲካ ፓርቲ እንደሁኔታው የዚህን አዋጅ አንቀጽ 5 ወይም አንቀጽ 6 መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

6. ማንኛውም ከዚህ በፊት የወንጀል ክስ ያለበት የፖለቲካ ፓርቲ ክሱ ሳይዘጋ ሊዋሀድ አይችልም።

33.<u>የፖለቲካ ፓርቲ መዋሀድ የሚያስከትለው ውጤት</u>

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 32/4/ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የውህደት ውጤት የሆነው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ፤

   ሀ/ የተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች ወራሽ ይሆናል፣

   ለ/ የተዋሃዱት የፖለቲካ ፓርቲዎች መብትና ግዴታ ይተላለፍለታል፣

   ሐ/ የተዋሃዱትን የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለፈ የሂሳብ እንቅስቃሴ ሪፖርት በቦርዱ ሲጠየቅ ያቀርባል፣

   መ/ ከዚህ በፊት እያንዳንዱ የተዋሃዱ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለባቸውን ፍርድ ወይም መብት ወይም በፍርድ ቤት በሂደት ያለን የፍተሃብሔር ወይም የአስተዳደራዊ አካል ክርክር ተተክቶ ያስፈጽማል፣ ይፈጽማል።

2. የውህደቱ ውጤት ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገበው አዲስ የፖለቲካ ፓርቲ በተመዘገበ በ6 ወር ጊዜ ውስጥ ውህደቱ ያስገኘውን ሀብት፣ ንብረትና እዳ የሚያሳይ የሂሳብ ሪፖርት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 54 እና 56 መሠረት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

34.<u>ግንባር ስለመፍጠር</u>

1. የራሳቸው ፕሮግራም፣ መተዳደሪያ ደንብ እና አባላት ያላቸው ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ግንባር መፍጠር ይችላሉ፡፡

2. ግንባር ለመፍጠር የሚቀርብ ማመልከቻ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፤

   ሀ/ እያንዳንዱ ፓርቲ የግንባሩን ምስረታ የተቀበለ መሆኑን የሚገልፅ የጉባኤ ውሳኔ፣ እና

   ለ/ ግንባሩ የሚኖረው ስም እና በዚህ አዋጅ አንቀፅ 8 የተዘረዘሩ ሰነዶችን።

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት ግንባር ለመፍጠር የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጥያቄያቸውን ለቦርዱ በፅሁፍ ያቀርባሉ፣ በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሠረትም ምዝገባው በቦርዱ ይፈፀማል።

4. ቦርዱ ህግ መሠረት የግንባር ምሥረታውን ጥያቄ የተቀበለው ከሆነ፤

   1. የግንባሩ አባል ድርጅቶች የምዝገባ የምስክር ወረቀት ሳይሰረዝ ለግንባሩ ሌላ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፣

   2. የእያንዳንዱ የግንባሩ አባል ድርጅቶች የራሳቸው ሀብትና ንብረት እንደተጠበቀ ሆኖ ግንባሩ የራሱ ሀብትና ንብረት ይኖረዋል።

5. ግንባር ሆኖ የተመሰረተ የፖለቲካ ፓርቲ እንደሁኔታው የዚህን አዋጅ አንቀጽ 5 ወይም አንቀጽ 6 መስፈርት ማሟላት አለበት፡፡

35. ስለፖለቲካ ፓርቲ መቀናጀት

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የተመዘገቡ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ለተወሰነ ጊዜ እና በተወሰኑ ጉዳዮች ዙሪያ ተቀናጅተው እንደሁኔታው በሃገር አቀፍ ወይም በክልል ደረጃ ሊንቀሳቀሱ ይችላሉ፡፡
2. ተቀናጅተው ለመንቀሳቀስ የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው የፖለቲካ ፓርቲው ከፍተኛ አመራር የተስማማበት መሆኑን የሚገልፅ ሰነድ በማያያዝ የፅሁፍ ማመልከቻ ለቦርዱ ማቅረብ አለባቸው። ቦርዱ ጥያቄውን ከተቀበለው ጊዜያዊ ምስክር ወረቀት ሊሰጥ ይችላል፡፡
3. ለመቀናጀት የፈለጉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ እንቅስቃሴ የስምምነት ነጥቦችን የያዘ ሰነድ ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርባቸዋል።
4. በዚህ አንቀፅ የተደነገገው ቢኖርም እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ ህጋዊ ሰውነቱን እንደያዘ ይቀጥላል።

36. ስለ ፖለቲካ ፓርቲ መተካት

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በፓርቲው ጉባዔ ውሳኔ ስሙንና ፕሮግራሙን ለውጦ በአዲስ የፖለቲካ ፓርቲነት ሊመዘገብ ይችላል።
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሰረት በአዲስ የተቋቋመው ፓርቲ የፈረሰው የፖለቲካ ፓርቲ ሀብት እና ንብረት ይተላለፍለታል፡፡
3. አዲስ የተተካው የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ መሰረት መመዝገብ አለበት፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለፖለቲካ ፓርቲ መሰረዝ ወይም መፍረስ

37. የፖለቲካ ፓርቲን ከምዝገባ ስለመሰረዝ

የፖለቲካ ፓርቲ ከሚከተሉት ሁኔታዎች በአንዱ ከፖለቲካ ፓርቲነት ሊሰረዝ ይችላል፤

1. በፓርቲው ህገደንብ መሠረት በራሱ ፈቃድ ከምዝገባ እንዲሰረዝ ሲጠይቅ፣
2. በህግ መሠረት ቦርዱ ሲወስን ወይም
3. የፖለቲካ ፓርቲው ከምዝገባ እንዲሰረዝ ፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሰጥ።

38. በፖለቲካ ፓርቲው ጥያቄ ከምዝገባ ስለመሰረዝ

1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በህገደንቡ መሠረት ራሱ ከፖለቲካ ፓርቲነት እንዲሰረዝ ቦርዱን በፅሁፍ ሊጠይቅ ይችላል።
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት የቀረበ የመሰረዝ ማመልከቻ በፓርቲው መሪ የተፈረመ መሆን ይገባዋል።
3. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ ከተገለፀው ማመልከቻ ጋር የሚከተለውን አያይዞ ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርበታል፤

   ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲውን የኦዲት፣ የሃብትና ንብረት ሪፖርት፣ እና

   ለ/ ስለፓርቲው መፍረስ በፖለቲካ ፓርቲው ጉባዔ የተወሰነበትን ሰነድ።
4. ከፖለቲካ ፓርቲነት ለመሰረዝ ማመልከቻ ባቀረበ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ላይ ተቃውሞ ወይም ሌላ የመብት ጥያቄ ያለው ማንኛውም ሰው ተቃውሞ ማቅረብ እንዲችል ቦርዱ የመሠረዝ ማመልከቻ መቅረቡን በተለያየ የማስታወቂያ መንገድ ለሕዝብ ይገልፃል።
5. ከላይ ንዑስ አንቀፅ /4/ መሠረት ተቃውሞ ያለው ሰው ማስታወቂያው በወጣ በ14 ቀን ውስጥ ተቃውሞውን ለቦርዱ ማቅረብ ይኖርበታል። ቦርዱ በዚህ ጊዜ ውስጥ የፖለቲካ ፓርቲውን አይሰርዝም።
6. በዚህ አንቀፅ መሰረት ቦርዱ የመሰረዝ ማመልከቻውን ከተቀበለው በ30 ቀናት ውስጥ ለጠያቂው ፓርቲ ስለመሰረዙ በፅሁፍ ያሳውቃል። የፓርቲውን መፍረስም ሕዝብ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡

39.<u>የፖለቲካ ፓርቲን በቦርዱ ውሳኔ ከምዝገባ ስለመሰረዝ</u>

1. ቦርዱ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ የፖለቲካ ፓርቲን ከምዝገባ ሊሰርዝ ይችላል፤

   ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲው የስም፣ የመለያ ምልክት፣ የሰነድ፣ የአመራር፣ የኦዲተር፣ የዋና ጽሕፈት ቤት እና የመሳሰለውን ለውጥ ሲያደርግ በዚህ አዋጅ መሠረት ለቦርዱ ሳያሳውቅ የቀረ እንደሆነ፣

   ለ/ የፖለቲካ ፓርቲው በዚህ አዋጅ መሰረት ለቦርዱ እንዲያቀርብ የተደነገገውን አመታዊ የስራ፣ የሂሳብ፣ ወይም ሌሎች ወቅታዊ ሪፖርቶች ሳያቀርብ የቀረ እንደሆነ፣

   ሐ/ የፖለቲካ ፓርቲው ለሁለት ተከታታይ የምርጫ ዘመን የጠቅላላ ወይም የአካባቢ ምርጫ ውድድርን ሳይሳተፍ የቀረ እንደሆነ፣

   መ/ የፖለቲካ ፓርቲው አጭበርብሮ ወይም አሳሳች መረጃ በማቅረብ የተመዘገበ ከሆነ ወይም በዚህ ህግ መሠረት መረጃ ሲጠየቅ የሃሰት መረጃ

ለቦርዱ የሰጠ እንደሆነ።

2. ቦርዱ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ጥሷል ብሎ ሲያምን ፓርቲው ስህተቱን እንዲያስተካክል የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል። በማስጠንቀቂያው መሠረት ያላስተካከለ እንደሆነ ከምዝገባ ሊሰርዘው ይችላል።
3. በዚህ አንቀፅ መሠረት ቦርዱ ያሳለፈውን ውሳኔ የተቃወመ የፖለቲካ ፓርቲ ውሳኔው በደረሰው በ14 ቀናት ውስጥ ይግባኙን ለፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ሊያቀርብ ይችላል።

40.<u>የፖለቲካ ፓርቲን በፍርድ ቤት ውሳኔ ስለመሰረዝ</u>

1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ህገ-መንግሥቱን፣ ይህንን አዋጅና ሌሎች የሀገሪቱን ህጎች በመጣስ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ በፍርድ ቤት ትዕዛዝ ይፈርሳል።
2. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በፈጸመው ከባድ ወንጀል በፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቀርቦ በሚሰጠው ውሳኔ ከፖለቲካ ፓርቲነት ሊሰረዝ ይችላል።
3. የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የወንጀል ክስ የቀረበበትን የፖለቲካ ፓርቲ ጥፋተኛ ሆኖ ሲያገኘው እንደወንጀሉ ክብደት በወንጀል ህጉ መሠረት በማስጠንቀቂያ ሊያልፈው፣ ለተወሰነ ጊዜ የፖለቲካ ስራውን ከማንቀሳቀስ ሊያግደው ወይም ከፖለቲካ ፓርቲነት ሊሰርዘው ወይምሊቀጣው ይችላል፡፡

41.<u>የፖለቲካ ፓርቲ መሰረዝ ወይም መፍረስ ውጤት</u>

1. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በራሱ ወይም በቦርዱ ውሳኔ እንዲፈርስ ሲወሰን የፓርቲው ንብረት ላለበት ዕዳ መሸፈኛ ይውላል፡፡
2. የፖለቲካ ፓርቲው ዕዳ የሌለበት ከሆነ ወይም ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት እዳውን ሸፍኖ ቀሪው ገንዘብና ንብረት በቦርዱ ትእዛዝ ለሥነ ዜጋና መራጮች ትምህርት እንዲውል ይደረጋል፡፡
3. አንድ የፖለቲካ ፓርቲ በፍርድ ቤት ውሳኔ ሲሰረዝ ወይም ሲፈርስ ፓርቲው ያለው ገንዘብና ንብረት በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ለመንግሥት ገቢ እንዲሆን ይደረጋል፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>ስለፖለቲካ ፓርቲዎች የገቢ ምንጭ እና የንብረት ሁኔታ</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>ከመንግሥት ስለሚሰጥ ድጋፍ</u>

42.<u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

1. መንግሥት በፌዴራልና በክልል ምክር ቤቶች ውክልና ላላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች የዕለት ተዕለት ሥራ ማከናወኛ ድጋፍ ይሰጣል፡፡
2. መንግሥት ለፌዴራል ወይም ለክልል ምክር ቤቶች የምርጫ ተግባር የሚውል ድጋፍ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ይሰጣል።
3. መንግሥት በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው ድጋፍ በገንዘብ፣ በዓይነትና በአገልግሎት ሊሆን ይችላል።
4. ስለመገናኛ ብዙኃን አጠቃቀም በምርጫ ህጉ በተደነገገው መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

43.<u>**በመንግሥት ስለሚሰጥ ድጋፍ ምንጭ**</u>

በመንግሥት የሚሰጠው ድጋፍ፤

1. ከመንግሥት የሚመደብ፣
2. ከውጪም ሆነ ከሀገር ውስጥ ከሚገኝ ድጋፍ ወይም እርዳታ እና
3. ከሌላ ከማንኛውም አካል የሚመነጭ ነው።

44.<u>**መርህ**</u>

1. ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ የመንግሥት ድጋፍ በፍትሃዊነት እና ያለ አድልኦ መፈጸም አለበት፡፡
2. የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የተሰጣቸውን ድጋፍ በአግባቡ እና ለታለመለት ተግባር መዋላቸውን የሚያሳውቁበት የግልጽነትና የተጠያቂነት መርህ መከተል አለባቸው።

45.<u>**የመንግሥት ድጋፍ የሚሰጥበት መስፈርት**</u>

1. ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ ድጋፍ የሚከፋፈለው በፌዴራል ወይም በክልል ምክር ቤቶች ባላቸው መቀመጫ ብዛት መሠረት ይሆናል፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተደነገገው ቢኖርም ለፌዴራል ወይም ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ተግባር የሚሰጥ ድጋፍ፤

   ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያቀረቡትን ዕጩ ብዛት፣

   ለ/ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያቀረቡትን የሴት ዕጩዎችን ብዛት፣ መሠረት በማድረግ የሚከፋፈል ይሆናል።
3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲ የሚሰጥ ድጋፍ፤

   ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲው የመንግሥት ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሚያደርጉትን መስፈርቶች ሲያጓድል ይቋረጣል፣

   ለ/ መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን ጀምሮ የተሰጠውን ድጋፍ መጠቀም

አይችልም፣

ሐ/ መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን ጀምሮ የተሰጠውን ድጋፍ ተመላሽ ያደርጋል።

4. ለፖለቲካ ፖርቲዎች የሚሰጥ ድጋፍ የሚከፋፈልበት ሁኔታና ጊዜ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

46.<u>ለፖለቲካ ፓርቲዎች የዕለት ከዕለት ተግባር ማከናወኛ የሚሰጥ ድጋፍ ለለሚመራበት አሰራር</u>

1. የፖለቲካ ፓርቲ የሚሰጠውን ድጋፍ ለተመደበለት ተግባር ብቻ ማዋል አለበት።
2. የፖለቲካ ፓርቲ የዕለት ተዕለት ተግባር የሚከተሉትን ያካትታል፤

ሀ/ የተለመደውን የፖለቲካ ፓርቲ የዕለት ተዕለት ተግባር፣

ለ/ የሕዝቡን የፖለቲካ ግንዛቤ ማዳበር፣

ሐ/ የፓርቲውን ዓላማ ለሕዝቡ ማስረጽ፣

መ/ ዜጎች በሀገሪቱ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው መቀስቀስ፣

ሠ/ በሕዝቡና በመንግሥት ተቋማት መካከል መልካም ግንኙነት እንዲጠናከር ማድረግ።

3. የፖለቲካ ፓርቲው ለዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ ከመንግሥት የተሰጠውን ድጋፍ በወጪ አርዕስት በመዘርዘር በኦዲተር የተረጋገጠ ወቅታዊ ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡
4. የፖለቲካ ፓርቲው ለዕለት ከዕለት ተግባር ማከናወኛ በመንግሥት ከተሰጠው ድጋፍ ያልተጠቀመበትን የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

47.<u>ለምርጫ ተግባር ከመንግሥት የሚሰጥ ድጋፍ የሚመራበት አሰራር</u>

1. መንግሥት በምርጫ ለሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው ድጋፍ ለፌዴራል ወይም ለክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ተግባር ብቻ መዋል አለበት።
2. ለምርጫ ተግባር የሚወጣ ወጪ ምን ምን እንደሚያካትት ቦርዱ በሚ ያወጣው መመሪያ መሠረት ይወሰናል፡፡
3. የፖለቲካ ፓርቲዎች ፓርቲዎች ለምርጫ ተግባር ከመንግሥት የተሰጣቸውን ድጋፉ በወጪ አርዕስት በመዘርዘር በኦዲተር የተረጋገጠ ወቅታዊ የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ አለባቸው።

4. የፖለቲካ ፓርቲው ተግባር ከመንግሥት ከተሰጠው ድጋፍ ያልተጠቀመበትን የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

48.<u>የፖለቲካ ፓርቲ የሂሳብ አያያዝ</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፤

ሀ/ በመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ በተለየ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ አለበት፣

ለ/ ሂሳቡን በህግ መሠረት ማንቀሳቀስና ከተፈቀደለት ውጪ ወጪ ማድረግ የለበትም፣

ሐ/ የተሰጠውን ድጋፍ በተለየ የሂሳብ መዝገብ በየወጪ አርዕስቱ ዘርዝሮ መያዝ አለበት፣

መ/ በፋይናንስ ህግ መሠረት በበጀት አመቱ ከመንግስት የተሰጠውን የገንዘብ መጠን እና ገንዘቡን ለምን ተግባር እንዳዋለ የሚያሳይ በኦዲተር የተረጋገጠ የሂሳብ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

2. ኦዲተሩ የመረመረውን ሂሳብ ከህግ ውጭ ወጪ የተደረገ መሆን አለመሆኑን በኦዲት ሪፖርቱ ላይ አስተያየት መስጠት አለበት።

3. የፖለቲካ ፓርቲው የኦዲት ሪፖርቱን፤

ሀ/ ለፓርቲው የዕለት ከዕለት ተግባር ማከናወኛ የተሰጠውን ድጋፍ በሚመለከት የሚቀርብ ሪፖርት የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፣

ለ/ ለምርጫ ተግባር የተሰጠውን ድጋፍ በሚመለከት ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ መሠረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

4. የፌዴራል ዋና ኦዲተር ከመንግሥት የተሰጠን ድጋፍ አጠቃቀም በተመለከተ በማንኛውም ጊዜ የፖለቲካ ፓርቲዎችን መመርመር ይችላል፡፡

49.<u>ስለተጠያቂነት እና ቅጣት</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከመንግሥት የሚሰጠውን ድጋፍ ከታለመለት ዓላማ ውጪ ካዋለ ወይም በወቅቱ ሪፖርት ካላቀረበ ወይም የሀሰት የሂሳብ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ፣ ወይም ከሚሰጠው ድጋፍ ጋር በተያያዘ ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ፤

ሀ/ የሚሰጠው ድጋፍ እንዲቀነስ ወይም እንዲቋረጥ፣

ለ/ ፓርቲው በወንጀል ህግ መሠረት በገንዘብ እንዲቀጣ፣ እንዲታገድ ወይም እንዲፈርስ፣

ሐ/ ፓርቲው ከመዝገብ እንዲሰረዝ ወይም

መ/ የፓርቲው ኃላፊ ወይም ኃላፊዎች በገንዘብ ወይም በእስር እንዲቀጡ ሊደረግ ይችላል።

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ የተዘረዘሩት ቅጣቶች እንደሁኔታው በተደራራቢነት ሊፈጸሙ ይችላሉ።

3. ቦርዱ በፖለቲካ ፓርቲ አላግባብ የወጣን ወጪ ክስ በመመስረት ወይም በማቻቻል ሊያስመልስ ይችላል፡፡

**50.<u>ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለሚቀርብ የሂሳብ ሪፖርት</u>**

1. ቦርዱ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተደረገውን ድጋፍ አስመልክቶ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሪፖርቱን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ አለበት። ይህ ሪፖርት፤

   ሀ/ በበጀት ዓመቱ ለፓርቲዎች ድጋፍ እንዲውል በመንግሥት የተመደበውንና ከሌላ ምንጭ የተገኘውን ጠቅላላ መጠን፣

   ለ/ በበጀት ዓመቱ ለእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ የተመደበውን የድጋፍ መጠን፣

   ሐ/ ህግ በሚፈቅደው መሠረት በእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በበጀት ዓመቱ ወጪ የተደረገ የገንዘብ መጠን፣

   መ/ በበጀት ዓመቱ የታየውን የሂሳብ ሚዛን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

2. ቦርዱ የሂሳብ ሪፖርቱን፣ መዝገቡን እና መግለጫውን ለዋናው ኦዲተር መላክ አለበት።

3. የሂሳብ ኦዲተር የሂሳብ ሪፖርት በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ሪፖርቱን ከዋናው ኦዲተር የሂሳብ መግለጫ ጋር በማያያዝ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላክ አለበት፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የገቢ ምንጭ</u>

**51.<u>የፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ ምንጭ</u>**

1. የአንድ የፖለቲካ ፓርቲ የገንዘብ ምንጭ፤

   ሀ/ ከአባላቱ የሚሰበሰብ የአባልነት መዋጮ፣

   ለ/ ቦርዱ አጥንቶ በሚያስቀምጠው ጣሪያ መሠረት በኢትዮጵያውያን ግለሰቦች እና ኩባንያዎች የሚደረግ ስጦታ ወይም እርዳታ፣

   ሐ/ ከአንቀጽ 42 እስከ አንቀጽ 50 በተደነገገው መሠረት ከመንግሥት

ከሚሰጠው ድጋፍና ዕርዳታ፣

ሊሆን ይችላል።

2. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በመንግሥት ወይም በብሔራዊ ክልላዊ መስተዳድር ፈቃድ የገንዘብ አቅሙን ለማጎልበት ቀጣይነት በሌለው መልክ ዝግጅቶችን በማደራጀት ገንዘብ ለማሰባሰብ ይችላል፡፡

3. የዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 2 ድንጋጌ ቢኖርም ማንኛውም ሕጋዊ ሰውነት ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የንግድና ኢንዱስትሪ ስራዎች መስራት አይችልም።

52.<u>ከመቀበል የተከለከለ ስጦታ ወይም እርዳታ</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከሚከተሉት ሰዎች ወይም አካላት የሚሰጥን ስጦታ ወይም እርዳታ መቀበል በጥብቅ የተከለከለ ነው፤

   ሀ/ ከውጪ ሀገር ዜጎች፣

   ለ/ ከውጪ ሀገር መንግሥት ወይም ሀገር የፖለቲካ ድርጅት፣

   ሐ/ ከበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት፣

   መ/ ከሃይማኖት ድርጅት፣

   ሠ/ ከፍርድ እስረኞች፣

   ረ/ ከህገ-መንግሥቱ ውጭ ሥልጣን ለመያዝ ከተደራጀ ቡድን ወይም ሰው፣

   ሰ/ ከሽብርተኛ ድርጅት፣

   ሸ/ ምንጩ ያልታወቀ ስጦታ ወይም እርዳታ፣

   ቀ/ ከመንግሥታዊ ድርጅት፣

   በ/ አንድን ነገር ወደፊት ለማስፈጸም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ወይም ከህግ ውጭ ጥቅም ለማግኘት በማለም ከማንኛውም አካል ወይም ሰው የሚሰጥ ስጦታ ወይም እርዳታ።

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ ከ/ሀ/ እስከ /በ/ የተከለከለን ስጦታ ወይም እርዳታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ የተቀበለ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ያገኘው ገንዘብ ወይም ንብረት ይወረሳል። እንደሁኔታው አግባብ ባለው ህግ ይጠየቃል።

3. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀጽ /1/ መሠረት የተከለከለ ስጦታ ወይም እርዳታ በማንኛውም መንገድ የደረሰው እንደሆነ ስጦታውን

ወይም እርዳታውን በተቀበለ በ21 ቀናት ውስጥ ከተያያዥ መረጃዎች ጋር ለቦርዱ ገቢ ማድረግ አለበት፡፡

53.<u>ከህግ ውጭ ስለተገኘ ሀብትና ንብረት</u>

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ ከተፈቀደለት ውጭ ገንዘብ፣ ወይም ማናቸውንም ንብረት፣ በስጦታ፣ በዳረጎት፣ በውርስ፣ በንግድና ኢንዳስትሪ ሥራ ወይም በማናቸውም መንገድ ተቀብሎ ቢገኝ ንብረቱ በፍርድ ቤት ውሳኔ ለመንግሥት ገቢ ይሆናል፣ አግባብ ባለው ህግም ይጠየቃል።

## <u>ምዕራፍ ሶስት</u>

## <u>ስለማህደር፣ ሂሳብ አያያዝና ቁጥጥር</u>

54.<u>የፖለቲካ ፓርቲ ማህደርና አዲት</u>

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የሚከተሉትን ጉዳዮች ያካተተ ትክክለኛና ቋሚ ማህደር በፓርቲው ዋና ጽሕፈት ቤት በአግባቡ መያዝ አለበት፤

1. ማንኛውም በዓይነትም ሆነ በገንዘብ የሚደረግ መዋጮ፣ ስጦታ፣ እና ቃል የተገባ ስጦታ ወይም መዋጮ፣
2. ከዚህ የሚከተሉትን ያካተተ የሂሳብ መግለጫ፤

   ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲውን የገንዘብ ምንጭ፣

   ለ/ መዋጮ ያደረገውን ወይም ስጦታ የሰጠውን ወይም ቃል የገባውን ሰው ስም፣

   ሐ ቃል የተገባ መዋጮ ወይም ስጦታ ካለም የሚከፈልበትን ጊዜ፣ እና

   መ/ አጠቃላይ የፖለቲካ ፓርቲውን የሂሳብ እንቅስቃሴ፡፡
3. የፖለቲካ ፓርቲ ቋሚ ንብረቶች ዝርዝር፣ መቼ እና እንዴት በባለቤትነት እንደያዘው፣
4. ከዚህ ጋር በተያያዘ ቦርዱ የሚፈልጋቸውን ሌሎች መረጃዎች።

55.<u>የሂሳብ መዝገብ</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የገቢና ወጭ ሂሳብ ስርአት ይኖረዋል።
2. የማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የገቢና ወጭ ሂሳብ አያያዝ ስርአት በሂሳብ አያያዝ ልምድ ተቀባይነት ባለው መንገድ መሆን አለበት፡፡
3. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል በማንኛውም ጊዜ ለስራ መሰናክል ሳይሆን አባል የሆነበትን የፓርቲውን የገቢና ወጭ ሂሳብ መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡

4. ማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ የሚያወጣቸው ወጪዎች ሁሉ ለፖለቲካ አላማው መዋላቸውን ለቦርዱ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፡፡

## 56.ዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በየዓመቱ በራሱ ኦዲተር የሂሳብ ምርመራ ያካሂዳል። የፖለቲካ ፓርቲው በቦርዱ ከተመዘገበ ከ 6 ወር ጀምሮ የሚሳብ ሪፖርቱን የበጀት አመቱ በተጠናቀቀ በሶስተኛው ወር ለቦርዱ ማቅረብ አለበት።
2. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ለቦርዱ የሚያቀርበው አመታዊ የሂሳብ ሪፖርት፤

   ሀ/ የገቢ መጠን እና የገቢ ምንጭ፣

   ለ/ የወጭ ዝርዝር እና

   ሐ/ ስለትክክለኛነቱ የፖለቲካ ፓርቲው መሪ ፈርሞበት በፓርቲው ማህተም የተረጋገጠ ሰነድን ያካተተ መሆን አለበት፡፡
3. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ የዓመት የሂሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ በይፋ ያወጣል። ይህ የዓመታዊ የሂሳብ ሪፖርት በቦርዱ ትዕዛዝ በውጭ ኦዲተር ተመርምሮ ተቀባይነት ያገኘ መሆን ይገባዋል።
4. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሠረት ሪፖርት ካላቀረበ ወይም ሪፖርት ቢያቀርብም ቦርዱ በተላከለት ሪፖርት ላይ ጥርጣሬ ሲኖረው ቦርዱ የውጭ ኦዲተር በመላክ ሂሳቡ እንዲመረመር ያደርጋል፡፡ ለዚህም የሚያስፈልገውን ወጭ የፖለቲካ ፓርቲው ይሸፍናል።

## ክፍል ስድስት

## የተከለከሉ ተግባራት እና የሚወሰዱ እርምጃዎች

## 57.ዓላማን በህገወጥ መንገድ ማስፋፋት የተከለከለ ስለመሆኑ

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በሃይል ወይም በማስፈራራት የፖለቲካ ዓላማውን ለማስረጽ ማንኛውንም ሰው ወይም ቡድን ማደራጀት ወይም ማሰልጠን ወይም ሰዎችን በግድ መመልመል በህግ ያስቀጣዋል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ወይም ቡድን ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ የተገለፀውን ተግባር የረዳ ወይም የተባበረ እንደሆነ አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል፡፡

## 58.በፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመሳተፍ ስለማይችሉ ሰዎች

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉት ሰዎች በፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመንቀሳቀስ አይችሉም፤

ሀ/ ዳኛ፣

ለ/ የመከላከያ ሰራዊት አባል፣

ሐ/ የፖሊስ አባል።

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ የተጠቀሱት ሰዎች በፖለቲካ ፓርቲ አባልነት ለመንቀሳቀስ ከፈለጉ የመንግሥት ስራቸውን መልቀቅ አለባቸው።
3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ የተደነገገውን የጣሰ ሰው ከያዘው የመንግሥት ሥራ በራሱ እንደለቀቀ ይቆጠራል።

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

59.*መሸጋገሪያ ድንጋጌ*

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት የተቋቋመ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አዋጅ እንደተመዘገበ ይቆጠራል። ይሁን እንጂ ቦርዱ በዚህ አዋጅ መሠረት መሟላት የሚገባውን ሰነድ ያላሟላ ፓርቲን እንዲያሟላ ሊያዝ ይችላል፡፡

60.የመተባበር ግዴታ

ማንኛውም ሰው ይህን አዋጅ በሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

61.ደንብና መመሪያ ስለማውጣት

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ለዚህ አዋጅ ማስፈፀሚያ የሚረዳ ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

62.የተሻሩ ህጎች

1. የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 46/1985 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 82/1986 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

63.አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም 14 ቀን 2001 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

# <u>አዋጅ ቁጥር 662/2002</u>

## <u>የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ</u>

ቀደም ሲል በሀገራችን ከተካሄዱ ምርጫዎች ትምህርት በመውሰድ ወደፊት የሚካሄዱ ምርጫዎች በመልካም ስነምግባር የሚመሩ ግልጽ፣ ነጻ፣ ፍትሃዊ ሰላማዊ፣ ህጋዊ፣ ዴሞክራሲያዊ እንዲሁም በህዝብ ተቀባይነት ያላቸው እንዲሆኑ ለማስቻል በምርጫ ወቅት የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ እጩዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች አባላት እና ደጋፊዎች የሚመሩበት ዝርዝር የስነምግባር ህግ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ሕዝብ ባሳለፈው የረጅም ጊዜ የመንግስት ስርዓት ሲታገልለት የኖረውን የሕዝብ ስልጣን አመንጪነት፣ ባለቤትነትና ተቆጣጣሪነት መብት አጠናክሮ መቀጠል በሀገራችን ሰብአዊ እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሳይሸራረፉ ተግባራዊ መሆኑን ለሰለጠነ ሰላማዊ ትግልና ውድድር ያላቸውን ፋይዳ በመገንዘብና በመቀበል፤

የምርጫ ቦርድ የፍትሕ አካላት እና የመገናኛ ብዙሃን ከማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲዎች በነፃነትና በገለልተኛነት ህዝብን ማገልገል እንዳለባቸው እንዲሁም የሀገር መከላከያ ሰራዊት በህገመንግስቱ መሰረት ተግባሩን ከፖለቲካ ፓርቲዎች ወገናዊነት ነፃ በሆነ አኳኋን እንዲያከናውን የተደረገ መሆኑን በመገንዘብ፤

ሦስቱ የመንግስት አካላት የግልጽነት፣ የታማኝነትና የተጠያቂነት ኃላፊነትና ግዴታ እንዳለባቸው የተቀበሉና ተግባራዊነቱንም ለማክበር እና ለማስከበር ቃል የገቡ መሆናቸውን በማጤን የፖለቲካ ፓርቲዎች ለተፈፃሚነቱ መቆም እንዳለባቸው በመገንዘብ፤

በዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መቻቻልን ማስፈን ተገቢ በመሆኑና በምርጫ ሂደት ነጻ የፖለቲካ ዘመቻ ማካሄድ እንዲሁም ግልጽ ህዝባዊ ውይይትን ማጎልበት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች በተስማሙባቸው ጉዳዮች በጋራ እየሰሩና በልዩነታቸው ላይ ደግሞ በሰላማዊና በሰለጠነ መንገድ ትግል በማካሄድና በህግ መሰረት የተካሄዱ ምርጫዎች ትክክለኛ ሂደትና ውጤት የህዝብ ውሳኔ መሆኑን በፀጋ ተቀብለው በመጓዝ በሀገር ግንባታ የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት መወጣት ያለባቸው መሆኑን በመገንዘብና ወደስልጣን ለመምጣት በሚያካሂዱት ውድድር ከጥላቻና ካለመተማመን የፀዳ፤ ጤናማ ግንኙነት ፈጥረው የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች በቅንነት፣ በመቻቻል እና ሰጥቶ በመቀበል መርህ እየተመሩ በሀገራችን የመድብለ ፓርቲ ስርዓት እና ዴሞክራሲያዊ ባህል እንዲጎለብት የማይተካ ሚና እንዲጫወቱ ለማስቻል፤

የህዝብ ውሳኔን በመጻረር የመንግስት ስልጣን ላይ መቆየትም ሆነ ከህገ-መንግስታዊ ሥርዓት ውጪ የመንግስት ስልጣን ለመያዝ የሚደረጉ ማናቸውም የሀገር ውስጥም ሆኑ የውጪ እንቅስቃሴዎች ተቀባይነት የሌላቸው መሆናቸውን በአፅንኦት ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የሰነምግባር አዋጁ ለመገናኛ ብዙሃን ነጻነት ለሰብአዊ መብት፣ ለዴሞክራሲ፣ ለህግ የበላይነት እና ለሕዝቦች ሁለንተናዊ እድገት ያለውን ልዩ አስተዋጽኦ በመገንዘብ ፤ ለተፈጻሚነቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ መቆም የሚያስችላቸው ሁኔታ ማመቻቸት በማስፈለጉ፤

ማንኛውም ለምርጫ አገልግሎት ሊውል የሚችል በመንግስት ቁጥጥር ስር የሚገኝ ሀብት፣ ንብረትና የአካባቢ መስተዳድር አካላት አገልግሎቶች ለሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በህግ መሰረት በፍትሀዊነትና ያለአድልዎ የሚሰጥበትን አሰራር ማጠናከር በማስፈለጉ፤

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የመምረጥና የመመረጥ መብቱን ለማረጋገጥ በሚያደርገው እንቅስቃሴ ምንም አይነት ተጽእኖ ወይም እንቅፋት እንዳይ ደረግበት የፖለቲካ ፓርቲዎች ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን በመገንዘብ፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች በሥነ-ምግባር አዋጁ ላይ ተከታታይ ትምህርትና ስልጠና የመስጠት፣ ግንዛቤ የመፍጠር እና ሌላውም እንዲያስተምር የማበረታታት ከፍተኛ ኃላፊነት ያለባቸው መሆኑን በግልጽ መደንገግ በማስፈለጉ፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች የሚያቀርቧቸውን የምርጫ አስፈፃሚዎች እና አሠራራቸው ወይም የምርጫም ሆነ ሌሎች ተያያዥ ችግሮች በዚህ አዋጅ መሰረት በመመርመር ተጨባጭ ሆነው ከተገኙ የማስተካከያ እርምጃ ለመውሰድ የሚያስችል አሰራር መዘርጋት በማስፈለጉ፤

ይህንን አዋጅ ተፈጻሚ ለማድረግ የሚያስችል አሠራር መዘርጋት እንዲሁም በየደረጃው የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቶች ማቋቋምና ስልጣንና ተግባራቸውንም በግልጽ መደንገግ ከፍተኛ ሕዝባዊ ጠቀሜታ ያለው መሆኑን በመገንዘብ፤

የፖለቲካ ፓርቲዎች ሰፊ ጊዜ በመውሰድ ተወያይተው የተስማሙባቸውን በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸውን መርሆዎች ከሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጋር አጣጥሞ የያዘ አዋጅ መደንገግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ /1/ እና ንዑስ አንቀጽ /2/መ/ መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ስነምግባር አዋጅ ቁጥር 662/2002 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1. "ቦርድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፤
2. "የምርጫ አስፈፃሚ" ማለት ቦርዱን ጨምሮ በየደረጃው ምርጫን ለማስፈፀም የሚደራጅ አካል ወይም ሰው ነው፤
3. "የጋራ ምክር ቤት" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 21 መሰረት በየደረጃው የሚመሰረት የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ነው፤
4. "የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ድርጅት" ማለት ከህብረተሰቡ ውስጥ የተወሰኑ ሰዎችን በማሰባሰብ የራሱን የፖለቲካ እምነት እና አላማ የሚያንፀባርቅበት ፕሮግራም በማውጣት በአገር አቀፍ ወይም በክልል የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ በዲሞክራሲያዊ ስርዓት የፖለቲካ ስልጣን ለመያዝ በህግ መሰረት የተመዘገበ ማህበራዊ ተቋም ነው፤
5. "እጩ ተወዳዳሪ" ማለት በምርጫ ለመወዳደር በፖለቲካ ፓርቲ ወይም በግሉ የተመዘገበ ሰው ነው፤
6. "ድምጽ መስጫ ጣቢያ" ማለት በየደረጃው በሚካሄዱ ምርጫዎች የመራጮች ምዝገባ የሚካሄድበት፣ መራጮች ድምጽ የሚሰጡበትና ቆጠራ የሚካሄድበት የምርጫ ጣቢያ ነው፤
7. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው።

3. **የተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ አዋጅ፡-

1. በማናቸውም የፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት ወይም ንቅናቄ፣ እና
2. በማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል እና ተጠሪ፤

ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. **የፆታ አገላለጽ**

በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

**ክፍልሁለት**

# የምርጫ ስነምግባር ድንጋጌዎች

5. **መርህ**

1. በመድብለ ፓርቲ ዴሞክራሲ ስርዓት የሚመረጥ መንግስት ህጋዊነት በሚከተሉት መርሆዎች ላይ ይመሠረታል፡-

   ሀ/ መራጮች በምርጫ ዘመቻው አማካኝነት ስለፖለቲካ ፓርቲዎች ፖሊሲዎችና ስለእጩዎች ባህሪ የተሟላ መረጃ ሲሰጣቸውና የራሳቸውን በእውቀት ላይ የተመሰረተ ውሳኔ ሲያደርጉ፤ እና

   ለ/ መራጮች በነፃነት፣ ያለ ማንም ጣልቃ ገብነት፣ ያለ ፍርሃት፣ ያለ ተፅእኖ፣ ያለጫና ወይም ከጉቦ ነፃ በሆነ መልኩ ድምፅ መስጠት ሲችሉ፣ ነው፡፡

2. ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች በቅን ልቦና እየተመሩ፡-

   ሀ/ የምርጫ ስነምግባር መርሆዎች እንዲከበሩ፣

   ለ/ ምርጫው የመላው ህዝብ ነፃ እና ተቀባይነት ያለው ውሳኔ መግለጫ ሆኖ እንዲታወቅ፣

   ሐ/ የመራጩ ህዝብ ውሳኔ በሁሉም የተከበረ እንዲሆን፣ መስራት አለባቸው፡፡

3. ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዙ ማናቸውም ጉዳዮች ሁሉም የፖለቲካ ፓርቲዎች ከዚህ አዋጅ ጋር በተጣጣመ አኳኋን መንቀሳቀስ አለባቸው።

6. **ለአዋጁ ተገዥ ስለመሆን**

1. ማንኛውም የፓለቲካ ፓርቲ ወይም የግል ዕጩ ተወዳዳሪ፦

   ሀ/ በዚህ የስነምግባር አዋጅ ተገዝቶ መንቀሳቀስ አለበት፤

   ለ/ መሪዎቹ፣ ኃላፊዎቹ፣ እጩዎቹ እና አባላቱ ይህንን የስነምግባር አዋጅ እንዳይጥሱ ቁርጠኛ እርምጃ መውሰድ አለበት፤

   ሐ/ የፓርቲው ኃላፊዎች፣ እጩዎችና አባላት ይህንን አዋጅ የሚጥስ ተግባር እንዳይፈጽሙ፤ ደጋፊዎቹም የተከለከሉ ድርጊቶች ከመፈጸም እንዲቆጠቡ የሚያደርግ አግባብ ያላቸውን እርምጃዎች መውሰድ አለበት፤

   መ/ ይህ አዋጅ ተጥሷል በሚል ሽፋን የሀሰትና የተጋነነ አቤቱታ እያቀረበ ቅሬታ የማሰማት መብቱን አለአግባብ መጠቀም የለበትም፡፡

2. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፤ የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊ፣ እጩዎች፣ አባላት ወይም ደጋፊዎች፦

   ሀ/ ይህንን የስነምግባር አዋጅ እንዲያከብሩ ማድረግ አለበት፤

ለ/ ይህ አዋጅ እንዲከበር ሌሎች አስፈላጊ እርምጃዎችን ሁሉ መውሰድ አለበት።

7. <u>ህግን ስለማክበር</u>

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ይህንን አዋጅ፥ የምርጫ ህግ፣ ደንብ እና መመሪያ ማክበር አለበት።

8. <u>ስለ ምርጫ ዘመቻ አካሄድ</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፦

ሀ/ የሌሎች የፓለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ የማካሄድ መብትና ነፃነት እና የፖለቲካ ሀሳቦችንና መርሆዎቻቸውን ያለስጋት የማሰራጨት መብትን የማክበር፤

ለ/ እንቅስቃሴው የሌላውን የፖለቲካ ፓርቲ፣ የመራጩን ሕዝብ እና የሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች መብቶችን ያከበረ የመሆን፤

ሐ/ የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን የማክበር፤

መ/ ድርጅቱ ያሉትን ጽሕፈት ቤቶች ሁሉ በመጠቀም፣ ተወዳዳሪ ፖለቲካ ፓርቲዎች ለመራጩ ሕዝብ ያላቸውን አግባብነት ያለው ተደራሽነት ለማረጋገጥ የመጣር፤

ሠ/ በፖለቲካ እንቅስቃሴ ለመሳተፍ የሚሹ የመምረጥ መብት ያላቸው ዜጎች ሁሉ በነጻነት እንዲንቀሳቀሱ የማስቻል፤

ግዴታ አለበት።

2. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፦

ሀ/ የግል ወይም የመንግስት ጋዜጠኞች በሙያዊ ስራቸው ላይ እንዳይሰማሩ ማዋከብ፣ እንቅፋት መፍጠር፣ ወይም በማንኛውም አይነት ድርጊት የሌሎች ፓርቲዎች የምርጫ ዘመቻ እንዲስተጓጎል፣ እንዲቋረጥ፣ እንዲበላሽ፣ እንዲዳከም ማድረግ፤

ለ/ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ማስታወቂያዎች፣ በራሪ ፅሁፎች እና ፖስተሮች እንዳይሰራጩ ማወክ፤

ሐ/ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች ፖስተሮች ማበላሸት፣ ማጥፋት ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ እንዳይታዩ ወይም እንዳይነበቡ ማድረግ፤

መ/ ሌላ የፖለቲካ ፓርቲ ሰፊ የሕዝባዊ ድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባዎች ወይም የእግር ጉዞ ወይም ሰላማዊ ሰልፎች እንዳያደርግ ማገድ ወይም በሌላ በማንኛውም መንገድ ማደናቀፍ፤

ሠ/ ማንኛውም ሰው በሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች የፖለቲካ ድጋፍ ሰልፍ እንዳይሳተፍ መከልከል፤

ረ/ ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተከለከሉ ማናቸውንም ተግባራት እንዲፈፅሙ መፍቀድ፤

የለበትም፡፡

9. <u>ስለምርጫ ሂደት</u>

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

1. ከምርጫ አስፈፃሚዎች ጋር በመተባበር፡-

ሀ/ ድምጽ የመስጠት ሂደቱ ሰላማዊ እና በአግባቡ የተከናወነ መሆኑን ለማረጋገጥ፣

ለ/ መራጮች ያላቸውን የመምረጥ መብት ከሚያደናቅፉ ማንኛውም ሁኔታዎች በፀዳ፣ ነፃና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ተግባራዊ እንዲያደርጉ፣

መስራት አለበት፡፡

2. ከድምጽ መስጫ ዕለት በፊት፣ በድምጽ መስጫ ዕለት፣ ከድምጽ መስጫ ዕለት በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎችን ፀጥታና ደህንነት ማረጋገጥ አለበት፤

3. የታዛቢነት ፈቃድ ያላቸውን ታዛቢዎች እና ኃላፊዎች ማክበር እና መተባበር አለበት፤

4. የድምፅ አሰጣጥ ሚስጢራዊነትን ማክበርና እንዲከበር ማገዝ አለበት፤

5. የድምጽ መስጫ ጣቢያን በኃይል በመቆጣጠር ወይም በሌላ በማንኛውም ህገወጥ መንገድ ድምፅ ለማግኘት መንቀሳቀስ የለበትም፤

6. ያለአግባብ ወይም ከቅን ልቡና ውጪ የምርጫ አስፈፃሚዎች ተግባራትን፣ የድምፅ አሰጣጥን ወይም የድምፅ ቆጠራ ሂደትን ማወክ ወይም ጣልቃ መግባት የለበትም፤

7. የድምፅ አሰጣጡ ሚስጥራዊ እንደማይሆን ለመራጮች የሀሰት መረጃ መስጠት የለበትም።

10. <u>ፍትሃዊና ነፃ የምርጫ ውጤትን ስለመቀበል</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በሚመለከተው ህጋዊ አካል የተረጋገጠን የምርጫ ውጤት መቀበል አለበት።

2. ማንኛውንም ቅሬታ ያለው አካል ቅሬታውን ለሚመለከተው የጋራ ምክር ቤት ወይም ለቦርዱ ወይም ለፍርድ ቤት ብቻ ማቅረብ አለበት።

3. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ በህግ መሠረት የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ያለው አካል የሰጠውን የመጨረሻ ውሳኔ መቀበል እና ተግባራዊ ማድረግ አለበት።

## 11.ለምርጫ ዘመቻ ጥቅም ላይ ስለሚውል የቋንቋ ይዘት

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

ሀ/ የምረጡኝ ዘመቻውን ሲያደራጅና ሲያካሂድ ለአጠቃላይ የምረጡኝ ዘመቻ፣ ለድምፅ አሰጣጥ፣ ለቆጠራ እና ለድህረ ምርጫ ሂደቱ ሰላማዊነትና ቀና አካሄድ አስተዋፅኦ በሚያደርግ አኳኋን መሆን አለበት፤

ለ/ ከሚጣልበት ኃላፊነትና ካለው ክብር ጋር በተመጣጠነ ደረጃ መንቀሳቀስ አለበት።

2. ማንኛውም ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ ላይ ንግግር የሚያደርግ ሰው፡-

ሀ/ ግጭት ቆስቋሽ ወይም ስም አጥፊ ንግግር ማስወገድ አለበት፤

ለ/ በማንኛውም መልኩ በግለሰቦች ወይም ቡድኖች ላይ አመጽ የሚጋብዝና ስጋት የሚፈጥር ንግግር ማስወገድ አለበት።

3. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በይፋም ሆነ በስውር አመፅ የሚቀሰቅስ ወይም የሚያስፈራራ የቋንቋ ይዘት ያለው በራሪ ወረቀት፣ የዜና መጽሔት ወይም ፖስተር ማውጣት ወይም ማሰራጨት የለበትም።

4. በህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አካል የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ዘመቻ ወቅት በሚያደርጉት ንግግር ምክንያት ተፅዕኖ ማድረስ የለበትም።

## 12.ስለምልክቶች

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ፡-

1. የሌሎች ፓርቲዎችን አርማ ወይም የምርጫ ምልክት መቅዳት ወይም አስመስሎ መጠቀም፤

2. የሌሎች ፓርቲዎች የፖለቲካ ወይም የምርጫ ቁሳቁስ መስረቅ፣ ማበላሸት፣ ማጥፋት፤ ወይም

3. ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተከለከለ ማንኛውንም ተግባር እንዲፈፅሙ መፍቀድ፤ የለበትም።

## 13.ስለማስፈራራት እና አመጽ ስለመቀስቀስ

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ማንኛውንም አይነት ማስፈራራት ወይም ወከባ የተከለከለ መሆኑን ተቀብሎ፡-

ሀ/ የፓርቲው ኃላፊዎች፣ እጩ ተወዳዳሪዎች፣ አባላት እና ደጋፊዎች ማንኛውንም ሰው በማንኛውም ጊዜ ማስፈራራት እንደሌለባቸው በግልፅ የሚከለክሉ መመሪያዎች ማውጣት፤

ለ/ አመፅ ወይም አመጽን የሚያነሳሳ ድርጊት በመቃወም ማስተማር፤

ሐ/ በኃላፊዎቹ፣ በእጩዎቹ፣ በአባላቱ ወይም በደጋፊዎቹ የሚፈፀሙ ስጋቶችና ውድመቶች ወይም የህዝብ ሰላም የሚያናጉ ድርጊቶች ወይምወደነዚህ የማያመሩ ዛቻዎች በመቃወም ማስተማር፤

መ/ የሌሎች ሰዎችን እና ፓርቲዎችን መብቶችና የንብረታቸውን ጥቅሞች ማክበር፤

አለበት።

2. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ የፓርቲው ኃላፊዎች፣ እጩዎች፣ አባላት እና ደጋፊዎች ማናቸውንም ባህላዊ ወይም ዘመናዊ የጦር መሳሪያዎች ወደ ፖለቲካ የድጋፍ ሰልፎች፣ ስብሰባዎች፣ የእግር ጉዞዎች ወይም ሰላማዊ ሰልፎች ይዘው እንዳይመጡ ማስተማር አለበት ።

3. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

ሀ/ የፓርቲውን ጥንካሬ ለማሳየት ወይም የበላይነቱን ለማረጋገጥ ሲል በማንኛውም የሁከት ወይም የአመፅ እንቅስቃሴ መሳተፍ ወይም እንዲደረግ መፍቀድ የለበትም፤

ለ/ በህዝብ ወይም በግለሰብ ንብረት ላይ ውድመት እንዳይደርስ የተቻለውን ሁሉ በማድረግ መከላከል አለበት፤

ሐ/ ደጋፊዎቹ በዚህ ክፍል የተደነገጉ ማናቸውንም ክልከላዎች እንዲፈፅሙ መፍቀድ የለበትም።

## 14.<u>ስልጣንን ያለአግባብ ስለመጠቀም</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

ሀ/ ያለውን የሥልጣን ኃላፊነትና የተለየ ዕድል ወይም ተፅዕኖ የማሳደር ችሎታ ለፖለቲካ ፍላጎቱ ለመጠቀም መደለያ ማቅረብን፣ ቅጣትን ወይም ማንኛውንም ህገወጥ ተግባር መጠቀም፤

ለ/ የፌዴራል መንግስትን፣ የክልል መንግሥትን፣ የከተማ ማዘጋጃ ቤትን ወይም ሌላ የህዝብ ሀብትን በምርጫ ህጉ ከተፈቀደው አኳኋን ውጭ ለምርጫ ቅስቀሳ ዓላማ መጠቀም፣

የለበትም።

2. በዚህ ክፍል ውስጥ "ስልጣን፣ ልዩ መብት ወይም ጫና" ማለት የወላጅ፣ የዝምድና፣ የመንግስት፣ የፖሊስ፣ የአካባቢ ታጣቂ ኃይል፣ የወታደራዊ ወይም ልማዳዊ ወይም ባህላዊ ስልጣንን ያካትታል።

15.<u>ስለሙስና ተግባር</u>

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

1. ኃይል በመጠቀም ወይም የገንዘብም ሆነ ሌላ አይነት መደለያ በመስጠት መራጬ ህዝብ ለአንድ ፓርቲ ወይም እጬ ድምጽ እንዲሰጥ ወይም እንዳይሰጥ ወይም ድምፁን ከመስጠት እንዲታቀብ ማድረግ፤
2. ኃይል በመጠቀም ወይም የገንዘብም ሆነ ሌላ አይነት መደለያ በመስጠት ሰዎች እጬ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀርቡ ወይም እንዳይቀርቡ ወይም ከእጬ ተወዳዳሪነታቸው እንዲወጡ ወይም ከእጬ ተወዳዳሪነት እንዳይወጡ ማድረግ፤
3. ማንኛውም የሥራ ኃላፊ ወይም የመንግስት ሠራተኛ በሚመራው ወይም በሚሠራበት ተቋም አግባብ ያልሆነ ድጋፍ ወይም እርዳታ በመጠቀም እጬ ተወዳዳሪን ማስተዋወቅ ወይም የሌሎች ተወዳዳሪዎችን የማስተዋወቅ ዕድል ማደናቀፍ ፤

የለበትም::

16.<u>ቀጣይ ግንኙነት ስለመፍጠር</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከሌሎች ፓርቲዎች ጋር ቀጣይ ግንኙነት ፈጥሮ መንቀሳቀስ አለበት።
2. በምርጫ ህጉ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በምርጫ ዘመቻ ወቅት እና በማናቸውም ጊዜ የጋራ ጉዳይ በሆኑ ነጥቦች ላይ የመወያያ መድረክ ሆኖ የሚያገለግል የጋራ ምክር ቤት በፖለቲካ ፓርቲዎች ይመሠረታል።
3. የግል እጩ ተወዳዳሪዎች በጋራ ምክር ቤቱ በታዛቢነት መሳተፍ ይችላሉ። ችግር በገጠማቸውም ጊዜ ለምክር ቤቱ ጥያቄያቸውን አቅርበው በዚህ አዋጅ መሰረት ያስወስናሉ።
4. የምርጫ አስፈፃሚዎች በጋራ ምክር ቤት ውይይት ላይ አይገኙም። ሆኖም የፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት በሙሉ ድምጽ ተስማምቶ እንዲገኙ ከወሰነ ያለድምጽ በስብሰባው ላይ መገኘት ይችላሉ።

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የስነምግባርአዋጁን ስለማስተዋወቅ</u>

17.<u>የፖለቲካ ፓርቲዎችና እጩ ተወዳዳሪዎች ኃላፊነት</u>

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ የምርጫ ስነምግባር አዋጁን ለመራጩ ህዝብ፣ ለእጩዎቹ ለአባላቱና ለደጋፊዎቹ በማስተማር በአባላቱ መታወቁንና መከበሩን ማረጋገጥ አለበት።
2. እያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በምርጫው ሂደት ለመራጩ ህዝብ አዋጁን ለማስተማር የሚደረጉ ጥረቶችን መደገፍና ማስተዋወቅ አለበት።
3. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ:-

   ሀ/ አዋጁን ማክበር ፤

   ለ/ እጩ ተወዳዳሪዎቹ፣ ባለስልጣኖቹ፣ ወኪሎቹ፣ አባሎቹና ደጋፊዎቹ የስነ ምግባር አዋጁንና የምርጫ ህጉን አክብረው እንዲንቀሳቀሱ መምራት እና ማክበራቸውንም የሚያረጋግጡ እርምጃዎች መውሰድ፤

   አለበት።
4. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ እና እጩ ተወዳዳሪ፤ ሁሉም ሰው:-

   ሀ/ የፖለቲካ እምነቱን እና አስተያየቱን በነፃ የመግለፅ፤

   ለ/ በሌሎች የፖለቲካ እምነት እና አስተያየት ላይ የመከራከር እና የመተቸት፤

   ሐ/ የራሱን የምርጫ ቅስቀሳ ቁሳቁሶች የማተምና የማሰራጨት፤

   መ/ ፖስተሮችን፣ ባነሮችንና ቢልቦርዶችን የመስቀል፤

   ሠ/ ህጉ በሚፈቅደው መሠረት ማንኛውም አይነት ገንዘብ፣ የቁሳቁስና የሰው ኃይል የምርጫ ድጋፍ የማሰባሰብ፤

   ረ/ አባላትን የመመልመል፤

   ሰ/ ህዝባዊ ስብሰባዎችን የማካሄድ፤

   ሸ/ በህዝባዊ ስብሰባዎች የመገኘት፤

   መብቶች እንዳሉት በይፋ የመግለፅ ግዴታ አለበት።
5. የፖለቲካ ፓርቲዎችና ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሥነ ምግባር አዋጁንና በአዋጁም ለመገዛት ያላቸውን ቁርጠኝነት ለህዝብ ይፋ ማድረግ አለባቸው።
6. የፖለቲካ ፓርቲዎች እና እጩ ተወዳዳሪዎች ነፃና ፍትሀዊ ምርጫን የሚጎዳ ወይም የሚያጣጥል ማንኛውንም ተግባር በይፋ ማውገዝ አለባቸው፡፡

## 18.<u>የቦርዱና የሌሎች ምርጫ አስፈፃሚ አካላት ኃላፊነት</u>

1. ቦርዱ ሁሉም ቀጥተኛና ተዘዋዋሪ ሚና የሚጫወቱትን መንግሥታዊና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በስነምግባር አዋጁ ላይ አስፈላጊውን ግንዛቤ እንዲይዙ ተገቢውን ሁሉ ማድረግ አለበት።
2. ቦርዱ የምርጫ ስነ ምግባር አዋጁን ለሚመለከተው ሁሉ የማሰራጨት ኃላፊነት አለበት
3. በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት በስነ ምግባር አዋጁ ላይ በቂ ግንዛቤ እንዲይዙ ለሚመለከታቸው ሁሉ ትምህርት መስጠት አለባቸው።

19. <u>የሌሎች አካላት ሚና</u>

1. የመገናኛ ብዙሃን ይህንን የስነ ምግባር አዋጅ አስመልክቶ ለህዝብ ትምህርት ይሰጣሉ።
2. በምርጫ ህጉ መሰረት ከቦርዱ ፈቃድ የተሰጣቸው አካላት ይህንን አዋጅ አስመልክቶ ትምህርት እንዲሰጡ ይደረጋል።

## <u>ክፍል አራት</u>
## <u>ስለጋራ ምክር ቤት አደረጃጀት፣ ኃላፊነትና አሰራር</u>

20. <u>ስለጋራ ምክርቤት አመሰራረት</u>

1. በምርጫ የሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይህንን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግና በምርጫው ሂደት በሚነሱ ልዩ ልዩ የአፈፃፀም እና ዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነት በኢትዮጵያ ለማጎልበት በሚያግዙ ጉዳዮች ላይ በመመካከር ችግሮችን እያቃለሉ ለመጓዝ ይችሉ ዘንድ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 16 የተደነገገውን ቋሚ የግንኙነት ሥርዓት በማበጀት የጋራ ምክር ቤት ይመሰርታሉ።
2. በምርጫ ህጉ መሰረት በቦርዱ የሚመሰረተው የፓርቲዎች የጋራ መድረክ እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ ምክር ቤት ከፌዴራል ጀምሮ እስከ ምርጫ ክልል ድረስ እንዲቋቋም ይደረጋል።

21. <u>ስለ ጋራ ምክርቤትአደረጃጀት</u>

1. አገር አቀፍ የጋራ ምክር ቤት እንደሚከተለው ይደራጃል፦
   ሀ/ በሀገር አቀፍ ደረጃ ለምርጫ ውድድር በተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይመሰረታል።
   ለ/ የጋራ ምክር ቤት አባል የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው ለጋራ ምክር ቤቱ የሚወክሏቸው አባላት ቁጥር የጋራ ምክር ቤቱ በሚያወጣው የመተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል።

2. ክልላዊ የጋራ ምክር ቤት እንደሚከተለው ይደራጃል፦

ሀ/ በክልል ለምርጫ ውድድር በተመዘገቡ ፓርቲዎች ይቋቋማል፤

ለ/ የጋራ ምክር ቤት አባል የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው ለጋራ ምክር ቤቱ የሚወክሏቸው አባላት ቁጥር የጋራ ምክር ቤቱ በሚያወጣው የመተዳደሪያ ደንብ ይወሰናል፡፡

3. የዞን የጋራ ምክር ቤት እንደሚከተለው ይደራጃል፦

ሀ/ በዞን ለምርጫ ውድድር በተመዘገቡ ፓርቲዎች ይቋቋማል፤

ለ/ የጋራ ምክር ቤት አባል የሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች እያንዳንዳቸው ለጋራ ምክር ቤቱ የሚወክሏቸው አባላት ቁጥር የጋራ ም/ቤቱ በሚያወጣው የውስጥ አሰራር ይወስናል፡፡

4. በምርጫ ክልል ደረጃ ያለው አደረጃጀት በምርጫ ክልሉ በሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲ ተወካዮች ይመሰረታል፡፡ ሆኖም የግል ተወዳዳሪዎች በታዛቢነትና ጉዳያቸውን በሚመለከት በአስረጂነት የሚሳተፉ ይሆናል፡፡

5. በየደረጃው የሚዋቀሩ የጋራ ምክር ቤቶች የየራሳቸው የአደረጃጀት ነፃነት ይኖራቸዋል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ የሚቋቋሙ የጋራ ምክር ቤቶች አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ከወጣ ጊዜ ጀምሮ ይህ አዋጅ እንዲወጣ ተስማምተው በፈረሙ የፖለቲካ ፓርቲዎች ይቋቋማሉ፡፡

7. የፖለቲካ ፓርቲዎች የስነምግባር አዋጁ ሲቀረፅ በልዩ ልዩ ምክንያት ያልተሳተፉ ሌሎች ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቱ አባል ለመሆን የጋራ ምክር ቤቱ የሚያወጣውን የስምምነት ሰነድ መፈረም ይኖርባቸዋል፡፡

8. በየደረጃው የሚዋቀሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቶች አሰራር እና የስብሰባ አመራር በየደረጃው ባሉ የጋራ ምክር ቤቶች በሚወጣ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት ይሆናል፡፡

9. በየደረጃው የሚዋቀሩ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤቶች በጀትና ጽህፈት ቤት በተመለከተ በየደረጃው ባሉ የህዝብ ምክር ቤቶች ይመቻቻል፡፡

22.<u>የጋራ ምክር ቤቱ ዓላማ</u>

የጋራ ምክር ቤቱ አላማዎች፦

1. በሀገራችን የሚካሄዱ ምርጫዎች ግልፅ፣ ነፃ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ተአማኒና ሰላማዊ እንዲሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ያለባቸውን ህገ መንግስታዊ ኃላፊነት በዚህ የስነምግባር አዋጅ እየተመሩ ለማስፈፀም የጋራ አካል ሆኖ ማገልገል፤

2. በምርጫ አፈፃፀም ሂደትና ውጤት፣ ባጠቃላይ በፖለቲካ ፓርቲዎች ግንኙነት ውስጥ የሚከሰቱ ችግሮች በምርጫ ህጉና በዚህ አዋጅ መሠረት በጋራ ውይይትና መግባባት ለመፍታት የሚያስችል የውይይት፥ የምክክርና የቁጥጥር አካል ሆኖ ማገልገል፤

ናቸው።

## 23.የጋራ ምክር ቤቱ ተግባርና ኃላፊነት

1. በሀገራችን በነፃነት ማሰብና መተግበር፣ እንዲሁም ዴሞክራሲ፣ ሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነት በሚጎለብቱበት ሁኔታ ላይ ይመክራል፣ የተደረሱባቸውንም ስምምነቶች ይተገብራል፤ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፣ አባል ድርጅቶቹ እንዲተገብሩ ያደርጋል፣ ይቆጣጠራል።
2. ምርጫው ግልጽ፣ ነፃ፣ ዴሞክራሲያዊ፣ ተአማኒ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ሆኖ እንዲካሄድ ፓርቲዎች ያለባቸውን ኃላፊነት በአግባቡ እንዲወጡ ያደርጋል።
3. ፓርቲዎች በልዩ ልዩ የምርጫ ጉዳዮች አፈፃፀም ዙሪያ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ ለመወያየትና ችግሮችን ለመፍታት እንዲችሉ መድረክ ሆኖ ያገለግላል።
4. ይህንን አዋጅ አስመልክቶ ፓርቲዎች ለአባሎቻቸውና ለደጋፊዎቻቸው ትምህርት መስጠታቸውን ያረጋግጣል።
5. አዋጁ በሁሉም ፓርቲዎች ተፈፃሚ መሆኑን ይከታተላል፣ ያረጋግጣል።
6. አዋጁ ተጥሷል የሚል ቅሬታ ሲቀርብ ከሚመለከታቸው ፓርቲዎች የተውጣጣ አጣሪ ኮሚቴ በማቋቋም ወይም የማጣራት ኃላፊነቱን ራሱ በመውሰድ ጉዳዩን ያጣራል፣ ይመረምራል።
7. ተጣርቶ በተገኘው ውጤት ላይ በመመስረት አስፈላጊውን የመፍትሔ አቅጣጫ ቀይሶ በፓርቲዎቹ የተባበረ ጥረት በተግባር እንዲተረጎም ያደርጋል። በአዋጁ እና በሌሎች የምርጫ አፈፃፀም ጉዳዮች ላይ የተደረሰበትን የጋራ ስምምነት ውሳኔ ለመንግሥትና ለቦርዱ ያቀርባል እንደአስፈላጊነቱም ይህንን በመገናኛ ብዙሃን ይፋ ያደርጋል።
8. ፓርቲዎች በልዩ ልዩ የምርጫ አፈፃፀም እና ሌሎች ዴሞክራሲያዊ፣ ሰብአዊ መብትና የህግ የበላይነት ጉዳዮች ላይ ተገናኝተው እንዲመክሩ ለማድረግ እና የውሳኔ ሃሳብ ለማቅረብ የሚያስችል ቋሚ የስብሰባ ጊዜ ይኖራቸዋል።
9. ከምርጫ ጋር የተያያዙ ደንቦችና መመሪያዎች አስመልክቶ ረቂቅ ሀሳብ በማዘጋጀት ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል።

## ክፍል አምስት

## አቤቱታዎች ወይም አለመግባባቶች ስለሚፈቱበት አሰራር

### 24.አቤቱታ ስለማቅረብ

1. ለምርጫ አስፈፃሚ አካላት ለማቅረብ ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የምርጫ ስነ ምግባር አዋጅ ተጥሷል ብሎ የሚያምን ወገን በማስረጃ የተደገፈ አቤቱታውን ለጋራ ምክር ቤት ማቅረብ ይችላል።
2. በምርጫ ህጉ ለቦርዱ የተሰጠው ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የጋራ ምክር ቤቱ የስነ ምግባር አዋጁ ተጥሷል የሚል አቤቱታ በቀረበለት ጊዜ አቤቱታውን በራሱ ሊያጣራ ወይም መርምሮና አጣርቶ የሚያቀርብ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል።
3. የምርጫ ስነ ምግባር አዋጁ ተጥሷል በሚል አቤቱታ ላይ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እራሱ ወይም በአጣሪ ኮሚቴው አማካኝነት ምርመራ ሲያከናውን ፓርቲዎች፣ እጩ ተወዳዳሪዎችና የሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

### 25.ስለአጣሪ ኮሚቴው አደረጃጀት

1. የስነ ምግባር ጥሰትን አስመልክቶ የቀረበን አቤቱታ እየተከታተለ በማጣራት ሪፖርት የሚያቀርብ አጣሪ ኮሚቴ በየደረጃው ባለ የጋራ ምክር ቤት ይቋቋማል።
2. አጣሪ ኮሚቴው አቤቱታ አቅራቢና አቤቱታ የቀረበበት የፖለቲካ ፓርቲ የሚወክሉበትና በሁለቱ ወገኖች ስምምነት የሚመደብ ሦስተኛ ገለልተኛ አካል የያዘ ይሆናል።
3. አጣሪ ኮሚቴው ተጠሪነቱ ላቋቋመው የጋራ ምክር ቤት ይሆናል።

### 26.አለመግባባት ስለሚፈታበት አሰራር

1. የስነ ምግባር አዋጁ ጥሰት አጋጥሟል በተባለ ጊዜ አቤቱታ አቅራቢው ፓርቲ አቤቱታ ከቀረበበት ፓርቲ ጋር በመነጋገር ችግሩን በስምምነት ለመፍታት ጥረት ያደርጋል።
2. የተከሰተው አለመግባባት በስምምነት መፈታት ካልቻለ ጉዳዩ ለጋራ ምክር ቤቱ ሪፖርት ይቀርባል።
3. የጋራ ምክር ቤት የቀረበለትን ሪፖርት ወይም አቤቱታ መሰረት በማድረግ በቀጥታ በመመርመር ወይም በሚያቋቁመው አጣሪ ኮሚቴ ተጣርቶ ሪፖርት እንዲቀርብለት በማድረግ ችግሩን ይፈታል።

4. የሚደራጀው አጣሪ ኮሚቴ ስራውን በገለልተኝነት ማከናወን አለበት። በአጣሪ ኮሚቴው አባላት መካከል ልዩነቶች ቢከሰቱ የብዙሃኑ ሃሳብ የኮሚቴው ሃሳብ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የሁሉም ሃሳብ ራሱን ችሎ ለጋራ ምክር ቤት መቅረብ አለበት።
5. አጣሪ ኮሚቴው በማጣራቱ ሂደት ያገኘውን መረጃ አጠናቅሮ ተጠሪ ለሆነለት የጋራ ምክር ቤት ብቻ ያቀርባል። የጋራ ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ መረጃው እንዴት ለህዝብ እንደሚገለፅ ይወስናል።
6. የጋራ ምክር ቤቱ ተጠናቅሮ በቀረበለት ሪፖርት ላይ በመመስረት ለችግሩ አግባብነት ያለው መፍትሄ ይሰጣል፣ ውጤቱንም እንደአስፈላጊነቱ ለህዝብ ይፋ ያደርጋል።
7. የጋራ ምክር ቤት አቤቱታ የሚቀበልበትን አሰራር እና አቤቱታው መፍትሄ የሚያገኝበትን የጊዜ ሰሌዳ በማዘጋጀት እንዲታተም ማድረግ አለበት።
8. የጋራ ምክር ቤት በፖለቲካ ፓርቲዎች ስምምነት ተግባራዊ የሚሆን የማስረጃ አቀባበልና አቀራረብ ለማፋጠን አስፈላጊ የሆኑ አሰራሮችን ማዘጋጀት ይችላል።
9. ሁሉም አቤቱታዎች ወይም ቅሬታዎች በአፋጣኝ መጣራት ይኖርባቸዋል።
10. የጋራ ምክር ቤት ወይም አጣሪ ኮሚቴ ለሚመለከታቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሁሉ ፍትሀዊ የመሰማት እድል መስጠት አለበት።
11. የጋራ ምክር ቤት ውሳኔ የሚተላለፈው በጋራ መግባባት ወይም በተባበረ ድምፅ ይሆናል።

## ክፍልስድስት

## የስነ ምግባር አዋጅ ጥሰቶች እና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

### ንዑስ ክፍል አንድ የስነ-ምግባር ጥሰቶች

27. **መደለያ ስለመስጠት፣ ኃይል ወይም ሥልጣን አለአግባብ ስለመጠቀም**

ማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፦

1. ማንኛውንም መደለያ ወይም ጉቦ የሰጠ ወይም የተቀበለ፤
2. በድምጽ አሰጣጡ ወይም በቆጠራው ጣልቃ የገባ ወይም ያወከ፤

3. ኃይል በመጠቀም፣ መደለያ በመስጠት ወይም በሌላ በማንኛውም አድራጎት መራጩ ሕዝብ ለአንድ ፓርቲ ወይም እጩ ድምጽ እንዲሰጥ ወይም እንዳይሰጥ ወይም ከመስጠት እንዲታቀብ ያደረገ፤
4. የድምጽ መስጫ ጣቢያን በሀይል የተቆጣጠረ ወይም ሕገ-ወጥ መንገድ በመጠቀም ድምጽ ለማግኘት የሞከረ፣
5. ሥልጣኑን መከታ በማድረግ መደለያ ወይም ቅጣት ወይም ሌላ የማስፈራሪያ ዘዴ የተጠቀመ፤
6. ማንኛውንም መደለያ በመስጠት ኃይል በመጠቀም፣ ወይም በማንኛውም አይነት ድርጊት እጩ ተወዳዳሪ ሆነው እንዲቀርቡ ወይም እንዳይቀርቡ ወይም ከእጩ ተወዳዳሪነት እንዲወጡ ወይም እንዳይወጡ ያደረገ፤
7. የመንግሥት ሰራተኛ እና ኃላፊ ሆኖ በራሱ የግል ጊዜ ካልሆነ በስተቀር በመንግስት የስራ ሰዓት እና ኃላፊነት ተቋሙን በመጠቀም እጩዎችን ያስተዋወቀ ወይም ሌሎች እጩዎች እራሳቸውን በሕጋዊ መንገድ ለማስተዋወቅ ያላቸውን እድል ያደናቀፈ፤
8. የመንግሥት ንብረት ለምርጫ ቅስቀሳ የተጠቀመ፤

እንደሆነ የስነምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል።

28.<u>**በምርጫ ሂደት ውስጥ ፍርሃት ወይም ሁከት መፍጠር እንዲሁም ማንኛውንም የምርጫ እንቅስቃሴ ማስተጓጎል**</u>

ማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፦

1. በምርጫ ሂደት ጫና ወይም ተጽዕኖ በመፍጠር ጣልቃ የገባ፤
2. ሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ሀሳባቸውን በነጻነት እንዳያሰራጩ ስጋት እና ፍርሀት የፈጠረ፤
3. በማንኛውም መንገድ የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የመራጩን ሕዝብ እቅንስቃሴ ያደናቀፈ ወይም ያወከ፤
4. ሕዝባዊ ቅስቀሳ ወይም ስብሰባ ወይም ውይይት ወይም ትምህርትና ስልጠና እንዳይካሄድ ያደናቀፈ ወይም ሁከት የፈጠረ፤
5. ሕዝብ ድምጽ ሲሰጥ ያወከ ወይም ድምጽ እንዳይሰጥ ችግር የፈጠረ፤

6. የሌሎች ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ ዘመቻ እንዲስተጓጐል ወይም እንዲቋረጥ ወይም እንዲበላሽ ወይም እንዲዳከም ያደረገ፤
7. ሕዝባዊ የድጋፍ ሰልፍ፣ ስብሰባ፣ የእግር ጉዞ ወይም ሰላማዊ ሰልፍ ያደናቀፈ፣ ወይም ሌላ ሰው እንዳይሳተፍ የከለከለ፣
8. መራጮችን ያበሳጨ ወይም የመምረጥ መብታቸውን ያደናቀፈ፤
9. ለምርጫው ሂደት የምርጫ አስፈፃሚዎችን እና የዕጩ ተወዳዳሪዎችን ፀጥታና ደህንነት እንዲረጋገጥ እገዛ ያላደረገ ወይም ያወከ፤
10. በማንኛውም አይነት መንገድ መራጩ ህዝብ እንዳይመዘገብ ወይም እንዳይመርጥ ያደረገ፤
11. የድምጽ አሰጣጡን ሚስጥራዊነት ያላከበረ ወይም እንዲከበር እገዛ ያላደረገ ፤
12. የሥነ-ምግባር አዋጁ ተጥሷል በሚል ሽፋን የሀሰትና የተጋነነ አቤቱታ በማቅረብ ቅሬታ የማሰማት መብቱን ያለአግባብ የተጠቀመ፤

እንደሆነ የሥነ-ምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል።

29.<u>**በምርጫ ሂደት ሰላምና ፀጥታ የሚያናጉ መልዕክቶችን ስለማስተላለፍ**</u>

ማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ:-

1. የምርጫ ዘመቻውን ሰላም የሚያናጋ ወይም ግጭት የሚቀሰቀስ ወይም ስም የሚያጠፋ ወይም አመፅ የሚጋብዝ ወይም ስጋት የሚፈጥር ንግግር ያደረገ፤
2. በይፋም ሆነ በስውር አመፅን የሚቀሰቅስ ወይም የሚያስፈራራ ቋንቋ ይዘት ያለው በራሪ ወረቀት፣ የዜና መጽሔቶች ወይም ፖስተር ያሰራጨ፤
3. በምረጡኝ ቅስቀሳ ወቅት በህዝቡ ላይ የፍርሃት እና የጭንቀት ሁኔታ የፈጠረ፤
4. የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ሚስጥራዊ እንደማይሆን የሀሰት መረጃ የሰጠ፤እንደሆነ የስነምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል።

## 30. የሌሎች የፖለቲካ ፓርቲዎች ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች የምርጫ እንቅስቃሴ ስለማደናቀፍ

ማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፡-

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ አባል እንዳይመለምልና ጽህፈት ቤት እንዳይከፍት በማናቸውም መንገድ ያደናቀፈ፣ ወይም የተከፈቱ ጽህፈት ቤቶች በነፃነት እንዳይንቀሳቀሱ በግልፅም ሆነ በስውር ያወከ ወይም ሁከት እንዲፈጠር ያደረገ ወይም በማንኛውም ዓይነት ድርጊት የማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ የምርጫ እንቅስቃሴ ያደናቀፈ፤
2. ፓርቲዎች ልሳኖቻቸው፣ የምርጫ ማስታወቂያዎቻቸው፣ በራሪ ጹሁፎቻቸው፣ ፖስተሮቻቸው እንዳይሰራጩ፣ እንዳይታዩ ወይም እንዲበላሹ ያደረገ ወይም እንዳይለጠፉ ያወከ ወይም የተለጠፉትን የቀደደ፣ ያበላሸ፣ ያጠፋ፤
3. የሌሎች የፖለቲካ ፖርቲዎች ምልክቶች ወይም አርማ የቀዳ ወይም አስመስሎ የተጠቀመ፤
4. የሌሎች ፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ቁሳቁስ የሰረቀ ወይም ያበላሸ ወይም ያጠፋ፤

እንደሆነ የስነምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል።

## 31. ከጋዜጠኞችወይም ከታዛቢዎችጋር አለመተባበር

ማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፡-

1. የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን የተጋፋ፣
2. በምርጫ ሂደት ጋዜጠኞችን ያዋከበ ወይም ስራቸውን ያደናቀፈ፣
3. የታዛቢነት ፈቃድ ያላቸውን ታዛቢዎች ያላከበረ ወይም ያልተባበረ፣

እንደሆነ የስነምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል።

## 32. የሥነ-ምግባር ደንቡን አለማስተዋወቅና ህገ ወጥ ድርጊቶች አለማውገዝ

ማንኛውም ፖለቲካ ፓርቲ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅት፣ ግንባር፣ ጥምረት፣ ንቅናቄ፣ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲ መሪ፣ ኃላፊ፣ እጩ፣ አባል፣ ወኪል ወይም ተጠሪ፡-

1. አመፅን ወይም ለአመፅ የሚጋብዙ ወይም የህዝብን ሰላም የሚያናጉ ድርጊቶች በይፋ ያላወገዘ ወይም ተቃውሞ ያላስተማረ፤
2. ለእጩ ተወዳዳሪዎቹ፣ ለአባላቱ፣ ለደጋፊዎቹና ለሕዝቡ ስለ ምርጫውና ስለ ሥነ-ምግባር አዋጁ ያላስተዋወቀ ወይም ያላስተማረ፤
3. መሪዎቹ፣ ኃላፊዎቹ፣ እጩዎቹና አባላቱ ይህን የስነምግባር አዋጅ እንዳይጥሱ ቁርጠኛ እርምጃ ያልወሰደ ወይም ደጋፊዎቹ የተከለከለ ተግባር ፈጽመው ሲገኙ ያላወገዘ ወይም አግባብነት ያለው እርምጃ ያልወሰደ፤
4. ኃላፊዎች፣ ተወዳዳሪዎች፣ አባላትና ደጋፊዎች ማንኛውም ሰው በየትኛውም ጊዜ ማስፈራራት እንደሌለባቸው በግልጽ የሚከለክል መመሪያ ያላወጣ ፤

እንደሆን የስነምግባር ጥሰት እንደፈጸመ ይቆጠራል፡፡

## ንዑስ ክፍል ሁለት

## በተለያዩ አካላት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

### 33.በጋራ ምክር ቤት ስለሚወሰዱ የመፍትሔ እርምጃዎች

የጋራ ምክር ቤቱ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፡-

1. ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ የፖለቲካ ፓርቲ ስህተቱን እንዲያርም ወይም እንዲያስተካክል ውሳኔ ያስተላልፋል፤
2. የሥነምግባር አዋጁን የጣሰውን የፖለቲካ ፓርቲ ስም እና ተግባር ጠቅሶ ለህዝብ እንዲጋለጥ ያደርጋል። ውሳኔውን በጋዜጣ፣ በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን ወይም በሌላ አመቺ በሆነ የመገናኛ ዘዴ ህዝቡ እንዲያውቀው ያደርጋል፤
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ በተደነገገው የመፍትሔ እርምጃ ያልረካ ወገን ቅሬታውን በምርጫ ህጉና በዚህ አዋጅ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት ማቅረብ ይችላል፤
4. በጋራ ምክር ቤቱ የሚሰጡት የመፍትሔ እርምጃዎች በጥሰቱ ጉዳት የደረሰበት ወገን በፍትሐ ብሔር ወይም በወንጀል ለመጠየቅ ያለውን መብት ሊያስቀሩ አይችሉም።

### 34.በቦርዱ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች

በዚህ አዋጅ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ /1/ እና /2/ የተዘረዘሩና በሌሎች ህጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ ከላይ በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል አንድ

የተዘረዘሩትን የስነ ምግባር ጥሰት በሚያረጋግጥበት ጊዜ የሚከተሉትን እርምጃዎች እንደሁኔታው ሊወስድ ይችላል።

1. ጥፋቱን ለፈፀመው ሰው ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ይፋ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤
2. ጥፋቱን የፈፀመ እጩ ወይም ፓርቲ ለአጭር ጊዜ በከፊል ወይም በሙሉ በሕዝብ መገናኛ ብዙሃን እንዳይጠቀም ማድረግ፤
3. ጥፋቱን የፈፀመ ፓርቲ በመንግስት ከሚሰጠው የፓርቲ ፋይናንስ ድጎማ ተጠቃሚ እንዳይሆን ማድረግ፤
4. ማንኛውንም በፓርቲ ወይም በግል የቀረበ እጩን እንደ ጥፋቱ ክብደት ከምርጫ ተወዳዳሪነት መሰረዝ፤
5. የፖለቲካ ፓርቲው በምርጫ ውድድር እንዳይሳተፍ ማገድ፡፡

35.<u>በፍርድ ቤት ስለሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

1. ፍርድ ቤት ከላይ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 34 የተደነገጉትን እርምጃዎች ከዚህ ቀጥለው ከተዘረዘሩት ቅጣቶች ወይም ክልከላዎች ጋር በተደራቢነት ሊወሰድ ይችላል።
2. በሌሎች ህጎች የተደነገጉት እንደተጠበቁ ሆኖ በድምፅ መስጫ እለት በድምፅ መስጫ ጣቢያ አካባቢ ድምፅ ከመስጠት ወይም የተሰጠን ህጋዊ ተግባር ከማከናወን ውጭ ሌላ ማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ፣ መሳተፍ፣ ወይም በተከለከለው ጊዜ ውስጥ የምርጫ ውጤትን ማተም፣ ማባዛት፣ ወይም በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 27፣28፣ እና/ወይም ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥፋቶች መፈፀም በገንዘብ መቀጮ ወይም እስከ ሦስት ዓመት በሚደርስ እስራት ያስቀጣል።

   ሀ/ በቦርዱ ወይም በምርጫ አስፈፃሚዎች ገለልተኝነት ጣልቃ የገባ፣ መደለያ ወይም የተስፋ ቃል በመስጠት አንድ ሰው ተግባሩን እንዳያከናውን ያደረገ፤

   ለ/ ምርጫን ለማወክ ወይም እንዳይካሄድ ለማድረግ ወይም በምርጫው ሂደት ወይም ውጤት ላይ ጫና ለመፍጠር በማሰብ ጥላቻን ወይም ፍርሀትን የሚያሰፍን ወይም በምርጫው ሂደት ወይም በምርጫው ውጤት ላይ ጫና የሚፈጥር የሐሰት መረጃ ያሳተመ፤

   ሐ/ የምርጫ ሚስጥራዊነትን የጣሰ፤

   መ/ ከድምፅ እና ከምርጫ ቁሳቁስ ጋር የተያያዙ ክልከላዎችን የተላለፈ፤ ወይም

   ሠ/ የቦርዱን ወይም የምርጫ አስፈፃሚዎችን እንቅስቃሴ ያወከ፡፡

3. ፍርድ ቤት የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ወይም የምርጫ ውጤት አገላለፅ፣ የመራጮች ወይም የፓርቲዎች መብት ወይም ማስመሰል አስመልክቶ የተባሉ ክልከላዎችን የጣሰ ወይም ሐሰት መሆኑን እያወቀ ወይም እውነት ስለመሆኑ በቂ ምክንያት ሳይኖረው ንግግር የሚያደርግ ሰው በገንዘብ መቀጮ ወይም ከአንድ አመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

4. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ ሆን ብሎ የቦርዱ፣ የምርጫ ዋና አስፈፃሚው፣ የቦርዱ ሰራተኛ ስልጣኑን ወይም ተግባሩንና ኃላፊነቱን በሚያከናውንበት ወቅት እንቅፋት የሆነ ወይም ያደናቀፈ እንደሆነ፤

ለ/ የቦርዱን የስብሰባ ሂደት ሆን ብሎ ያቋረጠ ወይም በነዚሁ ቦታዎች በማንኛውም ሁኔታ ያልተገባ ተግባር የፈፀመ እንደሆነ፤

ሐ/ ሆን ብሎ በቦርዱ የስራ ቦታ ወይም በመታየት ላይ ባለ ጉዳይ ላይ በሚሰጠው ውሣኔ ወይም ትዕዛዝ ላይ ተገቢ ያልሆነ ተጽእኖ ለማሳደር ሲባል ማንኛውም ተግባር የፈፀመ፤ ወይም

መ/ ከላይ በዚህ ክፍል ንዑስ ክፍል አንድ አንቀጽ 30 ወይም 31 የተደነገጉትን ጥፋቶች የፈፀመ እንደሆነ፤

በገንዘብ ወይም ከአንድ ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

## ክፍል ሰባት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 36.<u>የመተባበር ግዴታ</u>

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት።

### 37.<u>ደንብ ወይም መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ቦርዱ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የሚረዳ ደንብ ወይም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

### 38.<u>ተፈጻሚነት የሌላቸው ህጎች</u>

ማንኛውም ህግ ወይም አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

### 39.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከታህሣሥ 13 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ታህሣሥ 24 ቀን 2002 ዓ.ም.

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ፕሬዚዳንት

## አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም

## የተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርጫ ህግ አዋጅ

የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች በማንኛውም ሁኔታ ልዩነት ሳይደረግባቸው በቀጥታ እና በነፃነት በመረጧቸው ተወካዮች አማካኝነት ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር ስልጣናቸውን በተግባር ላይ ማዋል አስፈላጊ በመሆኑ፤

ማንኛውም የምርጫ እንቅስቃሴ ዓለምአቀፍ የምርጫ መርሆዎችን አካትቶ በያዘ ህግ እንዲመራ ማድረጉ አስፈላጊ በመሆኑ፤

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ በየደረጃው በሚካሄዱ ሁሉአቀፍ በእኩልነት ላይ የተመሰረተና በሚስጢር ድምፅ አሰጣጥ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልፅበት ነፃ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ምርጫ፣ በገለልተኝነት የሚያስፈፅም ተቋም ማቋቋም አስፈላጊ በመሆኑ፤

የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች የሚሳተፉበት እና አላማቸውን በሰላማዊና ህጋዊ መንገድ ለመራጩ ህዝብ የሚገልፁበት መራጩ ህዝብ በመረጃ ላይ በመመስረት ፈቃዱን በነፃነት በመግለፅ ወኪሎቹን የሚመርጥበት የምርጫ ስርአት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በምርጫው ተሳታፊ የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶችም ሆኑ የግል ዕጩዎች ለፍትሃዊ፣ ሰላማዊ፣ ነፃና ዲሞክራሲያዊ የምርጫ ስርአት መስፈን ገንቢ አስተዋጽኦ የሚያደርጉበት ግልፅ አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በምርጫ ሂደት የሚከሰቱ አለመግባባቶች የሚፈቱበት የጋራ የምክክር መድረክና ሌሎች አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጡ ተቋማትን ማቋቋምና ቅሬታዎች በየደረጃው በይግባኝ የሚታዩበት ግልፅና ቀልጣፋ ስርአት መዘርጋት ተገቢ በመሆኑ፤

በህገመንግስቱ አንቀፅ 55 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 102 መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

# ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ አዋጅ "የተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፤

1. "ኢፌዲሪ" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ነው።
2. "ህገ መንግስት" ማለት የኢፌዲሪ ህገመንግስት ነው።
3. "ክልል" ማለት በህገመንግስቱ አንቀፅ 47 መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም ሲባል አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ይጨምራል።
4. "ምርጫ" ማለት በፌዴራልና በክልል ህገመንግስታት እንዲሁም በሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት የሚካሄድ የጠቅላላ፣ የአካባቢ፣ የማሟያ ወይም የድጋሚ ምርጫ ነው።
5. "ጠቅላላ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው።
6. "የአካባቢ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የሚካሄድ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የማዘጋጃ ቤት፣ የክፍለ ከተማ ወይም የቀበሌ[6] ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው።
7. "ማሟያ ምርጫ" ማለት በይውረድልን ወይም በማንኛውም ምክንያት በየደረጃው የሚገኙ የተጓደሉ የምክር ቤት አባላት መቀመጫዎችን ለማሟላት የሚካሄድ ምርጫ ነው።
8. "ድጋሚ ምርጫ" ማለት በዚህ ህግ መሰረት ቦርዱ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወስን ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን መለየት በማይቻልበት ጊዜ የሚካሄድ ምርጫ ነው።
9. "ህዝበ ውሳኔ" ማለት በኢ.ፌ.ዴ.ሪ ህገመንግስት መሰረት ሲወሰን የህዝብ ፍላጎትን ለመለካት እና የህዝብን ውሳኔ ለማወቅ ድምፅ የሚሰጥበት ስርዓት ነው።

[6] ለአዲስ አበባ ከተማ አላማ ቀበሌ የሚል አደረጃጀት ስለሌለ የመጨረሻ እርከን በሆነው ወረዳ ተተክቶ ሀሳብ አለበት፡፡

10.“የመራጮች መዝገብ” ማለት በየደረጃው ለሚካሄድ ምርጫ መራጩ ህዝብ በምርጫ ጣቢያው በመራጭነት የሚመዘገብበት መዝገብ ነው።

11.“የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ” ማለት አንድ ሰው በመራጭነት ከተመዘገበ በኋላ በምርጫ ጣቢያው የሚሰጠው የተመዝጋቢነት መታወቂያ ነው።

12.“የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ፓርቲ” ማለት የፖለቲካ ፕሮግራሙን በህጋዊ መንገድ ለማራመድ በህግ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ቡድን ነው።

13.“የምርጫ ክልል” ማለት ለምርጫ አፈፃፀም እንዲያመች እና ህዝቡ ወኪሎቹን እንዲመርጥ በህግ መሰረት የሀገሪቱ ግዛት ተከፋፍሎ የሚደራጅ የምርጫ አካባቢ ነው።

14.“የምርጫ ጣቢያ” ማለት በየደረጃው በሚካሄዱ ምርጫዎች ምዝገባ የሚካሄድበት፣ መራጮች ድምፅ የሚሰጡበት እና ቆጠራ የሚካሄድበት ቦታ ነው።

15.“ታዛቢ” ማለት የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢና የውጭ የምርጫ ታዛቢን ያካትታል።

16.“የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ” ማለት በህግ የተመዘገበ እና ለማንም ያልወገነ ገለልተኛ ሀገር በቀል ድርጅት ሆኖ ከቦርዱ በሚሰጠው ፈቃድ መሰረት በሚወክለው ሰው ምርጫን የሚታዘብ አካል ነው፡፡

17.“የውጭ የምርጫ ታዛቢ” ማለት አገሪቱ በተቀበለቻቸው ስምምነቶች መሠረት ወይም መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ምርጫን እንዲታዘቡ የሚጋብዛቸው መንግስታት ወይም ዓለምአቀፍ፣ አህጉራዊ፣ ክፈለአህጉራዊ የሆኑና በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ናቸው።

18.“የህዝብ ታዛቢ” ማለት በእያንዳንዱ ምርጫ ክልል እና ምርጫ ጣቢያ ምርጫን እንዲታዘቡ በህዝብ የሚመረጡ ገለልተኛ የአካባቢ ነዋሪዎች ናቸው።

19.“ተቀማጭ ወኪል” ማለት በምርጫ ለመወዳደር በተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ የሚወክልና በምርጫ ክልልና በምርጫ ጣቢያ ተቀምጦ የምርጫ ሂደትንና የወከለውን አካል መብት መከበርን የሚከታተል ሰው ነው።

20.“ተንቀሳቃሽ ወኪል” ማለት በምርጫ ለመወዳደር በተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም በግል እጩ ተወክሎ በአንድ ምርጫ ክልል ውስጥ በሚገኙ የምርጫ

ጣብያዎች እየተንቀሳቀሰ የምርጫ ሂደት እና የወከለውን ድርጅት ወይም የግል ዕጩ መብት መከበር የሚከታተል ሰው ነው፡፡

21.“አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ” ማለት በየደረጃው በሚገኝ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት፣ ምርጫ ክልል እና የምርጫ ጣብያ ለሚነሱ ቅሬታዎች አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥ በዚህ አዋጅ መሰረት ለምርጫ ወቅት የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፡፡

22.“ጽህፈት ቤት” ማለት የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ ጽ/ቤት ነው፡፡

23.ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ ለጠቅላላ ምርጫ እንዲሁም እንዳግባብነቱ ለአካባቢ ምርጫ፣ ለማሟያ ምርጫ፣ ለድጋሚ ምርጫ እና በህገመንግስቱ መሰረት ለሚካሄድ ህዝበ ውሳኔ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለምርጫ ቦርድ በጠቅላላ</u>

### <u>ምዕራፍ አንድ</u>

### <u>ስለምርጫ ቦርድ</u>

4. <u>መቋቋም</u>

1. ተጠሪነቱ ለኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሆነ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ /ከዚህ በኋላ “ቦርድ” እየተባለ የሚጠራ የህግ ሰውነት ያለው ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ የሆነና እራሱን የቻለ የምርጫ አስፈፃሚ አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. የቦርዱ ዋና ጽህፈት ቤት አዲስ አበባ ይሆናል፡፡ ቦርዱ የምርጫን ስራ ለማስፈፀም ከፌዴራል እስከ ምርጫ ጣቢያ መዋቅሩን በመዘርጋት ቋሚ እና ጊዜያዊ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ይኖሩታል።

5. <u>ዓላማ</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል።

1. ህገመንግስቱን መሰረት በማድረግ ነፃ፣ ገለልተኛና ፍትሃዊ ምርጫ በማካሄድ በህዝብ ድምፅ የተመረጠ መንግስት እንዲቋቋም ማድረግ፣
2. ህገመንግስቱን እና በህግ የተመሰረቱ ተቋማትን የሚያከብሩ የፖለቲካ ድርጅቶች እና ግለሰቦች በእኩልነትና ያለአድልዎ የሚወዳደሩበት የምርጫ ሂደት መኖሩን ማረጋገጥ፣

3. ዜጎች በህገመንግስቱ በተጎናፀፉት የዴሞክራሲ በተለይም ደግሞ የመምረጥና የመመረጥ መብት በነፃነትና በእኩልነት እንዲጠቀሙ ማድረግ፣

6. የቦርዱ አባላት

1. ቦርዱ በህገ መንግስቱ አንቀፅ 102 መሰረት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሾሙ ዘጠኝ አባላት ይኖሩታል።
2. ጠቅላይ ሚኒስትሩ መስፈርቱን የሚያሟሉ ሰዎችን ለቦርድ አባልነት ለምክር ቤት ከማቅረቡ በፊት በምክር ቤቱ መቀመጫ ያላቸው ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች እጩ ሊሆኑ የሚችሉ ግለሰቦች ነፃና ገለልተኛ መሆናቸውን በማረጋገጥ ጉዳይ ላይ ተሳትፎ እንዲኖራቸው የሚያስችል በቂ የምክክር መድረክ እንዲኖር ያደርጋል፡፡
3. የቦርዱ አባላት ጥንቅር ብሔራዊ ተዋፅኦን እና የሴቶችን ተሳትፎ ከግምት ውስጥ ያስገባ ሆኖ ከአባላቱ መካከል ቢያንስ አንዱ የህግ ባለሞያ መሆን አለበት፡፡ አባላቱም፡-

   ሀ/ ለህገመንግስቱ ታማኝ የሆኑ፣

   ለ/ ከፖለቲካ ድርጅቶች ወገንተኝነት ነፃ የሆኑ፣

   ሐ/ የሞያ ብቃት ያላቸውና፣

   መ/ በመልካም ስነምግባራቸው የሚታወቁ መሆን ይገባቸዋል።
4. የቦርዱ አባላት የስራ ዘመን አምስት አመት ሆኖ ማንኛውም የቦርድ አባል ለተጨማሪ አንድ የስራ ዘመን ብቻ በድጋሚ ሊያገለግል ይችላል፡፡
5. ከላይ በንኡስ አንቀፅ 4 የተደነገገው ቢኖርም አባሉ በራሱ ምክንያት ከለቀቀ ወይም የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አንድ የቦርድ አባል፡-

   ሀ/ በህመም ምክንያት ተግባሩን በተገቢው ሁኔታ ማከናወን አይችልም ወይም

   ለ/ ከባድ የስነምግባር ጉድለት ታይቶበታል ብሎ ሲያምን ከቦርድ አባልነት ሊያሰናብተው ይችላል፡፡
6. ምክር ቤቱ ከላይ በንኡስ አንቀፅ 5 የተደነገገውን ውሳኔ ሲያስተላልፍ በህገመንግስቱ መሰረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሌላ እጩ እንዲያቀርብ ያዛል።
7. የቦርዱ ሰብሳቢ እና ምክትል ሰብሳቢ ከአባላቱ መካከል በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሰየማሉ።
8. የቦርዱ ጽህፈት ቤት ዋና ኃላፊ ድምፅ የመስጠት መብት ሳይኖረው የቦርዱ ፀሐፊ ይሆናል።

## 7. የቦርዱ ስልጣንና ተግባር[7]

ቦርዱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. በህገመንግስቱ እና በዚህ አዋጅ መሰረት የሚካሄድ ማንኛውንም ምርጫ እና ህዝበ ውሳኔ በገለልተኝነት የማስፈፀም፣
2. በየደረጃው እና በየጊዜው የሚካሄዱ ምርጫዎች ነፃና ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የሚካሄዱበትን ሁኔታ የማመቻቸት እና የማረጋገጥ፣
3. ምርጫን ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ቁሳቁሶች የማዘጋጀትና የማሰራጨት፣
4. ምርጫን አስመልክቶ ለህዝቡ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት በስፋት የመስጠት እና ትምህርት ለሚሰጡ አካላት ፈቃድ የመስጠት፣ የመከታተልና የመቆጣጠር፣
5. ለምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ የመስጠት፣ የመከታተልና የመቆጣጠር፣
6. የፖለቲካ ድርጅቶችን የመመዝገብ፣ ፈቃድ የመስጠት፤ በህጉ መሰረት የመከታተልና የመቆጣጠር፣
7. በየእርከኑ ለሚካሄዱ ምርጫዎች አፈፃፀም የሚያስፈልጉ የምርጫ አስፈፃሚ ጽህፈት ቤቶችን የሙያ ብቃት ባለው ገለልተኛ የሰው ሃይል በቋሚነት፣ በጊዜያዊነት ወይም በኮንትራት የማደራጀትና ከሌሎች ተቋማት በትውስት በመውሰድ የማሰማራት እንዲሁም የምርጫ አስፈፃሚዎችን የማሰልጠን፣
8. በየጊዜው የሚደረጉትን ምርጫዎች አፈፃፀምና የምርጫ ህጎች የመገምገም፣ ጥናት የማካሄድ፣ ስታቲስቲካዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ እና የማጠናቀር ማሻሻያ የሚያስፈልጋቸውን ጉዳዮች ለይቶ ለሚመለከተው አካል የማቅረብ፣ እንዲሁም ማናቸውንም የምርጫ ሰነዶች በአግባቡ እንዲያዙ የማድረግ፣
9. የፖለቲካ ድርጅቶችን የጋራ መድረክ የማደራጀትና የማስተባበር፣
10. በምርጫ ሂደት የተፈፀመ የህግ መጣስ፣ የማጭበርበር፣ ወይም የሰላምና ፀጥታ ማደፍረስ ድርጊት በስፋቱና በዓይነቱ የምርጫውን ውጤት እንደሚያዛንፍ ከተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶች፣ ከግል እጩዎች፣ ከታዛቢዎች፣ ከምርጫ አስፈፃሚዎች ወይም ከሌላ ከማንኛውም ምንጭ መረጃ ደርሶት ተጨባጭነቱን በራሱ ማጣራት ሲያረጋግጥ ወይም ተፈፅሟል ብሎ በራሱ ሲያምን ሁኔታውን

---

[7] የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድ በአዋጅ በ16/7(2002) አ.662 አንቀፅ 18 ስር ስነ-ምግባርን አስመልክቶ ተጨማሪ ስልጣን እና ተግባር ተሰጥቶታል፡፡

የመመርመር፣ ውጤቱን የመሰረዝና አዲስ ምርጫ እንዲካሄድ ወይም ድርጊቱ እንዲቆም የማዘዝ፣ ጥፋተኞች በህግ እንዲጠየቁ የማድረግ፣

11. በምርጫ ሂደት ለተከሰቱ አለመግባባቶች አስተዳደራዊ መፍትሄ የመስጠት፡ የምርጫ ጉድለቶችን የማረምና ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ውሳኔ የመስጠት፣
12. የምርጫ ውጤቶችን የማረጋገጥና በይፋ የማሳወቅ፣
13. በጀት አዘጋጅቶ የማቅረብና ሲፈቀድም በስራ ላይ የማዋል፣
14. እንደአስፈላጊነቱ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት የምርጫ አስፈፃሚዎችን በመመልመልና በመመደብ የማንቀሳቀስ፣
15. የምርጫ አስፈፃሚዎች በምርጫ ስራቸው ምክንያት ሊደርስባቸው ከሚችል ተፅዕኖ መከላከል፣ በምርጫ ስራ በመሳተፋቸው መብትና ጥቅማቸው እንዳይጓደልባቸው መጠበቅና መከላከል፣
16. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር በየደረጃው የሚካሄዱ ምርጫዎች የጊዜ ሰሌዳ የማውጣት፣ የማሻሻል፣ የመለወጥ በወቅቱ ለህዝብ ይፋ የማድረግ፣
17. ስለ ስራው እንቅስቃሴ በየጊዜው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት የማቅረብ፤
18. በየደረጃው የሚገኙ የቦርድ ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች ሠራተኞችን የስራ አፈፃፀም የመቆጣጠር፣ የመከታተል አስፈላጊ እርምጃም የመውሰድ፣
19. ምርጫውን ግልፅ፣ ነፃና ፍትሃዊ ለማድረግ የሚረዳ ደንብ ወይም መመሪያ የማውጣት፣
20. የጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ ስራውን ማከናወን ሳይችል ሲቀርና ውክልና መስጠት በማይችልበት ጊዜ ሌላ ኃላፊ እስከሚሾም ቦርዱ ከምክትል ዋና ኃላፊዎች አንዱን በውክልና እንዲሰራ የማድረግ፣
21. በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን በምርጫ የሚሳተፉበትን ሁኔታ አጥንቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ፣
22. ህገ መንግስቱ አንቀጽ 61 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የክልል ምክር ቤት የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላትን በቀጥታ ከህዝብ እንዲመረጡ ሲወስን ምርጫ የማካሄድ፣
23. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያግዙ ተመሳሳይ ተግባራትን የማከናወን።

8. <u>የቦርዱ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>

የቦርዱ ሰብሳቢ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. የቦርዱን ስብሰባ ይጠራል፤ ይመራል፡፡

2. የቦርዱ ውሳኔዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፡፡
3. የቦርዱ ጽህፈት ቤት ዋና ኃላፊን የስራ እንቅስቃሴ በበላይነት ይቆጣጠራል።
4. የፖለቲካ ድርጅቶችን የጋራ መድረክ በሰብሳቢነት ይመራል፡፡
5. የቦርዱ ጽህፈት ቤት ዋና ኃላፊ የስራ ግድፈት ሲፈፅም እርምጃ እንዲወሰድበት የውሳኔ ሃሳብ ለቦርዱ ያቀርባል። ውሳኔውንም ተግባራዊ ያደርጋል።
6. ከሀገር ውጭ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት በበላይነት ይመራል፤ እንዳስፈላጊነቱም የጽህፈት ቤቱን ዋና ኃላፊ ሊወክል ይችላል።
7. ማንኛውም የቦርዱን ወይም የጽህፈት ቤቱን የስራ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል፤ወይም የጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ እንዲያቀርብ ሊወክል ይችላል፡፡

9. <u>**የቦርዱ ምክትል ሰብሰቢ ስልጣንና ተግባር**</u>

የቦርዱ ምክትል ሰብሳቢ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

1. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል።
2. ሰብሳቢው በማናቸውም ምክንያት ስራውን ለመስራት ካልቻለ ሌላ ሰብሳቢ በዚህ አዋጅ መሰረት እስኪሰየም ድረስ ሰብሳቢ ሆኖ ያገለግላል።
3. ሰብሳቢው ለይቶ የሚሰጠውን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

10.<u>**የቦርዱ የስብሰባ ስነስርዓት**</u>

1. ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ በመደበኛነት ይሰበሰባል፤ ሆኖም ምርጫ በሚካሄድበት ወቅት ከወር ባነሰ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡
2. የቦርዱ ሰብሳቢ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
3. ከቦርድ አባላት መካከል 1/3ኛው ስብሰባ እንዲጠራ ሲፈልጉ ሰብሳቢው አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፡፡
4. ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይሆናል፡፡
5. የቦርዱ ውሳኔ በአባላት ድምፅ ብልጫ ይወሰናል፣ ሆኖም ድምፅ እኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው የደገፈው ሃሳብ የቦርዱ ውሳኔ ይሆናል፡፡
6. ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ስነ-ስርዓት ደንብ ያወጣል።

11.<u>**የቦርዱ አባላት መብት**</u>

ማንኛውም የቦርዱ አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፤

1. በማንኛውም የቦርዱ ስብሰባዎች የመሳተፍና ድምፅ የመስጠት፣
2. የቦርዱን ሰነዶች የመመልከት፣
3. የቦርዱን ስብሰባ ጥሪ እና አጀንዳ በወቅቱ እና በአግባቡ የማግኘት፣

4. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 10(3) መሰረት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ የመጠየቅ፣
5. ያለምንም ተፅእኖ እና ጣልቃ ገብነት ስራውን የማከናወን፣ እና
6. በቦርድ አባልነቱ ሊያገኝ የሚገባውን ክፍያ የማግኘት፡፡

12. **<u>የቦርዱ አባላት ስነምግባር</u>**

ማንኛውም የቦርድ አባል፡-

1. የተሰጠውን ሀላፊነት በገለልተኝነት፣ በነፃነትና በቅን ልቦና ማከናወን አለበት፡፡
2. ማንኛውንም በምርጫ የሚሳተፍ የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ የግል ዕጩ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በመደገፍም ሆነ በመቃወም መንቀሳቀስ የለበትም፡፡
3. በቦርድ አባልነቱ ምክንያት ባገኘው ሚስጥራዊ መረጃ ጥቅም ለማግኘት መንቀሳቀስ የለበትም፡፡
4. የቦርዱን ሚስጥር ለ3ኛ ወገን አሳልፎ መስጠት ወይም ማባከን የለበትም፡፡
5. በማንኛውም ሁኔታ የቦርዱን ወይም የአባሉን ተአማኒነት፣ ገለልተኝነትና ነፃነት ከሚጎዳ ወይም ከሚያጎድፍ ማንኛውም ተግባር መቆጠብ አለበት፡፡

13. **<u>የቦርዱ አባላት የጥቅም ግጭት</u>**

1. አንድ የቦርድ አባል የተሰጠውን ኃላፊነት በፍትሃዊነትና በገለልተኝነት በአግባቡ ከማከናወን የሚያግደው እና በቦርዱ በመታየት ላይ ካለ ማንኛውም ጉዳይ ጋር የተያያዘ የገንዘብ ወይም የሌላ ጥቅም ግንኙነት ያለው መሆኑ ሲረጋገጥ በዚሁ ስብሰባ ወይም ተግባር መገኘት፣ ድምፅ መስጠት ወይም በሌላ በማንኛውም ሁኔታ መሳተፍ የለበትም፡፡
2. ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው የጥቅም ግጭት መኖሩ የታወቀው ጉዳዩ ወይም ተግባሩ በቦርዱ መታየት ወይም መከናወን ከጀመረ በኋላ ከሆነ ጉዳዩ የሚመለከተው የቦርድ አባል ሁኔታውን ለቦርዱ በማስረዳት ከስብሰባው ወይም ከተግባሩ እራሱን ማግለል አለበት፡፡
3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገገው ሁኔታ ሲከሰት ጉዳዩ በቃለ ጉባኤ ተይዞ ስብሰባው ወይም ተግባሩ በቀሪዎቹ የቦርድ አባላት ይወሰናል ወይም ይከናወናል፡፡
4. ከጉዳዩ ጋር የጥቅም ግጭት ያለው የቦርድ አባል ሁኔታውን ሳይገልፅ በስብሰባው ወይም በተግባሩ ተሳታፊ በመሆን ውሳኔ የተላለፈ ወይም ተግባሩ የተከናወነ ከሆነ ውሳኔው ወይም ተግባሩ በቦርዱ እንደገና ሊታይ፣ ሊለወጥ ወይም ውድቅ ሊደረግ ይችላል፡፡

5. ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት አንድ የቦርድ አባል ከሚያከናውነው ተግባር ጋር ወይም በተሳተፈበት ስብሰባ በመታየት ላይ ካለው ጉዳይ ጋር የጥቅም ግጭት አለው ብሎ ካመነ ማስረጃውን ወዲያውኑ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለቦርዱ ጽህፈት ቤት

### 14.መቋቋም

ቦርዱ በአንድ ዋና ኃላፊና በሁለት ምክትል ዋና ኃላፊዎች የሚመራ ጽህፈት ቤት ይኖረዋል

### 15.የቦርዱ ጽህፈት ቤት ኃላፊዎች አሿሿምና ተጠሪነት

1. የጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊና ምክትል ዋና ኃላፊዎች በልምዳቸውና በችሎታቸው ተመርጠው በቦርዱ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ።
2. የጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ ተጠሪነቱ ለቦርዱ ይሆናል።
3. የቦርዱ ጽህፈት ቤት ምክትል ዋና ኃላፊዎች ተጠሪነት ለዋናው ኃላፊ ይሆናል፡፡

### 16.የጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ ስልጣንና ተግባር

የጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ጽህፈት ቤቱን በኃላፊነት ይመራል፣
2. ከቦርዱ ሰብሳቢ ጋር በመመካከር የቦርዱን የስብሰባ አጀንዳ ያዘጋጃል፣
3. የቦርዱን ቃለ ጉባዔና ሌሎች ሰነዶች በአግባቡ ይይዛል፣
4. የቦርዱ ውሳኔዎች ለሚመለከታቸው ወገኖች እንዲተላለፉ ያደረጋል፣
5. በመንግስት ሰራተኞች የአስተዳደር ህግ እና ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ መሰረት ሰራተኞችን ይቀጥራል፣ ይመድባል፣ ያዛውራል፣ ህግና ስርዓትን ተከትሎ የዲሲፕሊን እርምጃ ይወስዳል፣ ያሰናብታል፣
6. የቦርዱን ጽህፈት ቤት የአጭርና የረጅም ጊዜ ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
7. በአንቀፅ 8 ንኡስ አንቀጽ 6 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች የቦርዱን ጽህፈት ቤት ይወክላል፣

8. በህገ መንግስቱ፣ በዚህ አዋጅና ቦርዱ በሚያወጣቸው ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት በየደረጃው የሚካሄዱ ምርጫዎችና ህዝበ ውሳኔዎች እንዲካሄዱ የሚያስፈልገውን ሁሉ ያደርጋል፣
9. በዚህ አዋጅ ለቦርዱ የተሰጡት ዝርዝር የምርጫ አፈፃፀም ተግባራትን ያስፈፅማል። መሠረታዊ በሆኑ የምርጫ አፈፃፀም ጉዳዮች ላይ የፖለቲካ ድርጅቶችን ያማክራል፣
10. በቦርዱ መወሰን የሚገባቸውን ጉዳዮች ከአስተያየቱ ጋር ለቦርዱ ያቀርባል፣
11. የቦርዱ ጽህፈት ቤት ምክትል ዋና ኃላፊዎች የስራ ግድፈት ሲፈፅሙ እርምጃ እንዲወሰድባቸው የውሳኔ ሀሳብ ለቦርዱ ያቀርባል። ውሳኔውንም ተግባራዊ ያደርጋል፣
12. የፌደራልና የክልል ህገመንግስታትን መሰረት በማድረግ የምርጫ አፈፃፀም የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፣
13. የቦርዱ ጽህፈት ቤት በራሱ ተነሳሽነት ወይም በክልሎች በሚቀርብለት ጥያቄ መሰረት መራጩ ህዝብ ያለእንግልት በመራጭነት እንዲመዘገብና ድምፅ እንዲሰጥ ምቹ የምርጫ ጣቢያዎች እንዲደራጁ የውሳኔ ሃሳብ ለቦርዱ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፣
14. ስለ ጽህፈት ቤቱ የስራ እንቅስቃሴ በየጊዜው ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤
15. ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፣
16. ለስራው ቅልጥፍና አስፈላጊ በሆነ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ ለጽህፈት ቤቱ ምክትል ዋና ኃላፊዎች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፣
17. እርሱ በማይኖርበት ጊዜ ከምክትል ዋና ኃላፊዎቹ አንዱን በፅሁፍ ይወክላል፣

**17. <u>የጽህፈት ቤቱ ምክትል ዋና ኃላፊዎች ስልጣንና ተግባር</u>**

የጽህፈት ቤቱ ምክትል ዋና ኃላፊዎች የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፤

1. በጽህፈት ቤቱ መዋቅር ውስጥ የድርጅታዊ ድጋፍ ዘርፍን እና የአገልግሎቶችና ግንኙነት ዘርፍን በበላይነት ይመራሉ፡፡
2. በዋና ሀላፊው ተለይተው የሚሰጧቸውን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናሉ፡፡
3. የጽህፈት ቤቱ ዋና ኃላፊ በሌለበት ጊዜ በሚሰጣቸው ውክልና መሰረት ዋና ሀላፊውን ተክተው ይሰራሉ፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## ስለሌሎች የምርጫ አስፈጻሚዎች

### 18.የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት

1. በክልል ደረጃ ምርጫ የሚያስተባብር ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ይቋቋማል፡፡
2. የቦርዱ ጽህፈ ቤት የቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱን ኃላፊና ሌሎች ሰራተኞችን የሙያ ብቃት ካላቸውና ገለልተኛ ከሆኑ የክልሉ ነዋሪዎች መካከል አወዳድሮ ይቀጥራል፡፡
3. ቦርዱ የክልሎች ስፋትና የመራጮችን ብዛት መሰረት በማድረግ ለክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ተጠሪ የሆኑ ማስተባበርያ ጽህፈት ቤቶች በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ሊያቋቁም ይችላል፡፡ የማስተባበርያ ጽህፈት ቤቶች ተግባር፣ ኃላፊነትና አሰራር ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

### 19.የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ተግባርና ኃላፊነት

እያንዳንዱ የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ከዚህ በታች የተዘረዘረው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፤

1. ቦርዱ በሚያወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት በክልል ደረጃ የሚካሄደውን ምርጫ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ ይቆጣጠራል፣
2. በስሩ የሚቋቋሙት የምርጫ ጽህፈት ቤቶች ሰለሚደራጁበት ሁኔታ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሀሳብ ያቀርባል፣
3. ለምርጫ የሚያስፈልጉ ሰነዶችና ቁሳቁሶች ለሚመለከታቸው የምርጫ ጽህፈት ቤቶች በወቅቱ መድረሳቸውን ይከታተላል፤ ያረጋግጣል፣
4. ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፤ ያስተባብራል፣
5. ቦርዱ በሚሰጣቸው ፈቃድ መሰረት የስነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት የሚሰጡ ድርጅቶችን ያስተባብራል ይቆጣጠራል፣
6. የመራጮች አመዘጋገብ፤ የእጩዎች አቀራረብና የድምፅ አሰጣጥ ስርዓት ህጉ በሚፈቅደው መሰረት እየተካሄደ መሆኑን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፣
7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 6 በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ የሚነሱትን ቅሬታዎችና ተቃውሞዎች በክልል ደረጃ እየመረመረ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል፣
8. የክልሉን የምርጫ ሂደትና ውጤት በሚመለከት ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፣

9. ለምርጫ አፈፃፀም በሚያመች መልኩ አግባብ ያላቸውን መረጃዎች እየሰበሰበና እያጠና በየጊዜው ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፣

10. ስለስራ እንቅስቃሴው በየወቅቱ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡

11. ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በክልል፣ በምርጫ ክልል እና በምርጫ ጣቢያ ደረጃ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ እንዲዋቀር ያደርጋል፣ በክልል የሚቋቋመው የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፣

12. የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት ይቋቋማል፣

13. ቦርዱ የሚመድብለትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

20. <u>**የምርጫ ክልሎች**</u>

1. ለጠቅላላ ምርጫ አፈፃፀም የሚያገለግሉ የምርጫ ክልሎች እንደሚከተለው ይደራጃሉ፡፡

   ሀ/ ለምርጫ አፈፃፀም ተግባር የክልሎች ድንበር እንደተጠበቀ ሆኖ ወረዳን መሰረት በማድረግ አገሪቷ በህዝብ ቆጠራ ውጤት መሰረት ማስተካከል ሊደረግባቸው በሚችሉ በቋሚ ምርጫ ክልሎች ትከፋፈላለች፤

   ለ/ የሀገሪቱ ምርጫ ክልሎች ቁጥር የኢትዮጵያ ህዝብ ብዛትንና በልዩ ትኩረት ውክልና የሚሰጣቸው የህዝብ ብዛታቸው አነስተኛ የሆነ ብሔረሰቦችና ህዝቦችን ቁጥር መሰረት በማድረግ ከ550 የማይበልጥ ሆኖ የህዝብ ብዛታቸው አነስተኛ የሆነ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የሚወከሉበትን የምርጫ ክልል ሳይጨምር ተቀራራቢ የሆነ የህዝብ ብዛትን የሚያቅፍ ይሆናል።

   ሐ/ በህገመንግስቱ አንቀፅ 54 መሰረት የተለየ ውክልና ያስፈልጋቸዋል ተብለው የታመነባቸው ቁጥራቸው ከ20 የማያንሱ የህዝብ ብዛታቸው አነስተኛ ብሔረሰቦችና ህዝቦች የሚወከሉባቸው የምርጫ ክልሎች ይኖራሉ፡፡

   መ/ የተለየ ውክልና የሚያስፈልጋቸው የህዝብ ብዛታቸው አነስተኛ የሆነ ብሔረሰቦች ቀድሞ በሚዘጋጅ ግልፅ መስፈርት መሰረት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ይወስናል፡፡

   ሠ/ የምርጫ ክልሎች ዝርዝር ቦርዱ አጥንቶ በሚያቀርበው መሰረት በፌዴሬሽን ምክር ቤት ተወስኖ ለህዝብ ይገለጻል፡፡

2. በየደረጃው የሚካሄዱ የአከባቢ ምርጫዎች በየክልሉ ህግ መሰረት ለየምክር ቤቶቹ የሚመረጡትን አባላትና የመራጩን ብዛት መሰረት ያደረጉ ተመጣጣኝ የምርጫ ክልሎች በማቋቋም ይከናወናሉ፡፡
3. እያንዳንዱ የምርጫ ክልል እንደአግባብነቱ በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ 3 ሰዎችን የያዘ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ ይኖረዋል፡፡
4. እያንዳንዱ የምርጫ ክልል እንዳግባብነቱ ገለልተኛ የሆኑና ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ከህዝብ የሚመረጡ ከ3 የማይበልጡ የህዝብ ታዛቢዎች ይኖረዋል። ታዛቢዎቹም በየምርጫ ጣቢያው በተመረጡ የህዝብ ታዛቢዎች የሚመረጡ ይሆናሉ።
5. እያንዳንዱ ምርጫ ክልል በምርጫ ክልሉ ኃላፊ የሚመራና ሁለት የህዝብ ታዛቢዎች አባል የሚሆኑበት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይኖረዋል። ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

21.<u>የምርጫ ክልል ስልጣንና ተግባር</u>

እያንዳንዱ የምርጫ ክልል የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፤

1. ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት፡-

ሀ/ የምርጫ ቁሳቁሶች ለምርጫ ጣቢያዎች ያሰራጫል፣

ለ/ ዕጩዎችን ይመዘግባል፤ መስፈርቱን ላሟሉ ዕጩዎች መታወቂያ ካርድ ይሰጣል፣

2. ከምርጫ ጣቢያዎች የሚመጡ ሰነዶችና የምርጫ ቁሳቁሶች በአግባቡ ተሞልተው መምጣታቸውን ያረጋግጣል፣ ይረከባል፣ በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፣
3. ምርጫ ጣቢያዎች ተግባራቸውን በአግባቡ ማከናወናቸውን ይቆጣጠራል፣
4. በህግ መሰረት ለሚቀርቡ ቅሬታዎችና አቤቱታዎች ውሳኔ ይሰጣል፣
5. ከምርጫ ጣቢያ የመጡ የምርጫ ውጤቶችን በማዳመር አሸናፊዎችን ከለየ በኋላ ውጤቱን ለህዝብ ይፋ በማድረግ አስፈላጊ ቅጾችን በመሙላት ለቦርዱ ይልካል፣
6. ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የተመራጭነት መታወቂያ ካርድ ለአሸናፊዎች ይሰጣል፣
7. የዕጩ ወኪሎችን ዝርዝር ለምርጫ ጣቢያዎች ያስተላልፋል፣

8. የምርጫ ክልሉን የህዝብ ታዛቢዎች ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ያስመርጣል፣

9. የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ ሊያደራጅ ይችላል፡

10. ከቦርዱ ወይም ከክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

## 22. የምርጫ ጣቢያዎች ስለማቋቋም

1. የምርጫ ጣቢያዎች ቦርዱ በሚወስነው ስፍራና ሁኔታ የሚቋቋሙና ለህዝብ በይፋ የሚገለጹ ይሆናሉ።

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም ቦርዱ የአርብቶ አደሩን ህዝብ አኗኗር መነሻ በማድረግ ተንቀሳቃሽ የምርጫ ጣቢዎችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡

3. የምርጫ ጣቢያዎች የመራጮች ምዝገባ፣ የድምፅ መስጫ እና የቆጠራ ጣቢያ ሆነው ያገለግላሉ፡፡

4. ቦርዱ ለምርጫው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የምርጫ ጣቢያ ቦታዎችን ሊለዋውጥ ይችላል፡፡ ለውጡንም በንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

5. ወታደራዊ ካምፖች፣ የፖሊስ ጣቢያዎች፣ ቤተክርስትያናትና መስጊዶች፣ ሆስፒታሎች፣ መጠጥ ቤቶች፣ የፖለቲካ ወይም የሃይማኖት ድርጅቶች ህንፃዎች፣ መኖሪያ ቤቶች የምዝገባና የድምፅ መስጫ ሥፍራ በመሆን ሊያገለግሉ አይችሉም።

6. እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ የሚያስተናግደው የመራጮች ብዛት ከአንድ ሺ መብለጥ የለበትም፡፡

7. በአንድ ቦታ ላይ ከአንድ ምርጫ ጣቢያ በላይ መኖር የለበትም፡፡

8. እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ እንዳግባብነቱ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟሉ 5 የምርጫ አስፈፃሚዎችን የያዘ ኮሚቴ ይኖረዋል። የምርጫ ጣቢያው ሃላፊ ኮሚቴውን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡

9. እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ ገለልተኛ የሆኑና በህዝብ የሚመረጡ ከ5 ያልበለጡ የህዝብ ታዛቢዎች ይኖሩታል።

10. እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የሚመራና 2 የህዝብ ታዛቢዎች አባል የሆኑበት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይኖረዋል። ዝርዝሩ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## 23. የምርጫ ጣቢያ ስልጣንና ተግባር

እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብና የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የሚያከናውናቸው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፤ '

1. መራጮችን ይመዘግባል፤
2. ከምርጫ ክልሉ የሚላኩ የምርጫ ቁሳቁሶችን በጥንቃቄ እንዲያዙ ያደርጋል፣
3. ምርጫ ያካሂዳል፣
4. በህጉ መሰረት የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ያስተናግዳል፣
5. የተሰጠውን ድምፅ ቆጠራ በማካሄድ የምርጫ ውጤትን በማስታወቂያ ሰሌዳ በማውጣት ለህዝብ ያሳውቃል፡፡
6. የምርጫ ሰነዶችና ቁሳቁሶች በአግባቡ ተሞልተው እና ተጠብቀው ለምርጫ ክልሉ እንዲላኩ ያደርጋል፡፡
7. የምርጫ ጣብያ የህዝብ ታዛቢዎችን ያስመርጣል፣
8. ከቦርዱ፣ ከክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቱ ወይም ከምርጫ ክልሉ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

24.<u>በልዩ ሁኔታ የሚቋቋም ምርጫ ጣቢያ</u>

1. ቦርዱ ከምርጫ ክልላቸው ርቀው በካምፕ የሚኖሩ ወታደሮችና ሲቪል ሰራተኞች እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚማሩ ዜጎች በምርጫ የሚሳተፉበትን ሁኔታ ለማመቻቸት መራጮቹ በሚገኙበት ቦታ ወይም አካባቢ ልዩ ምርጫ ጣቢያ ለማቋቋም ይችላል፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተዘረዘሩት መራጮች የሚመዘገቡት እና ድምፅ የሚሰጡት በልዩ ምርጫ ጣቢያዎች ይሆናል፡፡
3. ከላይ በተጠቀሰው ምርጫ ጣቢያ የተመዘገበ መራጭ ወደ ካምፑ ወይም ወደ ትምህርት ተቋሙ ከመምጣቱ በፊት ይኖርበት በነበረው የምርጫ ክልል ውስጥ ለውድድር ከቀረቡት እጩዎች መካከል ይመርጣል።
4. ቦርዱ የምርጫ ውጤቶችን በመለየት ከየምርጫ ክልሉ በሚደርሰው ውጤት ላይ በማዳመር ውጤቱን ይፋ ያደርጋል፡፡
5. ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ ወይም መመርያ ይወሰናል፡፡

## <u>ክፍል ሶስት</u>

## <u>ስለምርጫ</u>

## <u>ምዕራፍ አንድ</u>

## <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

25.<u>የምርጫ ስርዓት</u>

የምርጫ ሥርዓቱ በአንድ የምርጫ ክልል ውስጥ ከሚወዳደሩ ዕጩዎች መካከል አብላጫ ድምጽ ያገኘ ዕጩ በምርጫው አሸናፊ የሚሆንበት የምርጫ ስርዓት ነው፡፡

26.<u>የምርጫ መርሆዎች</u>

1. ማንኛውም ምርጫ ሁሉአቀፍ፣ ቀጥተኛ፣ በምስጢር ድምፅ አሰጣጥ መራጩ ፈቃዱን በነፃነት የሚገልፅበት እና ያለምንም ልዩነት በእኩል ህዝባዊ ተሳትፎ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡
2. የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ በህግ ያልተገደበ ማንኛውም ኢትዮጵያዊ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት አለው፡፡
3. እያንዳንዱ መራጭ የሚሰጠው ድምፅ እኩል ነው።
4. ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ለመምረጥም ሆነ ለመመረጥ አይገደድም፡፡

27.<u>የምርጫ አይነቶች</u>

በኢትዮጵያ የሚካሄዱ ምርጫዎች የሚከተሉት ናቸው፤

1. ጠቅላላ ምርጫ፣
2. የአካባቢ ምርጫ፣
3. ሚሟያ ምርጫ፣
4. ድጋሚ ምርጫ፣
5. ህዝበ ውሳኔ፤

28.<u>ጠቅላላ ምርጫ</u>

1. ጠቅላላ ምርጫ በየአምስት አመቱ የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮች እና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው።
2. ጠቅላላ ምርጫ በመላ ሀገሪቱ በተመሳሳይ ጊዜ ይካሄዳል፡፡ ሆኖም ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እና ጉዳዩ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ቀርቦ ውሳኔ ሲያገኝ በተለያየ ጊዜ እንዲካሄድ ሊያደርግ ይችላል፡፡
3. ለፌደራል የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከአንድ የምርጫ ክልል አንድ ተወካይ ብቻ ይመረጣል፡፡
4. የክልል ምክር ቤቶች አባላት ቁጥር በየክልሉ ህግ መሠረት የሚወሰን ሆኖ ምክር ቤቶቹ የአባሎቻቸውን ቁጥር ለመቀየር ሲወስኑ ለፖለቲካ ፓርቲዎች በቂ የዝግጅት ጊዜ መስጠቱን ታሳቢ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

29.<u>የአካባቢ ምርጫ</u>

1. የአካባቢ ምርጫ በህግ በተደነገገው መሰረት በየደረጃው በሚገኙ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የማዘጋጃ ቤት፣ የክፍለ ከተማ ወይም የቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው።
2. ለአካባቢ ምርጫ በአንድ ምርጫ ክልል ምን ያህል ተወካዮች እንደሚመረጡ እንደየምርጫው አይነትና ለየምክርቤቱ የሚመረጡትን አባላት መሰረት በማድረግ በየክልሎቹ ህግ ይወሰናል።
3. የአካባቢ ምርጫ የሚካሄድበት ጊዜ በክልሎች ህግጋት መሰረት ይሆናል።
4. የአካባቢ ምርጫ ይህንን አዋጅ መሰረት በማድረግ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብና መመሪያ መሰረት የሚከናወን ይሆናል፡፡

## 30.<u>የሟሟያ ምርጫ</u>

1. የማሟያ ምርጫ የሚካሄደው፡-

   ሀ/ በየደረጃው ያሉ ምክር ቤቶች በተለያየ ምክንያት የተጓደሉባቸው አባላት እንዲሟሉላቸው ለቦርዱ ጥያቄ ሲያቀርቡ፡ ወይም

   ለ/ በህጉ መሰረት የቀረበ የይውረድልን ጥያቄ ተቀባይነት ሲያገኝ፣

   ነው።
2. ቦርዱ ጥያቄው በደረሰው በ3 ወር ጊዜ ውስጥ የማሟያ ምርጫ ያካሂዳል፡፡
3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተደነገገው ቢኖርም አንድ ምክር ቤት የስራ ዘመኑ ሊያልቅ 6 ወር የቀረው ከሆነ የማሟያ ምርጫ አይካሄድም።

## 31.<u>ድጋሚ ምርጫ</u>

1. ድጋሚ ምርጫ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ሊካሄድ ይችላል፡፡

   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 7 ንዑስ አንቀፅ 10 መሰረት ቦርዱ ሲወስን፣

   ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 76 ንዑስ አንቀፅ 3 መሰረት እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን መለየት አስቸጋሪ የሆነ እንደሆነ።
2. ድጋሚ ምርጫ ሲካሄድ፡-

   ሀ/ ሌላ አዲስ የመራጮች ምዝገባ ሳያስፈልግ በምርጫ ክልሉ ወይም ችግሩ የተከሰተባቸው የምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ ተመዝግበው በነበሩ መራጮች ይካሄዳል።

   ለ/ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 (ሀ) መሰረት ምርጫ እንዲካሄድ ሲወሰን አዲስ የእጩዎች ምዝገባ ሳያስፈልግ ቀድሞ በተመዘገቡ እጩዎች መካከል ብቻ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

ሐ/ የምርጫ ቅስቀሳ ማድረግ የተከለከለ ነው፡፡

3. የድጋሚ ምርጫ ዝርዝር አፈፃፀም ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ ወይም መመሪያ ይወሰናል፡፡

32.<u>ህዝበ ውሳኔ</u>

1. በህገመንግስቱ መሰረት አግባብ ባለው አካል ሲወሰን የህዝብን ፍላጎት ለመለካት ወይም ለመወሰን ድምጽ የሚሰጥበት ስርአት ነው።
2. ህዝበ ውሳኔው እንዲካሄድ የወሰነው አካል በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ቦርዱ ህዝበ ውሳኔ ያስፈለገበትን ጉዳይ ለመለየት በሚያስችለው መልኩ የድምጽ መስጫ ጣቢያዎችን በማደራጀት ህዝበ ውሳኔውን ያከናውናል፡፡
3. ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የመራጮች ምዝገባ</u>

33.<u>በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>

1. ማንኛውም ሰው፡-

   ሀ/ ኢትዮጵያዊ ከሆነ፣

   ለ/ በምዝገባው ዕለት ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ ከሆነ፣

   ሐ/ በምርጫ ክልሉ ቢያንስ 6 ወር የኖረ ከሆነ፣ በመራጭነት ሊመዘገብ ይችላል።

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 (ለ) የተጠቀሰው የተመዝጋቢው ዕድሜ 18 ዓመት ስለመሆኑ ጥርጣሬ ሲኖር በቤተሰቡ አንጋፋ አባል ወይም ዘመድ እነሱ ከሌሉ ስለግለሰቡ እድሜ በሚያውቅ በሌላ ሰው የምስክርነት ቃል ይወሰናል።
3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ከዚህ በታች የተመለከቱት በመራጭነት ሊመዘገቡ አይችሉም።

   ሀ/ በአዕምሮ ህመም ምክንያት የመወሰን አቅም የሌለው መሆኑ የሚታወቅ ሰው፣

   ለ/ በፍርድ የተወሰነበትን የእስራት ቅጣት በመፈፀም ላይ ያለ ሰው፣

   ሐ/ የመምረጥ መብቱ በህግ የተገደበበት ሰው፣

34.<u>የምዝገባ ጊዜ ሰሌዳ</u>

1. የጠቅላላ ምርጫ ምዝገባ በአገር አቀፍ ደረጃ ቦርዱ በሚወስናቸው ቀናት የሚጀመርና የሚጠናቀቅ ይሆናል፡፡ ቦርዱ የምዝገባ ቀናቱን ከመወሰኑ በፊት የፖለቲካ ድርጅቶችን ያማክራል፡፡
2. ቦርዱ የመራጮችን የምዝገባ ዕለት በምርጫ የጊዜ ሰሌዳው በማካተት ምዝገባው ከመጀመሩ ከ15 ቀን በፊት ጀምሮ በተከታታይ በመገናኛ ብዙሃንና በማስታወቂያዎች አማካይነት ለህዝቡ ይገልፃል፡፡
3. ቦርዱ ልዩ ሁኔታ ሲያጋጥም ልዩ የምዝገባ ቀን ሊወስን ይችላል፡፡
4. ማንኛውም ከአቅም በላይ የሆነ ሁኔታ ያጋጠመው ሰው በዚህ አዋጅ መሰረት በመራጭነት ለመመዝገብ የሚያስችለውን መስፈርት የሚያሟላ ከሆነ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ሊመዘገብ ይችላል፡፡
5. ቦርዱ የሚመለከታቸውን ክልሎች ህገ መንግስት ወይም ውሳኔ መነሻ በማድረግ የአካባቢ ምርጫዎችን የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ያወጣል። የጊዜ ሰሌዳውን በተመለከተ ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ይመካከራል።

35.<u>**የምዝገባ ቦታ**</u>

1. ምዝገባ መራጮች በየሚኖሩበት ቀበሌ በሚቋቋም የምርጫ ጣቢያ ይከናወናል፡፡ ሆኖም ከምርጫ ጣቢያው ውጭ ቤት ለቤት ወይም በተመሳሳይ ቦታ እየተዘዋወሩ ምዝገባ ማከናወን የተከለከለ ነው።
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም በአርብቶ አደሮች አካባቢ እንዳስፈላጊነቱ ተንቀሳቃሽ የምዝገባ ማዕከል በማቋቋም የመራጮች ምዝገባ ማከናወን ይቻላል፡፡
3. እያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ የራሱ የመራጮች መዝገብ ይኖረዋል።

36.<u>**የአመዘጋገብ ስርዓት**</u>

1. ተመዝጋቢው በሚኖርበት የምርጫ ጣቢያ ማንነቱን የሚገልፅ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት በመያዝ ለመመዝገብ ይችላል፡፡
2. የመታወቂያ ካርዱ ወይም ፓስፖርቱ ጊዜ ያለፈበት ቢሆንም እንኳ ለምዝገባ ሊያገለግል ይችላል።
3. የመታወቂያ ካርድ በሌለበት ወቅት በቅርቡ ፎቶግራፍ ተደርጎበት የተሰጠ እንደ የመንጃ ፈቃድ፣ የመኖሪያ የምስክር ወረቀት፣ ከውትድርና የተገለለበት ሰነድ፣ በተባበሩት መንግስታት የተሰጠ የስደተኛ ካርድ የመሳሰሉ የመለያ ማስረጃዎች ለመመዝገብ የሚያስችሉ ሰነዶች ተደርገው ይወሰዳሉ።

4. ከዚህ በላይ የተጠቀሱት የመለያ ማስረጃዎች በማይኖሩበት ወቅት መዝጋቢዎች መራጩን ለይተው የሚያውቁት ከሆነ ወይም በገጠር አካባቢ ሲሆን በባህላዊና ልማዳዊ ዘዴ ተመዝጋቢውን ለመለየት የሚቻልበት ሁኔታ ካለ ምዝገባው ይከናወናል፡፡
5. በምርጫ ጣቢያ በህዝብ የተመረጡ የህዝብ ታዛቢዎች በሚሰጡት ምስክርነት ተመዝጋቢውን ለመለየት የሚቻልበት ሁኔታ ካለ በቃለ ለጉባኤ ተይዞ ምዝገባው ሊከናወን ይችላል፡፡
6. ለመመዝገብ ብቁ የሆኑና አቅም የሚያንሳቸው ሰዎች እና አይነስውራን በረዳቶቻቸው አማካኝነት በአካል ተገኝተው ሊመዘገቡ ይችላሉ፡፡
7. ለመራጭነት ብቁ የሆነ ሰው በተዘጋጀው የመራጮች መዝገብ ላይ ስሙ ይመዘገባል።
8. በአግባቡ የተመዘገበ ማንኛውም ሰው ሙሉ ስም ከነአያቱ፣ የሚኖርበት ክልል፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ፣ የምርጫ ጣቢያ፣ የቤት ቁጥር፣ መንደር ወይም ጎጥ፣ የመዝገብ ቁጥር፣ የምዝገባ ተራ ቁጥር፣ የመዝገብ ገፅ፣ የመራጩ ፊርማ፣ የመዝጋቢ ፊርማ፣ የተመዘገበበት ቀን ተሞልቶ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ይሰጠዋል።

37.<u>የመራጮች መዝገብ ይዘት</u>

የመራጮች መዝገብ የሚከተሉትን አርዕስቶች ለመሙላት የሚያስችሉ አምዶች ይኖሩታል፡-

1. የምዝገባ ተራ ቁጥር፣
2. የምዝገባ ቀን፣
3. የተመዝጋቢው ሙሉ ስም ከነአያት፣
4. ዕድሜ፣
5. ፆታ፣
6. በምርጫ ክልሉ የኖረበት ጊዜ፣
7. የምዝገባው ዕለት የዕህፊት ወይም የአውራ ጣት ፊርማ፣
8. የምርጫ ዕለት የዕህፊት ወይም የአውራ ጣት ፊርማ፣
9. የቤት ቁጥር/መንደር ወይም ጎጥ/፣
10. ለአስፈላጊ ስራ አንድ አምድ፣

38.<u>የሰነዶች ስርጭትና ርክክብ</u>

1. ቦርዱ በምርጫው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ለምዝገባ የሚያስፈልጉትን ሰነዶች በወቅቱ ለምርጫ ጣቢያዎች እንዲደርስ ያደርጋል፡፡
2. በምዝገባ አገልግሎት ላይ የዋሉ ሰነዶች እና መዝገቦች ርክክብ ስነስርአትና ጊዜ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት ይወሰናል፡፡

39.<u>አንድ ጊዜ እና አንድ ቦታ ብቻ ስለመመዝገብ</u>

1. ማንኛውም መራጭ በአንድ ምርጫ ጣቢያ ከአንድ ጊዜ በላይ መመዝገብ ወይም ከአንድ ምርጫ ጣቢያ በላይ መመዝገብ የለበትም፡፡
2. አንድ መራጭ አንድ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርድ ብቻ ይኖረዋል።
3. ማንኛውም የመራጮች መታወቂያ ካርድ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት መራጭ ከድምፅ መስጫው እለት በፊት በማንኛውም የምርጫ ጣቢያው የሥራ ጊዜ ወይም በድምፅ መስጫው እለት ለምርጫ ጣቢያው ሊያመለክት ይችላል። በምርጫ ጽህፈት ቤቱም ከታመነበት ጉዳዩ በቃለ ጉባኤ ተይዞ በምትኩ ሌላ ሊሰጠው ወይም ድምፅ ሊሰጥ ይችላል፡፡

40.<u>ስለመራጮች መዝገብ መዘጋት</u>

1. በየዕለቱ ምዝገባ ከተጠናቀቀ በኋላ የመራጮች መዝገብ የዕለቱ የመጨረሻ ተመዝጋቢ ቁጥር በተዘጋጀው የመፈራረሚያ ቅፅ ላይ የመጨረሻውን ተመዝጋቢ ቁጥርና ቀን በመመዝገብ መዝጋቢዎችና የህዝብ ታዛቢዎች ይፈራረሙበታል።
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 በተቀመጠው ሁኔታ የመራጮች ምዝገባ እስኪጠናቀቅ ድረስ ምዝገባው ይቀጥላል። በምዝገባው ማጠቃለያ ዕለትም ከላይ የተጠቀሱት አካላት በመዝገቡ ላይ ከመጨረሻው ተመዝጋቢ ቀጥሎ ባለው ክፍት ቦታ ተፈራርመውበት መዝገቡ ይዘጋል።
3. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር መዝገቡ ከተዘጋና ከተፈራረሙበት በኋላ በመዝገቡ ላይ አዲስ መራጭ አይመዘገብም፣ የሚሰፍር ወይም የሚፃፍ ነገር አይኖርም።

41.<u>የመራጮች መዝገብ ለህዝብ ግልጽ ስለማድረግ</u>

1. የመራጮች ምዝገባ እንደተጠናቀቀ የመራጮች መዝገብ በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ለተከታታይ 5 ቀናት ይፋ ወጥቶ ህዝብ በግልፅ እንዲያየው ይደረጋል፡፡
2. ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

42.<u>የምዝገባ ተቃውሞን በተመለከተ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 93 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በምዝገባ ላይ ተቃውሞ ካለው ተቃውሞውን ከነምክንያቱ ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የቀረበውን አቤቱታ ተመልክቶ ባለጉዳዩ መልስ እንዲሰጥ ካደረገ በኋላ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

43. <u>ከምዝገባ ስለመሰረዝ</u>

1. ማንኛውም ተመዝጋቢ በአዕምሮ ህመም ምክንያት ለመወሰን ብቃት የሌለው ወይም በማጭበርበር የተመዘገበ ወይም የሞተ ወይም ሲፈረድበት ካልሆነ በስተቀር በሚቀርብ ተቃውሞ ከመራጭነት ምዝገባ አይሰረዝም፡፡
2. መራጮች ሲፈረድባቸው፣ የአዕምሮ ሕመምተኞች ሲሆኑ ወይም ሲሞቱ ወይም አጭበርብረው ሲገኙ ፍርድ ቤቶች፣ ሆስፒታሎች እና እድሮች ሁኔታው እንደተከሰተ ወዲያውኑ ለቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ወይም ለምርጫ ክልል ወይም ለየምርጫ ጣቢያ ሪፖርት የማድረግ ግዴታ አለባቸው።
3. የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ወይም የምርጫ ክልሎች ወይም የምርጫ ጣቢያዎች ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 መሰረት መረጃ እንደ ደረሳቸው አስፈላጊውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው።

## <u>ምዕራፍ ሶስት</u>

## <u>የዕጩዎች ምዝገባ</u>

44. <u>የእጩ ምዝገባ ቦታ</u>

የእጩ ምዝገባ ቦርዱ በሚያወጣው የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ለእጩዎች ምዝገባ በተያዘው ጊዜ ውስጥ በምርጫ ክልሎች ይከናወናል፡፡

45. <u>ለዕጩነት ስለሚያበቁ መመዘኛዎች</u>

1. ማንኛውም ሰው፡-

ሀ/ ኢትዮጵያዊ የሆነ፣

ለ/ የሚወዳደርበትን ብሔራዊ ክልል ወይም የአካባቢውን የስራ ቋንቋ የሚያውቅ ከሆነ፣

ሐ/ በምዝገባ ዕለት እድሜው 21 ዓመት ወይም ከዚያ በላይ የሆነው፣

መ/ ከምርጫው እለት አስቀድሞ በምርጫ ክልሉ ውስጥ በመደበኛነት ለሁለት አመት ከኖረ ወይም የትውልድ ቦታው በእጩነት ሊቀርብበት በፈለገበት ምርጫ ክልል ውስጥ ከሆነ ወይም ከተማው ወይም ወረዳው ከአንድ በላይ የምርጫ ክልሎች የሚያቅፍ ከሆነ በከተማው ወይም

በወረዳው ውስጥ ለሁለት ዓመት በመደበኛነት የሰራ ከሆነ በዚያው ከተማ ወይም ወረዳው በፈለገው የምርጫ ክልል፣

ሠ/ በህግ የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብቱ ያልተገፈፈ፣

ረ/ ለውድድር የቀረበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም በግል የቀረበ እጩ በዚህ አዋጅና ቦርዱ በአንቀፅ 105 መሰረት የሚያወጣውን የምርጫ ስነምግባር ደንብ ተቀብሎ የፈረመ፣

በእጩነት ሊቀርብ ይችላል፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 (መ) የተደነገገው መመዘኛ፡-

ሀ/ በስራ ወይም በትምህርት ምክንያት ከምርጫ ክልሉ ውጭ የነበረን ሰው፣

ለ/ ከዚህ በፊት በምርጫ ክልሉ ተመርጦ በመስራት ላይ ያለን ሰው

አይመለከትም፡፡

3. ከላይ ከተደነገገው መመዘኛ በተጨማሪ በግል የቀረበ እጩ በአካባቢው መስተዳድር የተረጋገጠ እድሜያቸው 18 አመትና ከዚያ በላይ ከሆናቸው መምረጥ በህግ ካልተከለከሉ የምርጫ ክልሉ ነዋሪዎች ውስጥ ከአንድ ሺህ የማያንስ የድጋፍ ፊርማ ማቅረብ አለበት።

46.<u>የዕጩ አቀራረብ</u>

1. ማንኛውም በህግ የተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት በዚህ አዋጅ መሰረት በሚካሄድ ምርጫ መስፈርቱን የሚያሟላ እጩ በማቅረብ ሊወዳደር ይችላል፡፡
2. በፖለቲካ ድርጅት ተወክለው የሚወዳደሩ እጩዎችን ዝርዝር ለቦርዱ የሚያሳውቀው የድርጅቱ ከፍተኛ አመራር ይሆናል።
3. በፖለቲካ ድርጅት ተወክሎ ለሚቀርብ እጩ በፓርቲው መወከሉን እና በእጩነት ለመቅረብ መስማማቱን የሚገልፅ ማስረጃ ከእጩነት ማስረጃው ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡
4. አንድ የፖለቲካ ድርጅት በአንድ የምርጫ ክልል ለአንድ የምክር ቤት መቀመጫ አንድ እጩ ብቻ ማቅረብ አለበት፡፡
5. ማንኛውም መስፈርቱን የሚያሟላ ግለሰብ እራሱን በእጩነት ሊያቀርብ ይችላል።
6. ማንኛውም እጩ በግንባር በመቅረብ መመዝገብ አለበት። በግንባር ቀርቦ መመዝገብ ካልቻለ ለእጩነት የሚያበቁ መስፈርቶች ማሟላቱን የሚያረጋግጡ ተጨባጭ የሰነድ ወይም የሰው ማስረጃዎች እጩውን ባቀረበው የፖለቲካ ድርጅት ወይም በወኪሉ አማካኝነት በማቅረብ ሊመዘገብ ይችላል።

## 47.በምርጫ የሚወዳደሩ የመንግስት ሰራተኞች መብት

1. ማንኛውም የመንግስት ሰራተኛ፡-

   ሀ/ በግሉ ወይም የፖለቲካ ድርጅት አባል በመሆን ለምርጫ መወዳደር ይችላል።

   ለ/ በምርጫ ውድድር በመግባቱ ምክንያት ተፈላጊውን የስራ ውጤት እስካመጣ ድረስ በውጤቱ ልክ ማግኘት ያለበትን ጥቅም ማጣት የለበትም።

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ዳኛ፣ ወታደር ወይም ፖሊስ በራሱ ወይም በፖለቲካ ድርጅት አማካኝነት እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ ከቀረበ የያዘውን የመንግስት ስራ መልቀቅ አለበት።

3. ዳኛ፣ ወታደር እና ፖሊስ በምርጫ ውድድር ጊዜ ማንኛውንም ተወዳዳሪ ለማስመረጥ በመደገፍ፣ በመናገር፣ በመፃፍና በመሳሰሉት ተሳታፊ አይሆንም።

4. ማንኛውም ወታደር ወይም ፖሊስ በፖለቲካ ድርጅት ስብሰባ ወይም በምርጫ እንቅስቃሴ መለዮውን አድርጎ መሳተፍ አይችልም፡፡

## 48.ለግል ዕጩ የድጋፍ ፊርማ ስለመስጠት

አንድ የመምረጥ መብት ያለው ነዋሪ በምርጫ ክልሉ ለውድድር ከቀረቡት መቀመጫዎች በላይ ለሆኑ እጩዎች የድጋፍ ፊርማ መስጠት አይችልም፡፡

## 49.የእጩዎች ብዛት ስለመለየት

1. በአንድ የምርጫ ክልል ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለመመረጥ የሚወዳደሩ እጩዎች ከ12 መብለጥ የለባቸውም፡፡

2. የእጩዎቹ ብዛት ከአስራ ሁለት ከበለጠ የፖለቲካ ድርጅቶች በቅድሚያ በእጩነት እንዲመዘገቡ ይደረጋል፡፡

3. በፖለቲካ ድርጅቶች የቀረቡት እጩዎች ከአስራ ሁለት በላይ ከሆኑ ባለፈው ምርጫ ከፍተኛ ድምፅ ላገኑ ከስድስት ለማይበልጡ ድርጅቶች ቅድሚያ ይሰጣል፡፡ ቀሪዎቹ የፖለቲካ ድርጅቶች በእጣ ይለያሉ።

4. በፖለቲካ ድርጅቶች የቀረቡ እጩዎች ከአስራ ሁለት በታች ከሆኑ የቀሩት ቦታዎች ባለፈው ምርጫ ከፍተኛ ድምፅ ባገኙ የግል ተወዳዳሪዎች እንዲሞሉ ይደረጋል፡፡

5. ባለፈው ምርጫ እኩል ድምፅ ያላቸው እጩዎች ካሉ በእጣ እንዲለዩ ይደረጋል።

6. በአንድ የምርጫ ክልል ለክልል ምክር ቤት ወይም ለሌሎች የምርጫ ደረጃዎች የሚቀርቡ እጩዎች ብዛት በቦርዱ ይወሰናል፡፡ የእጩ ቁጥር ቦርዱ ከወሰነው ቁጥር በላይ የሆነ እንደሆነ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 3፡4 እና 5 መሰረት እንደሁኔታው ይወሰናል፡፡
7. በዚህ አንቀፅ መሰረት እጩ ለመለየት የሚወጣው እጣ የሚመለከታቸው እጩዎች ወይም ተወካዮቻቸው በተገኙበት ይከናወናል፡፡

50.<u>ስለ እጩ መታወቂያ ካርድ</u>

1. ከላይ በአንቀፅ 49 መሰረት ለውድድር የሚቀርበው እጩ ከተለየ በኋላ በዕጩዎች መመዝገቢያ ቅፅ ስሙ እንዲሰፍር ተደርጎ የእጩነት መታወቂያ ካርድ ይሰጠዋል።
2. የፖለቲካ ድርጅት እጩዎች የእጩ መታወቂያ ካርድ ለእጩዎቹ በአካል ወይም ላስመዘገባቸው ድርጅት ሊሰጥ ይችላል፡፡

51.<u>ዕጩዎችን ለህዝብ ስለማሳወቅ</u>

እጩዎች በዚህ አዋጅ መሰረት ከተለዩ በኋላ ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት የምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት የተወዳዳሪ እጩዎችን ስም ዝርዝር ለህዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

52.<u>ስለእጩዎች መለያ ምልክት</u>

1. ማንኛውም እጩ የሚወዳደርበትን መለያ ምልክት ሊያቀርብ ወይም ቦርዱ ካዘጋጀው መለያ ምልክት ሊመርጥ ይችላል፡፡
2. የአንድ የፖለቲካ ድርጅት እጩዎች በሁሉም የምርጫ ደረጃዎች አንድ ዓይነት ምልክት ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡
3. የአንድ የፖለቲካ ድርጅት እጩዎች ለየምክርቤቱ ምርጫ በሁሉም የምርጫ ክልሎች አንድ ዓይነት መለያ ምልክት መጠቀም አለባቸው።
4. የምርጫ መለያ ምልክት በፓርቲም ሆነ በግል እጩ በይዞታነት አይያዝም፡፡ ሆኖም አንድ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ባለፈው ምርጫ የተጠቀመበትን ምልክት ቅድሚያ ተሰጥቶት እንዲመርጥ ሊደረግ ይችላል፡፡
5. በምርጫ መለያ ምልክት ላይ ለሚነሱ አለመግባባቶች ቦርዱ አስፈላጊውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡
6. ማንኛውም መለያ ምልክት፡-

ሀ/ ከሌሎች እጩዎች መለያ ምልክት ጋር የማይመሳሰል፣

ለ/ በብሔር ብሔረሰብ፣ በዘር፣ በሃይማኖት መካከል ጥላቻና ግጭት

የማይፈጥር፣

ሐ/ የጦርነት ወይም የሌላ ህገወጥ ድርጊት መልዕክት የማያስተላልፍ፣

መ/ ከፌደራልም ሆነ ከክልል መንግስታት ሰንደቅ አላማ ወይም አርማ ወይም ከሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች አርማ ወይም ከልዩ ልዩ ዓለምአቀፍ ድርጅቶች ዓርማና ሰንደቅ ዓላማ ወይም ከሃይማኖት ድርጅቶች ምልክቶች ጋር የማይመሳሰል፣

ሠ/ የህዝብን ሞራል፣ ስነ ምግባር እና የመሳሰሉትን የማይጥስ መሆን ይኖርበታል።

## 53.የእጩ ምልክቶችን መለወጥና መተካት

1. ቦርዱ በህትመት ምክንያት ወይም በአንቀፅ 52 ንዑስ አንቀፅ 6 መሰረት የአንድ ፖለቲካ ድርጅትን ወይም የግል እጩ መለያ ምልክትን ሊለውጥ ወይም እንዲለውጥ ሊያዝ ይችላል፡፡
2. የእጩ ምልክት በህትመት ወይም በሌላ ምክንያት እንዲለወጥ በቦርዱ ሲወሰን የእጩዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ጊዜ ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ ውሳኔውን ለፖለቲካ ድርጅቱ ወይም ለግል እጩው እንዲያውቀውና ተለዋጭ ምልክት እንዲያቀርብ ወይም እንዲመርጥ ይደረጋል፡፡
3. የፖለቲካ ድርጅትም ሆነ የግል እጩ ቀደም ሲል የመረጠውን ምልክት በሌላ ለመለወጥ ሲፈልግ የእጩዎች ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ጊዜ አንስቶ በአስር ቀናት ውስጥ ለውጡን ለቦርዱ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 54.የእጩ ከውድድር መውጣትና መተካት

1. አንድ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ከውድድር እራሱን ሊያገል ይችላል፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ከውድድር እራሱን ያገለለ የፖለቲካ ድርጅት እጩ ለወከለው የፖለቲካ ድርጅት በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡
3. የፖለቲካ ድርጅት እጩውን መለወጥ ወይም መተካት የሚችለው በእጩ ምዝገባ ወቅት ብቻ ነው።
4. እጩው በራሱ ፈቃድ ከምርጫው የለቀቀበት የፖለቲካ ድርጅት የእጩ ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ እስከሚያልቅ ድረስ ሌላ እጩ ሊተካ ይችላል፡፡ ሆኖም እጩው እራሱን ያገለለው በጊዜ ሰሌዳው የመጨረሻ ቀን ከሆነ እራሱን ካገለለበት ቀን ጀምሮ በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ሌላ እጩ እንዲተካ ይደረጋል፡፡

## 55.የእጩ መሞት

1. የአንድ የፖለቲካ ድርጅት እጩ የእጩ ምዝገባ ካለፈ በኋላ የሞተ እንደሆነ እጩው የሞተበት የፖለቲካ ድርጅት ከድምፅ መስጫው ቀን ከ15 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ ሌላ እጩ ሊተካ ይችላል።
2. አንድ ወደ ውድድር የገባ የፖለቲካ ድርጅት ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት በተባለው ጊዜ ውስጥ ተተኪ ካላቀረበ ምርጫው ባሉት እጩዎች በተያዘለት ጊዜ ውስጥ ይከናወናል።
3. አንድ የፖለቲካ ድርጅት እጩ የምርጫው ቀን ከመድረሱ 15 ቀናት ባነሰ ጊዜ ውስጥ የሞተ እንደሆነ በምርጫ ክልሉ የሚካሄደው ምርጫ ቆሞ እጩ የሞተበት የፖለቲካ ድርጅት እጩ እንዲተካ ተደርጎ ቦርዱ በሚወስነው መሰረት ሌላ ምርጫ ይካሄዳል።
4. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 3 የተገለፀው ቢኖርም እጩ የሞተበት የፖለቲካ ድርጅት ተተኪ እጩ ማቅረብ እንደማይችል በጽሁፍ የገለፀ እንደሆነ በቀሩት እጩዎች መካከል በተያዘለት ጊዜ ምርጫው ሊካሄድ ይችላል።
5. ከላይ በንዑስ አንቀፅ ሶስት በተገለፀው መሰረት የምርጫው ጊዜ የተለወጠ እንደሆነ በምርጫ ክልሉ ተመዝግበው የነበሩ መራጮች ሌላ ምዝገባ ሳይካሄድ፤ የሞተው እጩ ብቻ ተተክቶና ሌሎቹ እጩዎች እንዳሉ ሆነው ምርጫው ይካሄዳል።
6. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 5 መሠረት ለሚካሄደው ምርጫ በሞተው እጩ የሚተካው ግለሰብ እራሱን ለማስተዋወቅ የምርጫ ቅስቀሳ ማድረግ ይችላል፡፡

56.<u>**በአንድ ምርጫ ክልል ስለመወዳደር**</u>

1. ማንኛውም ሰው በአንድ የምርጫ ክልል ብቻ በእጩነት ይቀርባል፡፡
2. አንድ እጩ በእጩ ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ ውስጥ ከአንዱ የምርጫ ክልል ወደሌላው የምርጫ ክልል ተዛውሮ በህጉ መሰረት ለመወዳደር ይችላል። አፈፃፀሙ በቦርዱ ይወሰናል።

57.<u>**የእጩዎች ልዩ መብት**</u>

1. እጩዎች ከባድ ወንጀል ሲፈጽሙ እጅ ከፍንጅ ካልተያዙ በስተቀር ምርጫው እስኪጠናቀቅ ድረስ አይያዙም፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 1 ከተጠቀሰው በተለየ ሁኔታ ዕጩዎች ህገወጥ ድርጊት የፈፀሙ እንደሆነ ህጋዊ እርምጃ የሚወሰድባቸው የምርጫው ውጤት በቦርዱ አማካይነት በይፋ ለህዝብ ከተገለፀ በኋላ ብቻ ይሆናል።

3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 የተደነገገው ቢኖርም አሸናፊው ሰው በምርጫ ወቅት በፈጸመው ወንጀል የሚጠየቀው በሚመለከተው ምክር ቤት የህግ ከለላው ሲነሳ ነው።

## ምዕራፍ አራት

## የምርጫ ዘመቻ

### 58.የምርጫ ዘመቻ ስለማካሄድ

1. አንድ እጩ ተወዳዳሪ በዕጩነት ተመዝግቦ መታወቂያውን ካገኘበት ቀን አንስቶ ምርጫው ሁለት ቀን እስኪቀረው ድረስ ከአስተዳደሩም ሆነ ከማዘጋጃ ቤት ፈቃድ ሳይጠይቅ በፅሁፍ በማሳወቅ ብቻ ህጋዊ ግዴታዎቹን በማክበር በራሱም ሆነ በደጋፊዎቹ አማካይነት የድጋፍ ስብሰባዎችን የመጥራት ወይም ሰላማዊ ሰልፍ የማደራጀት መብት አለው፡፡ እንዲሁም ለምርጫ ውድድሩ ይጠቅሙኛል ያላቸውን መረጃዎች ከቦርዱ የማግኘት መብት ይኖረዋል።
2. እጩዎችና ደጋፊዎቻቸው ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ መሰረት የሚያካሂዱት የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ ድምፅ መስጠት ከመጀመሩ ከሁለት ቀናት በፊት መጠናቀቅ አለበት፡፡
3. የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ ህገመንግስቱና አግባብነት ያላቸውን ሌሎች ህጎች፣ የመራጮችን መብት፣ የሌሎች እጩዎችን የመወዳደር መብት በማክበር በሰላማዊና በዲሞክራሲያዊ መንገድ መካሄድ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሱት መብቶች በህግ ከተመለከቱት ድንጋጌዎች ውጭ ተፈፃሚ ሊደረጉ አይችሉም።
5. ምርጫው ሰላማዊ እና ፍትሃዊ በሆነ መልኩ ማከናወን እንዲቻል ቦርዱ የምርጫ ቅስቀሳ የስነምግባር ደንብ ያወጣል።

### 59.ስለመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም

1. በመንግስት ቁጥጥር ስር ያሉትን መገናኛ ብዙሃን ማለትም ሬዲዮ፣ ቴሌቪዥንና ጋዜጦችን የእጩ ደጋፊ የሆኑት የፖለቲካ ድርጅቶችና የህብረተሰብ ክፍሎች ያለ አድልዎ ለመጠቀም መብት አላቸው፡፡
2. እጩዎች በመንግስት የመገናኛ ብዙሃን ነፃ የአየር ጊዜ አግኝተው የመጠቀም መብት አላቸው፡፡
3. የመንግስት መገናኛ ብዙሃን አጠቃቀም ስርዓት የማስታወቂያ ሚኒስቴር[8] ከቦርዱ ጋር በመሆን በሚያወጣው ድልድል መሰረት ይከናወናል፡፡

[8] የማስታወቂያ ሚኒስቴር በአሁኑ ጊዜ የሌለ ሲሆን ይህ ስልጣኑ ለየትኛውም አካል አልተላለፈም፡፡

ድልድሉንም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶች እንዲያውቁት እና አስተያየት እንዲሰጡበት ይደረጋል፡፡

4. የመገናኛ ብዙሃንና የጋዜጠኞች የምርጫ አመዘጋገብ ስነምግባር ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ መሰረት ይወሰናል[9]፡፡

60.<u>የመንግስት አካላት ግዴታ</u>

በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የመንግስት አካላት ኃላፊዎች የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ እንዲሳካ ለማድረግ በየሃላፊነታቸው ስር የሚገኙትን የሬድዮ ጣቢያዎች፣ የስብሰባ አዳራሾች፣ ጋዜጦችና የመሳሰሉትን ዕቤዉዎችና ደጋፊዎቻቸው ያለአድልዎ ለመጠቀም የሚያስችላላ ሁኔታ የማመቻቸት ግዴታ አለባቸው።

61.<u>የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ የማይደረግባቸው ቦታዎች</u>

1. የሚከተሉት ቦታዎች የምርጫ ውድድር እንቅስቃሴ አይደረግባቸውም፣

ሀ/ ቤተክርስትያኖች፣

ለ/ መስጊዶች፣

ሐ/ ወታደራዊ ካምፖች እና ፖሊስ ጣቢያዎች፣

መ/ የመማር ማስተማር ሂደት ተግባር እየተከናወነ በሚገኝበት ወቅት በትምህርት ቤቶች እና በትምህርት ቤቶች አካባቢ በ500 ሜትር ዙሪያ ክልል፣

ሠ/ ህዝብ የእለት ከእለት ግብይት የሚፈፅምባቸው እና በተወሰኑ ቀናት በገጠርም ሆነ በከተማ በይፋ ገበያ የሚካሂድባቸው ቦታዎች በ500 ሜትር ዙሪያ ክልል፣

ረ/ የመንግስት ወይም የህዝብ መደበኛ ስራ በመከናወን ላይ የሚገኙባቸው የመንግስትና የህዝብ ተቋማት፣

ሰ/ ህዝባዊ ስብሰባ እየተካሄደ ባለባቸው ቦታዎች እና አካባቢዎች።

2. ዝርዝር አፈፃፀሙ ቦርዱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

<u>ምዕራፍ አምስት</u>

<u>ስለድምጽ አሰጣጥ</u>

62.<u>ስለምርጫ ጣቢያ ስራ መጀመር</u>

1. የድምፅ መስጠት ሂደት በሁሉም ምርጫ ጣቢያዎች ቦርዱ በሚወስነው ቀን አንድ ላይ ይጀመራል።

---

[9] የመገናኛ ብዙሃንና የጋዜጠኞች የምርጫ አዘጋገብ የስነ ምግባር የምርጫ ቦርድ ደንብ ቁጥር 6/2002 ወጥቷል፡፡(በነጋሪት ጋዜጣ ያልታተመ)፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም አስገዳጅ ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ የሚመለከታቸው ምርጫ ጣቢያዎች ስራቸውን በተለየ ቀን እንዲጀምሩ ቦርዱ ሊወስን ይችላል፡፡

3. ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት የድምፅ አሰጣጥ ስራ፡-

ሀ/ የፖለቲካ ድርጅት እና የግል እጩ ወኪሎች፣ የህዝብ ታዛቢዎች፣ የምርጫ አስፈፃሚዎች እና ስነስርአት አስተባባሪዎች በተገኙበት፣ እና

ለ/ የምርጫ ጣቢያ ኃላፊው የድምፅ መስጫ ሳጥን ባዶ መሆኑን ከላይ በ"ሀ" ለተገለጹት አካላት በማሳየት የምርጫ ሳጥኑ በተዘጋጀው ማሸጊያ ታሽጎ በታዛቢዎች ፊት ለፊት በቅርብ እይታና በግልፅ ስፍራ ከተቀመጠ ወይም ከተሰቀለ በኋላ ስለአጀማመሩ ቃለጉባኤ ተይዞ ቦርዱ ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው ቅፅ ላይ ከተሞላ በኋላ፣

ይጀመራል።

63.<u>**የምርጫ ጣቢያዎች ደህንነት**</u>

1. ጣቢያዎች የድምፅ መስጫ ዕለት ከመድረሱ በፊት ደህንነታቸውና ጥበቃቸው አስተማማኝ በሆነ ሁኔታ መዘጋጀት አለባቸው።
2. ለምርጫ ማስፈፀም ስራ ከተሰማሩት በስተቀር መራጮች ያልሆኑና ድምፅ የሰጡ ሰዎች በምርጫ ጣቢያው ክልል ውስጥ መገኘት የለባቸውም።
3. ማንኛውም ሰው ከምርጫ ጣቢያው በ500 ሜትር (አምስት መቶ ሜትር) ዙርያ ክልል ውስጥ በስካር፣ መሳሪያ በመያዝ ወይም በሌላ በማናቸውም ፀጥታን በሚያደፈርስ አኳኋን መገኘት የለበትም። በዚህ ሁኔታ ከተገኘም የምርጫ ጣቢያ ኃላፊው አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ሊያደርግ ይችላል።
4. የምርጫ ጣቢያዎችን ደህንነት የማስከበር ኃላፊነት የምርጫ ጽህፈት ቤቶች ኃላፊዎች ይሆናል። የምርጫ ፅህፈት ቤቶች ኃላፊዎች ወይም የምርጫ ጣቢያ የህዝብ ታዛቢ አካላት የጣቢያውን ደህንነት ለማስከበር የፖሊስ ኃይል እንደሚያስፈልግ ካመኑ እንዲመደብላቸው የሚመለከተውን አካል መጠየቅ ይችላሉ፡፡ ሆኖም የህዝብ ታዛቢዎች ጥያቄያቸውን የሚያቀርቡት በምርጫ ጽህፈት ቤቶች ኃላፊዎች አማካይነት ይሆናል፡፡
5. የምርጫው ጣቢያ ኃላፊ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ መግባት የሌለበትን ሰው ወይም የምርጫውን እንቅስቃሴ ለማወክ የሞከረን ማንኛውም ሰው ከምርጫ ጣቢያ እንዲወጣ ሊያዝ ይችላል፡፡ ይህን ትዕዛዝ ያላከበረ ሰው ካለ የፖሊስ ሀይል ጠርቶ ከምርጫ ጣቢያው እንዲወጣ ያደርጋል፡፡ ፖሊሱም

ይህን ተግባሩን እንደፈፀመ ከምርጫ ጣቢያው በመውጣት ወደተመደበበት ቦታ ይሄዳል።

6. ማንኛውም ህገ ወጥ ሰነድ ይዞ በምርጫ ጣቢያ ስለመገኘቱ አሳማኝ ጥቆማ የቀረበበትን ሰው የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ የሁሉም የፖለቲካ ድርጅት እና የግል እጩ ወኪሎች እንዲሁም የህዝብ ታዛቢዎች በተገኙበት ተጠርጣሪውን ሊፈትሽ ይችላል። ተጨባጭ ሆኖ ከተገኘም አስፈላጊው ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ያደርጋል።

64.<u>የድምጽ መስጫ ሰዓት</u>

1. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር የድምፅ መስጫ ሰዓት ከጠዋቱ 12 ሰዓት እስከ ምሽቱ 12 ሰአት ድረስ ይሆናል፡፡
2. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ የድምፅ መስጫ ሰዓት የወሰነ እንደሆነ በልዩ ሁኔታ የተወሰነውን የድምፅ መስጫ ሰአት ህዝቡ በይፋ እንዲያውቀው ያደርጋል፡፡
3. የድምፅ መስጫ ሰአት ሲያበቃ የምርጫ ጣቢያው ይዘጋል፡፡ ሆኖም በምርጫ ጣቢያው ቅጥር ግቢ ውስጥ ገብተው ድምፅ ለመስጠት በመጠባበቅ ላይ ያሉ መራጮች ድምፅ መስጠት አለባቸው፡፡
4. ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰው ቢኖርም ቦርዱ የምርጫውን ነፃና ፍትሃዊነት ይበልጥ ያሰፍናል ብሎ ካመነ የድምፅ መስጫ ሰአትን ሊያራዝም ይችላል፡፡
5. የምርጫ ጣቢያዎች ለምርጫ ከመከፈታቸውም ሆነ ድምፅ አሰጣጡ አልቆ ከተዘጉ በኋላ ከምርጫ አስፈፃሚዎች፣ ከህዝብ ታዛቢዎች፣ ከዕጩ ተወካዮች እና ከተፈቀደላቸው የምርጫ ታዛቢዎች በስተቀር ማንኛውም ሰው ወደ ምርጫ ጣቢያው መግባት አይችልም፡፡

65.<u>ድምፅ ስለመስጠት</u>

1. ማንኛውም መራጭ በአካል በመገኘት በሙሉ ነፃነት ድምፅ ይሰጣል።
2. እያንዳንዱ መራጭ ድምፅ የሚሰጠው አንድ ጊዜ ብቻ ይሆናል፣
3. ማንኛውም መራጭ ድምፅ ለመስጠት የሚችለው በመራጭነት በተመዘገበበት የምርጫ ጣቢያ ብቻ ሆኖ፡-

   ሀ/ የመራጮች መታወቂያ ካርድ ሲኖረው፣

   ለ/ በመራጮች መዝገብ ላይ ስሙ ሰፍሮ ሲገኝ፣

   ሐ/ ድምፅ ያልሰጠ መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

4. ቦርዱ በተለየ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ሁሉም መራጮች በተመሳሳይ የጊዜ ገደብ ውስጥ ድምፃቸውን ይሰጣሉ።

66. ድምፅ የመስጠት ሂደት

1. እያንዳንዱ መራጭ የመራጮች ምዝገባ መታወቂያ ካርዱን ለምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚዎች ካስረከበ በኋላ የምርጫ አስፈፃሚዎቹ የመራጩን ማንነት ባቀረበው ማስረጃ ይለያሉ።
2. የመራጩ ማንነት ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት ከተለየና ቀደም ሲል ያልመረጠ መሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ በመራጮች መዝገብ ውስጥ ለፊርማ በተዘጋጀው አምድ ላይ እንዲፈርም ይደረጋል፡፡
3. መራጩ በመዝገብ ላይ ከፈረመ በኋላ አውራጣቱን፤ አውራ ጣት ከሌለው ማንኛውንም ሌላ ጣት በተዘጋጀው የማይለቅ ቀለም እንዲቀባ ከተደረገ በኋላ የድምፅ መስጫ ወረቀት ተሰጥቶት ወደ ሚስጢር ድምፅ መስጫው ክፍል ይገባል፡፡ጣቶች የሌለው ከሆነ የምርጫ አስፈፃሚዎች አለመምረጡን ካረጋገጠ በኋላ እንዲመርጥ ይደረጋል።
4. መራጩ ወደ ምስጢር ድምፅ መስጫው ክፍል ገብቶ የሚመርጠው እጩ መለያ ምልክት በሚገኝበት ባለአራት ማዕዘን ቦታ ላይ የ"x" ምልክት ካደረገበት ወይም በጣት አሻራው ከፈረመበት በኋላ የድምፅ መስጫ ወረቀቱን እጥፎ በታዛቢዎች ፊት ለፊት በቅርብ እይታ በግልፅ ስፍራ በተቀመጠው የድምፅ መስጫ ሳጥን ወይም ኮሮጆ ውስጥ ይከታል፡፡
5. የማያነቡና የማይፅፉ መራጮች ከጣቶቻቸው አንዱን ለዚህ በተዘጋጀው ቀለም ከነከሩ በኋላ ከሚመርጡት ዕጩ መለያ ምልክት ትይዩ በሚገኘው ባለ አራት ማዕዘን ክፍት ቦታ ላይ የጣት አሻራቸው እንዲያርፍ በማድረግ ድምፅ ይሰጣሉ።
6. መራጩ የተሰጠውን የድምፅ መስጫ ወረቀት ባግባቡ ሳይጠቀምበት የቀረ ወይም የተበላሸበት እንደሆነ ይህንኑ መልሶ በምትኩ ሌላ በመቀበል ድምፅ ለመስጠት ይችላል፡፡
7. የምርጫ ጣቢያ ኃላፊ ከላይ በንኡስ አንቀፅ 6 መሰረት ተመላሽ የተደረገውን የድምፅ መስጫ ወረቀት የተለየ ምልክት ወይም የተበላሸ የሚል በጀርባው ላይ አድርጎበት ለዚሁ በተዘጋጀው ሳጥን ውስጥ ይከተዋል፡፡

67. ድጋፍ የማፈልጉ መራጮችን በተመለከተ

1. በምርጫ ድምፅ አሰጣጥ ምልክት ለማድረግና የድምፅ መስጫ ወረቀቱን ወደ ድምፅ መስጫው ሳጥን ወይም ኮሮጆ ለመክተት እርዳታ የሚያስፈልገው ማንኛውም መራጭ የሚረዳውን ሰው እራሱ የመወሰን መብት አለው፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ በድጋፍ ፈላጊው የተመረጠው ሰው ዕድሜ 18 አመት እና ከዚያ በላይ ሆኖ እጩ ወይም የእጩ ተወካይ መሆን የለበትም፡፡

68.<u>ድምፅ የመስጠት ሂደት የማይቋረጥ ስለመሆኑ</u>

1. ድምፅ የመስጠት ሂደት ሊቋረጥ ወይም ሊቆም አይችልም።
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፡-
   ሀ/ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት በተለያየ ምክንያት ለጥቂት ጊዜም ቢሆን ከተቋረጠና ሁኔታው መስተካከሉ በምርጫ አስፈፃሚዎች ከታመነበት በቃለ ጉባኤ ተይዞ ወዲያውኑ የድምፅ አሰጣጡ ሂደት ሊቀጥል ይችላል፡፡
   ለ/ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ የተቋረጠበት ሁኔታ ከአቅም በላይ ሆኖ ሊስተካከል ካልቻለ ሁኔታው በቃለ ጉባኤ ተይዞ የድምፅ አሰጣጥ ሂደቱ ባለበት ቆሞ ወዲያውኑ አጠቃላይ ሁኔታው ለበላይ ምርጫ ጽህፈት ቤት ሪፖርት ይደረጋል፡፡
3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2(ለ) መሰረት የተቋረጠ የድምፅ አሰጣጥ ቦርዱ በሚወስነው መሰረት በሌላ ጊዜ ይካሄዳል፡፡

69.<u>ድምፅ መስጠትን ስለመቃወም</u>

1. ማንኛውም መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከመሰጠቱ በፊት የእጩ ተወካይ ድምፅ በመስጠት ሂደት ላይ ያለው ሰው የመራጭነት መብት የሌለው ወይም በምርጫ ጣቢያው በመራጭነት ያልተመዘገበ ነው በማለት ሊቃወም ይችላል፡፡
2. አንድ መራጭ የድምፅ መስጫ ወረቀት ቢከለከል እራሱ ወይም ከእጩ ተወካዮች አንዱ ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
3. የእጩ ተወካይ ወይም መራጩ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 ከተደነገጉት መቃወሚያ ነጥቦች ውጭ በሆነ በማንኛውም የምርጫ አስፈፃሚ የእጩ ተወካይ ወይም በሌላ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ በተገኘ ሰው አግባብ ያልሆነ ድርጊት ተቃውሞ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
4. የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ የቀረበውን አቤቱታ ከተመለከተ በኋላ አቤቱታ ላቀረበው ሰው ወይም አካል ውሳኔውን ያሳውቃል።

5. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊ በዚህ አንቀፅ መሰረት የቀረቡ ቅሬታዎችንና ለቅሬታዎቹ የተሰጡ መልሶችን የፅሁፍ ሰነድ በመረጃነት ይይዛል፡፡

70.ጊዜያዊ ድምጽ ስለመስጠት

1. ከላይ በአንቀፅ 69 መሰረት ድምፅ እንዳይሰጥ ተቃውሞ የቀረበበት ሰው ጊዜያዊ ድምፅ መስጠቱ አስፈላጊ ነው ብሎ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ካመነ መራጩ ለዚህ በተዘጋጀው ፖስታ ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡
2. ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት የተሰጠ ጊዜያዊ ድምፅ በአንቀፅ 95 መሰረት ውሳኔ እንዳገኘ በቆጠራ የሚካተት ወይም ውድቅ የሚደረግ ይሆናል፡፡

71.ስለ ድምፅ መስጫ ወረቀት

1. ቦርዱ ለያንዳንዱ የምርጫ አይነት መራጩ በግልፅ ሊረዳው የሚችል እስከተቻለ ድረስ ለማጭበርበር የማይመች የድምፅ መስጫ ወረቀት ያዘጋጃል።
2. ቦርዱ የእጩዎች ፎቶግራፍ፣ የእጩ መለያ ምልክት፣ የእጩዎች ሙሉ ስምና የፖለቲካ ድርጅታቸው መጠሪያ የታተመበት የድምፅ መስጫ ወረቀት ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡
3. ቦርዱ በየምርጫ ጣቢያው በተመዘገበው መራጭ ቁጥር ልክ እና ለመጠባበቂያ የሚሆን የተወሰነ ቁጥር ያለው የድምጽ መስጫ ወረቀት ይልካል።
4. ቦርዱ እና በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈፃሚዎች ለድምፅ መስጫ ወረቀቶች ከፍተኛ ጥንቃቄና ጥበቃ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።
5. ማንኛውም የምርጫ ሰነድ ከአንዱ ሰው ወደሌላው ሰው በሚተላለፍበት ጊዜ ህጋዊ የርክክብ ስርዓትን ተከትሎ መፈፀም አለበት፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## የድምፅ ቆጠራና ውጤት አገላለጽ

72.የቆጠራ ቦታ

1. የማንኛውም ምርጫ ድምፅ ቆጠራ የሚካሄደው ድምፅ በተሰጠበት ምርጫ ጣቢያ ነው፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም አስገዳጅ በሆነ ምክንያት የምርጫ ጣቢያው የምርጫ አስፈፃሚ ለምርጫ ክልሉ ጥያቄ አቅርቦ ሲፈቀድ ወይም የምርጫ ክልሉ የምርጫ አስፈፃሚ ሲወስን ቆጠራው በምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት ይካሄዳል፡፡

3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት የሚካሄደው ቆጠራ የምርጫ ጣቢያው የእጩ ወኪሎችና የህዝብ ታዛቢዎች በተገኙበት ይሆናል፡፡

4. ለዚህ አንቀፅ አፈፃፀም ቦርዱ መመሪያ ሊያወጣ ይችላል።

## 73.የድምጽ ቆጠራ አጀማመር ሂደት

1. ድምፅ አሰጣጡ እንደተጠናቀቀ የምርጫ ጣቢያው ሀላፊ ቆጠራ ለመጀመር የእጩ ወኪሎች እና የህዝብ ታዛቢዎች እንዲገኙ በማድረግ፡-

   ሀ/ በዕለቱ ድምፅ የሰጡ መራጮችን ብዛት ይመዘግባል፣

   ለ/ የተበላሹና ስራ ላይ ያልዋሉ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች ብዛት ይመዘግባል፡፡

2. ድምጽ ቆጠራ ከመጀመሩ በፊት የድምጽ መስጫው ሳጥን እሽግ ያልተከፈተ እና ድምጽ መስጠት ከመጀመሩ በፊት በታሸገበት ሁኔታ መቆየቱን፣ ሳጥኑም ያልተቀደደና ብልሽት ያልደረሰበት መሆኑን ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሱት አካላት ካረጋገጡ እና ቃለጉባኤ ከተያዘ በኋላ እሽጉን በመክፈት ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች በሙሉ ይወጣሉ። ሳጥኑም ባዶ መሆኑ ይረጋገጣል፡፡

3. ለእያንዳንዱ ዕጩ ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች ተለይተው ይቆጠራሉ፡፡

4. ምርጫው የተካሔደው ለተለያዩ ምክር ቤቶች ከሆነ በመጀመርያ ለየምክር ቤቱ የተሰጡት የድምጽ መስጫ ወረቀቶች ከተለዩ በኋላ በንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት የአንዱ ምክር ቤት ተቆጥሮ እንዳለቀ የሌላው በመቀጠል ይቆጠራል።

5. የድምፅ ቆጠራ ሂደት በቦርዱ ውሳኔ ካልሆነ በስተቀር ሊቋረጥ ወይም ሊቆም አይችልም።

## 74.ስለ ዋጋ አልባ የድምፅ መስጫ ወረቀቶች

1. ድምፅ የተሰጠባቸው ወረቀቶች ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ዋጋ አልባ ሊሆኑ ይችላሉ፡-

   ሀ/ የመራጩ ማንነት በስም የተገለፀበት ከሆነ፣

   ለ/ ከተመራጮች ቁጥር በላይ ምልክት የተደረገበት ከሆነ፣

   ሐ/ ምንም ምልክት ያልተደረገበት ከሆነ፣

   መ/ መራጩ ማንን እንደመረጠ መለየት የሚያስቸግር ከሆነ፣

   ሠ/ ህጋዊ የድምፅ መስጫ ወረቀት ያልሆነ ወይም በምርጫ ጣቢያው ያልተሰራጨ የድምፅ መስጫ ወረቀት ከሆነ፣

2. ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት ዋጋ አልባ የተደረጉ ወረቀቶች በጀርባቸው ‹‹ውድቅ›› የሚል ፅሁፍ ተፅፎባቸው ለብቻቸው ተቆጥረው ይታሸጋሉ፡፡

75.ስለ ድምጽ ቆጠራ መጠናቀቅ

በምርጫ ጣቢያ የሚካሄደው የድምጽ ቆጠራ እንደተጠናቀቀ፡-

1. በወቅቱ በቦታው የተገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች የህዝብ ታዛቢዎች እና የእጩ ወኪሎች አጠቃላይ የድምፅ አሰጣጥ እና የቆጠራው ሂደት እንዲሁም ውጤቱ ትክክል ስለመሆኑ ለዚሁ በሚዘጋጀው ቃለጉባኤ እና የምርጫ ጣቢያ ውጤት መተማመኛ ቅፅ ላይ ይፈራረማሉ፡፡ ሆኖም በሂደቱና በውጤቱ ቅሬታ ያለው የእጩ ወኪል ቅሬታውን ሊያስመዘግብ ይችላል።
2. የተቆጠረው የድምፅ መስጫ ወረቀት ታሽጎ ከላይ በንዑስ አንቀፅ /1/ መሰረት የተፈረመው የምርጫ ጣቢያ ውጤት መተማመኛ ቅፅ፣ ቃለጉባዔ እና የምርጫ ውጤት ማሳወቂያ ቅፅ ለምርጫ ክልሉ ይላካል።
3. የድምፅ ቆጠራ ውጤት መተማመኛውን ለፈረመው የእጩ ወኪል አንድ ቅጂ ወዲያውኑ ይሰጣል።

76.የቆጠራ ውጤት አገላለፅ

1. በምርጫ ጣቢያ የተደረገ የቆጠራ ውጤት ቆጠራው በተጠናቀቀ በአንድ ሰዓት ውስጥ በምርጫ ጣቢያው በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ወጥቶ ለህዝብ በይፋ ይገልፃል።
2. የምርጫ ክልል የምርጫ ጽህፈት ቤቶች የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ውጤት ከየምርጫ ጣቢያ እንደደረሳቸው ተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው በተገኙበት አዳምረው የተገኘውን ውጤት ለህዝብ ይፋ ያደርጋሉ።
3. እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን ለመለየት አስቸጋሪ የሆነ እንደሆነ እኩል ድምፅ ያገኙት ተወዳዳሪዎች ብቻ ተለይተው ቦርዱ በሚወስነው ጊዜ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ይደረጋል።
4. የምርጫ ክልል የምርጫ ኃላፊዎች ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት ይፋ ያደረጉትን ውጤት፡-

ሀ/ ለተወዳዳሪዎች ወይም ወኪሎቻቸው የውጤት መተማመኛ ይሰጣሉ፣

ለ/ በውጤት ማሳወቂያ ቅፅ ሞልተው አንድ ቅጂ ለቦርዱ ጽህፈት ቤት እና በየደረጃው ለሚገኙ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤቶች ይልካሉ፡፡

5. ቦርዱ በአጠቃላይ የምርጫ ውጤት ከየምርጫ ክልሉ ተጠናቆ እስኪደርሰው ድረስ ከየምርጫ ክልሉ የመጣለትን የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት የምርጫ ውጤት በጊዜያዊነት በቦርዱ ጽህፈት ቤት ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡
6. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰው አሰራር ለአካባቢ ምርጫ ውጤትም እንደሁኔታው ተግባራዊ ይሆናል፡፡

77.<u>ይፋዊ መግለጫ</u>

የምርጫው ሂደት ከተጠናቀቀና አስፈላጊ መረጃዎች ከተሰበሰቡ በኋላ ቦርዱ ይፋ ባወጣው የጊዜ ሰሌዳ መሰረት ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱትን ነጥቦች የያዘ ይፋዊ መግለጫ ያወጣል።

1. የተመዘገቡ መራጮች ቁጥር፣
2. ድምፅ የሰጡ መራጮች ቁጥር፣
3. ድምፅ የሰጡና ያልሰጡ ተመዝጋቢ መራጮች መጠን በመቶኛ፣
4. የተመረጡ እጩዎች የስም ዝርዝርና የተመረጡበት የምርጫ ክልል፣
5. የአሸናፊ ፖለቲካ ድርጅቶች ስምና ለየምክርቤቱ ያሸነፉትን መቀመጫ ብዛት፣
6. ጥቅም ላይ የዋለ፣ ያልዋለ፣ ከጥቅም ውጭ የሆነ የድምፅ መስጫ ወረቀት እያንዳንዱ እጩ በየምርጫ ጣቢያው ያገኘው የድምፅ ውጤት እና ሌሎች ዝርዝር መረጃዎች ከየምርጫ ክልሉ እንደደረሰው እና አጠናቅሮ እንደጨረሰ ይፋ ያደርጋል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሰባት</u>

## <u>ስለምርጫ ታዛቢዎች፣ የእጩ ወኪሎች፣ ጋዜጠኞችና የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ</u>

78.<u>ስለ ምርጫ ታዛቢዎች</u>

1. የምርጫውን ሂደት ለመታዘብ የሚፈልጉ የአገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ከቦርዱ በሚሰጥ ፈቃድ ምርጫውን ለመታዘብ ይችላሉ፡፡
2. አገሪቱ የተቀበለቻቸው ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው መንግስት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የውጭ የምርጫ ታዛቢዎችን ሊጋብዝ ይችላል።

79.<u>ስለፍቃድ አሰጣጥ</u>

1. ቦርዱ የምርጫ የታዛቢነት ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን ያቀረበው ድርጅት፤

ሀ/ በህጋዊ መንገድ ፈቃድ አውጥቶ የሚንቀሳቀስ የአገር በቀል ድርጅት መሆኑን፣

ለ/ ከማንኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት የፀዳ መሆኑን፡

ሐ/ ለምርጫ ፍትሃዊነት ነፃነትና ሰለማዊነት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ዝግጅት ማድረጉን፡

መ/ ድርጅቱ የሚያሰማራቸው ግለሰቦች ምርጫውን በገለልተኝነት ለመታዘብ ችሎታ ያላቸው መሆኑን በማጣራትና በቦርዱ የተዘጋጀውን የምርጫ ታዛቢዎች የስነ ምግባር ደንብ ወይም መመሪያ መቀበላቸውን ድርጅቱንና ወኪሎቹን በማስፈረም የታዛቢነት ፈቃድና መታወቂያ ካርድ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2. ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀፅ የተደነገገው ባለመሟላቱ ፈቃድ የከለከለ እንደሆነ ይህንኑ ለአመልካቹ በፅሁፍ ያሳውቃል። [10]

3. ማንኛውም የምርጫ ታዛቢ ከስነምግባር ደንቡና ከገባው ግዴታ ውጭ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ቦርዱ እንደሁኔታው ለግለሰቡም ሆነ ለወከለው ድርጅት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቱን እንዲያርም ለማድረግ ወይም ፈቃድን እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ ሊወስድ ይችላል።

80.<u>የምርጫ ታዛቢ መብት</u>

1. የምርጫ የታዛቢነት ፈቃድ የተሰጠው የድርጅት ወኪል በምርጫ ጣቢያ በመዘዋወር የምርጫውን ሂደት የመከታተልና ተገቢ መረጃ ጠይቆ የማግኘት መብት አለው፡፡

2. የምርጫ ታዛቢዎች የምርጫውን ሂደት በሚመለከት የታዘቧቸውን ወይም ያጋጠሟቸውን ጉድለቶች ለቦርዱ ጽህፈት ቤት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡

81.<u>የምርጫ ታዛቢዎች ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ፈቃድ ያገኘ የምርጫ ታዛቢ፡-

ሀ/ የታዛቢነት መታወቂያውን መያዝና ማሳየት አለበት፡፡

ለ/ የምርጫ አስፈፃሚዎች የሚሰጡትን መመሪያ ማክበር አለበት፡፡

ሐ/ የምርጫው ሂደት በትክክልና በብቃት እንዳይካሄድ ከሚያደርግ ማንኛውም ተግባር መቆጠብ አለበት፡፡

መ/ ቦርዱ ያወጣውን የስነ-ምግባር ደንብ ማክበር አለበት፡፡

[10] በአማርኛው ቅጂ ላይ ንዑስ አንቀፅ (1) በስህተት ሁለቴ የተፃፈ እና ንዑስ አንቀፅ (3) የሌለው በመሆኑ በእንግሊዘኛው ቅጅ መሰረት የተስተካከለ፡፡

ሠ/ የምርጫ ታዛቢው የምርጫው ውጤት በይፋ ከመገለጹ በፊት በአገር ውስጥም ሆነ ከአገር ውጭ ሆኖ ስለምርጫው አስተያየቱን መስጠት የተከለከለ ነው።

ረ/ ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

2. ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የውጭ የምርጫ ታዛቢ ቦርዱ በሚያወጣው መመሪያ መሰረት በገለልተኝነት፣ የሀገሪቱን ሉአላዊነትና ልዩ ልዩ ህጎች በማክበር የምርጫውን ሂደት መታዘብ ይችላል።

## 82.<u>የህዝብ ታዛቢዎች</u>

1. እያንዳንዱ፡-

ሀ/ ምርጫ ክልል በአንቀፅ 20 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የሚመረጡ 3 የህዝብ ታዛቢዎች ይኖሩታል።

ለ/ ምርጫ ጣቢያ መራጩ ህዝብ በይፋ በሚደረግለት ጥሪ መሰረት በሚያደርገው ስብሰባ የሚመረጡ 5 የምርጫ ጣቢያ ታዛቢዎች ይኖሩታል፡፡

2. ቦርዱ የህዝብ ታዛቢዎች በሚመረጡበት ጊዜ ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅቶች እና የግል እጩዎች እንዲገኙ በጽሁፍ እንዲጋበዙ ያደርጋል።

3. የህዝብ ታዛቢዎችን በሚመለከት ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

## 83.<u>የፖለቲካ ድርጅት እና የግል ዕጩ ወኪሎች</u>

1. ማንኛውም ለምርጫ ዕጩ ያቀረበ የፖለቲካ ድርጅት የምርጫውን ሂደት የሚከታተልለት፡-

ሀ/ ለሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት አንድ ተቀማጭ ወኪል፣

ለ/ በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ስር ለሚገኝ ለእያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ አንድ ተቀማጭ ወኪል፣

መመደብ ይችላል።

2. ማንኛውም የግል ዕጩ፡-

ሀ/ ለሚወዳደርበት የምርጫ ክልል አንድ ተቀማጭ ወኪል፣

ለ/ በሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ስር ለሚገኙ ለእያንዳንዱ የምርጫ ጣቢያ አንድ ተቀማጭ ወኪል መመደብ ይችላል።

3. እያንዳንዱ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ በአንድ የምርጫ ክልል ከ5 የማይበልጡ ተዘዋዋሪ ወኪሎች መመደብ ይችላል፡፡

## 84.<u>የወኪሎችን ዝርዝር ስለማሳወቅ</u>

1. ማንኛውም ዕጩ ያቀረበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል ዕጩ የተቀማጭና የተዘዋዋሪ ወኪሎችን ስም ዝርዝር ተጠባባቂ ወኪሎችን ጨምሮ ከድምፅ መስጫው ዕለት 10 ቀን አስቀድሞ ለሚወዳደርበት የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት።
2. የምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት በየምርጫ ጣቢያው የተመደቡ ተቀማጭና ተዘዋዋሪ ወኪሎችን ለየምርጫ ጣቢያው በወቅቱ ያሳውቃል።

85. <u>የወኪሎች መብት</u>

1. የማንኛውም እጩ ተቀማጭ ወኪል በተመደበበት ቦታ የምርጫውን ሂደት የመከታተል፣ ቅሬታውን የማቅረብ እና መረጃ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. የማንኛውም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ተዘዋዋሪ ወኪል በተመደበበት ቦታ የምርጫ ሂደትን በሚመለከት ተገቢ መረጃ የማግኘት መብት አለው።
3. የማንኛውም ተወዳዳሪ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ወኪል ያለምንም ተፅዕኖ በህግ የተሰጠውን የውክልና ተግባር ያከናውናል።
4. ስለ አፈፃጸሙ ቦርዱ ዝርዝር መመሪያ ያወጣል፡፡

86. <u>የወኪሎች ግዴታ</u>

ማንኛውም ተዘዋዋሪም ሆነ ተቀማጭ ወኪል፡-

1. የምርጫ ኃላፊው የሚሰጠውን ትዕዛዝ ማክበር አለበት።
2. አግባብ ባለው አካል ሲጠየቅ መታወቂያውን ማሳየት አለበት።
3. የምርጫ ህጉን ማክበርና በህግ የተከለከሉ ተግባራትን ከመፈጸም መቆጠብ አለበት።
4. ቦርዱ የሚያወጣውን የወኪሎች የስነምግባር ደንብ መፈረምና ማክበር ይገባዋል።

87. <u>የወኪል አለመኖር</u>

1. ማንኛውም እጩ ወይም የእጩ ወኪል በራሱ ምክንያት በተመደበበት ቦታ ባልተገኘበት ወቅት የተካሄዱ የምርጫ ተግባራት ውድቅ እንዲደረግለት ሊጠይቅ አይችልም።
2. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ወኪሉ ያልተገኘው ሆን ተብሎ በተፈጠረ ምክንያት መሆኑ ሲረጋገጥ ይህ አንቀጽ ተፈፃሚ አይሆንም።

88. <u>መታወቂያ ካርድ ስለመስጠት</u>

ቦርዱ ለህዝብ ታዛቢዎች፣ ለተቀማጭና ተዘዋዋሪ ወኪሎች፣ ለጋዜጠኞች እና ለምርጫ ታዛቢዎች መታወቂያ ካርድ አዘጋጅቶ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

89.**<u>የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት</u>**

1. ቦርዱ የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም መራጩ ስለምርጫው በቂ ግንዛቤ የሚያገኝበት ስልት በመቀየስ የስነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፡፡
2. ቦርዱ የስነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት በሌላ ድርጅት መስጠት አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማስተማር ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል።
3. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው አግባብ ካለው አካል ጋር በመዋዋል የስነዜጋ እና የመራጮች ትምህርት እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል።

90.**<u>የፈቃድ አሰጣጥ</u>**

ቦርዱ መራጮችን የማስተማር ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብለት፡-

1. ጥያቄውን ያቀረበው አካል፡-

   ሀ/ በህጋዊ መንገድ ፈቃድ አውጥቶ የሚንቀሳቀስ ገለልተኛ የአገር በቀል ድርጅት መሆኑን፣

   ለ/ ለመራጮች ትምህርት ያወጣውን መስፈርት የሚያሟላ መሆኑን፣

   ሐ/ ተግባሩን በብቃት ሊወጣ የሚችል መሆኑን፣

   መ/ የተወከለው ግለሰብ ከማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ገለልተኛ መሆኑን፣

   ሠ/ የድርጅቱ ተወካይ ተግባሩን ለመፈፀም ብቃት ያለው መሆኑን፣

   ረ/ ድርጅቱ የስነዜጋና መራጮች ትምህርትን በማስፋፋት ፍትሃዊና ነፃ ምርጫ ለማካሄድ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑን፣

   በማጣራትና ቦርዱ ያዘጋጀውን የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ ስነምግባር ደንብ መቀበላቸውን ድርጅቱንና ወኪሎቹን በማስፈረም የማስተማር ፈቃድና መታወቂያ ካርድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተዘረዘሩትን ለማያሟላ አካል ፈቃድ አይሰጥም አለመፍቀዱንም በፅሁፍ ለአመልካች ያሳውቃል።
3. ማንኛውም የማስተማር ፈቃድ የተሰጠው ተቋምም ሆነ ተወካይ ከስነምግባር ደንቡና ከገባው ገዴታ ውጪ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ቦርዱ እንደሁኔታው በግለሰቡም ሆነ ለወከለው ድርጅት ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቱን

እንዲያርም ለማድረግ ወይም ፈቃዱን እስከመሰረዝ የሚደርስ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል።

4. በአንድ ምርጫ ወቅት የመራጮች ትምህርት ለመስጠት በቦርዱ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት በዚያው ምርጫ ላይ በምርጫ ታዛቢነት መሳተፍ አይችልም።

91.<u>ስለ ጋዜጠኞች</u>

1. ማንኛውም ጋዜጠኛ ቦርዱ የሚሰጠውን መታወቂያ በመያዝ የምርጫውን ሂደት ለመከታተል ይችላል።
2. ማንኛውም ጋዜጠኛ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሰ ተግባሩን ሲያከናውን ምርጫውን ከሚያደናቅፍ ማንኛውም ተግባር መቆጠብ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ጋዜጠኛ የምርጫው ውጤት በይፋ ከመገለጹ በፊት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ ሆኖ ስለምርጫው ውጤት አስተያየት መስጠት የለበትም፡፡
4. ማንኛውም ጋዜጠኛ ቦርዱ የሚያወጣውን የምርጫ አዘጋገብ የስነምግባር ደንብ ማክበር አለበት፡፡

## <u>ምዕራፍ ስምንት</u>

## <u>በምርጫ ሂደት ስለሚነሱ አቤቱታዎችና ክርክሮች</u>

92.<u>መርህ</u>

1. ቦርዱ በምርጫ ሂደት የሚነሱ አለመግባባቶች በውይይትና በስምምነት ለመፍታት የሚያስችል የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረክ በየደረጃው ያቋቁማል።
2. በዚህ ምዕራፍ መሰረት ክርክሮች እና አቤቱታዎች የቀረቡለት ውሳኔ ሰጭ አካል የምርጫው ሂደት ነፃ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ሆኖ እንዲቀጥል ለማስቻል የምርጫውን የጊዜ ሰሌዳ መሰረት በማድረግ መቀበልና አፋጣኝ ውሳኔ መስጠት ይኖርበታል።
3. ማንኛውም አቤቱታ በፅሁፍ መቅረብ አለበት፡፡
4. ቦርዱ ለሚቀርቡለት አቤቱታዎች በወቅቱ መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችለው አሰራር በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ ፅህፈት ቤቶች ይዘረጋል።
5. የምርጫ ክልሉ ኃላፊ ምርጫውን በሰላማዊና ህጋዊ በሆነ መንገድ ለማከናወን አስፈላጊ በሆነ መጠን የፖሊስ ሀይልን ትብብር ሊጠይቅ ይችላል።

6. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 79፣ 90 እና 91 ከተደነገገው በስተቀር ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ፡ ቦርዱ በምርጫ ሂደት የሚሰጠውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በመቃወም ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
7. ቦርዱ ወይም በየደረጃው የሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚዎች የቀረቡ አቤቱታዎችን ለመፍታት የሚያስችል የመንግስት አካልን ወይም መረጃ ሊሰጥ የሚችል ማንኛውም ሰው በአካል እንዲቀርብ ወይም የፅሁፍ ወይም ሌላ ማስረጃ እንዲያቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡
8. ቦርዱ የምርጫ ሂደትን የሚያደናቅፍ ማናቸውም ወንጀል መፈፀሙን ወይም በመፈፀም ላይ መሆኑን ሲያውቅ ወይም በመረጃ የተደገፈ አቤቱታ ሲደርሰው ህጋዊ እርምጃ እንዲወስድ ጉዳዩን ወደሚመለከተው አካል ይመራል፣ ይከታተላል።
9. በዚህ ምዕራፍ ከአንቀፅ 93 እስከ አንቀፅ 96 በተደነገገው መሰረት በተቀመጠው ጊዜ አቤቱታውን ወይም ይግባኙን ያላቀረበ ማንኛውም ሰው አቤቱታ ወይም ይግባኝ የማቅረብ መብቱ በይርጋ ይታገዳል።
10. ፍርድ ቤቶች ደረጃውን ጠብቆ የቀረበላቸውን የምርጫ ጉዳይ በህገ መንግስቱ እና አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት ያስተናግዳሉ፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም የምርጫ ጉዳዮችን የሚመለከት ችሎት ሊመድቡ ይችላሉ።
11. ፍርድ ቤቶች በቦርዱ ወይም በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ አስፈፃሚ አካላት በቅድሚያ ያልታየና የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኘን ከላይ በንኡስ አንቀፅ 10 የተደነገገውን የምርጫ ጉዳይ ማየት አይችሉም።

93. <u>በመራጮች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች</u>

1. ማንኛውም ሰው በመራጭነት ከመመዝገብ የሚያግድ ሁኔታ ሲያጋጥመው ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. መብት የሌለው ወይም በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ሰው ያለአግባብ ተመዝግቧል የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ተቃውሞውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው።
3. የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረቡለትን አቤቱታዎች መርምሮ በ24 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ያሰጣል።

4. የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 ለቀረበለት አቤቱታ በ24 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ በአቤቱታ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቆጠራል።
5. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 ለቀረበው አቤቱታ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ አቤቱታ አቅራቢው ለምርጫ ክልል ፅህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በ48 ሰዓት ውስጥ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው።
6. በምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርብ ይግባኝ ውሳኔ ከተሰጠበት በ48 ሰአት ውስጥ መቅረብ አለበት።
7. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ በ24 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
8. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበው ይግባኝ ለመራጭነት ከመመዝገብ የተከለከለ ሲሆን እና በ24 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ በይግባኝ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቆጠራል።
9. ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበውን ይግባኝ የተመዘገበን መራጭ ለመቃወም ሲሆን እና በ24 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ይግባኝ ባዩ በ24 ሰአት ውስጥ ለወረዳው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው።
10. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የምርጫ ጣቢያው ፅህፈት ቤት ስራውን ያከናውናል።
11. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ለወረዳው ፍርድ ቤት በ24 ሰዓት ውስጥ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው። የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡
12. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 የሚቀርብ አቤቱታ የመራጮች የምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ይሆናል፡፡
13. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 የሚቀርብ አቤቱታ ከመራጮች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የመራጮች መዝገብ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ እስከሚያልቅ ድረስ ይሆናል፡፡

94. <u>በዕጩዎች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች</u>

1. ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በዕጩነት ከመመዝገብ የሚያግድ ሁኔታ ሲያጋጥመው ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን አቅርቦ መልስ የማግኘት መብት አለው፡፡

2. አንድ ዕጩ በዕጩነት መቅረብ የለበትም የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅረቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

3. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ24 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

4. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ በንኡስ አንቀፅ 1 የቀረበለትን አቤቱታ በ24 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ በአቤቱታ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቆጠራል።

5. ከላይ በንኡስ አንቀፅ 2 ለቀረበው አቤቱታ የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በ24 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ አቤቱታ አቅራቢው በ72 ሰዓት ውስጥ ለክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

6. ለእጩነት ከመመዝገብ የተከለከለ የፖለቲካ ድርጅት እጩ ወይም የግል እጩ እንዲሁም የአንድን እጩ ምዝገባ የሚቃወም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት የምርጫ ክልሉን አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ከሚቴ በ72 ሰዓት ውሰጥ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡

7. የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ሲቀርብለት በ48 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።

8. ለክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበው ይግባኝ ለእጩነት ከመመዝገብ የተከለከለ ሲሆን እና በ48 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ በይግባኝ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቆጠራል።

9. ለክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበው ይግባኝ የአንድን እጩ ምዝገባ በመቃወም ሲሆን እና በ48 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ ይግባኝ ባዩ በ48 ሰአት ውስጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡

10. የክልሉ ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት የምርጫ ክልል ጽህፈት ቤት ስራውን ያከናውናል።

11. በክልሉ ቅርንጫፍ የጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ይግባኝ ባይ ይግባኙን ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ48 ሰአት ውስጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

12. በዕጩነት ከመመዝገብ የተከለከለን የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩን በሚመለከት የሚቀርብ አቤቱታ የእጩ ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ይሆናል፡፡

13. የአንድን ዕጩ ምዝገባ በመቃወም የሚቀርብ አቤቱታ ከእጩዎች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የተመዘገቡ እጩዎች ይፋ አስከሚሆንበት ቀን ድረስ ይሆናል፡፡

95. <u>በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች</u>

1. አንድ መራጭ ድምፅ ከመስጠት የሚያግደው ሁኔታ ሲፈጠር ወይም በመራጭነት መብቱ ላይ ተቃውሞ ሲቀርብበት ቅሬታውን ወዲያውኑ ለምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. የምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴም፡-

   ሀ/ ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ በማድረግ ጉዳዩን ወደምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት በመላክ ውሳኔ እንዲያገኝ ሊያደርግ ይችላል ወይም

   ለ/ ጊዜያዊ ድምፅ መስጠት የለበትም ብሎ ሊወስን ይችላል።
3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 (ሀ) መሰረት ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠ መራጭ ከምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም እንደሁኔታው ከወረዳው ፍርድ ቤት የመምረጥ መብት እንዳለው የሚገልፅ ውሳኔ የድምፅ ማዳመሩ ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት ካላቀረበ የሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ ውድቅ ይደረጋል፡፡
4. በንዑስ አንቀፅ 2 (ለ) የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለምርጫ ክልሉ ጽህፈት ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የድምፅ መስጫ ሰአት ከማለቁ በፊት ውሳኔ ማግኘት ይኖርበታል። ምርጫ ጣቢያውም በውሳኔው መሰረት ይፈፅማል፡፡
5. በምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ጊዜያዊ ድምፅ ከመስጠት የተከለከለ ሰው ወዲያውኑ ይግባኙን ለወረዳው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል። የወረዳው ፍርድ ቤት የድምጽ መስጫው ሰአት ከመጠናቀቁ በፊት ውሳኔ ይሰጣል፤ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡
6. የአንድን መራጭ ድምፅ መስጠት የሚቃውም ሰው ከላይ በተደነገገው መሰረት አቤቱታውን በየደረጃው የማቅረብና ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡

96. <u>በቆጠራ ሂደትና ውጤት ስለሚነሱ ክርክሮች</u>

1. በድምፅ ቆጠራ ሂደትና በውጤት ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ወይም ወኪል ቅሬታውን ለምርጫ ጣቢያው

አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አስመዝግቦ ይህንኑ ቅሬታ በ48 ሰዓት ውስጥ ለምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

2. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ በንዑስ አንቀፅ 1 መሰረት የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ48 ሰአት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል።
3. ከላይ በንዑስ አንቀፅ 2 በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠው በ5 ቀን ውስጥ ይግባኝ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቦርዱ የቀረበውን ይግባኝ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. ይግባኝ ባዩ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በ5 ቀን ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
5. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት ለቀረበለት ይግባኝ በተቻለ ፍጥነት ውሳኔ ይሰጣል።

## <u>ምዕራፍ ዘጠኝ</u>

## <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

### 97.<u>ጠቅላላ</u>

በኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ በህዝባዊ ምርጫ እና በድምፅ አሰጣጥ ላይ የሚፈፀሙ የወንጀል ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው በዚህ ምእራፍ የተከለከሉ ተግባራትን መፈፀም በህግ ያስቀጣል፡፡

### 98.<u>የምርጫ ሰነዶችን በህገወጥ መንገድ ስለማተምና መያዝ</u>

ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ከቦርዱ ፈቃድ ውጭ ማንኛውንም የምርጫ ሰነድና ቁሳቁስ ያተመ፣ ያባዛ፣ የፈበረከ ወይም ይህን የመሰለ ህገወጥ የምርጫ ሰነድ እና ቁሳቁስ ይዞ የተገኘ ወይም ያደለ እንደሆነ በእስራት ወይም በመቀጮ ይቀጣል።

### 99.<u>የምርጫ ማስታወቂያን ስለማጥፋት</u>

ማንኛውም ሰው ምርጫ ከተጀመረበት ቀን አንስቶ ውጤት እስከሚገለፅበት ቀን ድረስ የማንኛውንም እጩ ተወዳዳሪ ፖስተርን ወይም የምርጫ ማስታወቂያን ያበላሸ ያስወገደ ወይም የቀደደ እንደሆነ ከ1 ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም መቀጮ ይቀጣል።

### 100. <u>የምርጫ ትንበያ የተከለከለ ስለመሆኑ</u>

ማንኛውም ሰው በምርጫው ዕለት የምርጫ ውጤት ትንበያ መረጃ በማዘጋጀት ያሰራጨ ወይም እንዲዘጋጅ ያደረገ፣ ወይም በማንኛውም መንገድ ለህዝብ የገለፀ እንደሆነ ከአንድ አመት ባልበለጠ እስራት ወይም መቀጮ ይቀጣል።

## ምዕራፍ አስር

## የምርጫ ስነ-ምግባር አጠቃላይ መርሆዎች

101. **የምርጫ ስነምግባር አላማ**

የምርጫ ስነምግባር የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፣

1. በዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ መቻቻልን ማስፈን፣
2. ነፃ የፖለቲካ ዘመቻ እና ግልጽ ህዝባዊ ውይይትን ማጎልበት፣ እና
3. ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ እንዲካሄድ ማስቻል፡፡

102. **የምርጫ ስነምግባር**

1. ማንኛውም ቦርዱ በሚያወጣው የስነምግባር ደንብ ለመገዛት ፈቃደኛ የሆነ የፖለቲካ ድርጅት እና እጩ ተወዳዳሪ ደንቡን፡-

   ሀ/ ማክበር፣

   ለ/ ለህዝብ ማስተዋወቅ፣

   ሐ/ ለመራጮች ማስተማር፣

   መ/ እጩዎቻቸው፣ ተወካዮቻቸው፣ አባሎቻቸው እና ደጋፊዎቻቸው አክብረው እንዲንቀሳቀሱ መምራት እና ይህንንም ለማረጋገጥ የሚረዳ ማንኛውም እርምጃ መውሰድ አለበት፡፡

2. ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት እና እጩ ተወዳዳሪ፡-

   ሀ/ እያንዳንዱ ዜጋ ስለሚኖረው መብት በይፋ መግለጽ አለበት፡፡

   ለ/ የምርጫ ውጤትን መቀበል፣ በውጤቱ ቅሬታ ካለውም በፍርድ ቤት እንዲታይለት አቤቱታውን ማቅረብ ይችላል፡፡

3. ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት እና እጩ ተወዳዳሪ ከሌሎች በምርጫ ተፎካካሪ የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በመፍጠር በአንድ በተመሳሳይ ሰዓትና ቦታ የህዝብ ስብሰባ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሌላ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ለማካሄድ በተለያዩ አካላት ጥሪ አለመደረጉን ወይም ፕሮግራም አለመያዙን ማረጋገጥ አለበት፡፡

4. ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት እና እጩ ተወዳዳሪ

   ሀ/ የቦርዱን ስልጣን የመቀበል እንደዚሁም ህጋዊ ትዕዛዙን እና መመሪያውን ማክበር፣

   ለ/ ከቦርዱ እና በምርጫ ከሚወዳደሩ ሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ጋር መልካም ግንኙነት መፍጠር፣

ሐ/ ቦርዱ ለሚያካሂዳቸው የማጣራት ወይም የምርመራ ስራዎች ትብብር ማድረግ፣

መ/ የቦርድ አባላትን፣ ሠራተኞችን እና የምርጫ አስፈፃሚዎችን ደህንነት ማረጋገጥ፣ በእነዚህ አካላት ላይ በተወካዮቻቸው ወይም በደጋፊዎቻቸው ስድብ፣ ዛቻ፣ ማስፈራራት ወይም አደጋ እንዳይደርስባቸው አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ፣

ሠ/ በፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ መድረኮች ወይም በሌሎች በቦርዱ በሚዘጋጁ መድረኮች ላይ እጩዎቻቸው ወይም ወኪሎቻቸው እንዲገኙ ማድረግ፣

አለባቸው።

5. ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት እና እጩ ተወዳዳሪ፡-

ሀ/ መገናኛ ብዙሃን በምርጫው ሂደት ተገቢ ሚናቸውን እንዲጫወቱ አስፈላጊውን ትብብር ማድረግ፣

ለ/ ወኪሎቻቸው ወይም ደጋፊዎቻቸው በጋዜጠኞች ላይ ጥቃት፣ ማስፈራራት፣ አደጋ፣ ጫና፣ ድብደባ እንዳያደርሱባቸው ተገቢውን እርምጃ መውሰድ አለባቸው።

6. ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም እጩ ተወዳዳሪ በምርጫው ወቅት

ሀ/ ግጭት መቀስቀስ ወይም ማስነሳት፣

ለ/ በተወዳዳሪዎች፣ በፖለቲካ ድርጅት አባላት፣ በመራጮች፣ በእጩ ወኪሎች ወይም ደጋፊዎች ላይ ጫና መፍጠር፣

ሐ/ በሀሰት ስም ማጥፋትና የውንጀላ ጽሁፍ ማተም ወይም ንግግር ማድረግ፣

መ/ የሌላ ፓርቲን ምልክት አስመስሎ መጠቀም፣

ሠ/ ብሔርን፣ ብሔረሰብን፣ ዘርን፣ ጾታን፣ ቋንቋን፣ ቀለምን፣ ሃይማኖትን፣ ማህበራዊ አመጣጥን፣ ሃብትን፣ ትውልድን ወይም ሌላ ማንኛውንም አቋም መሰረት በማድረግ በምርጫ ወይም በፖለቲካ እንቅስቃሴዎች አድልዎ ወይም ልዩነት ማድረግ

የለበትም፡፡

7. ማንኛም ሰው፡-

ሀ/ ከምርጫ ወይም ከፖለቲካ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ መደለያ መስጠት፣

ለ/ በፖለቲካ ስብሰባዎች፣ በሠላማዊ ሠልፎች እና በሌሎች የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ላይ የጦር መሳሪያ ይዞ መገኘት፣

ሐ/ የፖለቲካ ድርጅትን ወይም የእጩ ተወዳዳሪዎችን የምርጫ ፖስተሮች

እና ሌሎች የምርጫ ቁሳቁሶችን ማበላሸት፣ ማስወገድ፣ መቅደድ፣

መ/ ሌላው ሰው ለመራጮች ትምህርት እንዳይሰጥ፣ ፊርማ ወይም ድጋፍ እንዳያሰባስብ እና አባላትን እንዳይመለምል ማድረግ፣ እና

ሠ/ ስልጣኑን ወይም ልዩ መብቱን ያለአግባብ መጠቀም፣

የለበትም፡፡

103. <u>ማስመሰል</u>

ማንኛውም ሰው ወይም አካል፡-

1. የፖለቲካ ድርጅት ወይም የእጩ ተወዳዳሪ ወኪል፣
2. የእጩ ተወዳዳሪ፣
3. የቦርዱ አባል፣ ሠራተኛ ወይም የምርጫ ኃላፊ፣
4. የታዛቢ ተወካይ፣
5. የሥነ ዜጋና መራጮች ትምህርት እንዲሰጥ የተፈቀደለት ሰው፣ መስሎ

መንቀሳቀስ የተከለከለ ነው፡፡

104. <u>የምርጫ ቅስቀሳ ስለሚቋረጥበት ጊዜ</u>

ማንኛውም ሰው ድምፅ ከመስጠቱ ከሁለት ቀን በፊት ጀምሮ ድምፅ መስጠት እስከሚጠናቀቅበት ድረስ ምንም አይነት የፖለቲካ ስብሰባ፣ ሰላማዊ ሰልፍ ወይም ሌላ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ማድረግ ወይም መሳተፍ የለበትም፡፡

105. <u>የምርጫ ስነምግባር ደንብ ስለማውጣት</u>

ቦርዱ የሚመለከታቸውን አካላት በማማከር ነፃና ፍትሐዊ ምርጫ ማከናወን የሚያስችሉ ሁኔታዎችን የሚያመቻች ተጨማሪ ዝርዝር የምርጫ ስነምግባር ደንብ ሊያወጣ ይችላል[11]፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

106. <u>ስለበጀት</u>

ቦርዱ በጀቱን በማዘጋጀት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

107. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማናቸውም የፌዴራልም ሆነ የክልል የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ ቡድን፣ የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ ይህንን አዋጅ በስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

108. <u>ቅጣት</u>

---

[11] የምርጫ ስነ ምግባርን በተመለከተ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ ፲6/17(2002) አ.662 ውዮቷል፡፡

ይህ አዋጅ በስራ ላይ እንዳይውል ያሰናከለ ወይም የስነምግባር ደንቡን የጣሰ ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ወይም በተሻሻለው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ህግ መሰረት ይቀጣል፡፡

109. <u>የተሻሩ ህጎች</u>

1. የሚከተሉት በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

ሀ/ የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግስት ጋር ለማጣጣም የወጣ አዋጅ ቁጥር 111/1987

ለ/ የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ጋር ለማጣጣም የወጣው (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 187/1992፣

ሐ/ የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት ጋር ለማጣጣም የወጣው አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 438/1997፣

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማናቸውም ህግ በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚ አይሆንም።

110. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

ቦርዱ ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚረዳ ደንብ እና መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

111. <u>አዋጁ የማፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሰኔ 18 ቀን 1999 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## በምርጫ ወቅት በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በየደረጃው ስለሚቋቋም አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት እና አሠራር ደንብ ቁጥር (የምርጫ ቦርድ)1/2001 ዓ.ም. (የተሻሻለ)

ማንኛውም ኢትዮጵያዊ ዜጋ የመምረጥ እና ወይም የመመረጥ መብቱን በሥራ ላይ ሲያውል በምርጫ ሂደት የሚነሱ ክርክሮችን በወቅቱ በመፍታት ሁሉም ዜጋ ዲሞክራሲያዊ መብቱን በሥራ ላይ እንዲያውል ማስቻሉ ተገቢ በመሆኑ፣

ምርጫን ነፃና ፍትሃዊ ለማድረግ በምርጫ አፈጻጸም በየደረጃው የሚነሱ አቤቱታዎችን ተመልክቶ ወቅታዊ መፍትሄ የሚሰጥ በየደረጃው የሚቋቋመውን አካል አደረጃጀት እና አሠራር በመደንገግ በምርጫ ሂደት ለሚነሱ አቤቱታዎችና ክርክሮች አፈታት ግልጽ አሰራር ማስፈን በማስፈለጉ፣

የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 19፣ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 12፣ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 5፣ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 10፣ አንቀጽ 92 ንዑስ አንቀጽ 4 እና አንቀጽ 110 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ

**አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በየደረጃው የሚቋቋም አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀትና አሠራር ደንብ ቁጥር 1/2001 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2. ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ፤

1. "ኢ.ፌ.ዲ.ሪ" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ነው፡፡
2. "የምርጫ ሕግ" ማለት የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም. ነው፡፡
3. "ቦርድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ነው፡፡
4. "ተንቀሳቃሽ ወኪል" ማለት በምርጫ ለመወዳደር በተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም በግል እጩ ተወክሎ በአንድ ምርጫ ክልል ውስጥ በሚገኙ የምርጫ ጣቢያዎች እየተንቀሳቀሰ የምርጫ ሂደትንና የወከለውን ድርጅት ወይም የግል እጩ መብት መከበር የሚከታተል ሰው ነው፡፡

5. “ተቀማጭ ወኪል” ማለት በምርጫ ለመወዳደር በተመዘገበ የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ የሚወክልና በምርጫ ክልልና በምርጫ ጣቢያ ተቀምጦ የምርጫ ሂደትንና የወከለውን አካል መብት መከበርን የሚከታተል ሰው ነው፡፡
6. “የሕዝብ ታዛቢ” ማለት በእያንዳንዱ ምርጫ ክልል እና ምርጫ ጣቢያ ምርጫን እንዲታዘቡ በህዝብ የሚመረጡ ገለልተኛ የአካባቢ ነዋሪዎች ናቸው፡፡
7. “ክልል” ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ይጨምራል፡፡
8. “የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት” ማለት በምርጫ ሕጉ መሠረት በክልል ደረጃ ምርጫን የሚያስተባብር በቦርዱ በቋሚነት የሚቋቋም ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ነው፡፡
9. “አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ” ማለት በየደረጃው በሚገኝ በክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት፣ ምርጫ ክልል እና የምርጫ ጣቢያ ለሚነሱ ቅሬታዎች አስተዳደራዊ ውሳኔ የሚሰጥ በምርጫ ህጉ እና በዚህ ደንብ መሠረት ለምርጫ ወቅት የሚቋቋም ኮሚቴ ነው፡፡
10. “የምርጫ ክልል” ማለት ለምርጫ አፈጻጸም እንዲያመች እና ህዝቡ ወኪሎቹን እንዲመርጥ በሕግ መሠረት የሀገሪቱ ግዛት ተከፋፍሎ የሚደራጅ የምርጫ አካባቢ ነው፡፡
11. “የምርጫ ጣቢያ” ማለት በየደረጃው በሚካሄዱ ምርጫዎች ምዝገባ የሚካሄድበት፣ መራጮች ድምፅ የሚሰጡበት እና ቆጠራ የሚካሄድበት ቦታ ነው፡፡
12. “የምርጫ አስፈጻሚ” ማለት በየደረጃው ለሚካሄዱ ምርጫ በተቋቀሙ የምርጫ ጽሕፈት ቤቶች በቋሚነት፣ በኮንትራት ወይም በጊዜያዊነት ተመድቦ በህግ መሠረት ምርጫን የሚያስፈጽም ሰው ነው፡፡
13. “አቤቱታ” ማለት በየደረጃው ለሚገኙ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አካላት በጽሑፍ የሚቀርብ ቅሬታ ነው፡፡
14. “ይግባኝ” ማለት በየደረጃው በሚገኙ የበታች አቤቱታ ሰሚ አካላት ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ሰው በዚህ ደንብና ቦርዱ ባዘጋጀው ቅጽ መሠረት በጽሑፍ ለበላይ አቤቱታ ሰሚ አካል የሚቀርብ አቤቱታ ነው፡፡
15. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

**አንቀጽ** 3. **<u>አተረጓጎም</u>**

በዚህ ደንብ ለሚፈጠር የህግ ክፍተት የኢፌዲሪ ህገመንግሥትን እና የተሻሻለውን የኢትዮጵያ ምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም ጋር በማጣጣም መተርጎም አለበት፡፡

**አንቀጽ 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በምርጫ ህጉ መሠረት በየደረጃው በሚካሄዱ ምርጫዎች ለሚነሱ ቅሬታዎች ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 5. <u>የጾታ አገላለፅ</u>**

በዚህ መመሪያ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ስለአቤቱታ ሰሚ አካል አደረጃጀት

**አንቀጽ 6. <u>ጠቅላላ</u>**

1. ቦርዱ በምርጫ ህጉ አንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ 11 መሠረት በምርጫ ሂደት ለሚከሰቱ አለመግባባቶች አስተዳደራዊ መፍትሄ የመስጠት፣ ጉድለቶችን የማረምና ለሚቀርቡ ቅሬታዎች ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አለው፡፡
2. ለቦርዱ በመጀመሪያ ደረጃ ወይም በይግባኝ የሚቀርቡ አቤቱታዎች በምርጫ ህጉ ላይ በተደነገገው እና ቦርዱ የራሱን አሠራር እና የስብሰባ ስነስርዓት አስመልክቶ በሚያወጣው ደንብ መሠረት መርምሮ ውሳኔ ይሰጥባቸዋል፡፡
3. ቦርዱ ለሚቀርቡለት አቤቱታዎች በወቅቱ መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችለው አሠራር በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ ጽሕፈት ቤቶች ይዘረጋል፡፡

**አንቀጽ 7. <u>በምርጫ ሂደት በየደረጃው ስለሚኖሩ አቤቱታ ሰሚ አካላት</u>**

ቦርዱ በምርጫ ህጉ እና በዚህ ደንብ መሠረት የሚከተሉት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴዎች በየደረጃው እንዲቋቋሙ ያደርጋል፣

1. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ፣
2. የምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ፣
3. የምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ፣

**አንቀጽ 8. <u>የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት</u>**

1. በምርጫ ህጉ አንቀጽ 19(12) መሠረት እያንዳንዱ የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ያደራጃል፡፡
2. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ፣ ጽሕፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ሶስት ይሆናሉ፡፡
3. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፡፡

4. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ከቦርዱ ጋር በመመካከር ከክልሉ የሕዝብ ታዛቢዎች መካከል ሁለት አባላት በቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ይመደባሉ፡፡

5. ከህዝብ ታዛቢዎች መካከል የሚመረጡት የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በተቻለ መጠን የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በተገቢው ሁኔታ በመመርመር ውሳኔ ለማሳለፍ የሚያስችል እውቀትና ልምድ ያላቸው እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 9. <u>የምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት</u>**

1. በምርጫ ህጉ አንቀጽ 20 ንዑስ አንቀጽ 5 ድንጋጌ መሠረት፤

ሀ/ በእያንዳንዱ የምርጫ ክልል ሦስት አባላት ያሉት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ያደራጃል፡፡

ለ/ የምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፡፡

ሐ/ የምርጫ ክልሉ ሁለት ታዛቢዎች የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባል ይሆናሉ፡፡

መ/ ከላይ በ"ሐ" የተጠቀሱት ሁለት ታዛቢዎች በምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ይሰየማሉ፡፡

2. ከሕዝብ ታዛቢዎች መካከል የሚመረጡት የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በተቻለ መጠን የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በተገቢው ሁኔታ በመመርመር ውሳኔ ለማሳለፍ የሚያስችል እውቀትና ልምድ ያላቸው እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 10. <u>የምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አደረጃጀት</u>**

1. በምርጫ ህጉ አንቀጽ 22 ንዑስ አንቀጽ 10 ድንጋጌ መሠረት፤

ሀ/ እያንዳንዱ ምርጫ ጣቢያ ሦስት አባላት የያዘ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ያደራጃል፡፡

ለ/ የምርጫ ጣቢያው የምርጫ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ይሠራል፡፡

ሐ/ የምርጫ ጣቢያው ሁለት የህዝብ ታዛቢዎች የምርጫ ጣቢያው የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባል ይሆናሉ፡፡

መ/ ከላይ በ"ሐ" የተጠቀሱት ሁለት ታዛቢዎች በምርጫ ጣቢያው ኃላፊ ይሰየማሉ፡፡

2. ከሕዝብ ታዛቢዎች መካከል የሚመረጡት የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በተቻለ መጠን የሚቀርቡ አቤቱታዎችን በተገቢው ሁኔታ በመመርመር ውሳኔ ለማሳለፍ የሚያስችል እውቀትና ልምድ ያላቸው እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

**አንቀጽ 11. ከአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ስለመነሳት**

1. ማንኛውም የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ለኮሚቴው የቀረበን አቤቱታ ቀደም ሲል በሥራው ምክንያት ያየውና ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ በአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢነቱ ተሰይሞ ለማየት አይችልም፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ሁኔታ ሲከሰት ከሌሎቹ የምርጫ አስፈጻሚ ኮሚቴ አባላት መካከል አንዱ ተተክቶ ጉዳዩን በጊዜያዊ ሰብሳቢነት እንዲያይ ይደረጋል፡፡
3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ሁኔታ የተከሰተው በክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ሲሆን ከቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱ ሠራተኞች አንዱ ተተክቶ በጊዜያዊ ሰብሳቢነት እንዲያይ ይደረጋል፡፡
4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰው ጉዳይ ውሳኔ ካገኘ በኋላ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ መደበኛ የሰብሳቢነት ሥራውን ይቀጥላል፡፡

**አንቀጽ 12. የተጓደሉ አቤቱታ ሰሚ አባላትን ስለመተካት**

1. የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በተለያየ ምክንያት ሲጓደሉ ወዲያውኑ መተካት አለባቸው፡፡
2. የተጓደሉት አባላት የሚተኩት በሚከተለው አሠራር ይሆናል፣
   ሀ/ የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ሲጓደሉ ወዲያውኑ በክልሉ ውስጥ ከተመረጡ የሕዝብ ታዛቢዎች መካከል በክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አማካኝነት ይተካሉ፡፡
   ለ/ የተጓደለው አባል የምርጫ ክልሉ ኃላፊ ሲሆን ከምርጫ ክልሉ እንዲሁም ከምርጫ ጣቢያው ሲሆን ከምርጫ ጣቢያ የምርጫ አስፈጻሚዎች መካከል አንዱ ተክቶ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴን በሰብሳቢነት ይመራል፡፡
   ሐ/ የተጓደለው አባል ከሕዝብ ታዛቢዎች የተመረጠው ከሆነ በሰብሳቢው አማካኝነት ከቀሩት ታዛቢዎች መካከል አንዱ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው አባል ሆኖ እንዲተካ ይደረጋል፡፡ የተጓደለው ታዛቢ በተጠባባቂ ታዛቢነት ተመርጠው ከተያዙት ውስጥ ከፍተኛ ድምጽ ያለው እንዲተካ ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## አቤቱታ ሰሚ አካላት በምርጫው ሂደት ለሚነሱ

## ቅሬታዎች ውሳኔ የሚሰጡበት አሠራር

### አንቀጽ 13. በመራጮች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች

በመራጮች ምዝገባ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች በምርጫ ሕጉ አንቀጽ 93 መሠረት ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ውሳኔ ያገኛሉ፤

1. ማንኛውም ሰው በመራጭነት ከመመዝገብ የሚያግድ ሁኔታ ሲያጋጥመው ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. መብት የሌለው ወይም በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ሰው ያለአግባብ ተመዝግቧል የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ተቃውሞውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
3. የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረቡለትን አቤቱታዎች መርምሮ በ24 ሰዓት ውስጥ ውሣኔ ያሰጣል፡፡
4. የምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 ለቀረበለት አቤቱታ በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ፤

   ሀ/በመራጭነት ከመመዝገብ የተከለከለ ሲሆን በአቤቱታ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቀጠራል፡፡ ለአቤቱታ አቅራቢው ይህንኑ የሚገልፅ ማስታወሻ ይሰጠዋል፡፡ ምርጫ ጣቢያውም በማስታወሻው መሠረት ይመዘግበዋል፡፡

   ለ/ አቤቱታው በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ሰው ያለአግባብ ተመዝግቧል የሚል ሲሆን አቤቱታ አቅራቢው ለምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በ48 ሰዓት ውስጥ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡
5. በምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርብ ይግባኝ ውሣኔ ከተሰጠበት በ48 ሰዓት ውስጥ መቅረብ አለበት፡፡
6. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ይግባኝ መርምሮ በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
7. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ለወረዳው ፍርድ ቤት በ24 ሰዓት ውስጥ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የሰጠው ውሳኔም የመጨረሻ ይሆናል፡፡
8. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ለቀረበለት ይግባኝ በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካለሰጠ፤

   ሀ/ አቤቱታው ለመራጭነት ከመመዝገብ የተከለከለን ሰው ሲሆን በአቤቱታ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቆጠራል፡፡ ለአቤቱታ አቅራቢው ይህንኑ

የሚገለፅ ማስታወሻ ይሰጠዋል፡፡ ምርጫ ጣቢያውም በማስታወሻው መሠረት ይመዘግበዋል፡፡

ለ/ ይግባኙ በመራጭነት የተመዘገበን ሰው በመቃወም ሲሆን ይግባኝ ባዩ በ24 ሰዓት ውስጥ ለወረዳ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

9. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት የምርጫ ጣቢያው ጽሕፈት ቤት ሥራውን ያከናውናል፡፡

10. በመራጭነት ከመመዝገብ በተከለለ ሰው የሚቀርብ አቤቱታ የመራጮች የምዝገባ የጊዜ ሠሌዳ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ይሆናል፡፡

11. የተመዘገበን መራጭ በመቃወም የሚቀርብ አቤቱታ ከመራጮች የምዝገባ ቀን ጀመሮ የመራጮች መዝገብ ለሕዝብ ይፋ የሚሆንበት ጊዜ እስከሚያልቅ ድረስ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 14. <u>በዕጩዎች ምዝገባ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች</u>**

በዕጩዎች ምዝገባ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች በምርጫ ህጉ አንቀጽ 94 መሠረት ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ውሳኔ ያገኛሉ፤

1. ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በዕጩነት ከመመዝገብ የሚያግድ ሁኔታ ሲያጋጥመው ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን በፅሑፍ አቅርቦ መልስ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. አንድ ዕጩ በዕጩነት መቅረብ የለበትም የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን በፅሑፍ አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
3. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮማቴ የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 ለቀረበለት አቤቱታ በ24 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ፤

ሀ/ በእጩነትት ከመመዝገብ የሚያግድ ሁኔታ ያጋጠመው ሰው ሲሆን የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በአቤቱታ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቆጠራል፡፡ ለአቤቱታ አቅራቢው ይህንኑ የሚገልፅ ማስታወሻ ይሰጠዋል፡፡ አቤቱታ አቅራቢው ከአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው የተሰጠውን ማስታወሻ ለምርጫ ክልሉ በማቅረብ በእጩነት ይመዘገባል፡፡

ለ/ አቤቱታው አንድን ዕጩ በእጩነት መቅረብ የለበትም የሚል ተቃውሞ ሲሆን አቤቱታ አቅራቢው በ72 ሰዓት ውስጥ ለክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

5. ለዕጩነት ከመመዝገብ የተከለከለ የፖለቲካ ድርጅት ዕጩ ወይም የግል ዕጩ እንዲሁም የአንድን ዕጩ ምዝገባ የሚቃወም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት የምርጫ ክልሉን አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ በመቃወም ለክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በ72 ሰዓት ውስጥ ይግባኝ ለማቅረብ ይችላል፡፡
6. የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ሲቀርብለት በ48 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
7. በክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ይግባኝ ባይ ይግባኙን ውሳኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ48 ሰዓት ውስጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡
8. ለክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ይግባኝ መርምር በ48 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠ፣

ሀ/ አቤቱታው በዕጩነት ከመመዝገብ የተከለከለው ሲሆን በይግባኝ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቆጠራል፡፡ ለአቤቱታ አቅራቢው ይህንኑ የሚገልፅ ማስታወሻ ይሰጠዋል፡፡ አቤቱታ አቅራቢው ከአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው የተሰጠውን ማስታወሻ ለምርጫ ክልሉ በማቅረብ ይመዘገባል፡፡

ለ/ የቀረበው ይግባኝ የአንድን ዕጩ ምዝገባ በመቃወም ሲሆን ይግባኝ ባዩ በ48 ሰዓት ውስጥ ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡

9. የክልሉ ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ መሠረት የምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት ሥራውን ያከናውናል፡፡
10. በዕጩነት ከመመዝገብ የተከለከለን የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል ዕጩን በሚመለከት የሚቀርብ አቤቱታ የዕጩ ምዝገባ የጊዜ ሠሌዳ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ይሆናል፡፡
11. የአንድን ዕጩ ምዝገባ በመቃወም የሚቀርብ አቤቱታ ከዕጩዎች የምዝገባ ቀን ጀምሮ የተመዘገቡ ዕጩዎች ይፋ እስከሚሆንበት ቀን ድረስ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 15. <u>በድምፅ አሰጣጥ ሂደት ስለሚነሱ ክርክሮች</u>**

በድምፅ አሰጣጥ ሂደት የሚነሱ ክርክሮች በምርጫ ህጉ አንቀጽ 95 መሠረት ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ውሳኔ ያገኛሉ፣

1. አንድ መራጭ ድምፅ ከመስጠት የሚያግደው ሁኔታ ሲፈጠር ወይም በመራጭነት መብቱ ላይ ተቃውሞ ሲቀርብበት ቅሬታውን ወዲያውኑ ለምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በፅሑፍ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
2. የምርጫ ጣቢያ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴውም፡-
   ሀ/ ጊዜያዊ ድምፅ እንዲሰጥ በማድረግ ጉዳዩን ወደምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት በመላክ ውሳኔ እንዲያገኝ ሊያደርግ ይችላል ወይም
   ለ/ ጊዜያዊ ድምፅ መስጠት የለበትም ብሎ ሊወስን ይችላል፡፡
3. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 (ሀ) መሠረት ጊዜያዊ ድምፅ የሰጠ መራጭ ከምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም እንደ ሁኔታው ከወረዳው ፍርድ ቤት የመምረጥ መብት እንዳለው የሚገልፅ ውሳኔ የድምፅ ማዳመጡ ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት ካላቀረበ የሰጠው ጊዜያዊ ድምፅ ውድቅ ይደረጋል፡፡
4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2(ለ) የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ለምርጫ ክልሉ ጽሕፈት ቤት የሚቀርብ አቤቱታ የድምፅ መስጫ ሰዓት ለማለቁ በፊት ውሳኔ ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ምርጫ ጣቢያውም በውሳኔው መሠረት ይፈፅማል፡፡
5. በምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር የተሰኘ ጊዜያዊ ድምፅ ከመስጠት የተከለከለ ሰው ወዲያውኑ ይግባኙን ለወረዳው ፍርድ ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡ የወረዳው ፍርድ ቤት የድምፅ መስጫው ሰዓት ከመጠናቀቁ በፊት ውሳኔ ይሰጣል፣ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡
6. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2"ለ" መሠረት ጊዜያዊ ድምፅ መስጠት የለበትም የተባለ ይግባኝ አቅራቢ በምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ወይም በወረዳው ፍርድ ቤት ድምፅ እንዲሰጥ ከተወሰነ፤
   ሀ/ የድምፅ መስጫ ሰዓት ከመጠናቀቁ በፊት ለምርጫ ጣቢያው ውሳኔውን ካላቀረበ ድምፅ ሊሰጥ አይችልም፡፡
   ለ/ ከላይ በዚህ ንዑስ አንቀጽ "ሀ" የተደነገገው ቢኖርም የምርጫ ጣቢያው ተዘግቶ እና በምርጫ ጣቢያው በግቢ ውስጥ የተሰለፉ መራጮች ድምፅ በመስጠት ላይ ባሉበት ጊዜ ውሳኔውን ይዞ ከደረሰ እንዲመርጥ ይደረጋል፡፡
7. የአንድን መራጭ ድምፅ መስጠት የሚቃወም ሰው ከላይ በተደነገገው መሠረት አቤቱታውን በየደረጃው በፅሑፍ የማቅረብና ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
8. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት የሚወሰን ውሳኔ እንደሁኔታው በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀጽ 2 እስከ 6 ባለው ድንጋጌ መሠረት ይፈፀማል፡፡

**አንቀጽ 16. <u>በቆጠራ ሂደትና ውጤት ስለሚነሱ ክርክሮች</u>**

በቆጠራ ሂደትና ውጤት የሚነሱ ክርክሮች በምርጫ ህጉ አንቀጽ 96 መሠረት ከዚህ ቀጥሎ ባለው ሁኔታ ውሳኔ ያገኛሉ፤

1. በድምፅ ቆጠራ ሂደትና በውጤት ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል ዕጩ ወይም ወኪል ቅሬታውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አስመዝግቦ ይህንኑ ቅሬታ በ48 ሰዓት ውስጥ ለምርጫ ክልል አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከነማስረጃው በጽሑፍ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ቅሬታ የሚያቀርብ ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል ዕጩ ወይም ወኪል፤
   ሀ/ ለምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ያስመዘገበበትን ማስረጃ ከሚያቀርበው አቤቱታ ጋር ማያያዝ አለበት፡፡
   ለ/ ቅሬታ አቅራቢው በምርጫ ጣቢያ ካስመዘገበው ጭብጥ ውጪ የሆነ አዲስ ነገር ማቅረብ አይችልም፡፡
3. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ እና ማስረጃ መርምሮ በ48 ሰዓት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
4. የምርጫ ክልሉ ውሳኔ፤
   ሀ/ ቅሬታ የቀረበበት ቆጠራ እንደገና እንዲካሄድ ወይም
   ለ/ ቅሬታ የቀረበበት ቆጠራ ትክክል ስለሆነ ቅሬታው አግባብነት የለውም የሚል ሊሆን ይችላል፡፡
   ሐ/ በቆጠራ ላይ የቀረበው ቅሬታ የምርጫ ክልሉን አጠቃላይ ውጤት በመሠረቱ የማይለውጠው ከሆነ ድጋሚ ቆጠራ ማካሄድ አያስፈልግም ብሎ ሊወሰን ይችላል፡፡
   መ/ ሌላ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ውሳኔ በህጉ መሠረት ሊወሰን ይችላል፡፡
5. የምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አቤቱታ አቅራቢ ውሳኔ በተሰጠው በ5 ቀን ውስጥ ይግባኝ ለቦርዱ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቦርዱ የቀረበውን ይግባኝ መርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
6. ይግባኝ ባዩ ቦርዱ የሰጠውን ውሳኔ በመቃወም በ5 ቀን ውስጥ ለፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡
7. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤትም ከላይ በንዑስ አንቀጽ 6 መሠረት ለቀረበለት ይግባኝ በተቻለ ፍጥነት ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 17. <u>የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ተግባርና ኃላፊነት</u>**

1. በየደረጃው የሚገኝ የምርጫ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ፤

ሀ/ በምርጫ ህጉ እና በዚህ ደንብ መሠረት በያለበት ደረጃ ለሚቋቋም አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፡፡

ለ/ በዚህ ደንብ መሠረት የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላትን ይሰይማል፡፡

ሐ/ ለአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት ሥራ ያከፋፍላል፡፡ የሥራ ክፍፍሉ በቃለ-ጉባኤ ተመዝግቦ እንዲያዝ ያደርጋል፡፡

መ/ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው ውይይት እና ውሳኔ በቃለጉባኤ እንዲያዝና ለሚመለከተው አካል እንዲላክ ያደርጋል፡፡

ሠ/ ማናቸውንም ሰነዶች በአግባቡ እንዲጠበቁ ያደርጋል፡፡

ረ/ ይግባኝ የማቅረብ መብት ላለው ሰው የተሟላ ሰነድ በመስጠት በይግባኝ መብቱ እንዲጠቀም ያደርጋል፡፡

2. በየደረጃው የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባል ሆነው ከተመደቡ ሰዎች አንደኛው አባል በተደራቢነት በቃለጉባኤ ያዥነት በኮሚቴው ሰብሳቢ ተመድቦ የኮሚቴውን ቃለ ጉባኤዎች እና ውሳኔዎች በጽሁፍ ይይዛል፡፡

3. የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አባላት በአቤቱታ የቀረበላቸውን ጉዳይ በመመርመር አፋጣኝ እና ህጋዊ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት አለባቸው፡፡

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>ስለአቤቱታ አቅራቢ፣ አቤቱታ አቀራረብ እና አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አሠራር</u>

**አንቀጽ 18.** <u>ስለ አቤቱታ አቅራቢ</u>

1. በምርጫ ህጉ አንቀጽ 79፣ 90 እና 91 ከተደነገገው በስተቀር የሚከተሉት አካላት ወይም ሰዎች የምርጫውን ሂደት አስመልክቶ አቤቱታ በፅሑፍ የማቅረብና በየደረጃው ውሳኔ የማግኘት መብት አላቸው፡፡
2. ማንኛውም ሰው በመራጭነት ከመመዝገብ የሚያግድ ሁኔታ ሲያጋጥመው ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
3. በመራጭነት ለመመዝገብ መብት የሌለው ወይም በመራጭነት ለመመዝገብ ብቁ ያልሆነ ሰው ያለአግባብ ተመዝግቧል የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ተቃውሞውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
4. ማንኛውም ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት በእጩነት ከመመዝገብ የሚያግድ ሁኔታ ሲያጋጥመው ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ቅሬታውን አቅርቦ መልስ የማግኘት መብት አለው፡፡

5. አንድ እጩ በእጩነት መቅረብ የለበትም የሚል ተቃውሞ ያለው ሰው ወይም የፖለቲካ ድርጅት ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አቤቱታውን አቅርቦ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
6. አንድ መራጭ ድምፅ ከመስጠት የሚያግደው ሁኔታ ሲፈጠር ወይም በመራጭነት መብቱ ላይ ተቃውሞ ሲቀርብበት ቅሬታውን ወዲያውኑ ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በማቅረብ ውሳኔ የማግኘት መብት አለው፡፡
7. በድምፅ ቆጠራ ሂደትና በውጤት ላይ ቅሬታ ያለው ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩ ወይም ወኪል ቅሬታውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ አስመዝግቦ ይህንኑ ቅሬታ በ48 ሰዓት ውስጥ ለምርጫ ክልሉ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 19. <u>የአቤቱታ አቀራረብ</u>**

1. እያንዳንዱ አቤቱታ አቅራቢ የሚያቀርበው አቤቱታ በፅሁፍ ሆኖ ሌላ አከራካሪ ጉዳይ በማያስከትል ሁኔታና ትክክለኛ ውሳኔ ለመስጠት በሚያስችል መልክ ተዘጋጅቶ፤
   ሀ/ አቤቱታው የተፃፈበት ቀን እና ሰዓት፣
   ለ/ የአቤቱታ አቅራቢውን ሙሉ ስምና አድራሻ፣
   ሐ/ ለአቤቱታ መነሻ ምክንያት የሆነውን ጉዳይ፣
   መ/ እየተጠየቀ ያለውን መፍትሄ፣
   ሠ/ የማስረጃ ዝርዝር፣
   ረ/ የሚቀርበው የሰው ማስረጃ በሆነ ጊዜ የምስክሮቹን ማንነት ዝርዝር እና
   ሰ/ አቤቱታው የሚቀርብበት አካል በግልፅ ያመላከተ መሆን አለበት፡፡
2. ለአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሚቀርብ አቤቱታ ወይም ይግባኝ ቦርዱ ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው ቅፅ በሶስት ቅጂ ተዘጋጅቶተ በአቤቱታ አቅራቢው መፈረም አለበት፡፡
3. ማንኛውም አቤቱታ በአቤት ባዩ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ መቅረብ ይኖርበታል፡፡
4. አቤቱታ አቅራቢው የማያነብ እና ወይም የማይፅፍ ከሆነ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው አቤቱታው በቃል እንዲቀርብ በማድረግ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው አባላት በተገኙበት፤
   ሀ/ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው የአቤቱታ አቅራቢውን ቃል ሰምቶ በጽሁፍ ይመዘግባል፡፡
   ለ/ የአቤቱታ አቅራቢውን ቃል ከላይ በዚህ ንዑስ አንቀጽ "ሀ" መሠረት ሲመዘግብ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን መስፈርት ያሟላ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

ሐ/ ከላይ በዚህ ንዑስ አንቀጽ "ለ" መሠረት ወደ ጽሑፍ የተለወጠው አቤቱታ ለአቤቱታ አቅራቢው ተነቦለት በፅሁፍ ወይም በጣት አሻራ ወይም ጣት የሌለው ከሆነ በሚችለው ሌላ ምልክት እንዲፈርምበት ያደርጋል፡፡

5. ማንኛውም አቤቱታ ወይም ይግባኝ ለሚመለከተው አካል ከቀረበ በኋላ አቤቱታ አቅራቢው ወይም ይግባኝ ባዩ ወይም ህጋዊ ወኪሉ ጉዳዩን እንደማይቀጥልበት ወይም እንዳቋረጠ በፅሁፍ ከገለፀ አቤቱታ ወይም ይግባኝ ሰሚው አካል ይህንኑ ፅሁፍ ከአቤቱታው ወይም ከይግባኙ ጋር በማያያዝ በአጭር ቃለ ጉባኤ ጉዳዩን ይዘጋል፡፡

**አንቀጽ** 20. <u>አቤቱታ ስለመቅረቡ የሚሰጥ ማስረጃ</u>

1. በየደረጃው ያለ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በማንኛውም ሰው ወይም አካል አቤቱታ ሲቀርብለት በዚህ ደንብ አንቀፅ 19 ያለውን መመዘኛ ያሟላ መሆኑን በማረጋገጥ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ለአቤቱታ መረከቢያ ማረጋገጫነት የተዘጋጀውን ቅፅ ሞልቶ በመፈረም ለአቅራቢው ይሰጠዋል፤
2. የአቤቱታ መረከቢያ ማረጋገጫ ቅፅም፤

ሀ/ አቤቱታው ገቢ የተደረገበት ቀንና ሰዓት፣

ለ/ አቤቱታው የቀረበለትን አካል፣

ሐ/ አቤቱታው በዚህ ደንብ አንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገውን ያሟላ መሆኑን፣

መ/ የአቤቱታውን መነሻ በአጭሩ እና

ሠ/ የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ ስምና ፊርማ መያዝ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ** 21. <u>ስለ ይርጋ</u>

ማንኛውም አቤቱታ ወይም ይግባኝ ሊቀርብ የሚችለው በምርጫ ህጉ መሠረት ሆኖ፤

1. በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት በመራጭነት ከመመዝገብ የሚያግድ ሁኔታ ያጋጠመው ሰው በሆነ ጊዜ የመራጮች የምዝገባ የጊዜ ሠሌዳ እስከሚጠናቀቅበት ቀን ይሆናል፡፡
2. በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 ድንጋጌ መሠረት መብት የሌለው ሰው ወይም በመራጭነት መመዝገብ የሌለበት ሰው ያለአግባብ ተመዝግቧል የሚል ሲሆን ከመራጮች የምዝገባ መጀመሪያ ቀን ጀምሮ የመራጮች መዝገብ ለሕዝብ ይፋ እስከሚሆንበት የመጨረሻ ቀን ድረስ ይሆናል፡፡
3. በእጩነት ከመመዝገብ የተከለከለን የፖለቲካ ድርጅት ወይም የግል እጩን በሚመለከት ሲሆን የእጩ ምዝገባ የጊዜ ሰሌዳ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ይሆናል፡፡

4. የአንድን እጩ ምዝገባ በመቃወም የሚቀርብ ሲሆን ከእጩዎች ምዝገባ ቀን ጀምሮ የተመዘገቡ እጩዎች ይፋ እስከሚሆኑበት ቀን ድረስ ይሆናል፡፡
5. በዚህ ደንብ አንቀጽ 15 ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ መሠረት አንድ መራጭ ድምፅ ለመስጠት የሚያግደው ሁኔታ ሲፈጠር ወይም በመራጭነት መብቱ ላይ ተቃውሞ ሲቀርብ እና ከተጣራ በኋላ ለማዳመር ወይም ለመጣል ጊዜያዊ ድምፅ በፖስታ እንዲሰጥ ከተደረገ የድምፅ ማዳመሩ እስከሚጠናቀቅበት ሰዓት ድረስ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
6. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ድምፅ ለመስጠት የሚያግደው ሁኔታ ተፈጥሮ ወይም በመራጭነት መብቱ ላይ ተቃውሞ በመቅረቡ ጊዜያዊ ድምፅ መስጠት የለበትም ተብሎ ሲወሰን የድምፅ መስጫ ሰዓት ከማለቁ በፊት ድረስ ውሳኔ እንዲሰጠው ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**አንቀጽ 22. <u>የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ስብሰባና ውሳኔ አሠጣጥ</u>**

1. በየደረጃው የሚቋቋም የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ስብሰባ በሙሉ አባላት ይካሄዳል፡፡
2. የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የአቤቱታ አቅራቢውን አቤቱታና ማስረጃ እና አቤቱታ የቀረበበትን አካል ወይም የምርጫ አስፈጻሚውን ክፍል ምክንያትና መልስ ከሰማ እና የቀረበለትን ማስረጃ ካገናዘበ በኋላ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
3. አቤቱታ አቅራቢውም ሆነ ቅሬታ የቀረበበት ሰው በኮሚቴው የመሰማት፣ ማስረጃውን የማሰማትና ራሱን የመከላከል መብት አለው፡፡
4. አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የቀረበለትን አቤቱታ ከመረመረ በኋላ በተባበረ ድምፅ ወይም በድምፅ ብልጫ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
5. ድምፅ እኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው የደገፈው ወገን የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል፡፡
6. የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው አቤቱታ የቀረበበት የምርጫ አስፈጻሚ ወይም አካል መልስ እንዲሰጥ አስፈላጊ አይደለም ብሎ ሲያምን ወይም መልስ መስጠት ሳይችል ሲቀር የአቤቱታ አቅራቢውን አቤቱታና ማስረጃ በመመርመር ብቻ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፡፡
7. የሀሳብ ልዩነት ያለው የኮሚቴ አባል ልዩነቱ በአጭሩ እንዲመዘገብለት ሊያደርግ ይችላል፡፡
8. ማንኛውም አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የውይይት ቃለ ጉባኤውን ወይም የሚሰጠውን ውሳኔ በጋራ ፊርማ ማረጋገጥ አለበት፡፡
9. የአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ የሚከተሉትን አካቶ የያዘ መሆን ይኖርበታል፤

   ሀ/ አቤቱታው የቀረበለትን ኮሚቴ ስም እና አድራሻ፣

   ለ/ የኮሚቴውን አባላት ስም ዝርዝርና ፊርማ፣

ሐ/ የአቤቱታ አቅራቢውን ሙሉ ስምና አድራሻ፣

መ/ የማስረጃዎች ይዘት እና/ወይም የምስክሮች ቃል በአጭሩ፣

ሠ/ ምክንያታዊ የሆነ የውሳኔ ሀተታ፣

ረ/ በውሳኔው መሠረት መወሰድ ስለሚኖርበት እርምጃ እና

ሰ/ ውሳኔው የተሰጠበት ቀንና ሰዓት፡፡

10. እያንዳንዱ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ፤

   ሀ/ የቀረበን አቤቱታ ከቀረበለት ማስረጃ ጋር በማገናዘብ ይመረምራል፣ ውሳኔውንም በፅሁፍ ያሰፍራል፡፡

   ለ/ ከቀረበለት አቤቱታ ጋር ግንኙነት ያለው ወይም ያገባኛል ባይ ጥያቄ ሲያቀርብ ከአቤት ባዩ ጋር አብሮ እንዲሰማ እድል ሊሰጥ ይችላል፡፡

   ሐ/ አቤቱታ ሰሚው ጥያቄ ሲያቀርብ ኮሚቴው በራሱ አስተያየት አቤቱታ አቅራቢውን እና አቤቱታ የቀረበበትን ወይም ውሳኔ ለመስጠት ይረዳኛል የሚለውን ሰው ጠርቶ ሊጠይቅ ወይም አስፈላጊ ማስረጃ እንዲቀርብለት ሊያደርግ ይችላል፡፡

   መ/ አቤቱታ ሲቀበል መቼና በስንት ሰዓት እንደሚታይ እና የት እንደሚታይ እንዲሁም ውሳኔ መቼ እንደሚሰጥ ለአቤቱታ አቅራቢውና ለሚመለከታቸው ማሳወቅ አለበት፡፡

11. በየደረጃው የሚገኝ አቤቱታ ሰሚ አካል የቀረበለትን አቤቱታ ከተመለከተ በኋላ ውሳኔውን አቤቱታ ላቀረበው ሰው ወይም አካል በወቅቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

12. የእያንዳንዱ አቤቱታ ውሳኔ በሶስት ቅጂ ተዘጋጅቶ፤

   ሀ/ አንዱ ቅጂ ለአቤቱታ አቅራቢው ይሰጣል፡፡

   ለ/ ሁለተኛው ቅጂ በውሳኔው መሠረት ለሚፈፅም ወይም ውሳኔው ይግባኝ ለተባለበት አካል ይሰጣል፡፡

   ሐ/ ሦስተኛው ቅጂ አቤቱታውን መርምሮ ውሳኔ በሰጠው አካል እጅ በሰነድነት ይያዛል፡፡

13. እያንዳንዱ ውሳኔ በአቤቱታ ሰሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ የተፈረመበት መሸኛ ይኖረዋል፡፡

**አንቀጽ 23. <u>ስለይግባኝ መብት</u>**

1. ማንኛውም አቤቱታ አቅራቢ አቤቱታውን ባቀረበበት አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ ቅር ከተሰኘ በምርጫ ህጉ መሠረት በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ የማቅረብ መብት አለው፡፡

2. በየደረጃው ያለ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ ኮሚቴው በሰጠው ውሳኔ ላይ የይግባኝ መብት ላለው ሰው ወይም አካል፤

ሀ/ ይግባኝ የማቅረብ መብት እንዳለው፣

ለ/ ይግባኙን ለማን ማቅረብ እንዳለበት፣

ሐ/ ይግባኙን ኮሚቴው ውሳኔ ከሰጠበት ቀን ጀምሮ በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ማቅረብ እንዳለበት፣ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፣

3. ማንኛውም አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የይግባኝ መብት ላለው ሰው፤

ሀ/ የኮሚቴውን ውሳኔ አንድ ቅጂ፣

ለ/ ውሳኔ የተሰጠበትን አቤቱታ አንድ ቅጂ እና

ሐ/ የተሰጠውን ውሳኔ እና አቤቱታ ቅጂዎች በአባሪነት የያዘ በአቤቱታ ሰሚው ኮሚቴ ሰብሳቢ ፊርማ የተረጋገጠ መሸኛ ደብዳቤ ሊሰጠው ይገባል፡፡

4. በየደረጃው የሚገኙ ይግባኝ ሰሚ ኮሚቴዎች፤

ሀ/ የዚህ ደንብ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 4 (ለ) እና አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 4 (ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየደረጃው በሚገኙ የበታች አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴዎች ተመርምሮ የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኘን ጉዳይ ማየት የለባቸውም፡፡

ለ/ የቀረበላቸውን ይግባኝ በመመልከት የበታች አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴዎችን ውሳኔ ሊያፀኑ፣ በከፊል ወይም በሙሉ ሊለውጡ ወይም ሊያሻሽሉ ይችላሉ፡፡

ሐ/ የቀረበላቸውን ይግባኝ ተመልክተው አፋጣኝ ውሳኔ በመስጠት በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈጻሚዎች ውሳኔውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ትዕዛዝ መስጠት አለባቸው፡፡

5. ይግባኝ የቀረበለት አቤቱታ ሰሚ አካል በዚህ ደንብ መሠረት በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

6. የምርጫ ህጉ አስገዳጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ይግባኝ የሚቀርበው ለመደበኛ ፍርድ ቤቶች በሚሆንበት ጊዜ አግባብ ያለው የሕግ ድንጋጌ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

7. የዚህ ደንብ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 8(ለ) እና አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 8(ለ) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ፍርድ ቤቶች በምርጫ ህጉ አንቀጽ 92/11/ መሠረት ቦርዱ ወይም በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት በቅድሚያ ያልታየና የመጨረሻ ውሳኔ ያላገኘን የምርጫ ጉዳይ ማየት አይችሉም፡፡

**አንቀጽ 24. <u>ስለይግባኝ አቤቱታ አወሳሰን</u>**

ይግባኝ የቀረበው ይግባኝ ሰሚ ለሆነው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ከሆነ እንደሁኔታው በዚህ ደንብ ስለመጀመሪያ ደረጃ አቤቱታ የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

## <u>ምዕራፍ አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀጽ 25. <u>ስለመተባበር</u>**

ማናቸውም የፌዴራልም ሆነ የክልል የመንግሥት መሥሪያ ቤት፣ የፖለቲካ ድርጅት፣ ቡድን፣ የግል ድርጅት ወይም ግለሰብ ይህንን ደንብ በሥራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 26. <u>ስለቅጣት</u>**

ይህ ደንብ በሥራ ላይ እንዳይውል ያወከ ወይም ድንጋጌዎቹን የጣሰ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ ይቀጣል፡፡

**አንቀጽ 27. <u>የተሻሩ ደንቦች እና አሠራሮች</u>**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**አንቀጽ 28. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በቦርዱ ከፀደቀበት ከነሐሴ 13 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**መርጋ በቃና (ፕሮፌሰር)**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ**

**ሰብሳቢ**

## የስነ ዜጋ እና የመራጮች ትምህርት ፈቃድ አሰጣጥ እና ስነ-ምግባር ደንብ (የምርጫ ቦርድ) ቁጥር 2/2002 ዓ.ም (የተሻሻለው)

### መግቢያ

የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት በስፋት እና በጥራት ለዜጎች እና ለሚመለከታቸው አካላት መሰጠቱ የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በህገመንግሥት የተረጋገጠላቸውን ሰብዓዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን እንዲገነዘቡ የሚያስችል እና ነፃ፣ ቀጥተኛና ፍትሃዊ ምርጫን ለማካሄድ የሚረዳ በመሆኑ፣ የሀገሪቱ ህዝቦች፣ በምርጫው የሚሳተፉ ወይም ለምርጫው አስተዋፅኦ የሚያደርጉ አካላት በምርጫው እንቅስቃሴ ያላቸውን መብትና ግዴታ በመገንዘብ ተግባራቸውን በአግባቡ ለማከናወን የሚያስችላቸው በመሆኑ፣

የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ስለሚሰጡ አካላት፣ ትምህርቱ ስለሚሰጥበት አሠራር እና ለነዚህ አካላት የማስተማር ፈቃድ አሰጣጥ እና ስነምግባር መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተሻሻለው የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 110 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

### አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የስነ-ዜጋ እና የመራጮች ትምህርት ፈቃድ አሰጣጥ እና ስነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 2/2002 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

1. "ቦርድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡
2. "ክልል" ማለት በህገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ይጨምራል፡፡
3. "የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት" ማለት በምርጫ ህጉ መሠረት በክልል ደረጃ ምርጫን የሚያስተባብር በቦርዱ በቋሚነት የሚቋቋም የቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ነው፡፡
4. "ምርጫ" ማለት በፌዴራልና በክልል ህገ መንግሥታት እንዲሁም በሌሎች አግባብ ባላቸው ህጎች መሰረት የሚካሄድ የጠቅላላ፣ የአካባቢ፣ የማሟያ ወይም የድጋሚ ምርጫ ነው፡፡

5. "የምርጫ ህግ" ማለት የተሻሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም. ነው፡፡
6. "የምርጫ አስፈጻሚ" ማለት በየደረጃው ለሚካሄድ ምርጫ በተቋቋሙ ምርጫ ጽሕፈት ቤቶች በቋሚነት፣ በኮንትራት ወይም በጊዜያዊነት ምርጫን የሚያስፈጽም ሰው ነው፡፡
7. "የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ፓርቲ" ማለት የፖለቲካ ፕሮግራሙን በሕጋዊ መንገድ ለማራመድ በሕግ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ቡድን ነው፡፡
8. "ወኪል ወይም ተወካይ" ማለት የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፈቃድ በቦርዱ የተሰጠው ድርጅት የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት እንዲሰጥ የሚያሰማራው ግለሰብ ነው፡፡
9. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ወይም ድርጅት ነው፡፡

**አንቀጽ 3. <u>አተረጓጎም</u>**

በዚህ ደንብ የአተረጓጎም ክፍተት ቢፈጠር ህገመንግሥቱን፣ የምርጫ ህጉን፣ ሌሎች የሀገሪቱን ህጎችን መሠረት ማድረግ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ የስነምግባር ደንብ በመላ ሀገሪቱ በምርጫ ህጉ መሠረት በሚካሄድ በማንኛውም ምርጫ እና ህዝበ ውሳኔ ዙሪያ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት በሚሠጡ ሰዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 5. <u>የፆታ አገላለፅ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የስነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ስለመስጠት</u>

**አንቀጽ 6. <u>የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የመስጠት ኃላፊነት</u>**

1. በምርጫ ህጉ እና በዚህ ደንብ መሠረት የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የመስጠት ኃላፊነት የቦርዱ ነው፡፡
2. ቦርዱ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የሚሰጥበትን እና የሚመራበትን ማኑዋል ያዘጋጃል፡፡ ትምህርቱ በማኑዋሉ መሠረት እንዲመራ ያደርጋል፡፡
3. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ቦርዱ በስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ዙሪያ እያዘጋጀ በሚልክለት እቅድና የማስተማሪያ ማኑዋል ላይ ተመስርቶ ቦርዱ

በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ከሚመለከታቸው ጋር በመተባበር የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ይሰጣል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፡፡

4. በምርጫ ህጉና በዚህ ደንብ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው፡-

   ሀ/ ቦርዱ በምርጫ ህጉና በዚህ ደንብ የተደነገገውን መመዘኛ ለሚያሟላ ሀገር በቀል ድርጅት የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፈቃድ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ወይም

   ለ/ አግባብ ካለው ህጋዊ አካል ጋር በመዋዋል የስነዜጋ እና የመራጮች ትምህርት እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

5. ማንኛውም ሰው ያለቦርዱ ፈቃድ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለመስጠት አይችልም፡፡

**አንቀጽ 7. <u>የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት ኃላፊነት</u>**

1. የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት በዚህ ደንብ አንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ 3 በሚያደርገው ክትትል እና ቁጥጥር የቦርዱ ፈቃድ ሳይኖራቸው የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት በሚሰጡ ማናቸውም አካላት ላይ በሕግ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል፡፡
2. በስነዜጋና በመራጮች ትምህርት ዙሪያ የተሰሩ ሥራዎችን እና የተከሰቱ ችግሮችን በመለየት ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ ለቦርዱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. ቦርዱ ከደረሰው ሪፖርት በመነሳት በስነዜጋና የመራጮች ትምሕርት ዙሪያ የተፈጠሩ ችግሮችን ለማስወገድ በየወቅቱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት እርምጃ ይወስዳል፡፡

**አንቀጽ 8. <u>የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፈቃድ ስለመጠየቅ</u>**

1. በምርጫ ህጉ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 መሠረት የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የማስተማር መስፈርትን የሚያሟላ ማንኛውም ህጋዊ ሀገር በቀል ድርጅት፡-

   ሀ/ ቦርዱ ለዚሁ ያዘጋጀውን የማመልከቻ ቅፅ በመሙላት እና ማስረጃዎቹን በማያያዝ የምርጫው ቀን ቢያንስ 6 ወራት ሲቀረው ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

   ለ/ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለማስተማር የሚያስፈልገውን የገንዘብ መጠን፣ የማስተማር ሥራውን ለማጠናቀቅ የሚፈጅበት ጊዜ፣ የሰው ኃይል አመዳደቡን፣ እና የማስተማር ሥራውን የሚያካሂድበትን ክልል፣ ከተማ፣ ክፍለ

ከተማ፣ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌ ያካተተ ዝርዝር እቅድ በማዘጋጀት ከማመልከቻው ጋር አያይዞ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

ሐ/ ለስነዜጋና የመራጮች ትምህርት በመሪነት፣ በአስተባባሪነት፣ በአስተማሪነት እና በመሳሰለው ተግባር የሚያሠማራቸውን ሰዎች ዝርዝር በዚህ ደንብ አንቀጽ 10 መሠረት ቦርዱ ባዘጋጀው ቅጽ በመሙላት ተያያዥ ማስረጃዎችን አባሪ በማድረግ ከማስተማር ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻው ጋር ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

2. የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለማስተማር ከቦርዱ ፈቃድ የሚጠይቅ ሀገር በቀል ድርጅት በህጋዊነት ተመዝግቦ እና ፈቃድ አውጥቶ በስራ ላይ መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡
3. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ በድርጅቱ ዋና ኃላፊ ፊርማ እና በድርጅቱ ማህተም ተረጋግጦ መቅረብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 9. <u>ስለፈቃድ አሠጣጥ</u>**

1. ቦርዱ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፈቃድ ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን ያቀረበው ድርጅት፡-

ሀ/ በህጋዊ መንገድ ፈቃድ አውጥቶ የሚንቀሳቀስ ሀገር በቀል ድርጅት መሆኑን፣

ለ/ ለመራጮች ትምህርት ቦርዱ ያወጣውን መስፈርት የሚያሟላ መሆኑን፣

ሐ/ ተግባሩን በብቃት ሊወጣ የሚያስችል የሰው ኃይል፣ የትምህርተ ዝግጅት፣ የቁሳቁስ እና የመሳሰለውን ሁኔታ ያሟላ መሆኑን፣

መ/ ድርጅቱም ሆነ የድርጅቱ ተወካይ ከማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ገለልተኛ መሆኑን፣

ሠ/ ድርጅቱ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርትን በማስፋፋት ፍትሃዊና ነፃ ምርጫ ለማካሄድ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር መሆኑን፣ በማረጋገጥ እና ቦርዱ ያዘጋጀውን የዚህን ደንብ የስነምግባር ግዴታ በማስፈረም የማስተማር ፈቃድ ሊሰጠው ይችላል፡፡

2. በአንድ ምርጫ ወቅት የመራጮች ትምህርት ለመስጠት በቦርዱ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት በዚያው ምርጫ ላይ የምርጫ ታዛቢነት ፈቃድ ሊሰጠው አይችልም፡፡
3. ለስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ዕቅድ እና የማስተማሪያ ቁሳቁስ ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የሚያዘጋጅ እና ቦርዱ ባፀደቀው ማኑዋል መሠረት በስራ ላይ የሚያውል መሆን አለበት፡፡
4. ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለማስተማር የሚሰማራ ወኪል፡-

ሀ/ እድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ፣

ለ/ የመምረጥና የመመረጥ መብቱ በህግ ያልተገደበ፣

ሐ/ ተግባሩን ለመፈፀም ሞያዊ ብቃት፣ ልምድና የትምህርት ዝግጅት ያለው፣

መ/ የሚያስተምርበትን አካባቢ ቋንቋ መናገር፣ መስማት፣ መፃፍና ማንበብ የሚችል፣

ሠ/ ቀደም ሲል የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ከማስተማር ጋር በተያያዘ በቦርዱ ያመቸገደ ወይም በፍርድ ቤት ያልተፈረደበት መሆን አለበት፡፡

5. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ የተዘረዘሩትን ለማያሟላ ሰው ፈቃድ አይሰጥም፡፡ ፈቃድ አለመስጠቱንም ለአመልካቹ በፅሁፍ ያሳውቃል፡፡

## አንቀጽ 10. <u>ወኪሎችን ስለማሳወቅ</u>

ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት፡-

1. የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የሚሰጡለት ወኪሎች ይኖሩታል፡፡ ወኪሎቹንም ለቦርዱ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡
2. የወኪሎቹን ዝርዝር ለማሳወቅ የሚጠቀመው ቅፅ በቦርዱ የተዘጋጀ እና ለእያንዳንዱ ወኪል የሚሞላ ነው፡፡

## አንቀጽ 11. <u>ወኪል ስለመለወጥ</u>

ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወኪሉን ሲለውጥ በ7 ቀናት ውስጥ የሚተካውን ሰው ለቦርዱ አሳውቆ ፈቃድ ሲያገኝ ብቻ ሊለውጥ ይችላል፡፡

## አንቀጽ 12. <u>የማስተማር ፈቃድ እና መታወቂያ ካርድ ስለመስጠት</u>

1. ቦርዱ በምርጫ ህጉ አንቀጽ 90 ንዑስ አንቀጽ 1 እና በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ለሰጠው ድርጅት የማስተማር ፈቃድ እና ለወኪሉ መለያ መታወቂያ ካርድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የማስተማር ፈቃድም ሆነ መለያ መታወቂያ ካርድ አገልግሎት የሚሰጠው አንድ የምርጫ ወቅት እስከሚጠናቀቅበት ዕለት ብቻ ይሆናል፡፡

## አንቀጽ 13. <u>የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት አሰጣጥ</u>

1. ቦርዱ ለስነዜጋና ለመራጮች ትምህርት የሚሆን የፅሁፍ፣ የምስል ወይም የድምፅ እና የመሳሰሉትን ማስተማሪያዎች በማዘጋጀት ወይም በሌላ ሰው እንዲዘጋጅ በማድረግ ወይም ሌላ ሰው አዘጋጅቶ የሚሰጠውን ጽሁፍ፣ ድምፅ ወይም ምስል ይዘት እና ብቃት በማረጋገጥ ለማስተማሪያነት ሊገለገልበት ይችላል፡፡

2. ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ስልጣን ያለው ወይም ፈቃድ የተሰጠው ሰው የሚከተለውን የትምህርት አሰጣጥ በስራ ላይ ሊያውል ይችላል፡

ሀ/ የገፅ ለገፅ ስልጠና ለሚመለከታቸው አካላት ወይም ሰዎች በማዘጋጀትና በመስጠት እና ወይም

ለ/ የተለያየ የማስተማሪያ ፅሁፍ፣ መስል፣ ድራማና የመሳሰለውን በማዘጋጀት እና እንዲዘጋጅ በማድረግ በሬድዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በጋዜጣ፣ በመጽሔት፣ በፖስተር፣ በቢልቦርድ፣ በበራሪ ጽሁፍ እና ዋይረ የመሳሰሉ መገናኛዎችን በመጠቀም ሊሆን ይችላል፡፡

3. ቦርዱ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርትና የመሳሰሉትን የማስተማሪያ ዘዴዎች በተለያዩ ቋንቋዎች በማዘጋጀት ወይም በመተርጎም መራጩ ስለምርጫ እንቅስቃሴ በቂ ግንዛቤ እንዲያገኝ ያደርጋል፡፡

4. ማንኛውም በምርጫ ህጉ ወይም በዚህ ደንብ አንቀጽ 9 መሠረት ቦርዱ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የሚሰጥ ሰው፡-

ሀ/ አስቀድሞ ባዘጋጀውና ቦርዱ ባፀደቀለት የማስተማር እቅድ እና ይዘት መሠረት ማስተማር አለበት፡፡

ለ/ ለስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የሚውል ማስተማሪያ በምስል፣ በድምፅ ወይም በጽሁፍ በማዘጋጀትና በቦርዱ እንዲፀድቅ በማድረግ ማስተማር አለበት፡፡

5. ማንኛውም ከላይ በንዑስ አንቀጽ 4"ለ" መሠረት በቦርዱ የፀደቀ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ማስተማሪያ ቦርዱ ካፀደቀው በኋላ ምንም ነገር መቀነስ መለወጥ ወይም ሌላ ተጨማሪ ማስተማሪያ ፕሮግራም፣ ምዕራፍ፣ ክፍል፣ ዘዴ፣ ቁሳቁስ ወይም የመሳሰሉትን ነገሮች ማካተት አይቻልም፡፡

6. ማንኛውም ሰው ከላይ በንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት ለማካተት ያሰበውን የማስተማሪያ ክፍል ወይም ዘዴ በማዘጋጀትና ቦርዱ እንዲያፀድቀው በማድረግ በስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ውስጥ እንዲካተት ሊያደርግ ይችላል፡፡

7. ማንኛውም ሰው የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የሚያስተምረው ቦርዱ ባፀደቀው የርዕስ ቅደም ተከተል መሠረት ብቻ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 14. <u>የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ሊሰጣቸው የሚችሉ ሰዎች</u>**

1. ቦርዱ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለሰልጣኞቹ በሚመጥን ደረጃ ሆኖ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ቦርዱ ለመራጩ ህዝብ፣ በየደረጃው ለሚገኙ የምርጫ አስፈጻሚዎች፣ ለምርጫ ታዛቢዎች፣ ለጋዜጠኞች፣ በሀገሪቱ ህግ መሠረት ተመዝግበው ለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ለመንግስታዊ ድርጅቶች፣ ለሙያ ማህበራትና ለሕዝባዊ ድርጅቶች የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ይሰጣል ወይም በዚህ ደንብ መሠረት በሌላ ህጋዊ ሰው እንዲሰጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የሚሰጡ ሰዎች መከተል ስለሚኖርባቸው ስነምግባር

### አንቀጽ 15. ገለልተኛ ስለመሆን

1. ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ፈቃድ የወሰደ ድርጅት ወይም እርሱ ያሰማራው ወኪል፦
   ሀ/ ከማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ገለልተኛ መሆን አለበት፡፡
   ለ/ ማንኛውንም የፖለቲካ ድርጅት ወይም እጩ በመወገን፣ በመቃወም ወይም በመንቀፍ መንቀሳቀስ የለበትም፡፡
   ሐ/ ማንኛውም ሌላ ሰው አንዱን እንዲደግፍ ሌላውን እንዲቃወም፣ እንዲነቅፍ ወይም እንዲያጥላላ በማሰብ ማስተማር ወይም መቀስቀስ የለበትም፡፡
2. ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮችን ትምህርት ለመስጠት ፈቃድ የወሰደ ድርጅት ወኪል በምርጫ እንቅስቃሴ የሚሳተፍ የፖለቲካ ድርጅትን፣ የእጩውን ወይም የግል እጩን ማንኛውንም አይነት ደጋፊ ወይም ተቃራኒ ምልክት፣ መፈክር፣ ወይም የመሳሰለውን በመለጠፍ፣ በመስቀል፣ በማውለብለብ ወይም በማንኛውም መልኩ ይዞ መገኘት የለበትም፡፡
3. እየተካሄደ ባለ ምርጫ ላይ የግል አስተያየት ከመስጠት የመቆጠብ ግዴታ አለበት፡፡
4. ገለልተኛ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

### አንቀጽ 16. የጥቅም ግጭት

1. ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለማስተማር ፈቃድ የወሰደ ሀገር በቀል ድርጅት በንብረት፣ በገንዘብ፣ በዝምድና ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ ከምርጫ ተወዳዳሪ እጩ ወይም የፖለቲካ ድርጅት ጋር የጥቅም ግንኙነት ሲያጋጥመው ጉዳዩን ዘርዝሮ ወዲያውኑ ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡

2. ቦርዱ የጥቅም ግጭት ያጋጠመው ሰው ሪፖርት ሲደርሰው በሌላ አካባቢ እንዲያስተምር፣ ማስተማሩን እንዲቀጥል ወይም ሌላ አስፈላጊ ነው የሚለውን ትዕዛዝ ሊሰጠው ይችላል፡፡

**አንቀጽ** 17. <u>ሀቀኝነት</u>

ማንኛውም በምርጫ ህጉ እና በዚህ ደንብ መሠረት የማስተማር ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ወኪሉ፡-

1. በማንኛውም ጊዜ የሚያስተምረው የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት፣ የሚያሠራጨው መረጃ፣ ወይም ለማንኛውም ሰው የሚያቀርበው ሪፖርት በእውነተኛ ማስረጃ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡
2. የሚያስተምረው የስነ ዜጋና የመራጮች ትምህርት ዝግጅት፣ ዕቅድ እና የትምህርት አሠጣጥ ቦርዱ ባፀደቀው የትምህርት ይዘትና ቅደም ተከተል መሠረት ብቻ መሆን ይኖርበታል፡፡
3. ስለዜጋና ለመራጮች ትምህርት የተመደበለትን ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ ብቻ ማዋል አለበት፡፡

**አንቀጽ** 18. <u>ሚስጥር መጠበቅ</u>

ማንኛውም በምርጫ ህጉ እና በዚህ ደንብ መሠረት የማስተማር ፈቃድ የተሰጠው ሰው ወይም ወኪሉ፡-

1. በማስተማር የስራ እንቅስቃሴው ያወቀውን ማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲዎችን ወይም ቦርዱን የሚመለከት ሚስጢራዊ ጉዳይ ወይም መረጃ አሳልፎ መስጠት የለበትም፡፡
2. በቦርዱ ይፋ ያልተደረገን ማንኛውንም መረጃ፣ ውሳኔ ወይም ሌላ የምርጫ ጉዳይ በቦርዱ ይፋ እስከሚደረግ ድረስ በምስጢር መያዝ አለበት፡፡
3. ማንኛውንም በእጁ የገባን የቦርዱን ቅፅ ወይም ሰነድ ላልተፈቀደለት ሰው አሳልፎ መስጠት የለበትም፡፡

**አንቀጽ** 19. <u>ህግ ማክበርና ማስከበር</u>

1. ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት የማስተማር ህጋዊ ፈቃድ የተሰጠው ድርጅትም ሆነ ወኪሉ ህገመንግሥቱን፣ የምርጫ ህጉን እና ሌሎች የሀገሪቱን ህጎች እንዲሁም በዚህ ስነምግባር ደንብ የገባውን ግዴታ ማክበር እና ማስከበር አለበት፡፡
2. ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለማስተማር ህጋዊ ፈቃድ የተሰጠው ሰው በዚህ ደንብ ከገባው የስነምግባር ግዴታ ውጪ ሲንቀሳቀስ የተገኘን ድርጅትም ሆነ ወኪሉን ቦርዱ እንደሁኔታው፣

ሀ/ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቱን እንዲያርም ለማድረግ ወይም

ለ/ ፈቃድ እስከመሰረዝ እና መለያ መታወቂያ እስከመቀማት ሊደርስ የሚችል እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡

3. ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት እንዲሰጥ ፈቃድ የተሰጠው ሰው የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለማስተማር የተሰጠውን የተረጋገጠ የፈቃድ ቅጂ እና መለያ መታወቂያ የመያዝ እና አግባብ ባለው ሰው ሲጠየቅም ማሳየት፣
4. ማንኛውም በምርጫ ህጉ እና በዚህ ደንብ መሠረት የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ፈቃድ ያገኘ ሰው በህግ መሠረት ብቻ የማስተማር፣
5. በየደረጃው በሚገኙ የምርጫ አስፈጻሚዎች የሚሰጠውን መመሪያ እና ደንብ የማክበር፣
6. የምርጫ ሂደት በትክክል እንዳይካሄድ ከሚያደርግ እንቅስቃሴ እና ከተሰጠው ፈቃድ ውጭ ከመንቀሳቀስ የመቆጠብ፣
7. በዚህ ደንብ በተደነገገው ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ዝርዝር ሪፖርት የማቅረብ፣
8. ወኪሉ ህገወጥ ድርጊት በመፈፀሙ ወይም ይህንን የስነምግባር ደንብ በመጣሱ ምክንያት ቦርዱ ማስጠንቀቂያ የሰጠው እንደሆነ አፋጣኝ ማስተካከያ በመውሰድ ለቦርዱ የማሳወቅ ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 20. <u>የገንዘብ ምንጭ</u>**

1. ቦርዱ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለመስጠት የሚያስፈልገውን ገንዘብ ይመድባል፡፡
2. ማንኛውም ሰው ቦርዱ ከሚመድብለት ውጪ ለስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ማካሄጃ የሚውል ገንዘብ ማሰባሰብም ሆነ መመደብ አይችልም፡፡

**አንቀጽ 21. <u>የሂሳብ አያያዝ</u>**

ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለመስጠት በቦርዱ ፈቃድ የተሰጠው ሰው ከቦርዱ የተመደበለትን ገንዘብ በአግባቡና ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን ቦርዱ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በህጋዊ ሰነድ ማወራረድ አለበት፡፡

**አንቀጽ 22. <u>ሪፖርት ስለማቅረብ</u>**

ማንኛውም የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለማስተማር ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት፡-

1. የሥራ አፈጻጸምና የሂሳብ ሪፖርት በየሶስት ወሩ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው ቢኖርም በማንኛውም ጊዜ በቦርዱ ሲጠየቅ ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡

3. ማስተማሩን እንዳጠናቀቀ በ15 ቀናት ጊዜ ውስጥ የሥራ እና የገንዘብ ወጪ ሪፖርት እና የሂሳብ ሰነዶቹን ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡
4. ቦርዱ ወቅታዊ የሥራ አፈጻጸም ግምገማ ያደርጋል፡፡

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀጽ 23. <u>የመተባበር ግዴታ</u>**

ማንኛውም ሰው ይህን ደንብ በስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 24. <u>ቅጣት</u>**

በዚህ ደንብ የተደነገገውን የስነምግባር ግዴታ ያልፈፀመ ወይም የጣሰ ሰው አግባብ ባለው ህግ መሰረት ይቀጣል፡፡

**አንቀጽ 25. <u>መመሪያ ስለማውጣት</u>**

ቦርዱ ይህንን የስነምግባር ደንብ በስራ ላይ ለማዋል የሚያስችል መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 26. <u>የተሻሩ ህጎች እና አሠራሮች</u>**

ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ደንብ ወይም አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም፡፡

**አንቀጽ 27. <u>የተፈጻሚነት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በቦርዱ ከፀደቀበት ከጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**መርጋ በቃና (ፕሮፌሰር)**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ**

## የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ አሰጣጥ፣ አሰራር እና ስነምግባር

## ደንብ ቁጥር 3/2002 ዓ.ም (የተሻሻለው)

**መግቢያ**

ምርጫን መታዘብ የዴሞክራሲያዊ ምርጫ አንዱ አካል መሆኑን በመገንዘብ፣

የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ተግባራቸውን በከፍተኛ ስነምግባር እና ከወገንተኝነት በፀዳ አኳኋን በማከናወን ተአማኒነትና ተቀባይነት ያለው ትክክለኛ ሪፖርት ማቅረብ ያለባቸው መሆኑን በመገንዘብ፣

ምርጫን ለመታዘብ የሚችሉ የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ማንነት፣ የፈቃድ አሰጣጥና ስምሪት በዝርዝር መደንገግ በማስፈለጉ፣ እና

በሀገር ውስጥ በምርጫ ታዛቢነት የሚሰማሩ ሰዎች አሰራርና ሊከተሏቸው የሚገቡ የስነምግባር መርሆዎችን በግልጽ መደንገግ ተገቢ በመሆኑ፣

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተሻሻለው የኢትዮጵያ ምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ዓ.ም አንቀጽ 79 ንዑስ አንቀጽ 1 እና አንቀጽ 110 በተሰጠው ስልጣን መሠረት የሚከተለውን ደንብ አውጥቷል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

**አንቀጽ** 1. **አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ፈቃድ አሰጣጥ፣ አሠራር እና ስነምግባር ደንብ ቁጥር 3/2002 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ** 2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፤

1. "ህገመንግስት" ማለት የሚትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግሥት ነው፡፡
2. "ቦርድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡
3. "ጠቅላላ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡
4. "የአካባቢ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሠረት የሚካሄድ የዞን፣ የወረዳ፣ የከተማ፣ የማዘጋጃ ቤት የክፍለ ከተማ ወይም የቀበሌ ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡

5. "ድጋሚ ምርጫ" ማለት በምርጫ ህጉ መሠረት ቦርዱ ድጋሚ ምርጫ እንዲካሄድ ሲወስን ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች እኩል ድምፅ በማግኘታቸው ምክንያት አሸናፊውን መለየት በማይቻልበት ጊዜ የሚካሄድ ምርጫ ነው፡፡
6. "ማሟያ ምርጫ" ማለት በይውረድልን ወይም በማንኛውም ምክንያት በየደረጃው የሚገኙ የተጓደሉ የምክር ቤት አባላት መቀመጫዎችን ለማሟላት የሚካሄድ ምርጫ ነው፡፡
7. "ህዝብ ውሳኔ" ማለት በኢ.ፌ.ዲ.ሪ ህገመንግስት መሰረት የህዝብ ፍላጎትን ለመለካት እና የህዝብን ውሳኔ ለማወቅ ድምፅ የሚሰጥበት ስርዓት ነው፡፡
8. "የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ" ማለት በህግ የተመዘገበ እና ለማንም ያልወገነ ገለልተኛ ሀገር በቀል ድርጅት ሆኖ ከቦርዱ በሚሰጠው ፈቃድ መሠረት በሚወክለው ሰው ምርጫን የሚታዘብ አካል ነው፡፡
9. "ምርጫ ጣቢያ ማለት በየደረጃው በሚካሄዱ ምርጫዎች ምዝገባ የሚካሄድበት፣ መራጮች ድምፅ የሚጥሉበት እና ቆጠራ የሚካሄድበት ቦታ ነው፡፡
10. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡
11. "ወኪል" ማለት በቦርዱ የታዛቢነት ፈቃድ ያገኘ ድርጅት ምርጫውን እንዲታዘብለት የሚመድበውና በቦርዱ ተቀባይነት ያገኘ ሰው ነው፡፡
12. "የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት" ወይም "የኢትዮጵያ ማሕበር" ማለት የበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማሕበራትን ለመመዝገብና ለማስተዳደር በወጣው አዋጅ ቁጥር 621/2001 አንቀጽ 2 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት በኢትዮጵያ ሕግ መሠረት የተመሠረተ ድርጅት ነው፡፡

**አንቀጽ 3. <u>አላማ</u>**

የዚህ ደንብ አላማ፡-

1. ማንኛውም የምርጫ ሂደትን የመታዘብ እንቅስቃሴ
   ሀ/ ከወገንተኝነት የፀዳ ሁሉ አቀፍ እና ትክክለኛ እንደዚሁም፣
   ለ/ የሀገሪቱን ህጎች ያከበረ ግልፅና ተአማኒነት ያለው መሆኑን ማረጋገጥ፡፡
2. ታዛቢዎች በምርጫ ሂደቱ ጣልቃ ሳይገቡ ተግባራቸውን እንዲያከናውኑ ማስቻል፡፡
3. ታዛቢዎች ከማንኛውም አካል ጣልቃ ገብነት ውጭ ህግን ተከትለው ተግባራቸውን እንዲፈጽሙ ማድረግ ነው፡፡

**አንቀጽ 4. <u>አተረጓጎም</u>**

በዚህ ደንብ አተረጓጎም ላይ ክፍተት ቢፈጠር የምርጫ ህጉን እና ሌሎች የሀገሪቱን ህጎች መሠረት በማድረግ ይወሰናል፡፡

**አንቀጽ 5. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ በጠቅላላ ምርጫ፣ በአካባቢ ምርጫ፣ በማሟያ ምርጫ፣ በድጋሚ ምርጫ እንዲሁም በህገመንግሥቱ እና በምርጫ ሕጉ መሠረት የሚካሄድ ህዝብ ውሳኔ ላይ በሚሳተፉ የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 6. <u>የፆታ አገላለፅ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

**<u>ምዕራፍ ሁለት</u>**

**<u>የሀገር ውስጥ ታዛቢ ፈቃድ የሚያገኝበት መመዘኛ እና ስለፈቃድ አሰጣጥ</u>**

**አንቀጽ 7. <u>ጥያቄ ማቅረብ ስለሚችሉ አካላት</u>**

1. የሀገር ውስጥ ታዛቢዎች ምርጫን ለመታዘብ ጥያቄያቸውን ለቦርዱ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
2. የሚከተሉት አካላት በሀገሪቱ ውስጥ የሚካሄዱ ምርጫዎችን በሚወክሏቸው ሰዎች አማካይነት ለመታዘብ ይችላሉ፡፡

   ሀ/ የሀይማኖት ድርጅቶች፣

   ለ/ የብዙሃን ማህበራት፣

   ሐ/ የሙያ ማህበራት፣

   መ/ የኢትዮጵያ የበጎ አድራጎት ድርጅት ወይም ማህበር፣

**አንቀጽ 8. <u>የምርጫ ሂደትን የመታዘብ መብት እና አጠቃላይ ቅድመ ሁኔታ</u>**

1. በምርጫ ሕጉ እና በዚህ ደንብ የተደነገገውን መመዘኛ የሚያሟላ ማንኛውንም አካል ቦርዱ የሚሰጠውን የታዛቢነት ፈቃድና መታወቂያ በመያዝ የምርጫ ሂደትን መታዘብ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ለመሆን የሚፈልግ ሰው ከቦርዱ ፈቃድ ሳያገኝ በታዛቢነት ሊሰማራ አይችልም፡፡
3. ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ምርጫን የሚታዘበው በቦርዱ ተመዝግቦ ፈቃድ እና መታወቂያ ወረቀት በተሰጠው ወኪል አማካይነት ይሆናል፡፡
4. ማንኛውም የሀገር ውስጥ ታዛቢ ወይም ወኪል ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተጠቀሰ ተግባሩን ሲያከናውን ምርጫውን ከሚያደናቅፍ ማንኛውም ተግባር እንዲሁም በምርጫው ሂደት ጣልቃ ከመግባት መቆጠብ አለበት፡፡
5. ማንኛውም ምርጫን የሚታዘብ ሰው ለዚህ ሥራ የሚያስፈልገው ወጪ የሚሸፈነው በራሱ ወይም በወከለው ተቋም ይሆናል፡፡ የቦርዱን ተሽከርካሪ ወይም ሌላ ሀብት የመጠቀም መብት የለውም፡፡

6. ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ተቋም የወከላቸው ታዛቢዎች ተግባራቸውን ከመጀመራቸው በፊት፡-

ሀ/ ስለምርጫ ሂደቶች፣

ለ/ በምርጫ ህጐች እና አሠራሮች እንዲሁም

ሐ/ በዚህ የስነምግባር ደንብ ድንጋጌዎች ላይ የተሟላ ስልጠና እንዲያገኙ እና በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ አለበት፡፡

7. ማንኛውም ወኪል የታዘበውን ጉዳይ ወይም ግድፈት በየደረጃው ለሚገኙ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት በማቅረብ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ማድረግ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ አካላቱ በቀረቡት ጉዳዮች ወይም አስተያየቶች ላይ ምላሽ እንዲሰጡ ወይም እርምጃ እንዲወስዱ አይገደዱም፡፡

8. ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ወይም ወኪል ከፍተኛ የሙያ ስነምግባር ሊኖረው ይገባል፡፡

9. ድርጅቱ ይህንን የስነ ምግባር ደንብ አክብሮና ተገዥ ሆኖ ለመንቀሳቀስ መስማማቱን ለዚሁ ተግባር በቦርዱ የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት እና በፊርማው በማረጋገጥ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

10. እያንዳንዱ የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ወኪሉ ይህንን የስነምግባር ደንብ አክብሮ እንዲንቀሳቀስ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡

**አንቀጽ 9. <u>ፈቃድ ለማግኘት መሟላት ያለበት መመዘኛ</u>**

1. ለሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢነት ፈቃድ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ድርጅት፡-

ሀ/ በኢትዮጵያውያን የተመሰረተ፣ የኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ወይም ማህበር ሆኖ የተመዘገበ እና ፈቃድ ይዞ የሚንቀሳቀስ ድርጅት፣

ለ/ ከማንኛውም የፖለቲካ ወገንተኝነት የፀዳ፣

ሐ/ በምርጫ ህጉ እና በዚህ ደንብ የተደነገገውን ግዴታ የተቀበለና ለመፈፀም ፈቃደኝነቱን በፊርማው ያረጋገጠ፣

መ/ ለምርጫ ፍትሃዊነት፣ ነፃነትና ሰላማዊነት ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር ዝግጅት ያደረገ፣ መሆን አለበት፡፡

2. ማንኛውም ፈቃድ ጠያቂ ድርጅት የሌሎች ፈቃድ ያወጡ የኢትዮጵያ በጐ አድራጐት ድርጅት ወይም የኢትዮጵያ ማህበር ህብረት ከሆነ ሁሉም አባል ድርጅቶች በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ግዴታዎች ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. በንዑስ አንቀጽ 2 ከተጠቀሱት ድርጅቶች በዚህ ደንብ የተደነገጉትን ግዴታዎች ያላሟሉ ከሆነ ቦርዱ አስፈላጊውን እርምጃ ሊወስድ ይችላል፡፡
4. ቦርዱ ድርጅቱ የሚያሰማራቸው ግለሰቦች ምርጫውን በገለልተኝነት ለመታዘብ ችሎታ ያላቸው መሆኑን በማጣራትና በቦርዱ የተዘጋጀውን የምርጫ ታዛቢዎች የስነ ምግባር ደንብ መቀበላቸውን፣ ድርጅቱንና ወኪሎቹን በማስፈረም፣ የታዛቢነት ፈቃድና መታወቂያ ካርድ ሊሰጥ ይችላል፡፡
5. ማንኛውም በሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት የሚሠማራ ወኪል፡-
   ሀ/ ኢትዮጵያዊ ዜጋ የሆነ፣
   ለ/ ዕድሜው 18 ዓመት እና ከዚያ በላይ የሆነ፣
   ሐ/ የመምረጥ እና መመረጥ መብቱ በሕግ ያልተገደበ፣
   መ/ ቀደም ሲል በምርጫ ታዛቢ ወኪልነት ተሰማርቶ በቦርዱ ያልታገደ መሆን አለበት፡፡
6. ቦርዱ በዚህ ደንብ የተዘረዘሩትን ለማያሟላ ወኪል ፈቃድ አይሰጥም፡፡ ፈቃድ አለመስጠቱንም ለአመልካቹ በፅሁፍ ያሳውቃል፡፡

**አንቀጽ 10. <u>የምርጫ ታዛቢ መሆን ስለማይችል ሰው</u>**

1. ድርጅቱ በተሰማራበት ሥራው በፍርድ ቤት የታገደ፣
2. ማንኛውም ከዚህ በፊት በሀገር ውስጥ ታዛቢነት ተሰማርቶ በነበረበት ወቅት ከህግ ውጪ በመንቀሳቀሱ በቦርዱ የታገደና እገዳው ያልተነሳለት፣
3. ምርጫን ለመታዘብ በጠየቀበት ምርጫ ላይ የስነዜጋና የመራጮች ትምህርት ለመስጠት ፈቃድ የወሰደ መሆን የለበትም፡፡

**አንቀጽ 11. <u>የፈቃድ ጥያቄ አቀራረብ /ስለማመልከቻ አቀራረብ/</u>**

1. ማንኛውም በምርጫ ታዛቢነት ለመሰማራት የሚፈልግ ድርጅት፡-
   ሀ/ የታዛቢነት ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻውን ቦርዱ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላትና ማስረጃዎቹን በማያያዝ ከድምፅ መስጫው ዕለት ከ4 ወር በፊት ጥያቄውን በፅሁፍ ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡
   ለ/ በሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢነት የሚያሰማራቸውን ወኪሎች ዝርዝር፣ የሚታዘቡበትን አካባቢ እና ሌሎች መረጃዎችን ቦርዱ በሚያዘጋጀው ቅፅ መሠረት በመሙላትና ተያያዥ መረጃዎችን አባሪ በማድረግ ከታዛቢነት ፈቃድ መጠየቂያ ማመልከቻው ጋር ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡
2. በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚቀርብ ማመልከቻ በድርጅቱ ዋና ኃላፊ ወይም እርሱ በወከለው ሰው ፊርማ እና በድርጅቱ ማህተም የተረጋገጠ መሆን አለበት፡፡

3. ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ የታዛቢነት የሥራ ዕቅዱን፣ የታዛቢነት ዓላማና ግቡን ለቦርዱ በጽሁፍ የማቅረብ ግዴት አለበት፡፡
4. ቦርዱ ለቀረበለት የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻው ተሟልቶ በደረሰው በ15 ቀን ውስጥ በደብዳቤ ምላሽ ይሰጣል፡፡
5. ቦርዱ የቀረበለትን ማመልከቻ መርምሮ መመዘኛውን አሟልቶና ብቁ ሆኖ ለተገኘ የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅትና ወኪል ፈቃድ እና መታወቂያ ካርድ ይሰጣል፡፡

**አንቀጽ 12. <u>የማመልከቻ ይዘት እና የወኪሎችን ዝርዝር ስለማሳወቅ</u>**

1. ቦርዱ ማመልከቻ የሚቀርብበትን ቅፅ /ፎርም/ የሚያዘጋጅ ሲሆን ምርጫ ለመታዘብ ጥያቄ የሚያቀርብ የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢም በማመልከቻው ውስጥ የሚከተሉትን ማካተት ይኖርበታል፡፡

   ሀ/ የድርጅቱን ስምና አድራሻ፣

   ለ/ የድርጅቱን ባለቤት ስም፣

   ሐ/ መከታተል የሚፈልገው የምርጫ ሂደት፣

   መ/ መከታተል የሚፈልግበት ቦታ፣

   ሠ/ ቡድኑን የሚመራው ሰው ስም እና አድራሻ፣
2. ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢነት ፈቃድ እንዲሰጠው ጥያቄ ያቀረበ ድርጅት፡-

   ሀ/ ቦርዱ በሚያዘጋጀው ቅፅ መሠረት የወኪሎቹን ዝርዝር እና ሌሎች ተያያዥ መረጃዎችን ሞልቶ ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

   ለ/ ወኪሉን መቀየር ሲፈልግ የሚተካውን ሰው በወኪል ዝርዝር ማቅረቢያው ቅፅ መሠረት አስቀድሞ ለቦርዱ ማቅረብ እና ማስፈቀድ አለበት፡፡

**አንቀጽ 13. <u>ከማመልከቻ ጋር ተያይዞ ስለሚቀርብ ሰነድ</u>**

ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ከሚያቀርበው የማመልከቻ ቅፅ ጋር የሚከተሉት ሰነዶች ተያይዘው መቅረብ አለባቸው፡፡

1. ከቦርዱ ፈቃድ የሚጠይቅ የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት በኢትዮጵያ በጎ አድራጎት ወይም ማህበርነት ተመዝግቦ እና ህጋዊ ፈቃድ አውጥቶ በሥራ ላይ መሆኑን የሚያሳይ በዘመኑ የታደሰ የፈቃድ ማስረጃ፡፡
2. የወኪሎችን ሙሉ ስም፣ ዜግነት፣ የትውልድ ቀንና ዘመን እንዲሁም ሌሎች የፓስፖርት ወይም የመታወቂያ መረጃን፣ ወኪሉ በተግባሩ ዙሪያ በቂ ስልጠና የተሰጠው መሆኑን እና ቦርዱ ያወጣውን ወይም ያፀደቀውን የስነምግባር ደንብ

አክብሮ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ መሆኑን የሚገልጽ በእያንዳንዱ ወኪል ፊርማ የተረጋገጠ ሠነድ /ቅፅ/፡፡

3. የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅቱ ቦርዱ ያወጣውን የስነምግባር ደንብ አክብሮ ለመንቀሳቀስ ፈቃደኛ መሆኑን የሚገልጽ በተቋሙ ማህተምና የበላይ ኃላፊ ፊርማ የተረጋገጠ ሰነድ፡፡
4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 ከተጠቀሰው እያንዳንዱ ወኪል ካረጋገጠው ቅጽ ወይም ሰነድ ጋር ተያይዞ የሚቀርብ የወኪሉ ሙሉ ስም እና የወከለውን ድርጅት ስም በጀርባው የያዘ ወኪሉ በቅርብ ጊዜ የተነሳው ሁለት የፓስፖርት ፎቶግራፍ፡፡
5. የወኪሉ የፓስፖርት ወይም ሌላ የመታወቂያ ካርድ ኮፒ፡፡

**አንቀጽ 14. <u>ስለፈቃድ አሰጣጥ</u>**

1. በምርጫ ህጉ አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 5 መሠረት የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢነት ፈቃድ የመስጠት ስልጣን የቦርዱ ነው፡፡
2. ቦርዱ የሀገር ውስጥ የታዛቢነት ፍቃድ ጥያቄ ሲቀርብለት ጥያቄውን ያቀረበው ድርጅት፡-

   ሀ/ በሀገሪቱ ህግ መሠረት ህጋዊ ፈቃድ አውጥቶ የሚንቀሳቀስ መሆኑን፣

   ለ/ በምርጫ ህጉ ወይም በዚህ ደንብ የተደነገጉትን መስፈርቶች እና ግዴታዎች ያሟላ መሆኑን፣

   ሐ/ ምርጫ የመታዘብ ተግባሩን በብቃት ሊወጣ የሚያስችል በቂ የሰው ኃይል እና አደረጃጀት ያለው መሆኑን፣

   መ/ የወከላቸው ሰዎች ከማንኛውም የፖለቲካ እንቅስቃሴ ወገንተኝነት የፀዱ መሆናቸውን በማጣራትና ይህንን ደንብ መቀበሉን ድርጅቱን በማስፈረም የታዛቢነት ፈቃድ ይሰጣል፡፡

3. ቦርዱ በምርጫ ህጉ አንቀጽ 79 እና በዚህ ደንብ የተደነገገው ባለመሟላቱ የሀገር ውስጥ የታዛቢነት ፈቃድ የከለከለ እንደሆነ ይህንኑ ለአመልካቹ በፅሁፍ ያሳውቀዋል፡፡
4. ማንኛውም በቦርዱ የተሰጠ የታዛቢነት ፈቃድ የሚያገለግለው በአንድ ወቅት የሚካሄድ የምርጫ ውጤት በቦርዱ በይፋ እስከሚገለፅበት ዕለት ብቻ ነው፡፡

**አንቀጽ 15. <u>ማመልከቻ ውድቅ የሚሆንባቸው ምክንያቶች</u>**

አንድ የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ወይም ወኪል እንደአግባብነቱ በሚከተሉት ምክንያቶች ምርጫን ለመታዘብ ያቀረበው የፈቃድ ጥያቄ ማመልከቻ ውድቅ ሊሆን ይችላል፡-

1. የማመልከቻ ማቅረቢያ ጊዜ ካለፈ በኋላ የሚቀርብ የፈቃድ ጥያቄ፣
2. ያልተሟላ ወይም የተሳሳተ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ ማመልከቻ፣
3. የፈቃድ ጥያቄ የማቅረብ መብት በሌለው ሰው የቀረበ ማመልከቻ፣
4. ጥያቄውን ያቀረበው ድርጅት ወይም ወኪል በህግ የተደነገጉ ቅድመ ሁኔታዎችን የማያሟላ ሆኖ ከተገኘ፣
5. ተግባሩን ከወገንተኝነት በፀዳ ሁኔታ ሊያከናውን አይችልም ብሎ ቦርዱ ሲያምን፣ ወይም
6. የአንድ ወኪል ስም የተለያዩ ተቋሚት በላኩት የታዛቢዎች የስም ዝርዝር ውስጥ ተካቶ ከተገኘ ነው፡፡

## አንቀጽ 16. <u>የታዛቢነት መታወቂያ ካርድ ስለመስጠት</u>

1. ቦርዱ በተሻሻለው የምርጫ ህግ እና በዚህ ደንብ መሠረት የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢነት ፈቃድ ለሰጠው ድርጅት ወኪል በቦርዱ የተዘጋጀውን የዚህን ደንብ ግዴታ የሚያሟላና የሚቀበል ስለመሆኑ በማስፈረም የታዛቢነት መታወቂያ ካርድ ይሰጣል፡፡
2. ማንኛውም በቦርዱ የተሰጠ የታዛቢነት መታወቂያ ካርድ የሚያገለግለው በአንድ ወቅት የሚካሄድ የምርጫ ውጤት በየምርጫ ጣቢያውና በየምርጫ ክልሉ እስከሚገለፅበት ዕለት ብቻ ነው፡፡
3. ፍቃድ ያገኘ ድርጅት ወኪሉን ከቀየረ ወይም የመታዘብ ሥራውን ካቋረጠ የታዛቢነት መታወቂያውን ተረክቦ ለቦርዱ መመለስ አለበት፡፡
4. ቦርዱ ፈቃድ ለሚሰጣቸው ወኪሎች የሚያዘጋጀው የመታወቂያ ካርድ የሚከተሉትን ነጥቦች የያዘ ይሆናል፡፡

   ሀ/ የቦርዱን ሎጎ/አርማ/፣

   ለ/ የወከለውን ድርጅት ስም እና የወኪሉን ፎቶግራፍ፣

   ሐ/ የወኪሉን ሙሉ ስም፣

   መ/ የቦርዱ ማህተም፣

   ሠ/ መታወቂያው የሚፀናበት ጊዜ፣

   ረ/ የመታወቂያ ቁጥር፣

   ሰ/ ፈቃዱን የሠጠው ኃላፊ ስም እና ፊርማ፣ እና

   ሸ/ የባለመታወቂያው ፊርማ፣

## <u>ምዕራፍ ሶስት</u>

## <u>የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ መብት፣ ግዴታና የተከለከሉ ተግባራት</u>

**አንቀጽ 17. <u>የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት መብት</u>**

የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት፡-

1. ምርጫን የሚታዘብለት ህጋዊ ወኪል የማሰማራት፣
2. በወኪሉ አማካኝነት በተሰማራበት በምርጫ ክልል እና በምርጫ ጣቢያ በመዘዋወር የምርጫውን ሂደት የመከታተልና ተገቢ መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣
3. በምርጫው ሂደት የታዘባቸውን ወይም ያጋጠሙትን ጉድለቶች ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት በጽሁፍ የማቅረብ፣
4. ያሰማራውን ወኪል በዚህ ደንብ መሠረት የመቀየር መብት አለው፡፡

**አንቀጽ 18. <u>የወኪሎች መብት</u>**

ማንኛውም ምርጫን ለመታዘብ ፈቃድ የተሰጠው የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ወይም ወኪል እንደአግባብነቱ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡፡

1. ከግል ደህንነቱ ጋር በተያያዘ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ያለቅድሚያ ማስታወቂየ ጥያቄ ባቀረበበት እና ፈቃድ ባገኘበት በየትኛውም ክልል፣ ዞን፣ ከተማ፣ የምርጫ ክልል፣ ወረዳ ወይም የምርጫ ጣቢያ ምርጫን መከታተል፣ ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ፈቃድ የጠየቁት ታዛቢዎችን የስምሪት አካባቢ በስምምነት ሊያሸጋሽግ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የምርጫ ሂደት ማለትም የመራጮች ምዝገባን፣ የእጩዎች ምዝገባንና የምርጫ ቅስቀሳን እንደዚሁም የድምፅ አሰጣጥን፣ የቆጠራ ሂደትን እና የውጤት አገላለጽን መከታተል፣
3. ምልከታውን፣ ትዝብቱን ወይም ግኝቱን እና የደረሰበትን ድምዳሜ አስመልክቶ ሪፖርት የማቅረብ፣
4. ከመንግስት፣ ከቦርዱና ከሌላ ከማንኛውም ሰው ተፅእኖ ውጪ በገለልተኛነት የታዛቢነት ሥራውን ብቻ የማከናወን፣
5. ከቦርዱና ከአካባቢ ባለስልጣናት እንደዚሁም በየደረጃው ከሚገኙ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት ትብብር የማግኘት፣
6. በምርጫ ጣቢያ በመዘዋወር የምርጫውን ሂደት የመከታተልና ተገቢ መረጃ ጠይቆ የማግኘት፣ እና
7. የምርጫውን ሂደት በሚመለከት የታዘበውን እና ያጋጠመውን ጉድለት ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት ወይም በአካባቢው ለሚገኝ የምርጫ ጽሕፈት ቤት የማቅረብ መብት አለው፡፡

**አንቀጽ 19. <u>ሕግን ስለማክበርና ማስከበር</u>**

ማንኛውም ፈቃድ የተሰጠው ድርጅት ወይም ወኪል፡-

1. የሀገሪቱን ሉአላዊነት እንደዚሁም የዜጎችን ሰብአዊ መብትና መሠረታዊ ነፃነት ማክበር፣
2. የምርጫ ህጉን፣ ደንቦችንና መመሪያዎችን እንደዚሁም ሌሎች ተዛማጅ ህጎችን ጠንቅቆ ማወቅ፣
3. ህገ መንግስቱን፣ የምርጫ ህግን እና ሌሎች የሀገሪቱን ህጎች የማክበርና የማስከበር፣ እና
4. የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችንና ህዝቦችን ቋንቋ፣ ባህል፣ ማንነትና መብት ማክበር እና ማስከበር፣ አለበት፡፡
5. የህግ ማእቀፎችን መተርጉም እና የምርጫ ሂደትን የሚመለከት ህጋዊ ያልሆነ መረጃ ወይም መመሪያ መስጠት የለበትም፡፡
6. የሀገሪቱን እና የአካባቢውን ባህልና ልምድ ማክበር አለበት፡፡
7. በቦርዱ የተሰጠውን የመታወቂያ ካርድ በሚታይ ቦታ አድርጎ መንቀሳቀስ እና በሚመለከተው አካል ሲጠየቅ ማንነቱን የሚያረጋግጥ ፓስፖርት ወይም መታወቂያ ማሳየት አለበት፡፡

**አንቀጽ 20. <u>የምርጫ አስፈጻሚዎችን ስልጣን ማክበር</u>**

1. የቦርዱን እና በየደረጃው ያሉ የምርጫ አስፈጻሚዎችን፣ የፀጥታና ደህንነት እንደዚሁም የሌሎች የመንግስት አካላት የሚሰጡትን ህጋዊ ትዕዛዝና መመሪያ የመቀበልና የማክበር፣
2. ከምርጫ አስፈጻሚ አካላት ጋር ቅርብ የሥራ ግንኙነት መፍጠር፣
3. ከምርጫ አስፈጻሚዎች እንደዚሁም ከሌሎች ታዛቢዎችና ባለድርሻ አካላት ጋር ተባብሮ መስራት አለበት፡፡
4. በምርጫ አስፈጻሚ አካላት ተአማኒነት ወይም ተቀባይነት ላይ የሀሰት ግንዛቤ እንዲፈጠር አለማድረግ፡፡

**አንቀጽ 21. <u>የምርጫ ሂደትን አለማወክ</u>**

ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት እና ወኪሉ

1. የምርጫው ሂደት በትክክልና በብቃት እንዳይካሄድ ከሚያደርግ ማንኛውም ተግባር መቆጠብ አለበት፡፡
2. ለምርጫ አስፈጻሚዎች ከኃላፊነታቸው ጋር የተያያዘ መመሪያ ወይም ምክር አለመስጠት፡፡

3. የሚመለከቷቸውን የጎሉ ስህተቶችን ለምርጫ አስፈጻሚዎች ሪፖርት ከማድረግ ውጭ ምክር በመስጠት ችግሮችን ለመፍታት አለመንቀሳቀስ፡፡
4. የአፈታት ሂደቱን ከመታዘብ ውጭ የውይይቱ አካል በመሆን በቅሬታ /አቤቱታ/ በመፍታት ሂደት ውስጥ አለመሳተፍ፡፡

**አንቀጽ 22. ገለልተኛ ስለመሆን**

የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ወይም ወኪሉ፡-

1. ተግባራቱን ከወገንተኝነት በፀዳ አኳኋን ማከናወን፤ ከማንኛውም አካል ጋር በማንኛውም ሁኔታ ገለልተኝነቱን ከሚጎዳ ወይም ወገንተኝነትን ከሚያሳይ እንቅስቃሴ መቆጠብ፣
2. የፖለቲካ ድርጅቶችን ወይም እጩን ወገንተኝነት ሊገለፅ ከሚችል በነዚህ አካላት ወይም ሰዎች ከተዘጋጀ የጉብኝት፣ የግብዣ ወይም ሌላ መሰል እንቅስቃሴዎች መታቀብ፣
3. ማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ወይም እጩን ከመደገፍ ወይም ከመንቀፍ መቆጠብ፤ ከባለስልጣናት፣ ከፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ከእጩ ተወዳዳሪዎች ከመራጮችና ከመገናኛ ብዙኃኖች ጋር የተያያዘ ወይም አወዛጋቢ በሆነ የምርጫ ጉዳይ ላይ ወገንተኝነትን ከማሳየት ወይም ከመግለጽ መታቀብ አለበት፡፡
4. የማንኛውንም በምርጫ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለ የፖለቲካ ድርጅትን ወይም እጩን፣ ማንኛውንም አይነት ምልክት ወይም የቅስቀሳ ቁሳቁስ በግቢው፣ በቢሮው፣ በመጓጓዣው፣ በራሱ ላይ እንደሁኔታው በማሳየት፣ በመያዝ፣ በማስቀመጥ፣ በመስቀል በመለጠፍ ወይም በመልበስ በመሳሰለው ሁኔታ መንቀሳቀስ፣ ማሳየት ወይም ይዞ መገኘት የለበትም፡፡

**አንቀጽ 23. የምርጫን ሚስጥራዊነት እና የመራጮችን መብት ስለማክበር**

1. መራጩ ድምፁን ለማን እንደሰጠ ወይም ማንን እንደሚመርጥ መጠየቅ የለበትም፡፡
2. በድምፅ መስጫ ክፍል እና በድምፅ ቆጠራ ቦታ ካሜራም ሆነ ሌላ የድምፅ ወይም የምስል መቅረጫ መሳሪያ መጠቀም የለበትም፡፡
3. ማንኛውንም ለመመዝገብ የቀረበ መራጭ/ድምፅ ሰጪ ወይም የምርጫ አስፈጻሚ ያለፈቃዱ በፊልም መቅረጽ፣ ፎቶግራፍ ማንሳት ወይም በቃለ-መጠይቅ ማወያየት አይፈቀድለትም፡፡
4. የመራጮች ምዝገባ መረጃዎች በሰነድ ላይ ሲሰፍሩ ወይም መራጩ በድምፅ መስጫው ወረቀት ላይ የምርጫ ምልክት ሲያደርግ፣ ተደብቆ በፊልም መቅረጽ

ወይም ፎቶግራፍ ማንሳት ወይም ማናቸውንም ምስል፣ የተቀረፀ ፊልም ወይም አስተያየት የተቀዳበትን የድምፅ ክር በስውር እጁ ማስገባት አይፈቀድለትም፡፡

5. የድምፅ ሰጪዎችን ምርጫ ምስጢራዊነት በሚነካ አኳኋን የመራጮችን መዝገብ፣ የመራጮችን ምዝገባ መታወቂያ ወይም ማናቸውንም ሌላ ሰነድ በፊልም መቅረጽ፣ ፎቶግራፍ ማንሳት ወይም ኮፒ ማድረግ አይፈቀድለትም፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ሊከተላቸው የሚገቡ የስነምግባር ድንጋጌዎች

### አንቀጽ 24. ጥቅም አለመቀበል ወይም አለመስጠት

ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ወይም ወኪል ከማንኛውም በምርጫ እንቅስቃሴ ከሚሳተፍ የፖለቲካ ድርጅት፣ እጩ፣ ደጋፊ ወይም ማንኛውም ሰው ወይም አካል በምርጫ ሂደት ማንኛውንም ተግባር ለማድረግ ወይም ላለማድረግ ወይም በደጋፊነት ለመንቀሳቀስ በማሰብ ጥቅም መቀበል ወይም መስጠት፣ ለመቀበል ወይም ለመስጠት መዋዋል ወይም ቃል መግባት በህግ ያስቀጣል፡፡

### አንቀጽ 25. የጥቅም ግጭት

አንድ የምርጫ ታዛቢ ወይም ወኪል፡-

1. የምርጫ ሂደትን ከመታዘብ ተግባሩ ጋር የተያያዘ የጥቅም ግጭትን ለቦርዱ ማሳወቅ አለበት፡፡
2. የጥቅም ግጭት የሚያስከትል ወይም ሊያስከትል በሚችል በማንኛውም እንቅስቃሴ ውስጥ መሣተፍ የለበትም፡፡
3. ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ወይም ወኪል በምርጫ ታዛቢነት ሥራው ላይ በንብረት፣ በገንዘብ፣ በዝምድና ወይም በማንኛውም ሌላ ሁኔታ የጥቅም ግጭት ሁኔታዎች ያጋጠመው፣

   ሀ/ ወኪሉ ሲሆን ጉዳዩን ወዲያውኑ ለተሰማራበት አካባቢ የምርጫ ክልል ጽሕፈት ቤት እና ላሰማራው ድርጅት፣

   ለ/ ድርጅት ሲሆን ጉዳዩን ወዲያውኑ ለተሰማራበት አካባቢ የቦርዱ የክልል ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤት እና ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት ማሳወቅ አለበት፡፡
4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የጥቅም ግጭት አጋጥሞት ወይም እንደሚያጋጥመው በማወቁ ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ያቀረበ ሰው የታዛቢነት ሥራውን አቁሞ ቦርዱ የሚሰጠውን ውሳኔ መጠባበቅ ይኖርበታል፡፡

5. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ መሠረት የጥቅም ግጭት ካጋጠመው ሰው ወይም ከሚመለከተው የምርጫ አስፈጻሚ ሪፖርት ሲደርሰው ጉዳዩ ነፃ፣ ቀጥተኛና ፍትሃዊ ምርጫን የሚያደናቅፍ መሆኑን በራሱ በማጣራት በቦታው ላይ ሥራውን እንዲቀጥል ወይም ወደ ሌላ ቦታ እንዲዛወር ወይም ከታዛቢነቱ እንዲሰረዝ ሊወስን ይችላል፡፡ ውሳኔውንም ወዲያውኑ ለሚመለከተው አካል ያሳውቃል፡፡

**አንቀጽ 26. ሀቀኝነት**

ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅትም ሆነ በድርጅቱ የሚሰማራ ወኪሉ፡-

1. በማንኛውም ጊዜ የሚያቀርበው፣ የሚያሰራጨው መረጃ ወይም ሪፖርት ሀቀኛ፣ ተደራሽ እና በበቂ ማስረጃ የተደገፈ ግልፅና የማያሻማ መሆን አለበት፡፡
2. ያቀረበው ወይም ያሰራጨው ሪፖርት ወይም መረጃ ተቀባይነት ባለው አሰራር የተሰበሰበ፣ የተጠናቀረ፣ የታተመ እና የተፈረመበት መሆን አለበት፡፡
3. የሚያገኘው መረጃ በሚመለከተው አካል ውሳኔ ያልተሰጠበት ሆኖ ሲያገኘው ውሳኔ እስኪሰጥበት ድረስ በመረጃነት መጠቀም የለበትም፡፡

**አንቀጽ 27. ቅንነት**

1. ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ወይም ወኪሉ የታዛቢነት ተግባሩን በሚያከናውንበት ሂደት ፍፁም ቅንነት የተሞላበት ስነምግባር ሊኖረው ይገባል፡፡
2. የተጣለበትን ኃላፊነት ለመወጣት የማያስችል ሁኔታ ሲያጋጥመው ጉዳዩን ወዲያውኑ ለላከው ድርጅት ማቅረብ አለበት፡፡

**አንቀጽ 28. ስለምርጫው ውጤት አስቀድሞ አስተያየት ስለመከልከሉ**

ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ድርጅት ወይም ወኪል የምርጫ ውጤት በቦርዱ በይፋ ከመገለፁ በፊት በሀገር ውስጥም ሆነ ከሀገር ውጪ ሆኖ ስለምርጫው ውጤት አስተያየቱን መስጠት የተከለከለ ነው፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ሪፖርት ስለማቅረብ እና የስነምግባር ደንብ በማያከብር የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ላይ ስለሚወሰድ እርምጃ

**አንቀጽ 29. ሪፖርት ስለማቅረብ**

1. ማንኛውም ወኪል ለወከለው ድርጅት ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ የተሰማራበት የምርጫ ጣቢያ ወይም የምርጫ ክልል ውጤት በተገለፀ ከ7 እስከ 10 ቀን ባለው ጊዜ ውስጥ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

2. ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ስለታዘበው የምርጫ እንቅስቃሴ ዝርዝር ሪፖርት አዘጋጅቶ ቦርዱ የምርጫውን ውጤት ይፋ ካደረገበት ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ የማቅረብ ግዴታ አለበት የሪፖርቱ ይዘትም፡-
   ሀ/ ድርጅቱ በምርጫ ታዛቢነት ሥራው የሸፈነው ክልል፣ ዞን፣ የምርጫ ክልል ወይም ምርጫ ጣቢያ ብዛት እና የመረጃ አሰባሰብ ዘዴውን፣
   ለ/ በእያንዳንዱ የምርጫ እንቅስቃሴ ሂደት፣ በምርጫ ዝግጅት፣ በመራጮች ምዝገባ፣ በእጩዎች ምዝገባ፣ በምርጫ ዘመቻ፣ በድምፅ አሰጣጥ፣ በድምፅ ቆጠራ እና በውጤት አገላለፅ ላይ የታዘባቸውን ሁኔታዎች ያካተተ መሆን አለበት፡፡
3. ማንኛውም የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ከትዝብቱ ጋር ያገኘውን መረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡
4. በትክክለኛ መረጃ፣ ከወገንተኝነት በፀዳ የመረጃ ትንተና፣ በተጨባጭ ማስረጃ ላይ የተመሰረተ፣ በመከራከሪያ ምክንያቶች የተደገፈ፣ ሁሉ አቀፍ የምርጫ ሂደትን የተመለከተ እና የምርጫ ሂደትን የሚጎዱ እውነታዎችን ወይም ፍሬ ነገሮችን ከግምት ውስጥ ያስገባ ሪፖርት ማዘጋጀት አለበት፡፡

**አንቀጽ 30. <u>ፈቃድ የሚሠረዝበት ሁኔታ</u>**

1. ቦርዱ አንድ የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ወይም ወኪል የምርጫ ሂደትን እንዲከታተል የተሰጠውን ፈቃድ በሚከተሉት ምክንያቶች ሊያግድ ወይም ሊሠረዝ ይችላል፡-
   ሀ/ በስራ ላይ ያሉ ህጎችን፣ ደንቦችን፣ መመሪያዎችን እና ሌሎች አሰራሮችን ጥሶ ሲገኝ፡፡
   ለ/ በህግ ከተደነገገው ውጭ ማንኛውንም አድልዎ ለየትኛውም እጩ ወይም ፖለቲካ ፓርቲ አሳይቶ ሲገኝ፡፡
2. ቦርዱ የሰጠውን ፈቃድ ሲሰርዝ ወይም ሲያግድ ውሳኔውን የወሰደበትን ምክንያት በመጥቀስ ለሚመለከተው ሰው ማሳወቅ አለበት፡፡

**አንቀጽ 31. <u>ስለሚወሰድ እርምጃ</u>**

የሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢ ወይም ወኪሉ ከዚህ የስነምግባር ደንብ እና ከገባው ግዴታ ውጪ ሲንቀሳቀስ ከተገኘ ቦርዱ እንደሁኔታው፡-

1. ማስጠንቀቂያ በመስጠት ስህተቱን እንዲያርም ወይም ወኪሉ እንዲቀየር ሊያደርግ፣
2. ለሀገር ውስጥ የምርጫ ታዛቢነት የሰጠውን ፈቃድ ሊሰርዝ፣
3. በህግ እንዲጠየቅ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሰድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**አንቀጽ 32. የመተባበር ግዴታ**

ማንኛውም ሰው ይህንን ደንብ በስራ ላይ ለማዋል የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 33. የተሻሩ ደንቦችና መመሪያዎች**

ማንኛውም ከዚህ ደንብ ጋር ተቃራኒ የሆነ ደንብ፣ መመሪያ እና አሠራር ይህንን ደንብ በሚመለከት ተፈጻሚነት የለውም፡፡

**አንቀጽ 34. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ ቦርዱ ካፀደቀበት ከጥር 10 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**መርጋ በቃና /ፕሮፌሰር/**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ**

**ሰብሳቢ**

## ደንብ ቁጥር 5/2001 ዓ.ም

## መንግሥት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ የሚከፋፈልበትን አሠራር ለመደንገግ የወጣ ደንብ

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

**አንቀጽ 1. አውጪው አካል**

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ በተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000 ዓ.ም አንቀጽ 61 በተሰጠው ስልጣን መሠረት ይህንን ደንብ አውጥቷል፡፡

**አንቀጽ 2. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ "ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው ድጋፍ የሚከፋፈልበትን አሠራር ለመደንገግ የወጣ ደንብ ቁጥር 5/2001 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 3. ትርጓሜ**

1. "የምዝገባ አዋጅ" ማለት የተሻሻለው የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000 ዓ.ም ማለት ነው፡፡
2. "ቦርድ" ማለት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡
3. "የፖለቲካ ፓርቲ" ወይም "የፖለቲካ ድርጅት" ማለት ከህብረተሰቡ ውስጥ የተወሰኑ ሰዎችን በማሰባሰብ የራሱን የፖለቲካ እምነትና ዓላማ የሚያንጸባርቅበት ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ በምዝገባ አዋጅ መሠረት የተመዘገበ ተቋም ነው፡፡
4. "የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ" ማለት በምዝገባ አዋጁ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች በምርጫ ወቅት ወይም ለእለት ተእለት ሥራ ማከናወኛ መንግስት በገንዘብ፣ በዓይነት እና/ወይም በአገልግሎት መልክ የሚሠጠው ድጋፍ ነው፡፡
5. "የፖለቲካ ፓርቲዎች በምክር ቤት ያላቸው መቀመጫ" ማለት የፖለቲካ ፓርቲዎች ቀደም ሲል በህዝብ ተመርጠው መቀመጫ ያገኙባቸው የፌዴራል ወይም የክልል ምክር ቤቶች ናቸው፡፡
6. "ምርጫ" ማለት ጠቅላላ ምርጫ ነው፡፡
7. "ጠቅላላ ምርጫ" ማለት አግባብ ባለው ህግ መሰረት የሚካሄድ የህዝብ ተወካዮችና የክልል ምክር ቤቶች አባላት ምርጫ ነው፡፡
8. "ኦዲተር" ማለት የሞያ ብቃቱ የተረጋገጠ፣ በማናቸውም መንገድ ከሚሾመው የፖለቲካ ፓርቲ ጋር ግንኙነት የሌለው በፖለቲካ ፓርቲ የሚሾም ሰው ነው፡፡

9. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሠው ወይም በህግ የሰውነት መብት የሰጠው አካል ነው፡፡
10. "የሥራ ዘመን" ማለት በምርጫ ህጉ መሠረት የህዝብ ተወካዮች ወይም የክልል ምክር ቤቶች ምርጫ የሚካሄድበት የአምስት ዓመት የሥራ ጊዜ ነው፡፡
11. "ብቁ መመዘኛ" ማለት ህጋዊ ሆኖ የተመዘገበ፣ ከአንድ እና ከዚያ በላይ እጩ ያቀረበ፣ ለነፃና ፍትሐዊ ምርጫ የሚሰራ፣ የምርጫ ስነምግባር ደንብ የፈረመ እና ቅሬታውን በሕግ አግባብ የሚፈታ ነው፡፡

**አንቀጽ 4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>**

ይህ ደንብ ለጠቅላላ ምርጫ ተግባርና ለዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ ከመንግስት ድጋፍ በሚሰጣቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 5. <u>የጾታ አገላለፅ</u>**

በዚህ ደንብ ውስጥ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

**አንቀጽ 6. <u>ዓላማ</u>**

የዚህ ደንብ ዓላማ መንግሥት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ የሚከፋፈልበት መስፈርት ወይም ቀመር እንዲሁም ጥቅም ላይ ስለሚውልበትና ስለሚተዳደርበት ሁኔታ ግልጽ አሰራር በመዘርጋት የፖለቲካ ፓርቲዎች ለዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ የበኩላቸውን ሚና እንዲጫወቱ ማስቻል ነው፡፡

**አንቀጽ 7. <u>የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ የሚከፋፈልበት መርህ</u>**

1. በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው ማንኛውም ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው ማንኛውም የፋይናንስ ድጋፍ በፍትሃዊነት እና ያለአድልዎ መፈፀም አለበት፡፡
2. በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 44 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት የተሰጣቸውን የፋይናንስ ድጋፍ በአግባቡ እና ለታለመለት ህጋዊ ዓላማና ተግባር ብቻ ማዋል አለባቸው፡፡
3. ማንኛውም የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ ቀድሞ ለተካሄደ የምርጫ ወጪ መሸፈኛ ሊጠየቅ አይችልም፡፡
4. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በመንግስት በሚሰጥ ማንኛውንም የፋይናንስ ድጋፍ ተጠቃሚ እንዲሆን አይገደድም፡፡
5. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ሂሳቡን በሕግ መሠረት ማንቀሳቀስ አለበት፡፡ ከተፈቀደለት ውጪ ወጪ ማድረግ የለበትም፡፡

<u>**ምዕራፍ ሁለት**</u>

<u>**የፋይናንስ ድጋፍ ምንጭና ዓይነት**</u>

**አንቀጽ 8. <u>ስለፋይናንስ ድጋፍ ምንጭ</u>**

መንግስት በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 43 ወይም በዚህ ደንብ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ፡-

1. ከመንግስት የሚመደብ፣
2. ከውጪ ሀገርም ሆነ ከሀገር ውስጥ ከሚገኝ ድጋፍ ወይም እርዳታ፣ እና
3. ከሌላ ከማንኛውም አካል የሚመነጭ ሊሆን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 9. <u>ስለፋይናንስና ድጋፍ ዓይነት</u>**

መንግስት በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 42 ንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት ወይም በዚህ ደንብ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ እንደ ሁኔታው፡-

1. በገንዘብ
2. በዓይነት እና/ወይም
3. በአገልግሎት ሊሆን ይችላል፡፡

**አንቀጽ 10. <u>ድጋፍን የማከፋፈል ስልጣን</u>**

1. ማንኛውም በዚህ ደንብ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲዎች በመንግስት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ ዓይነት እና መጠን በቦርዱ የሚለይና የሚተዳደር ይሆናል፡፡
2. በመንግስት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ ቦርዱ በሚያወጣው ቀመር መሰረት ይከፋፈላል፡፡
3. ቦርዱ ከላይ በንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ክፍፍሉ የሚከናወንበትን ቀመር ለተጠቃሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 11. <u>በገንዘብ ስለሚሰጥ ድጋፍ</u>**

መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች በገንዘብ የሚሰጠው ድጋፍ በጥሬ ገንዘብ በሚሆን ጊዜ በፖለቲካ ፓርቲው <u>ህጋዊ</u> አካውንት ውስጥ የሚገባና ለታቀደለት ህጋዊ ዓላማ እና ተግባር ብቻ የሚውል ነው፡፡

**አንቀጽ 12. <u>በዓይነት ስለሚሰጥ የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ</u>**

መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች በዓይነት የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ በፖለቲካ ፓርቲው ፍላጎት መሠረት ፖስተር፣ ቲ-ሸርት፣ ኮፍያ፣ ቢልቦርድ፣ ባነር፣ የእጩ ምልክት፣ የእጩ ፎቶግራፍ፣ ኮምፒዩተር፣ ፕሪንተር፣ ፎቶኮፒ ማንሻ T፣ ፋክስ፣ ወይም ስካነር፣ በራሪ ጽሁፍ፣ ማይክሮፎን፣ ባጅ፣ ስቲከር፣ ባንዲራ እንደ ሁኔታው ገዝቶ ወይም አሳትሞ ማከፋፈልን ያካትታል፡፡

**አንቀጽ 13. <u>በአገልግሎት መልክ ስለሚሰጥ የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ</u>**

1. መንግስት በአገልግሎት መልክ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ በመንግስት የመሰብሰቢያ አዳራሽ በነፃ እንዲገለገሉ ማድረግ፣ በህግ መሠረት የመገናኛ ብዙኃን አገለግሎት መስጠት፡ ወይም የመሳሰሉትን አገልግሎቶች ያካትታል፡፡
2. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 18 መሠረት፡-
   ሀ/ ከአባላቱና ከደጋፊዎቹ በሚገኘው ገቢ ላይ ምንም ዓይነት የገቢ ግብር አይከፍልም፡፡
   ለ/ ቀጥሮ ከሚያሰራቸው ሠራተኞች ደመወዝ ላይ በህግ በተወሰነ መሰረት የገቢ ግብር ሰብስቦ ለመንግስት ገቢ ከማድረግ ነጻ ነው፡፡
3. አንድ ፖለቲካ ፓርቲ በዚህ ደንብ መሠረት ከተመደበለት የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ ለመገናኛ ብዙሃን መጠቀሚያ የተሰጠውን ድርሻ ቦርዱ በገንዘብ አስልቶ ለሚመለከተው የፖለቲካ ፓርቲ ያሳውቃል፡፡

## ምዕራፍ ሶስት

## ለምርጫ ተግባር ለፖለቲካ ፓርቲዎች

## ከመንግስት የሚሰጥ ድጋፍ ስለሚመራበት አሰራር

### አንቀጽ 14. ለምርጫ ተግባር ድጋፍ ስለሚሰጥበት ሁኔታ

1. በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 47 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት መንግስት በፌዴራል ወይም በክልል ምክር ቤቶች ምርጫ ለሚሳተፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች ድጋፍ ይሰጣል፡፡
2. ለዚህ ደንብ አፈጻጸም ለምርጫ ተግባር የሚወጣ ወጪ፡-
   ሀ/ እጩ ለማቅረብ፣
   ለ/ የፖለቲካ ፕሮግራምን ለመላው ህዝብ በማስተዋወቅ የምርጫ ቅስቀሳ ለማድረግ፣
   ሐ/ የምርጫ ሂደት ነፃ፣ ፍትሐዊ፣ ሰላማዊ፣ ህጋዊና ዴሞክራሲያዊ እንዲሆን ለመላው ህዝብ ለማስተማር፣
   መ/ የፓርቲ ወኪሎቹን ለማሰልጠን እና ለማሰማራት እና የመሳሰሉ ወጪዎችን ያካትታል፡፡

በምዝገባ አዋጁ ወይም በዚህ ደንብ መሠረት ለምርጫ ተግባር የሚውል ከመንግስት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ ለጠቅላላ ምርጫ እና ለፌዴራልና ለክልል ምክር ቤቶች የማሟያ ምርጫ ብቻ ይሆናል፡፡

### አንቀጽ 15. ለምርጫ ተግባር የሚውል የፋይናንስ ድጋፍ ስለሚሰጥበት መስፈርት

1. በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 45 መሠረት በምርጫ ወቅት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ፡-

   ሀ/ ለፌዴራል ምክር ቤት ምርጫ ሲሆን የፖለቲካ ፓርቲው ቀደም ሲል በተካሄደ ምርጫ በፌዴራሉ ምክር ቤት ባለው መቀመጫ ብዛት፣ ወይም

   ለ/ ለክልል ምክር ቤት ምርጫ ሲሆን የፖለቲካ ፓርቲው ቀደም ሲል በተካሄደ ምርጫ በክልል ምክር ቤት ባለው የመቀመጫ ብዛት መሠረት ይሆናል፡፡

2. የንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም በምርጫ ወቅት የሚሰጥ የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ በሚከተሉት መስፈርቶች የሚከፋፈል ይሆናል፡፡

   ሀ/ የፖለቲካ ፓርቲው ለውድድር ባቀረበው የእጩ ብዛት፣ እና

   ለ/ የፖለቲካከ ፓርቲው ለውድድር ባቀረበው የሴት እጩ ብዛት፣

3. መንግስት ለምርጫ ተግባር ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ በየጊዜው ቦርዱ እያዘጋጀ በሚያቀርበው ቀመር መሠረት ይመራል፡፡ ቦርዱ ያዘጋጀውን ቀመር ለፖለቲካ ፓርቲዎች ያሳውቃል፤ አስተያየት እንዲሰጡበት ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 16. <u>ለምርጫ ተግባር ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት ስለሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ ጥያቄ አቀራረብ</u>**

1. ቦርዱ ለምርጫ ጊዜ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ ዝርዝር ክፍፍልን አስመልክቶ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ካወጣበት ጀምሮ በ15 ቀናት ውስጥ አመቺ በሆነ ማስታወቂያ ለምርጫ ለመወዳደር ለተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

2. ማንኛውም በምዝገባ አዋጁና በዚህ ደንብ መሠረት ለምርጫ ተግባር የሚሰጥ የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሚያደርግ መመዘኛን የሚያሟላ የፖለቲካ ፓርቲ አስፈላጊውን መመዘኛ ማሟላቱን የሚያመለክት ዝርዝር መረጃ በዚህ ደንብ አንቀጽ 17 እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች አንቀጾች መሠረት ጥያቄውን ያቀርባል፡፡

**አንቀጽ 17. <u>ለምርጫ ጊዜ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግሥት የሚሰጥ ፋይናንስ ድጋፍ ስለሚከፋፈልበት የጊዜ ሠሌዳ</u>**

1. ለምርጫ ጊዜ ለፖለቲካ ፓርቲዎች ከመንግስት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ በሚከተለው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ይከፋፈላል፡፡

   ሀ/ ማንኛውም ለፖለቲካ ፓርቲ በዓይነት የሚሰጥ የመንግስት ድጋፍ የእጩ ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ይከፋፈላል፡፡

ለ/ ማንኛውም ለአንድ የፖለቲካ ፓርቲ ቀድሞ በነበረው የምክር ቤት መቀመጫ ብዛት መሰረት በገንዘብ የሚሰጥ ድጋፍ በዚህ አንቀጽ በፊደል "ሀ" በተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ ይከፋፈላል፡፡

ሐ/ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለምርጫ ባቀረበው ጠቅላላ እጩ እና በሴት እጩ ብዛት መሰረት በገንዘብ የሚሰጥ ድጋፍ የእጩ ምዝገባ ከተጠናቀቀበት ቀጥሎ ባለው 15 ቀናት ውስጥ ይከፋፈላል፡፡

መ/ ማንኛውም ለፖለቲካ ፓርቲ በአገልግሎት መልክ የሚሰጥ ድጋፍ ቦርዱ ባወጣው የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ መሠረት የምርጫ ዘመቻ ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ እስከሚጠናቀቅበት ዕለት ድረስ ብቻ ይሰጣል፡፡

ሠ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1/መ/ የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ ደንብ አንቀጽ 13 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት ከገቢ ግብር ነጻ በመሆኑ ላይ ገደብ አይደረግበትም፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገገው የምክር ቤት መቀመጫ ብዛት የፌዴራል የሕዝብ ተወካዮች ወይም የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባዔ በወቅቱ በሚኖረው የምክር ቤት መቀመጫ ላይ ተመስርቶ በሚሰጠው ማስረጃ መሠረት ይረጋገጣል፡፡
3. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው ጊዜ ውጪ የፋይናንስ ድጋፍ ጥያቄ ለማቅረብ አይችልም፡፡
4. የመንግስት የመገናኛ ብዙኃንን አገልግሎት ለማግኘት በፖለቲካ ፓርቲ የሚቀርብ ጥያቄ በምርጫ ህጉ እና በምርጫ ወቅት የፖለቲካ ፓርቲዎች የመገናኛ ብዙሃን አጠቃቀምን ለመወሰን በወጣው መመሪያ መሠረት ይመራል፡፡
5. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ለምርጫ ተግባር ከመንግስት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ የሚከፋፈልበትን የጊዜ ሰሌዳ ሊያሻሽል ይችላል፡፡ የተሻሻለውን የጊዜ ሰሌዳ የመንግስትን የፋይናንስ ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ለሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡
6. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ለምርጫ ተግባር ከመንግስት ከተሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ ያልተጠቀመበትን የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡
7. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ምርጫ ሳይጠናቀቅ አቋርጦ የወጣ እንደሆነ በጥሬ ገንዘብና በቋሚ ንብረት የተሰጠውን የመንግሥት የፋይናንስ ድጋፍ እንዲመልስ ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## ለፖለቲካ ፓርቲዎች የዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ

## ከመንግስት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ የሚመራበት አሰራር

**አንቀጽ 18.** **ለዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ ስለሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ**

1. መንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የእለት ተእለት ተግባር ማከናወኛ የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ እንደሁኔታው በገንዘብ፣ በዓይነት እና/ወይም በአገልግሎት ሊሆን ይችላል፡፡
2. በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ማንኛውም በዚህ ደንብ መሰረት ለእለት ተእለት ተግባር ማከናወኛ የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ የሚያገኝ የፖለቲካ ፓርቲ በየምክር ቤቶቹ ባለው ጠቅላላ መቀመጫ መሰረት ብቻ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 19.** **ስለፖለቲካ ፓርቲ የዕለት ተዕለት ተግባር**

በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 46 ንዑስ አንቀጽ 2 መሠረት የፖለቲካ ፓርቲ የዕለት ተዕለት ተግባር፡-

1. የህዝቡን የፖለቲካ ግንዛቤ ማዳበርን፣
2. ዜጎች በሀገሪቱ ፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ንቁ ተሳትፎ እንዲኖራቸው ማድረግን፣
3. የፖለቲካ ፓርቲውን ዓላማ ለህዝብ ማስረፅን፣
4. በህዝቡና በመንግስት ተቋማት መካከል መልካም ግንኙነት እንዲጠናከር ማድረግን ያካትታል፡፡

**አንቀጽ 20.** **ለዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ የሚውል የፋይናንስ ድጋፍ ስለሚሰጥበት መስፈርት**

1. ለዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ የሚውል የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ የሚያገኙት በፌዴራል ወይም በክልል ምክር ቤቶች ውክልና ያላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ይሆናሉ፡
2. ማንኛውም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚጥ የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ የፖለቲካ ፓርቲዎቹ በፌዴራል ወይም በክልል ምክር ቤቶች ባላቸው መቀመጫ ብዛት መሠረት የድጋፉ ተጠቃሚ ይሆናሉ፡፡
3. መንግስት ለእለት ተእለት ተግባር ማከናወኛ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ በየጊዜው ቦርዱ እያዘጋጀ በሚያቀርበው ቀመር መሠረት ይመራል፡፡ ቦርዱ ያዘጋጀውን ቀመር ለፖለቲካ ፓርቲዎች ያሳውቃል፤ አስተያየት እንዲሰጡበት ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 21.** **ለእለት ተእለት ተግባር ማከናወኛ ከመንግስት ፋይናንስ ድጋፍ ስለሚሰጥበት ጊዜና ድጋፍ ጥያቄ አቀራረብ**

ማንኛውም ለእለት ተእለት ተግባር ማከናወኛ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የሚሰጥ የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ፡-

1. የፌዴራል የሕዝብ ተወካዮች ወይም የክልል ምክር ቤት የሥራ ዘመን በይፋ በተከፈተ አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ በሚቀርብ ጥያቄ መሰረት እና በየዓመቱ በተመሳሳይ ጊዜ ይከፋፈላል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ድንጋጌ ቢኖርም ለጠቅላላ ምርጫ የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ በሚሰጥበት ጊዜ የዕለት ከዕለት የመንግሥት የፋይናንስ ድጋፍ ለፖለቲካ ፓርቲዎች አይሰጥም፡፡
3. ቦርዱ በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት በሚቀርብለት ጥያቄ ላይ ተመስርቶ ጥያቄው በደረሰው በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ድጋፉን ለጠያቂው የፖለቲካ ፓርቲ ይሰጣል፡፡
4. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው የምክር ቤት መቀመጫ ብዛት የፌዴራል የሕዝብ ተወካዮች ወይም የክልል ምክር ቤት አፈ ጉባዔ በወቅቱ በሚኖረው የምክር ቤት መቀመጫ ላይ ተመስርቶ በሚሰጠው ማስረጃ መሠረት ይረጋገጣል፡፡
5. ማንኛውም ለእለት ተእለት ተግባር የመንግስት ድጋፍ ለማግኘት ብቁ የሆነ የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 ከተደነገገው የመንግስት ድጋፍ ክፍፍል ጊዜ በፊት ወይም በኋላ የድጋፍ ጥያቄ ለማቅረብ አይችልም፡፡
6. ቦርዱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በዚህ ደንብ መሠረት የተደነገገውን ለእለት ተእለት ተግባር ከመንግስት የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ የሚከፋፈልበትን የጊዜ ሰሌዳ ሊያሻሽል ይችላል፡፡ የተሻሻለውን የጊዜ ሰሌዳ ሁሉም የመንግስትን ድጋፍ ለማግኘት ብቁ ለሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎች እንዳያውቁት ያደርጋል፡፡

**አንቀጽ 22. <u>ለምርጫ ወይም ለዕለት ተዕለት ተግባር የተሰጠ ወይም የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ ስለሚቋረጥበት ሁኔታ</u>**

1. ለማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከመንግስት ለምርጫ ወይም ለእለት ተእለት ተግባር ማከናወኛ የሚሰጥ የፋይናንስ ድጋፍ በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀስ 1 መሠረት የፖለቲካ ፓርቲው መመዘኛውን ሲያጓድል ወይም በህግ መሰረት በቦርዱ ውሳኔ ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ እንደሁኔታው በሙሉ ወይም በከፊል ይቋረጣል፡፡
2. በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 45 ንዑስ አንቀጽ 3(ለ) እና (ሐ) መሠረት ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ፡-

ሀ/ መመዘኛው ከተጓደለበት ቀን ጀምሮ የተሰጠውን የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ መጠቀም አይችልም፡፡

ለ/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2/ሀ/ መሠረት መመዘኛው ያጓደለ የፖለቲካ ፓርቲ የፋይናንስ ድጋፉን በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ተመላሽ ያደርጋል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## ስለፖለቲካ ፓርቲ የሂሳብ አያያዝ እና ሪፖርት አቀራረብ

### አንቀጽ 23. ስለሂሳብ አያያዝ

1. በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) መሠረት ማንኛውም ለምርጫ ወይም ለዕለት ተዕለት ተግባር ከመንግስት ድጋፍ ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ የተሰጠውን ድጋፍ እንደሁኔታው፡-

   ሀ/ በተለየ የሂሳብ ወይመ የንብረት መዝገብ ለይቶ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

   ለ/ የወሰደውን የገንዘብ ድጋፍ በተለየ የባንክ ሂሳብ ማስቀመጥ ይኖርበታል፡፡

2. ማንኛውም ለምርጫ ወይም ለዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ ከመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ የተሰጠውን የፋይናንስ ድጋፍ ከታለመለት ህጋዊ ዓላማ እና ተግባር ውጪ ወጪ ማድረግ የለበትም፡፡

3. ለፖለቲካ ፓርቲው የተሰጠው ድጋፍ ገንዘብ በሆነ ጊዜ፤ በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 48 ንዑስ አንቀጽ 1(ሐ) እና (መ) መሠረት፡-

   ሀ/ ያወጣውን ወጪ በየወጪ አርዕስቱ ዘርዝሮ መያዝ አለበት፡፡

   ለ/ በፋይናንስ ህግ መሠረት በበጀት ዓመቱ የተሰጠውን የገንዘብ መጠን እና ገንዘቡን ለምን እንዳዋለው በምዝገባ አዋጁ መሠረት በኦዲተር ኦዲት ማስደረግ አለበት፡፡

### አንቀጽ 24. ሪፖርት ስለማቅረብ

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ 4 መሠረት የሚያወጣቸውን ወጪዎች ለታለመለት ሕጋዊ አላማና ተግባር ማዋሉን ለቦርዱ የማስረዳት ኃላፊነት አለበት፡፡

2. ማንኛውም የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ ያገኘ የፖለቲካ ፓርቲ፡-

   ሀ/ ለዕለት ተዕለት ተግባር ማከናወኛ የተሰጠ የፋይናንስ ድጋፍ በሆነ ጊዜ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በ3 ወር ጊዜ ውስጥ በምዝገባ አዋጁ መሠረት በኦዲተር የተረጋገጠ የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

   ለ/ ለምርጫ ተግባር የተሰጠ የፋይናንስ ድጋፍ በሆነ ጊዜ ድጋፉ የተመደበለት የምርጫ ተግባር ተጠናቆ የምርጫ ውጤት ይፋ ከተደረገበት ዕለት ጀምሮ

ባሉት 3 ወራት ጊዜ ውስጥ በኦዲተር የተረጋገጠ የመንግስት ድጋፍ አጠቃቀም ሪፖርት ለቦርዱ ማቅረብ አለበት፡፡

3. በምዝገባ አዋጁ ከአንቀጽ 54 እስከ አንቀጽ 56 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር በዚህ ደንብ መሠረት ለፖለቲካ ፓርቲ የተሰጠን ድጋፍ አስመልክቶ የመረመረውን ሂሳብና ንብረት ከህግ ውጪ ወጪ ያደረገ ወይም በስራ ላይ ያላዋለ መሆኑን ከኦዲት ግኝቱ ከተገነዘበ ለፓርቲው በሚያቀርበው ኦዲት ሪፖርት ውስጥ ይህንኑ አስተያየት ማካተት አለበት፡፡

4. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚያቀርበው ሪፖርት የፓርቲውን ኦዲተር ሪፖርት አንድ የተረጋገጠ ቅጂ እና አስፈላጊውን ማብራሪያ በማካተት ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 25** <u>**ስለፌዴራል ዋና ኦዲተር ኃላፊነት**</u>

1. የፌዴራል ዋና ኦዲተር ከመንግስት ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተሰጠን ማንኛውንም የፋይናንስ ድጋፍ አጠቃቀም በተመለከተ በራሱ ተነሳሽነት ወይም አግባብ ባለው አካል እንደሁኔታው ሲታዘዝ ወይም ሲጠየቅ በማንኛውም ጊዜ ለመመርመር ይችላል፡፡

2. የፌዴራል ዋና ኦዲተር በዚህ አንቀጽ መሠረት የመረመረውን የመንግስት የፋይናንስ ድጋፍ አጠቃቀም ሪፖርት ከአስፈላጊው መግለጫ ጋር ለቦርዱ ያቀርባል፡፡

## <u>ምዕራፍ ስድስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

**አንቀጽ 26.** <u>**ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስለሚቀርብ የሂሳብ ሪፖርት**</u>

1. ቦርዱ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የተደረገውን ድጋፍ አስመልክቶ የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአጭር ጊዜ ውስጥ ሪፖርቱን ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ማቅረብ አለበት፡፡ ይህ ሪፖርት፤

   ሀ/ በበጀት ዓመቱ ለፓርቲዎች ድጋፍ እንዲውል በመንግሥት የተመደበውንና ከሌላ ምንጭ የተገኘውን ጠቅላላ መጠን፣

   ለ/ በበጀት ዓመቱ ለእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ የተመደበውን የድጋፍ መጠን፣

   ሐ/ ህግ በሚፈቅደው መሠረት በእያንዳንዱ የፖለቲካ ፓርቲ በበጀት ዓመቱ ወጪ የተደረገ የገንዘብ መጠን፣

   መ/ በበጀት ዓመቱ የታየውን የሂሳብ ሚዛን ያካተተ መሆን አለበት፡፡

2. ቦርዱ የሂሳብ ሪፖርቱን፣ መዝገቡን እና መግለጫውን ለዋናው ኦዲተር መላክ አለበት፡፡

3. የሂሣብ ኦዲተር የሂሳብ ሪፖርት በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ሪፖርቱን ከዋናው ኦዲተር የሂሣብ መግለጫ ጋር በማያያዝ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላክ አለበት፡፡

**አንቀጽ 27. ስለተጠያቂነት**

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር የምዝገባ አዋጁን ወይም የዚህን ደንብ ድንጋጌ በአግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ይጠበቅበታል፡፡ በአግባቡ ተግባራዊ ካላደረገ በምዝገባ አዋጁ፣ በዚህ ደንብ ወይም በሌላ አግባብ ባለው ህግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 28. ስለ ቅጣት**

1. ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ከመንግስት የሚሰጠውን የፋይናንስ ድጋፍ ከታለመለት ህጋዊ አላማና ተግባር ውጪ ካዋለ ወይም በወቅቱ ሪፖርት ካላቀረበ ወይም የሀሰት የሂሳብ ሰነድ ያቀረበ እንደሆነ ወይም ከሚሰጠው ድጋፍ ጋር የተያያዘ ግዴታውን ያልተወጣ እንደሆነ በምዝገባ አዋጁ አንቀጽ 49 መሠረት፡-

   ሀ/ የሚሰጠው የፋይናንስ ድጋፍ እንዲቀነስ ወይም እንዲቋረጥ፣

   ለ/ የፖለቲካ ፓርቲው በወንጀል ህግ መሠረት በገንዘብ እንዲቀጣ፣ እንዲታገድ ወይም እንዲፈርስ፣

   ሐ/ የፖለቲካ ፓርቲው ከምዝገባ እንዲሰረዝ፣ ወይም

   መ/ የፖለቲካ ፓርቲው ኃላፊ ወይም ኃላፊዎች በገንዘብ ወይም በእስር እንዲቀጡ ይደረጋል፡፡

2. ከላይ በንዑስ አንቀጽ 1 የተደነገጉት ቅጣቶች እንደሁኔታው በተደራራቢነት ወይም ተጣምረው ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡

3. ቦርዱ በፖለቲካ ፓርቲ ያለአግባብ የወጣን ወጪ ክስ በመመስረት ወይም በማቻቻል ሊያስመልስ ይችላል፡፡

4. ይህ ደንብ በስራ ላይ እንዳይውል ያወከ ወይም ድንጋጌዎቹን የጣሰ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ህግ መሠረት ይቀጣል፡፡

**አንቀጽ 29. የመተባበር ግዴታ**

የፖለቲካ ፓርቲ፣ የፖለቲካ ፓርቲ ኦዲተር ወይም ዋና ኦዲተር ወይም ቦርዱ እንደሁኔታው በዚህ ደንብ ወይም በሌላ ህግ የተሰጠ ኃላፊነታቸውን በሚወጡበት ወይም ተግባራዊ በሚያደርጉበት ጊዜ ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

**አንቀጽ 30. <u>የተሻሩ ደንቦች ወይም አሰራሮች</u>**

ማንኛውም ደንብ ወይም አሠራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት የለውም፡፡

**አንቀጽ 31. <u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ ደንብ በቦርዱ ከፀደቀበት ከሐምሌ 13 ቀን 2001 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**መርጋ በቃና /ፕሮፌሰር/**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ**

**ሰብሳቢ**

<u>የኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ ደንብ ቁጥር 6/2002</u>

<u>የመገናኛ ብዙሃን እና የጋዜጠኞች የምጫ አመዘጋገብ</u>

<u>የሥነ - ምግባር ደንብ</u>

ቀጣዩን ምርጫ ተቀባይነት ያለው ግልጽ፣ነጻ፣ፍትሃዊ፣ሰላማዊና ዲሞክራሲያዊ እንዲሆን ለማስቻል በምርጫ ወቀት የመገናኛ ብዙሃን ጋዜጠኞች የሚመሩበት ዝርዝር የሥነ-ምግባር ደንብ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የመገናኛ ብዙሃን ከምርጫ አስፈጻሚዎች የሚሰጡ ምርጫ ነክ መልዕክቶች ሕዝቡ እንዲያውቀው በማድረግ ረገድ ያላቸውን ከፍተኛ አስተዋፅዖ በመረዳት፤

በምርጫው ሂደት የመገናኛ ብዙሃን ብዙሃንን ተግባራት አስመልቶ ሚዲያዎች፣የፖለለቲካ ፓርቲዎች ዕጩ ተወዳዳሪዎች፣ የምርጫ አስፈጻሚ አካላት የሚመሩበት  አንድ የጋራ የሥነ-ምግባር ደንብ በማውጣት ሁሉም አካላት በደንቡ መሠረት አንዱ የሌላው መብትና ነጻነት አክብረው የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት በማስፈለጉ፣

የመገናኛ ብዙሃን ሕዝቡ ስለ ምርጫ ስርአቱ፣ ስለ ዕጩዎች ማንነትና ስላቀረቡዋቸው ፖለቲካዎች ፕሮግራም በቂ መረጃና እውቀት እንዲይዝ በድምጽ መስጫ ካርድ አማካይነት የሚሰጠው ውሳኔ መረጃና እውቀትን መሠረት ያደረገ እንዲሆን በማገዝ የሚበረክቱትን አስተጽኦ በመረዳት፣

መገናኛ ብዙሃን በዴሞክራሲያዊ የምርጫ ሂደት ውስጥ መራጮች በማበረታታት፣ ለመራጮች ውሣኔ የሚያግዙ የተሟሉ መረጃዎች ማቅረብ እንዲችሉና፣ከመንግስት ከፖሊቲካ ፓርቲዎች እና ከማንኛውም እጩ ተወዳዳሪ ራሳቸውን ነጻና ገለልግተኛ አድርገው በመንቀሳቀስ ፍታዊ ሚዛናዊና ትክክለኛ ሪፖርት ዘገባ ማቅረብ እንዲችሉ፣

የመገኛኛ ብዙሃን ወይም ጋዜጠኞች የዴሚክራያዊ ስርአት ግንባታ አካል በሆነው የምርጫ ሂደት ውስጥ የሚጠበቅባቸውን ሃላፊነት ሙያዊ ሥነ ምግባርን በተከተለ አኳኋን  በአግባቡ ለመወጣት የሚያስችላቸው አሰራር መዘርጋት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

ለጋራ መግባባት ከባለድርሻ አካላት ጋር በተደረጉ ውይይቶችና ምክክሮች የጋራ መግባባት ላይ የተደረሰባቸውን ጉዳዮች መሠረት በማድረግ የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ በተሻሻለው የምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 532/199 ዓም አንቀጽ 59(4) .9(4) እና 110 መሠረት ይህን የሥነ ምግባር ደንብ አውጥቷል፡፡

**አንቀጽ 1. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ የምርጫ አዘጋገብ ስነምግባር ደንብ ቁጥር 6/2002 ዓ/ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

**አንቀጽ 2 ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትረጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ ውስጥ፡-

1. ‹‹መገናኛ ብዙሃን›› ማለት በየጊዜው የሚወጡ ህትመቶችንና ብሮድካስቶችን /የኤሌክትሮኒክል ሚዲያን/ የሚያካትት ሥራ ነው፡፡
2. ‹‹ምርጫ ህግ›› ማለት የተሸሻለው የኢትዮጵያ የምርጫ ህግ አዋጅ ቁጥር 532/1999 ነው፡፡
3. ‹‹ቦርድ ማለት በምርጫ ሕጉ የተቋቋመው የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ነው፡፡
4. ‹‹ምርጫ ነክ መልዕክት›› ማለት ለምርጫ የሚወዳደር ፓርቲ ድምጽ ሰጪዎችን ለማግባባት የሚያቀርበው የምረጡኝ መልዕክቶች እና በተወዳዳሪዎች የሚያቀርበው የምረጡኝ መልዕክቶች እና በተወዳዳሪዎች የሚቀርብ ፣ ማንኛውም ትችትና አስተያየት ነው፡፡
5. ‹‹የፖለቲካ ማስታወቂያ ›› ማለት ለምርጫ ውድድር የተመዘገበ የፖለቲካ ፓርቲ ገንዘብ በመክፈል ወይም ለመክፈል ቃል በመግባት በሬዲዮ ወይም በቴሌቭዥን ወይም በጋዜጣ የሚነገረው ማስታወቂያ ነው፡፡
6. ‹‹የፖለቲካ ፓርቲ ››ወይም የፖለቲካ ድርጅት ማለት ከህብረተሰብ የራሱን የፖለቲካ እምነትና ዓላማ የሚያንጸባርቅበት ፕሮግራም በማውጣት በሀገር አቀፍ ወይም በክልል የፖለቲካ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ በዴሞክራዊያዊ ስርዓት የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ በህግ ተመዝግቦ የሚንቀሳቀስ ማህበራዊ ተቋም ነው፡፡
7. ‹‹የምርጫ ወቅት›› ማለት ቦርዱ የምርጫ የጊዜ ሰሌዳ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ የመጨረሻ የምርጫ ውጤት በይፋ በቦርድ እስከሚገለጽበት ያለው ጊዜ ነው፡፡
8. ‹‹የምርጫ ዜና ወይም የወቅታዊ ጉዳዮች ዘገባ›› ማለት አገራዊ ወይም ዓለም አቀፋዊ ይዘት ያላቸው ፖለቲካዊ ፣ማህበራዊ ወይም ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ጋር የተያያዙ ምርጫ ነክ ሁነቶች ላይ የሚያተኩር ወይም በእነዚህ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ የሚቀርቡ ትንታኔዎችን ፣አስተያየቶችን የሚያካትት ነው፡፡
9. ‹‹ ሰው›› ማለት ማንኛው የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሠጠው አካል ነው፡፡

**አንቀጽ 3 ዓላማ**

ይህ የስነ ምግባር ደንብ መገናኛ ብዙኃን ከፓርቲዎችና እጩ ተወዳዳሪዎች የሚተላለፉ ፖቲካዊ መልእክቶችን እና ከምርጫ አስፈጻሚ አካላት የሚወጡ መልእክቶችን ለህብረተሰብ የሚያደርሱበትን እንዲሁም የምርጫውን አጠቃላይ ሂደት የሚመለከቱ ነጻ እና ገለልተኛ ግምገማዎችና አስተያየቶችን ማቅረብ የሚችሉበትን ሁኔታ የማመቻቸት አላማ አለው፡፡

**አንቀጽ 4 የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ የስነ ምግባር ደንብ ሀገሪቱ ምርጫን አስመልክቶ ዜና ዘገባ ሪፖርት ወይም መረጃ በሚያቀርቡ ፣ በሚያስተላለፉ ወይም በሚያሰራጩ ጋዜጠኞች ወይም የመገናኛ ብዙሃን ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

**አንቀጽ 5 ህግን ስለማክበር**

ማናቸውም የመገናኛ ብዙሃን ወይም ጋዜጠኛ ሕገ መንግስቱን እና ሌሎች የሀገሪቱን ሕጎች ማክበር አለበት፡፡

**አንቀጽ 6 የጋዜጠኞች ኃላፊነት**

ማንኛውም ጋዜጠኛ፡-

1. ትክክለኛና ከአድልዎ የፀዳ ዜናና ዘገባ ማቅረብ አለበት፡፡
2. ምንጭ ያላቸው ስለመሆናቸው እርግጠኛ በሆነባቸው ፍሬ ነገሮች ላይ ብቻ የተመሰረቱ ዜናና ዘገባዎችን ማቅረብ አለበት፡፡
3. ለዘገባው አስፈላጊ ወይምጠቃሚ የሆኑ ፍሬ ነገሮችን ማስቀረት ወይም ማፈን የለበትም፡፡
4. በእምነት የተሰጠ መረጃን ሚስጢራዊነት የመጠበቅ ሙያዊ ግዴታ አለበት፡፡
5. የዘገባዎችን ሚዛናዊነት መጠበቅ አለበት፡፡ በእጩ ተወዳዳሪዎች መሀከል መወቃቀስና መወነጃጀል ሲከሰት ጋዜጠኛው በተቻለው ሁሉ የሁለቱንም ወገኖች አስተያየት ያካተተ ዘገባ ማስተላለፍ አለበት፡፡
6. ጎጂ ስህተት እንዳለበት የታወቀ ማንኛውምን የታተመ መረጃን በተቻለ ፍጥነት የማረም ወይም የማስተካከል ሃላፊነት አለበት፡፡
7. በሚቻለው ሁሉ የምርጫ ተወዳዳሪዎችንም ሆነ የፖለቲካ ፓርቲዎችን አስተያየት በሌሎች ወገኖች ብለዋል ተብሎ እንደተገለጸው ሳይሆን በቀጥታና ራሳቸው የተናገሩትን ቃል በቃል ማስተላለፍ አለበት፡፡
8. ዘርን፣ ጾታን፣ የፍትወት ዝንባሌንና ሀይማኖትን ፖለቲካዊ ወይም ሌላ ማንኛውም አይነት አመለካከትና ብሄራዊ ወይም ማህበራዊ አወጣጥን ጨምሮ በሌላ ማኛውም

አቋም ላይ የተመሠረት እድልዎን ወይም አመጽን የሚያራግቡ ስሜታዊ አገላለጾችን መጠቀም የለበትም፡፡

9. አድልዎን ልዩነትን ወይም አመጽን የሚቀሰቅሱ ወገኖች አመለካከት ሲዘግብ ይህ ምግባር ለማጋለጥ በሚስችል አግባብ ማቅረብና የአስተያየቱ ወይም የቅስቀሳው ኢላማ የሆኑ ወገኖችን አስተያየትም ማካተት ይኖርበታል፡፡
10. ከማንኛውም ሊፓርቲ ፣ እጩ ተወዳዳሪም ሆነ ግለሰብ ማኛውምንም አይነት መደለያ ወይ መግባቢያ መቀበል የለበትም፡፡
11. የዘገባውን ይዘት በሚመለከት ለማንኛውም ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ ቃል መግባት የለበትም፡፡
12. የህዝብ አስተያየት ዳሰሳ ወይም ጥናት ግኝቶችን በሚዘግበበት ጊዜ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት፡፡ የሚያስተላልፈው ዘገባም በተቻለ መጠን፡-
   ሀ/ ጥናቱን ማን እንዳሰጠናውና በማን እንደተከናወነ ፣
   ለ/ ምን ያህል ሰዎች ቃለ መጠይቅ እንደተደረገላቸው የት እና እንዴት ቃለ መጠይቁን እንደሰጡ፣ እንዲሁም በግኝቱ ላይ ሊከሰት ይችላል ተብሎ የሚገመተውን ስህተት መጠን ፣
   ሐ/ የቀረቡትን ጥያቄዎች ቃል በቃል የሚሳዩ መረጃዎችን ያካተቱ መሆኑ ይኖርባቸዋል፡፡
13. የሚከተሉትን ድርጊቶች ግዙፍ የሙያ ጥፋቶች መሆናቸውን መገንዘብ ይኖርበታል፡፡
   ሀ/ የሌላውን የሥራ ውጤት እንደራስ አድርጎ ማቅረብ፣
   ለ/ በትንኮል የሆነውን እንዳልሆነ አዛብቶ ማቅረብ፣
   ሐ/ አሉባልታ ፣ ዘለፋ ፣ በሀሰት ስም ማጥፋት የሀሰት ውንጀላ፣
   መ/ ማንኛንም አይነት መደለያ ወይም ጉቦ መቀበል፣

**አንቀጽ 7 የመገኛኛ ብዙሃን ኃላፊነት**

1. ማንኛውም የመገናኛ ብዙሃን ፤ የፍሬ ነገር ዘገባን እና አስተያየትን በግልጽ ለይቶ ማስቀመጥ አለበት የዜና ዘገባ ጋዜጠኛው እውንታውን በሃቅ የተገነዘበበትን ሁኔታ ማንጸባረቅ አለበት፡፡ አስተያየት የሀትመቱን ኤዲቶሪያል አቋም ሊያንጸባርቅ ይችላል፡፡
2. የህዝብ መገናኛ ብዙሃን በርእስ አንቀጾቻቸው ላይ ማንኛውንም የፖለቲካ ፓርቲ የሚደግፍ ወይም የሚቃወም ሃሳብ ወይም አስተያየት ማቅረብ የለባቸውም፡፡

3. መገናኛ ብዙሃን ሚዛናዊና ገለልተኛ የምርጫ ነክ ዘገባዎችን የማቅረብ ግዴታ ያለባቸው ሲሆን ለምርጫ ውድድርና የአየር ሰአት አገልግሎት ወይም አምድ ሲያቀርቡም በፖለቲካ ፓሪቲዎች ወይም በእጩ ተወዳዳሪዎች መሃል አድልዎ ወይም ልዩነት ማድረግ የለባቸውም፡፡

4. መገናኛ ብዝሃን ተቋማት የፖለቲካ ማስታወቂያዎችን በክፍያ ሊያስተናግዱ ከፈለጉ ሁሉንም ፓርቲዎች ያለአድልዎ ማገልገልና ለሁሉም እኩል በሆነ ክፍያ መሆን አለበት፡፡

5. የመገናኛ ብዙኃን ተቋማት የሚተላለፉ ዜናዎችን ቃለ መጠይቆች እና ወቅታዊ ዘገባዎች አንድን ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪዎች ከመደገፍ ወይም ከመጥላት የሚነሱ መሆን አይኖርባቸውም፡፡

6. የመገናኛ ብዙሃን ተቋማት ለሁሉም የፖለቲካ-ፓሪቲዎች ፤እና ተወዳዳሪዎች እና መድረኮቻቸው ፍትሃዊ ቋሚ የዘገባ ሽፋን መስጠት አለባቸው፡፡

7. መገናኛ ብዙሃን ተቋማት መራጮች ሀሳባቸውንና አስተያየታቸውን እንዲሰጡ ማበረታታትና እድሉንም መስጠት አለባቸው፡፡

8. መገናኛ ብዙሃን ስለዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደርና የህግ የበላይነት ህብረተሰቡን ማስተማር ይኖርባቸዋል፡፡

9. በታተመው ወይም በተሰራጨው ዘገባ ስሙ መጥፋቱን ወይም ጉዳት የደረሰበት መሆኑን አስመልክቶ ምክንያታዊ ቅሬታ ካቀረበ በዚያው ሚዲያ አስመልክቶ ምክንያታዊ ቅሬታ ካቀረበ በዚያው ሚዲያ መልስ የመስጠት ወይም ማስተካከያ የማውጣት መብቱ በብድሮካስተሩ ወይም በአሳታሚው መከበር ይኖርበታል የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቱም በተቻለ ፍጥነት የቀረበለትን አስተያየት ብሮድካስት የማድረግም ሆነ የማተም ግዴታ አለበት የማድረግም ሆነ የማተም ግዴታ አለበት፡፡

10. መደበኛ የመንግስት ስራ ክንዋኔዎችን ሳይሆን ፖለቲካዊ ውዝግብ ያስነሱ ጉዳዮችን በሚመለከት በርዕስ መንግስቱ፣ በሚኒስትሮች ወይም በፓርላማ አካላት የሚዘጋ የፕሬስ መግለጫዎች ወይም ለህዝብ የሚደረጉ ንግግሮች የዜና ሽፋን አሰጣጥ ምላሽ የመስጠት መብትን ወይም የእኩል ጊዜ አጠቃቀም ህግ መሠረት በማድረግ መከናወን ይኖርበታል፡፡ ይህ ግዴታ በተለይ መግለጫውን ወይም ማብራሪያውን የሚሰጠው ባስልጣን የምርጫ ተወዳዳሪ በሚሆንበት ጊዜ በጥብቅ ተፈጻሚ መሆን ይኖርበታል፡፡

11.የህዝብ ሚዲያ መራጩን ህብረተሰብ ለማስተማር የተዘጋጁ ማስተማሪያዎችን ብሮድካስት የማድረግ ወይም አትሞ የማሰራጨት ግዴታ አለባቸው፡፡

12.መራጩን ለማስተማር የሚወጣ ማቴሬቲያል የተሟላና ትክክኛ መሆን ይርበታል፡፡ ለመራጩ ህዝብ ድምጽ መስጠትን ጥቅም ጨምሮ የድምጽ አሰጣጡ ሁኔታ፣ መቸ እና የተመራጮች ምዝገባ እንደሚደረግ ምዝገባውንም እንዴትና የት ማረጋገጥ እንደሚቻል፤ እንዲሁም ድምጽ መቸና እንዴት እንደሚሰጥ፣ የድምጽ አሰጣጡን ሚስጥራዊነትና ድምጽ የመስጠት ጠቀሜታን ውድድር የሚደረግባቸው የስልጣን አካላትና ተግባራቶቻቸውን በመሳሰሉ ጉዳዮች ላይ የተሟላ መረጃ የሚሰጥ መሆን ይኖርበታል፡፡

13.የመራጮች ትህምርት አናሳና በታሪክ አጋጣሚ የተገለገሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ቋንቋ በተዘጋጀ ፕሮግራሞች ያካተተና እንዲሁም በባህላዊ ተጽእኖ ምክንያት ከፖለቲካ ተሳትፎ የተገለሉ ሴቶችንና አካል ጉዳተኞችን ታሳቢ ያደረገ መሆን ይኖርበታል፡፡

14.የሚዲያ ተቋማት የሚያስተላልፏቸው ዜናዎችና ፕሮግራሞች የስነምግባር መመሪያ ደንቡን መስፈርቶች የጠበቁ መሆናቸውን ዘወትር መከታተል ይኖርባቸዋል፡፡

## አንቀጽ 8 የፖለቲካ ፓርቲዎች

1. የፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ እና ተወዳዳሪዎች የሚዲያ ተቋማትን ነጻነት ማክበር ይሆርባቸዋል፡፡

   ፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ እና ተወዳዳሪዎች የጋዜጠኞችን ሥራ የሚያውክ ወይም የሚያሰናክል ተግባር መፈጸም የለባቸውም፡፡
2. የፖለቲካ ፓራቲዎችም ሆኑ እና ተወዳዳሪዎች የጋዤጠኞችን ስራ የሚያውክ ወይም የሚያሰናክል ተግባር መፊጽም የለባቸውም፡፡
3. በስልጣን ላይ ያለው ፓርቲም ሆነ እና ተወዳዳሪዎች የጋዜጠኞች ስልጠናቸውን ተጠቅመው የተለየ የሚዲያ የአየር ሰዓት ለማግኘት ሙከራ ማድረግ የለባቸውም፡፡ ይህ አንቀጽ በሁሉም መገናኛ ብዙሃን ላይ ተፈጻሚ የሚሆን ሲሆን በተለይም ደጋሞ የህዝብ መገናኛ ብዙሃኑ በስልጣን ላይ ባለው የህግ አስፈጻሚ አካል ቀጥተኛ ቁጥጥር ስር የሚገኙ ከሆነ በነዚህ ተቋማት ላይ የበለጠ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡
4. ፓርቲዎችም ሆኑ እና ተወዳዳሪዎች ለጋዜጠኞች ወይም ለሚዲያ ተቋማት ጉቦ ወይም መደለያ በመስጠት የተለየ ተጽእኖ በማድረግ በምርጫ ዘመቻ እንቅስቃሴ ዝግጅቶች ወይም ሁነቶች ላይ እንዲገኙ ወይም ስለነሱ አወንታዊ ዘገባ

እንዲያቀርቡላቸው ወይም በሌላ ፓርቲ ወይም እጩ ተወዳዳሪ ላይ አሉታዊ ዘገባ እንዲያቀርቡ ማበረታታት ወይም ማግባባት የለባቸውም፡፡

5. የፖለቲካ ፓርቲዎችና እጩዎች ያለአግባብ የሌሎች ፓርቲዎችን ወይም እጩ ተወዳዳሪዎችን አቋም ያለ አግባብ አዛብተው ማቅረብ ወይም ሌሎች ፓርቲዎችን ወይም እጩ ተወዳዳሪዎችን የሚመለከቱ ማንኛቸውም አይነት የተሳሳቱ የፍሬ ነገር መረጃዎችን መረጃ ማቅረብ የለባቸውም፡፡
6. ፖለቲካ ፓርቲዎችም ሆኑ እና ተወዳዳሪዎ ግጭትን የሚቀሰቅሱና የሌላውን መልካም ስምና ዝና የሚጎድፉ ወይም የሚያዋርዱ ቃላቶችና አነጋገሮችን ከመጠቀም መቆጠብ ይኖርባቸዋል፡፡
7. የፓርቲ አመራሮች በዚህ የስነ ምግባር ደንብ ውስጥ የሰፈሩት የነጻ ክርክርና የመቻቻል እሴቶች ለምርጫ ዘመቻ ሠራተኞቻቸው እንዲያውቁዋቸው መደረጉንና ማብራሪያም ያገኑ መሆናቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለባቸው፡፡

**የምርጫ ማስፈጸሚያ አዋጆች፤ ደምቦችና መመሪያዎች ጥራዝ**

ፓርቲዎች በነሱ ስም የቅስቀሳ ስራ ለማከናወኑ ወገኖች ንግግርና ድርጊት ሙሉ ሃላፊነት መውሰድ ይኖርባቸዋል፡፡

**አንቀጽ 9 የምርጫ አስፈጻሚ አካላት**

1. የምርጫ አስፈጻሚ አካላት የኤዲቶርያል ነጻነትን ጨምሮ የሚዲያ ተቋማትን ነጻነት የፖለቲካዊ ወገንተኛነትን የመግለጽ መብት ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡
2. የምርጫ አስፈጻሚዎች የፓርቲዎችንና የእጩ ተወዳዳሪዎችም ሀሳብን በነጻነት የመግለፅ መብት ማክበር ይኖርባቸዋል፡፡
3. የምርጫ አስፈጻሚ ምርጫን በግልጽና በታማኝነት ማከናወን አለባቸው፡፡
4. የምርጫ አስፈጻሚዎች የሥራ ክንዋኔአቸው ሙሉ ለሙሉ ለሚዲያ ምርመራ ግልጽ መሆኑን የማረጋገጥ ሃላፊነት አለባቸው፡፡
5. የምርጫ አስፈጻሚዎች በክፍያ የሚደረግ ማስታወቂያም ሆነ በነጻ የሚሰጥ መረጃን በተመለከተ በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ማስተላለፍ አለባቸው፡፡
6. የምርጫ አስፈጻሚዎች ህብረተሰቡ በእውቀት ላይ ተመስርቶ የመምረጥ መብቱን ተግባራዊ እንዲያደርግ ለማስቻል ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃዎችን በመገናኛ ብዙሃም አማካኝነት ማስተላለፍ አለባቸው፡፡
7. የምርጫ አስፈጻሚ አካላት የምርጫ ሂደቱን ቀናነት ለመጠበቅ እጅግ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ለምሳሌ የድምፅ ቆጠራውን ሂደት በሚመለከቱ የመገናኛ ብዙሃን የዜና ዘገባዎች ላይ ገደቦችን ሊያበጁ ይችላሉ፡፡

**አንቀጽ 10. የተሻሩ ደንቦችና መመሪያዎች**

ይንን ደንብ የሚቃረን ማንኛውም ደንብ መመሪያ እና አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**አንቀጽ 11. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በቦርዱ ከጸደቀበት ከሚያዝያ 7 ቀን 2002 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**መርጋ በቃና ( ፕሮፌሰር)**

**የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ**

**ሰብሳቢ**

## ክፍል ሶስት

## ምክር ቤቶች እና የሪፐብሊኩ ፕሬዝዳንት

### ሀ/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

### አዋጅ ቁጥር 32/1988

### የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትን የዕረፍትና የሥራ ጊዜ ለመወሰን የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገመንግሥት አንቀጽ 58 (2) የምክር ቤቱን የሥራ ጊዜ ሲደነግግ ምክር ቤቱ በሚወስነው መሠረት በመካከሉ የአንድ ወር ዕረፍት እንደሚኖረው ያስቀመጠ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዕረፍትና የሥራ ጊዜ አዋጅ ቁጥር 32/1988" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **የዕረፍት ጊዜ**

   የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የዕረፍት ጊዜ በየዓመቱ ከየካቲት 1 እስከ መጋቢት 30 እና ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ ዋዜማ ድረስ ይሆናል፡፡[12]

3. **የሥራ ጊዜ**

   የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሥራ ጊዜ በየዓመቱ ከመስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ እስከ ጥር 30 እና ከመጋቢት 1 እስከ ሰኔ 30 ድረስ ይሆናል፡፡[13]

4. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

   ይህ አዋጅ ከየካቲት 28 ቀን 1988 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 28 ቀን 1988 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

[12] በ8/9(1994) አ.263 አንቀፅ 2(1) ተሻሻለ፡፡

[13] በ8/9(1994) አ.263 አንቀፅ 2(2) ተሻሻለ፡፡

## አዋጅ ቁጥር 88/1989 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በመራጮቻቸው አመኔታ በሚያጡበት ጊዜ ስለሚወሰድ እርምጃ የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 54 ንዑስ አንቀጽ (7) ማናቸውም የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የመረጠው ሕዝብ አመኔታ ባጣ ጊዚ በሕግ መሠረት ከምክር ቤት አባልነቱ እንደሚወገድ ስለሚደነግግ፣

ይህ መሠረታዊ ዲሞክራሲያዊ መርሆ በሥራ ላይ መዋሉ አስፈላጊ በመሆኑ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በመራጮቻቸው አመኔታ በሚያጡበት ጊዜ ስለሚወሰድ እርምጃ የወጣ አዋጅ ቁጥር 88/1989" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   1. በዚህ አዋጅ ውስጥ "ተመራጭ" ማለት በኢትዮጵያ የምርጫ ቦርድ አስፈጻሚነት በተካሄደ ምርጫ አንድን የምርጫ ክልል ለመወከል የተመረጠና በምርጫ ቦርድ የምስክር ወረቀት የተሰጠው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ነው፡፡
   2. [14]፡
   3. "መራጭ" ማለት በሕጉ መሠረት አሥራ ስምንት ዓመት የሞላውና በምርጫ ክልሉ ለሁለት ዓመት[15] ወይም በላይ የኖረ ግለሰብ ነው፣
   4. "ወረዳ" ማለት የክልሉ ምክር ቤት በሚወስነው መሠረት የተከለለ የአስተዳደር እርከን ነው።

### ክፍል ሁለት

### መብቶችና ግዴታዎች

3. **መሠረታዊ መብቶች**

[14] በ13/54(1999) አ.532 በአንቀፅ 2(13) እና በአንቀፅ 20 በግልፅ ሳይነገር ተሻረ፡፡
[15] በተጨማሪም 13/54(1999) አ.532 አንቀፅ 33ን ተመልከት፡፡

1. ማንኛውም ዜጋ ሕጉ በሚፈቅደው መሠረት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተወካዩን የመምረጥ መብት አለው ።
2. ማንኛውም ዜጋ ከሌሎች መራጮች ጋር በመሆን የወከለውን ተመራጭ በየጊዜው መመርመር፡ መገምገምና መመዘን ይችላል፡፡
3. ማንኛውም ዜጋ ለወከለው ተመራጭ ሲሰጥ የነበረውን ድጋፍ የማቋረጥ ወይም የመቀጠል መብት አለው፡፡
4. ማንኛውም ተመራጭ በመራጮች የሚቀርብለትን ምስጋና፡ ተግሳጽ ግምገማ ወይም ሂስ በግልጽና በአደባባይ የማስተጋባት፡ የመቃወምና ሂስ የማድረግ መብት አለው።

4. <u>የመራጮች አመኔታ የሚለካበት ዘዴ</u>

አንድ ተመራጭ የመራጮች አመኔታ የለውም ሊባል የሚችለው፤

1. በተወከለበት የምርጫ ክልል ከሚገኙ መራጮች ከ15,000 በላይ የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የይውረድልን ጥያቄ ለምርጫ ቦርድ ሲያቀርቡ፤
2. በተወከለበት የምርጫ ክልል በሚገኙ 10 ሺህ መራጮች አሳሳቢነት የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የወረዳ ምክር ቤቶች በአብላጫ ድምጽ ተወካዩ ተመልሶ እንዲጠራ ውሳኔ ያሳለፉ እንደሆነ፤
3. የልዩ ምርጫ ክልል ተወካይን በተመለከተ የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የመራጮች አመኔታ ማጣቱ ሲረጋገጥ፤
4. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተመራጮች በሚያሳየው ሥነ ምግባር የወከለውን ሕዝብ በብቃት ሊወክል አልቻለም ብሎ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ሲወስን ይሆናል።

5. <u>የሥነ ምግባር መለኪያዎች</u>

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ተገኘነቱ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 54(4) (ሐ) ለሕሊናውም ጭምር በመሆኑ በማናቸውምረገድ የጸዳና የጠራ መሆን አለበት፡፡
2. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሕዝብን ጉዳይ በሚወያይበት ጊዜ ሀቀኛና ግልጽ የመሆን ኃላፊነት አለበት።
3. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል የሀሰት ማስረጃዎች መፍጠር፡ መትጠፍ፡ ያልተጣሩ ጉዳዮች ወደ ምክር ቤቱ መድረክ ማቅረብና መዋሸት ዋነኞቹ የሥነ ምግባር ብልሹነት መግለጫዎች ናቸው።

6. <u>በሥነ ምግባር ብልሹነት ላይ የሚወሰዱ እርምጃዎች</u>

1. ምክር ቤቱ በሚያቋቁመው ኮሚቴ አማካይነት በሥነ ምግባር ብልሹነት የተከሰሰ ተመራጭ ጉዳይ ይጣራል።
2. አጣሪ ኮሚቴው በሚሰጠው የውሳኔ ሃሳብ ምክር ቤቱ ተወያይቶ ይወስናል፡፡
3. ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ ይችላል፤

   ሀ/ የሥነ ምግባር ብልሹነት ለተገኘበት ተመራጭ ለሕዝብ ይፋ በሆነ መልኩ የማስጠንቀቂያ ተግሳጽ ሊሰጠው ይችላል፤

   ለ/ የሥነ ምግባር ብልሹነት የተገኘበት ተመራጭ ለተወሰነ ጊዜ ከምክር ቤቱ እንዲታገድ ማድረግ ይችላል፤

   ሐ/ የሥነ ምግባር ብልሹነት የተገኘበት ተመራጭ በዚህ ንዑስ አንቀጽ (ሀ) እና (ለ) የተደነገጉትን ቅጣቶች ከተቀበለ በኋላ የሥነ ምግባር ብልሹነቱ የቀጠለ እንደሆነ ምክር ቤቱ በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ከምክር ቤት አባልነቱ ሊሰርዘው ይችላል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከቱት ተከታታይ የዲስፕሊን እርምጃዎች እንደጥፋቱ ክብደት ቅደም ተከተላቸው ሳይጠበቅ ተፈጻሚ ሊደረጉ ይችላሉ፡፡

7. <u>ከምክር ቤቱ መወገድ የሚኖረው ውጤት</u>

1. አንድ ተመራጭ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 እና 6 መሠረት መቀመጫውን ሲያጣ በምርጫ ቦርድ የተሰጠው የተወካይነት መታወቂያ ሕጋዊነቱ ያከትማል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የምክር ቤት መቀመጫውን ያጣ የቀድሞ ተመራጭ በምርጫ ክልሉ መቀመጫውን ለመሙላት በሚደረገው ምርጫ ተወዳዳሪ ለመሆን ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተጠቀሰው ምርጫ የሚከናወነው የቀድሞው ተመራጭ የምክር ቤት መቀመጫውን ካጣበት ቀን ጀምሮ ከ3 ወራት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ይሆናል፡፡

8. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ 30 ቀን 1989 ዓ.ም. ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 30 ቀን 1989 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## የኢትዮጵያ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ደንብ ቁጥር 2/1991

## በየደረጃው የሚገኙ ምክር ቤቶች አባላት የመረጣቸውን ሕዝብ እመኔታ በሚያጡበት ጊዜ በአባልነት የሚወገዱበትን የአፈጻጸም ሥርዓት ለመወሰን የወጣ ደንብ

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ

1. **አውጪው ባሥልጣን**

   ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የኢትዮያ ፌደራላዊ ዲሚክራሲያዊ ሪፐብክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት በመራጮቻቸው አመኔታን በሚቀያጡበት ጊዜ ስለሚወሰድ እርምጃ በወጣው አዋጅ ቁጥር 88/1997 ንዑስ አንቀጽ(1) ፣ (2) እና (3) እንዲሁም ክልሎች ባወጧቸው አዋጆች አግበብነት ያላቸው አንቀጾች በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

2. **አጭር ርዕስ**

   ይህ ደንብ ‹‹መራጮች ላይ አመኔታ ያጡ መሆኑን የሚገልፁበትን ሥርዓት ለመወሰን የወጣ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ደንብ ቁጥር 2/1999" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

3. **ትርጓሜ**

   1. ‹‹ የወረዳ ምርጫ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ›› ማለት

      ሀ/ የምርጫ ክልሉ በሚገኝበት ወረዳ በቦርዱ የቋሚ ምርጫ አስፈጻሚነት መታወቂያ የተሰጠው የወረዳ ምርጫ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ነው፡፡

      ለ/ ከአንድ በላይ የሆኑ ወረዳዎች በአንድ የምርጫ ክልልነት በተጣመሩበት ሁኔታ የመጀመሪያ ደረጃ የይውረድልን ጥያቄ አቅራቢዎች በብዛት በሚገኙበት ወረዳ የሚገኘው የወረዳ ምርጫ ጽ/ቤት ኃላፊ ነው፡፡

   2. ‹‹ የምርጫ ክልል ›› ማለት ለምጫው አፈጻጸም ተግባር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሰየመውና ለየምክር ቤቶች የተወሰነ ብዛት ያላቸው የተመራጮች የሚወከሉበት አካባቢ ነው፡፡

   3. ‹‹ ቦርድ›› ማለት የኢትዮጵያን የምርጫ ሕግ ከኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሰት ጋር ለመጣጣም በወጣው አዋጅ ቁጥር 111/1995 አንቀጽ 3 መሠረት የተቋቋመው ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ ነው፤

   4. ‹‹ የምርጫ ጣቢያ ›› ማለት ቦርዱ ባወጣው መመሪያ መሠረት በየቀበሌው የተቋቋመ ምርጫ አስፈጻሚ አካል ነው፡፡

5. ‹‹ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ‹‹ ማለት በብረሃራዊ የምርጫ ቦርድ ደንብ ቁጥር 1/1994 አንቀጽ 48 መሠረት በምርጫ ጣቢያ ወይም በወረዳ ምርጫ ጽሕፈት ቤት ደረጃ የተቋቋመና በዚህ ደንብ አፈጻጸም ሂደት በሚነሱ አቤቱታዎች ላይ አስተዳደራዊ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን የሚኖረው ኮሚቴ ሲሆን ፣ የቦርዱ ጽሕፈት ቤት በሚወጣው መመሪያ መሠረት፣ በቀበሌ ምርጫ ጽሕፈት ቤት ደረጃ የሚቋቋመውንም አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይጨምራል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የመጀመሪያ ደረጃ የይውረድልን ጥያቄ ስለሚቀርብበት ሥርዓት

4. **የይውረድልን ጥያቄ አቀራረብ**

1. በመጀመሪያ ደረጃ አንድ መቶ (100) የሚሆኑ መራጮች የይውረድልን ጥያቄያቸውን በሚኖሩበት ወረዳ ለሚገኘው የወረዳ ምርጫ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ለማቅረብ ይችላሉ፡፡
2. በየትኛውም ደረጃ በተቋቋመ ምክር ቤቶች አባላት ላይ የይውረድልን ጥያቄ ሊያቀርቡ የሚችሉት ተመራጩ በሚወክለው የምርጫ ክልል የሚኖሩ መራጮች ብቻ ናቸው፡፡
3. የወረዳው ምርጫ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የይውረድልን ጥያቄ ማመልከቻውን የሚቀበለው የቦርዱ ጽሕፈት ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት እና ማመልከቻው በምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 111/1995 አንቀጽ 19 መሠረት የመምረጥ መብት ባላቸው ግለሰቦች የቀረበ ሲሆን ብቻ ነው፡፡
4. የወረዳው ምርጫ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) በተጠቀሰው መሠረት የተቀበለውን ማመልከቻ.

   ሀ/ ያልተሟላ ከሆነ አለመሟላቱን፣

   ለ/ የተሟላ ከሆነ መሟላቱን፣

   አረጋግጦ ከቦርዱ ጽሕፈት ቤት በሚላከው ቅጽ ላይ የራሱን እና የሁለቱን የወረዳ ምርጫ ጽሕፈት ቤት አባላት ፊርማ በማኖር ከአስራ አምስት (15) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ወደ ቦርዱ ጽሕፈት ቤት የመላክ ግዴታ አለበት፡፡
5. የቦርዱ ጽሕፈት ቤት የቀረበውን ማመልከቻ ለቦርዱ አቅርቦ ቦርዱ ተገቢውን ውሣኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡

5. **ቦርዱ**

ሀ/ የቀረበው ማመልከቻ ለይውረድልን ጥያቄው መነሻ ሊሆን አይችልም

ብሎ ውሣኔ ከሰጠ ጽሕፈት ቤቱ ይህንኑ ውሣኔ በመገናኛ ብዙሃን እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡ወይም

ለ/ ማመልከቻው ለይውረድልን ጥያቄው መነሻ ብቁ ነው ብሎ ከወሰነ ጽሕፈት ቤቱ በምርጫ ክልሉ አግባብ ያለው ብዛት ያላቸው መራጮች ይህንኑ ጥያቄያቸውን ለማቅረብ በየምርጫው ጣቢያ እየቀረቡ እንዲመዘገቡ፣

(i) ምዝገው የሚጀመርበት ቀን፣

(ii) ምዝገባው የሚጠናቀቅበትን ቀን፣

(iii) የይውረድልን ጥያቄ አቅራቢዎቹ የተመዘገቡባቸው መዛግብት ለሕዝብ ይፋ የሚሆኑባቸውን ቀናት፣

የጊዜ ሰሌዳ አዘጋጅቶ ለቦርዱ በማቅረብ ሲጸድቅ በመገናኛ ብዙሃን በይፋ ለሕዝብ ያሳውቃል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የይውረደልን ጥያቄ አቅራቢዎች አመዘጋገብ ሥርዓት

### 6. የአመዘጋገብ ሥርዓት

1. ቦርዱ በሚያወጣው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት የይውረድልን ጥያቄ አቅራቢዎችን ለመመዝገብ ምርጫ ጣቢያዎች ክፍት ሆነው ሥራቸውን ያካሂዳሉ፡፡
2. የይውረድልን ጥያቄ ለማቅረብ መመዝገብ የሚችሉት
   ሀ/ ኢትዮጵያዊ የሆኑ፣
   ለ/ በምርጫ ክልሉ ቢያንስ ሁለት ዓመት የኖሩ፣
   ሐ/ ዕድሜያቸው ከአስራ ስምንት(18) ዓመት ያላነሰ፣
   መ/ በአዕምሮ በሽታ ምክንያት ለመወሰን ያልተሳናቸው
   ሠ/ በፍርድ የተወሰነባቸው የእሥራት ቅጣት ካለ ይህንኑ የፈጸሙ፣ ግለሰቦች ናቸው፡፡
3. የይውረድልን ጣያቄ አቅራቢዎች መመዝገብ የሚችሉት የሚኖሩበት ቀበሌ በሚገኝ ምርጫ ጣቢያ በግንባር በመቅረብ ብቻ ነው፡፡
4. ማንኛውም የይውረድልን ጥያቄ አቅራቢ አንድ ምርጫ ጣቢያ ላይ ብቻ አንድ ጊዜ ይመዘግባል፡፡
5. ማንኛውም የይውረድልን ጥያቄ ለማቅረብ መመዝገብ የሚፈለግ ለምዝገባ በተወሰኑት ቀናት ውስጥ ማንነቱን የሚገልጽ መረጃ በማቅረብ በምርጫ ጣቢያው ተገኝቶ ይመዘገበል፡፡

6. የተመዝጋቢውን ማንነት የሚገልጽ ዝርዝር መረጃ በምርጫ ጣቢያው ውስጥ በሚገኘው የይውረድልን ጥያቄ አቅራቢዎች መዝገብ ውስጥ ይሰፍራል፡፡
7. ቀጥሎም ተመዝጋቢው የጽሑፍ ፊርማውን ወይም የቀኝ አውራ ጣት አሻራውን በይውረድልን ጥያቄ አቅራቢዎች መዝገብ
ውስጥ ከራሱ ስም አንጻር በሚገኘው ክፍት ቦታ ላይ እንዲሰፍር ያደርጋል፡፡

7. <u>ስለሕዝብ ታዛቢዎች እና ወኪሎች</u>

1. የምርጫ ጣቢያው ኃላፊው ቀደም ሲል በተከናወኑ ምርጫዎች በምርጫ ጣቢያው የሕዝብ ታዛቢዎች የነበሩትን ግልሰቦች የይውረድልን ጥያቄ አቅራቢዎች ምዝገባ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ የምዝገባውን ሂደት በምርጫ ጣቢያው በመገኘት እንዲታዘቡ ያደርጋል፡፡
2. የይውረድን ጥያቄ የቀረበበት ተመራጭ ቦርዱ ባወጣው የጊዜ ሠሌዳ መሠረት ፣ በየምረጫ ጣቢያው የይውረድልን ጥያቄ አቅራቢያዎች ምዝገባ ተጀምሮ እስከሚጠናቀቅበት ጊዜ ድረስ እንዲሁም እንደ አግባብነቱ በምርጫ ጣቢያ፣ በቀበሌ ወይም በወረዳ ምርጫ ጽ/ቤት የተመዝጋቢዎች ብዛት በሚጠቃለልበት ጊዜ ወኪሎቹን የመመደብ መብት አለው፡፡

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>በይውረድልን ጥያቄ አቅራቢያዎች አመዘጋገብ ላይ ስለሚቀርብ አቤቱታ እና የውሣኔ አሰጣጥ</u>

8. <u>ስለ አቤቱታ አቀራረብ</u>

1. ቅሬታ አቅራቢዎች በዚህ ደንብ አንቀጽ (5) ንዑስ አንቀጽ (2) በተጠቀሱት ምክንያቶች ብቻ በማንኛውም ጊዜ በተመዝጋቢዎች ላይ አቤቱታቸውን ለምርጫ ጣቢያው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
2. ቅሬታ አቅራቢዎች በዚህ አንቀጽ (1) ከተጠቀሰው ውጪ የአመዘጋገብ ሂደቱንም ሆነ የተመዝጋቢዎች ብዛት ማጠቃለልን አስመልክቶ አቤቱታቸውን እንደ አግባብነቱ ለምርጫ ጣቢያዎች ለቀበሌ ወይም ለወረዳ አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ማቅረብ ይችላሉ፡፡
3. የምርጫ ጣቢያው ወይም የቀበሌው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይ (2) መሠረት ለቀረበለት አቤቱታ በሃያ አራት (24) ሰዓት ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

4. የምርጫ ጣቢያው ወይም የቀበሌው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ወይም (2) መሠረት ለቀረበለት አቤቱታ በሃያ አራት (24) ሰዓት ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ካልሰጠ በአቤቱታ አቅራቢው ጥያቄ እንደተስማማ ይቆጠራል፡፡
5. የምርጫ ጣቢያው ወይም የቀበሌው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ በሰጠ በአርባ ስምንት (48) ሰዓት ጊዜ ውስጥ እንደ አግባብነቱ ለቀበሌው ወይም ለወረዳው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኝ ካልቀረበ የይግባኙ መብት በይርጋ የታገደ ይሆናል፡፡
6. የቀበሌው ወይም የወረዳው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ይግባኙ በቀረበለት በሃያ አራት (24) ሰዓት ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ካልሰጠ እንደ አግባብነቱ የምርጫ ጣቢያው ወይም የቀበሌው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ የሰጠውን ውሳኔ እንዳፀናው ይቆጠራል፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## የይውረድልን ጥያቄ ስለሚረጋገጥበት ሥርዓት

9. ስለማረጋገጥ

1. የወረዳ ምርጫ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ የቦርድ ጽሕፈት ቤት በሚያወጣው መመሪያ መሠረት፡-

 ሀ/ የይውረድልን ጥያቄው በምርጫ ሕግ አዋጅ ቁጥር 111/197 አንቀጽ 19 መሠረት የመምረጥ መብት ባላቸው መራጮች የቀረበ መሆኑን፣

 ለ/ የይውረድልን ጥያቄውን ያቀረቡት መራጮች ብዛት አግባብ ባለው መጠን መሠረት መሟላቱን ወይም አለሟሟላቱን ፣

 ሐ/ የይውረድልን ጥያቄው ያቀረበው በልዩ ምርጫ ክልል ተወካይ ላይ ከሆነ ደግሞ የቅሬታ አቅራቢዎች ብዛት በየጊዜው ቦርዱ በሚወስነው መጠን መሠረት መሆኑን ወይም አለመሆኑን በማረጋገጥ ከቦርዱ ጽሕፈት ቤት በሚላከው የሪፖርት ማስተላለፊያ ቅጽ ላይ የራሱን እና የሁለቱን የወረዳ ምርጫ ጽሕፈት ቤትአባላት ፊርማ በማኖር ቦርዱ ከወሰነው የምዝገባ ማጠናቀቂያ ዕለት ጀምሮ ከአስራ አምስት (15) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት ይልካል፡፡

2. የወረዳው ምርጫ ጽ/ቤት ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1) ከተጠቀሰው ሪፖርት ጋር በማያያዝ የይውረድልን ጥያቄ አቅራቢዎችን ወይም ሌሎች የአመዘጋገብ ሂደቱንም ሆነ የተመዝጋቢዎን ብዛት ማጠቃለልን አስመልቶ የቀረቡ አቤቱታዎች ካሉ ፡-

 ሀ/ የምርጫ ጣቢያው ወይም የቀበሌው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ የሰጠ ከሆነ የውሳኔውን ግልባጭ፤

ለ/ ውሣኔ ያልሰጠ ከሆነ አቤቱታውን ግልባጭ፤

ሐ/ በይግባኝ ለመጣለት አቤቱታ የቀበሌው ወይም የወረዳው አቤቱታ ሰሚ ኮሚቴ ውሳኔ የሰጠ ከሆነ የውሳኔው ግልባጭ፤

ለቦርዱ ጽ/ቤት ይልካል፡፡

3. በዚህ ደንብ አንቀጽ 4 ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የይውረድልን ጥያቄ አቅራቢዎቹ ብዛት የወረዳ ወይም የቀበሌ ምክር ቤቶች ድጋፍ የሚፈልገው ከሆነ የወረዳው ምርጫ ጽሕፈት ቤት ኃላፊ ይኸው ድጋፍ መስጠቱን የቦርዱ ጽሕፈት ቤት በሚያጣው መመሪያ መሠረት አረጋግጦ በሪፖርት መላኪያ ቅጽ ላይ በመሙላት ለቦርዱ ጽሕፈት ቤት ይልካል፡፡

4. የቦርዱ ጽሕፈት ቤት ከወረዳው ምርጫ ጽሕፈት ቤት የቀረበለትን ሪፖርት ለቦርዱ በማቅረብ ቦርዱ ተገቢውን ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡

10.<u>ቦርዱ</u>

ሀ/ በቀረበው ሪፖርት አግባብ ያለው የይውረድልን ጥያቄ አቅራቢዎች ብዛት አልተሟላም በማለት የይውረድልን ጥያቄው ውድቅ እንዲሆን ከወሰነ የቦርዱ ጽ/ቤት ይህንኑ ውሳኔ በመገናኛ ብዙሃን በይፋ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡

ለ/ በቀረበው ሪፖርት አግባብ ያለው የይውረድልን ጥያቄው የቀረበበት ተመራጭ የመረጠውን ሕዝብ አመኔታ አጥቷል፡፡ ብሎ ከወሰነ፣ የሕዝብ አመኔታውን ባጣው ተመራጭ ምትክ በምርጫ ክልሉ የሚሟያ ምርጫ ለማካሄድ የቦርዱ ጽሕፈት ቤት የምርጫ አፈጻጸም የጊዜ ሠሌዳ አዘጋጅቶ ለቦርዱ በማቅረብ ሲጸድቅ በመገናኛ ብዙሃን በይፋ እንዲገለጽ ያደርጋል፡፡ ሆኖም የሚሟያ ምርጫው መካሄድ ያለበት ቦርዱ ተመራጩ የመረጠውን ሕዝብ አመኔታ አጥቷል ብሎ በይፋ ከወሰነበት ቀን ጀምሮ ከሦስት (3) ወራት ባልጠለጠ ጊዜ ውስጥ ነው፡፡

11.<u>ቅጣት</u>

ይህን ደንብ በሥራ ላይ እንዳይውል ያሰናከለ ወይም የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የተላለፈ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል፡፡

12.<u>ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ ከመጋቢት 14 ቀን 1999 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 2 ቀን 1999 ዓ/ም**

**ከማል በድሪ**

**የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ**

## አዋጅ ቁጥር 906/2007 ዓ.ም

## የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤትን እንደገና ለማቋቋም

## የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕገ መንግሥቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሚገባ እንዲወጣ ለማስቻል የራሱ የሆነ ጽህፈት ቤት ማቋቋም አስፈላጊነት ያለው በመሆኑ፤

በስራ ላይ የነበረው የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ምክር ቤቱ ከደረሰበት የእድገት ደረጃ በሚመጥን መልኩ መሻሻል ያለበት በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤትን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 906/2007" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፦

   1. "የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግስት አንቀፅ 53 መሠረት የተቋቋመው የፌደራሉ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፤
   2. "አፈ ጉባዔ" ማለት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈጉባዔ ነው፤
   3. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለጸው የሴትንም ይጨምራል።

3. **መቋቋም**

   1. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤት (ከዚህ በኋላ "ጽህፈት ቤት" እየተባለ የሚጠራ) ራሱን የቻለ የህግ ሰውነት ያለው የፌደራል መንግስት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ እንደገና ተቋቁሟል።
   2. የጽህፈት ቤቱ ተጠሪነት ለአፈጉባዔው ይሆናል።

4. **ዓላማ**

   ጽህፈት ቤቱ የተቋቋመበት ዓላማ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕገ መንግስታዊ ተልዕኮውን ለማሳካት የሚያስፈልጉ ሙያዊ ድጋፍና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት ነው።

5. <u>የጽህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለምክር ቤቱ ህግ አወጣጥ፣ ክትትልና ቁጥጥር እንዲሁም ለውክልና ስራ የሚያስፈልጉ ሙያዊ ድጋፍና አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ይሰጣል፤
2. ለምክር ቤቱና ምክር ቤቱ ለሚያቋቁማቸው ኮሚቴዎችና ሌሎች ውስጣዊ አካላት አጠቃላይ ሙያዊና አስተዳደራዊ አገልግሎት ይሰጣል፤
3. የፌደራል ነጋሪት ጋዜጣን ያስተዳድራል፤
4. የምክር ቤቱን የህዝብ ግንኙነት ተግባራት ያከናውናል፤
5. ተቋማዊ ቀጣይነትን ያረጋግጣል፤
6. ለምክር ቤቱ አባላት እና አካላት በህግ የተወሰኑ ጥቅማጥቅሞችን እና ልዩ መብቶችን ያስፈጽማል፤
7. የምክር ቤት አባላት መኖሪያ ቤቶችን ያስተዳድራል፣ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ፀጥታና ደህንነት መከበሩን ይከታተላል፤ በማንኛውም የምክር ቤቱ ቅጥር ግቢ ፀጥታና ስነስርዓት መከበሩን ያረጋግጣል፤
8. የምክር ቤቱን በጀት ያዘጋጃል፤
9. ለምክር ቤቱ አካላትና አባላት የቤተ መጽሃፍት፣ የምርምር፤ የመረጃ እና ዶክሜንቴሽን አገልግሎት ይሰጣል፤
10. የአቅም ግንባታ ስራዎችን ይሰራል፣
11. ለምክር ቤቱና ለምክር ቤቱ የተለያዩ አካላት የቃለጉባኤ፤ የአዳራሽ አገልግሎት፤ የህትመትና ሌሎች የኮንፈረንስ አገልግሎቶች ይሰጣል፤
12. ለምክር ቤቱ አባላትና አካላት የትራንስፖርት አገልግሎት ይሰጣል፤
13. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤
14. ዓላማውን ለማሳካት የሚረዱ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን ያከናውናል።

6. <u>የጽህፈት ቤቱ አደረጃጀት</u>

1. ጽህፈት ቤቱ፦

ሀ/ አፈ ጉባዔው ከመንግስት ዋና ተጠሪና ከዋና ተቃዋሚ ፓርቲ ዋና ተጠሪ ጋር በመመካከር የሚመድበው ገለልተኛና ባለሙያ ዋና ፀሃፊ፤

ለ/ በዋና ፀሃፊው አቅራቢነት በአፈጉባዔው የሚሾሙ አንድ ምክትል ዋና ፀሃፊና ቁጥራቸው እንደአስፈላጊነቱ የሚወሰን የመምሪያ ሃላፊዎች፤ እና

ሐ/ አስፈላጊው ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች፤

ይኖሩታል።

2. ምክትል ዋና ዐሃፊውና የመምሪያ ሃላፊዎች ተጠሪነታቸው ለዋና ዐሃፊው ይሆናል።
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ /1/ ንዑስ ፊደል (ሀ) እና (ለ) የተጠቀሱት የጽህፈት ቤቱ ሃላፊዎች በፌደራል የመንግስት ሰራተኞች ህግ አይካተቱም፣ የስራ ሁኔታቸው በተመለከተ በአፈጉባዔው በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡
4. አፈጉባዔው በሚወስነው መሰረት ጽህፈት ቤቱ ፓርላሜንታዊ የሆነ መዋቅር ይኖረዋል።
5. ጽህፈት ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ በምክር ቤቱ የሚወሰን የራሱ የሆነ የደሞዝ እርከን ይኖረዋል፡፡

7. <u>የጽህፈት ቤቱ ዋና ፀሃፊ ስልጣንና ተግባር</u>

1. የጽህፈት ቤቱ ዋና ዐሃፊ የጽህፈት ቤቱ ዋና ስራ አስፈፃሚ በመሆን ከአፈጉባዔው በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሰረት የጽህፈት ቤቱን ስራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ፀሃፊው፦

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 5 የተመለከቱትን የጽህፈት ቤቱን ስልጣንና ተግባራት በስራ ላይ ያውላል፤

ለ/ ምክትል ዋና ፀሃፊውንና የመምሪያ ሃላፊዎችን ለሹመት ያቀርባል፣ ያስተዳድራል፤

ሐ/ የጽህፈት ቤቱን ድጋፍ ሰጪ ሰራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሰረት ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

መ/ የጽህፈት ቤቱን የስራ ፕሮግራምና በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፈቀድም በስራ ላይ ያውላል፤

ሠ/ በተፈቀደው በጀት መሰረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣ ሃብትና ንብረት ያስተዳድራል፤

ረ/ የጽህፈት ቤቱን የስራ አፈፃፀምና የሂሳብ ሪፖርቶች አዘጋጅቶ ለአፈጉባዔው ያቀርባል፤

ሰ/ ጽህፈት ቤቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጽህፈት ቤቱን ይወክላል።

3. ዋና ፀሃፊው ለጽህፈት ቤቱ የስራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከስልጣንና ተግባሩ በከፊል ለጽህፈት ቤቱ ሌሎች ኃላፊዎችና ሰራተኞች በውክልና ሊሰጥ ይችላል፡፡

8. **የምክትል ዋና ፀሃፊ ስልጣንና ተግባር**

ምክትል ዋና ፀሃፊው፦

1. ዋና ፀሃፊው በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የጽህፈት ቤቱን የአስተዳደር ዘርፍ ይመራል፤
2. ዋና ፀሃፊው በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤
3. በዋና ፀሃፊው ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

9. **በጀት**

የጽህፈት ቤቱ በጀት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይመደባል።

10. **የሂሳብ መዛግብት**

1. ጽህፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብት ይይዛል።
2. የጽህፈት ቤቱ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይማቸው ኦዲተሮች በየዓመቱ ይመረመራሉ።

11. **መመሪያ የማውጣት ስልጣን**

አፈጉባዔው ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

12. **የተሻሩ ህጎች**

የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽህፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 253/1993 /በአዋጅ ቁጥር 519/1999 እንደተሻሻለ/ በዚህ አዋጅ ተሽሯል።

13. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ሐምሌ 15 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

# የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 6/2008

# የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት

# የአሰራርና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንብ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሕገ መንግሥት የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር እንዲሁም ከህዝቡ የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣት የሚያስችለው በግልፅነት፣ በተጠያቂነት እና በአሳታፊነት ላይ የተመሰረተ የአደረጃጀትና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

የምክርቤት አባላት እና የፓርላማ ቡድኖች በምክር ቤቱ ተግባራት ውስጥ ገንቢ ሚና የሚጫወቱበት እና ንቁ ተሳትፎ የሚያደርጉበት፣ አባላት የምክር ቤት ተግባሮቻቸውን ሲያከናውኑ ሊከተሏቸው ስለሚገባ የሥነ-ሥርዓት እና የሥነ-ምግባር ጉዳዮች እንደዚሁም የአባላት መብቶችን መደንገግ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በአጠቃላይ የተሟላ፣ ግልጽ፣ የሃሳብ ልዩነት በአግባቡ የሚስተናገድበት፣ የአብላጫ ድምጽ የሚከበርበት፣ የአነስተኛው ድምጽ የሚሰማበት ዲሞክራሲያዊ የአሰራር ባህል የሚዳብርበት ከአገሪቱ ህጎች፣ ከዓለም አደቀፍ የፓርላማ መርሆዎች፣ አሰራሮች እና ልምዶች ጋር የተጣጣመ ደንብ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀፅ 55 (19/ እና አንቀፅ59 (2/ መሰረት ይህ የምክር ቤቱ የአሰራርና የአባላት ሥነ-ምግባር ደንብ ወጥቷል፡፡

## ምዕራፍ አንድ

## ጠቅላላ

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ “የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአሰራርና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 6/2008” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያስጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ ደንብ፡-

1. “ሕገ መንግሥት” ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ነው፤
2. “ምክር ቤት” ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 53 የተቋቋመው የፌደራሉ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፤
3. “አፈጉባዔ” ማለት የምክር ቤቱ አፈጉባዔ ነው፤

4. “አባል” ማለት የምክር ቤቱ አባል ነው፤

5. “ኮሚቴ” ማለት የምክር ቤቱን ተግባር ለማከናወን እንደሁኔታው በምክር ቤቱ ወይም በኮሚቴ የሚቋቋም የምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ፡ አስተባባሪ ኮሚቴ፡ ልዩ ኮሚቴ፣ ቋሚ ኮሚቴ፣ጊዜያዊ ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ነው፤

6. “ፅህፈት ቤት” ማለት የምክር ቤቱ ፅህፈት ቤት ነው፤

7. “መንግስታዊ አካል” ማለት ማንኛውም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል በፌደራል መንግስት በጀት የሚተዳደር የፌደራል መንግሥት መሥሪያቤት ነው፤

8. “የመንግሥት አጀንዳ” ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተዘጋጅቶ ለምክርቤቱ የሚቀርብ ማንኛውም አጀንዳነው፤

9. “አስረጂ” ማለት ማንኛውንም ጉዳይ እንዲያብራራ እንደ ሁኔታው በምክር ቤቱ ወይም በኮሚቴ የሚጠራ ሰው ነው፤

10. “የምክር ቤቱ ክብርና ሞገስ” ማለት ምክር ቤቱ በሕገ-መንግሥቱ ከተሰጠው ደረጃ አኳያ በህብረተሰቡ ወይም በሌሎች አካላት ያለው መልካም ስም ነው፤

11. “አላስፈላጊ ባህርያት ወይም አላስፈላጊ ተግባራት” ማለት የምክር ቤቱን ክብር እና ሞገስ የሚያበላሹ ተግባራት ሆነው እንደ ዝሙት፣ ስካር፣ በአልባሌ ቦታዎች ማሳለፍ፣ አሉባልታ፣ የማታለል ተግባር እና የመሳሰሉትን ያጠቃልላል፤

12. “የኮሚቴ አመራር” ማለት አንድን የምክር ቤት ኮሚቴ በበላይነት የሚመራ ሊቀመንበር ወይም ምክትል ሊቀ መንበር ነው፤

13. “ተጋባዥ እንግዳ” ማለት በአንድ ጉዳይ ወይም አጀንዳ ላይ ሪፖርት እንዲያቀርብ ወይም እንዲያስረዳ ወይም በታዛቢነት እንዲሳተፍ በምክር ቤቱ ወይም በኮሚቴ የሚጋበዝ ማንኛውም ሰው ነው፤

14. “መመሪያ” ማለት ምክር ቤቱ ወይም ኮሚቴ ለዚህ ደንብ ዝርዝር አፈጻጸም እንዲረዳ የሚያወጣው ወይም ወደ ሌላ አካል የሚያስተላልፈው የአሠራር አቅጣጫን የሚያጠቃልል ሆኖ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ህግ በሚሰጠው የውክልና ስልጣን የሚወጣ መመሪያንም ያካትታል፤

15. “የቀድሞ የምክር ቤት አባል” ማለት ባለፉት የምርጫ ዘመናት የምክር ቤት አባል የነበረ እና በወቅቱ የምርጫ ዘመን የምክር ቤት አባል ያልሆነ ሰው ነው፤

16. “የህግ ከለላ” ማለት በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 54 (6/ መሠረት ለምክር ቤቱ አባላት የተሰጠ ልዩ መብት ነው፤

17. “የመንግሥት ረቂቅ ህግ” ማለት በሚኒስትሮች ምክር ቤት የሚቀርብ ረቂቅ ህግ ነው፤

18.“የመጀመሪያ ንባብ” ማለት ረቂቅ ህግ ለመጀመሪያ ጊዜ ለምክርቤቱ ቀርቦ በህጉመሠረታዊ ይዘት ላይ አጠቃላይ የሆነ ውይይት ከተደረገ በኋላ ለዝርዝርእይታናምርመራ ወደሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ የመምራት ወይም ወደ ሁለተኛ ንባብ የማሳለፍ ሂደት ነው፤

19.“ሁለተኛ ንባብ” ማለት በቋሚ ኮሚቴ የቀረበ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ ወይም ከመጀመሪያ ንባብ በተሸጋገረ ረቂቅ ህግ ወይም ጉዳይ ላይ ዝርዝር ውይይት የሚደረግበት እና ውሳኔ የሚሰጥበት ሂደት ነው፤

20.“ሦስተኛ ንባብ” ማለት ከሁለተኛ ንባብ በኋላ ምክርቤቱ በበለጠና በስፋት እንዲታይ ለቋሚ ኮሚቴ እንደገና የመራውን ረቂቅ ህግ አስመልክቶ የተዘጋጀ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ወደ ምክር ቤቱ ከቀረበ በኋላ የሚደረግ ውይይትና ውሳኔ የሚተላለፍበት ሂደት ነው፤

21.“የቴክኒክ ዕርምት” ማለት የቋንቋ እና መሠል ግድፈት ማስተከከያ ሲሆን በማንኛውም መልኩ የህጉን ይዘት የማይለውጥ ነው፤

22.“የመንግሥት ተጠሪዎች” ማለት በምክር ቤቱ ውስጥ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ከጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች በምክር ቤቱ ውስጥ የፓርቲውን ወይም የፖርቲዎቸን ሥራዎች እንዲያሰተባብሩ የሚወከላቸው ወይም የሚወከሉዋቸው የምክር ቤቱ አባል የሆኑ አባላቱ ወይም አባሎቻቸው ናቸው፤

23.“የፓርቲ ተጠሪዎች” ማለት ከገዥው ፓርቲ ወይም ከጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች ውጭ በምክር ቤቱ መቀመጫ ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶች በምክር ቤቱ ውስጥ የፓርቲያቸውን ስራዎች እንዲያስተባብሩ የሚወከሏቸው የምክር ቤት አባል የሆኑ አባሎቻቸው ናቸው፤

24.“ዋና ተቃዋሚ ፓርቲ” ማለት በምክር ቤቱ ውስጥ ከገዢው ፓርቲ ቀጥሎ ከፍተኛ መቀመጫዎችን ያገኘ ፓርቲ ነው፤

25.“ሁለተኛ ተቃዋሚ ፓርቲ” ማለት በምክር ቤቱ ውስጥ ከዋናው ተቃዋሚ ፓርቲ ቀጥሎ ከፍተኛ መቀመጫዎችን ያገኘ ፓርቲ ነው፤

26.“ሰራተኛ” ማለት የፅህፈት ቤቱ ሰራተኛ ነው፤

27.“ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

28.ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ይጨምራል

3. <u>አተረጓጎም</u>

1. በዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚፈጠር የህግ ክፍተት የምክር ቤቱን ልምዶች፣ የዓለም አቀፍ የፓርላማ መርሆዎች እና ልምዶች እንዲሁም የአገሪቱ ሌሎች ህጐችን በማጣጣም ወይም እንደ ጉዳዩ ክብደት ህግ በማውጣት ሊሞላ ይችላል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1/ ድንጋጌ የሕገመንግሥቱን ድንጋጌዎች እና ሌሎች የአገሪቱን ህጎች በተቃረነ ሊፈፀም አይችልም።
3. በዚህ ደንብ ውስጥ በኮሚቴዎች አሠራር የሚፈጠር ክፍተት እንደ ሁኔታው ከምክር ቤቱ አጠቃላይ አሠራር ጋር በማጣጣም ይሞላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የምክር ቤቱ ሥልጣን፣ተግባር እና አደረጃጀት

### 4. የምክር ቤቱ ዋና ዋና ሥልጣን እና ተግባራት

1. ምክርቤቱ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 55 እንዲሁም በአንቀፅ 70 (1/፣ አንቀፅ 79 (4/ (ሐ/፣ (አንቀፅ 82 (2/ (ሐ/ ፣አንቀፅ 101፣ አንቀፅ 102፣አንቀፅ 103 እና አንቀፅ 104 የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባራት ያሉት ሲሆን ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉትናቸው፡-

   ሀ/ ህግ ማውጣት፤

   ለ/ የፌደራል መንግስት በጀትን ማፅደቅ፤

   ሐ/ መንግሥታዊ አካላትን መከታተል፣ መቆጣጠር እና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም እርምጃ መውሰድ፤

   መ/ የራሱን የተለያዩ ከሚቴዎችና ሌሎች አስፈላጊ ክፍሎችን ማቋቋምና ማደራጀት፤

   ሠ/ በራሱ የሚሰየሙ፣የሚሾሙ እና የሚመረጡ የመንግሥት ባለስልጣናትን መሰየም፣ መሾም፣ ማፅደቀና መምረጥ፤

   ረ/ አባላቱ ከመረጣቸው ህዝብ ጋር እንዲገናኙ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።
2. ምክር ቤቱ ተግባራቱን ሲያከናውን የሚከተሉትን አጠቃላይ መርሆዎች መሠረት በማድረግይሆናል፡-

   ሀ/ በአጭርና ረጅም ጊዜ እቅድ በመመራት፤

   ለ/ ለተግባራቱ ውጤታማነት የሚረዳ ምቹ የሥራ ሁኔታን በመፍጠር

   ሐ/ የግልፅነት፣የተጠያቂነትና የአሳታፊነት መርህን በመከተል፤

   መ/ ተግባራትን በመገምገም፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2/ የተዘረዘሩት መርሆዎች እንደ ሁኔታው ለኮሚቴ ተጣጥመው ተፈጻሚ ይሆናሉ።

## 5. የምክር ቤቱ አጠቃላይ አደረጃጀት

1. በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 45 እና አንቀፅ 50 (1/ መሠረት የኢትዮጵያ ስርዓተ መንግስት ፓርላሜንታዊ ሆኖ በፌደራላዊ ስርዓት የተዋቀረ ነው።
2. በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 53 መሰረት የፌደራሉ መንግስት የህዝብ ተወካዮች ምክርቤት እና የፌደሬሽን ምክር ቤት ይኖሩታል።
3. በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 50 (3/ መሠረት የፌዴራሉ መንግስት ከፍተኛ የስልጣን አካልምክር ቤቱ ነው፡፡
4. የምክር ቤቱ አጠቃላይ አደረጃጀት እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

   ሀ/የምክር ቤቱ ጠቅላላ ጉባዔ፤

   ለ/አፈጉባዔ፤

   ሐ/ምክትል አፈጉባዔ፤

   መ/የተለያዩ ኮሚቴዎች፤

   ሠ/ የመንግስት ተጠሪዎች፤

   ረ/ ፓርቲ ወይም የፓርላማ ቡድን ተጠሪዎች፤

   ሰ/ የምክር ቤቱ ፅህፈት ቤት፤

   ሸ/ የምክር ቤቱ የክብር ጥበቃ ሃይል።
5. ምክር ቤቱ የራሱ መለያ ዓርማ ወይም ሎጎ ይኖረዋል።
6. የምክር ቤቱ ፅህፈት ቤት አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር አግባብነት ባለው ህግ ይወሰናል።

## 6. ስለምክር ቤቱ የስራ ዘመን እና መበተን

1. በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 54(1/ መሠረት የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ነዉ፡፡
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ የተደነገገው ቢኖርም፦

   ሀ/ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 60(1/ መሠረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ የስልጣን ዘመኑ ከማለቁ በፊት አዲስ ምርጫ ለማካሄድ በምክ ርቤቱ ፈቃድ ምክር ቤቱ እንዲበተን ለማድረግ ይችላል፡፡

   ለ/ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 60 (2/ መሠረት በጣምራ የመንግስት ስልጣን የያዙ የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራነታቸው ፈርሶ በምክር ቤቱ የነበራቸውን አብላጫነት ያጡ እንደሆነ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ተበትኖ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ባሉ የፖለቲካ ድርጅቶች ሌላ ጣምራ መንግስት በአንድ ሳምንት ጊዜ ውስጥ ለመመስረት እንዲቻልፕሬዚዳንቱ የፖለቲካ ድርጅቶችን

ይጋብዛል፡፡ የፖለቲካ ድርጅቶቹ አዲስ መንግሥትለመፍጠር ወይም የነበረውን ጣምራነት ለመቀጠል ካልቻሉ ምክር ቤቱ ተበትኖ አዲስ ምርጫ ይደረጋል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ መሰረት ምክር ቤቱ የተበተነ እንደሆነ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 60(3/ መሠረት ከስድስት ወር ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አዲስ ምርጫ መደረግ አለበት፡፡
4. በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 60(4/ መሠረት ምርጫው በተጠናቀቀ በሠላሳ ቀናት ውስጥ አዲሱ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ስራውን ይጀመራል።
5. በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 60(5/ መሠረት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከተበተነ በኋላ ሀገሪቱን የሚመራው ስልጣን ይዞ የነበረው የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅቶች ጣምራ የእለት ተእለት የመንግስት ስራ ከማከናወንና ምርጫ ከማካሄድ በስተቀር አዲስ አዋጆችን ደንቦችንና ድንጋጌዎችን ማውጣት ወይም ነባር ሕጎችን መሻርና ማሻሻል አይችልም፡፡

7. <u>የምክር ቤቱ እና የፌደሬሽን ምክር ቤቱ የጋራ ስልጣንና ተግባራት</u>

1. ምክር ቤቱ እና የፌደሬሽን ምክር ቤት የሚከተሉትን ጉዳዮች በጋራ ያከናውናሉ፡-
   ሀ/ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 70 (2/ መሠረት የሪፐብሊኩን ፕሬዚዳንትመምረጥ፤
   ለ/ በሕገመንግስቱ አንቀፅ 71 (1/ መሠረት የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚያቀርበውን የመክፈቻ ንግግር ማዳመጥ፤
   ሐ/ በማንኛውም ክልል የሰብዓዊ መብቶች ሲጣሱና ድርጊቱን ክልሉ ማቆም ሳይችልሲቀር በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 55 (16/ መሠረት ሊወሰድ የሚገባውን ተገቢእርምጃ አስመልክቶ በምክር ቤቱ በሚቀርብ ጥያቄ ላይ መወሰን፤
   መ/ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 99 መሠረት ለፌዴራሉ መንግስት ወይም ለክልሎች ተለይቶ ያልተሰጠ ታክስና ግብር የመጣል ስልጣን መወስን
   ሠ/ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 105 (2/(ሀ/ መሠረት ሕገመንግስቱን ማሻሻል፡፡
2. የምክርቤቶቹ የጋራ ተግባራት ምክር ቤቶቹ በጋራ በሚያወጡት የአሰራር ደንብ መስረትየሚፈፀም ይሆናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>ስለ አፈጉባዔና ምክትል አፈጉባዔ</u>

8. <u>የአፈ ጉባዔና የምክትል አፈጉባዔ አመራረጥ</u>

1. በሕገመንግሥቱአንቀፅ 55 (19/ መሠረት ምክር ቤቱን የሚመሩ አፈጉባዔና ምክትል አፈጉባዔ በምክር ቤቱ ይመረጣሉ።
2. አፈጉባዔው የሚመረጠው በምክር ቤቱ የሥራ ዘመን መጀመሪያ በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ወይም በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የመድረክ መሪነት ይሆናል፡፡
3. የአፈጉባዔ አመራረጥ በሚከተለው አኳኋን ይፈፀማል፡
   ሀ/ ማንኛውም አባል እጩ አፈጉባዔ መጠቆም ይችላል፤ሲጠቁምም እጩውን በተመለከተ አጭር ማብራሪያ ማቅረብ ይኖርበታል፤
   ለ/ አንድ በእጩነት የተጠቆመ አባል በሌላ አንድ አባል መደገፍ አለበት፤
   ሐ/ በዚህ ንዑስ አንቀፅ ፊደል ተራ (ሀ/ እና (ለ/ መሰረት የተጠቆመ አባል እጩ ሆኖእንዲቀርብ ፈቃደኝነቱን መግለፅ ይኖርበታል፤
   መ/ ማንኛውም አባል ከአንድ እጩ በላይ መጠቆም ወይም እጩ ሆኖ እንዲቀርብ ድጋፍመስጠት አይችልም፤
   ሠ/ የተጠቆሙ እጩዎች ስም ዝርዝር በፊደል ተራ ይመዘገባል፤በዚሁ ቅደም ተከተል መሰረትም ድምፅ ይሰጣል፤
   ረ/ አብላጫ ድምፅ ያገኘ እጩ አባል አፈጉባዔ ይሆናል፤
   ሰ/ በተደረገው ምርጫ አብላጫ ድምፅ ያገኘ እጩ ከሌለ ከተሰጠው ድምፅ ውስጥ ከአስር በመቶ በታች ያገኘ ወይም ውጤቱ ከተገለፀ በኋላ ወዲያውኑ ራሱን ያገለለ እጩ ከውድድር ውጭ ሆኖ በቀሩት እጩዎች መካከል አንድ እጩ አብላጫ ድምፅ እስኪያገኝ ድረስ ምርጫው ይቀጥላል፤
   ሸ/ እጩነት የቀረበው አንድ አባል ብቻ ቢሆንም የምክር ቤቱን አብላጫ ድምፅ ማግኘትይኖርበታል፤ድምፅ አሰጣጡም እጅ በማውጣት ይከናወናል፤
   ቀ/ ከአንድ በላይ እጩ ሲቀርብ ምርጫው በሚስጥር ድምፅ አሰጣጥ ይከናወናል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (3/ መሰረት የተመረጠው አፈጉባዔ በመድረኩ ይገለፃል፤የአፈጉባዔነት ወንበሩን እንዲይዝም ይደረጋል፡፡
5. የመድረኩ መሪ በሚሰጠው መመሪያ መሰረት ፅህፈት ቤቱ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፡-
   ሀ/ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (3/ መሰረት እጩ ይመዘገባል፤
   ለ/ ለምርጫ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ያዘጋጃል፣ የድምፅ መስጫ ካርድ ያሰራጫል፣ ያሰባስባል፣ ይቆጥራል፣ ውጤቱንም ለመድረኩ መሪ ያሳውቃል፤

ሐ/ ድምፅ የተሰጠባቸውና ግልፅ ያልሆኑ ወይም ለምርጫው ከተቀመጡ አሰራሮችውጭድምፅ የተሰጠባቸው ካርዶች ሲያጋጥሙ በመድረኩ መሪ ውሳኔ እንዲያገኙ ያደርጋል።

6. በዚህ አንቀፅ የተደነገገው የአፈጉባዔ የአመራረጥ ስርዓት ለምክትል አፈጉባዔ አመራረጥም ተፈፃሚ ይሆናል፣ይሁን እንጂ መድረኩ የሚመራው በአፈጉባዔ ይሆናል፡፡

7. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት አፈጉባዔው ወይም ምክትል አፈጉባዔው በተለያዩ ምክንያቶች ሥራቸውን ቢለቁ በስራ ላይ ባለው አፈጉባዔ ወይም ምክትል አፈጉባዔ መሪነት በዚህ አንቀጽ በተቀመጠው አሠራር መሠረት ከምክርቤቱ አባላትመካከል እንዲመረጥ ይደረጋል።

8. የምክር ቤቱ የሥራ ዘመን ከማለቁ በፊት በተለያዩ ምክንያቶች አፈጉባዔው እና ምክትል አፈጉባዔው በአንድ ጊዜ ሥራቸውን ቢለቁ በዚህ አንቀፅ መሠረት ምርጫው ይካሄዳል፡፡

9. ማንኛውም ተመራጭ አፈጉባዔ ወይም ምክትል አፈጉባዔ ሥራ ከመጀመሩ በፊት በዚህደንብ አንቀፅ 111 መሠረት ቃለ መሃላ ይፈጽማል፡፡

9. <u>የአፈጉባዔው ሥልጣንና ተግባራት</u>

አፈጉባዔው የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ምክርቤቱን በበላይነት ይመራል፣ ያስተዳድራል፤
2. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፣ ሥነሥርዓት ያስከብራል፣ ልዩና አስቸኳይ ስብሰባዎችን ይጠራል፤
3. በስብሰባ ወቅት ለሚነሱ የትርጉም ጥያቄዎች በዚህ ደንብ በአንቀፅ 3 መሠረት ውሳኔ ይሰጣል ወይም ለሚመለከተው አካል ይመራል፤
4. የኮሚቴዎችን ሊቃነ መናብርት፣ ምክትል ሊቃነመናብርት እና አባላት እንዲሁም ምክርቤቱ በህግ መሠረት በሚወከልባቸው አካላት ውስጥ የሚወከሉ አባላትን ያስመርጣል፣ እንዲወከሉ ያደርጋል፤
5. የቋሚ ኮሚቴዎችን ሥራ ያስተባብራል፤
6. ምክር ቤቱን በመወከል ግንኙነት ያደርጋል፤
7. ከስልጣንና ተግባሩ ውስጥ በከፊል ለምክትል አፈጉባዔው በጽሁፍ ውክልና ሊሰጥ ይችላል፤
8. ከመንግስት ዋና ተጠሪና ከዋናው ተቃዋሚ ፓርቲ ዋና ተጠሪ ጋር በመመካከር ገለልተኛ እና ባለሙያ የሆነ የዕህፈት ቤት ዋና ፀሃፊ ይመድባል፤

9. በዚህ ደንብ በተደነገገው መሠረት የምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴን እና አስተባባሪ ኮሚቴን ያደራጃል፣ይመራል፤

10. በህግ ለአፈጉባዔው ተጠሪ የሆኑ አካላትን ይሾማል፡ ይመድባል፤

11. ምክር ቤቱ በአባላት ላይ የወሰነውን የዲስፕሊን እርምጃ ያስፈፅማል፤

12. በምክር ቤቱ እና በሌሎች ህጎች የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

10. <u>የምክትል አፈጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል አፈጉባዔው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. አፈጉባዔው በማይኖርበት ጊዜ ወይም አቋም ይዞ ለመከራከር ሲፈልግ አፈጉባዔውን ተክቶ ይሠራል፤
2. በምክር ቤቱ ወይም በአፈጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>የምክር ቤቱ የመክፈቻሥነ-ሥርዓት እና የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ንግግር</u>

11. <u>የምክር ቤቱ የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. ምክር ቤቱ በየዓመቱ መጀመሪያ ስራውን የሚጀምረው በሪፐብሊኩ ብሔራዊ መዝሙር እና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓቶችን በማከናወን ይሆናል፡፡
2. ምክር ቤቱ በስራ ዘመኑ መጀመሪያ ላይ የሚኖረው የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፡-

   ሀ/ የሪፐብሊኩ ብሔራዊ መዝሙር ይዘመራል፣

   ለ/ ቃለ-መሃላ ይፈፀማል፤

   ሐ/ የቃላ-መሃላው ይዘትም "እኔ ------------------ በዛሬው እለት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባል ሆኜ ስራዬን ስጀምር ለሕገመንግስቱ ታማኝ በመሆን ከአገሪቷና ከህዝቧየተጣለብኝን ሃላፊነት በቅንነት፣ በታታሪነት እንዲሁም ህግንና ሥርዓትን መሠረት በማድረግ ስራዬን እንደምፈጽም ቃል አገባለሁ" የሚል ይሆናል፡፡ ቃለ-መሃላው በፅሁፍ ተዘጋጅቶና ለአባሉ ቀርቦ በፊርማ ይረጋገጣል፣ በሰነድነትም ይያዛል፤

   መ/ ቃለ-መሃላው በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት አማካኝነት ይፈፀማል፤

   ሠ/ ማንኛውም አባል በዚህ ንዑስ አንቀፅ በፊደል ተራ (መ/ የተጠቀሰውን ቃለ-መሃላየመፈፀምግዴታ አለበት፡፡ ይህንን የማይፈጽም አባል በአፈጉባዔው አማካኝነት ለጊዜው ይታገዳል፣ በቀጣይም አፈጉባዔው በሚያቀርበው

ሞሽን ምክር ቤቱ ተወያይቶ በዚህሰሰደንብ አንቀፅ 143 (7/ መሠረት ውሳኔ ያሳልፋል፤

ረ/ በዚህ ደንብ በአንቀፅ 8 መሠረት የአፈጉባዔና የምክትል አፈጉባዔ ምርጫ ይካሄዳል፤

ሰ/ በዚህ ደንብ በአንቀፅ 107 መሠረት ጠቅላይ ሚኒስትር ይሠየማል፤

ሸ/ የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ሁለቱ ምክር ቤቶች ሥራ መጀመራቸውን በማብሰር የመክፈቻ ንግግር ያደርጋል፡፡

3. የምክር ቤቱና የፌደሬሽን ምክር ቤት ዓመታዊ የጋራ ስብሰባ የመክፈቻ ሥነ-ሥርዓት እንደሚከተለው ይሆናል፦

ሀ/ የሪፐብሊኩ ብሔራዊ መዝሙር ይዘመራል፤

ለ/ የሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ሁለቱ የፌደራል መንግሥት ምክር ቤቶች ዓመታዊ ስራቸውን መጀመራቸውን በማብሰር የፌደራል መንግሥት ዓመታዊ አቅድን ያቀርባል።

12.<u>በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የመክፈቻ ንግግር ላይ የሚደረግ ውይይት</u>

1. አፈጉባዔው በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 71(1/ መሰረት በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት በሚቀርበው ንግግር ላይ ለሚደረገው ውይይት የሚያስፈልገውን ጊዜ ከመንግስት ዋና ተጠሪ ጋር በመመካከር ይመድባል፡፡
2. በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ንግግር ዙሪያ በሚቀርብ የድጋፍ ሞሽን ላይ አባላት ነፃ ሆነው ውይይት ያደርጋሉ፤በአንድ አባል የሚቀርብ የድጋፍ ሞሽን በሌላ የምክር ቤት አባል ድጋፍ ማግኘት ይኖርበታል።
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ በቀረበው ሞሽን ላይ አፈጉባዔው ሲፈቅድ የማሻሻያ ሞሽን ሊቀርብ ይችላል፤ የማሻሻያ ሞሽኑም በአንድ ሌላ አባል መደገፍ አለበት፡፡
4. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በፕሬዚዳንቱ ንግግር ላይ ውይይት ለማካሄድ በተያዘው ጊዜ ሌሎች የምክር ቤት ስራዎች ሊከናወኑ ይችላሉ፤ የተቋረጠው ውይይት የሚቀጥልበት ጊዜም በአፈጉባዔው ይወሰናል፡፡
5. ቅድሚያ በሚሹ የመንግስት ረቂቅ ህጎች ወይም ሌሎች ጉዳዮች እንዲሁም በዚህ ደንብ አንቀፅ 33 መሠረት በሚቀርብ ሞሽን ምክንያት በፕሬዚዳንቱ ንግግር ላይ የሚደረገው ውይይት በአፈጉባዔው ውሳኔ ለሌላ ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል፡፡
6. ለጉዳዩ የሚያስፈልገው የንግግር ጊዜ በአፈጉባዔው ይመደባል።

7. በውይይቱ መጨረሻም የመንግስት አቋም በጠቅላይ ሚኒስትሩ ይገለፃል፣ በቀረበው የድጋፍ ሞሽን ላይ ድምፅ ተሰጥቶ ውይይቱ ይጠቃለላል።

## ምዕራፍ አምስት

## ስለ ምክር ቤቱ ስብሰባ

### 13.የስብሰባ ዓይነቶች

ምክር ቤቱ የሚከተሉት የስብሰባ ዓይነቶች ይኖሩታል፡-

1. መደበኛ ስብሰባ፤
2. አስቸኳይ ስብሰባ፤
3. ልዩ ስብሰባ፤እና
4. ዝግ ስብሰባ፡፡

### 14.መደበኛ ሰብሰባ

1. መደበኛ ስብሰባ በሳምንት ሁለት ቀን በዚህ ደንብ በአንቀፅ 24 በተቀመጠው ጊዜ መሠረት የሚካሄድ ስብሰባነው።
2. መደበኛ ስብሰባ በምክር ቤቱ ውስጥ ለዚሁ በተዘጋጀ የስብሰባ አዳራሽ ይካሄዳል፡፡
3. የምክር ቤተ መደበኛ ስብሰባ ለዚሁ በተወሰኑት ቀናት አባላቱ ሰዓት አክብረው በመገኘት   የሚከናወን ይሆናል፣ይህንን ስብሰባ ለማካሄድ የተለየ የጥሪ ዘዴ አያስፈልገውም፡፡
4. መደበኛ ስብሰባ የማይካሄድ ከሆነ የምክር ቤቱ አባላት እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

### 15.አስቸኳይ ስብሰባ

1. ምክር ቤቱ በዕረፍት ላይ እያለ የምክር ቤቱን ውሳኔ የሚሹ አስቸኳይ ጉዳዮች ሲያጋጥሙ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
2. በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 58(4/ መሠረት ምክር ቤቱ በዕረፍት ላይ በሚሆንበት ጊዜአፈጉባዔው ወይም ከግማሽ በላይ የሚሆኑ አባላት አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራ ከጠየቀአፈጉባዔው የተለያዩ የመገናኛ ዘዴዎችን በመጠቀም አስቸኳይ ስብሰባ ይጠራል፡፡
3. አስቸኳይ ስብሰባ ከተጠራ ቦኋላ የተጠራበት ጉዳይ እልባት እስኪያገኝ ድረስ በማንኛውም የሳምንቱ ቀናትና ሰዓታት ስብሰባው ይካሄዳል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (3/ የተደነገገው ቢኖርም አፈጉባዔው በሚወስነው መሠረት ምክር ቤቱ ዕረፍት ሊያደርግ ይችላል፡፡

5. አስቸኳይ ስብሰባ አፈጉባዔው አመቺ ነው ባለው ቦታ ይካሄዳል፡፡

## 16.ልዩ ስብሰባ

1. ምክር ቤቱ በመደበኛ የስራ ወቅት ላይ እያለ የስራ መደራረብ ወይም አፋጣኝ መፍትሄ የሚሻ ጉዳይ ሲያጋጥመው ከመደበኛው የስብሰባ ጊዜ ውጭ ባሉት ቀናት ልዩ ስብሰባ ሊያካሂድ ይችላል፡፡
2. የምክር ቤቱ ልዩ ስብሰባ የሚጠራው በአፈጉባዔው ወይም በማንኛውም አባል በሚቀርብ ሞሽን ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ የቀረበ ሞሽን በአብላጫ ድምፅ መደገፍ አለበት፡፡
4. ልዩ ስብሰባ የሚካሄደው በምክር ቤቱ ውስጥ ለዚህ ተብሎ በተዘጋጀ የስብሰባ አዳራሽይሆናል።

## 17.የምክር ቤቱ ስብሰባዎች በግልፅ ስለመካሄዳቸው

በዚህ ደንብ ከአንቀፅ 14 እስከ አንቀፅ 16 ያሉት የስብሰባ ዓይነቶች በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 58 (5/ መሰረት በግልፅ ይካሄዳሉ።

## 18.ዝግ ስብሰባ

1. በዚህ ደንብ አንቀፅ 17 የተደነገገው ቢኖርም በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 58 (5/ መሰረት የምክር ቤቱ ስብሰባ በዝግ እንዲካሄድ በአንድ ሦስተኛ የምክር ቤቱ አባላት ከተጠየቀና ከግማሽ በላይ አባላት ከደገፉት ወይም በህግ አስፈጻሚው አካል ከተጠየቀና ከምክር ቤቱአባላት ከግማሽ በላይ ከደገፉት ዝግ ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፡፡
2. የዝግ ስብሰባ ጊዜ እና የመሰብሰቢያ ቦታ እንደየሰብሰባው ዓይነት ይወሰናል፡፡

## 19.የስብሰባ አጠራር

1. ምክር ቤቱ የተለያዩ ስብሰባዎችን ለመጥራት የሚጠቀምበት የማስታወቂያ ዘዴ በተቻለመጠን አባላትና ሌሎች የሚመለከታቸው አካላት በግልፅ ሊያዩት ወይም ሊሰሙት ወይም ሊያውቁት በሚያስችል መንገድ መሆንአለበት፡፡
2. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በሚመለከተው አካል ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም አባል በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባዎች መገኘት አለበት፡፡

## 20.የአባላት የስብሰባ እና የአቀማመጥ ፕሮቶኮል

1. ማንኛውም አባል በምክር ቤቱ የስብሰባ ጊዜያት የምክር ቤቱን ክብርና ሞገሰ የጠበቀ አለባበስ ሊኖረው ይገባል፡፡
2. የዚህ አንቀፅ የንዑስ አንቀፅ (1/ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባልሙሉ ልብስ ወይም የባህል ልብሰ መልበስ ይኖርበታል።
3. የኮሚቴ አባላት ምክር ቤቱን ወክለው በሚያደርጉት ግንኙነት የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ የሚጠብቅ አለባበስ ሊኖራቸው ይገባል፡፡
4. ማንኛውም አባል ወይም ተጋባዥ እንግዳ ከስብሰባው ጋር ፊፅሞ የማይዛመድ ወይም አላስፈላጊ የሆነ ቁሳቁስ ይዞ ወደ ምክር ቤቱ ቅጥር ግቢ መግባት የለበትም፡፡
5. የምክር ቤቱ ስብሰባ በሚካሄድበት አዳራሽ ውስጥ የአባላት ወይም የተጋባዥ እንግዶች አቀማመጥ የሚመለከታቸውን በማማከር በአፈጉባዔው ይወሰናል፡፡
6. ማንኛውም አባል ወይም ተጋባዥ እንግዳ በስብሰባው ሂደት ከመቀመጫው ውጭ መቀመጥ የለበትም፡፡
7. የዚህን አንቀፅ አፈፃፀም ፅህፈት ቤቱ ያረጋግጣል።

21.<u>ስብሰባ ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች</u>

1. ፅህፈት ቤቱ ስብሰባ ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች መሟቸታቸውን አስቀድሞ ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. የስብሰባ ሰዓት መድረሱን ለማመልከት ደወል ሲደወል ወይም በሌላ መንገድ ሲገለፅ አባላት ወደ መሰብሰቢያ አዳራሽ መግባትና ቦታቸውን መያዝ ይጠበቅባቸዋል።
3. የዕለቱ ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት ፅህፈት ቤቱ የስም ቁጥጥር ያካሂዳል።
4. ስብሰባውን ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች ያልተሟሉ ከሆነ ወይም ከአቅም በላይየሆነ ሁኔታ ያጋጠመ እንደሆነ ፅህፈት ቤቱ ወዲያውኑ ለአፈጉባዔው ማሳወቅ አለበት፡፡
5. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (4/ መሰረት ስብሰባውን ለማካሄድ ያልተቻለ እንደሆነ አፈጉባዔው በፅህፈት ቤቱ በኩል አባላት እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

22.<u>ስብሰባ ስለመጀመር</u>

1. አባላት ቦታቸውን ከያዙ እና ሌሎች አስፈላጊ ሁኔታዎች ከተሟሉ ቦኋላ አፈጉባዔው በፕሮቶኮል አማካኝነት ቦታውን ይይዛል፣ ስብሰባውን በመዶሻ ድምፅ ይከፍታል፡፡

2. አፈ-ጉባዔው በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 58 (1/ መሠረት ምልዓተ ጉባዔ መሟላቱን ያረጋግጣል።
3. ምልዓተ ጉባዔ መኖሩ ከተረጋገጠ በኋላ አፈጉባዔው በዚህ ደንብ መሰረት የተቀረጹትን የእለቱን አጀንዳዎች ለቤቱ ያቀርባል።

23.<u>የስብሰባ አመራር</u>

1. በዚህ ደንብ አንቀፅ 9 (2/ መሠረት ማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባዎች በአፈጉባዔው ይመራሉ፡፡
2. አፈ-ጉባዔው ማንኛውንም ስብሰባ በሚመራበት ወቅት ገለልተኛ፣ ፍትሃዊ እና ሚዛናዊ የሆነ መርንሀ መከተል ይገባዋል።
3. አፈ-ጉባዔው በራሱ አስተያየት የተለየ የመናገርእድል ለአባላት መስጠት ሲፈልግ የሁሉንም ወገኖች ተሳትፎ ግምት ውስጥ ያስገባ መሆን አለበት፡፡
4. አፈ-ጉባዔው ስብሰባ በሚመራበት ወቅት የስብሰባው አካሄድ የአገር እና የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ የጠበቀ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል።
5. ማንኛውም አባል ሀሳቡን በሚገልጽበት ጊዜ በዚህ ደንብ የተመለከቱትን ሥነ-ምግባሮችና ሥነ-ሥርዓቶች ካልተላለፈ በስተቀር አፈጉባዔው ጣልቃ በመግባት ማቋረጥ የለበትም፡፡
6. አፈ-ጉባዔው በምክር ቤቱ ስብሰባ ሂደት የሥነ-ሥርዓት ጥያቄ ለሚያነሳ አባል የቅድሚያእድል ይሰጣል፣ በዚህም ምክንያት ንግግሩ የተቋረጠበት አባል የተቋረጠው ጊዜ ይካካስለታል።
7. በአጀንዳነት የቀረበ ጉዳይ በተያዘለት የጊዜ ገደብ ውስጥ በቂ ውይይት ከተደረገበት ቦኋላ አፈጉባዔው በጉዳዩ ላይ ውሳኔ እንዲሰጥበት ያደርጋል፡፡
8. አፈ. ጉባዔው በውይይት ወቅት ከአባላት የተነሱ የተለያዩ ሀሳቦችን ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልኩ በማደራጀት ድምጽ ያሰጣል።
9. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች እንደ አግባብነቱ በኮሚቴ ስብሰባ አመራር ላይም ተፈጻሚ ይሆናሉ።

24.<u>የምክር ቤቱ የሥራ እና የዕረፍት ጊዜያት</u>

1. በሕገ-መንግሥቱ አንቀፅ 58 (2/ መሠረት የምክር ቤቱ የአንድ ዓመት የሥራ ጊዜ ከመስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ ጀምሮ እስከ ሰኔ 30 ቀን ድረስ ይሆናል።
2. ምክር ቤቱ በየዓመቱ በየካቲት ወርና ከሐምሌ 1 እስከ መስከረም ወር የመጨረሻ ሳምንት ሰኞ ድረስ በዕረፍት ላይ ይሆናል፡፡

3. የምክር ቤቱ መደበኛ ስብሰባ ዘወትር ማክሰኞና ሐሙስ ይካሄዳል፡፡
4. በተለየ ሁኔታ በአፈጉባዔው ካልተወሰነ በስተቀር የመደበኛና የልዩ ስብሰባ የሥራ ሰዓት እንደሚከተለው ይሆናል፦
   ሀ/ከሰዓት በፊት ከ3ሰዓት እስከ 6:30:
   ለ/ ከሰዓት ቦኋላ ከ8፡30 እስከ 11:30::
5. የምክር ቤቱ አስቸኳይ እና ዝግ ስብሰባ አፈጉባዔው በሚወስነው በማንኛውም ጊዜሊካሄድ ይችላል፡፡
6. ከአቅም በላይ የሆነ አሳማኝ ምክንያት ከሌለ በስተቀር በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1/ የተደነገገው የምክር ቤቱ የዕረፍት ጊዜ መከበር አለበት፡፡

25.**<u>የምክር ቤቱ የሥራ ቋንቋ</u>**

1. የምክር ቤቱ የሥራ ቋንቋ አማርኛ ነው፤ማንኛውም ስብሰባ በአማርኛ ቋንቋ ይካሄዳል፡፡
2. አባላት ሃሳባቸውን በሚገልጹበት ጊዜ ምክር ቤቱ የትርጉም አገልግሎት ባዘጋጀላቸውእና ሃሳባቸውን በሚገባ በሚገልጹባቸው ቋንቋዎች መናገር ይችላሉ፣ አስፈላጊ ከሆነ ምየራሳቸው ተርጓሚ ይዘው ሊመጡ ይችላሉ፡፡
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ መሠረት አንድ አባል ሃሣቡን በተርጓሚ በሚገልፅበት ጊዜ በተናጋሪውና በተርጓሚው መካከል መሰረታዊ የሆነ የትርጉም ስህተት ተፈጥሯል የሚል ማንኛውም አባል የማስተከከያ ሀሳቡን ሊያቀርብ ይችላል።

26.**<u>የቃለ-ጉባዔ አያያዝ</u>**

1. ማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ በቃለ-ጉባኤ ይያዛል፡፡
2. ቃለ-ጉባዔው እንደ አስፈላጊነቱ በፅሁፍ፣ በምስል ወይም በድምፅ ይያዛል፡፡
3. በማናቸውም ዘዴ የተያዘ የምክር ቤቱ ቃለ-ጉባዔ በአማርኛ ቋንቋ በጽሁፍ ተዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ይደረጋል፡፡
4. አንድ ቃለ-ጉባዔ በትክክል አልተያዘም በሚል በአባላት የሚቀርብ የማስተካከያ ሃሣብ በመቅረፀ ድምፅ ከተያዘው ጋር ተነፃፅሮ ተገቢ ሆኖ ከተገኘ እንዲታረም ይደረጋል፡፡
5. ማንኛውም ቃለ-ጉባዔ በቀላሉ ለማግኘት እና ለመጠቀም በሚያስችል መልኩ በዘመናዊ የሰነድ አያያዝ ሥርዓት ይቀመጣል።
6. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች ለኮሚቴ ስብሰባዎችም ተጣጥመው ተግባራዊ ይሆናሉ።

27.<u>በስብሰባ ስለሚገኝ ተጋባዥ እንግዳ</u>

1. ማንኛውም ተጋባዥ እንግዳ በስብሰባ ላይ ሊገኝ ይችላል።
2. ማንኛውም ተጋባዥ እንግዳ የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ መጠበቅ እናሥነ-ሥርዓት ማክበር ይኖርበታል።
3. በስብሰባ የሚገኝ ተጋባዥ እንግዳ የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ የማይጠብቅ እና ሥነ-ሥርዓት የማያከብር ከሆነ በምክር ቤቱ የክብር ጥበቃ አማካኝነት ጉድለቱን እንዲያስተካክል ይደረጋል፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም የዚህ ደንብ አንቀፅ 30 (14/ ተፈፃሚ ይሆናል።

28.<u>ስለ ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞች</u>

1. በስብሰባ ወቅት የሚመደብ ማንኛውም ሠራተኛ የምክር ቤቱን ስብሰባ ሳያውክ ስራውን ማከናወን አለበት።
2. ማንኛውም ሠራተኛ የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ መጠበቅ እና ሥነ-ሥርዓት ማክበር ይኖርበታል።
3. ማንኛውም ሠራተኛ በስብሰባ ወቅት የፈፀመው ጥፋት ከባድ ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀፅ 30 (14/ ከተደነገገው እርምጃ በተጨማሪ ፅህፈት ቤቱ ጉዳዩን በዲስፕሊን አይቶ በህግ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ እንዲወስድ አፈጉባዔው ሊያዝይችላል።

29.<u>የአባላት የንግግር ሥነ-ምግባር እና ሥነ-ሥርዓት</u>

1. ማንኛውም አባል በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 54 (5/ መሰረት በምክር ቤቱ ስብሰባ ሃሳቡን በነፃነት የመግለጽ መብቱ የተጠበቀ ነው።
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1/ እና ሌሎች የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖማንኛውም አባል የሚከተለውን ሥነ-ምግባር ማክበር ይኖርበታል፦

   ሀ/ ንግግሩ ከተያዘው አጀንዳ ጋር አግባብነት ያለው፣ አጭር፣ ግልጽ፣ ያልተደጋገመ እና የተፈቀደለትን ጊዜ ያከበረ መሆን፤

   ለ/ በፍርድ ቤት ሂደት ላይ ያለ ጉዳይ በምክር ቤቱ ስብሰባ አለማቀረብ፤

   ሐ/ በቅን ልቦና ወይም በእውነት ላይ የተመሰረተ ንግግር ማድረግ፤

   መ/ የአገሪቱን እና የህዝቦቿን ሰላምና ፀጥታ የሚያውክ ንግግር አለማድረግ፤

   ሠ/ ንግግሩ የምክር ቤቱን፣ የአባላቱን፣የሌሎች ሰዎችን እና ተቋማትን ክብርናሞገስ የጠበቀ መሆን፤

ረ/ ንግግሩ ሃሳብን የመግለጽ፣የመደገፍ ወይም የመቃወም መርህን የተከተለና የሌሎችአባላትን መብት የሚያከብር መሆን፤

ሰ/ ሌላ አባል ሃሳቡን በመግለጽ ሂደት ላይ እያለ በማጉረምረም፡ በመጮህ፡ በማጨብጨብ፣ በማፏጨት እና በአጠቃላይ በማንኛውም ሥነ-ምግባር በጎደለው አኳኋን ንግግሩን አለማቋረጥ፤

ሸ/ በስብሰባ ወቅት ከአጀንዳው ጋር ተያያዥነት የሌለው ማንኛውን ምዕሁፍ አለማንበብ፤

ቀ/ አግባብነት ባላቸው ህጎች መሰረት በተከለከሉ የምክር ቤቱ ቦታዎች ሲጋራ አለማጨስ፤

በ/ አስተያየት ሰጥቶወዲያውኑ ከስብሰባው አለመውጣት፤

ተ/ ከምክር ቤቱ ስራጋርተያያዥነት የሌለው ማንኛውንም ሰነድ በግቢው ውስጥ አለማሰራጨት፤

ቸ/ በስብሰባ ላይ ዶክመንቶችን በመቅደድ ተቃውሞን አለመግለፅ፤ በምክር ቤቱ ኮሪደር ላይ ስብሰባውን በሚያውክ ሁኔታ ከማውራትና ድምፅ ከማሰማት መቆጠብ፤

ነ/ በጋለሪ ላይ ያለን እንግዳ አለመጥራት ወይም ጠቅሶ አስተያየት አለመስጠት፤

ኘ/ አፈጉባዔው በሚናገርበት እንዲሁም ድምፅ በሚስጥበትና በሚቆጠርበት ወቅት ከስብሰባ አለመውጣት፤

አ/ ባንዲራ፣ አርማ ወይም ሌላ ምልክት ይዞ አለመግባት እንዲሁም መፈክር አለማስማት፤

ከ/ አፈጉባዔው ስብስባ በሚመራበት ወቅት በአካል ሄዶ አለማናገር።

3. ንግግር ለማድረግ የሚፈልግ አባል የሚከተሉትን ሥነ-ሥርዓቶች መከተል ይኖርበታል፦

ሀ/ ንግግሩን "እመስግናለሁ የተከበሩ አፈጉባዔ" በማለት መጀመር፤

ለ/ ሌላ አባልን መጥቀስ ሲፈልግ "የተከበሩ" ወይም የመንግሥት ከፍተኛ ባለሥልጣንን መጥቀስ ሲፈልግ "ክብርት" ወይም "ክቡር" የሚሉትን ቃላት እንደሁኔታው መጠቀም፤

ሐ/ ሃሳብ መስጠት ሲፈልግ ወይም የሥነሥርዓት ጥያቄ ያለው ከሆነ ለአፈጉባዔው በሚታይ መልክ እጁን ከፍ አድርጎ ከማሳየት ውጭ ድምጽ

በማስማት፣ ተገቢያልሆነ እንቅስቃሴና ጠባይ በማሳየት የንግግር ዕድል ለማግኘት አለመሞከር፤

መ/ በመናገር ላይ እያለ አፈጉባዔው ሲያቋርጠው ንግግሩን ማቆም እና በአፈጉባዔው የሚሠጠውን መመሪያ ማክበር፡፡

4. የመናገር እድል ሳይሰጠው እንደተሰጠው በመቁጠር ንግግር የጀመረ አባል በሚኖርበት ጊዜ አፈጉባዔው ንግግሩን አስቀሞ ለተፈቀደለት አባል እድሉን ይሰጣል፡፡

5. ለውይይት ሃሳብ ያቀረበ አባል በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ያቀረበውን ሃሳብ ለማንሳት ይችላል፣ ሃሳቡን እንዳነሳም በጉዳዩ ላይ የተጀመረው ውይይት ይቆማል።

6. አስቀድሞ በአፈጉባዔው ካልተፈቀደ በስተቀር ፅሁፍ እያነበቡ ንግግር ማድረግ አይቻልም ይሁን እንጂ አጫጭር ማስታወሻ አዘጋጅቶ መናገር ይቻላል፡፡

7. ማንኛውም አባል በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (3/ (ሐ/ መሠረት የሚያቀርበው የሥነሥርዓት ጥያቄ፦

ሀ/ መረጃ የሚጠይቅ፤

ለ/ አቋሙን የሚያብራራ፤ወይም

ሐ/ በመላምት ላይ የተመሠረተ፤

መሆን የለበትም።

8. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (7/ በሚቀርብ የሥነ-ሥርዓት ጥያቄ ላይ ክርክር ማድረግአይፈቀድም፣ይሁን እንጂ አፈጉባዔው አስፈላጊ መስሎ ከታየው የማብራሪያ ጥያቄሊያቀርብ ይችላል፡፡

9. ማንኛውም አባል ፓርቲው ወይም የፓርላማ ቡድኑን በመወከል ሃሳቡን ለመግለፅ ሲፈልግ በፓርቲው ተጠሪ አማካኝነት ስሙ ለአፈጉባዔው መተላለፍ አለበት።

30.<u>የስብሰባ ሥነ-ምግባር እና ሥነ-ሥርዓት ስለማስከበር</u>

1. አፈጉባዔው ሥነ-ሥርዓት የሚያስከብርበትና ውሳኔውን የሚያስፈፅምበት አስፈላጊው ስልጣን ይኖረዋል።

2. በዚህ ደንብ የተደነገገ ማንኛውም የሥነ-ምግባር ወይም የሥነ-ሥርዓት ድንጋጌ ሲጣስ፣ አፈጉባዔው እንደ አግባቡ ንግግር ያስቆማል፣በስም ጠቅሶም የእርምት ማሳሰቢያ ይሰጣል፡፡

3. በመናገር ላይ የነበረ አባል በአፈጉባዔው የተሰጠውን ማሳሰቢያ ተቀብሎ ይቅርታ ከጠየቀ በኋላ ንግግሩን ሊቀጥል ይችላል፡፡
4. የተሰጠውን የእርምት ማሳሰቢያ የማያከብር አባል በአፈጉባዔው ትዕዛዝ ከስብሰባ እንዲወጣ ይደረጋል።
5. አፈጉባዔው አንድ አባል ከስርዓት ውጭ የሆነ ባህሪ አሳይቷል ብሎ ካመነ ከስብሰባ ሊያስወጣው ይችላል፣ እንዲወጣ የታዘዘው አባልም ወዲያውኑ ከስብሰባው መውጣትአለበት፡፡
6. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (4/ ወይም (5/ የተጠቀሰውን ትዕዛዝ የማያከብር አባልበምክር ቤቱ የክብር ጥበቃ ኃይል ተገዶ እንዲወጣ አፈጉባዔው ሊያዝ ይችላል፡፡
7. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (4/ ወይም (5/ መሰረት የወጣ አባል እንደሁኔታው በቀጣይ በሚካሄዱ እስከ ሁለት የስብሰባ ቀናት በአፈጉባዔው ሊታገድ ይችላል፡፡
8. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (6/ መሠረት ተገዶ ከምክር ቤቱስ ብሰባሰባ እንዲወጣ የተደረገ ማንኛውም አባል በቀጣይ በሚካሄዱ እስከ አምስት የምክር ቤቱ ስብሰባዎች እና ከምክርቤቱ ሥራዎች በአፈጉባዔው ይታገዳል፣ በዚህ ጊዜም ደመወዝ አይከፈለውም፡፡
9. የተፈፀመው የሥነ-ምግባር ወይም የሥነ-ሥርዓት ጥፋት ከባድ ወይም ተደጋጋሚ ሆኖ ሲገኝ እንደ አስፈላጊነቱ አፈጉባዔው በሚያቀርበው ሞሽን ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ መክሮ ውሳኔ ይሰጣል ወይም በህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተመርምሮ እንዲቀርብለት በማድረግ በዚህ ደንብ በአንቀፅ 143 (7/ መሰረት ውሳኔ ያስተላልፋል።
10. ምክር ቤቱ ማንኛውም አባል በሚያቀርበው ሞሽን መሰረት በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ(9/ የተላለፈውን ውሳኔ በማንኛውም ጊዜ ሊያነሳው ይችላል፡፡
11. አፈጉባዔው የተፈጠረው የሥነ-ሥርዓት ችግር አጠቃላይ የዕለቱን የስብሰባ ሂደት በጉላ መልኩ የሚያውክ ወይም በአባላትመካከል ጠብ ሊያስከትል የሚችል ወይም የፅጥታ መደፍረስ ሊፈጠር ይችላል ብሎ ከገመተ ወይም የፅጥታ መደፍረስ የተፈጠረ እንደ ሆነ ስብሰባውን ሊያቋርጥ ይችላል፣ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘም የምክር ቤቱ የክብር ጥበቃ ኃይል ጣልቃ ገብቶ ችግሩን እንዳያስወግድ ሊያዝይ ችላል፡፡

12. አፈጉባዔው የተቋረጠውን ስብሰባ በዕለቱ ማስቀጠል ከቻለ በሚወስነው ሰዓት ስብሰባው እንዲቀጥል ያደርጋል ወይም ለሌላ ጊዜ ሊያስተላልፈው ይችላል፣ ስብሰባው ሲጀመርም ምክር ቤቱ በጉዳዩ ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ያስተላልፋል።

13. በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ (2/ እስከ (9/ የተደነገጉት ከአንድ በላይ በሆኑአባላትወይም የአፈጉባዔው ትዕዛዝ እንዳይከበር ባደረጉ ወይም በተባበሩ አባላት ላይም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

14. በምክር ቤቱ ስብሰባ ሂደት በተጋባዥ እንግዳ ወይም በሠራተኛ የሚፈጸም የሥነ- ምግባር ወይም የሥነ-ሥርዓት ጉድለት ሲከሰት አፈጉባዔው የእርምት ማሳሰቢያ ይሰጣል ወይም ሌሎች አስፈላጊ እርምጃዎችን ይወስዳል፡፡

## ምዕራፍ ስድስት

## ስለ አጀንዳ አቀራረጽ እና ጊዜ አመዳደብ

### 31. አጀንዳ ስለማመንጨት

ምክር ቤቱ የሚወያይባቸው አጀንዳዎች የሚመነጩት፡-

1. በመንግሥት፤
2. በአፈጉባዔው፤
3. በኮሚቴዎች፤
4. በአባላት፤ወይም፤
5. በፓርላማ ቡድን፤

ሊሆንይችላል፡፡

### 32. አጀንዳ አቀራረፅ

1. ምክር ቤቱ የሚወያይበት ማንኛውም አጀንዳ የሚቀረፅው በምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ መሰረት የሚቀረፅ አጀንዳ ለምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ የሚቀርበው፡-
   ሀ/ በዚህ ደንብ በአንቀፅ 31 (1/ እና (5/ የሚመነጭ አጀንዳ በተጠሪዎቻቸው አማካኝነት፤
   ለ/ በዚህ ደንብ በአንቀፅ 31 (2/፣ (3/ እና (4/ የሚመነጭ አጀንዳ በአፈጉባዔው አማካኝነት፤ ይሆናል።
3. አማካሪ ኮሚቴው ለውይይት የሚቀርበውን አጀንዳ በስምምነት ይወሰናል፣ ስምምነት የተደረሰበት አጀንዳ መጽደቅ ሳያስፈልገው በቀጥታ ለምክር ቤቱ ውይይት ይቀርባል፡፡

4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (3/ መሰረት ስምምነት ያልተደረሰበት አጀንዳ በአፈጉባዔው አማካኝነት ለምክር ቤቱ ቀርቦ በምክር ቤቱ አባላት አንድ ሦስተኛ ድምፅ ከተደገፈ በአጀንዳነት ይፀድቃል፡፡

5. በማንኛውም ጊዜ የመንግሥት አጀንዳ ቅድሚያ ተሰጥቶት ለውይይት ይቀርባል፡፡

6. ዕለታዊ አጀንዳ እና የተመደበው የውይይት ጊዜ በአፈጉባዔው አማካኝነት ከምክር ቤቱስብሰባ ከአርባ ስምንት ሰዓት በፊት አባላት እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

7. ምክር ቤቱ የተለየ አቅጣጫ ካላስቀመጠ በስተቀር በምክር ቤቱ ውድቅ የሆነ አጀንዳ በዚያው ዓመት ተመልሶ አይቀርብም፡፡

33.<u>በዕለታዊ አጀንዳ ያልተቀረፀ ጉዳይ እንዲታይ ሞሽን ስለማቅረብ</u>

1. በዕለታዊ አጀንዳ ያልተቀረፀ ነገር ግን የአፈጉባዔውን ፈቃድ ያገኘ ለሕዝብ ጠቀሚታ ያለው አስቸኳይ ጉዳይ በአባላት ወይም በፓርላማ ቡድን ሲቀርብ በምክር ቤቱ ውይይትይደረግበታል።

2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ መሠረት የአፈጉባዔውን ፈቃድ ያላገኘ ሞሽን ወደ ምክር ቤቱ አይቀርብም፣ አፈጉባዔውም ሞሽኑን ያልተቀበለበትን ምክንያት ለመግለፅ አይገደድም።

3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ የተጠቀሰው ሞሽን ከምክር ቤቱ የስብሰባ ቀን ከአስርሰዓት በፊት ለአፈጉባዔው መቅረብ ያለበት ሆኖ የሚከተሉት አካላትም በአፈጉባዔው በኩል እንዲያውቁት መደረግ ይኖርበታል፡-
   ሀ/ የምክር ቤቱ ፅህፈትቤት፤
   ለ/ የመንግሥት ዋናተጠሪ፤እና
   ሐ/ ጉዳዩ የሚመለከተው መንግስታዊ አካል፡፡

4. በዚህ አንቀፅ መሰረት ተቀባይነት ካገኙ ተመሳሳይ ሞሽኖች ውስጥ ቅድሚያ ተሰጥቶት ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ሞሽን በአፈጉባዔው ይወሰናል፡፡

5. በዚህ ደንብ አንቀፅ 45 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አንቀፅ መሰረት የሚቀርብ ሞሽን የሚከተሉትን ማሟላትአለበት፡-
   ሀ/ አንድ አባል በአንድ ጊዜ ከአንድ ሞሽን በላይ ማቅረብ አይችልም፤
   ለ/ ለአንድ የስብሰባ ወቅት የሚቀርብ ሞሽን አንድ ብቻ ነው፤
   ሐ/ በቀረበው ሞሽን ላይ የሚደረገው ውይይት በአንድ ጉዳይ ላይ የተወሰነ መሆን ይገባዋል፤

መ/ የሚቀርበው ሞሽን በፌደራሉ መንግስት የስራ ሃላፊነት ስር የሚወድቅና ወቅታዊመሆን ይገባዋል፤

ሠ/ የልዩ መብት ጥያቀን የሚያነሳ መሆን የለበትም፤

ረ/ ቀደም ሲል እንዲታይ ቀጠሮ የተያዘለት ወይም በሂደት ላይ የሚገኝ ጉዳይ ምንእንደሚሆን የሚተነብይ መሆን የለበትም፡፡

6. በዚህ አንቀፅ መሰረት ፈቃድ ያገኘ ሞሽን አቅራቢ በአፈጉባዔው አማካኝነት ሞሽኑን ለማቅረብ የምክር ቤቱን ፈቃድ እንዲጠይቅ ይደረጋል፡፡

7. አፈጉባዔው የሞሽኑ ፍሬ ነገርግልጽ ካልሆነለት ለጉዳዩ ስምምነቱን ከመስጠቱ ወይም ከመንፈጉ በፊት የቀረበለትን ሞሽን ለምክርቤቱ በንባብ በማቀረብ እና የሚመለከተው መንግስታዊ አካል ወይም አቀራቢው አባል በጉዳዩ ላይ ማብራሪያ እንዲሰጥበት ካደረገ ቦኋላ ውሳኔ ሊሰጥ ይችላል፣ ሞሽኑን ከተቀበለውም በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (6/ መሠረት እንዲቀርብ ፈቃድ ይሰጣል፡፡

8. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (6/ ወይም (7/ መሠረት የአረጉባዔውን ፈቃድ ያገኘማንኛውም ሞሽን በምክር ቤቱ ሃምሳ አባላት ከተደገፈ ለዉይይት ይቀርባል፡፡

9. ለሞሽኑ የሚያስፈልገው የውይይት ጊዜ በአፈጉባ ዔው ይመደባል።

34.<u>የጊዜ አመዳደብ</u>

1. ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ማንኛውም አጀንዳ እንደ ሁኔታው አስፈላጊው የውይይት ጊዜ ይመደብለታል።

2. በዚህ ደንብ የተጠቀሱት ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ለእያንዳንዱ አጀንዳ የሚያስፈልገው የውይይት ጊዜ የሚመደበው በምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ ስምምነት ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ መሰረት ስምምነት ያልተደረሰበት የጊዜ አመዳደብ በአፈጉባዔው አማካኝነት ሁሉም አማራጮች ለምክር ቤቱ ቀርበው በጉዳዩ ላይ ልዩነት ያላቸው አካላት ሃሳባቸውን እንዲያቀርቡ ከተደረገ ቦኋላ በምክር ቤቱ ይወሰናል፡፡

4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ የተደነገገው ቢኖርም የፕሬዚዳንቱ ዓመታዊ የመክፈቻ ንግግር እንዲሁም የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት የጊዜ ገደብ አይደረግበትም፣ ሆኖም በቀረበው ጉዳይ ላይ ለሚደረገው ውይይት አስፈላጊው ጊዜ ይመደባል።

5. ማንኛውም ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ሪፖርት ወይም የውሳኔ ሃሳብ እንደ አስፈላጊነቱ የማቅረቢያና የውይይት ጊዜ ይመደብለታል፡፡
6. ለማንኛውም ረቂቅ ህግ ለእያንዳንዱ ንባብ ደረጃ የሚያስፈልገው የውይይት ጊዜ እንደየአስፈላጊነቱ ይመደባል።
7. የፓርላማ ቡድኖች በምክር ቤቱ ውስጥ ያላቸውን መቀመጫ መሰረት በማድረግ ለሚያቀርቡት ሃሳብ ለአጀንዳው ከተያዘው ጠቅላላ ጊዜ ውስጥ ይመደብላቸዋል።
8. አባላት ሃሳባቸውን ለመግለፅ እንዲችሉ ለአጀንዳው ከተመደበው ጠቅላላ ጊዜ ውስጥ እንደአስፈላጊነቱ የንግግር ጊዜ ይመደብላቸዋል፡፡
9. በቀረበ አጀንዳ ዙሪያ በሚነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ላይ የሚመለከተው አካል መልስወይም አስተያየት ለመስጠት የሚያስፈልገው ጊዜ ለጉዳዩ ከተመደበው አጠቃላይ ጊዜ ውስጥ የሚመደብ ይሆናል፡፡

## 35. ለተቃዋሚዎች የተመደበ ቀን

1. በምክር ቤቱ መቀመጫ ያላቸው ተቃዋሚ ፖርቲዎች በሚያቀርቡት አጀንዳ ምክርቤቱ በየወሩ ለአንድ ሰዓት ውይይት ያደርጋል፣ ይህም ቀን የተቃዋሚዎች ቀን ተብሎ ይጠራል፡፡
2. በተቃዋሚዎች ቀን ውይይት የሚደረግበት አጀንዳ በምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴውስጥ ያሉ አብዛኛዎቹ የተቃዋሚ ፓርቲ ወይም የፓርላማ ቡድን ተወካዮች ቅድሚያ የሚሰጡት የተቃዋሚ አጀንዳ ይሆናል። ሆኖም አንድ ተቃዋሚ ፓርቲ ወይም የፓርላማ ቡድን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ አጀንዳ የማስያዝ እድል ይኖረዋል።
3. ለተቃዋሚዎች በተመደበው ቀን አስቸኳይ አጀንዳ በመኖሩ ምክንያት ጊዜው የሚተየር ከሆነ የሚተየረው ጊዜ ከሚቀጥለው ወር ሊያልፍ አይችልም።

## 36. የንግግር ጊዜ

1. አፈጉባዔው በዚህ ደንብ በአንቀፅ 34 መሰረት የተወሰነውን የጊዜ አጠቃቀም ያስፈጽማል።
2. የፓርቲ ወይም የፓርላማ ቡድን መሪዎች ወይም ተጠሪዎች ወይም ተወካዮች ፓርቲያቸውን በመወከል ሃሳብ እንዲያቀርቡ ቅድሚያ እድል ይሰጣቸዋል፣ በመቀጠልም ሌሎች አባላት ሃሳብ እንዲየቀርቡ እድል ሊሰጣቸው ይችላል፡፡

3. በዚህ ደንብ በአንቀፅ 34 (7/ መሠረት ለፓርቲ የተመደበው የጊዜ አጠቃቀም በፓርቲው ወይም በፓርላማ ቡድኑ ይወሰናል፡፡
4. አፈጉባዔው በዚህ ደንብ አንቀፅ 34 (8/ መሰረት ሌሎች አባላት ጥያቄዎችንና አስተያየቶችን እንዲያቀርቡ እድል ይሰጣል፡፡
5. ማንኛውም ተናጋሪ በተመደበለት ጊዜ ውስጥ ንግግር ሲያደርግ ከእርሱ ውጭ በሆነ ምክንያት የባከነው ጊዜ በአፈጉባዔው ይካካስለታል፡፡
6. አፈጉባዔው የሚሰጣቸው ገለፃዎች እንዲሁም በማንኛውም አካል ወይም ግለሰብ ለምክርቤቱ እንዲሰጥ የተፈለገ ማብራሪያ ወይም ምስክርነት የንግግር የጊዜ ገደብ አይደረግበትም፡፡
7. አንድ አባል በአንድ ጉዳይ ላይ ከአንድ ጊዜ በላይ የመናገር እድል አይኖረውም፡፡ ሆኖም ተናጋሪው አዲስ ሃሳብ ሳይጨምር ቀደም ብሎ በተናገረው ጉዳይ ሃሳቡን ለማስተካከል ወይም በሃሳቡ ዙርያ የእርምት አስተያየት ለማቅረብ ሲፈልግ አፈጉባዔዉ ድጋሚ የንግግር እድል ሊሰጠው ይችላል፡፡
8. ለእያንዳንዱ ንግግር የተቀመጠው የጊዜ ገደብ ሲጠናቀቅ አፈጉባዔው ንግግር ያስቆማል፤ሆኖም አስፈላጊ መስሎ ከታየው ተጨማሪ የንግግር ጊዜ ሊሰጥይ ችላል፡፡

## ምዕራፍ ሰባት

## ስለሞሽን

### 37.ትርጓሜ

1. ሞሽን ማለት ምክርቤቱ በአንድ ጉዳይ ላይ ውይይት እንዲያካሂድበት ብቻ ወይም ተወያይቶ ውሳኔ እንዲያሳልፍበት በመንግሥት ወይም በአባላት ወይም በፓርላማ ቡድን የሚቀርብ ማንኛውም ሃሳብ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ የተጠቀሰው ሞሽን ክርክር የሚደረግበት ወይም ክርክር  የማይደረግበት ሊሆን ይችላል፡፡

### 38.የሞሽን ዓይነቶች

ምክር ቤቱ ተወያይቶ ውሳኔ ወይም አስተያየት እንዲሰጥበት የሚጠይቅ ሞሽን፦

1. መሰረታዊ ሞሽን፤
2. የምክር ቤቱን አሰራር የሚመለከት ሞሽን፤
3. የማሻሻያ ሞሽን፤ወይም

4. ንዑስ ማሻሻያ ሞሽን፤

ሊሆንይችላል፡፡

## 39. የሞሽን አቀራረብ

1. በዚህ ደንብ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር የሞሽን አቀራረብ በዚህ አንቀፅ መሰረት ይመራል፡፡
2. ማንኛውም ሞሽን እንደ ሁኔታው በምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ በአጀንዳ ተቀርጾ ወይም በአፈ-ጉባዔው ሲፈቀድ ሊቀርብ ይችላል።
3. ማንኛውም ሞሽን እንደ ሁኔታው በቃል ወይም በጽሑፍ ማስታወቂያ ሊቀርብ ይችላል።
4. ማንኛውም የሞሽን ማስታወቂያ የሞሽኑን መስረታዊይዘት ያካተተ እና ምክር ቤቱ በሞሽኑ ላይ ውሳኔ መስጠት ያለበት መሆኑን ወይም አለመሆኑን በግልጽ የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡
5. የሚከተሉት የሞሽን ዓይነቶች ማስታወቂያ ሳያስፈልጋቸው ለምክርቤቱ ሊቀርቡይችላሉ፡-

ሀ/ የማሻሻያ ሞሽን፤

ለ/ ንዑስ ማሻሻያ ሞሽን፤

ሐ/ የሥነ-ሥርዓት ጥያቄ የሚያነሳ ሞሽን፤

መ/በአለታዊ አጀንዳ የተቀረጸን ጉዳይ ለሌላጊዜ እንዲተላለፍ ወይም በተያዘው ቅደምተከተል እንዲፈጸም ወይም ቅድሚያ እንዲሰጠው የሚጠይቅ ሞሽን፣

ሠ/ በኮሚቴ በቀረበ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ ውይይት ከተደረገ ቦኋላ ውሳኔ እንዲሰጥበት የሚጠይቅ ሞሽን፤

ረ/ አንድ ረቂቅ ህግ ወደኮሚቴ ሳይመራ በቀጥታ ወደ ሁለተኛ ንባብ ተሸጋግሮ ዝርዝር ውይይት እንዲደረግበት የሚጠይቅ ሞሽን

ሰ/ ምክር ቤቱ በአንድ አጀንዳ ላይ በቂ ውይይት ስላደረገ ውይይቱ ቆሞውሳኔእንዲተላለፍ የሚጠይቅ ሞሽን፤

ሸ/ በአጀንዳ ላይ ውይይት ከተደረገ ቦኋላ ውሳኔው ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ የሚጠይቅሞሽን።

6. አንድ አባል በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ሞሽን ማቅረብ አይችልም።
7. የምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ ወይም አፈጉባዔው የምክርቤቱን ደንብ ወይም ልማዳዊ አሰራር የሚቃረንሞሽን ሲቀርብ ሞሽኑን እንደ ሁኔታው

ሊያሻሽለው ወይም ሞሽኑን ያቀረበው አካል አስተካክሎ እንዲያቀርብ ሊያደርግይ ችላል፡፡

8. በቀረበው ሞሽን ላይ የሚደረገው ውይይት በአንድ ጉዳይ ላይ ብቻ የተወሰነ መሆን አለበት፡፡

40.<u>መሠረታዊ ሞሽን</u>

መሰረታዊ ሞሽን ማለት እራሱን የቻለ እና በሌላ ሞሽን ላይ ወይም ምክር ቤቱ በሚወያይበት ማንኛውም አጀንዳ ላይ ያልተመሰረተ ሆኖ የምክር ቤቱን ውሳኔ ወይም አስተያየት የሚጠይቅ እና የማሻሻያ ሞሽን ሊቀርብበት የሚችል ሞሽን ነው።

41.<u>ስለማሻሻያ ሞሽን</u>

1. የአፈጉባዔውን ፈቃድ ያገኘ መሠረታዊ ሞሽን ላይ የማሻሻያ ሞሽን ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. በውይይቱ ማጠቃለያም ሞሽኑን ያመነጨው አካል መልስ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡
3. ለምክር ቤቱ የሚቀርብ የማሻሻያ ሞሽን፦

   ሀ/ በቀረበው ሞሽን የተካተቱ ቃላት እንዲወጡ፤

   ለ/ በቀረበው ሞሽን የሚገኙ ቃላት እንዲሠረዙና በሌላ ቃላት እንዲተኩ፤ ወይም

   ሐ/ በቀረበው ሞሽን ቃላት እንዲጨመሩ የሚጠይቅ ሞሽን ሊሆን ይችላል፡፡
4. ማንኛውም ማሻሻያ ሞሽን፦

   ሀ/ከቀረበው ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያለው፤

   ለ/አዲስ ጉዲይ እንዲካተት የማይጠይቅ፤

   ሐ/የቀረበውን የመሠረታዊ ሞሽን ወሰን የማያሰፋ፤

   መ/የቀረበውን ሃሳብ የበለጠ ግልጽ የሚያደርግ፤

   መሆንይኖርበታል።

42.<u>ስለ ንዑስ ማሻሻያ ሞሽን</u>

1. በአፈጉባዔው ፈቃድ በቀረበ የማሻሻያ ሞሽን ላይ ንዑስ የማሻሻያ ሞሽን ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም ንዑስ ማሻሻያ ሞሽን፡-

   ሀ/ ከማሻሻያ ሞሽንጋርበቀጥታ አግባብነት ያለው፤

   ለ/ የማሻሻያ ሞሽኑን ብቻ ለማሻሻል ያለመ እና መሰረታዊ ሞሽኑን የማይነካ፤

ሐ/ ማሻሻያ ሞሽኑን ወሰን የማያሰፋ ሆኖ አዲስ እና የተለየ ሃሳብ የማያካትት፤

መ/ የማሻሻያ ሞሽኑን ሙሉ በሙሉ የማይሰርዝና ውድቅ የማያደርግ፤

መሆን ይኖርበታል።

3. በንዑስ ማሻሻያ ሞሽን ላይ የሚካሄደው ውይይት በቀረበው የማሻሻያ ጉዳይ ላይ ብቻ ያተኮረ መሆን አለበት፡፡
4. በንዑስ ማሻሻያ ሞሽን ላይ ሌላ ማሻሻያ አይቀርብም።

43.<u>ስለማሻሻያ እና ንዑስ ማሻሻያ ሞሽኖች ተጨማሪ ሥነ-ሥርዓት</u>

1. ማንኛውም ማሻሻያ ወይም ንዑስ ማሻሻያ ሞሽን እንዲሻሻል የተፈለገውን ጉዳይ በቃል ወይም በጽሑፍ በመግለጽ ለአፈጉባዔው መቅረብ አለበት፡፡
2. ማሻሻያ ሞሽን ሲቀርብ በመሰረታዊ ሞሽን ላይ የሚደረገው ውይይት እንደዚሁም ንዑስ ማሻሻያ ሞሽን ሲቀርብ በማሻሻያ ሞሽን ላይ የሚደረገው ውይይት ይቋረጣል፤ በማሻሻያ ሞሽኑ ላይ ወይም በንዑስ ማሻሻያ ሞሽኑ ላይ አንደ ቀደም ተከተላቸው ውይይት ተደርጎ ውሳኔ ከተሰጠ በኋላ በመሠረታዊ ሞሽኑ ላይ ውይይት ይቀጥላል።
3. በዚህ ደንብ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ የማሻሻያ ሞሽንወይም ንዑስ ማሻሻያ ሞሽን ሊቀርብ አይችልም። ሆኖም በማሻሻያው ላይ የሚደረገውውይይት ሲጠናቀቅ ሌላ ማሻሻያ ወይም ንዑስ ማሻሻያ ሊቀርብ ይችላል፡፡

44.<u>የምክር ቤቱን አሰራር የሚመለከት ሞሽን</u>

1. የምክር ቤቱን አሰራር የሚመለከት ሞሽን ማለት ምክር ቤቱ የሚወያይበትን አጀንዳ ወይም ሂደት በተመለከተ የሚቀርብ የሥነ-ሥርዓት ጥያቄ ሲሆን ውሳኔ የሚያገኘውም በአፈጉባዔው ይሆናል፡፡
2. የዚህ ደንብ አንቀፅ 29 (7/ እና (8/ ድንጋጌዎች የምክር ቤቱን አሰራር የሚመለከትሞሽን ላይ ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

45.<u>የሞሽን መመዘኛ</u>

በዚህ ደንብ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ሞሽን፡-

1. በፌደራል መንግሥት የሥልጣን ክልል ስር የሚወድቅ ጉዳይን የሚመለከት፤
2. አንድ መሠረታዊ የሆነ ጉዳይን ብቻ የያዘ፤
3. ግልጽና የተብራራ፤
4. ለሚቀርበው ሃሳብ አስፈላጊ ያልሆኑ መግለጫዎችን፣ጥቅሶችን ወይምሌሎች ጉዳዮችን ያልያዘ፤

5. የምክር ቤቱን የወደፊት ውሳኔ የማይተነብይ፤
6. በተመሳሳይ የምክር ቤቱ የስራ ዓመት ተቀባይነት ያገኘ ወይም ውድቅ ከተደረገ ጉዳይጋር በይዘቱ ተመሳሳይ የሆነ ጉዳይን የማይመለከት፤
7. አግባብነት የሌላቸው ወይም አላስፈላጊ አገላለጾችን ያልያዘ፤
8. በህግ መሠረት ሙሉ ወይም ከፊል የዳኝነት ወይም አስተዳደራዊ ፍርድ የመስጠት ሥራን በሚሠራ ወይም አንድን ጉዳይ እንዲያጣራ ወይም እንዲመረምር በተቋቋመ አካል በመታየት ላይ ያለን ጉዳይ የማይመለከት፤ መሆን ይኖርበታል።

## ምዕራፍ ስምንት

## ስለ ውሳኔ አሠጣጥ

### 46.ዉሳኔ ስለማሳለፍ

1. እያንዳንዱ አጀንዳ በዚህ ደንብ በአንቀፅ 23 (7/ እና (8/ መሰረት ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡
2. ማንኛውም አባል በአጀንዳው ላይ በቂ ውይይት ተደርጓል ብሎ ሲያምን ውይይቱ ተቋርጦ ውሳኔ እንዲሰጥ ሞሽን ማቅረብ ይችላል፣ ይህም ሞሽን በአፈጉባዔው ተቀባይነት ካገኘበጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይተላለፋል፡፡
3. በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 59 (1/ መሰረት ማንኛውም ውሳኔ የሚተላለፈው በምክር ቤቱ አባላት የአብላጫ ድምፅ ነው፡፡
4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (3/ የተደነገገው ቢኖርም የሚከተሉትን ጉዳዮች ለመወሰን የምክርቤቱ የሁለት ሦስተኛ ድምፅ ድጋፍ ያስፈልጋል፡-
   ሀ/ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 104 የሰፈረውን የሕገመንግሥት ማሻሻያ ሃሣብ ማመንጨት በተመለከተ፤
   ለ/ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 93 (2/ (እና (3/ ላይ የተመለከተውን የአስቸኳይጊዜአዋጅ ለማፅደቅ እንዲሁም የጊዜ ገደቡን ለማራዘም፤
   ሐ/ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 105 (1/ (ለ/ መሠረት የመሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶችን፣የሕገመንግሥቱ አንቀፅ 104 እና አንቀፅ 105 ድንጋጌዎችን ለማሻሻል፤ እና
   መ/ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 78 (2/ መሠረት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት እናየመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በአገሪቱ በሙሉ ወይም በከፊል እንዲደራጅ ለመወሰን፡፡

5. የምክር ቤቱ ድምፅ አሰጣጥ እንደ ሁኔታው እጅ በማውጣት ወይም በሚስጥር ድምጽ በመስጠት ይከናወናል፡፡
6. የድምጽ አቆጣጠር የሚከናወነው አፈጉባዔው በሚመድበው የፅህፈት ቤቱ ሰራተኛ አማካኝነት ይሆናል፡፡
7. በውሳኔ ወቅት ድምፅ እኩል በእኩል ሲሆን አፈጉባዔው የሚደግፈው ወገን የምክርቤቱ ውሳኔ ይሆናል፡፡
8. ምክርቤቱ ውሳኔውን በስምምነት ለማሳለፍ ሲፈልግ አፈጉባዔው ተቃውሞ ካለ ጠይቆየሚቃወም ከሌለ ምክርቤቱ ሙሉ የድምጽ ድጋፍ እንደሰጠ ይቆጠራል። ሆኖም ተቃውሞ ከቀረበ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (5/ መሠረት ድምጽ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡
9. ድምፅ የሚሰጥበት ጉዳይ ክፍል በክፍል መፅደቅ የሚገባው ሲሆን የውሳኔ አሰጣጥ ሂደቱ በዚሁ መልክ ይከናወናል፡፡ በመጨረሻም በጉዳዩ ላይ በአጠቃላይ ድምፅ በመስጠት ይፀድቃል፡፡
10. ምክርቤቱ ተወያይቶ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮች ቀንና ተከታታይ መለያ ቁጥር እየተሰጣቸው ይመዘገባሉ።
11. በዚህ አንቀፅ የተደነገጉት ለኮሚቴም ተጣጥመው ተግባራዊ ይሆናሉ።

47.<u>ለውሳኔ የሚያስፈልግ የመነሻ ሃሳብ ስለሚቀርብበት ሁኔታ</u>

1. ምክር ቤቱ ለውሳኔ የሚያስፈልግ የመነሻ ሃሳብ ለማግኘት የሚከተሉትን ስልቶች ሊጠቀም ይችላል፦
   ሀ/ የተለያዩ ሊሰሙ፣ ሊነበቡ እና ሊታዩ የሚችሉ ማስረጃዎች ከሚመለከተው አካል እንዲቀርቡ በማድረግ፤ ወይም
   ለ/ በተለያዩ ኮሚቴዎች አማካኝነት ጉዳዩ ተጣርቶ እንዲቀርብ በማድረግ፡፡
2. የምክር ቤቱ ኮሚቴዎች በጋራ እንዲሰሩ ሲወሰን ጉዳዩን በዋናነት የሚመራውና የሚያስተባብረው ኮሚቴ ተለይቶ መገለጽ አለበት፡፡
3. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች ለኮሚቴም ተጣጥመው ተግባራዊ ይሆናሉ።

48.<u>ውሣኔን ለሌላ ጊዜ ስለማስተላለፍ</u>

1. በሚከተሉት ምክንያቶች በምክር ቤቱ በተያዘ አጀንዳ ላይ የሚሰጥ ውሳኔ ለሌላ ጊዜ ሊተላለፍ ይችላል፦
   ሀ/ አጀንዳው ተጨማሪ ውይይት የሚያስፈልገው መሆኑ በሞሽን ሲጠየቅና ምክርቤቱ ሲወስን፤

ለ/ ስብሰባው ሲጀመር የነበረው ምልዓተ ጉባዔ ውሳኔ ለመስጠት የማያስችል ስለመሆኑ ሞሽን ቀርቦ ጉድለቱ ሲረጋገጥ፤

ሐ/ በዚህ ደንብ በአንቀፅ 30 (11/ የተጠቀሰው ሁኔታ የተፈጠረ እንደሆነ፤

መ/ ለውሳኔ አሰጣጥ ይረዳ ዘንድ እንዲቀርብ የተፈለገው ማስረጃ ያልቀረበ መሆኑ በሞሽን ሲጠየቅና በምክር ቤቱ ሲወሰን፤

ሠ/ በስነስርዓት ጥያቄዎች ምክንያት ውይይቱ እንዲቋረጥ ምክር ቤቱ የወሰነ እንደሆነ፤

ረ/ በአጀንዳው ዙሪያ የተጀመረው ውይይት ሳያልቅ በቅድሚያ መታየት የሚገባው አስቸኳይ የሆነ አጀንዳ የተፈጠረ እንደሆነ፤

ሰ/ ውይይቱ በመካሄድ ላይ እያለ በምክር ቤቱ አባላት ወይም ተጋባዥ እንግዶች ላይ ያልታሰበ እና ከባድ የሆነ አደጋ የተፈጠረ እንደሆነ።

2. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች ለኮሚቴም ተጣጥመው ተግባራዊ ይሆናሉ።

## 49.ውሳኔ የተሰጠበትን ጉዳይ እንደገና ስለማየት

1. ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ እንደገና እንዲታይ ወደ ምክር ቤቱ ሊቀርብ አይችልም።

2. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀፅ (1/ የተደነገገው ቢኖርም በሚከተሉት ሁኔታዎች ውሳኔ የተሰጠበት ጉዳይ እንደገና እንዲታይ ለምክር ቤቱ ሊቀርብ ይችላል፦

ሀ/ ምክር ቤቱ ውሳኔ ሲሰጥ የነበረው ጉድለት ታርሞ ወይም ተሟልቶ እንደገና ከቀረበ፣

ለ/ ቀደም ሲል በተወሰነው ጉዳይ ላይ ምክር ቤቱ መሠረታዊ የህግ ወይም የፍሬ ነገር ስህተት መፍጠሩ ከታወቀ

ሐ/ መንግስት በጉዳዩ ላይ በቂ ማብራሪያ በመስጠት እንደገና እንዲታይለት ሲጠይቅ።

3. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2/ በተጠቀሱት ምክንያቶች እንደገና የሚታይ ጉዳይ በዚህደንብ በአንቀፅ 32 መሠረት ለምክር ቤቱ ይቀርባል፡፡

4. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች ለኮሚቴም ተጣጥመው ተግባራዊ ይሆናሉ።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## ስለ ህግ አወጣጥ

## 50.ህግ ማውጣት የሚያካትታቸው ጉዳዮች

ህግ ማውጣት የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

1. አዲስ ህግ ማውጣት፤

2. ነባር ህግ ማሻሻል ወይም መሻር፤

3. ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን ማጽደቅ፤

4. ውሳኔ ማስተላለፍ፡፡

## 51.<u>ህግ ስለማመንጨት</u>

1. ህግ ማመንጨት በዋናነት የመንግስት ተግባር ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ የተደነገገው ቢኖርም፦

   ሀ/ አባላት፤

   ለ/ ኮሚቴዎች፤

   ሐ/ የፓርላማ ቡድኖች፤

   መ/ በህግ ሥልጣን የተሰጣቸው ሌሎች አካላት፤

   ህግ የማመንጨት ሥልጣን አላቸው፡፡
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ የተደነገገው ቢኖርም የፋይናንስ ህጎችን የማመንጨት ሥልጣን የመንግሥት ብቻ ነው።
4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ መሰረት የሚመነጭ ረቂቅ ህግ በሚኒስትሮች ምክርቤት ማህተም ተደግፎ መቅረብ አለበት።
5. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ (ሀ/ መሠረት የሚመነጭ ረቂቅ ህግ በጽሑፍ ሆኖ በአባሉ ፊርማ ተደግፎ ለአፈ ጉባዔው መቅረብ አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ (ለ/ መሠረት የሚመነጭ ረቂቅ ህግ በኮሚቴውሊ ቀመንበር ተፈርሞ ለአፈ ጉባዔው መቅረብ አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ (መ/ መሠረት የሚመነጭ ረቂቅ ህግ በተቋሙ የበላይ ሃላፊ ፊርማ ተደግፎ ለአፈጉባዔው መቅረብ አለበት፡፡
8. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ (ሐ/ መሠረት የሚመነጭ ረቂቅ ህግ በመሪው ወይም በተጠሪው ፊርማ የተደገፈ መሆን አለበት፡፡
9. ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ማንኛውም ረቂቅ ህግ በአማርኛና በእንግሊዘኛ ቅጅ የተዘጋጀ ሆኖ ራሱን የቻለ ማብራሪያ ሊኖረው ይገባል።
10. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (9/ የተገለፀው የረቂቅ ህግ ማብራሪያ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦

    ሀ/ የረቂቅ ህጉ አስፈላጊነት፤

    ለ/ የረቂ ህጉ ዓላማ፤

    ሐ/ ረቂቅ ህጉ የፖሊሲ መነሻ፤

    መ/ የረቂቅ ህጉ ይዘት፤

ሠ/ በረቂቅ ህጉ የዝግጅት ሂደት የሚመለከታቸው አካላት ተሳትፎና አጠቃላይ አስተያየት፤እና

ረ/ ሊሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች።

52.<u>የምክር ቤቱ ንባቦች</u>

አንድ ረቂቅ ህግ በሚከተሉት ሦስት የንባብ ደረጃዎች ሊያልፍ ይችላል፦

1. የመጀመሪያ ንባብ፤
2. ሁለተኛ ንባብ፤ እና
3. ሦስተኛ ንባብ።

53.<u>የመጀመሪያ ንባብ</u>

የመጀመሪያ የንባብ ደረጃ እንደሚከተለው ይከናወናል፡-

1. በአጀንዳ የተያዘውን ረቂቅ ህግ ያመነጨው አካል ስለ ረቂቅ ህጉ ዓላማና ይዘት አጭር ማብራሪያ ያቀርባል፤
2. ረቂቅ ህጉ በአስቸኳይነቱ ምክንያት ከአርባ ስምንት ሰዓት በፊት ለአባላት ያልደረሰ ከሆነ ሰነዱ ለምክር ቤቱ በንባብ ይቀርባል፤
3. በቀረበው ረቂቅ ህግ ዓላማና ይዘት ላይ አጠቃላይ ውይይት ይደረጋል፤
4. በረቂቅ ህጉ ላይ በቂ ውይይት ተደርጓል ተብሎ በአፈጉባዔ ውሲታመን ወይም ሞሽንቀርቦ ተቀባይነት ካገኘ ረቂቅ ህጉ ለዝርዝር ምርመራ ወደ ኮሚቴ ሊመራ ይችላል፤
5. ረቂቅ ህጉ ወደሚመለከተው ኮሚቴ ለዝርዝር ምርመራ ሲመራ ቀጥር ይሰጠዋል፣ በኮሚቴዎች በጋራ እንዲታይ ሲወሰንም ዝርዝር ምርመራውን በዋናነት የሚመራናየሚያስተባብር ኮሚቴ ተለይቶ ይገልፃል።
6. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (4/ የተደነገገው ቢኖርም ረቂቅ ህጉ ወደ ኮሚቴ ሳይመራወደ ሁለተኛ ንባብ እንዲሸጋገር የሚጠይቅ ሞሽን ለምክር ቤቱ ቀርቦ ተቀባይት ካገኘ ምክር ውሳኔ ሊያሳልፍ ይችላል።

54.<u>ሁለተኛ ንባብ</u>

የሁለተኛ የንባብ ደረጃ እንደሚከተለው ይከናወናል፡-

1. በረቂቅ ህጉ ላይ ዝርዝር ውይይት ይካሄዳል፤
2. በዚህ ደንብ በአንቀፅ 53 (6/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በረቂቅ ህጉ ላይ የተዘጋጀ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሣብ በሚመለከተው ኮሚቴ ወይም ኮሚቴዎች አማካኝነት ለምክር ቤቱ ይቀርባል፤

3. በቀረበው ሪፖርትና የውሳኔ ሃሣብ መነሻነት በረቀቀ ህጉ ላይ ዝርዝር ውይይት ይካሄዳል፤

4. በቀረበው ረቂቅ ህግ ወይም ሪፖርት እና የውሳኔ ሃሳብ ላይ የማሻሻያ ሞሽን ማቅረብ ይቻላል፤

5. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (4/ የቀረበው ማሻሻያ ሞሽን ተቀባይነት ካገኘና ተጨማሪ ምርመራ ያስፈልጋል ተብሎ ምክር ቤቱ ከታመነ ረቂቅ ህጉ እንደገና እንዲታይ ወደኮሚቴ ይመራል፡፡

6. በረቂቅ ህጉ ላይ የሚደረገው ውይይት በቂ መሆኑ በምክር ቤቱ ከታመነ በድምፅይወሰናል፡፡

## 55.ሦስተኛ ንባብ

የሦስተኛ የንባብ ደረጃ እንደሚከተለው ይከናወናል፡-

1. በዚህ ደንብ አንቀፅ 54 (5/ መሠረት ረቂቅ ህጉ ዳግም የተመራለት ኮሚቴ የመጨረሻ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሣቡን ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤

2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ መሠረት በቀረበው ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ላይ ምክር ቤቱ በቂ ውይይት ካካሄደ በኋላ ውሳኔ ይተላለፋል፡፡

## 56.ድምፅ አሰጣጥ

ምክር ቤቱ ረቂቅ ሲያፀድቅ ክርክር በተደረገባቸው አንቀፆች ላይ አንቀፅ በአንቀፅ ውሳኔ ያስተላልፋል፤ በመጨረሻም በረቂቅ ህጉ በጠቅላላው ድምፅ በመስጠት ህግ ሆኖ እንዲወጣሊ ያደርግ ይችላል፡፡

## 57.ረቂቅ ህግ የመመርመሪያ ጊዜ

1. በምክር ቤቱ በአስቸኳይነቱ የሚታመንበት ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ረቂቅ ህግ የተመራለት ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን አጥንቶ የውሳኔ ሃሳቡን ለምክር ቤቱ ለማቅረብ ቢያንስ ሃያ የሥራ ቀናት ይሰጠዋል።

2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ የተደነገገው ቢኖርም የረቂቅ ህጉን ስፋትና ክብደት ከግምት ውስጥ በማስገባት ተጨማሪ ጊዜ በአፈጉባዔው ሊፈቀድ ይችላል፡፡

## 58.የፀደቀ ህግ ለሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ፊርማ ስለማቀረብ

1. አፈጉባዔው በምክር ቤቱ የፀደቀን ህግ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 57 መሠረት ለሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ፊርማ ያቀርባል።

2. ፕሬዚዳንቱ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ መሠረት የቀረበለትን ህግ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ በመፈረም ለአፈጉባዔው ይመልሳል።

3. ፕሬዚዳንቱ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ካልፈረመ ህጉ በስራ ላይ ይውላል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (3/ መሠረት በስራ ላይ የሚውል ህግ በአፈጉባዔው ስምና ፊርማ ይወጣል።
5. ህጉ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከመውጣቱ በፊት አስፈላጊ የሆኑ የቴክኒክ እርምቶች በአፈጉባዔው አማካኝነት ሊከናወኑ ይችላሉ፡፡

59.<u>ስለ ሕገመንግሥት ማሻሻያ</u>

1. የሕገመንግሥት ማሻሻያ በሚኖርበት ጊዜ እያንዳንዱ የሕገመንግሥት ማሻሻያ ቁጥር ተሰጥቶት በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ መታተም ይኖርበታል።
2. እያንዳንዱ የሕገመንግሥት ማሻሻያ በሚታተመው ሕገመንግሥት መጨረሻ ላይ“ማሻሻያ” የሚል ርዕስ ተሰጥቶት ይካተታል፡፡
3. የተሻሻሉት የሕገመንግሥት አንቀፆች እንደነበሩ ይቀመጣሉ፣ማሻሻያ የተደረገባቸው መሆኑን የሚገልፅ ምልክት ሊደረግ ይችላል፡፡

60.<u>ደንብና መመሪያ ስለማውጣት</u>

1. ምክር ቤቱ በሚያወጣው ህግ ማስፈፀሚያ ደንብና መመሪያ በውክልና እንዲወጣ ስልጣን ሊሰጥ ይችላል፡፡
2. ደንብና መመሪያ እንዲወጣ በህግ ምክር ቤቱ የውክልና ስልጣን በግልፅ ካልሰጠ በስተቀር ማንኛውም አካል ደንብ ወይም መመሪያ ማውጣት አይችልም።
3. ምክር ቤቱ በሚያወጣው ህግ በውክልና ደንብና መመሪያ እንዲወጣ ስልጣን ሲሰጥ ደንቡን እና መመሪያውን የሚያወጡ አካላትን በግልፅ ማመልከት አለበት፡፡
4. ማንኛውም የሚወጣ ደንብ የአዋጁን ወሰን የጠበቀና የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል።
5. ማንኛውም የሚወጣ መመሪያ የአዋጁን እና የደንቡን ወሰን በጠበቀና የተጣጣመ መሆን ይኖርበታል።
6. ምክርቤቱ በሚያወጣው ህግ ላይ ደንብና መመሪያ እንዲወጣ ሲወሰን የተጠቀሰው ደንብና መመሪያ ህጉ በስራ ላይ በዋለ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ መውጣት አለበት፡፡
7. ማንኛውም መመሪያ ለማንኛውም ሰው ተደራሽ መሆን ይኖርበታል፣ ተደራሽነቱንም የሚመለከተው ተቋም የበላይ ኃላፊ የማረጋገጥ ግዴታ ይኖርበታል።

8. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (7/ የተደነገገውን የመመሪያዎች ተደራሽነት ኃላፊነት ያልተወጣ ተቋም የበላይ ኃላፊ ተጠያቂነት ይኖርበታል።

## 61.<u>ህግ ስለ ማሳተም</u>

1. በምክር ቤቱ የፀደቀ ህግ በአፈጉባዔው አማካኝነት በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ይታተማል።
2. ምክርቤቱ ህጎችን የሚያትምበት የራሱ ማተሚያ ቤት ይኖረዋል፤ ይህ ካልሆነ በሌላተቋም እንዲታተም ያደርጋል፡፡
3. ቅድሚያ ተሰጥቶት በአስቸኳይ እንዲታተም የሚፈለግ ህግ ሲኖር አፈጉባዔው ለሚመለከተው አታሚ አካል መመሪያ ይሰጣል፡፡
4. በምክር ቤቱ ውሣኔ መሠረት ህጉ በአማርኛና በእንግሊዝኛ ቅጅዎች ተዘጋጅቶ ወደ ማተሚያ ቤት ይላካል።
5. ፅህፈት ቤቱ የህጎችን ትርጉምና ህትመት ይከታተላል፡፡

## 62.<u>ህጎችን ስለማሠራጨት</u>

1. አግባብነት ባለው አካል የወጡ ህጎች በሚመለከተው የአስፈፃሚ አካል ይሰራጫሉ፡፡
2. ምክር ቤቱ የወጡ ህጎች በአግባቡ እየተሠራጩ ስለመሆናቸው አስፈላጊውን ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ የተደነገገውን አፈፃፀም በዋናነት የሚመለከተው ኮሚቴ ይከታተላል።

## 63.<u>የህጎችን ዝርዝር ስለመያዝ</u>

ምክር ቤቱ በየዓመቱ የሚያወጣቸውን ህጎች ዝርዝር ይይዛል፤ የሚመለከታቸው አካላት እንዲያውቁትም ያደርጋል፡፡

## 64.<u>ስለምክር ቤቱ ውሳኔ</u>

1. ምክር ቤቱ በተለያዩ ጉዳዮች ላይ ውሳኔዎችን ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡
2. የምክር ቤቱ ውሳኔ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡-

   ሀ/ ፖሊሲን ማፅደቅ ወይም ውድቅ ማድረግ፤

   ለ/ እርምጃ እንዲወስድ መጠየቅ፤

   ሐ/ ለአንድ ጉዳይ ወይም ሁኔታ መንግስት ትኩረት እንዲሰጥ መጠየቅ፤

   መ/ አንድን የመንግስት ተግባር መደገፍ ወይም መቃወም፤

   ሠ/ የአቋም መግለጫ፤

   ረ/ ምክረ ሃሳብ፤

ሰ/ መልዕክት ማስተላለፍ፡፡

## 65.ስለ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አፀዳደቅ ሥነ-ሥርዓት

የዚህ ደንብ የህግ አወጣጥ ሥነ-ሥርዓት ድንጋጌዎች እንደ አግባቡ ምክር ቤቱ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 55(10) መሠረት በሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የአፀዳደቅ ሂደት ላይም ተፈፃሚነት ይኖራቸዋል።

## ምዕራፍ አስር

## የበጀት አፀዳደቅ ሂደት

## 66.የበጀት አቀራረብ

1. በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 77 (3) መሠረት የፌደራል መንግሥት ረቂቅ በጀት በሚኒስትሮች ምክር ቤት ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ይቀርባል፡፡
2. አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር የበጀት ዓመቱ ከመጀመሩ ከአንድ ወር በፊት ረቂቅ በጀቱ በጥቅል እና በዝርዝር ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ መቅረብ አለበት፡፡

## 67.የውይይት ጊዜ

በረቂቅ በጀት ላይ ለሚደረግ ውይይት የሚመደበው ጊዜ ከሁለት ቀን ያላነሰ ይሆናል፡፡

## 68.የበጀት መግለጫ

1. ረቂቅ በጀቱ ለምክር ቤቱ ከደረሠ በኋላ አፈጉባዔው በሚወስነው ቀን እና በሚመድበው ሠዓት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስትሩ በቀረበው ረቂቅ በጀት ላይ መግለጫ ይሠጣል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ መስረት ከሚኒስትሩ የበጀት መግለጫ በመቀጠል ምክርቤቱ በመርህ እና በአጠቃላይ በጀቱ ላይ ውይይት ያካሂዳል።
3. በበጀት መግለጫው ላይ የሚደረገው አጠቃላይ ውይይት እንዳበቃ ረቂቅ በጀቱ ወደ በጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይመራል፡፡

## 69.የረቂቅ በጀት መመርመሪያ መርሆዎች

ለምክር ቤቱ የቀረበ ረቂቅ በጀት የሚከተሉትን መሠረታዊ መርሆዎች መነሻ በማድረግ ይመረምራል፦

1. የህዝብ ተጠቃሚነት፤
2. ፍትሃዊ የሃብት ክፍፍል፤
3. ድህነት ተኮር ለሆኑ ስራዎች ትኩረት የተደረገ መሆኑ፤

4. በጀትን በቁጠባና በውጤታማነት ለመጠቀም የሚያስችል መሆኑ፤
5. ራስን የመቻል አቅጣጫን የተከተለ መሆኑ፤
6. የመንግስት የትኩረት አቅጣጫን የተከተለ መሆኑ፤
7. ለክልሎች የሚሰጠው ድጎማ የፌደሬሽን ምክር ቤት ባስቀመጠው ቀመር መሠረት መሆኑ፤
8. ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገትን ለማፋጠን የሚያስችል መሆኑ፤እና
9. ሌሎች አግባብነት ያላቸው የመመርመሪያ ስልቶች፡፡

70.**የውይይት ጊዜ አመዳደብ**

አፈጉባዔው ከምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ ጋር በመመካከር በቀረበው ረቂቅ በጀት ላይ ዝርዝር ውይይት የሚካሄድበትና ድምጽ የሚሠጥበት በቂ ጊዜ ይመድባል።

71.**የበጀት ቅነሳ ሞሽን ስለማቅረብ**

በዚህ ደንብ በአንቀፅ 70 መስረት በተመደበው የውይይት ጊዜ ማንኛውም አባል ወይም የፓርላማ ቡድን በረቂቅ በጀቱ ላይ የቅነሳ ሞሽን ማቅረብ ይችላል፡፡

72.**የበጀት ቅነሳ ሞሽን አቀራረብ**

የበጀት ቅነሳ ሞሽን እንደሚከተለው ይቀርባል፦

1. እንዲቀነስ የሚፈለገው የበጀት መጠን ፖሊሲን ባለመቀበል ከሆነ አቅራቢው የሚቃወመውን ፖሊሲ በግልጽ ማሳየትና አማራጭ ፖሊሲ በጽሑፍ ማቅረብ ይኖበታል፣
2. እንዲቀነስ የሚፈለገው የበጀት መጠን ከሆነ ቅነሳው በኢኮኖሚው ላይ የሚኖረውን ውጤት የሚያመላክት መሆን ይኖርበታል። የቅነሳው ጥያቄ በጥቅል ወይም አንድ የበጀት ርዕስ እንዲሠረዝ ወይም አንድ የበጀት ርዕስ በተወሰነ መጠን እንዲቀነስ የሚጠይቅ ሊሆን ይችላል፡፡

73.**የበጀት ቅነሳ ሞሽን መመዘኛ**

ረቂቅ የበጀት ጥያቄን ለመቅነስ የሚቀርብ ሞሽን የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡-

1. ከአንድ የበጀት ፍላጐት ጋር ብቻ የተያያዘ መሆን አለበት፤
2. በግልጽ የተቀመጠ፣ አወዛጋቢ ያልሆነ እውነታን የያዘ፣ስም የማያጠፋ፣ ከስሜታዊነት እና ከመሳሰሉት የፀዳ መሆን አለበት፤
3. ግልጽ የሆነና በተወሰነ አንድ ጉዳይ ላይ ያተኮረ መሆን ይገባዋል፤
4. በግለሰብ ባህሪ ላይ ያተኮረ መሆን የለበትም፤

5. በስራ ላይ የሚገኙ ህጐችን ማሻሻል ወይም መሻርን የሚጠይቅ መሆን የለበትም፤

6. መንግስትን በቀጥታ የሚመለከት ጉዳይ መሆን አለበት፤

7. የልዩ ጥቅም ጥያቄን የሚያነሳ መሆን የለበትም፤

8. በተመሳሳይ የስራ ዓመት ምክር ቤቱ ውይይት አድርጐ ውሳኔ የሰጠበትን ጉዳይ ለማንሳት ያለመ መሆን የለበትም፤

9. ሙሉ ወይም ከፊል የዳኝነት ስራን በሚያከናውኑ አካላት አየታየ ወይም በህግ በተቋቋሙ ሌሎች አካላት እየተጣራና እየተመረመረ ያለን ጉዳይ የሚመለከት መሆን የለበትም፤

10. ጥቃቅን የሆኑ ጉዳዮችን የሚያነሳ መሆን የለበትም፡፡

## 74. የቅነሳ ሞሽን ተቅባይነት ስለሚያገኝበት ሁኔታ

በአፈጉባዔው አስተያየት የቀረበው ሞሽን የዚህን ደንብ ድንጋጌዎች የማያሟላ ወይም የምክር ቤቱን አሰራርና ተግባር የሚያደናቅፍ ወይም ሞሽን የማቅረብ መብትን ያለአግባብ ለመጠቅም የታለመ ሆኖ ካገኘው የቅነሳ ሞሽኑ እንዳይቅርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 75. የቅነሳ ሞሽን ማስታወቂያ ጊዜ

የቅነሳ ሞሽኑ በበጀት ጥያቄው ላይ ውይይት ከመደረጉ ከአንድ ቀን በፊት ለአፈጉባዔው በጽሑፍ መቅረብ አለበት፡፡

## 76. ረቂቅ በጀት ስለማጽደቅ

በዝርዝር በጀቱ እና በቅረቡ የቅነሳ ሞሽኖች ላይ የሚደረገው ውይይት እንደተጠናቀቀ በበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ መነሻነት ውይይት ተካሂዶ ድምጽ ይሰጣል፡፡

# ምዕራፍ አስራ አንድ

# ክትትልና ቁጥጥር

## 77. የክትትል እና ቁጥጥር ዓላማ

የምክር ቤቱ የክትትልና ቁጥጥር ዓላማ የሚከተሉትን ያጠቃልላል፦

1. ስራዎች ህግና ስርዓትን መሰረት አድርገው እየተከናወኑ መሆናቸውን፤

2. ፈጣን፣ ፍትሃዊ፣ ቁጣይነትና ዘላቂነት ያለው የልማት አቅጣጫ መኖሩን፤

3. ዲሞክራሲና መልካም አስተዳደር መስፈኑን፤

4. የቡድንና የዜጎች ዲሞክራሲያዊና ሰብዓዊ መብቶች፣ ሰላምና ፀጥታ መከረበሩን፤

5. በመንግስት አካላት መካከል የተቀናጀ አሰራር መኖሩን፤

ለማረጋገጥ ነው።

## 78.ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግባቸው ጉዳዮችና አካላት

1. ምክር ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር የሚያደርግባቸው ጉዳዮች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፦

   ሀ/ የአገሪቱ ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎች፣ እቅዶች፣ ህጎችና አሠራሮች በተግባር ላይ ስለመዋላቸዉ እንዲሁም ለአገሪቱ አድገት በሚበጅ አቅጣጫ እየተከናወኑ መሆናቸውን፤

   ለ/የዜጎች መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መከበራቸውን፤ እና

   ሐ/ የፌደራል መንግስት በጀት እና ሀብት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን፡፡

2. ምክር ቤቱ በሚከተሉት አካላት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋል፡-

   ሀ/ የፌደራል መንግስት አካላትን፤

   ለ/ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 55 (16/ መሰረት የሰብዓዊ መብቶች መጣስ ሊያስቆምና ሊቆጣጠር ያልቻለን ክልል፡፡

3. ምክር ቤቱ በሕገመንግስቱ አንቀፅ 49 እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ህገች መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያካሂዳል፣ ምክር ቤቱ በከተማ አስተዳደሮቹ የሚያካሂደው ዝርዝር ክትትልና ቁጥጥር አፈፃፀም በዚህ ደንብ መሰረት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## 79.የክትትልና ቁጥጥር ስልት

1. በሕገመንግሥቱ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የምክር ቤቱ የክትትል እና የቁጥጥር ስልቶች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፦

   ሀ/ መንግስታዊ አካላት ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በቀጥታ ለምክር ቤቱ ወይም ለሚመለከተው ኮሚቴ በአካል ሪፖርት እንዲያቀርቡ በማድረግ፤

   ለ/ ጠቅላይ ሚኒስትሩና ሚኒስትሮች በተያዘላቸው የጥያቄ ጊዜ በአካል ተገኝተው የቃልመልስ እንዲሰጡ በማድረግ፤

   ሐ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በመንግስታዊ አካላት ላይ የሂሣብ ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ በመስጠት፤

መ/ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተቋማትን፣ ምስክሮችን፣ ባለሙያዎችን ወይም ሰነዶችን በማስቅረብና ጉዳዮችን በማጣራት፤

ሠ/ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ ተቋማትን እና ስራዎችን በተመለከተ የመስክ ጉብኝት በማድረግ።

2. ምክር ቤቱ ከመንግሥት አካላት፣ ከኮሚቴዎች፣ ከህብረተሰቡና መንግስታዊ ካልሆኑ አካላት የሚቀርብለትን ሪፖርትና ጥቆማ መሰረት በማድረግ ክትትል እና ቁጥጥር ያደርጋል።

3. ምክር ቤቱ መንግስታዊ አካላትን ሲከታተልና ሲቆጣጠር በተቋማት የእለት ተዕለት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ጣልቃ መግባት የለበትም፡፡

4. በሕገመንግሥቱ ወይም በሌሎች ህጎች መሠረት ሥራቸውን በነፃነትና ያለ ጣልቃገብነት እንዲያከናውኑ ሆነው የተቋቋሙ መንግስታዊ አካላትን በመቆጣጠርና በመከታተል ሂደት ምክር ቤቱ ነፃነታቸውን ማክበር አለበት፡፡

## 80.<u>በክትትልና ቁጥጥር ሂደት ስለሚወሰድ የመፍትሄ እርምጃ</u>

በክትትልና ቁጥጥር ሂደት በመንግስታዊ አካላት ላይ የታዩ ችግሮችን አስመልክቶ ምክር ቤቱ የሚከተሉትን የመፍትሄ እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፦

1. የተከሰተው ችግር ከህግ የመነጨ ከሆነ በህግ እንዲደገፍ ወይም ክፍተቱ በህግ እንዲሞላ ያደርጋል፤

2. በመንግሥታዊ አካሉ ላይ የለያቸው ችግሮች ከበጀት ጋር የሚያያዙ ከሆኑና ይህም በሚመለከተው አካል ከተረጋገጠ አስፈላጊውን የእርምት ማስተካከያ ያደርጋል፤

3. ችግሩ የተከሰተው በመንግስታዊ አካሉ ድክመት ከሆነ መንግሥታዊ አካሉ ችግሩን እንዲያውቅ እና የፈፀመውንም ድክመት እንዲያርም መመሪያ ይሰጣል፣ ድክመቱ መታረሙንም ያረጋግጣል፤

4. ችግሩ ካልታረመ እና መሠረታዊ ከሆነ፣ለችግሩ ተጠያቂ በሆነው አካል ላይ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አማካኝነት እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፤

5. ችግሩ የተፈጠረው ተጠሪነቱ በቀጥታ ለምክር ቤቱ በሆነ ሌላ መንግሥታዊ አካል ከሆነ በህግ መሠረት አስፈላጊውን እርምጃ ይወስዳል።

## 81.<u>ለምክር ቤቱ በቀጥታ ስለሚቀርብ ሪፖርት</u>

1. በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 55 (17/ መሰረት ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ባገኘው ጊዜ የፌዴራል መንግስት ባለስልጣናትን ለጥያቄ ይጠራል፣የህግ አስፈፃሚውን አሰራር ይመረምራል።

2. በዚህ ደንብ በአንቀፅ 12 መሰረት ምክር ቤቱ የፌደራል መንግስትን ዓመታዊ አቅድ ያዳምጣል፣ ያፀድቃል፡፡

3. ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሚያዝለት ፕሮግራም መሠረት የመንግስትን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ አስመልክቶ በዓመት ሁለት ጊዜ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፣ ሆኖም መቅረብ የሚገባው ጉዳይ አለ ብሎ ካመነ በማንኛውም ጊዜ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ ይችላል፡፡

4. ምክር ቤቱ ማንኛውም መንግሥታዊ አካል በቀጥታ ሪፖርት እንዲያቀርብ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

5. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ለምክር ቤቱ በቀጥታ ሪፖርት የሚቀርበው፡-

   ሀ/ መንግሥታዊ አካሉ አንገብጋቢ በሆኑ ወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ለምክር ቤቱ ማብራሪያ መስጠቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፤

   ለ/ መንግሥታዊ አካሉለ ቋሚ ኮሚቴ ሪፖርት ሲያደርግ ወይም በኮሚቴው የክትትል እና የቁጥጥር ሂደት መሠረታዊ ችግር የታየበት ከሆነ፤

   ሐ/ በመንግሥታዊ አካሉ ላይ አንገብጋቢ የሆኑ ጥያቄዎች በተደጋጋሚ ከህዝብ የሚነሱ ከሆነ፣

   መ/ መንግሥታዊ አካሉ ላይ ከአባላት ተደጋጋሚ ጥያቄ የሚነሳከ ሆነ፤

   ሠ/ በህግ መሠረት በቀጥታ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ የሚገባቸው መንግሥታዊ አካላት ከሆኑ፤

   ነው።

6. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ ሙስና ኮሚሽን፣ የሰብዓዊ መብት ኮሚሽን፣ የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም እና የፌደራል ዋና ኦዲተር በምክር ቤቱ በመገኘት ሪፖርት ሲያቀርቡ ከጠቅላይ ሚኒስትሩ በስተቀር የምክር ቤት አባላት የሆኑ የመንግስት የስራ ሃላፊዎች በስብሰባው መገኘት ይኖርባቸዋል።

7. የምክር ቤት አባላት ያልሆኑ የመንግስት የስራ ሃላፊዎች በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ(6/ የተጠቀሱት አካላት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ሲያቀርቡ በምክር ቤቱ በሚዘጋጅላቸው ቦታ በመገኘት ስብሰባውን ይከታተላል።

8. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6/ እና (7/ የተጠቀሱት የስራ ሃላፊዎች በምክር ቤት ስብሰባ መገኘት የማይችሉ ከሆነ ይህንኑ አስቀድመው ለአፈጉባዔው በማሳወቅ ከአፈጉባዔው በሚሰጥ ፈቃድ መሰረት ሌላ የተወከለ የስራ ሃላፊ በስብሰባው ሊገኝ ይችላል።

## 82.<u>ስለ ሪፖርት አቀራረብ</u>

1. ለምክር ቤቱ ሪፖርት የሚያቀርበው የመንግሥታዊ አካሉ ኃላፊ ነው፤ኃለፊው ሊያግዙት የሚችሉ የሥራ ባልደረቦቹን ይዞ መምጣት ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ የተደነገገው ቢኖርም ኃላፊው ከአቅም በላይ የሆነሁኔታ ሲያጋጥመው ሁኔታውን በቅድሚያ በማሳወቅ በአፈጉባዔው ፈቃድ ሪፖርቱ በምክትሉ ወይም በተወካዩ እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## 83.<u>የሪፖርት አቅራቢው የአጠራር ሥነ-ሥርዓት</u>

1. አፈጉባዔው በዚህ ደንብ በአንቀፅ 81 እናአንቀፅ 82 የተጠቀሱት አካላት ለምክር ቤቱ ሪፖርት እንዲያቀርቡ በፅሁፍ ያሳውቃል።
2. አፈጉባዔው ሪፖርት የሚቀርብበትን ጊዜና ቦታ ቢያንስ ከአንድ ወር በፊት ማሳወቅ አለበት፡፡
3. ሪፖርት የማቀረቢያው ጊዜ አመቺ አለመሆኑ በመንግስታዊ አካሉ ጥያቄ ቀርቦ በአፈጉባዔው ተቀባይነት ካገኘ ጊዜው ሊለወጥ ይችላል፡፡
4. ሪፖርት አቅራቢው መንግስታዊ አካል በአንቀፅ 82 (1/ መሰረት በስብሰባ ወቅት የሚገኙ ሰዎችን ስም ዝርዝር የሪፖርቱን ከመድረሱ ከአንድ ቀን በፊት ለምክር ቤቱ ማሳወቅ አለበት፡፡

## 84.<u>የሪፖርቱ ይዘትና የሚላክበት ጊዜ</u>

1. ሪፖርቱ በመደበኛ የሥራ እንቀስቃሴ ላይ የሚያተኩር ሆኖ የሚከተሉትን መያዝ ይኖርበታል፦

   ሀ/ ዓመታዊ የሥራ ዕቅድ እና የተከናወኑ ተግባራት፤

   ለ/ የበጀት አፈፃፀም፤

   ሐ/ የሰዉ ሃይል አስተዳደር፤

   መ/ የተገኘው ጤት፤

   ሠ/ ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች እና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች፤

   ረ/ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች እና

   ሰ/ ሌሎች አግባብነት ያላቸው መረጃዎች።

2. በምክር ቤቱ የተፈለገን አንድ ጉዳይ በሚመለከት የሚቀርብ ሪፖርት ከሆነ የተፈለገውን ጉዳይ አጠቃላይ በሆነ መልኩ ሊዳሰስ በሚችል መልኩ ተዘጋጅቶ መቅረብ ይኖርበታል።

3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ እና (2/ የተጠቀሰው ሪፖርት ለምክር ቤቱ ከመቀረቡ ቢያንስ ከአስር ቀን በፊት በሚመለከተው መንግስታዊ አካል ሃላፊ ፊርማ ተረጋግጦ ለአፈጉባዔው መድረስ ይኖርበታል፤ አፈጉባዔውም ሪፖርቱን ለሚመለከተው ኮሚቴ ወዲያውኑ ያስተላልፍል።

## 85.የምክር ቤቱ ሪፖርት ስለሚሰማበት ፕሮግራም

1. በምክር ቤቱ ሪፖርት የሚሰማበትን ፕሮግራም አስቀድሞ ማዘጋጀት ይጠበቅበታል፡፡

2. ምክር ቤቱ የሚያዘጋጀው የሪፖርት ፕሮግራም ሃላፊነቱን ለመወጣት በሚያስችለው እና ውጤታማ ሊያደርገው በሚችል መንገድ መሆን አለበት፡፡

## 86.የሪፖርት አቅራቢዎችፕ ሮቶኮል እና ሥነ-ምግባር

1. በማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ የጠበቀ ፕሮቶኮልና ሥነ- ምግባር ሊኖረው ይገባል፡፡

2. የዚህ ደንብ አንቀፅ 27 እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ሪፖርት አቅራቢ የሚከተሉትን ማክበር ይኖርበታል፦

   ሀ/ በተዘጋጀለት መግቢያ ወደ ምክር ቤቱ ግቢ ከገባ በኋላ በፕሮቶኮል አማካኝነት የተዘጋጀለትን ቦታ መያዝ፣

   ለ/ አለባበሱ የምክር ቤቱ ንክብር የጠበቀ መሆን፤

   ሐ/ ለሪፖርት አቀራረቡ ከሚያስፈልጉት ቁሳቁስ እና ሰነዶች ውጭ ሌሎች አላስፈላጊ ቁሳቁሶች አለመያዝ፤

   መ/ በምክር ቤቱ አዳራሽ ሲጋራ ማጨስ እና ሌሎች አላስፈላጊ ተግባራትን አለመፈፀም።

3. የፅህፈት ቤቱ ፕሮቶኮል ክፍል የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል።

   ሀ/ ወደ ምክር ቤቱ የሚመጣን ሪፖርት አቅራቢ ተዘጋጅቶ መጠበቅ እና በአግባቡ መቀበል፤

   ለ/ ሪፖርት አቀራቢው መምጣቱን ለአፈጉባዔው ማሳወቀና የሚሰጠውን ትዕዛዝ መፈፀም፤

   ሐ/ በስብሰባው ጊዜ ሪፖርት አቀራቢውን ወደ ስብሰባው አዳራሽ ማስገባት እና የተዘጋጀለትን ቦታ እንዲይዝ ማድረግ፤

መ/ ሪፖርት አቀራቢው ሪፖርቱን ካቀረበ በኋላ በአግባቡ መሸኘት፡፡

87.<u>በሪፖርት ላይ የሚደረግ ውይይት የሚመራበት ስርዓት</u>

1. በአፈጉባዔው ጋባዥነት የሚመለከተው ኮሚቴ ሊቀመንበር አቅራቢውን በማስተዋወቅ ሪፖርቱን እንዲያቀርብ ይጋብዛል፡፡
2. ሪፖርት አቀራቢው የተዘጋጀውን ሪፖርት እንደ አመቺነቱ በንባብ ወይም በገለፃ መልክ ሊያቀርብ ይችላል፡፡
3. ሪፖርቱ ከተሰማ በኋላ በሚመለከተው ኮሚቴ የተዘጋጁ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች እንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡
4. ከኮሚቴው ለቀረቡ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች መልስ ከተሰጠ በኋላ የፓርላማ ቡድኖች እና አባላት ጥያቄና አስተያየት እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡
5. ሪፖርት አቀራቢው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4/ ለተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች ምላሽ ይሰጣል።
6. ሪፖርት አቀራቢው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4/ እና (5/ መሰረት በቀረቡ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በሰጠው ምላሽ የማይስማማ አባል ተጨማሪ ጥያቄ ማቅረብ ይችላል።
7. ለተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች በሙሉ ምላሽና ማብራሪያ በሪፖርት አቅራቢው ከተሰጠ በኋላ አፈጉባዔው ሪፖርቱን አስመልክቶ የማጠቃለያ አስተያየት በሚመለከተው ኮሚቴ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡
8. የቀረበው ሪፖርትና የተሰጠው ምላሽ አከራካሪ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ምክር ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ በሪፖርቱ ላይ ድምፅ ሊሰጥ ይችላል፡፡
9. ምክር ቤቱ በቀረበው ሪፖርት ላይ ጥርጣሬ ካደረበት ወይም በበቂ ሁኔታ አልቀረበም ብሎ ካመነ ወይም በማያጠራጥር ሁኔታ መሠረታዊ ችግር ያለው ሆኖ ካገኘው ጉዳዩ በሚመለከተው ኮሚቴ ተጣርቶ እንዲቀርብለት በማድረግ ወይም ማጣራት ሳያስፈልገው በዚህ ደንብ አንቀፅ 80 የተመለከቱትን እርምጃዎች እንደሁኔታው ተፈፃሚ ሊያደርግ ይችላል።

88.<u>ኮሚቴ ለምክር ቤቱ ስለሚያቀርበው ሪፖርት</u>

1. በእያንዳንዱ ኮሚቴ እንደአስፈላጊነቱ ስለስራ እንቅስቃሴው ለምክር ቤቱ ሪፖርት ሊያቀርብ ይችላል፡፡
2. በኮሚቴ የሚቀርብ ሪፖርት የሚከተሉትን ጉዳዮች የሚመለከት ሊሆን ይችላል፡-

ሀ/ ምክር ቤቱ ሊያውቃቸው ወይም ውሳኔ ሊያስተላልፍባቸው የሚገቡ

ጉዳዮች፤

ለ/ የእቅድ አፈፃፀሙን፤

ሐ/ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎችን፤ ወይም

መ/ ሌሎች አግባብነት ያላቸው ጉዳዮችን።

3. የኮሚቴ ሪፖርት የሚቀርበው በሊቀመንበሩ አማካኝነት ይሆናል፡፡

89. <u>ማስረጃ ስለ መመርመር</u>

1. ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ማናቸውንም ምስክር፣ ሰነድ ወይም ሎሎች ማስረጃዎችንና መረጃዎችን መስማት ወይም መመርመር ይችላል፡፡
2. ምክር ቤቱ እንደ አስፈላጊነቱ በራሱ ወይም በኮሚቴ አማካኝነት ምስክርነት ሊሰማ ወይም ሠነድ ሊመረምር ይችላል፡፡
3. ምክር ቤቱ ለምስክርነት የሚፈለገውን ግለሰብ ምስክርነት የሚሰጥበትን ጉዳይ፣ ቦታና ጊዜ በማሳወቅ እንደአስፈላጊነቱ በደብዳቤ ይጠራል፡፡
4. ለምስክርነት የሚፈለገው ግለሰብ የሚሰጠው ምስክርነት እንደሁኔታው በፅሑፍ የተደገፈ ወይም ጥያቄው ተራ በተራ እየቀረበለት የቃል መልስ በመስጠት ሊሆን ይችላል፡፡
5. ምስክሩ በጥያቄ ያልቀረበለት ነገር ግን ለጉዳዩ ጠቃሚ የሆነ የሚያውቀው መረጃ ካለ አስፈቅዶ ነጥቡን በተጨማሪነት ሊገልፅ ይችላል፡፡
6. ምክር ቤቱ ለያዘው ጉዳይ አግባብነት ያለው ሰነድ እንዲቀርብለት የሚመለከተውን አካል ወይም ግለሰብ ሰነዱን እንደሁኔታው ዋናውን ወይም ቅጂውን በሚፈለገው ጊዜ እንዲያቀርብ በደብዳቤ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል።
7. በምክር ቤቱ የሚፈለገው ሰነድ ከተመረመረ በኋላ ለሚመለከተው አካል ወይም ግለሰብ በአግባቡ ይመለሳል፡፡
8. ምክር ቤቱ ከሚመለከተው አካል ወይም ከግለሰብ አስፈላጊ ሰነድ እንዲቀርብለት ሲጠይቅ ወይም የቃል ምስክርነት ቀርቦ እንዲሰጥ ሲያደርግ በሕገመንግሥቱና በሌሎች ህጎች የተደነገጉትን ገደቦችና ነፃነቶች ማክበር አለበት፡፡
9. ምስክርነት የሚሰጥ ወይም ሰነድ የሚያቀርብ፡ግለሰብ የሚከተለውን ቃለ መሃላ ይፈፅማል፡-

   እኔ................ በዛሬው ዕለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት (ወይም በ................ኮሚቴ/ ፊት የምሰጠው

ቃል ወይም ያቀረብኩት ሰነድ ትክክለኛ እና የደበቅሁት ነገር የሌለ መሆኑን አረጋግጣለሁ፡፡

10.በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (9/ የተጠቀሰው ቃለ መሃላ በሚመለከተው አካል ይከናወናል፡፡

## 90.ምክር ቤቱ ስለሚሰጠው የኦዲት ትዕዛዝ

1. ምክር ቤቱ ማንኛውም አካል የተመደበለትን በጀት ከዓላማው ውጭ ማዋሉን ሲገምት ወይም ከፍተኛ የበጀት አጠቃቀም ስርዓት መጓደል ወይም መባከን መኖሩን ሲገነዘብ የሂሳብ ምርመራ እንዲደረግ ሊያዝ ይችላል፡፡
2. ምክር ቤቱ የሚሰጠው የኦዲት ትዕዛዝ የሚከናወነው በፌደራል ዋና ኦዲተር ወይም እርሱ በሚወክለው አካል ይሆናል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ የተደነገገው የኦዲት ትዕዛዝ የሚሰጠው በአፈጉባዔው ሆኖ፡-

   ሀ/ ሊመረመር የተፈለገውን አካል፤

   ለ/ የሚመረመረውን ጉዳይ፤እና

   ሐ/ የኦዲት ሪፖርት የሚቀርብበትን ጊዜ፤

   ያመላከተ መሆን አለበት፡፡
4. ምክር ቤቱ የኦዲት ሪፖርቱን ከሰማ በኋላ በዚህ ደንብ አንቀፅ 80 የተጠቀሱትን እርምጃዎች እንደሁኔታው ሊወስድ ይችላል።

## 91.ጥቆማዎችን ስለመቀበል

1. ምክር ቤቱ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ጥቀማዎችን ሊቀበል ይችላል፦

   ሀ/ በመንግሥት ወይም በህዝብ ሀብት እና ጥቅም ላይ የደረሰ ወይም ሊደርስ የሚችል ጉዳትን በሚመለከት፤

   ለ/ ሕገመንግሥቱን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ ከተፈጠረ ወይም ይፈጠራል ተብሎ ሲገመት፤

   ሐ/ የመንግስት ፖሊሲ እና ስትራቴጂን የሚያደናቅፍ ሁኔታ ሲከሰት፤

   መ/ በህዝቦች መካከል ግጭት ከተፈጠረ ወይም ግጭት ሊያስነሳ የሚችል ሁኔታ ሲያጋጥም፤

   ሠ/ የሰብዓዊ መብት ሲጣስ፤

   ረ/ ከፍተኛ የሆነ ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ አደጋ ሲከሰት፡፡
2. ማንኛውም የሚቀርብ ጥቆማ ትክክለኛ ማስረጃ ሊኖረው ይገባል፡፡

3. ጥቆማው በጽሑፍ ተዘጋጅቶ የጠቋሚውን ስም፣ ሙሉ አድራሻ እና ፊርማ የያዘ መሆን አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (3/ መሰረት ያልቀረበ ጥቆማ ተቀባይነት የለውም።
5. በአግባቡ የቀረበ ጥቆማ ተጣርቶ አስፈላጊው ውሳኔ ይሰጥበታል፤ ጠቋሚውም ውሳኔውን እንዲያውቀው ሊደረግ ይችላል።
6. ምክር ቤቱ የጠቋሚዎችን ማንነት በሚስጥር ይጠብቃል።

92.<u>የጥያቄ ጊዜ</u>

1. አፈጉባዔው በሌላ ሁኔታ ካልወሰነ በስተቀር ምክር ቤቱ ሚኒስትሮች በቃል መልስ የሚሰጡበት በየሳምንቱ ሐሙስ የአንድ ሰዓት የጥያቄ ጊዜ ይኖረዋል።
2. ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ ከተጠቀሰው ጊዜ ውስጥ በወር አንድ ጊዜ የቃል መልስ የሚሰጥበት የአንድ ሰዓት የጥያቄ ጊዜ ይኖረዋል።
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ የተደነገገው ቢኖርም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሪፖርት በሚያቀርብበት ወር የጥያቄ ጊዜ አይኖረውም።

93.<u>የጥያቄ አቀራረብ</u>

1. ማንኛውም የቃል መልስ የሚፈልግ ጥያቄ የሚያቀርብ አባል ጥያቄውን ቢያንስ ከአስር ቀን በፊት ለአፈጉባዔው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።የጥያቄ ማስታወቂያውም፡-

   ሀ/ የጥያቄውን ይዘት፣

   ለ/ መልስ እንዲሰጥ የሚፈለገው የሚኒስቴር መስሪያ ቤት ስም፤

   ሐ/ የጠያቂውን ስምና ፊርማ፤

   የያዘ መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም አባል ለህዝብ ጠቀሜታ ባለው ጉዳይ ላይ ለሚመለከተው ሚኒስትር ጥያቄ ማቅረብ ይችላል፡፡
3. ማንኛውም አባል በአንድ የጥያቄ ጊዜ ከአንድ ጥያቄ በላይ ማቅረብ አይችልም።
4. አፈጉባዔው በዚህ ደንብ በአንቀፅ 95 መሠረት የተቀበላቸውን ጥያቄዎች በማደራጀት ለሚመለከተው ሚኒስትር ይልካል፣ መልስ የሚሰጥበትን ፕሮግራምም ከሚመለከተው አካል ጋር በመመካከር ይወሰናል፣ አባላትም እንዲያውቁት ያደርጋል።

94.<u>የጥያቄ ይዘት</u>

የቃል መልስ የሚፈልግ ማንኛውም ጥያቄ የሚከተሉትን ማሟላት ይኖርበታል፡-

1. ግልጽ፣ አጭር፣ ለአንድ የተወሰነ ጉዳይ መልስ የሚፈልግ እና የመሪ ጥያቄ ባህሪ የሌለው መሆን አለበት፤
2. የሰዎችን መልካም ስም የማይጐዳ ቋንቋውም የምክር ቤቱን ክብር የጠበቀ መሆን አለበት፤
3. የግል አስተያየትን፣ ለተወሳሰበ የህግ ጥያቄ መፍትሄ የሚጠይቅና በመላምት ላይ የተመሠረተ መሆን የለበትም፤
4. የግለሰብን ባህሪ ወይም ፀባይ የተመለከተ መሆን የለበትም፤
5. ጉዳዩ በፌደራል መንግሥት የሥልጣን ክልል ስር የሚወድቅ መሆን አለበት፤
6. በኮሚቴ በመታየት ላይ ያለን ጉዳይ የሚጠይቅ መሆን የለበትም፤
7. በተመደበው የጥያቄ ጊዜ ውስጥ ሊመለስ የማይችል ሰፊ የፖሊሲ ጥያቄ መሆን የለበትም፤
8. ቀደም ሲል ምላሽ ያገኘ ወይም ተቀባይነት ያጣ ጥያቄን የሚመለከት መሆን የለበትም
9. በጥቃቅን ጉዳዮች ላይ መረጃ የሚጠይቅ መሆን የለበትም፤
10. ለወቅቱ ሁኔታ ጠቀሜታ የሌለው ያለፈ ታሪክ የሚያንፀባርቅ መረጃ የሚጠይቅ መሆን የለበትም፤
11. በቀላሉ ከሰነድ ወይም ከጽሁፍ ማግኘት የሚቻል መረጃን የሚመለከት መሆን የለበትም፣
12. በፌደራል መንግሥት ቀጥተኛ ኃላፊነት ሥር ያልሆነና በሌላ አካል ወይም ግለሰብ ቁጥጥር ሥር የሆነ ጉዳይን የሚመለከት መሆን የለበትም፤
13. በፍርድቤት በመታየት ላይ ያለን ጉዳይ ወይም ከፊል የፍርድ ቤት ሥልጣን ባለው ወይም ሥልጣን በተሰጠው ሌላ አካል በመመርመር ወይም በመጣራት ላይ ያለን ጉዳይ የሚመለከት መሆን የለበትም፤
14. ጥያቄው በሚኒስቴሩ ሥልጣን ስር የሚገኝ መሆን አለበት፤
15. የወዳጅ አገራትን ክብር የሚነካ መሆን የለበትም፤
16. በባህሪያቸው አገራዊ ሚስጥር የሆኑ ጉዳዮችን የሚመለከት መሆን የለበትም።

## 95.ጥያቄው ተቀባይነት ስለሚያገኝበት ሁኔታ

1. አፈጉባዔው የቀረበውን የጥያቄ ማስታወቂያ በዚህ ደንብ በአንቀፅ 93 እና በአንቀፅ 94 መሠረት በመመርመር ሊቀበለው ወይም ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

2. ተቀባይነት አግኝተው ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ከስብሰባ በፊት ለአባላት መድረስ አለባቸው።
3. በአንድ የሰብሰባ ወቅት መቅረብ ያለበት የጥያቄ ብዛት ከአስራ አምስት መብለጥ የለበትም፡፡
4. አፈ-ጉባዔው የተቀበላቸውን ጥያቄዎች እንደቅደም ተከተላቸው የአቅራቢዎቹን ስም በመጥቀስ መልስ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡
5. በዚህ ደንብ የተደነገገውን መመዘኛ ያሟሉ ከአስራ አምስት በላይ ጥያቄዎች ሲኖሩ ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ ጥያቄዎች የህዝብን ጥቅም መሠረት በማድረግ በአፈ-ጉባዔው ይለያሉ፣ ቀሪዎቹ በሌላ የጥያቄ ጊዜ መልስ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡
6. አንድ አባል ያቀረበውን ጥያቄ መተው ሲፈልግ ስብሰባው ከመጀመሩ በፊት ለአፈ-ጉባዔው ያሳውቃል፣ ለጥያቄውም መልስ አይሰጥበትም፡፡
7. በጥያቄ ጊዜ በሚቀርብ ጥያቄና በሚሰጥ መልስ ላይ ምንም ዓይነት ክርክር አይካሄድም።

96.ስለተጨማሪ ጥያቄ

1. አፈ-ጉባዔው ለጥያቄ በተመደበው ጊዜ ውስጥ በሚኒስትሮች የተሰጠን መልስ መነሻ በማድረግ ተጨማሪ የማብራሪያ ጥያቄ በአቀራቢው ወይም በሌላ አባል እንዲቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. አፈ-ጉባዔው ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች ተጨማሪ የማብራሪያ ጥያቄ ላይቀበል ይችላል፦

ሀ/ ከቀረበው ጥያቄ ወይም ከተሰጠው መልስ ውጭ ሲሆን፤

ለ/ መረጃ ከመጠየቅ ይልቅ መረጃ የሚሰጥ ሲሆን፤

ሐ/ ከአንድ በላይ የሆኑ ጉዳዮችን ያካተተ ሲሆን፤

መ/ የማመን ወይም የመካድ አስተያየት የሚጠይቅ ሲሆን፤

ሠ/ በዚህ ደንብ በአንቀፅ 93 (3/ እና አንቀፅ 94 የተደነገጉትን የማያሟላ ከሆነ፡፡

97.በአጭር ጊዜ ማስታወቂያ የሚቀርብ ጥያቄ

1. በዚህ ደንብ አንቀፅ 93 የተደነገገው ቢኖርም ለህዝብ ጠቀሜታ ያለው አስቸኳይ ጥያቄ ከአስር ቀን ባነሰ ማስታወቂያ በአፈ-ጉባኤው ፈቃድ ለምክር ቤቱ ሊቀረብ ይችላል።

2. በአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያ የሚቀርብ ጥያቄን ያቀረበ አባል ምክንያቱን በተብራራ መልኩ በጽሁፍ ማቅረብ አለበት፤ ሆኖም በቂ ማብራሪያ ያልተሰጠበት ማስታወቂያ ለአባሉ እንዲመለስ ይደረጋል፡፡

3. አፈ-ጉባኤው ጥያቄ የቀረበለትን ሚኒስትር አስቀድሞ በማማከር በጥያቄው ጊዜ መልስ እንዲሰጥበት ሊያደርግ ይችላል፡፡

4. ሚኒስትሩ በወቅቱ መልስ መስጠት ካልቻለ ከአፈ-ጉባኤው ጋር በመመካከር በሌላ የጥያቄ ጊዜ መልስ መስጠት ይችላል፡፡

5. በአንድ የጥያቄ ጊዜ በአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያ ሊቀርብ የሚችለው ጥያቄ አንድ ብቻ ይሆናል፡፡

6. በአስቸኳይ ጊዜ የሚቀርብ ማስታወቂያ ጥያቄ ከአንድ በላይ በሆኑ አባላት ፊርማ የቀረበ ከሆነ በቀረበው የስም ዝርዝር ላይ መጀመሪያ በተጠቀሰው ስም እንደቀረበ ተደርጎ ይወሰዳል፡፡

7. በአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያ የቀረቡ ተመሳሳይ ጥያቄዎች ላሉ አፈ-ጉባኤው ለይቶ ያቀርባል ወይም ጥያቄዎቹን በአንድ አጠቃሎ ሊቀርብ ይችላል ሚንስትሩም ተጠቃሎ ለቀረበው ጥያቄ አጠቃላይ መልስ ይሰጣል፡፡

8. ጥያቄውና አቅራቢው በአፈ ጉባኤው ከተገለፁ በኋላ ሚኒስቴሩ መልስ እንዲሰጥበት ይደረጋል፡፡

9. በዚህ ደንብ ስለ ጥያቄ አቀራረብ የተደነገጉት ለዚህ አንቀፅ አፈፃጸም እንደ አስፈላጊነቱ ተፈፃሚ ይሆናሉ፡፡

98.<u>ስለ እምነት ማጣት ድምጽ</u>

ማንኛውም አባል በሚኒስትሮች ምክር ቤት ላይ እምነት አጥቻለሁ የሚል ሞሽን ማቅረብ ይችላል፡፡

99.<u>ስለ እምነት ማጣት ሞሽን አቀራረብና ተቀባይነት</u>

1. የሞሽኑ ማስታወቂያ ከምክር ቤቱ ስብሰባ ከሁለት ቀን በአፈ-ጉባኤው በኩል ለምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ በፅሁፍ መቅረብ አለበት፡፡

2. አማካሪ ኮሚቴው የማታወቂያ ሞሽኑ ስርዓቱን ተከትሎ በአግባቡ የቀረበ ሆኖ ካገኘው ለምክር ቤቱ እንዲያቀርብ ሊያደርግ ይችላል፡፡

3. አፈ-ጉባኤው በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ መሰረት በአማካሪ ኮሚቴው ተቀባይነት ያገኘውን የሞሽን ማታወቂያ አቅራቢዊ በንባብ ለምክር ቤቱ እንዲያቀረብ ያደርጋል፡፡

4. የቀረበው የእምነት ማጣት ሞሽን በአንድ ሦስተኛ የምክር ቤት አባላት ከተደገፈ በአስራ አምስት ቀናት ውስጥ ውይይት እንዲደረግ አፈጉባኤው ቀጠሮ ይይዛል፡፡
5. የእምነት ማጣት ሞሽኑ የአንድ ሦተኛ የምክር ቤት አባላት ድምፅ ድጋፍ ካላገኘ ጥያቄው ውድቅ መሆኑን አፈጉባኤው ለምክር ቤቱ ይገልፃል፡፡
6. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (4/ መሠረት ሞሽኑ ድጋፍ ካገኘ ውይይት ይካሄዳል፣ አፈጉባዔውም በጉዳዩ ላይ በቂ ውይይት ተደርጓል ብሎ ሲያምን ድምፅ እንዲሰጥ ያደርጋል፡፡
7. አፈጉባኤው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (4/ መሠረት ድጋፍ ባገኘው ሞሽን ላይ ለሚደረገው ውይይት አስፈላጊውን የንግግር ጊዜ ይመድባል፡፡

## ምዕራፍ አስራ ሁለት

## የህዝብ ተሳትፎ

100.**ጠቅላላ**

ምክር ቤቱ አስፈላጊ ናቸው በሚላቸው ጉዳዮች ዜጎችና የተለያዩ አካላት እንዲሳተፉ ያደርጋል፡፡

101. **ተሳትፎ የሚደረግባቸው ጉዳዮች**

በዚህ ደንብ በአንቀፅ 100 የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ የሚከተሉትን ተግባራት ሲያከናውን የዜጎችና የተለያዩ አካላትን ተሳትፎ ሊጠቀም ይችላል፦

1. በህግ አወጣጥ ሂደት፤
2. የወጡ ህጎች አፈፃፀምና ያስገኙትን ውጤት በተመለከተ፤
3. በበጀት ማፅደቅ ሂደት፤
4. በበጀት አፈፃፀም፣ በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉና የተፈለገውን ውጤት ስለማስገኘቱ በተመለከተ፤
5. በኦዲት "በመንግስትና በዘርፍ ደረጃ በሚወጡ ፖሊሲዎችና እቅዶች፤
6. በመንግስትና በዘርፍ ደረጃ በሚወጡ ፖሊሲዎችና እቅዶች
7. በፖሊሲዎችና በእቅዶች አፈፃፀምና የተፈለገውን ውጤት ማምጣታቸውን በተመለከተ፤
8. በመስክ ጉብኝት ግኝቶችና ሪፖርቶች
9. በምርጫ ክልል ጥያቄዎችና አስተያየቶች፤
10. በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ፤

11.ሌሎች የህዝብንና የመንግስት ጥቅምን በሚመለከቱ ጉዳዮች፡፡

## 102.ተሳታፊ አካላት

ተሳትፎ የሚያደርጉ አካላት እንደ የጉዳዩ አግባብነት የሚወሰኑ ሆኖ ምክር ቤቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት የሚከተሉት አካላት ሊሳተፉ ይችላሉ፡-

1. የክልል መንግስታትና የከተማ አስተዳደሮች፤
2. የመንግስት አካላት፤
3. የትምህርት ተቋማት፤
4. የብዙሃን ማህበራት፤
5. የሙያ ማህበራት፤
6. የንግዱ ማህበረሰብ፤
7. የፖለቲካ ፓርቲዎች፤
8. የአነስተኛና ጥቃቅን ማህበራት፤
9. የመገናኛ ብዙሃን፤
10. ሌሎች ባለድርሻ አካላት፡፡

## 103. ተሳትፎ የሚፈፀምባቸው መንገዶች

ምክር ቤቱ በሚያከናውናቸው ተግባራት የዜጎችንና የተለያዩ አካላትን ተሳትፎ ለማረጋገጥ የሚከተሉትን መንገዶች በስራ ላይ ያውላል፡-

1. የህዝብ አስተያየት መስጫ መድረኮችን በማዘጋጀት፤
2. በፅሁፍ አስተያየቶችን ፣ጥያቄዎችንና ጥቆማዎችን በመቀበል፤
3. በነፃ የስልክ ጥሪ፤
4. የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂን በመጠቀም፤
5. በፋክስና በፖስታ፤
6. የመገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም፤
7. በሚደረግ ጥሪ መሠረት በምክር ቤቱና በቋሚ ኮሚቴዎች ስብሰባዎች ሂደት በመታዘብ፤
8. አግባብነት ያላቸው ሌሎች መንገዶችን በመጠቀም።

## 104. የተሳትፎ ሪፖርትና ግብዓት

1. ማናቸውም ለአስተያየትና ለተሳትፎ የቀረበ ጉዳይ ሂደቱ እንደ ተጠናቀቀ ራሱን የቻለ ሪፖርት ይዘጋጅለታል፡፡

2. ሪፖርቱ አጠቃላይ የተሳትፎውን መረጃ የሚይዝ ሆኖ የተነሱ ጥያቄዎችና አስተያየቶች እንዲሁም በግብዓትነት ተቀባይነት የሚያገኙና የማያገኙ ነጥቦችን መግለፅ ይኖርበታል።

3. በግብዓትነት ተቀባይነት ያገኙና ያላገኙ ነጥቦች በሪፖርቱ በሚገለፁበት ጊዜ ለምን ተቀባይነት እንዳገኙና እንዳላገኙ የሚያስረዳ በቂ ምክንያትና ማብራሪያ መቀመጥ ይኖርበታል፤ የሚመለከታቸዉ አካላትም እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

## ምዕራፍ አስራ ሦስት

## የሹመት እና የአሰያየም ሥነ-ሥርዓት

### 105.በምክር ቤቱ የሚመረጡ፣ የሚሾሙ እና ሹመታቸው የሚፀድቅ ባለስልጣናት

ምክርቤቱ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 55(13/ ፣አንቀፅ 55 (19/፣ አንቀፅ 73 (1/፣ አንቀፅ 81(1/: አንቀፅ 101 (1/፣ አንቀፅ 102(2/ እና አንቀፅ 103(2/ መሠረት የሚከተሉትን ባለሥልጣናት ይመርጣል፣ ይሰይማል፣ ይሾማል ወይም ሹመታቸውን ያፀድቃል፦

1. የጠቅላይ ሚኒስትርን፤
2. የምክር ቤቱን አፈጉባኤና ምክትል አፈጉባዔን፤
3. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት፣ ምክትል ፕሬዚዳንት እና ሌሎች
4. የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞችን፤
5. ሚኒስትሮችን፣
6. ኮሚስትሮችን፤
7. የፌደራል ዋና ኦዲተርን፤
8. የብሔራዊ የምርጫ ቦርድ አባላትን፤
9. የህዝብ ቆጠራ ኮሚሽን አባላትን፤ ሌሎች ሹመታቸው በምክር ቤቱ የሚጸድቅ ወይም የሚመረጡ ባለስልጣናትን፡፡

### 106.የምክር ቤት አፈጉባኤና ምክትል አፈ ጉባኤ አመራረጥ

የአፈጉባኤውና የምክትል አፈጉባኤው አመራረጥ በዝህ ደንብ አንቀፅ 8 መሰረት ይከናወናል፡፡

### 107.የጠቅላይ ሚኒስትሩ አሰያየም

1. በህገ መንግስቱ አንቀፅ 73 መሰረት ጠቅላይ ሚንስትሩ አብላጫ መቀመጫ ካገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ የፖለቲካ ድርጅቶች ከምክር ቤት አባላት መካከል በምክር ቤቱ ይሰየማል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ መሰረት አብላጫ መቀመጫ ካገኘው የፖለቲካ ድርጅት ወይም ጣምራ ድርጅቶች የተወከለው አባል የሚሰየመውን ጠቅላይ ሚኒስትር ለምክር ቤቱ እንዲያስተዋውቅ በአፈጉባዔው እድል ይሰጠዋል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ መሰረት የቀረበውን ጠቅላይ ሚኒስትር ምክር ቤቱ በቀጥታ ተቀብሎ ያፀድቀዋል፡፡ የተሰየመው ጠቅላይ ሚኒስትርም በዚህ ደንብ በአንቀፅ 109 መሰረት በአጭር ጊዜ ውስጥ ካቢኔውን በማደራጀት ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያፀድቃል፡፡

108.<u>የፌደራል ፍርድ ቤቶች ዳኞች የሹመት አፀዳደቅ</u>

1. በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 74 (7/ እና አንቀፅ 81(1/ መሠረት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማሉ።

2. ሌሎች የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞችን በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስትሩ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 81 (2/ እና በፌደራል ዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ማቋቋሚያ አዋጅ መሠረት የቀረቡለትን እጩዎች ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያሾማል።

3. ጠቅላይ ሚኒስትሩ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ እና (2/ መሠረት ዳኞችን ለሹመት ሲያቀርብ የእያንዳንዱን ተሿሚ አጠቃላይ መረጃ ከሹመት ጥያቄው ጋር አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል።

4. አባላት በቀረቡ እጩ ዳኞች ላይ ክርክር በሚያደርጉበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም እርሱ የወከለው ሰው ወይም የፌደራል የዳኞች አስተዳደር ጉባዔ ተወካይ በመቅረብ አስፈላጊውን ማብራሪያ ለምክር ቤቱ መስጠት አለበት፣ ምክር ቤቱም ተወያይቶ የቀረበውን ሹመት ያፀድቃል፡፡

5. ምክር ቤቱ ተሿሚውን አስመልክቶ መሟላት ያለበት ተጨማሪ መረጃ መቅረብ አለበት ብሎ ካመነ የተፈለገው መረጃ እስኪሟላ ድረስ የሹመት ጥያቄውን ሊያዘገየው ይችላል፡፡

6. ምክር ቤቱ በእጩነት በቀረበው ዳኛ ላይ መሠረታዊ ችግር አለ ብሎ ካመነ የቀረበውን የሹመት ጥያቄው ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

7. በህግ በተደነገገው መሠረት ከሥራው እንዲነሳ በዳኞች አስተዳደር ጉባዔ የውሳኔ ሃሳብ የቀረበበት ዳኛ በምክር ቤቱ ተጣርቶ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

109.<u>የሚኒስትሮች፣ የኮሚሽነሮች፣ የዋና ኦዲተር፣ የምርጫ ቦርድ አባላት እና የህዝብ ቆጠራ ኮሚሽን አባላት የሹመት አፀዳደቅ</u>

1. ምክር ቤቱ በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 74 (2)፣ አንቀፅ 74 (7)፣ አንቀፅ 101 (1)፣ አንቀፅ 102 (2) እና አንቀፅ 103 (2) መሠረት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት የሚኒስትሮች ምክር ቤት አባላትን፣ ኮሚሽነሮችን፣ ዋና ኦዲተርን፣ የብሔራዊ ምርጫ ቦርድ አባላትን ፣የህዝብ ቆጠራ ኮሚሽን አባላትን እንዲሁም በሌሎች ህጎች በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በምክር ቤቱ የሚሾሙ ባለስልጣናትን ሹመት ያፀድቃል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተሿሚዎችን ለምክር ቤቱ ሲያቀርብ የእያንዳንዱን ተሿሚ አጠቃላይ መረጃ ከሹመት ጥያቄው ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡
3. አባላት በእያንዳንዱ ዕጩ ተሿሚ ላይ ክርክር በሚያደርጉበት ወቅት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም እንደ ሁኔታው እርሱ የሚወክለው ሰው በመገኘት ለምክር ቤቱ ማብራሪያ መስጠት አለበት፡፡ ምክር ቤቱም በሹመት ጥያቄው ላይ ውይይት ካደረገ በኋላ ሹመቱን ያፀድቃል፡፡
4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (3) የተደነገገው ቢኖርም ምክር ቤቱ የዚህን ደንብ አንቀፅ 108 (5) እና (6) ድንጋጌዎች እንደሁኔታው ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፡፡
5. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) የተጠቀሱት ባለሥልጣናት ከሥልጣናቸው ሲነሱ የተወሰደውን እርምጃ በተመለከተ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ለአፈጉባዔው ያሳውቃል።
6. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (5) የተደነገገው ቢኖርም ተጠሪነታቸው ለምክር ቤቱ የሆኑትን ተቋማት የሚመሩ ሆነው ሹመታቸው በጠቅላይ ሚኒስትሩም ሆነ በሌላ አካል አቅራቢነት በምክር ቤቱ የጸደቀላቸው ባለሥልጣናት ከሥልጣናቸው የሚነሱት በህግ መሠረት በምክር ቤቱ ይሆናል፡፡

110.<u>ሹመታቸው በቀጥታ በምክር ቤቱ ስለሚፀድቅ ባለስልጣናት</u>

1. ሹመታቸው በቀጥታ በምክር ቤቱ መፅደቅ የሚገባቸው ባለስልጣናት በአፈጉባዔው ወይም በሚመለከተው ኮሚቴ አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይፅድቃል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) መሠረት የሹመት ጥያቄ ለምክር ቤቱ የሚያቀርብ አካል የተሿሚውን አጠቃላይ መረጃ አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡ምክር ቤቱም በሹመት ጥያቄው ላይ ከተወያየ በኋላ ሹመቱን ያፀድቃል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2) የተደነገገው ቢኖርም ምክር ቤቱ የዚህን ደንብ አንቀፅ 108 (5) እና (6) ድንጋጌዎች እንደ ሁኔታው ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል፡፡

111. <u>**ቃለ-መሃላ ስለመፈፀም**</u>

1. ማንኛውም ሹመቱ በምክር ቤቱ የሚፀድቅ ወይም የሚሰየም ወይም የሚመረጥ ባለስልጣን በምክር ቤቱ ፊት በመቅረብ ቃለ-መሃላ መፈፀም ይኖርበታል።
2. ማንኛውም ሹመቱ በምክር ቤቱ የፀደቀ ወይም የተሰየመ ወይም የተመረጠ ባለስልጣን በምክር ቤቱ ፕሮቶኮል አማካኝነት የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ በጠበቀ መልኩ ተዘጋጅቶ ወደ ምክር ቤቱ አዳራሽ በመግባት በፌደራል ጠ;ቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ወይም ምክትል ፕሬዚዳንት አማካኝነት ቃለ-መሃላውን ይፈፅማል።
3. የቃለ-መሃላው ይዘትም እንደሚከተለው ይሆናል፦ "እኔ…………በዛሬው ዕለት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፊት ቀርቤ……..ሆኜ ስሾም ለሕገመንግሥቱ ታማኝ በመሆን፤ ከአገሪቷ እና ከህዝቡ የተጣለብኝን ኃላፊነት በቅንነት፣ በታታሪነት እንዲሁም ህግንና ስርዓትን መሠረት በማድረግ ሥራዬን ለመፈጸም ቃል እገባለሁ፡፡
4. ቃለ-መሃላውን የሚፈፅመው የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሆነ ጊዜ ምክትሉ ቃለ-መሃላውን ያስፈፅማል።
5. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (3/ የተደነገገውን ቃለ-መሃላ ሳይፈፅም ማንኛውም ተሿሚ ሥራ መጀመር አይችልም።
6. በአሳማኝ ምክንያት ካልቀረበ በስተቀር ማንኛውም ሹመቱ በምክር ቤቱ የፀደቀ ወይም የተየሰመ ወይም የተመረጠ ባለስልጣን ወዲያውኑ ቃለ-መሃላውን መፈፀም አለበት፡፡
7. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (6/ መሠረት ወደ ምክር ቤቱ ቀርቦ ቃለ-መሃላ ያልፈፀመ ባለስልጣን በሚመለከተው የምክር ቤቱ አካል ወይም በአባላት ጥያቄ ሹመቱ ሊነሳ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ አስራ አራት

## አባላት ከመራጮቻቸው ጋር ስለሚገናኙበት

### 112. አባላት ከመረጣቸው ህዝብ ጋር የሚገናኙበት ጊዜ

1. ማንኛውም አባል አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ከመረጠው ህዝብ ጋር መገናኘት ይችላል፡፡
2. በዚህ ደንብ በአንቀፅ 24 በተጠቀሰው የምክር ቤቱ የዕረፍት ጊዜያት አባላት ከመረጣቸው ህዝብ ጋር ይገናኛሉ።

### 113. አባላት ከመረጣቸው ህዝብ ጋር በመገናኘት ሂደት ምክርቤቱ ያለው ድርሻ

1. ምክር ቤቱ አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ጉዳይ አባላቱ ከህዝብ ጋር ተገናኝተውና ሃሳብ አሰባስበው እንዲያቀርቡለት ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. ምክር ቤቱ አባላት ያዘጋጁትን ሪፖርት ይቀበላል፣ እንደ አስፈላጊነቱም መፍትሄ ይሰጣል እንዲሁም ለምክር ቤቱ ተግባራት በግብዓትነት ይጠቀምበታል፣ የተላለፈ ውሳኔ ሲኖርምአፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡
3. ለምክር ቤቱ የሚቀርብ ሪፖርት የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡-

   ሀ/ ውይይት የተደረገባቸው ዋና ዋና ርዕሶች፤

   ለ/ አባሉ አስተያየት ለመሰብሰብ የተጠቀመባቸው ዘዴዎች፤

   ሐ/ በመስክ ስራው የተገኙ ዋና ዋና ጭብጦች፤

   መ/ ያጋጠሙ ዋና ዋና ችግሮች እና የተወሰዱ መፍትሄዎች፤

   ሠ/ በጉዳዩ ላይ የአባሉ አስተያየት፣

   ረ/ የአባሉ የምርጫ ክልል፣ስም እና ፊርማ።
4. አባላት ትብብር ሲጠይቁ ከመራጮቻቸው ጋር የመገናኘት ተግባራቸውን በአግባቡ መወጣት እንዲችሉ በምርጫ አካባቢያቸው ትብብር የሚያገኙበት ሁኔታ በምክር ቤቱ ይመቻቻል።
5. አባላት ከመራጮቻቸው ጋር የሚያደርጉት ውይይት በፌደራል መንግስት የስልጣን ክልል ስር የሚወድቅ መሆን አለበት፡፡
6. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (5/ የተደነገገው እንደ ተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል ከፌደራል መንግስት የስልጣን ክልል ውጭ የሆነ ጉዳይ በመራጩ ህዝብ ሲቀርብለት በደረጃው ከሚገኝ የክልል አካል ጋር ሊወያይ ይችላል፡፡

### 114. አባላት ከመራጮቻቸው ጋር የሚገናኙበት መንገድ

አባላት በሚከተለው መንገድ ከመራጮቻቸው ጋር በመገናኘት ስራቸውን ሊያከናውኑ ይችላሉ፡-

1. መራጩን ህዝብ እንደ አመቺነቱ በመሰብሰብ፤
2. መንግስታዊ እና መንግስታዊ ያልሆኑ አካላትን በማነጋገር፤
3. ጥቆማዎችን፣ ሙያዊ አስተያየቶችን በማሰባሰብ።

## ምዕራፍ አስራ አምስት

## ሌሎች የምክር ቤት ተግባራት

### 115. የምክር ቤት አባልን የህግ ከለላ ስለማንሳት

1. በወንጀል የተጠረጠረ ማንኛውም አባል በዚህ ደንብ አንቀጽ 119 የተደነገገው ሥነ-ሥርዓት ሳይሟላ በቀጥታ ለመያዝም ሆነ ለመክሰስ ፈቃደኛ ቢሆንም የሚመለከተው የፍትህ አካል አባሉን መያዝም ሆነ መክሰስ አይችልም።
2. ለምክር ቤት አባል የተሰጠው የህግ ከለላ እንዲነሳ የሚፈልግ አካል፡-
   ሀ/ የመያዝና የመክሰስ ስልጣን ያለው የፌደራል የፍትህ አካል በሆነ ጊዜ ጥያቄው ለምክር ቤቱ የሚቀርበው በፍትህ ሚኒስትሩ ወይም በፌደራል ጠቅላይ ዓቃቤ ህግ ወይም በፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር[16] በተፃፈ ደብዳቤ ይሆናል፤
   ለ/ የመያዝና የመክሰስ ስልጣን ያለው የክልል መንግስት የፍትህ አካል በሆነ ጊዜ ጥያቄው ለምክር ቤቱ የሚቀርበው በክልሉ ርዕስ መስተዳድር በተፃፈ ደብዳቤ ይሆናል፡፡
3. ማንኛውም የህግ ከለላ የማንሳት ጥያቄ ለአፈጉባዔው በጽሑፍ መቅረብ አለበት፡፡
4. አፈጉባዔው የቀረበለትን የህግ ከለላን የማንሳት ጥያቄ በቀጥታ ለምክር ቤቱ ሊያቀርበው ወይም ለህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሊመራው ይችላል፡፡
5. ምክር ቤቱ በአፈጉባዔው በኩል የቀረበለትን የህግ ከለላ የማንሳት ጥያቄ እንደ ሁኔታው ተጣርቶ የውሳኔ ሃሳብ እንዲቀርብለት ለህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሊመራው ወይም በቀጥታ ውሳኔ ሊሰጥበት ይችላል፡፡
6. የህግ ከለላ የማንሳት ጥያቀው የተመራለት የህግ፣ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሪፖርት ሲያዘጋጅ አባሉ ወንጀል መፈፀሙን የማረጋገጥ ስልጣን የመደበኛ ፍርድ ቤት ሆኖ የኮሚቴው ድርሻ የህግ ከለላን ለማንሳት የሚያስችሉ በቂ አመላካች ሁኔታዎች መኖራቸውን ማረጋገጥ ይሆናል፡፡
7. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (6/ የተጠቀሱት ሁኔታዎች መኖራቸውን ለመገንዘብ ቋሚ ኮሚቴው አስፈላጊ የሰው ወይም የሰነድ ማስረጃዎች እንዲቀርብለት ወይም

[16] በ22/62 (2008/ አ. 943 መሰረት የፌደራል የሥነ-ምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ኮሚሽነር የመያዝና የመክሰስ ስልጣን የለውም፡፡

የሚመለከተው አካል ጉዳዩን በአካል ቀርቦ እንዲያስረዳ ወይም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጥያቄው የቀረበበትን አባል ሊጠይቅ ይችላል፡፡

8. ቋሚ ኮሚቴው የውሳኔ ሃሳብ ሲያዘጋጅ ተፈፀመ የተባለውን ወንጀል አጠቃላይ ክብደትና አመላካች ሁኔታዎችን አገናዝቦ በመገምገም ይሆናል፡፡

9. ምክር ቤቱ የቀረበለትን ሪፖርት እና የውሳኔ ሃሳብ መነሻ በማድረግ ውሳኔ ያስተላልፋል።

10. ምክር ቤቱ የደረሰበትን ውሳኔ በአፈጉባዔው በኩል የህግ ከለላው እንዲነሳ ለጠየቀው አካል እና ለሚመለከተው አባል በፅሑፍ ያሳውቃል።

11. የህግ ከለላው የተነሳበት አባል በሌሎች ህጎች የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ የምክር ቤት አባልነቱ አይቋረጥም እንዲሁም በምክር ቤት አባልነቱ የሚያገኘው ደሞዝ፣ የቤት ኪራይ አበል፣ የታሰረ ከሆነ ደግሞ በመታሰሩ ምክንያት ሊቋረጡ የማይገባቸው ሌሎች ጥቅማጥቅሞች አይቋረጡበትም።

12. በአንድ የወንጀል ድርጊት ተጠርጥሮ የህግ ከለላው የተነሳበት አባል በዚህ ጊዜ ውስጥ በሌላ የወንጀል ድርጊት ቢጠረጠር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ ሊያዝ ወይም ሊከሰስ አይችልም።

13. በምክር ቤቱ የተነሳ የህግ ከለላ በሚከተሉት ሁኔታዎች ለአባሉ ሊመለስ ይችላል፦

ሀ/ የሚመለከተው የወንጀል መርማሪ ወይም ከሳሽ የሆነ አካል አባሉን ሊያስከስሰው የሚያስችል ጭብጥ ባለማግኘቱ የክስ መዝገቡን የዘጋ እንደሆነ፤

ለ/ ክስ የቀረበለት ፍርድ ቤት አባሉ ከወንጀሉ ነፃ መሆኑን ሲያረጋግጥ፤

ሐ/ በሌላ ህግ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር የሚመለከተው ፍርድ ቤት በአባሉ ላይ የጥፋተኛነት ፍርድ ሲሰጥ እና እስራት ተፈርዶበት ከሆነ እስራቱን ሲጨርስ፡፡

14. የህግ ከለላው የተነሳበት አባልን ጉዳይ በምን ሂደት ላይ እንደሚገኝ የህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን በያዙት የፍትህ አካላት ሥራ ውስጥ ጣልቃ ሳይገባ ይከታተላል፣ አስፈላጊ ከሆነም ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያደርጋል፡፡

15. የህግ ከለላው እንዲነሳ ጥያቄ ያቀረበው አካል የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ በፅሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

116. <u>ስለጉብኝት እና ስብሰባ ተሳትፎ</u>

1. አባላት ምክር ቤቱን በመወከል በአገር ውስጥ ወይም በውጭ አገር የሥራ ጉብኝት ሊያደርጉ ወይም በስብሰባ ሊካፈሉ ይችላሉ፡፡
2. ምክር ቤቱን በመወከል በማንኛውም ጉብኝት ወይም ስብሰባ የሚካፈል አባል ለጉዳዩ አግባብነት ያለው መሆን ይገባዋል።
3. ምክር ቤቱን በመወከል በማናቸውም ጉብኝት ወይም ስብሰባ የተከፈለ አባል ስለ ተልዕኮው ለሚመለከተው አካል ሪፖርት ማቅረብ አለበት፡፡
4. ምክር ቤቱ የስብሰባ ወይም የጉብኝት ሪፖርቶች በአግባቡ እንዲያዙ ያደርጋል፡፡

117. <u>ስለ ሽልማት እና ስጦታ</u>

1. ምክር ቤቱ በሚከተሉት ሁኔታዎች ሽልማት ወይም ስጦታ ሊያበረክት ይችላል፦
   ሀ/ በአገር አቀፍ ደረጃ ጥሩ ውጤት እና ዓርዓያነት ያለው ተግባር ላከናወነ ግለሰብ ወይም አካል፤
   ለ/ ምክር ቤቱን ለሚጎበኝ የውጭ አገር እንግዳ ወይም አካል፤
   ሐ/ ምክር ቤቱን በመወከል ወደ ውጭ አገር በሚሄዱ አባላት አማካኝነት ለውጭ አገር ሰው ወይም አካል፤
2. ማንኛውም በምክር ቤቱ ስም የሚሰጥ ሥጦታ ወይም ሽልማት በተቻለ መጠን የምክር ቤቱ የውስጥ አርማ ወይም ሎጎ፣ ስም እና የመሳሰሉትን የሚገልጽ መሆን አለበት፡፡
3. ምክር ቤቱ ከውጭ ወይም ከአገር ውስጥ ሽልማት ወይም ስጦታ ሊቀበል ይችላል፤
4. ምክርቤቱ የሚያበረክተውም ሆነ የሚቀበለው ስጦታ ወይም ሽልማት የአገሪቱንና የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ የጠበቀ መሆን አለበት፡፡
5. በምክር ቤቱ ስም ሽልማት ወይም ስጦታ የተቀበለ ማንኛውም አባል ስጦታውን ወይም ሽልማቱን ለአፈጉባዔዉ ማስረከብ ይኖርበታል።
6. ለምክር ቤቱ የተበረከተ ስጦታ ወይም ሽልማት ለዚሁ ተብሎ በተዘጋጀ ቦታ ይቀመጣል።

118. <u>በክብር እንግድነት ስለመገኘት</u>

1. ምክር ቤቱ በክብር እንግድነት እንዲገኝ የቀረበለትን ግብዣ እንደ ሁኔታው ሊቀበለው ይችላል፡፡

2. ምክር ቤቱን በመወከል በክብር እንግድነት ሊገኝ የሚችለው አፈጉባዔው ወይም ምክትል አፈጉባዔው ወይም በአፈጉባዔው የሚወክል አባል ይሆናል፡፡
3. የክብር እንግድነቱ የመክፈቻ ወይም የመዝጊያ ንግግር ማድረግን የሚጠይቅ ሲሆን ንግግሩ በፅሁፍ መዘጋጀት አለበት፡፡

## ምዕራፍ አስራ ስድስት

## የአባላት መብት

119. ያለመያዝና ያለመከሰስ መብት

በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 54 (6/ መሠረት ማንኛውም አባል ከባድ ወንጀል ሲፈፅም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም በወንጀልም አይከሰስም፡፡

120. በቋንቋው የመናገር መብት

በዚህ ደንብ አንቀፅ 25 በተደነገገው መሠረት ማንኛውም አባል በምክር ቤቱ የስብሰባ ወቅት በቋንቋው የመናገር መብት አለው፡፡

121. በሚሰጠው ድምፅ ወይም አስተያየት ያለመጠየቅ መብት

በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 54 (5/ መሠረት ማንኛውም አባል በሚሰጠው ድምፅ ወይም አስተያየት ምክንያት አይከሰስም፤ አስተዳደራዊ እርምጃም አይወሰድበትም፡፡

122. ከመራጭ ህዝብ ጋር የመገናኘት መብት

ማንኛውም አባል ከመራጩ ህዝብ ጋር የመገናኘት መብት አለው፡፡

123. በኮሚቴ ስብሰባ የመገኘት መብት

የዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ ማንኛውም አባል ቋሚ ኮሚቴ በሚያዘጋጀው ስብሰባ ያለድምፅ የመሳተፍ መብት አለው፡፡

124. የህግ ረቂቅ የማመንጨት እና አጀንዳ የማቅረብ መብት

ማንኛውም አባል በዚህ ደንብ መሠረት ረቂቅ ህግ የማመንጨት እና አጀንዳ የማቅረብ መብት አለው፡፡

125. የወሊድ ፈቃድ የማግኘት መብት

ሴት የምክር ቤት አባል የሦስት ወር የወሊድ ፈቃድ የማግኘት መብት አላት።

126. አባልነትን የመተው መብት

1. ማንኛውም አባል በማንኛውም ጊዜ በራሱ ፈቃድ የምክር ቤት አባልነቱን ሊተው ይችላል፡፡

2. የምክር ቤት አባልነቱን ለመልቀቅ የሚፈልግ አባል ጥያቄውን ለአፈጉባዔው በጽሑፍ ማቅረብ አለበት፡፡
3. አፈጉባዔዉ የቀረበለትን ከአባልነት የመልቀቅ ጥያቄ ለምክር ቤቱ ያሳውቃል።
4. አፈጉባዔው ጥያቄውን ለምክር ቤቱ ካሳወቀበት ጊዜ ጀምሮ አባልነቱ ይቋረጣል፡፡

127. ስለቀድሞ የምክር ቤት አባላት መብት

በሌሎች ህጎች የተደነገጉት እንደተጠበቀ ሆኖ የቀድሞ የምክር ቤት አባል የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

1. ያከናወናቸውን ሥራዎች በሚገልፅ ሁኔታ የተዘጋጀ የምስክር ወረቀት፣ የቀድሞ የምክርቤቱ አባል መሆኑን የሚገልፅ መታወቂያ እና ደብዳቤ ይሠጠዋል፤
2. በሌላ የመንግሥት ሥራ በሚመደብበት ወይም በሚቀጠርበት ጊዜ በምክር ቤቱ ያገለገለበት ዘመን በመንግሥት የሥራ አገልግሎት ዘመንነት ይያዝለታል፤
3. በማንኛውም የሥራ ቀን ወደ ምክር ቤቱ ግቢ የመግባት፣በቤተ-መፅሃፍት የመጠቀም፣ ለምክር ቤቱ እድገት የሚያገለግሉ ሃሳቦችን የማቅረብ መብት ይኖረዋል።

128. አገልግሎት ስለማግኘት

የምክር ቤት አባላት ለስራቸው የሚያስፈልግ አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ በመመሪያ ይወሰናል፡፡

## ምዕራፍ አሥራ ሰባት
## የአባላት ሥነ-ምግባር

129. አጠቃላይ መርህ

ማንኛውም አባል በዓለም አቀፍም ሆነ በአገር አቀፍ ደረጃ በግልፅ የታወቁትን የሥነ-ምግባር መርሆዎች ከሥራው ጋር አጣጥሞ በተግባር ላይ ማዋል ይጠበቅበታል፡፡

130. አገራዊ እሴቶችን ስለማዳበር

1. ማንኛውም አባል ለኢትዮጵያ ህዝቦች ታማኝነትን አገልጋይ እና ዓርዓያ መሆን ይኖርበታል።
2. ማንኛውም አባል ሕገመንግሥቱንና ሌሎች ህጎችን ማክበርና ማስከበር አለበት፡፡
3. ማንኛውም አባል ተግባሩ የአገሪቱንና የህዝቦቿን ጥቅም በማስቀደም፣ በማስጠበቅ እና በማክበር ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት፡፡

131. <u>ሀቀኛና ግልጽ ስለመሆን</u>
1. በዚህ ደንብ በአንቀፅ 135 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል በማንኛውም ጊዜ ሀቀኛና ግልጽ መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም አባል የሃሰት ማስረጃዎችን ወይም ያልተጣሩ ጉዳዮችን እውነት አስመስሎ ለምክር ቤቱ ማቅረብ የለበትም፡፡

132. <u>ሥልጣንን በአግባቡ ስለመጠቀም</u>
1. ማንኛውም አባል በህግ የተሰጠውን ስልጣን ያለአግባብ መጠቀም የለበትም፡፡
2. የዚህ አንቀፅ የንዑስ አንቀፅ (1/ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም አባል ስልጣንና ተግባሩን የህዝብን እና የዜጎችን ጥቅም ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ከማስከበር ውጭ ለግል ጥቅም እና አድሏዊ ተግባራትን ለመፈፀም መጠቀም የለበትም፡፡

133. <u>ሃላፊነትን ስለመወጣት</u>
1. አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር ማንኛውም አባል ለምክርቤቱ ሥራ ሲመረጥ ወይም ሲወክል በሙሉ ፈቃደኝነት ማገልገል ይጠበቅበታል፡፡
2. ማንኛውም አባል በህዝብ የተጣለበትን አደራ እና በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ተግባራት ሙሉ እውቀቱንና ልምዱን በአግባቡ በመጠቀም ኃላፊነቱን በብቃት መወጣትይኖርበታል።

134. <u>የምክር ቤቱን ክብርና ሞገስ ስለመጠበቅ</u>
1. ማንኛውም አባል በማንኛው ምቦታ የምክርቤቱን ክብርና ሞገስ የጠበቀ መሆን አለበት፡፡
2. ማንኛውም አባል ከአላስፈላጊ ተግባራት መቆጠብ አለበት፡፡
3. ማንኛውም አባል በምክርቤቱ ቅጥር ግቢ ውስጥ ሌላውን ሰው መሳደብ፣ ማንጓጠጥ፣ መተንኮስ ወይም የምክር ቤቱን ተግባራት ማወክ የለበትም፡፡

135. <u>ሚስጥር ስለመጠበቅ</u>

አባላት ሥራቸውን በግልፅ የማከናወን መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ፦

1. ማንኛውም አባል በሥራው አጋጣሚ ወይም በሌላ ምክንያት ያወቃቸውን የመንግስት ወይም የህዝብ ጥቅም፣ ሰላምና ፀጥታ ሊጎዱ የሚችሉ በሚስጥር መጠበቅ ያለባቸው ጉዳዮችን በሚስጥር መያዝ አለበት፤
2. ማንኛውም አባል በምክር ቤቱ ዝግ ስብሰባ ታይቶ አግባብ ባለው ሥነሥርዓት ግልፅ ከመሆኑ በፊት ሚስጥር ማውጣት የለበትም፤
3. ማንኛውም የኮሚቴ አባል በኮሚቴ በመታየት ላይ ያለና ኮሚቴው ለምክር ቤቱ ሪፖርት እስከሚያደርግ ድረስ በሚስጥር እንዲያዝ የወሰነውን ጉዳይ በሚስጥር መያዝ ይጠበቅበታል፡፡

136. <u>ከሙስና የፀዳ ስለመሆን</u>

1. ማንኛውም አባል ከሙስና ተግባር ራሱን በማፅዳት የሙስና ድርጊቶችን መቃወም፣ በተጨባጭ ሙስናን መዋጋት እና በፀረ-ሙስና ትግል ዓርዓያ መሆን ይጠበቅበታል፡፡
2. ማንኛውም አባል በገንዘብ ወይም በሌሎች ጥቅማጥቅሞች በመደለል በምክር ቤቱ ውስጥ አስተያየት ወይም ድምጽ መስጠት ወይም ሌሎች ተግባራትን ማከናወን የለበትም፡፡
3. ማንኛውም አባል የሕዝብን ገንዘብ ከማባከን፣ከማጭበርበር፣እምነት ከማጉደል እና ከመሳሰሉት የጸዳ መሆን ይጠበቅበታል፡፡
4. ማንኛውም አባል አግባብ ባለው ህግ መሠረት ሃብተና ንብረቱን የማስመዝገብ ግዴታ አለበት፡፡

137. <u>ህዝብን ከህዝብ ከሚያጋጩ ድርጊቶች ስለ መቆጠብ</u>

1. ማንኛውም አባል በማንኛውም መንገድ ህዝብን ከህዝብ ከሚያጋጩ፣ ከአመጽ፣ ከአድማ፣ ከሁከት እና ከመሳሰሉት ሕገ ወጥ ድርጊቶች መቆጠብ ይጠበቅበታል፡፡
2. ማንኛውም አባል አንዱን በመደገፍ እና ሌላውን በማጥላላት ወይም ማንኛውንም አስተያየት በማቅረብ ብሔርን ከብሔር፣ ጎሣን ከጎሣ፣ ሃይማኖትን ከሃይማኖት እንደዚሁም ዜጎችን ለግጭት ማነሳሳትና ማጋጨት የለበትም፡፡

138. <u>ተጠያቂነት</u>

በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 12 መሠረት ማንኛውም አባል ስለሚያከናው ነው ተግባር ሁሉ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

139. <u>ዓርዓያ ስለመሆን</u>

1. ማንኛውም አባል በራስ የመተማመን አቅሙን በማጎልበትና በሃላፊነት ስሜት ተግባራትን በመምራት፣ በመወሰን እና በማከናወን ዓርዓያ መሆን ይጠበቅበታል፡፡
2. ማንኛውም አባል የሃላፊነት ስሜት የሚሰማው፣ የተሻለ ለውጥን የሚደግፍ፣ የሥራ ባህልና በራስ መተማመን እንዲጎለብት የሚያደርግ፣ በአመራር ስጭነቱ ለስራ ባልደረቦቹ እና ለህዝቡ ዓርዓያ መሆን ይጠበቅበታል፡

140. <u>የጥቅም ግጭት</u>

1. ማንኛውም አባል በምክር ቤቱ ተመርጦ ወይም ተወክሎ በሚያከናው ነው ተግባር ምክንያት የቀረበለት ጉዳይ ከራሱም ሆነ ከቅርብ ዘመዱ ጥቅም ጋር ተያይዞ ሲያገኘው እንደአግባቡነቱ ለምክር ቤቱ፣ ለአፈጉባዔው ወይም አባል ለሆነበት ኮሚቴ በማሳወቅ ጉዳዩን ከማየት ራሱን ማግለል ይኖበታል፡፡
2. ማንኛውም አባል ከተጣለበት ኃላፊነት ጋር በማይጣጣም ወይም የተሰጠውን አደራ በሚያጓድል ወይም የምክርቤቱን ክብርና ሞገስ በሚያጉድፍ ሥራ ላይ ተቀጥሮም ሆነ በግሉ መሰማራት የለበትም፡፡
3. ምክር ቤቱ ከሌሎች አካላት ጋርየሚኖረው መተባበርና መደጋገፍ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ኮሚቴ ወይም አባል ከማንኛውም መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆነ አካል ወይም ሃላፊ ወይም ግለሰብ ሃብት፣ ስፖንሰርሺፕ ወይም ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን መጠየቅ፣ ማፈላለግ ወይም መቀበል የለበትም፡፡

## <u>ምእራፍ አስራ ስምንት</u>

## <u>የአባላትን መብት እና ሥነ-ምግባር ስለ ማስከበር</u>

141. <u>ጠቅላላ ድንጋጌ</u>

በሌሎች ህጎች የተቀመጡት ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የአባላት መብትና ሥነ-ምግባር ማስከበርን በተመለከተ የዚህ ምዕራፍ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

142. <u>መብትን ስለ ማስከበር</u>

1. ማንኛውም አባል ወይም የቀድሞ የምክር ቤት አባል መብቴ ተጥሷል ወይም መብቴ ተግባራዊ ይሁንልኝ የሚል ጥያቄ ካለው ጥያቄውን ለአፈጉባዔው ወይም ለህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀፅ በንዑስአንቀፅ (1/ የተደነገገው ቢኖርም የመብቱ መከበር ጥያቄ አብዛኛዎቹን አባላት የሚመለከት በሆነ ጊዜ ጥያቄው ለምክር ቤቱ ቀርቦ እንዲታይ ይደረጋል።

3. ጥያቄው የቀረበለት የህግ፣ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ጉዳዩን በማጣራት አስተያየቱን ለአፈጉባዔው ያቀርባል።
4. አፈጉባዔው በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ እና (3/ መስረት የቀረበለትን ጉዳይ በተለያዩ መንገዶች በማጣራት አስፈላጊውን አስተዳደራዊ ውሳኔ ይስጥበታል ወይም ለምክር ቤቱ አቅርቦ ያስወስናል፡፡
5. ምክር ቤቱ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ ወይም (4/ መስረት የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
6. የመብቱ መጣስ ሁኔታ ሳያቋርጥ በተከታታይ እየተፈፀመ ያለ ካልሆነ በስተቀር መብቱ እንዲከበርለት የሚፈልግ ማንኛውም አባል ወይም የቀድሞ የምክር ቤት አባል መብቱ ከተጣሰበት ጊዜ ጀምሮ በሦስት ወራት ጊዜ ውስጥ ጥያቄውን ካላቀረበ በይርጋ ይታገድበታል፤ የማቀረቢያው ጊዜም ለቀጣይ የምክር ቤቱ ዘመን አይሸጋገርም፡፡
7. አፈጉባዔው በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (4/ እና (5/ መሠረት የተሰጡ ውሳኔዎችን እየተከታተለ እንዲፈፀሙ ያደርጋል፡፡

143. <u>ሥነ-ምግባርን ስለ ማስከበር</u>

1. ምክር ቤቱ በዚህ ደንብ የተደነገገውን ሥነ-ምግባር ወይም ሥነ-ሥርዓት በሚጥስ ወይም ተግባራዊ በማያደርግ ማንኛውም አባል ላይ አስፈላጊውን የዲስፕሊን እርምጃ ይወስዳል።
2. ማንኛውም አባል የሥነ-ምግባር ወይም የሥነ-ሥርዓት ጉድለት መኖሩን ሲገነዘብ ጉድለት ፈጽሟል በተባለው በማንኛውም አባል ላይ አስፈላጊው የዲስፕሊን እርምጃ እንዲወሰድበት ምክርቤቱን ሊጠይቅ ይችላል፡፡
3. በዚህ አንቀፅ ንዑስአ ንቀፅ (2/ መሠረት የሚቀርብ ጥያቄ በጽሑፍ ሆኖ ከነማስረጃው ለአፈጉባው መቅረብ ይኖርበታል።
4. አፈጉባዔው ጉዳዩን ለህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ይመራዋል፤ ምክር ቤቱም ቋሚ ኮሚቴው የሚያቀርበውን ሪፖርት እና የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ አስፈላጊውንውሳኔ ይሰጣል፣ ውሳኔውም የመጨረሻ ይሆናል፡፡
5. የዲስፕሊን እርምጃ እንዲወሰድበት ጥያቄ የቀረበበት ማንኛውም አባል ራሱን የመከላከል መብት ይኖረዋል።
6. ማንኛውም የዲስፕሊን እርምጃ እንዲወስድ የሚቀርብ ጥያቄ ተጣሰ የተባለው የሥነ-ምግባር ጉዳይ ከተፈጸመበት ከአንድ ዓመት በኋላ ሊቀርብ አይችልም፤ ጥያቀው ለቀጣይ የምክር ቤቱ ዘመንም አይሸጋገርም።

7. ምክር ቤቱ እንደሁኔታው ደረጃውን ጠብቆ የሚከተሉትን የዲስፕሊን እርምጃዎች ሊወሰድ ይችላል፦

ሀ/ የቃል ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ለ/ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ መስጠት፤

ሐ/ ከሃያ አራት የስብሰባ ቀናት ያልበለጠ እገዳ ማድረግ እና እንደሁኔታውም አባሉ ለታገደበት ጊዜ ያገኝ የነበረውን ደመወዝ እንዳይከፈለው ማድረግ፤

መ/ ጥፋቱ ከባድ ከሆነ ወይም ሲደጋገም በህግ መሠረት ከአባልነት ማስወገድ፡፡

8. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (7/ (መ/ መሠረት የተላለፈውን ውሳኔ አግባብ ባለው ህግ መሠረት አስፈላጊው እንዲፈጸም ምክርቤቱ ለብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ያሳውቃል።

9. በዚህ ደንብ መሠረት በአፈጉባዔው ቅጣት የተወሰነበትና በውሳኔው ቅር የተሰኘ አባል አቤቱታውን ለህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ይህ አቤቱታም ቅጣት የተወሰነበት አባል ውሳኔው ከደረሰው ቀን ቀጥለው ባሉት ሁለት ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ መቅረብ አይችልም።

10. ኮሚቴው በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (9/ መሠረት የቀረበለትን አቤቱታ መርምሮ ለምክር ቤቱ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ በማቀረብ ያስወስናል።

## ምዕራፍ አስራ ዘጠኝ

## ስለ ኮሚቴዎች

### 144. ጠቅላላ ድንጋጌ

በዚህ ደንብ በሌላ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ኮሚቴዎች በዚህ ምዕራፍ በተዘረዘሩት ድንጋጌዎች ይመራሉ፡፡

### 145. የኮሚቴ አደረጃጀት

በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 55 (19/ መሰረት ምክርቤቱ የሚከተሉት የኮሚቴ ዓይነቶች ይኖሩታል፡-

1. የምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ፤
2. አስተባባሪ ኮሚቴ፤
3. ልዩ ኮሚቴ፤
4. ቋሚ ኮሚቴ፤
5. ንዑስ ኮሚቴ፤

6. ጊዜያዊ ኮሚቴ

146. <u>ስለ ኮሚቴ ስብሰባ</u>

1. የኮሚቴ ስብስባ የሚመራው በሊቀመንበሩ ሆኖ ከአባላቱ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
2. ማንኛውም የኮሚቴ ሊቀመንበር ስብሰባ ከመጀመሩ በፊት ምልዓተ ጉባዔ መሟላቱን ማረጋገጥና ለአባላቱ መግለፅ አለበት፡፡
3. የኮሚቴውን ስብስባ ለማካሄድ አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን የኮሚቴው ሊቀመንበር አስቀድሞ ማረጋገጥ አለበት፡፡
4. ለውይይት የሚያስፈልግ ሰነድ ለአባላት በቅድሚያ መድረስ አለበት፡፡
5. ማንኛውም የኮሚቴ አለታዊ አጀንዳ በአመራሩ ወይም በአባላቱ ሊመነጭ ይችላል፣ አጀንዳውም በስብሰባው ከተገኙ አባላት በአንድ ሦስተኛ ድምጽ መጽደቅ ይኖርበታል፣ የአጀንዳው ቅደም ተከተል በሊቀመንበሩ ይወሰናል፡፡
6. ለውይይት የሚያስፈልገው ጊዜ አመራሩ በሚያቀርበው መነሻ ሃሳብ በኮሚቴው ይወሰናል፡፡
7. የኮሚቴ ስብስባ በአማርኛ ቋንቋ ይካሄዳል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ምስክር ወይም ማስረጃ በሚሰማበት ወይም በሚቀበልበት ጊዜ የትርጉም አገልግሎት ሊጠቀም ይችላል፡፡
8. የኮሚቴ መደበኛ የስራ ቦታ በምክር ቤት ቅጥር ግቢ ለዚሁ ተብሎ በተመደበ ቢሮ ወይም አዳራሽ ይሆናል፣ ሆኖም ኮሚቴው አፈጉባዔውን በማስፈቀድ ከምክር ቤት ቅጥር ግቢ ውጭ ስብሰባ ማካሄድ ይችላል፡፡
9. ኮሚቴው ወይም አመራሩ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ከመደበኛ ስብስባ ውጭ ስብስባ ሊያካሒድ ይችላል፡፡
10. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ወይም በሊቀ መንበሩ ፈቃድ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም የኮሚቴ አባል በኮሚቴ ስብስባ መገኘት ይኖርበታል።
11. ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ከስብሰባ የቀረ አባል የቀረበትን ምክንያት ለኮሚቴው ሊቀመንበር ማስረዳት ይኖርበታል።
12. የኮሚቴ ውሳኔ በስብስባ በተገኙ አባላት አብላጫ ድምፅ ይፀድቃል፣ ድምፅ እኩል በእኩል በሚሆንበት ጊዜ ሊቀመንበሩ የሚደግፈው ሃሳብ የኮሚቴው ውሳኔ ይሆናል።
13. ምክር ቤቱ በዕረፍት ላይ በሚሆንበት ጊዜ በኮሚቴ መከናወን የሚገባው አስቸኳይ ጉዳይ ሲያጋጥም የኮሚቴው ሊቀመንበር አባላትን ሊጠራ ይችላል፡፡

14.የኮሚቴው ስብሰባ በእለቱ የማይካሄድ ወይም በሰዓቱ የማይጀመር ከሆነ ሊቀመንበሩ ጉዳዩን አባላት እንዲያውቁት ያደርጋል፡፡

147. <u>ተጠሪነት</u>

1. እያንዳንዱ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ይሆናል፡፡
2. የኮሚቴ ሊቀመንበር ተጠሪነቱ ለአፈጉባዔውና ለኮሚቴው ይሆናል፡

148. <u>የስራ ዘመን</u>

1. የኮሚቴ የስራ ዘመን የምክር ቤቱ የስራ ዘመን ይሆናል፡፡
2. የኮሚቴ የሥራ ወቅት ከምክር ቤቱ የሥራ ወቅት ጋር ተመሳሳይ ነው፣ ሆኖም በአፈጉባዔው ፈቃድ በዕረፍት ጊዜ ስራውን ማከናወን ይችላል፡፡

149. <u>ስለማስረጃ</u>

1. በኮሚቴ የሚሰማ ምስክርነት በሚስጥር የሚካሄድ ወይም የማይካሄድ መሆኑ በኮሚቴው ይወሰናል፡፡
2. ለኮሚቴ የቀረበ የማስረጃ ሰነድ ያለኮሚቴው ፈቃድ ሊለወጥ ወይም ሊወሰድ አይችልም።

150. <u>ስለ ሪፖርት</u>

እያንዳንዱ ኮሚቴ የስራውን እንቅስቃሴና የተሰጠውን ተልዕኮ በሚመለከት ለምክርቤቱ ወይም ለአፈጉባዔው ወይም ተጠሪ ለሆነለት አካልበ ሊቀመንበሩ አማካኝነት ሪፖርትያቀርባል።

151. <u>የውስጥ አደረጃጀት እና አሰራር</u>

1. ማንኛውም ኮሚቴ ለስራው ቅልጥፍና እንዲረዳው ለራሱ ተጠሪ የሆነ ንዑስ ኮሚቴ ከአባላቱ መካከል ሊያቋቁም ይችላል፣ ስልጣንና ተግባሩንም በመለየት ይወስናል።
2. እያንዳንዱ ኮሚቴ እንደ አስፈላጊነቱ ድጋፍ ሰጪ ሰራተኛ ይኖረዋል።
3. እያንዳንዱ ኮሚቴ በዚህ ደንብ መሰረት የራሱን የውስጥ አሰራር መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

<u>ምዕራፍ ሃያ</u>

<u>የምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ</u>

152. <u>አደረጃጀት</u>

1. አፈጉባዔውን፣ ምክትል አፈጉባዔውንና የፓርቲ ተጠሪዎችን ጨምሮ የምክር ቤቱ የፓርላማ ቡድኖች ባላቸው መቀመጫ መጠን የሚወከሉበት በአፈጉባዔ የሚመራ የምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ ይደራጃል፡፡
2. አማካሪ ኮሚቴው በየምክር ቤቱ የስራ ዘመን የሚደራጅ ሆኖ ቁጥሩ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1/ መሰረት በፓርቲ ተጠሪዎች ምክክር ተደርጎበት በምክር ቤቱ ይወሰናል፡፡

153. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

የምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

1. በዚህ ደንብ በአንቀፅ 32 መሰረት ምክር ቤቱ የሚወያይበትን አጀንዳ ይቀርፃል፤
2. በዚህ ደንብ በአንቀፅ 34 መሰረት ለእያንዳንዱ አጀንዳ የሚያስፈልገውን የውይይት ጊዜ ይመድባል፤
3. የምክር ቤቱን ረቂቅ ዓመታዊ በጀት በማዘጋጀት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤
4. የምክር ቤቱን የሰው ሀይል፣ የፋይናንስ እና የንብረት አስተዳደር ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም በአፈጉባዔው በኩል ተገቢ እርምጃ እንዲወሰድ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤
5. በዚህ ደንብ ላይ አስፈላጊ መስሎ የታየውን ረቂቅ ማሻሻያ ሃሳብ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣
6. በዚህ ደንብ አንቀፅ 3 የተደነገገውን መርህ በመከተል ይህን ደንብ ይተረጉማል፤
7. ለዚህ ደንብ አፈፃፀም የሚረዳ መመሪያ ወይም ማንዋል ያወጣል፤
8. በአፈጉባዔው ሲጠየቅ በምክር ቤቱ ጉዳዮች ዙሪያ የምክር አገልግሎት ይሰጣል፤
9. ስራውን አስመልክቶ ዓመታዊ ሪፖርት ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤
10. በአፈጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

154. <u>የስብሰባ ጊዜ እና የውሳኔ አሰጣጥ</u>

1. የምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ በየሳምንቱ አርብ ይሰበሰባል፣ ሆኖም አፈጉባዔው አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በማንኛውም ጊዜ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
2. ማንኛውም የአማካሪ ኮሚቴ አባል አስቸኳይ ስብሰባ እንዲጠራለት አፈጉባዔውን በፅሁፍ ሊጠይቅ ይችላል፣ አፈጉባዔው ጥያቄውን ከተቀበለው ስብሰባውን ሊጠራ ይችላል፡፡

3. የአማካሪ ኮሚቴው ውሳኔ በአብላጫ ድምፅ ይወሰናል፡፡

4. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (3) የተደነገገው ቢኖርም አማካሪ ኮሚቴው የእለታዊ አጀንዳ አቀራረፅና የጊዜ አመዳደብ በዚህ ደንብ አንቀፅ 32 (3) እና አንቀፅ 34 (1) መሠረት በስምምነት ይወሰናል።

## ምዕራፍ ሃያ አንድ

## አስተባባሪ ኮሚቴ

### 155. አደረጃጀት

1. የምክር ቤቱ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ አፈጉባዔው፤

ለ/ ምክትል አፈጉባዔው፤

ሐ/ የቋሚ ኮሚቴ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር፤

መ/ የዕህፈት ቤቱ ዋና ፀሃፊ፤

ሠ/ የመንግስት ዋና ተጠሪ፤

2. አስተባባሪ ኮሚቴው የሚመራው በአፈጉባዔው ይሆናል፡፡

### 156. ሥልጣንና ተግባር

የምክር ቤቱ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል፦

1. የቋሚ ኮሚቴዎችን አጠቃላይ የስራ ሂደት ያስተባብራል፣ ያቀናጃል፣ ስኬታማነቱን ይከታተላል፣

2. የቋሚ ኮሚቴዎችን አጠቃላይ የስራ እንቅስቃሴ ይገመግማል፤ መሰረታዊ በሆኑ ጉዳዮች ላይ አቅጣጫ ያስቀምጣል፤

3. ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከታተሏቸውንና የሚቆጣጠሯቸውን መንግስታዊ አካላትን ለይቶ ይመድባል፤

4. አዲስ የመንግስት መሥሪያ ቤት ሲመሰረት ወይም የመዋቅር ለውጥ ሲደረግ ከተቋሙ የስራ ባህሪ በመነሳት ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግበት ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ይመድባል፤

5. የቋሚ ኮሚቴዎችን እቅድና የአፈፃፀም ሪፖርት ይመረምራል፣ እንደአስፈላጊነቱ የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል፤

6. የምክር ቤቱን አገራዊና ዓለም አቀፋዊ የገፅታ ግንባታ ተግባርን ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤

7. የቋ ሚኮሚቴዎችን ፍላጐትና ውጤታማ ስለሚሆኑበት ሁኔታ ጥናት ያካሂዳል፤

8. አፈጉባዔው ወይም ቋሚ ኮሚቴዎች ወይም የራሱ አባላት በሚያቀርቧቸው ሌሎች ጉዳዮች ላይ ተወያይቶ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

157. **<u>የስብሰባ ጊዜ</u>**

የአስተባባሪ ኮሚቴው መደበኛ ስብሰባ በየአስራ አምስት ቀኑ በአፈጉባዔው በሚወሰነው ጊዜ ይካሄደል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሃያ ሁለት</u>

## <u>የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ጉዳዮች ልዩ ኮሚቴ</u>

158. **<u>መቋቋም</u>**

ምክር ቤቱ የአገሪቷን የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ጉዳዮችን በተመለከተ ክትትልና ቁጥጥር የሚያካሂድ የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ጉዳዮች ልዩ ኮሚቴ ይኖረዋል።

159. **<u>የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ጉዳዮች ልዩ ኮሚቴ ተግባርና ሃላፊነት</u>**

1. የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ጉዳዮች ልዩ ኮሚቴ የሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያካሂዳል፦

   ሀ/ የአገሪቷ የግዛት ሉዓላዊነት እየተከበረ መሆኑን፤

   ለ/ የአገሪቱን ሉዓላዊነት ሊያስከብር የሚችል የብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦችን ተዋፆ የጠበቀ የመከላከያ ሠራዊት መደራጀቱን፤

   ሐ/ የአገር መከላከያ ሰራዊት አባላት የስራ ሁኔታና አስተዳዳር፣

   መ/ ከሌሎች አገራት ጋር የሚደረጉ ወታደራዊ ስምምነቶችና አፈፃፀሞች፤

   ሠ/ ክፍለ አህጉራዊ፣ አህጉራዊና ዓለም አቀፍ የሰላም ስምምነቶችን፣ ግዴታዎችና አፈጻጸሞችን በተመለከተ፤

   ረ/ የአገር መከላከያ ሰራዊት በሌሎች አገራት የሚያካሂደውን የሰላም ማስከበር ተልዕኮ፤

   ሰ/ ለሕገመንግሥቱና ለሕገመንግሥታዊ ስርዓቱ በታማኝነትና በፅናት የሚቆም፣ አገራዊና አለም ዓቀፋዊ ተጨባጭ ሁኔታዎችን በማገናዘብ ዘመናዊና ጠንካራ ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት መገንባቱን፤

   ሸ/ ጥራት ያለው መረጃ በማቅረብና አስተማማኝ የደህንነት አገልግሎት በመስጠት የአገሪቷ ብሔራዊ ደህንነት እየተጠበቀ መሆኑን፤

   ቀ/ የዜግነት እና የኢሚግሬሽን ጉዳዮች በህግ መሠረት ተግባራዊ መሆናቸውን፤

በ/ የአገሪቱን የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አፈፃፀም፤

ተ/ የፌዴራል ዋና ኦዲተር በመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ተቋማት የሂሣብና ገንዘብ ነክ ሰነዶች ላይ አግባብ ባለው ህግ መሰረት በሚያደርገው ምርመራ የሚያቀርባቸው የኦዲት ግኝት ሪፖርቶችን፤

ቸ/ የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ተቋማት በጀት አፈፃፀም።

2. ልዩ ኮሚቴው የሚያካሂደው አጠቃላይ የክትትልና ቁጥጥር ተግባር በመከላከያ እና በብሔራዊ መረጃና ደህንነት ተቋማት ማቋቋሚያ ህጎች በተደነገገው መሠረት ይፈፀማል።

160. <u>**የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ጉዳዮች ልዩ ኮሚቴ አባላት**</u>

1. አፈጉባዔው የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ጉዳዮች ልዩ ኮሚቴ ሰብሳቢ ይሆናል፡፡
2. ልዩ ኮሚቴው ሰብሳቢውንና ምክትል ሰብሳቢውን ጨምሮ ሰባት አባላት ይኖሩታል።
3. የልዩ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢና ሌሎች አባላት በአፈጉባዔው አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይመረጣሉ።

161. <u>**የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ጉዳዮች ልዩ ኮሚቴ ስብሰባ እና የሪፖርት አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት**</u>

1. አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በስተቀር የልዩ ኮሚቴው ስብሰባዎች በዝግ ይካሄዳሉ።
2. ኮሚቴው ስላካሄደው ክትትልና ቁጥጥር አስመልክቶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፡፡
3. በምክር ቤቱ አባላት በአንድ ሦስተኛ ጥያቄ ወይም በልዩ ኮሚቴው ውሳኔ አስፈላጊ በሆነ ጉዳይ ላይ የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ተቋማት ኃላፊዎች ለምክር ቤቱ ሪፖርት ሊያቀርቡ ይችላሉ፡፡
4. የመከላከያ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት ተቋማት የሚመለከታቸው የበላይ ኃላፊዎች በልዩ ኮሚቴው በመገኘት ሪፖርት ያቀርባሉ፡፡
5. በዚህ ደንብ ለሌሎች ኮሚቴዎች የተደነገገው አሰራር እና ሥነ-ሥርዓት ለልዩ ኮሚቴውም በተጣጣመ መልኩ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

## <u>ምዕራፍ ሃያ ሦስት</u>

## <u>ቋሚ ኮሚቴ</u>

162. <u>**አደረጃጀት**</u>

1. የቋሚ ኮሚቴ አባላት እንደ ሁኔታው ከአስራ አንድ እስከ ሃያ አምስት ይሆናሉ።
2. የእያንዳንዱ የቋሚ ኮሚቴ አባላት፤ ሊቀመንበሩንና ምክትል ሊቀመንበሩን ጨምሮ በአፈጉባዔው አቅራቢነት ምክር ቤቱ ከአባላቱ መካከል ይመርጣል።
3. አንድ አባል ከአንድ ቋሚ ኮሚቴ በላይ አባል መሆን አይችልም።
4. የቋሚ ኮሚቴ አባላት ሲጓደሉ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ መሠረት እንዲሟሉ ይደረጋል።
5. ከቋሚ ኮሚቴ መልቀቅ የሚፈልግ አባል ጥያቄውን በጽሁፍ ለአፈጉባዔውና ለኮሚቴው ማቅረብ ይችላል፣ በአፈጉባዔው ስምምነቱን ከገለጸበት ጊዜ ጀምሮም ከኮሚቴው እንደለቀቀ ይቆጠራል።
6. አንድ አባል ያለበቂ ምክንያት ከሦስት ተከታታይ ስብሰባዎች በላይ የቀረ እንደሆነ በሚመለከተው ኮሚቴ በሚቀርብ ሞሽን ምክር ቤቱ ከኮሚቴ አባልነት እንዲነሳ ሊወስን ይችላል።

163. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

1. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ የሚከተሉት አጠቃላይ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

   ሀ/ የተመራለትን ረቂቅ ህግ በመመርመር ለምክር ቤቱ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፤

   ለ/ በመንግስታዊ አካላት ላይ ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ፤

   ሐ/ ህግ ማመንጨት፤

   መ/ ጥቆማ መቀበል፤

   ሠ/ ምስክሮችን መስማት እና ሰነድ መመርመር፤

   ረ/ በተቋቋመበት ዓላማ ዙሪያ ጥናት ማካሄድ፤

   ሰ/ ልዩ ልዩ አውደ ጥናቶችና የውይይት መድረኮችን ማዘጋጀት፤

   ሸ/ የልምድ ልውውጥ ማድረግ፤

   ቀ/ ከምክር ቤቱ ወይም ከአፈጉባዔው የሚሰጠውን ሌሎች ስራዎች ማከናወን፡፡
2. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ተግባራቱን ሲያከናውን የፆታ አድልዎን ያስወገደ እና ስርዓተፆታን፣ ኤች.አይቪ/ኤድስንና አካባቢ ጥበቃን ያገናዘበ መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል።
3. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ምክር ቤቱ ለዕረፍት በሚዘጋበት ወቅት አፈጉባዔውን በማሳወቀ እና አስፈላጊውን የሰው ሃይል በመወከል ተግባራቱን ያከናውናል።

164. <u>የቋሚ ኮሚቴ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የቋሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ኮሚቴውን ይመራል፣ ያስተባብራል፣የስብሰባ ሥነሥርዓት ያስከብራል

ለ/ የኮሚቴውን ሪፖርት ለምክር ቤቱ ወይም ለአፈጉባዔው ያቀርባል፤

ሐ/ ኮሚቴውን በመወከል ከሦስተኛ ወገን ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤

መ/ ተጋባዥ እንግዶችና ምስክሮች እንዲገኙ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፤

ሠ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከመደበኛ ስብሰባው ዉጭ ስብሰባ ይጠራል፤

ረ/ ከምክር ቤቱ፣ ከአፈጉባዔው ወይም ከኮሚቴው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

2. የቋሚ ኮሚቴ ምክትል ሊቀመንበር የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ ሊቀ መንበሩ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሰራል፤

ለ/ የኮሚቴው ሰነዶችና ቃለጉባዔዎች በአግባቡ መያዛቸውን ያረጋግጣል፤ በኮሚቴው የተገኙ እና ያልተገኙ አባላትን ይቆጣጠራል፤ በኮሚቴው ወይም በሊቀመንበሩ የሚሰጡትን ሊሎች ተግባራት ያከናውናል።

165. <u>ስለቋሚ ኮሚቴ ስብሰባ</u>

1. የቋሚ ኮሚቴ መደበኛ ስብስባ ዘወትር ሰኞ እና ረቡዕ ከጠዋቱ 3 ሰዓት እስከ 6:30 እና ከሰዓት በኋላ 8:30 እስከ 11:30 ይሆናል፡፡

2. የቋሚ ኮሚቴ አባላት በመደበኛ ስብስባ ጊዜ የተለየ ጥሪ ሳያስፈልግ በሰዓቱ መገኘት ይኖርባቸዋል።

3. አስገዳጅ ሁኔታ ከሌለ በስተቀር የቋሚ ኮሚቴ አባላት ያልሆኑ የምክር ቤቱአባላትበማንኛውም የቋሚ ኮሚቴ ስብስባ ያለድምፅ መሳተፍ ይችላል፤

4. ጉዳዩ ቋሚ ኮሚቴዎች በጋራ ስብስባ የሚታይ በሚሆንበት ጊዜ ውይይቱንየሚመራውጉዳዩን በዋናነት የሚያስተባብረው ቋሚ ኮሚቴ ሊቀመንበ ር ይሆናል፡፡

166. <u>ረቂቅ ህግ ስለመመርመር</u>

1. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ የተመራለትን ረቂቅ ህግ መርምሮ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ለማዘጋጀት የሚከተሉትን ስልቶች ሊጠቀም ይችላል፦

ሀ/ ከአስረጅዎች ጋር በረቀቀ ህጉ ዙሪያ መወያየት፤

ለ/ የህዝብ አስተያየት መስጫ መድረክ ማዘጋጀት እና ሃሳብ ማሰባሰብ፤

ሐ/ የሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት ወይም ግለሰቦች በረቂቅ ህጉ ላይ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ፤

መ/ በንዑስ ኮሚቴ ተጣርቶ እንዲቀርብለት ማድረግ፤

ሠ/ የተለያዩ ልምዶችና አሠራሮችን ተግባራዊ ማድረግ።

2. ተጋባዥ እንግዶች እንደሁኔታው በተለያዩ የማስታወቂያ ዘዴዎች ወይም በደብዳቤ እንዲጠሩ ሲደረግ የስብሰባው አጀንዳ፣ ጊዜና ቦታ፣ ስብሰባውን የሚያካሂደው ቋሚ ኮሚቴና አድራሻ፣ በስብሰባው ለመገኘት የማይችሉ አካላት ወይም ግለሰቦች በአጀንዳው ዙሪያ ያላቸውን አስተያየት የሚገልፁበትን መንገድ የያዘ መሆን ይኖርበታል።

3. የህዝብ አስተያየት መስጫ መድረክ እንደ ሁኔታው በምክር ቤቱ ቅጥር ግቢ ወይም በሌላ ማንኛውም ቦታ ሊዘጋጅ ይችላል፡፡

4. ቋሚ ኮሚቴ በሚዘጋጀው የውይይት መድረክ ላይ የሚገኙ ሰዎች ስም ዝርዝር አስቀድሞ የሚያውቀበትን መንገድ ያመቻቻል፣የመግቢያ ፈቃድ እንዲዘጋጅም ያደርጋል።

5. ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ የተመራለት ረቂቅ ህግ መሰረታዊ ችግር አለበት ብሎ ካመነ ጉዳዩን ለአፈጉባዔው በማሳወቅ ረቂቅ ህግ ተስተካክሎ እንዲላክለት ለሚመለከተው አካል ሊመልሰው ይችላል፡፡

167. <u>በረቂቅ ዙሪያ ስለሚደረግ ውይይት</u>

1. ከባለሙያዎች ወይም ከአስረጂዎች ጋር እንደዚሁም በህዝብ አስተያየት መስጫ መድረክ የሚካሄድ ውይይት እንደሁኔታው በሚከተለው ሥነ ሥርዓት ይመራል፦

ሀ/ የቋሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር የእለቱን አጀንዳ እና እስረጂዎቹን ያስተዋውቃል፤

ለ/ ለእስረጂዎቹ የረቀቀ ህጉን አስፈላጊነት እና ዋና ዋና ይዘቶች ለተሳታፊዎች ያቀርባሉ፤

ሐ/ የቋሚ ኮሚቴ አባላትም ሆኑ ሌሎች ተሳታፊዎች በአጀንዳው ዙሪያ መነሳት የሚገባውን ጥያቄ እና አስተያየት እንዲያቀርቡ ዕድል ይሰጣቸዋል፤

መ/ አስረጂዎቹ ወይም ባለሙያዎቹ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች እና አስተያየቶች ዝርዝር ማብራሪያ እንዲሰጡ ይደረጋል፤

ሠ/ በዚህ አንቀፅ በፊደል ተራ (መ) መሠረት አስረጂዎቹ ወይም ባለሙያዎቹ በሰጡት መልስ እና ማብራሪያ ዙሪያ ተሳታፊዎቹ ተጨማሪ አስተያየት እና ጥያቄዎች እንዲያቀርቡ ይደረጋል፤

ረ/ አስረጂዎች ወይም ባለሞያዎች ለተነሱ ጥያቄዎች እና አስተያየቶች መልስ እና ማብራሪያ ይሰጣሉ፤

ሰ/ የቋሚ ኮሚቴ ሊቀመንበር በዕለቱ አጀንዳ የማጠቃለያ አስተያየት እና አቅጣጫ በማስቀመጥ ስብሰባውን ያጠቃልላል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1) የተዘረዘሩት ቅደም ተከተሎች ቢኖሩም የቋሚ ኮሚቴው ሊቀመንበር ስብሰባውን በመምራት ሂደት በውይይቱ ጣልቃ እየገባ ያልተመለሱ እና ያልተብራሩ ጭብጦች እንዲገለጹ፣ ውይይቱ ከመስመር ሲወጣ ወደ መስመርእንዲመለስ፣ በስህተት የተተረጎሙ ሃሳቦች የማስተካከል፣ በአጠቃላይ ስብሰባውን የመምራት ሥነ ሥርዓቶች እንዲከበሩ ያደርጋል፡፡

3. ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ በረቂቅ ህግ ዙሪያ ከባለሙያዎች፣ ከአስረጂዎች እንዲሁም ከህዝብ ጋር የሚያደርገው ውይይት እንደሁኔታው በተደጋጋሚ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

4. ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ በረቂቁ ህግ ዙሪያ ከአስረጂዎች ወይም ባለሙያዎች ጋር የሚያደርገው ውይይት እንደሁኔታው ከህዝብ አስተያየት መስጫ መድረክ በፊት ወይም በኋላ ሊሆን ይችላል፡፡

168. <u>*መንግሥታዊ አካላትን መከታተል እና መቆጣጠር*</u>

1. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ መንግስታዊ አካላትን በመከታተል እና በመቆጣጠር ሂደት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናውናል፦

ሀ/ መንግሥታዊ አካሉ የተቋቋመበት ህግ እና ተያያዥነት ያላቸው ህጉችን እንዲሁም መንግስታዊ አካሉን የሚመለከቱ ጠቃሚ ሰነዶች በመመርመር የተሟላ ግንዛቤ ይይዛል፤

ለ/ የመንግሥታዊ አካሉ ዓመታዊ እቅድ እንዲደርሰው በማድረግ ይመረምራል፤

ሐ/ የስራ አፈፃፀም ሪፖርቱን በየሩብ ዓመቱ በመቀበል ይገመግማል፣ በዓመት አንድ ጊዜም ሪፖርት ያዳምጣል፤

መ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በክትትልና ቁጥጥር ሂደት ያገኘውን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።

2. ስለመንግስታዊ አካላት ሪፖርት አቀራረብ በዚህ ደንብ ከአንቀፅ 82 እስከ አንቀፅ 87 የተዘረዘሩት ድንጋጌዎች እንደ ሁኔታው ተጣጥመው ይፈጸማሉ፡፡
3. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ መንግሥታዊ አካላትን በመቆጣጠር እና በመከታተል ሂደት የሚከተሉትን አሰራሮች ሊከተል ወይም እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፦
   ሀ/ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በመንግሥታዊ አካሉ ላይ የሂሣብ ምርመራ እንዲደረግ የሚጠይቅ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ለምክርቤቱ ማቅረብ፤
   ለ/ በሂደቱ ያገኛቸው ችግሮች ከህግ የመነጩ ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀጽ 80 (1) መሠረት በህግ እንዲደገፉ ወይም ክፍተቶቹ በህግ እንዲሞሉ የህግ ረቂቅ አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ማቅረብ፤
   ሐ/ በሂደቱ ያገኛቸው ችግሮች ከበጀት ጋር የሚያያዝ ከሆነ በዚህ ደንብ አንቀፅ 80 (2) መሠረት ምክር ቤቱ አስፈላጊውን ውሳኔ እንዲሰጥ በትሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ማቅረብ፤
   መ/ ከህብረተሰቡ የሚቀርቡለትን ጥቆማዎች መሠረት በማድረግ የሚመለከታቸውንመንግሥታዊ አካላት መቆጣጠር እና መከታተል፤
   ሠ/ በዚህ ደንብ አንቀፅ 80 (3/ መሠረት መስሪያ ቤቱ ችግሩን እንዲያውቅና ድክመቱን እንዲያርም መመሪያ መስጠት፤ ድክመቱን ስለማረሙም ማረጋገጥ፤
   ረ/ የታየው ችግር መሠረታዊ ከሆነ በዚህ ደንብ ንቀፅ 80 (4) መሠረት ምክር ቤቱ ህጋ እርምጃ እንዲወስድ ሪፖርትና ሃሳብ ማቅረብ፡፡
4. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ መንግስታዊ አካላትን በመከታተልና በመቆጣጠር ሂደት ምስክሮችን መስማት እና ማስረጃ መመርመር ይችላል፤ አፈጻጸሙም በዚህ ደንብ አንቀፅ 89 በተደነገገው መሰረት እንደሁኔታው ይከናወናል፡፡
5. ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው በመንግስታዊ ተቋሙ በአካል በመገኘት የክትትል እና ቁጥጥር ሥራ ሊያካሂድ ይችላል፡፡
6. ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ ክትትል እና ቁጥጥር ሥራዎቹን ሲያከናውን በተቋሞቹ የዕለትተዕለት የስራ እንቅስቃሴ፣ የሥራ ነፃነት እና በሌሎች ህጎችየተቀመጡአስገዳጅሁኔታዎችን በመጋፋትና በመፃረር መሄድ የለበትም
7. ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ ሪፖርት ሲያዳምጥ ከታች ባሉ ተቋማት ጀምሮ የእነሱን የበላይተጠሪ የሆነ ተቋም በመጨረሻ መጥራት ይኖርበታል።

169. <u>የክትትልና ቁጥጥር ተግባራት</u>

እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ተለይተው በተሰጡት ዘርፎችና ተቋማት የሚያካሂደው ክትትልና ቁጥጥር እንደተጠበቀ ሆኖ በሚከተሉት ጉዳዮች ሁለም ቋሚ ኮሚቴዎች ክትትልና ቁጥጥር ያደርጋሉ፤-

1. የአምስት ዓመት የፌደራል መንግስት ዕቅድ፤
2. ውጤታማና ቆጣቢ የሆነ የበጀት አጠቃቀም፤
3. ውጫዊና ውስጣዊ መልካም አስተዳደር፤
4. ቀልጣፋና ተጠያቂነት ያለበት የህዝብ አገልግሎት አሰጣጥ፤
5. የሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ማሻሻያ፤
6. የሰብዓዊ መብት አከባበር፤
7. የመረጃ ነፃነት አተገባበር፤
8. የወጡ ህጎች የተፈለገውን ውጤት ማስገኘታቸው፤
9. የኦዲት ግኝት
10. ሴቶች፣ ወጣቶች፣ ህፃናት፣ አካልጉዳተኞች፣ አካባቢ ጥበቃ፣ አርብቶ አደር፣ የስነ ተዋልዶ እና የመሳሰሉት የባለብዙ ዘርፍ ጉዳዮች፡፡

170. **<u>ህግ ስለማመንጨት</u>**

እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ምክር ቤቱ በሚሰጠው መመሪያ ወይም ከሚያከናው ነው አጠቃላይ ስራ በመነሳት ወይም ከሚከታተለው እና ከሚቆጣጠረው መንግስታዊ አካል ሚቀርብለትን ሃሳብ መነሻ በማድረግ ህግ ሊያመነጭ ይችላል፡፡

171. **<u>ጥቆማ ስለማስተናገድ</u>**

1. ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ የሚቀርብለትን ጥቆማ በስልጣኑ የሚወድቅ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
2. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ የቀረበለትን ጥቆማ መርምሮ የሚከተሉትን እርምጃዎች ሊወስድ ይችላል፦

ሀ/ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመወያየት ጉዳዩ መፍትሄ እንዲያገኝ ማድረግ፤

ለ/ ከአባላቱ መካከል ጉዳዩን አጣርቶ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ እንዲያቀርብለት ማድረግ፤

ሐ/ የሚመለከተውን መንግስታዊ አካል ማሳሰብ ወይም ትዕዛዝመስጠት፤

መ/ ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ አዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ ማቅረብ፡፡

3. ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ ጥቆማውን በሚመለከት በመጨረሻ የደረሰበትን ማጠቃለያ እንደ አስፈላጊነቱ ለጠቋሚው ወይም ጉዳዩ ለሚመለከተው አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

4. የዚህ ደንብ አንቀፅ 91 ድንጋጌ እንደአግባብነቱ ተጣጥሞ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

172. <u>ስለ ሪፖርትና የውሳኔ ሀሳብ</u>

1. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ የሚያዘጋጀውን ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ወይም የሚያስተላልፈውን ውሳኔ ለምክር ቤቱ ወይም ለአፈጉባዔው ወይም ለሚመለከተው ኮሚቴ ወይም አካል ያሳውቃል፣ እንደአስፈላጊነቱም ተግባራዊነቱን ይከታተላል፡፡

2. የቋሚ ኮሚቴ ውሳኔ ወይም ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ በፅሁፍ የተዘጋጀ ሆኖ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡-

   ሀ/ የጉዳዩ ርዕስ፣ መለያ ቁጥር እና መግቢያ፤

   ለ/ ጉዳዩን ለመመርመር የተደረጉ እንቅስቃሴዎች፤

   ሐ/ በህዝብ አስተያየት መስጫ መድረክና በሌሎች መንገዶች የተሰባሰቡ መሰረታዊ ጭብጦች እና ማስረጃዎች፤

   መ/ የአነስተኛው ድምጽ የልዩነት ሃሳብ፤

   ሠ/ የኮሚቴው አስተያየትና የውሳኔ ሃሳብ፤

   ረ/ የውሳኔ ሃሳቡን ያቀረበው ቋሚ ኮሚቴ ስም።

3. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ በምክር ቤቱ ትዕዛዝ ወይም በራሱ አነሳሽነት ያከናወነውን ሥራ በሚመለከት ለምክር ቤቱ ወይም ለአፈጉባዔው ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

4. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ በየጊዜው ተጠሪ ለሆነለት አካል የፅሑፍ ሪፖርት ያቀርባል።

5. በቋሚ ኮሚቴ የሚዘጋጅ ሪፖርት የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡-

   ሀ/ የተከናወነው ተግባርና የተገኘው ውጤት፤

   ለ/ ሥራውን ለማከናወን የተደረጉ ጥረቶችና የተከተለው አቅጣጫ፤

   ሐ/ ሥራውን በማከናወን ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሄዎች፤

   መ/ ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች፤

   ሠ/ የኮሚቴው አስተያየት፡፡

173. <u>በቋሚ ኮሚቴ ስለሚዘጋጁ ዓውደ ጥናቶች እና የውይይት መድረኮች</u>

1. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በስልጣንና ተግባሩ ዙሪያ አውደጥናቶች እና የውይይት መድረኮች ሊያዘጋጅ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ መሰረት የሚዘጋጁ ዓውደጥናቶችና የውይይት መድረኮች የሚከተሉትን ያጠቃልላሉ፦

ሀ/ ሰፊ የህዝብ ተሳትፎ በሚጠይቁ አጀንዳዎች፤

ለ/ አቋም ሊወሰድባቸው በሚገቡ ጉዳዮች፤

ሐ/ በፖሊሲዎች እና በስትራቴጂዎች አፈፃፀ ምዙሪያ፤

መ/ የተለያዩ ልምዶችን ለማግኘት፤

ሠ/ በወቅታዊ ጉዳዮች እና ዋናዋና ችግሮች፤

ረ/ በሚቋቋሙ አዳዲስ ተቋማት ሥልጣንና ተግባር ዙሪያ፤

ሰ/ በምክርቤቱ እና በኮሚቴዎች አሰራር ዙሪያ፤

ሸ/ በአዋጆች ዙርያ፤

ቀ/ ምክር ቤቱ በሚወስናቸው ሌሎች አጀንዳዎች ዙሪያ።

3. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ በሚያዘጋጀው ዓውደ ጥናት እና የውይይት መድረክ የሚከተሉትን ቅድ መሁኔታዎች ማሟላት ይጠበቅበታል

ሀ/ በኮሚቴው ዓመታዊ ዕቅድ መካተት አለበት፤

ለ/ የዓውደ ጥናቱ ወይም የውይይት መድረኩ የራሱ ዝርዝር አቅድ ያለው መሆን ይኖርበታል፤

ሐ/ በሚመለከተው አካል የተፈቀደ መሆን አለበት፤

መ/ አስፈላጊ በጀት የተመደበለት ሊሆን ይገባል፤

ሠ/ ውጤት ተኮር መሆን ይኖርበታል፤

ረ/ አግባብነት ያላቸው አካላትን ያሳተፈ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

174. <u>ስለ ቋሚ ኮሚቴ መግለጫ</u>

1. በሌላ ህግ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ ሥራውን አስመልክቶ መግለጫ መስጠት ይችላል፡፡

2. እያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ የሚከታተለውን መንግሥታዊ አካል መግለጫ እንዲሰጥ ሊያዝ ይችላል፡፡

3. በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ እና (2/ መሠረት የሚሰጥ መግለጫ በቅድሚያ የአፈጉባዔውን ፈቃድ ማግኘት አለበት፡፡

175. <u>የቋሚ ኮሚቴ አባላት ሥነ-ምግባር</u>

የዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም የቋሚ ኮሚቴ አባል የሚከተሉትን ሥነ-ምግባሮች ማክበር ይጠበቅበታል፦

1. የስራ ሰዓት ማክበር፤
2. የተሰጠውን ሃላፊነት ወይም ተግባር በሙሉ አገራዊ ስሚት ማከናወን፤
3. ስራውን ውጤታማ በሆነ መልኩ መፈጸም፤
4. ባለጉዳዮችን ገለልተኛ፣ ፍትሃዊ፣ ካላስፈላጊ ጠባይ በጸዳ አኳኋን እና በህግ መሠረት በአግባቡ ማስተናገድ፤
5. ለስራው የተመደበለትን ሃብትና ንብረት በጥንቃቄና በአግባቡ መጠቀም፡፡

176. <u>የቋሚ ኮሚቴዎች ቅንጅታዊ አሰራር</u>

1. በቋሚ ኮሚቴዎች የስራ ሂደት የስራ መደራረብ በሚያጋጥምበት ጊዜ ወይም በአንድ ጉዳይ ላይ ሁለትና ከዚያ በላይ የሆኑ ቋሚ ኮሚቴዎች የሚመለከታቸው ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ ውጤታማ አፈፃፀምን የጋራ መግባባትን መነሻ በማድረግ እንደሚከተለው ይፈፀማል፡-
   ሀ/ ጉዳዩ በበለጠ ለሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ሪፖርትና አስፈላጊ መረጃዎችን በመስጠት፤
   ለ/ ጉዳዩን አንድ ቋሚ ኮሚቴ በበላይነት እንዲመራና እንዲያስተባብር በማድረግና የሚመለከተው ቋሚ ኮሚቴ ወይም ኮሚቴዎች ድጋፍና ትብብር እንዲያደርጉ በማድረግ፤ ወይም
   ሐ/ እንደ ሁኔታው ጉዳዩ ለአስተባባሪ ኮሚቴ በማቅረብና በአስተባባሪ ኮሚቴው የሚቀመጠውን አቅጣጫ በመከተል።
2. ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ በክትትልና ቁጥጥር የሚያገኘው ግኝትና ሪፖርት ሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች የሚከታተሏቸውን ዘርፎችና ተቋማት የሚመለከት ሆኖ ሲያገኘው ለሚመለከታቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ሪፖርቱና ግኝቱ እንዲደርሳቸው ማድረግ ይኖርበታል።
3. ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2/ መሰረት ሪፖርቱና ግኝቱ ከተሰጣቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ጋር በጉዳዩ ላይ ይወያያል፣ እንደ አስፈላጊነቱም ችግሩ ተደጋጋሚና የጎላ ሆኖ ሲገኝ ከቋሚ ኮሚቴዎቹ ጋር በመሆን የህዝብ ይፋ መድረክ ያዘጋጃል።

177. <u>ንዑስ ኮሚቴ</u>

1. የንዑስ ኮሚቴ ተጠሪነት ለዋናው ኮሚቴ ይሆናል፡፡

2. የንዑስ ኮሚቴ የስብሰባ ጊዜ ዘወትርአርብ ከ 3 እስከ 5:30 እንደዚሁም ከሰዓት በኋላ 7፡30 እስከ 11:30 ይሆናል፡፡
3. ማንኛውም ንዑስ ኮሚቴ የራሱ ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበር ይኖረዋል።
4. በዚህ ደንብ ስለቋሚ ኮሚቴዎች የተቀመጡ ድንጋጌዎች እንደአግባብነቱ ለንዑስ ኮሚቴም ተፈፃሚ ይሆናሉ።

178. <u>ጊዜያዊ ኮሚቴ</u>

1. ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ጊዜያዊ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡
2. የጊዜያዊ ኮሚቴ ስልጣንና ተግባር በምክር ቤቱ ተለይቶ ይወሰናል፡፡
3. ጊዜያዊ ኮሚቴ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ይሆናል፡፡
4. የጊዜያዊ ኮሚቴ አባላት ቁጥር በምክር ቤቱ ይወሰናል፣ የኮሚቴው ሊቀመንበርና ምክትል ሊቀመንበርም በምክር ቤት ይመረጣል፡፡
5. ጊዜያዊ ኮሚቴው በምክር ቤቱ የተሰጠውን ተግባር ካከናወነ በኋላ ይከስማል።
6. ጊዜያዊ ኮሚቴ የራሱን የውስጥ የአሰራር ሥነ-ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሃያ አራት

## የቋሚ ኮሚቴዎች መቋቋምና ልዩ ልዩ ተግባራት

179. <u>መቋቋም</u>

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ቋሚ ኮሚቴዎች ይኖሩታል፡፡

1. የህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
2. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ፣
3. የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
4. የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
5. የሰው ሃብት ልማት እና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
6. የሳይንስ፣ መገናኛና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
7. የሴቶችና ህፃናት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
8. የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
9. የባህል፣ ቱሪዝምና መገናኛ ብዙሃን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
10. የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
11. የትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
12. የንግድ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣
13. የእርብቶ አደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤
14. የኢንዱስትሪ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤

15. የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤

16. የከፍተኛ ትምህርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤

17. የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፤

18. የውጭ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

180. <u>የህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

1. የህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡

ሀ/ የፌደራል መንግሥቱ የፍትህ አስተዳደር ሕገመንግሥቱን መሠረት በማድረግ መደራጀቱንና በአግባቡ ተግባሩን እያከናወነ መሆኑን፤

ለ/ በሕገመንግሥቱ የተደነገጉ መብቶችና ነፃነቶች በአግባቡ መተግበራቸውን፤

ሐ/ ነፃና ፍትሃዊ የምርጫ ስርዓት መዘርጋቱን እና ሂደቱን፤

መ/ ሕብረተሰቡ ነፃ፣ ፍትሃዊና ቀልጣፋ የፍትህ አገልግሎት ማግኘቱን፤

ሠ/ ሙስናና ብልሹ አሠራርን መከላከልና መቆጣጠር የሚያስችል ሥርዓት በአግባቡ መዘርጋቱንና ሥራ ላይ መዋሉን፤

ረ/ በሕገመንግሥቱ አንቀፅ 54 (6/ የተመለከተውን የህግ ከለላ የማንሳት እንዲሁም ሌሎች የአባላት መብትና ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን፤

ሰ/ የወንጀል መከላከል ስራ በአግባቡ እየተከናወነ መሆኑን እንደዚሁም ለወንጀል ድርጊት ጠቋሚዎችና ምስክሮች በቂ ጥበቃ መደረጉን፤

ሸ/ የህዝብና የመንግስትን መብትና ጥቅም ለማስከበር የሚያስችል የህግ ምክር፣ ክስና ክርክር እየተካሄደ መሆኑን፤

ቀ/ የህዝብ ሠላም መጠበቁን እንደዚሁም አለመግባባቶችንና ግጭቶችን ለመከላከልና በዘላቂነት ለመፍታት የሚያስችል አሠራርና እንቅስቃሴ መኖሩን፤

በ/ በፌደራል መንግስትና በክልሎች መካከል በመግባባትና በአጋርነት ላይ የተመሠረተ መልካም ግንኙነትና ትብብር እንዲጠናከር የሚደረገውን እንቅስቃሴ፤

ተ/ የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህገች፣ ስትራቴጂዎች እና ዕቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፣

ቸ/ የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን።

2. የህግ፣ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምክር ቤቱ ወደ ማንኛውም ቋሚ ኮሚቴ የሚመራውን ረቂቅ ህግ እና የሚቀርቡ ረቂቅ ህጎችን የረቂቅ ህግ አዘገጃጀት መርሆዎችን የተከተሉ መሆናቸውንና የተሟሉ መሆናቸውን ይመረምራል።

181. <u>**የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ**</u>

1. የመንግስት የልማት ድርጅቶች ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡-

ሀ/ በመንግስት የኢኮኖሚና የፋይናንስ ፖሊሲ መሠረት የመንግስት የልማት ድርጅቶች በአገሪቱ የኢኮኖሚና ንግድ እንቅስቃሴ ገንቢ ሚና እያበረከቱ መሆኑን፤

ለ/ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የስራ እንቅስቃሴ ትርፋማነትና የቴክኖሎጂ ሽግግርን የሚያረጋግጥ መሆኑን፤

ሐ/ የመንግስት የልማት ድርጅቶች በህግ የተሰጣቸውን ተግባር በአግባቡ እየተገበሩ መሆኑን፤

መ/ የመንግስት የልማት ድርጅቶች ውጤታማ በሆነ መንገድ መመራታቸውንና በአግባቡ ወደ ግል ይዞታ የተዛወሩ መሆናቸውን፤

ሠ/ የመንግስት የልማት ድርጅቶች የሚሰጡት የህዝብ አገልግሎት በአግባቡ መከናወኑን እና የውስጥና የውጭ መልካም አስተዳደር ጉዳዮችን በተመለከተ፣

ረ/ የመንግስት የልማት ድርጅቶች አነስተኛና ጥቃቅን ተቋማትን ጨምሮ በልማት ለሚሳተፉ ሌሎች ተቋማት የሚያደርጉት ድጋፍ።

2. ቋሚ ኮሚቴው ክትትልና ቁጥጥር ሲያከናውን የመንግስት የልማት ድርጅቶችን የስራ ባህሪ ግምት ውስጥ በማስገባት በስትራቴጂያዊ ጉዳዮችና በፖሊሲ አቅጣጫዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ይኖርበታል።

3. ቋሚ ኮሚቴው የልማት ድርጅቶችን የንግድ ባህሪ መነሻ በማድረግ ስብሰባውን በዝግ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

4. ቋሚ ኮሚቴው ምክንያታዊ የሆነ ጥርጣሬ ሲኖረው ወይም ጥቆማ ሲደርሰው በማንኛውም የመንግስት የልማት ድርጅት ፋይናንስ፣ ግዥና ንብረት አስተዳደር ላይ ክትት ልና ቁጥጥር ያካሂዳል።

5. ቋሚ ኮሚቴው ከሚያካሂደው የክትትልና ቁጥጥር ዘርፍ ልዩ ባህሪ መነሻ በማድረግ በዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች ለሌሎች ቋሚ ኮሚቴዎች የተሰጠው ስልጣን እና ተግባራትን በማጣጣም ተግባሩን ያከናውናል።

182. <u>የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

1. የመንግሥት ወጪ አስተዳደር እና ቁጥጥር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ለፌደራል መንግሥት የተመደበ ማንኛውም በጀት በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
2. ቋሚ ኮሚቴው የፌደራል ኦዲተር ሪፖርትን ይመረምራል፤በሚመረምርበት ወቅትም፦

   ሀ/ የተመደበው በጀት ለታለመለት ዓላማና አገልግሎት ወጪ የተደረገ መሆኑን፤

   ለ/ ወጪው ስልጣን ባለው አካል የተረጋገጠ መሆኑን፤

   ሐ/ የበጀት ዝውውር ሲኖር በፋይናንስ ህጉ መሰረት መከናወኑን፤ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል።
3. ቋሚ ኮሚቴው በምክር ቤቱ ትዕዛዝ በዋና ኦዲተር የተከናወነ የንብረት ኦዲት ውጤትን ይገመግማል፡፡
4. በማንኛውም መንግስታዊ አካል በበጀት ዓመቱ ከተመደበው በላይ የበጀት አጠቃቀም ሲኖር በምክር ቤቱ ውሳኔ ኮሚቴው ከበጀት በላይ ለማውጣት አስገዳጅ የሆነውን ምክንያት የማጣራትና አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም ሪፖርትና የውሳኔ ሃሳብ ለምክር ቤቱየማቅረብ ሃላፊነት አለበት፡፡
5. ቋሚ ኮሚቴው በኦዲት ግኝት ላይ ኦዲት ተደራጊ ተቋማትን ለሚከታተላቸው ቋሚ ኮሚቴዎች ሪፖርቱ እንዲደርሳቸው ያደርጋል፡፡
6. በኦዲት ግኝት ላይ ኦዲት ተደራጊውን ተቋም ከሚከታተለው ቋሚ ኮሚቴ ጋር በመሆን ይወያያል፡፡
7. ቋሚ ኮሚቴው እንደ አስፈላጊነቱ ችግሩ ተደጋጋሚና የጎላ ሆኖ ሲገኝ ኦዲት ተደራጊውን ተቋም ከሚከታተለው ቋሚ ኮሚቴ ጋር በጋራ በመሆን የኦዲት ግኝቱን በተመለከተ ይፋ የህዝብ ውይይት መድረክ ያዘጋጃል።
8. ቋሚ ኮሚቴው የሚያካሂደው ክትትልና ቁጥጥር በኦዲት ግኝት ላይ ብቻ የተወሰነ ይሆናል፡፡

183. <u>የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የማህበራዊ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡-

1. የጤና አገልግሎት የማስፋፋትና የጤና ጠንቆችን የማስወገድ ተግባራትን፤
2. ወረርሽኝና ተላላፊ በሽታዎችን ለመከላከል የሚያስችሉ ስልቶች መቀየሳቸውና በአግባቡ ተግባራዊ መሆናቸውን፤
3. ወጣቶች በብሔራዊ ልማት ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶችና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈፃፀም በተለይ ጥቅሞቻቸውን የሚነኩ ፕሮጀክቶች ላይ ሐሳቦቻቸውን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ ለማስቻል ብሔራዊ የወጣቶች ጉዳይ ፖሊሲ በተለያዩ መንግሥታዊ ድርጅቶች ውስጥ በአጠቃላይ በብሔራዊ ደረጃ በተግባር እየተተረጎመ መሆኑን እንዲሁም የወጣቶችን ሥራ ፈጣሪነት፣ ተጠቃሚነትና መብት የሚያጠናክሩ ሥልቶች መቀየሳቸውና ውጤታማ መሆናቸውን፤
4. ወጣቶች እንደፍላጐታቸውና እንደችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው የሚታገሉበት ሁኔታ መመቻቸቱን እንዲሁም ጉዳያቸው በፌደራል መንግስት አካላት በሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱን፤
5. የኤች አይ ቪ / ኤድስ ስርጭትን ለመግታት የሚደረጉ እንቅስቃሴዎች፤
6. የማህበራዊ ዋስትና አገልግሎቶች በተቀመጠላቸው ሥርዓት መሠረት ግባራዊ መሆናቸውን፤
7. የህብረተሰቡን ጤና ሊጎዱ የሚችሉ ድንገተኛ ሁኔታዎች ሲፈጠሩ የመከላከል እርምጃ መወሰዱን፣በአገሪቱ ውስጥ የአስፈላጊ መድሃኒቶችና የህክምና መሳሪያዎች በቂአቅርቦት መኖሩንና በአግባቡ ጥቅም ላይ መዋሉን፣የጤና ባለሙያዎች ስልጠና በጥራትና አግባብነት ባለው ሁኔታ መካሄዱን፤
8. የመድሃኒትና የጤና ክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ስራ በአግባቡ እየተፈፀመ መሆኑን፤
9. የኢንዱስትሪ ሰላም መስፈኑን፤
10. ቀልጣፋና ፍትሃዊ የሥራ ስምሪት አገልግሎት መኖሩን፤
11. ህዝባዊ መሰረት ያለው ስፖርት መስፋፋቱንና ስኬታማ መሆኑን፤
12. የአካል ጉዳተኞች እኩል እድል ተጠቃሚ እና ተሳታፊ መሆናቸውን፣ አረጋውያን ክብካቤ ማግኘታቸውን፣ እንዲሁም የማህበራዊ ችግሮችን ለመከላከልና በችግሩ ውስጥ የሚገኙ የህብረተሰብ ክፍሎች የተሃድሶ አገልግሎት የሚያገኙበት ሁኔታ መመቻቸቱን፤

13.የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና ዕቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤

14.የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን።

184. <u>የሰው ሃብት ልማትና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የሰው ሃብት ልማትና መልካም አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡

1. ፈጣን ልማት ለማምጣትና በዲሞክራሲ የታነፀ ሕብረተሰብን ለመፍጠር በብቃት፣በጥራት፣በታማኝነትና በቁርጠኝነት ሊሠራ የሚችል የሰለጠነ የህዝብ አገልጋይ የሰውኃይል በአጭር ጊዜና በስፋው ለማፍራት የሚደረገውን እንቅስቃሴ፤
2. የትምህርትና ስልጠና ስታንዳርድ መውጣቱን፣ በየደረጃው ጥራትና አግባብነት ያለው ትምህርትና ስልጠና መስጠቱንና የተማሪዎች ቅበላና ምደባ ፍትሃዊ መሆኑን፤
3. የአገሪቱ የቴክኒክና ሙያ ትምህርት ስልጠና ስትራቴጂ መቀረጹንና በሥራ ላይ መዋሉን፤
4. ፐብሊክ ሰርቪሱ ብቃት ያለውናው ጤታማ መሆኑን፤ የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች ምልመላና መረጣ በብቃት ላይ የተመሰረተና ፐብሊክ ሰርቪሱ በቀጣይነት የሚለማበትና ጥቅም ላይ የሚውልበት እንዲሁም በብቃትና በአፈጻፀም ላይ የተመሰረተ የከፍያና በረታቻ ስርዓት መዘርጋቱንና ተግባራዊ መሆኑን፤
5. የፌደራል መንግሥት ሠራተኞች የሥነምግባር መከታተያ ሥርዓት መዘርጋቱን፤ የመንግሥት ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ ስታንዳርድና የቅሬታ አቅራረብና አፈታትሥርዓት መዘርጋቱንና በቀጣይነት የሚሻሻልበት ሰልት መቅየሱን፤
6. ከማዋዕለ ህፃናት እስከመሰናዶ እና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ድረስ ያለውን የፖሊሲና ስትራቴጂ አፈፃፀም፤
7. የማህበራዊ ሳይንስ 30 በመቶ እና የተፈጥሮ ሳይንስ 70 በመቶ ቅበላ ምጣኔ አፈፃፀምና ውጤታማነተን በተመለከተ፤
8. የመምህራን ምልመላ፣ ስልጠናና ስምሪት በአግባቡ መከናወኑን፤
9. የሥነምግባርና የሥነ-ዜጋ ትምህርት ውጤታማነትን፤

10.የሲቪል ሰርቪስ ማሻሻያ ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ መንግስታዊ አገልግሎት ማስገኘቱን በተመለከተ፤

11.የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና ዕቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤

12.የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን።

185. <u>የሳይንስ፣ መገናኛና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የሳይንስ፣ መገናኛና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡-

1/ የአገሪቱን የልማት አቅጣጫ መሠረት ያደረገ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ፍላጎትና አጠቃቀም ስርዓት መዘርጋቱንና አፈፃፀሙን

2/ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴዎችና አገራዊ የምርምር ሥራዎች ከአገሪቱ የልማት ፍላጎት ጋር ተጣጥመው መከናወናቸውን፤

3/ በትምህርት፣በምርምር ተቋማትና በኢንዱስትሪው ዘርፍ መካከል ለምርምርና ቴክኖሎጂ ልማት እንቅስቃሴ የሚያግዝ ምቹ የእርስበርስ ትስስርና ቅንጅታዊ አሠራር ለመፍጠር የሚያስችሉ ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን፤

4/ የአገሪቱ የረዥም ጊዜ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን የሰው ኃይል ልማት መታቀዱንና ተግባራዊነቱን፣ የአገሪቱ ስርዓተ ትምህርት ከሳይንስና ቴክኖሎጂ ልማት አንፃር ለመቃኘት የሚያስችል ትብብር መፈጠሩን፣ በመንግሥትና በግሉ ዘርፍ በሳይንስና ቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ የሚሳተፉ ተቋማትና ባለሙያዎች አቅም ለመገንባት የሚያስችል ድጋፍ መሰጠቱንና ለፈጠራ ሥራዎች እድገት ተገቢው ትኩረት መሰጠቱን፤

5/ የመገናኛ አገልግሎቶችና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት እንዲስፋፋ መደረጉን፣ የአገልግሎት ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና አስተማማኝነታቸው እንዲጠበቅ የሚያስችሉ ደረጃዎች ወጥተው ተግባራዊ መደረጋቸውን፤

6/ የቴክኒክ ብቃታቸው በተረጋገጠ የቴሌኮም መሳሪያዎች መረጃ በተፋጠነ መልክና በተመጣጠነ ወጪ ማግኘት የሚቻልበት ሁኔታ መመቻቸቱን፤

7/ በፌደራልና በክልል ተቋማት መካከል እንዲሁም በፌደራልና በክልል ተቋማት ውስጥ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን መረብ መዘርጋቱንና በመንግሥት ተቋማት መካከል የተቀናጀና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ፍሰትና ልውውጥ እንዲኖር ተገቢው ድጋፍ መሰጠቱንና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል መደረጉን፤

8/ የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤

9/ የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በስራ ላይ ማዋላቸውን፡፡

186. <u>የሴቶችና ህጻናት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የሴቶችና እና ህጻናት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናዉናል ፡-

1. በሕገመንግስቱ እና በሌሎች ህጎች የተደነገጉት የሴቶች እና የህጻናት መብቶች መከበራቸዉንና ተጠቃሚ መሆናቸዉን፤
2. ከሴቶችና ህጻናት መብቶች ጋር የሚቃረኑ ህጎች እንዲሻሻሉ መደረጉን፤
3. ህጎችና እቅዶች ሲወጡና ሲጸድቁ የጾታ አድሎን ያስወገዱና ሥርዓተ-ጾታን ያገናዘቡ መሆናቸዉን
4. በፖለቲካ በኢኮኖሚና በማህበራዊ መስኮች እንዲሁም በምንግስትና በግል ተቋማት ሴቶች ከወንዶች እኩል ተወዳዳሪና ተሣታፊ እንዲሆኑ ማስቻልና የልዩ ድጋፍ ተጠቃሚ መሆናቸዉን፣
5. የሴቶች የልዩ ድጋፍ መብት ስራ ላይ ለማዋል ስልት መቀየሱንና በአግባቡ ተግባራዊ መሆኑን፤
6. ሴቶች ንብረት የማፍራት፣የማስተዳደርና የመቆጣጠር ፣የመጠቀም፣ የማስተላለፍና የመዉረስ መብቶቻቸዉ መከበሩን፤
7. ሴቶች በቅጥር፣ በሥራ እደገትና እኩል ክፍያና ጡረታ ለማስተላለፍ ያላቸዉ እኩልነት መብት መረጋገጡን፤
8. ሴቶች በብሔራዊ ልማት ፖሊሲዎች፣ ዕቅዶችና በፕሮጀክቶች ዝግጅትና አፈጻጸም በተለይ ጥቅሞቻቸዉን የሚነኩ ፕሮጀክቶች ላይ ሐሳቦቻቸዉን በተሟላ ሁኔታ እንዲሰጡ ለማስቻል ብሄራዊ የሴቶች ጉዳይ ፖሊሲ በተለያዩ መንግስታዊ ድርጅቶች ዉስጥ በአጠቃላይ በብሔራዊ ደረጃ በተግባር እየተተረጎመ መሆኑን፤

9. ሴቶች እና ህጻናት ከጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች ተጽእና መላቀቃቸዉን፣ ሴቶችን እና ህጻናትን የሚጨቁኑ፣ በአካላቸዉ ወይም በአዕምሯቸዉ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ወጎችና ልምዶች መወገዳቸዉን፤
10. ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደረስባቸዉን ጉዳት መከላከልና ጤንነታቸዉን ለማስጠበቅ የሚያስችል የቤተሰብ ምጣኔ ትምህረርት መረጃ የማግኘት መብትን፤
11. የህጻናት መብትና ደህንነት መጠበቁን፤
12. ሴቶች እንደፍላጉታቸውና እንደችግሮቻቸው ተደራጅተው ለመብቶቻቸው የሚታገሉበት ሁኔታ መመቻቸቱን እንዲሁም ጉዳያቸው በፌደራል መንግስት አካላት በሚዘጋጁ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ የልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች መካተቱን፤
13. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤
14. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን፡፡

187. <u>የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡ -

1. የአገሪቱን የገንዘብ እና የኢኮኖሚ ልማትና ትብብር ተግባራት በአግባቡ እየተከናወኑ መሆናቸውን፤
2. የፌደራል መንግስት ታክስና ቀረጥ አስተዳደር እንዲሁም የመንግስት ገቢ አሰባሰብ በአግባቡ እየተከናወነ መሆኑን፤
3. የፌደራል መንግሥትን ዓመታዊና ተጨማሪ በጀት በአግባቡ ተዘጋጅቶ መቅረቡን እና መጽደቁን፤
4. ለክልሎች የሚሰጥ ድጎማ በቀመሩ መሠረት መጽደቁን፤
5. የፌደራል መንግስት ፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር በአግባቡ መከናወኑን እና ውጤታማ መሆኑን፤
6. የአገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት ቀጣይነት እና ፍትሃዊነት እንዲሁም የተረጋጋ የማክሮ ኢኮኖሚ ለማረጋገጥ የሚያስችሉ ፖሊሲዎች መመንጨታቸውን እና

በአግባቡ ስራ ላይ መዋላቸውን፣ ኢኮኖሚው በተገቢው መንገድ እየተመራ መሆኑን፤

7. የአገሪቱ የልማት እቅድ እና የልማት ፕሮጀክቶች የአዘገጃጀትና አፈፃፀም ስርዓት መዘርጋቱን እንዲሁም በወቅቱ በስራ ላይ መዋሉን፤
8. የአገሪቱ የስነ-ህዝብ ፖሊሲ መዘጋጀቱን፣ የማክሮ ኢኮኖሚና የፊስካል ፖሊሲዎች መመንጨታቸውን እና በትክክል በስራ ላይ መዋላቸውን፤
9. ትክክለኛ የሆነ የመንግስት የበጀት፣ የሂሳብ አያያዝ፣ የክፍያና የውስጥ ኦዲት ስርዓት መዘርጋቱንና በአግባቡ እየተፈፀመ መሆኑን፤
10. የኢኮኖሚ ትብብሮችና ትስስሮች ከመደረጋቸው በፊት በአገሪቱ የኢኮኖሚ አፈጻጸም ላይ የሚያስከተሉት ዉጤት የሚፈትሽ እና የሚገመግም መሆኑን
11. የሚከታተላቸዉና የሚቆጣጠራቸዉ የቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸዉን፣
12. የሚከታተሏቸዉና የሚቆጣጠራቸዉ ተቋማት የተመደበላቸዉን በጀት በአግባቡና በዉጤታማነት በስራ ላይ መዋላቸዉን፡፡

188. <u>የባህል፣ቱሪዝምና መገናኛ ብዙሃን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የባህል፣ ቱሪዝምና መገናኛ ብዙሃን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናዉናል፡-

1. የኢትዮጵያ ቤሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ታሪክ፣ባህል፣ቅርስ እና ቋንቋ መጠናታቸዉንና ጽሁፎችቻዉ መዳበራቸዉን፣ በባህላዊ ተጽኖ ሳቢያ ማህበራዊ እድገቶችን የሚያጓትቱ አመለከካከቶች፣ እምነቶችና ልማዳዊ አሰራሮችን የመለወጥ ስራ መሰራቱን እንዲሁም የባህል ዘርፉ ልማታዊ አስተዋጾ መስፋፈቱን፤
2. የመገናኛ ቡዙሃን ለአገሪቱ ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ፣ ሠላምና ልማት የበኩላቸዉን ሚና እየተጫወቱ መሆኑን፣
3. ባህላዊና ታሪካዊ እሴቶች ተጠብቀዉ ለትዉልድ የሚተላለፉበት መንገድ መቀየሱንና ተግባራዊ መሆኑን፣
4. ለአገሪቱ የቱሪዝም ምንጭነት የሚያገለግሉ አስፈላጊ ሁኔታዎች መመቻቸታቸዉን እና የቱሪዝም መስህቦችና መልካም ገጽታዎች መተዋወቃቸዉን፤
5. የምንግስት መገናኛ ብዙሃን ቦርዶች የተጣለባቸዉን ሃላፊነት በአግባቡ መወጣታቸዉን፤

6. የሚከታተላቸዉና የሚቆጣጠራቸዉ ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸዉን፤
7. የሚከታተላቸዉና የሚቆጣጠራቸዉ ተቋማት የተመደበላቸዉን በጀት በአግባቡና በዉጤታማነት በስራ ላይ መዋላቸዉን፡፡

189. <u>**የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ**</u>

የተፈጥሮ ሃብት ልማትና አካባቢ ጥበቃ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡

1. የውሃ ሃብት፣የኢነርጂና የማዕድን ልማትና አጠቃቀምን፣ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እድገትና ስርጭትን፤
2. የንፁህ መጠጥ ውሃ አቅርቦት ሽፋን እንዲያድግ እገዛ መደረጉን፣ የአማራጭ ኢነርጂ ምንጮችና ቴክኖሎጂዎች ልማት እንዲስፋፋ መደረጉን እና የመካከለኛና ከፍተኛ መስኖ ልማት ለማስፋፋት የሚያስችሉ የጥናት፣ የዲዛይን እና የግንባታ ሥራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን፤
3. የሜቲዎሮሎጂ አገልግሎት ሥራ በአግባቡ መከናወኑን ፣የአገሪቷ የተፈጥሮ ሃብቶችና የአካባቢ ደህንነት ተጠብቆ ዘላቂ ልማት እንዲረጋገጥ ለማስቻል የሚደረገውን እንቅስቃሴ፤
4. በማዕድን፣ በነዳጅና በተፈጥሮ ጋዝ ፍለጋና ልማት ለሚሰማሩ ባለሃብቶች ምቹ ሁኔታ መፈጠሩንና ግዴታቸውንም በገቡት ውል መሠረት እንዲፈጽሙ የሚደረገውን እንቅስቃሴ፣
5. የማዕድን፣ የነዳጅና የተፈጥሮ ጋዝ ልማት መስፋፋቱንና መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተው ለአገልግሎት ዝግጁ መደረጋቸውን፤
6. የተፈጥሮ ጋዝና የነዳጅ ምርቶች የጥራት ደረጃ መረጋገጡንና የማከማቻና ማከፋፈያ ተቋማት ደረጃ አሰጣጥ በአግባቡ መከናወኑን፤
7. የአካባቢ ደህንነትና ጥበቃ ዓላማዎችና ፖሊሲዎች በስራ ላይ መዋላቸውንና ውጤታማነታቸው መረጋገጡን፤
8. የልማት ፕሮጀክቶችና ፕሮግራሞች በአካባቢ ተፅኖ ግምገማ ስርዓት መሰረት ተግባራዊ መሆናቸው፤
9. የአገሪቱ የደን ሃብት መስፋፋቱን፣ መጠበቁን እንዲሁም ዘላቂነት ያለው አጠቃቀም መረጋገጡን፤
10. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤

11. የሚመለከታቸውና የሚቆጣጠሯቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን፡፡

190. <u>የትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የትራንስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡፡

1. የትራንስፖርት አገልግሎቶች የአገሪቱን የልማት ስትራቴጂ በተሟላ ሁኔታ ለማገልገል በሚያስችል መልኩ በተቀናጀ መንገድ መስፋፋታቸውንና ከሌሎች ዘርፎች ጋር ተደጋግፈው የሚያድጉበት አሠራር መዘርጋቱን እና ውጤታማነቱን፤
2. የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶች ስታንዳርድ የወጣላቸው መሆኑን እንዲሁም የአጠቃቀም፣ የአያያዝና የአስተዳደር ስርዓቶች መወሰናቸውን እና ተግባራዊ መሆናቸውን፤
3. የትራንስፖርት አገልግሎቶች አስተማማኝና ደህንነታቸው የተጠበቀ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል የቁጥጥር ስልት መዘርጋቱን እና ተግባራዊ መሆኑን፤
4. የትራንስፖርት መሠረተ ልማቶች መዘርጋታቸውን፣ መስፋፋታቸውንና መጠገናቸውን እንዲሁም በተያዘላቸው የጊዜ ሰሌዳ ጥራታቸውን ጠብቀው በውጤታማነት መከናወናቸውን፤
5. የትራንስፖርት መሰረተ ልማቶችና አገልግሎቶችን የሚመለከቱ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አሰራሮች ጥቅም ላይ መዋላቸውን፣ መስፋፋታቸውን እና መዳበራቸውን፤
6. የደረቅ ወደብ አገልግሎትና አስተዳደርን፤
7. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤
8. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠሯቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን፡፡

191. <u>የንግድ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የንግድ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡-

1. የንግድ ፖሊሲ እና ስትራቴጂ የአገሪቱን የኢኮኖሚ ዕድገት በሚያፋጥን መልኩ ተግባራዊ መሆኑን፤

2. የአገር ውስጥ ንግድ እንዲስፋፋ እና ህጋዊ የንግድ አሠራር እንዲሠፍን የሚያስችሉ እና የሚያበረታቱ ተግባራት በአግባቡ መከናወናቸውን፤
3. የውጪ ንግድን ለማስፋፋትና ለማጠናከር የሚያስችሉ ሁኔታዎች መመቻቸታቸውን፤
4. ከወጪና ገቢ እቃዎች ጋር የተያያዙ ችግሮችን እንደዚሁም ፀረ-ውድድር የንግድ ተግባራትን ለመከላከል የሚያስችሉ ስርዓቶች መዘርጋታቸው፤
5. ለሸማቾች አስፈላጊው ጥበቃ መደረጉን፤
6. የሸማቾች የህብረት ስራ ማህበራት እና የንግድ የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤቶች እንዲቋቋሙና እንዲጠናከሩ ለማድረግ እየተደረገ ያለውን ማበረታቻ፤
7. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤
8. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን፡፡

192. <u>**የአርብቶ አደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ**</u>

የአርብቶ አደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናዉናል፡-

1. በሕገመንግስቱ የተደነገጉት የአርብቶ አደር መብቶች መከበራቸዉን ማረጋገጥ፤
2. የፌደራል መንግስት ለአርብቶ አደሮች የሚያደርገዉን ልዩ ድጋፍ አፈጻጸም፤
3. በአርብቶ አደሩ ዉስጥ ፈጣን ልማት ባማምጣ ኢኮኖሚያዊና ምህበራዊ ህይወቱን ለመለወጥና የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የፌደራ መንግስት የሚያደርገዉን እንቅስቃሴ፤
4. በፌደራል መንግስት የሚወጡ ህጎች፣ ፖሊሲዎች፣ ፕሮግራሞችና እቅዶች የአርብቶ አደሩን ጥቅም ያገናዘቡ መሆናቸዉን፤
5. የአርብቶ አደሩን አቅም በአጭሩ ጊዜ መገንባት እንዲቻል የአቅም ግንባታ ተቋማት መስፋፋታቸዉን በተለይም አዳሪ እና ተንቀሳቃሽ ትምህርት ቤቶች እንደዚሁም ሌሎች ትምህርት ቤቶች እንደየሁኔታዉ መስፋፋታቸዉን፤
6. የአርብቶ አደሩ የኑሮ መሠረት ለሆኑት እንስሳት የጤና አገልግሎት የገበያ መሠረተ ልማት፣ የመኖና የዉሃ አቅርቦት እንዲኖር በመንግስት የሚመደበዉ በጀት በአግባቡ በስራ ላይ መዋሉን፤

7. በአርብቶ አደሩ አካባቢ የሚታቀዱ የመንደር ምስረታ ፕሮግራሞች በአርብቶ አደሩ ፈቃደኝነት ላይ የተመሠረቱ መሆናቸዉንና የተሟሉ የመሰረተ ልማት አገልግሎቶች መገንባታቸዉን፣
8. ለአርብቶ አደሩ የኤክስቴንሽን ድጋፍ መሰጡን፤
9. በአርብቶ አደር አካባቢ የቅድሚያ ማስጠንቀቂያ ጥናቶች መከናዎናቸዉን፤
10. በምርምርና ጥናት ተቋማት የአርብቶ አደሩ የእንስሳት ሀብት ምርታማነት የሚያድግበትና በተጓዳኝም የግብርና ዉጤቶች ተጠቃሚ የሚሆንበት የምርምርና የጥናት ሥርዓት መዘርጋቱን፤
11. በአርብቶ አደሩ አካባቢ ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶች የሚወገዱበትን ሁኔታ፤
12. ልዩ ድጋፍ ለሚሹ ክልሎች ትኩረት በመስጠት የተቀናጀ ድጋፍ መደረጉን፤
13. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤
14. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን፡፡

193. <u>የኢንዱስትሪ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የኢንዱስትሪ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡-

1. ኢንዱስትሪንና ኢንቨስትመንትን ለማስፋፋት የሚያበረታቱ ተግባራት በአግባቡ እየተከናወኑ መሆናቸውን፣
2. ስትራቴጂያዊ ትኩረት ለሚሠጣቸው ኢንዱስትሪዎች ተገቢው ድጋፍ እየተሠጠ መሆኑን፤
3. የኢንዱስትሪ ልማትን ለማፋጠን የሚያስችሉ እና ለኢንቨስትመንት የተመቻቹ ህጎች፣ ፓሊሲዎችና ስትራቴጂዎች መኖራቸው እና በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤
4. የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማትን ለማስፋፋት የሚደረገው እንቅስቃሴ፤
5. ለኢንዱስትሪዎች አስተማማኝ ግብዓት ለማቅረብ የሚያስችል ስልት መቀየሱን እና የግብዓት አቅርቦት ትስስር ስርዓት መዘርጋቱን፤
6. በአነስተኛ፣ በመካከለኛና በከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች መካከል የተቀናጀ ትስስር እንዲፈጠር የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን እንዲሁም አነስተኛ ኢንዱስትሪዎች ወደ መካከለኛና ከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች እንዲሸጋገሩ አስፈላጊው ድጋፍ መሰጠቱን፤

7. የኢንዱስትሪ የዘርፍና የሙያ ማህበራት እንዲቋቋሙና ጠንክረው እንዲንቀሳቀሱ የሚደረገውን ማበረታቻ፤

8. የሚከታተላቸውናየሚቆጣጠራቸው ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፣

9. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን።

194. <u>የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የከተማ ልማትና ኮንስትራክሽን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡-

1. ከተሞች የአካባቢያቸው የልማት ማዕከል እንዲሆኑ ሁለገብና የተቀናጀ ድጋፍ መሰጠቱን፣ በጥናት ላይ የተመሰረተ አከታተምና የከተሞች ደረጃ መመዘኛ መውጣቱን እንዲሁም የከተሞች አገልግሎት አሰጣጥ እንዲሻሻል የአቅም ግንባታ እገዛ መደረጉን፤

2. የከተሞች ልማት ከገጠር ልማት ጋር ተቀናጅቶ የሚከናወንበት መንገድ መጠናቱንና ከክልሎች ጋር በመተባበር ተግባራዊ መደረጉን፤

3. የከተማ ልማት ሥራ ከድህነት ቅነሳ ጋር ተቀናጅቶ መከናወኑንና የከተማው ነዋሪ ተመጣጣኝ የመኖሪያ ቤት የሚሰራበትን አቅጣጫ ለመቀየስ የሚያስችል ጥናትና ለከተሞች የአቅም ግንባታ ድጋፍ መሰጠቱን፤

4. የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ በብቃት እንዲገነባ ምቹ ሁኔታ መፈጠሩን፣

5. የፌዴራል መንግሥት ቤቶች አስተዳደር በአግባቡ መመራቱን፤

6. በፌደራል መንግሥት በጀት የሚሰሩ ህንፃዎች በጥራትና በአግባቡ መከናወናቸውን፤

7. በአገር ውስጥ የሚመረቱ የኮንስትራክሽን ዕቃዎች አይነትና ጥራት ለማሻሻል የሚደረገውን እንቅስቃሴ፤

8. ኮሚቴው የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና እቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤

9. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን፡፡

195. <u>የከፍተኛ ትምህርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የከፍተኛ ትምህርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡-

1. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በአገሪቱ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እና ትኩረቱ በእውቀትና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ የሆነ እና ለልማትና ዲሞክራሲ የሚያግዝ ምርምር እያረጋገጡ መሆኑን፤
2. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የማስፋፋትና የማጠናከር ተግባር በአግባቡ መከናወኑን፤
3. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለአገሪቱ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት የሰለጠነ የሰው ሃይል ለማፍራት የሚያደርጉትን እንቅስቃሴ፤
4. የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች ቅበላና ምደባ ፍትሃዊ መሆኑን፤
5. በከፍተኛ ትምህርት የማህበራዊ ሳይንስ 30 በመቶ እና የተፈጥሮ ሳይንስ 70 በመቶ የቅበላ ምጣኔ አፈፃፀምና ውጤታማነትን፤
6. በከፍተኛ ትምህርት የሴቶች መብቶችና ተጠቃሚነት መረጋገጡን፤
7. የከፍተኛ ትምህርት መምህራን ምልመላ፣ ስልጠና እና ስምሪት በአግባቡ መከናወኑን፤
8. የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት መልካም አስተዳደር፣ የመማር ማስተማር እና ማህበራዊ ጉዳዮችን በተመለከተ፤
9. ኮሚቴው የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የመንግስትን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና እቅዶች በአግባቡ በስራ ላይ ማዋላቸውን፤
10. የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን እና የባለብዙ ዘርፍ ለሆኑ ስራዎች ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን፡፡

196. <u>የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡-

1/ የግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ምርትና ምርታማነትን በተመለከተ፤

2/ የአገሪቷን በምግብ እህል ራስን የመቻልና የምግብ ዋስትና የማረጋገጥ ዓላማ ግቡን እንዲመታ የሚከናወኑ ተግባራትን፤

3/ የአነስተኛ መስኖ ልማት መስፋፋቱን፣ የግብርና ምርምር በቅንጅትና በትብብር ለመስራት የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱን፤

4/ ለገበያ የሚቀርብ የግብርና ምርት የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ለማድረግ የሚያስችል ስርዓት መኖሩን፤

5/ የእፀዋት በሽታዎች ወረርሽኝና ተዛማጅ ተባዮች ለመከላከል የሚያስችል ስርዓት መዘርጋቱንና በአግባቡ ስራ ላይ መዋሉን፤

6/ የፀረተባይ ኬሚካሎች አስተዳደርና ቁጥጥር ስራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን፣

7/ የግብርና ምርታማነትና ጥራትን የሚያረጋግጡ ውጤታማ ቴክኖሎጂዎች መስፋፋታቸውንና በአገር ውስጥ የሚበዙበት ሁኔታ መመቻቸቱን፤

8/ የህብረት ስራ ማህበራት መስፋፋታቸውን፤

9/ የእንስሳት መድሃኒቶችና መኖ ጥራት እንዲሁም የእንስሳት ህክምና አስተዳደርና ቁጥጥር ስራዎች በአግባቡ መከናወናቸውን፤

10/የአደጋ መከላከልና ዝግጁነት ስራዎች በአግባቡ እየተከናወኑ መሆናቸውን፤

11/የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማትን የሚመለከቱ ፖሊሲዎች፣ ህጎች፣ ስትራቴጂዎች እና ዕቅዶች በአግባቡ በሥራ ላይ መዋላቸውን፤

12/የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን፡፡

197. <u>የውጭ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ</u>

1. የውጭ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ክትትልና ቁጥጥር ያከናውናል፡-

ሀ/ መንግስት የሚፈራረማቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች የአገሪቱን ብሔራዊ ጥቅም የሚያረጋግጡና ሉአላዊነትን የሚያስከብሩ፣ ከውጭ ግንኙነት መርሆና ፖሊሲ ጋር የተጣጣሙ መሆኑን፤

ለ/ መንግስት የሚያካሂዳቸው የውጭ ግንኙነት ተግባራት የአገሪቱን ዘላቂ ሠላም፣ ዲሞክራሲና ልማት የሚያረጋግጡ መሆኑ፤

ሐ/ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲና ስትራቴጂ እንዲሁም እቅዶችና ህጎች በአግባቡ በስራ ላይ መዋላቸውንና የሚፈለገውን ውጤት ማስገኘታቸውን፤

መ/ ኮሚቴው የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የመንግስትን ፖሊሲዎች፣ ስትራቴጂዎችና እቅዶች በአግባቡ በስራ ላይ ማዋላቸውን፤

ሠ/ የሚከታተላቸውና የሚቆጣጠራቸው ተቋማት የተመደበላቸውን በጀት በአግባቡና በውጤታማነት በስራ ላይ ማዋላቸውን እና የባለብዙ ዘርፍ ለሆኑ ስራዎች ተገቢውን ትኩረት ሰጥተው እየተንቀሳቀሱ መሆኑን፡፡

2. ቋሚ ኮሚቴው ምክር ቤቱ ከሌላ አገር ምክር ቤቶች እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያካሂዳቸውን የሁለትዮሽ እና የባለ-ብዙ ወገን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነቶች ያስተባብራል፣ አፈፃፀሙንም ይከታተላል፡፡

## ምዕራፍ ሀያ አምስት

## ስለ ፓርላማ ህብረት እና የወዳጅነት ቡድን

### 198. የወዳጅነት ቡድንን ስለ ማቋቋም

1. ምክር ቤቱ ከተለያዩ አገሮች አቻ የፓርላማ የወዳጅነት ቡድኖች ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ የወዳጅነት ቡድኖችን ሊያቋቁም ይችላል፡፡
2. እያንዳንዱ የወዳጅነት ቡድን ሊቀመንበሩንና ምክትል ሊቀመንበሩን ጨምሮ በምክር ቤቱ የሚመረጡ ከዘጠኝ እስከ አስራ አንድ የሚደርሱ አባላት ይኖሩበታል፡፡
3. ማንኛዉም የወዳጅነት ቡድን ተጠሪነት ለዉጭ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይሆናል፡፡
4. በዚህ አንቀጽ የተደነገገዉ ቢኖርም ምክር ቤቱ የሚያቋቁማቸዉን የወዳጅነት ቡድኖች እንደሁኔታዉ በአህጉር፣ በክፍለ አህጉር ወይም በአካባቢ ደረጃ ሊያደራጅ ይችላል፡፡

### 199. የወዳጅነት ቡድን ተግባር እና ኃላፊነት

የወዳጅነት ቡድን የሚከተሉት ትግባርና ሃላፊነት ይኖሩበታል፡-

1. በአገሮቹ ህዝቦች መካከል ጠንካራ ወዳጅነት እና በጎ ግንኙነት እንዲኖር ጥረት ማድረግ
2. ከአቻ ፓርላማዎች ጋር መተባበር ልምድ መለዋወጥና ወዳጅነትን ማጠናከር፤
3. አገራዊ ገጽታን መገንባት፤
4. ስለሌላኛዉ አገር ፓለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ሁኔታ የተሟላ ግንዛቤ መያዝ፤
5. በኢትዮጵያና በሌላኛዉ አገር ያሉ የየወቅቱ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፓለቲካዊ ግንኙነቶችን መከታተልና የተሟላ ግንዛቤ መያዝ፤
6. ሌሎች ተያያዥነት ያላቸዉን ተግባራት ማከናወን፡፡

### 200. የወዳጅነት ቡድን አሠራር

1. ማንኛዉም የወዳጅነት ቡድን የመሠረተበትን አገር የሚመለከት አጠቃላይ መረጃ እና ሌሎች ጠቃሚ ሰነዶችን በማሰባሰብ ለስራዉ በግብአትነት ይጠቀማል፡፡

2. ማንኛውም የወዳጅነት ቡድን ስራዉን በእቅድ ይመራል፣በየጊዜዉ የስራ አፈጻጸሙን ይገመግማል፡፡

3. ማንኛዉም የወዳጅነት ቡድን እንደአስፈላጊነቱ ስጦታዎችን ሊለዋወጥ፥ ጥናትና ዓዉደ ጥናት ሊያካሂድ ወይም በአገር ዉስጥና በዉጭ አገር በተለያዩ ስብሰባዎች ተሳትፎ ሊያደርግ ይችላል፡፡

4. ማንኛዉም የወዳጅነት ቡድን ሰነዶቹን በአግባቡ መያዝ እና ስራዉን በቃለ-ጉባዔ መዝግቦ መያዝ ይኖርበታል፡፡

5. እያንዳንዱ የወዳጅተነት ቡድን እቅዱን እና የስራ አፈጻጸሙን ሪፓርቱን ለዉጭ ጉዳይ ቋሚ ኮሚቴ ያቀርባል፡፡

6. ማንኛዉም የወዳጅነት ቡድን የራሱን የዉስጥ የአሰራር ሥነ-ሥርዓት ሊያወጣ ይችላል፡፡

7. በዚህ ደንብ ለኮሚቴ አባላት የተዘረዘሩ የሥነ-ምግባር ድንጋጌዎች እንደአስፈላጊነቱ ለወዳንነት ቡድን አባላትም ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡

201. <u>ከፓርላማ ህብረት ጋር ስለሚኖር ግንኙነት</u>

1. ምክር ቤቱ በዓለም አቀፋዊ፣በአህጉራዊ እና በሌሎች የፓርላማ ዲፕሎማሲ ተግባራት ሊሳተፍ ይችላል፡፡

2. በፓርላማ ህብረት መድረኮች ላይ የሚሳተፉ አባላት ቁጥር በህግ መሠረት ወየም ከበጀት አንጻር እየታየ የሚወሰን ይሆናል፡፡

3. በዚህ አንጽ በንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት ምክር ቤቱን በቋሚነት የሚወክሉ አባላት በአፈጉባዔዉ አቅራቢነት በምክር ቤቱ የሚሰየሙ ሲሆን ተጠሪነታቸዉ ለአፈጉባዔዉ ይሆናል፡፡

4. አፈጉባዔዉ ምክር ቤቱን በጊዜያዊነት በመወከል በተለያዩ ስብሰባዎች የሚሳተፉ አባላትን ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመመካከር ይመርጣል፡፡

5. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) እና (4) መሠረት ምክር ቤቱን በመወከል በተለያዩ መድረኮች የሚሳረፉ ልዑካን በተሳረፉበት ቦታ ሁሉ ስለጉዳዩ በቂ ዝግጅት ማድረግና አግበብ ካላቸዉ አካላት ዝርዝር መረጃ በማግኘት የአገሩቱን ጥቅም ያስጠበቀ እንዲሁም ምክር ቤቱ የገባቸዉን ግዴታዎች እና ስምምነቶች በማክበር መንቀሳቀስ ይጠበቅባቸዋል፡፡

6. በዚህ አንቀጽ መሠረት በተለያዩ መድረኮች የሚሳተፉ ልዑካን በዚህ ደንብ የተደነገጉ አግባብነት ያላቸዉ ሥነ-ምግባሮችና እንደሁኔታዉ በአንቀጽ 200 ላይ የተደነገገዉን ተግባራዊ ማደረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

7. በዚህ አንቀጽ መሠረት ምክር ቤቱን በመወከል በተለያዩ መድረኮች የሚሳተፉ ልዑካን ከተልዕኮ በኋላ ለሚመለከተዉ አካል ሪፓርት ያቀርባሉ፡፡

## ምዕራፍ ሃያ ስድስት

## ስለ ፓርቲ ተጠሪዎች

202. ስለ ፓርላማ ቡድን

1. በሌሎች ህጎች ስለፓርቲ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ ስራዉን በተደራጀና በተገቢዉ መንገድ ለመወጣጥ እንዲያስችለዉ በምክር ቤቱ መቀመጫ ያላቸዉን ፓርቲዎች ቡድኖች ለምክር ቤት ስራ እንደ ፓርላማ ቡድን ይቆጥራሉ፡፡
2. የፓርላማ ቡድን ማለት አንድ ፓርቲ ወይም በምርጫ ክልሎች እርስ በርሳቸዉ ያልተወዳደሩ፣ በአንድ ፓለቲካ ፕሮግራም የተወዳደሩ ፓረቲዎች አባላት ስብሰብ ሆኖ ከአስር የማያንስ መቀመጫ ያለዉን ወይም ያላቸዉን ፓርቲ ወይም ፓርቲዎች የያዘ ነዉ፡፡

203. የመንግስት ተጠሪዎች አደረጃጀት

በምክር ቤቱ ዉስጥ አብላጫ መቀመጫ ያገኘ የፓለቲካ ፓርቲ ወይም ጣምራ ፓርቲዎች አንድ ዋና ተጠሪ እና ከአራት ያልበለጡ ረዳት ተጠሪዎች ይወከላል ወይም ይወከላሉ፡፡

204. የመንግስት ተጠሪዎች አሰያየም

የምንግስት ዋና ተጠሪ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየም ሲሆን ረዳቶቹ ደግሞ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ከዋናዉ የመንግስት ተጠሪ ጋር በመመካከር ይሠይማቸዋል፡፡

205. የመንግስት ተጠሪዎች ተጠሪነት

1/ የመንግሥት ዋና ተጠሪ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

2/ የመንግስት ረዳት ተጠሪዎች ተጠሪነት ለመንግስት ዋና ተጠሪ ይሆናል፡፡

206. የመንግስት ዋና ተጠሪዎች ሥልጣንና ተግባር

1. የዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ የመንግስት ተጠሪዎች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

ሀ/ የፓርቲያቸዉ አባላት ስለ ምክር ቤቱ አጀንዳዎች አስቀድሞ እንዲያዉቁ ይደረጋሉ፤

ለ/ የፓርቲያቸዉ አባላት በምክር ቤቱ ስብሳባዎች እንዲገኙ እና ለፓርቲያቸዉ ድምጽ እንዲሰጡ ያደርጋሉ፤

ሐ/ በምክር ቤቱ ዉስጥ የሚገኙ የፓርቲዉ አባላት ለሥራቸዉ ብቁና ዝግጁ ሆነዉ እንዲገኙ ቀጣይነት ያለዉ ሥራ ይሠራሉ፣

መ/ ፓርቲዉን በመወከል በምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎችም ሆነ በሌሎች ፓርቲዉን በሚመለከቱ ተልዕኮዎች የሚሳተፉ የፓርቲዉ አባላትን ዝርዝር ለሚመለከተዉ አካል ያቀርባሉ፡፡

2. የዚህ ደንብ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ በምክር ቤቱ ወስጥ የመንግስት ዋና ተጠሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ/ በፓርቲዉ አመራር እና በምክር ቤቱ ዉስጥ ፓርቲዉን በወከሉ የምክር ቤት አባላት መካከል የተቀናጀ ግንኙነት በመፍጠር እንደ ድልድይ ሆኖ ይሠራል፣

ለ/ ፓርቲዉን በመወከል በምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎች ዉስጥ የሚሳተፉ እንዲሁም ለሌሎች ተልዕኮዎች የሚያስፈልጉ አባላትን ዝርዝር ለሚመለከተዉ አካል ያቀርባል፣

ሐ/ በምክር ቤቱ ሥራዎች እና አሠራሮች ዙሪያ መንግሥትን ያማክራል፣ መንግሥት በሚያስቀምጥለት አቅጣጫም ሥራዎችን ተግባራዊ ያደርጋል፣

መ/ ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ የመንግስት አጀንዳዎች እና ለዉይይት የሚስፈልገዉን ጊዜ ለምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ አቅርቦ ያስወስናል፣

ሠ/ ከተለያዩ የፓርቲ ዋና ተጠሪዎች ጋር በምክር ቤቱ አጀንዳዎች እና ሌሎች ተግባራት ዙሪያ ይመካከራል፣

ረ/ በምክር ቤቱ ዉስጥ ያሉ የፓርቲ አባላትንና ረዳት ተጠሪዎችን ይመራል፣ያስተባብራል፣

ሰ/ ከሚኒስትሮች ጋር በስራቸዉ ዙሪያ የጠበቀ ግንኙነት በመፍጠር ተግባሩን ያከናዉናል፣

ሸ/ መንግስት በምክር ቤቱ የሚኖረዉን ሳምንታዊ ፕሮግራም እና አጀንዳ በመለየት አባላቱ ቀድመዉ እንዲያዉቁ እንደዚሁም በወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ አባላቱ ግንዛቤ እንዲኖራቸዉ ያደርጋል፣

ቀ/ ፓርቲዉን በመወከል በምክር ቤቱ ስብሰባ ሐሰብ የሚያቀርቡ የፓርቲ አባላት ስም ዝርዝር ለምክር ቤቱ አፈጉባዔ ያስተላልፋል፣

በ/ በምክር ቤቱ ዉስጥ በተለያየ ምክንያት በቋሚነት የተጓደሉ አባላትን ለፓርቲዉ ያሳዉቃል፣ በሟሟያ ምርጫ እንዲተኩ የዉሳኔ ሀሳብ ለፓርቲዉ ያቀርባል፣

ተ/ እርሱ በማይኖርበት ጊዜ በምትኩ የሚሰራ ከረዳቶች መካከል ይወከላል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1/ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የመንግስት ረዳት ተጠሪዎች በምክር ቤቱ ወስጥ በመንግስት ዋና ተጠሪ ተለይተዉ የሚሰጧዉን ሌሎች ተግባራት ያከናዉናሉ፡፡

207. <u>**የፓርቲ ተጠሪዎች አደረጃጀት**</u>

1. በመክር ቤቱ ዉስጥ ያለዉ ዋናዉ ተቃዋሚ ፓርቲ አንድ ዋና ሁለት ረዳት ተጠሪዎች ይኖሩታል፡፡
2. በምክር ቤቱ ዉስጥ የለዉ ሁለተኛ ተቃዋ የፓለቲካ ፓርቲ አንድ ዋና እና አንድ ረዳት ተጠሪ ይኖሩታል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዕስ አንቀጽ (1) እና (2) ከተጠቀሱት ዉጭ ያሉ ሌሎች በምክር ቤቱ መቀመጫ ያላቸዉ ፓርቲዎች ወይም የፓርላማ ቡድኖች እያንዳንዳቸዉ አንድ ተጠሪ ይኖራቸዋል፡፡

208. <u>**የፓሪቲ ተጠሪዎች አሰያየም**</u>

የፓርቲ ተጠሪዎች በመክር ቤቱ ባሉ አባሎቻቸዉ ወይም በፓርቲ መሪዎቻቸዉ ይሰየማሉ፡፡

209. <u>**የፓርቲ ተጠሪዎች ተጠሪነት**</u>

1. እያንዳንዱ ፓርቲ ዋና ተጠሪ ተጠሪነት ለወከለዉ ፓርቲ መሪ ይሆናል፡፡
2. የረዳት ተጠሪዎች ተጠሪነት ለዋና ተጠሪዎች ይሆናል፡፡

210. <u>**የፓርቲ ተጠሪዎች ስልጣንና ተግባር**</u>

1. የፓርቲ ተጠሪዎች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-
   ሀ/ አባሎቻቸዉ ስለምክር ቤቱ አጀንዳዎች አስቀድመዉ እንዲያዉቁ ያደርጋል፤
   ለ/ አባሎቻቸዉ በምክር ቤቱ ዉስጥ ያሉ ስብሰባዎች እንዲገኙና ለፓርቲያቸዉ ድምጽ እንዲሰጡ ያደርጋሉ፤
   ሐ/ በምክር ቤቱ ዉስጥ የሚገኙ የፓርቲዎች አባላት ለሥራቸዉ ብቁና ዝግጁ ሆነዉ እንዲገኙ ቀጣይነት ያለዉ ስራ ይሠራሉ፤
   መ/ ፓርቲዎቻቸዉን በመወከል በምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎች የሚተሩ ወይም ለሌሎች ተልዕኮዎች የሚያስፈልጉ አባሎቻቸዉን ዝርዝር ለሚመለከተዉ አካል ያቀርባሉ፤
2. በምክር ቤቱ ወስጥ ያሉ የፓርቲዎች ዋና ተጠሪዎች የሚከተሉት ሥልንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

ሀ/ በፓርቲያቸዉ አመራር እና በምክር ቤቱ ዉስጥ ፓርቲዉን በወከሉ የምክር ቤት አባላት መካከል የተቀናጀ ግንኙነት በመፍጠር እንደ ድልድይ ሆነዉ ይሠራሉ፤

ለ/ በመክር ቤቱ ወስጥ ያሉ ረዳት ተጠሪዎቻቸዉንና አባሎቻቸዉን ይመራሉ፤

ሐ/ ለምክር ቤቱ የሚቀርቡ አጀንዳዎቻቸዉን እና የሚያስፈልገዉን ጊዜ ለምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ አቅርበዉ ያስወስናሉ፤

መ/ ፓርቲዉን በበመወከል በምክር ቤቱ ስብሰባ ሀሳብ የሚያቀርቡ የፓርቲያቸዉን አባላት ስም ዝርዝር ለአፈጉባዔዉ ያስተላልፋሉ፤

ሠ/ ፓርቲያቸዉን በመወከል በምክር ቤቱ የተለያዩ ኮሚቴዎች የሚሳተፉ ወይም ለሌሎች ተልዕኮዎች የሚያስፈልጉ አባሎቻቸዉን ዝርዝር ለማመለከተዉ ያቀርባሉ፤

ረ/ በምክር ቤቱ ወስጥ በተለያዩ ምክንያቶች በቋሚነት የተጓደሉ አባሎቻቸዉን በሚመለከት ለየፓርቲዎቻቸዉ ያሳዉቃሉ፣ በሚሚያ ምርጫም እንዲተኩ የዉሳኔ ሀሳብ ለፓርቲያቸዉ ያቀርባሉ፤

ሰ/ ከመንግስት ዋና ተጠሪ ጋር በመሆን በምክር ቤቱ አጀንዳዎችና ሌሎች ተግባራት ዙሪያ ይመካከራሉ፤

ሸ/ እነሱ በማይኖሩበት ጊዜ ተክተዋቸዉ የሚሰሩ ከረዳቶቻቸዉ ወይም ከምክር ቤት አባሎቻቸዉ መካከል ይወክላሉ፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ የፓርቲ ረዳት ተጠሪዎች በዋና ተጠሪዎቻቸዉ ተለይተዉ የሚሰጣቸዉን ሌሎችተግባራት ያከናዉናሉ፡፡

## <u>ምዕራፍ ሃያ ሰባት</u>
## <u>የምክር ቤቱ የክብር ጥበቃ ኃይል</u>

### 211. <u>አደረጃጀት</u>

1. የምክር ቤቱ የክብር ጥበቃ ኃይል፡-

ሀ/ ዋና የክብር ጥበቃ ኃላፊ፤

ለ/ ረዳት የክብር ጥበቃ ኃላፊ፤ እና

ሐ/ አስፈላጊ የሰዉ ኃይል ይኖሩታል፡፡

2. የምክር ቤቱ ዋና የክብር ጥበቃ ኃላፊና ረዳቱ በአፈጉባዔ ይሾማሉ፡፡

3. ዋና የክብር ጥበቃ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለአፈጉባዔዉ ሲሆን ረዳት የክብር ጥበቃ ኃላፊ ተጠሪነቱ ለዋናዉ የክብር ጥበቃ ኃላፊ ይሆናል፡፡

212. <u>ተግባርና ኃላፊነት</u>

1. የምክር ቤቱ የክብር ጥበቃ ኃይል የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፡፡

ሀ/ የምክር ቤቱ የስብሰበ አዳራሾችና ቅጥር ግቢ ዉስጥ ህግና ስነ-ስርዓትን ያስከብራል፤ይጠብቃል፤

ለ/ ከሚመለከታቸዉ ሌሎች የጸጥታ ክፍሎች ጋር ግንኙነት ያደርጋል፤

ሐ/ ስለ ምክር ቤቱ የጸጥታ ጉዳይ አፈጉባዔዉን ያማክራል፣ስለ ስራዉ እንቅስቃሴ ሪፖርት ያቀርባል፡፡

2. የክብር ጥበቃ ኃይል አደረጃጀትና ዝርዝር ተግባራት በዚህ ደንብ መሰረት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሃያ ስምንት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

213. <u>የሴቶች ኮከስ</u>

1. የሴቶች እና ህፃናት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የሴቶች ኮከስ የሚከተሉት ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ/ የሴት የምክር ቤት አባላት የልምድ ልውውጥ ያካሂዳል፤

ለ/ የሴቶች መብትና ተጠቃሚነትን በሚመለከቱ የተለያዩ አጀንዳዎች ምክክር ያካሂዳል፤

ሐ/ የአቅም ግንባታና የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎችን ያከናውናል፤

መ/ ከክልል ሴቶች ኮከሶች ጋር ግንኙነት ያደርጋል።

2. የሴቶች ኮከስ ተጠሪነት ለአፈጉባዔው ይሆናል፣ የኮከሱ ዝርዝር አደረጃጀትና አሰራር በዚህ ደንብ መሰረት በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል።

214. <u>የምክር ቤቱ በጀት</u>

1. የምክር ቤቱ ዓመታዊ ረቂቅ በጀት በፅህፈት ቤቱ ተዘጋጅቶ ለአፈጉባዔው ይቀርባል፣ አፈጉባዔውም ረቂቅ በጀቱ እንዲመረመር ለበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይመራዋል።

2. የበጀትና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (1/ መሠረት የተመራለትን ረቂቅ ዓመታዊ የምክር ቤቱን በጀት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር በመመካከር ይመረምራል፣ የማጣቃለያ

አስተያየቱንም በአፈጉባዔው በኩል ለምክር ቤቱ ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ ያቀርባል።

3. የምክር ቤት አማካሪ ጉዳዮች ኮሚቴ በዚህ አንቀፅ በንዑስ አንቀፅ (2/ መሠረት የቀረበለትን አስተያየት ከገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ጋር በመወያየት መርምሮ በረቂቅ ዓመታዊ በጀቱ ላይ የውሳኔ ሃሳቡን ለምክር ቤቱ ያቀርባል።

215. <u>ደንቡን ስለማሻሻል</u>

1. ይህን ደንብ ለማሻሻል አባላት ወይም ኮሚቴ የማሻሻያ ሃሳብ ሊያመነጩ ይችላሉ፡፡
2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1/ መሰረት የመነጨው የማሻሻያ ሃሳብ ለምክር ቤቱ ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ መቅረብ አለበት፣ አማካሪ ኮሚቴውም የቀረበውን የማሻሻያ ሃሳብ ከተቀበለው ረቂቅ ማሻሻያ ደንብ ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ለህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ይመራዋል።
3. የምክር ቤቱ ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2/ መሰረት በህግ፣ ፍትህና አስተዳደር ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ተዘጋጅቶ የቀረበለትን ረቂቅ የማሻሻያ ደንብ በመመርመር ለምክር ቤቱ ውሳኔ ያቀርባል።

216. <u>የደንቡን ድንጋጌዎች ስለማገድ</u>

ምክር ቤቱ በአፈጉባዔው አቅራቢነት የደንቡን መሰረታዊ ዓላማ ሳይነካ የደንቡን ድንጋጌዎች ለማገድ እንዲሁም የኮሚቴዎችን አደረጃጀት፣ ስልጣን እና ተግባር ማሻሻል ይችላል፡፡

217. <u>መመሪያ ስለማዉጣት</u>

የምክር ቤት ጉዳዮች አማካሪ ኮሚቴ ለዚህ ደንብ አፈጻጸም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

218. <u>ስለተሻሩ ህጎች</u>

1. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የአሰራርና የአባላት የሥነ-ምግባር ደንብ ቁጥር 3/1998 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡
2. የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የኮሚቴወች አደረጃጀትን ለመወሰን የወጣዉን ዉሳኔ ቁጥር 2/2003 በዚህ ደንብ ተሽሯል፡፡
3. ከዚህ ደንብ ጋር የሚቃረን ማንኛዉም ህግ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ ደንብ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረዉም፡፡

219. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በምክር ቤቱ ከጸደቀበት ከመስከረም 27 ቀን 2008 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 13 ቀን 2008 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

ለ/ <u>የፌደሬሽን ምክር ቤት</u>

## አዋጅ ቁጥር 251/1993

## የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ለማጠናከርና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር የወጣ አዋጅ

የህጎች ሁሉ የበላይ በሆነው የፌዴራሉ ሕገ መንግሥት የኢትዮጵያ ብሔር፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች የሚወከሉበት የፌዴሬሽን ምክር ቤት እንደ አንድ ሕገመንግሥታዊ ተቋም የተቋቋመ በመሆኑና ሥልጣንና ተግባሩ ጠቅለል ባለ መልክ በሕገመንግስቱ ውስጥ የተመለከተ ስለሆነ፣

በጥቅል የተቀመጡት ሃላፊነቶችም ለአፈጻጸም ያመች ዘንድ በመደበኛው ሕግ ዘርዘር ብለው እንዲደነገጉ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የኢትዮጵያፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55 /1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ለማጠናከርና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር የወጣ አዋጅ ቁጥር 251/1993" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ

   1. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 47(1) መሠረት በክልልነት የታወቁት ሲሆኑ እንዳስፈላጊነቱ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደርንና የድሬዳዋ ከተማ ካውንስልን ይጨምራል፣
   2. "ህግ" ማለት በፌዴራል ወይም በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ አዋጆች እና በሌሎች የፌዴራልና የክልል የመንግሥት አካላት የሚወጡ ደንቦችና መመሪያዎች ሲሆኑ ኢትዮጵያ ያጸደቀቻቸውን አለምአቀፍ ስምምነቶችንም ያካትታል፡፡
   3. ምክር ቤት ማለት ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፣
   4. "ሕገመንግሥት" ማለት ኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት ነው፣

5. “ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ” ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንፀባርቅ ባህል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው የጋራ የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው፣

6. “የሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ” ማለት የፌዴራል መንግሥቱ የሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ነው፣

7. ፍርድ ቤት ማለት በማንኛውም ደረጃ የሚገኝ የፌዴራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት ነው፡

8. “አፈ ጉባኤ” እና “ምክትል አፈጉባኤ” ማለት የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አፈጉባዔና ምክትል አፈጉባዔ ናቸው።

3. <u>የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክር ቤቱ፡

1. ሕገ መንግሥቱን ይተረጉማል፣
2. የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን ያደራጃል፣
3. የብሔሮች ብሔረሰቦች ሕዝቦች የራስን እድል በራስ የመወሰን እስከ መገንጠል መብት በተመለከተ በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ በሕገ መንግሥት መሠረት ይወስናል፡
4. በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው የሕዝቦች እኩልነትና በሕዝቦች መፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር ያደርጋል፣
5. በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች መፍትሔ ይፈልጋል፣
6. የክልሎችና የፌዴራል መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን፡ እንዲሁም የፌዴራል መንግሥት ለክልሎች ድጐማ የሚሰጥበትን ቀመር ይወስናል፣
7. በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐብሄር ጉዳዮችን ይለያል፣
8. ማንኛውም ክልል ፌዴራል ሕገመንግሥቱን በመጣስ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የጣለ እንደሆነ የፌዴራል መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ያዛል፣
9. በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 103/5/ መሠረት የምርጫ ቦርድ በሚያቀርብለት ረቂቅ የምርጫ ክልሎች አከላለልን ይወስናል፣

10.በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 99 መሠረት ለፌዴራል ወይም ለክልል መንግሥታት ተለይተው ባልተሰጡ ታክስና ግብር የመጣል ሥልጣኖች ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በጋራ ይወስናል፣

11.በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 70/2/ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጋር በሚደረግ የጋራ ስብሰባ የአገሪቱን ፕሬዝዳንት ይመርጣል፣

12.በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 105 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) በተገለጸው መሠረት ሕገመንግሥቱን በማሻሻል ሂደት ይሳተፋል፣

13.በሥልጣኑ ሥር በሚካተቱ ጉዳዮች ላይ ከሌሎች ጋር በመተባበር ትምህርትና ሥልጠና ይሰጣል እንደአስፈላጊነቱም ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣

14.የምክር ቤቱ ቋሚና ጊዚያዊ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፣

15.የራሱን አፈጉባዔና ምክትል አፈጉባዔ ይመርጣል።

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ሀገ መንግስትን ስለመተርጎም</u>

4. <u>መሠረቱ</u>
   1. ምክር ቤቱ ሕገመንግስቱን የመተርጎም ሥልጣን ይኖረዋል።
   2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተጠቀሰው ቢኖርም፤ ምክር ቤቱ በሕገመንግሥት ትርጉም የምክር አገልግሎት ለመስጠት አይገደድም፡፡

5. <u>ትርጉም ስለመስጠት</u>
   1. ምክር ቤቱ የሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሕገመንግሥትን መተርጎም ያስፈልጋል በማለት በጉዳዩ ላይ የሚያቀርበውን የውሣኔ ሃሣብ መርምሮ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፡፡
   2. የሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ የሕገመንግሥት ትርጉም አያስፈልገውም በማለት ውሣኔ በሰጠባቸው ጉዳዮች ቅር የተሰኘ ወገን ይግባኙን ለምክር ቤት ማቅረብ ይችላል፡፡

6. <u>ለሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ስለመላክ</u>

   ምክር ቤቱ በቀጥታ የሚቀርብለትን አዲስ የሕገመንግሥት ትርጉም ጥያቄ ለአጣሪ ጉባኤው ይልካል።

7. <u>በሕገመንግሥት ትርጉም ተፈፃሚ ስለሚሆኑ መርሆዎች</u>

1. ምክር ቤቱ የሚቀርብለትን የሕገመንግሥት ነክ ጉዳዮች መርምሮ ለመወሰን ጠቃሚ ናቸው ብሎ የሚያምንባቸውን የሕገመንግሥት አተረጓጎም መርሆዎች መለየትና በሥራ ላይ ማዋል ይችላል፡፡

2. ለምክር ቤት የቀረበው ጥያቄ በህገመንግሥት የሰፈሩትን መሠረታዊ ነፃነቶች የሚመለከት ሲሆን ትርጉሙ ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን አለም አቀፍ ሰብአዊ መብቶች ሕግጋት፣ አለምአቀፍ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶችና የአለም አቀፍ ሰነዶች መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መንገድ ይተረጎማል።

8. <u>ተጨማሪ መረጃ ስለማሰባሰብ</u>

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በሕገመንግስት ትርጉም ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት እንደአስፈላጊነቱ ተጨማሪ አስተያየት ሊያሰባስብ ወይም ማስረጃ እንዲቀርብ ሊያዝ ይችላል፡፡

9. <u>ሕገ መንግስታዊነትን ስለሚያስረዳ አካል</u>

1. ምክር ቤቱ የአንድን ሕግ ሕገመንግስታዊነት ሲያጣራ ግምቱን የሚያፈርስ ሌላ ሁኔታ እስካልተፈጠረ ድረስ የወጣው ሕግ ሕገመንግስታዊ ነው ከሚል ግምት ይነሳል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የአንድ ሕግ ሕገመንግስታዊነት አከራካሪ ሆኖ ሲገኝ የማስረዳት ግዴታ የሚጣለው እንደነገሩ ሁኔታ የፌዴራል ወይም የክልል መንግስቱን በሕግ ጉዳዮች ላይ የማማከር ሥልጣንና ተግባር በተሰጠው የመንግስት አካል ይሆናል።

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት አከራካሪ ሆኖ የተገኘው ሕግ ሕገመንግሥታዊነቱን እንዲያስረዳ አግባብነት ያለው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥታዊ አካል ምክር ቤቱ በሚወስነው ቀን ቀርቦ እንዲያስረዳ ሊታዘዝ ይችላል፡፡

4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ከተገለጸው በተጨማሪ በጉዳዩ ላይ ውሣኔ ከመሰጠቱ በፊት እንዳስፈላጊነቱ ጉዳዩን ከያዘው ፍርድ ቤት ማብራሪያ መጠየቅ ወይም ባለጉዳዩን ወይም ሌላውን ተከራካሪ ወገን ማነጋገር ይችላል፡፡

10. <u>አስተያየት ስለማሰባሰብ</u>

ምክርቤቱ በሕገመንግሥት ትርጉም የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸውን ተቋማት፣ ባለሙያዎች ወይም ባለጉዳዮች ቀርበው አስተያየት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

11. <u>የሕገመንግሥት ነክ ጉዳዮች ውሣኔ ውጤት</u>

1. በሕገመንግሥት ትርጉም ላይ ምክር ቤቱ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ አጠቃላይ ውጤት ይኖረዋል። በመሆኑም ወደፊት በሚነሱ ተመሳሳይ ሕገመንግሥታዊ ጉዳዮች ላይ የአስገዳጅነት ባህርይ ይኖረዋል።
2. ውሣኔው በሁሉም ዘንድ እንዲታወቅም ምክር ቤቱ ለዚህ ዓላማ በሚያዘጋጀው ልዩ መጽሔት ታትሞ ይወጣል።

12. <u>ሕገመንግሥታዊ አይደለም ስለተባለ ሕግ</u>

የአንድ ሕግ አካል ድንጋጌ ሕገመንግሥታዊ አይደለም የሚል ውሳኔ የተሰጠበት እንደሆነ፣ አስፈላጊ ሆኖ ካልተገኘ በቀር ውጤቱ ተወስኖ የሚቀረው በዚያው ድንጋጌ ላይ ብቻ ይሆናል፡፡

13. <u>ጉዳይን በአጭር ጊዜ ውስጥ ስለመወሰን</u>

1. ምክር ቤቱ የቀረበለትን ጉዳይ መርምሮ በአፋጣኝ ውሣኔ መስጠት ይኖርበታል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ የተመለከተው ቢኖርም ምክር ቤቱ ከሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የውሣኔ ሃሣብ ሲቀርብለት በሰላሳ ቀናት ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

14. <u>ስለውሣኔ አሰጣጥ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 46/3/ የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ምክር ቤቱ በሕገመንግሥት ትርጉም ላይ በተባበረ ድምጽ ውሣኔ ሊሰጥ ይችላል፣
2. አንድ ጉዳይ በተባበረ ድምጽ የተወሰነ የሚባለው በስብሰባው ከተገኙት የምክር ቤቱ አባላት ውስጥ ምንም ተቃውሞ ያልቀረበበት እንደሆነ ነው፣
3. በህገ መንግስቱ ትርጉም ላይ ምክር ቤቱ የሚሰጠው የመጨረሻ ውሣኔ ጥያቄውን ለአቀረበውና ጉዳዩ ለሚመለከታቸው አካላት እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

15. <u>የውሣኔው ይዘት</u>

የምክር ቤቱ ውሣኔ የጉዳዩን ዝርዝር መግለጫ፣ የሕገመንግሥት ትርጉም ያስፈልጋል ወይም አያስፈልግም ያለበትን ምክንያትና የደረሰበትን መደምደሚያ በግልጽ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል።

16. <u>በሕገመንግስት ነክ ጉዳይ ላይ የሚሰጥ ውሣኔ ተፈጻሚ መሆን ስለሚጀምርበት ጊዜ</u>

1. በሕገመንግስት ትርጉም ላይ ምክር ቤቱ በሚሰጠው ውሣኔ በግልጽ ካልተመለከተ በስተቀር ተፈጻሚ የሚሆነው ውሣኔው ከተሰጠበት ጊዜ ጀምሮ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ቢኖርም፤ አንድ ሕግ ሕገመንግስታዊ አይደለም ብሎ የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት ሕጉን ላወጣው የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት አካል በስድስት ወር ጊዜ ውስጥ ሕጉን እንዲያሻሽል እንዲለውጥ ወይም እንዲሰርዝ ሊገልጽለት ይችላል፡፡

17.<u>ስለ ክፍያ</u>

1. ለምክር ቤት የሚቀርብ የሕገመንግሥት ትርጉም ጥያቄ ከክፍያ ነፃ ነው፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው ቢኖርም እንደአስፈላጊነቱ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሠረት አቤቱታ አቅራቢው ክፍያ እንዲፈጽም ሊያደርግ ይችላል፡፡

18.<u>የውሣኔ አሰጣጥ ሂደት</u>

1. ምክር ቤቱ ከሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የሚቀርቡለትን የውሣኔ ሃሣቦችና በሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ውሣኔ ቅር በመሰኘት በይግባኝ የሚመጡ ጉዳዮችን እየመረመረ የውሣኔ ሃሣብ የሚያቀርብ ከአባላቱ የተውጣጣ ኮሚቴ ሊያቋቁም ይችላል፡፡
2. ኮሚቴው በሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ውሣኔ ቅር በመሰኘት በይግባኝ የቀረበ ጉዳይ ለምክር ቤቱ አጠቃላይ ስብሰባ መቅረብ ይገባዋል ወይም አይገባውም በማለት እንዲወስን ውክልና ሊሰጠው ይችላል፡፡ ዝርዝሩ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል።

<u>ክፍል ሶስት</u>

19.<u>የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን በተመለከተ የሚነሱ ጥያቄዎችን ስለማስተናገድ</u>

1. የፌዴሬሽን ምክር ቤት የብሔር፣ ብሔረሰቦች ወይም ሕዝቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብትን በተመለከተ በሚቀርቡ ጥያቄዎች ላይ ውሣኔ የመስጠት ሥልጣን ይኖረዋል። ማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ማንነቱ አልታወቀልኝም፣ የራስ በራስ ማስተዳደር መብቱ ተሸራርፏል፤ ቋንቋዬ፣ ባህሌንና ታሪኬን የማሳድግበት ሁኔታ አልተመቻቸልኝም፣ በአጠቃላይ በፌዴራል ሕገ-መንግሥት የተደነገገው መብቴ አልተከበረም ወይም

በማንኛውም ሌላ ምክንያት አድልዎ ተፈጽሞብኛል የሚል እምነት ካደረበት ተዋረዱን ጠብቆ ጥያቄውን ለምክር ቤቱ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. የመገንጠል ጥያቄን በተመለከተ፣ ምክር ቤቱ የመገንጠል ጥያቄው በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 39/1/4/ መሠረት በብሔር ብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ምክር ቤት ሕግ አውጭ አካል ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ድጋፍ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥ እና ጥያቄው በጽሑፍ ሲቀርብለት፤

   ሀ/ የብሔር ብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ ምክር ቤት ሕግ አውጪ ውሣኔ በደረሰው በ3 ዓመት ጊዜ ውስጥ ለጠየቀው ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሣኔ ያደራጃል፣

   ለ/ የመገንጠሉ ጥያቄ በሕዝበ ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ መደገፉን አረጋግጦ ለብሔር ብሔረሰቡ ምክር ቤት ሥልጣን ያስረክባል፣

   ሐ/ በሕግ በሚወሰነው መሠረት የንብረት ክፍፍል ያደርጋል፡፡

3. ክልል የማቋቋም ጥያቄ ሲሆን፤

   1) የማንኛውም ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ክልል የመመስረት ጥያቄ፤

      ሀ/ የክልል መመስረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም በሕዝብ ምክር ቤት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ተቀባይነት ማግኘቱ ሲረጋገጥና ጥያቄው በጽሑፍ ለክልሉ ምክር ቤት ሲቀርብ፣

      ለ/ ጥያቄው የቀረበለት የክልል ምክር ቤት ጥያቄው በደረሰው በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ለተጠየቀው ብሔር፣ ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሕዝበ ውሣኔ ሲያደራጅ፣

      ሐ/ ክልል የመመስረት ጥያቄው በብሔሩ፣ በብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ፣ ሕዝበ ውሣኔ በአብላጫ ድምጽ ሲደገፍ፣

      መ/ የክልሉ ምክር ቤት ሥልጣኑን ለጠየቀው ብሔር ብሔረሰብ ወይም ሕዝብ ሲያስረክብ፣

      ሠ/ በሕዝበ ውሣኔ የሚፈጠረው አዲስ ክልል ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልገው በቀጥታ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አባል ሲሆን በስራ ላይ ይውላል፡፡

   2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3(1) ለ፣ በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ክልል የመመስረት ጥያቄ አልተፈጸመልኝም ወይም በተሰጠው ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ጥያቄውን ለምክር ቤቱ ማቅረብ ይችላል።

3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የተመለከተው ጥያቄ ለምክር ቤቱ የሚቀርበው በጽሁፍ ሆኖ የክልል ምሥረታ ጥያቄ ባቀረበው የብሔረሰብ ምክር ቤት ይሆናል፡፡

4) ምክር ቤቱ በዚህ መልኩ በቀረቡለት ጉዳዮች ላይ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

20.<u>የክልል መፍትሄን አሟጦ የመጨረስ ግዴታ</u>

1. በአንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ጥያቄ ወደ ምክር ቤቱ የሚቀርበው በክልሉ በሚገኙ የተለያዩ የመስተዳድር እርከኖች ቀርቦ አጥጋቢ መፍትሔ ያልተሰጠው መሆኑ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።
2. ክልሎች በአንቀጽ 19 ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት ማናቸውም ጥያቄ ሲቀርብላቸው በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ይወስናሉ፡፡ ዝርዝሩ ክልሎች በሚያወጡት ህግ ይወሰናል፡፡
3. የቀረበው ጥያቄ በክልሉ በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ካልተሰጠው ወይም በተሰጠው ውሣኔ ቅሬታ አለኝ የሚል ወገን ጉዳዩ ምክር ቤቱ በቀጥታ ሊቀርብ ይችላል።

21.<u>ጥያቄው ስለሚቀርብበት ስርዓት</u>

1. የራስን እድል በራስ የመወሰን መብትን አስመልክቶ የሚነሳ ጥያቄ የሚቀርበው በጽሁፍ መሆን ይኖርበታል፡፡ የሚቀርበው ጽሁፍ የጥያቄውን ይዘት በዝርዝር የሚያሳይና ጥያቄው የነዋሪው ሕዝብ ወይም የብሔር ብሔረሰቡ መሆኑን ለማመልከት እንደአስፈላጊነቱ ከነዋሪው መካከል ቢያንስ አምስት ከመቶ ወይም ከብሔር ብሔረሰቡ አባላት ቢያንስ አምስት ከመቶ የስም ዝርዝር ፊርማና አድራሻ የያዘ ወይም እንዳስፈላጊነቱ ጥያቄ ባቀረበው የመስተዳድር አካል ባለሥልጣን የተፈረመና ማህተም ያረፈበት መሆን ይገባዋል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለምክር ቤት የሚቀርብ ጥያቄ ለማቅረብ የሚመጣ ግለሰብ ወይም ግለሰቦች ከጠያቂው ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ የተወከሉ ለመሆናቸው በቂ ማረጋገጫ ማቅረብ አለበት ወይም አለባቸው። ዝርዝሩ በምክር ቤቱ ደንብ ይወሰናል፡፡

22.<u>ውሣኔ የሚሰጥበት የጊዜ ገደብ</u>

ምክር ቤቱ የቀረበለትን ጥያቄ ጥያቄው ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

## ክፍል አራት

## አለመግባባቶችን ስለመፍታት

**23.ጠቅላላ**

የፌዴሬሽን ምክር ቤት በክልሎች መካከል ወይም በፌዴራል መንግስትና በክልል መካከል የሚፈጠርን አለመግባባት ለመፍታት ይጥራል።

**24.ለውይይት ዝግጁ የመሆን ግዴታ**

1. ከፌዴራል መንግሥት ወይም ከሌላ ክልል ጋር የሚያወዛግብ ነጥብ አለኝ ብሎ የሚያምን ወገን ከሌላው ጋር በዚሁ ጉዳይ ለመወያየት ያለውን ፍላጐት የሚገልጽ የጽሑፍ ጥሪ ሊያቀርብ ይገባል፡፡
2. ጥሪው የደረሰው አካል በቅን ልቦናና በተቻለ ፍጥነት ቢረዝም በአርባ አምስት ቀናት ውስጥ ለውይይት ዝግጁ መሆን ይኖርበታል።
3. ሁለቱም ወገኖች ጉዳዩን በመቀራረብ ለመፍታት ፍቃዳቸውን የገለጹ ሲሆን ምክር ቤቱ ውይይቱ ፍሬያማ እንዲሆን አስፈላጊውን እገዛ ሁሉ ያደርጋል፡፡ ሂደቱንም በቅርብ ይከታተላል።

**25.ጥያቄውን ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ስለማቅረብ**

1. በአንዱ ወገን በቀረበው ጥያቄ ሌላኛው ወገን ለመወያየት ፈቃደኛ አለመሆኑ ከተረጋገጠ ወይም የተጀመረው ውይይት መልካም ውጤት ካላስገኘ ጉዳዩ በአንዱ ወይም በሁለቱም ወገኖች አመልካችነት በምክር ቤቱ ሊታይ ይችላል፡፡
2. ምክር ቤቱ ጥያቄው እንደቀረበለት እንደነገሩ ሁኔታ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመመካከር ለጊዜው የሚበጅ የመፍትሄ እርምጃ ሊወስድ ወይም እንዲወሰድ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**26.የምክር ቤቱ እርምጃዎች ቅደም ተከተል**

ምክር ቤቱ የመጨረሻ ውሣኔ ከመስጠቱ በፊት እንዳስፈላጊነቱ ባለጉዳዮቹ ውይይት የሚቀጥሉበትን ሁኔታ ያመቻቻል ወይም የአለመግባባት መንስኤ የሆኑትን ጭብጦች በመለየት በሚሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አስተያየታቸውን በጽሑፍ እንዲያቀርቡ ያደርጋል፡፡ ባለጉዳዮች አሉን የሚሏቸውን ማስረጃዎች ጭምር እንዲያቀርቡያደርጋል፡፡

**27.የድንበር ውዝግብን ስለመፍታት**

የቀረበው ጥያቄ የድንበር ውዝግብን የሚመለከት ከሆነ ምክር ቤቱ የሕዝቡን አሰፋፈርና ፍላጐት መሠረት በማድረግ ይወስናል።

**28.የሕዝብ አሰፋፈርና ፍላጐት**

1. ምክር ቤቱ የሕዝቡን አሰፋፈር በማጥናት አካባቢው ወደየትኛው ክልል መካለል እንዳለበት ለመወሰን የሚያስችል በቂ መረጃ እንዳለው ካመነ በዚያው መሠረት ይወስናል፡፡
2. ምክር ቤቱ የሕዝቡን አሰፋፈር በማጥናት አከራካሪው አካባቢ ወዴት መካለል እንዳለበት ለመወሰን የማይቻል መሆኑን ካመነ የሕዝቡን ፍላጐት መጠየቅ ይኖርበታል።

29.<u>የሕዝብን ፍላጎት ስለማረጋገጥ</u>

1. የሕዝብ ፍላጎት በምስጢር ድምጽ አሰጣጥ በሚከናወን ሕዝበ ውሳኔ ይረጋገጣል፣
2. የሕዝብን ፍላጐት ለማረጋገጥ የሚከናወን ሕዝበ ውሣኔ የምርጫ ሕግን መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል ይካሄዳል፣
3. በድርድር ውዝግብ የሕዝብን ፍላጐት ለማረጋገጥ የሚጠራ ሕዝበ ውሣኔ በቀበሌ ደረጃ ይከናወናል፡፡ የቀበሌው ስፋት ወይም ወሰን በተከራካሪ ወገኖች ስምምነት ካልተደረሰበት በምክር ቤቱ ይወሰናል፡፡
4. ምክር ቤቱ ሕዝበ ውሣኔውን ለማስፈጸም ብሔራዊ የምርጫ ቦርድን ሊወክል ይችላል፣
5. የሕዝበ ውሣኔውን ውጤት መሠረት በማድረግ አወዛጋቢ የሆነው አካባቢ ከድምጽ ሰጪው ሕዝብ አብዛኛው ድምጽ ወደሰጠበት ክልል እንዲካለል ይደረጋል፣ ሆኖም የሕዝበ ውሣኔው ውጤት አንዳንድ አካባቢዎችን በኪስ መሬትነት የሚያስቀር ከሆነ አወዛጋቢ የሆነው አካባቢ ሕዝቦች ሁኔታው እየታየ ባሉበት ክልል መብታቸው የሚከበርበት ሁኔታ ይመቻችላቸዋል፡፡

30.<u>ድምጽ የመስጠት መብት</u>

1. አግባብ ያላቸው የምርጫ ህግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም አምስት ዓመትና ከዚያ በላይ አወዛጋቢ በሆነው ቦታ በነዋሪነት የተመዘገበና እድሜው ከ18 ዓመት በላይ የሆነ ኢትዮጵያዊ ድምጽ የመስጠት መብት ይኖረዋል። ዝርዝር አፈፃጸሙ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይወሰናል፡፡
2. ሆኖም አካባቢውን ለመልቀቅ የተገደደው በድንበር ውዝግቡ ምክንያት በተከሰተ የሕዝብ መፈናቀል መሆኑ ከተረጋገጠ ከአካባቢው የለቀቀ ቢሆንም ድምጽ የመስጠት መብቱ አይታገድም።

**31.የጊዜ ገደብ**

ምክር ቤቱ የቀረበለትን የድንበር ጥያቄ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሣኔ ይሰጣል፡፡

**32.ሌሎች አለመግባባቶች**

1. ምክር ቤቱ ከድንበር ውዝግብ ውጭ አለመግባባቶች ሲከሰቱ በጉዳዩ ያልተግባቡ ወገኖች ችግራቸውን በሰላምና በውይይት እንዲፈቱት ይጠይቃል፤ ሊያግባባቸውም ይጥራል፤
2. አለመግባባቱን በውይይት ሊፈቱ ካልቻሉ ምክር ቤቱ እንዳስፈላጊነቱ ተገቢ መስሎ የታየውን ሥርዓት በመዘርጋት ለአለመግባባቱ መፍትሔ ይፈልጋል፤
3. የሕገመንግሥቱ የሥልጣን ክፍፍል መርህ እንደተጠበቀ ሆኖ በፌዴራል መንግሥቱና በክልሎች መካከል ለሚነሱ አለመግባባቶች ምክር ቤቱ መፍትሔ ይሰጣል፡፡

**33.የግጭት መከላከል እና ማስወገጃ ስልት ስለመዘርጋት**

ምክር ቤቱ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለማስወገድ የሚረዱ ባህላዊም ሆነ ዘመናዊ የግጭት መከላከያና ማስወገጃ ስልቶችን በማጥናት የአሰራር ሥርዓትና ስልት ይዘረጋል። ተቋማዊ ይዘትና አደረጃጀት እንዲኖራቸውም ያደርጋል፡፡

## ክፍል አምስት

## ተጨማሪ ኃላፊነቶች

**34.የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ስለመለየት**

1. ምክር ቤቱ አንድ የኢኮኖሚ ማኅበረሰብ ለመፍጠር አስፈላጊ ናቸው ብሎ ያመነባቸውን የፍትሐብሔር ጉዳዮች ሕግ እንዲወጣላቸው ለፌዴራሉ ሕግ አውጪ ያስተላልፋል።
2. ምክር ቤቱ አንድ የኢኮኖሚ ማሕበረሰብ ለመፍጠር አስፈላጊ ናቸው ተብለው የሚታመንባቸውን የፍትሐብሔር ጉዳዮች የሚለያቸው በራሱ አነሳሽነት ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው መንግሥታዊ አካላት በሚቀርብለት አስተያየት መሠረት ሊሆን ይችላል፡፡
3. ምክር ቤቱ በጉዳዩ ካመነበት የሕግ ረቂቅ አዘጋጅቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

**35.የድጐማ ቀመር ዝግጅትና የጋራ ገቢዎች ክፍፍል**

1. ምክር ቤቱ የፌዴራል መንግሥት ክልሎችን የሚደጉምበትን አሠራር በተመለከተ አግባብነት ካለው የአስፈጻሚ አካል የሚያገኘውን መረጃ መሠረት

በማድረግ ተጨባጭነትና ተቀባይነት ያለው በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ የድጎማ ቀመር ያዘጋጃል።

2. አግባብነት ያላቸው የመንግሥት አካላት ምክር ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) የተመለከተውን ተግባር ለማከናወን የሚያስችሉትን የተሟሉ መረጃዎች በአግባቡና በወቅቱ የማቅረብ ግዴታ አለባቸው።
3. ከጋራ የገቢ ምንጮች የሚሰበሰቡ ገቢዎችን በፌዴራሉ መንግሥትና በተጋሪው ክልል መካከል የሚከፋፈሉበትን ሥርዓት በየወቅቱና እንደሁኔታው ቀመሮች ያዘጋጃል።
4. ድጎማውና የጋራ ገቢ ክፍፍሉ በቀመሩ መሠረት መፈጸሙን ይከታተላል።
5. በክልሎች መካከል የተመጣጠነ እድገት ለማምጣት እና ክልሎች በተቻለ መጠን ከድጎማ ሥርዓት እንዲላቀቁ ለማስቻል ድጎማው እና የገቢ ክፍፍሉ ያስከተለውን ውጤት ለመመርመር እና ለመገምገም ምክር ቤቱ ተከታታይ ጥናቶችን ያከናውናል። በጥናቱ ውጤት መሠረት አስፈላጊውን የማስተካከያ እርምጃ ይወስዳል ወይም እንደነገሩ ሁኔታ ተገቢው እርምጃ እንዲወሰድ ያደርጋል።

36.<u>የፌዴራሉ መንግሥት ጣልቃ እንዲገባ ስለማዘዝ</u>

1. ምክር ቤቱ በአንድ ክልል ውስጥ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱ አደጋ ላይ ወድቋል ብሎ ሲያምን የፌዴራሉ መንግሥት ተገቢና ተመጣጣኝ እርምጃ እንዲወስድ ለማዘዝ ይችላል፡፡
2. ምክር ቤቱ ይህንን እርምጃ የሚወስደው አጠቃላይ ሕገመንግሥታዊ አወቃቀርና የሥልጣን ክፍፍል ግምት ውስጥ በማስገባት ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ግን ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱ አደጋ ላይ ወደቀ ለማሰኘት በቂ ናቸው፣

   ሀ/ በሕገመንግሥቱ እውቅና የተሰጣቸው መንግሥታዊ ተቋሞች ሥራቸውን እንዳያከናውኑ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የተገደቡ እንደሆነ፣ ወይም

   ለ/ ማንኛውም ክልል በፌዴራሉ ሕገመንግሥት አንቀጽ 55(16) መሠረት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የተሰጠውን መመሪያ ተግባራዊ ማድረግ ካቃተው ወይም ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ፣ ወይም

   ሐ/ ከክልል አቅም በላይ የሆነ የፀጥታ መደፍረስ ሲያጋጥምና ክልሉ በተለመደው የሕግ ማስከበር ሥርዓት ማቆም ካልቻለና የፌዴራል መንግሥቱም ጣልቃ እንዲገባለት ካልጠየቀ፣

3. የፌዴራል መንግሥቱ ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱ ተረጋግቷል ብሎ ሲያምን በክልሉ ውስጥ የነበረውን ጣልቃ ገብነት ለማብቃት ያለው መብት እንደተጠበቀ ሆኖ ምክር ቤቱ በጥናቱ መሠረት ሕገመንግሥታዊ ሥርዓቱ ከአደጋ ወጥቷል ብሎ ሲያምን ፌዴራል መንግሥቱ ጣልቃ ገብነቱ እንዲያበቃ ሊያዘው ይችላል፡፡

## 37.በሕዝቦች መካከል እኩልነትና አንድነት ሥር እንዲሰድ ስለመጣር

1. ምክር ቤቱ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመመካከር የሕዝቡን ዴሞክራሲያዊ ባሕል እና ንቃተ ሕገመንግሥት ለማዳበር የሚያስችሉ የተለያዩ ዝግጅቶች በየወቅቱና በየአካባቢው ያከናውናል።
2. በየደረጃው ያሉት የትምህርት ተቋሞች በሕዝቦች መካከል እኩልነትና አንድነትን የሚያጠናክሩ የትምህርት ዓይነቶች በሥርዓተ ትምህርታቸው ማካተታቸውን ምክር ቤቱ ይከታተላል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ለተመለከተው ዓላማ የመንግሥት መገናኛ ብዙኃንም በቂ ሽፋንና አምድ መመደባቸውን ይከታተላል፡፡
4. ለሕዝቦች እኩልነትና አንድነት መጠናከር እንቅፋት ሊሆኑ የሚችሉ አመለካከቶችና አዝማሚያዎች በማጥናትና በመለየት የመፍትሄ አቅጣጫ ቀይሶ የሚመለከታቸው ሁሉ እንዲያስፈጽሟቸው ያደርጋል፡፡
5. ምክር ቤቱ በክልሎች መካከል ያለው ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንኙነት እንዲጠናከርና በሕዝቦች መካከል እኩልነትና አንድነት ሥር እንዲሰድና እንዲዳብር፤

   ሀ/ ክልሎች በየዓመቱ የሚመደብላቸውን በጀት በተገቢው መንገድ በጥቅም ላይ ለማዋል የሚያስችላቸውን አቅም እንዲያገኙ ያደርጋል፣

   ለ/ ማሕበራዊ ኢኮኖሚያዊ ልማትን ለማፋጠንና በክልሎች መካከል የተመጣጠነ እድገት ለማምጣት የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፣

   ሐ/ የፌዴራሉ የልማት አውታሮች ስርጭት ለኢንቨስትመንት ትርጉም ያላቸውና ፍትሐዊ መሆናቸውን ይከታተላሉ፣

   መ/ በፌዴራሉ ሕገመንግሥት የሰፈሩትን የመንግሥት አወቃቀርና የሥልጣን ክፍፍል መሠረት በማድረግ ክልሎች የሚረዱበትንና በጋራ ለጋራ ጥቅም የሚሰሩበትን መድረኮች እና ሁኔታዎች ያመቻቻል፤ እየተጠናከሩ እንዲሄዱም ድጋፍ ይሰጣል፣

   ሠ/ በብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝቦች መካከል የመቻቻልና ለጋራ ዓላማ

የመሥራት ባሕል እንዲዳብር እንዲሁም አንድነታቸው እንዲጠናከር የሚያስችሉ እርምጃዎችን ይወስዳል፣

ረ/ በእድገት ወደኋላ የቀሩ ብሔር ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች በሰው ሃይል ሥልጠናና በሌሎች መስኮች ልዩ ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣ አፈጻጸሙንም ይከታተላል።

38.<u>የምርጫ ክልሎችን ስለመወሰን</u>

1. ምክር ቤቱ የሕገመንግሥቱን አንቀጽ 103/5/ መሠረት በማድረግ ብሔራዊ የምርጫ ቦርድ የምርጫ አከላለልን አስመልክቶ የሚያቀርብለትን የውሣኔ ሃሣብ መርምሮ ያጸድቃል፡፡
2. ምክር ቤቱ የውሣኔ ሃሣቡን ከማጽደቁ በፊት የውሣኔ ሃሣቡ የሕዝቦችን ሚዛናዊና ተመጣጣኝ ውክልና የማግኘት መብት የሚያስጠብቅ መሆኑን መመርመር ይኖርበታል።

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>የፌዴሬሽን ምክር ቤት አወቃቀር</u>

39.<u>የምክር ቤቱ አደረጃጀት</u>

ምክር ቤቱ አፈጉባዔ፣ ምክትል አፈጉባዔ፣ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች እንዲሁም ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል።

40.[17]

41.<u>ሕጋዊ ሰውነት</u>

ምክር ቤቱ የራሱ ሕጋዊ ሰውነት ይኖረዋል፡፡

42.<u>የምክር ቤቱ አፈጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>

አፈጉባዔው፤

1. የምክር ቤቱን ስብሰባዎች ይመራል፣
2. የምክር ቤቱን ጠቅላላ የአስተዳደር ሥራዎችን ይመራል፣
3. ምክር ቤቱ በአባላቱ ላይ የሚወስደውን የዲሲፕሊን እርምጃ ያስፈጽማል፡፡
4. ምክር ቤቱ የሚያስተላልፋቸው ውሣኔዎች ተግባራዊ መሆናቸውን ይከታተላል፣
5. የምክር ቤቱን የሥራ እቅድና በጀት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ሥራ ላይ ያውላል፣
6. ሌሎች በሕግ የሚሰጡትን ተግባራት ያከናውናል።

43.<u>የምክር ቤቱ ምክትል አፈጉባዔ ሥልጣንና ተግባር</u>

---
[17] በ14/3(2000) አ.556/2000 አንቀጽ 11(2) ተሻረ፡፡

የምክር ቤቱ ምክትል አፈጉባዔ፤

1. በምክር ቤቱ አፈጉባዔ የሚመራለትን ሥራ ያከናውናል፣
2. የምክር ቤቱ አፈጉባዔ በማይኖርበት ጊዜ አፈጉባዔውን ተክቶ ይሠራል።

44.[18]

45.<u>ስለሠራተኞች ቅጥር</u>

ጽሕፈት ቤቱ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግ መሠረታዊ መርሆዎችን ተከትሎ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፡፡

46.<u>የምክር ቤቱ ስብሰባና ሥነሥርዓት</u>

1. ምክር ቤቱ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ ይሰበሰባል፣
2. ምክር ቤቱ ምልዓተ ጉባዔ የሚኖረው ከአባላቱ መካከል ሁለት ሶስተኛው የተገኙ እንደሆነ ነው፣
3. ምክር ቤቱ ውሣኔ የሚያሳልፈው በአብላጫ ድምፅ ይሆናል፡፡

47.<u>የምክር ቤቱ አባላት አመራረጥ</u>

1. እያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ በፌዴሬሽን ምክር ቤት ቢያንስ አንድ ተወካይ ይኖረዋል። በተጨማሪም የብሔር ወይም ብሔረሰቡ አንድ ሚሊዮን ሕዝብ አንድ ተጨማሪ ወኪል ይኖረዋል።
2. የተወካዮች ብዛት የሚወሰነው የብሔር ብሔረሰቡ ወይም ሕዝቡ በሃገር ደረጃ በሚኖረው ብዛት መሠረት ነው፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)እና(2) የተመለከቱት መሠረት በማድረግ ምክር ቤቱ ክልሎች መላክ የሚገባቸውን የእያንዳንዱ ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ ተወካዮች ብዛት ወስኖ የፌዴራል ምክር ቤቶች የመጀመሪያው የጋራ ስብሰባ ከመጀመሩ ከስድስት ወር በፊት ለያንዳንዱ ክልል ያሳውቃል።
4. የክልል ምክር ቤቶች ፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚልክላቸው የተወካዮች ብዛት መሠረት በምክር ቤቶቹ በራሣቸው ወይም በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጡ በማድረግ የፌዴራል ምክር ቤቶች የጋራ ስብሰባ ከመጀመሩ ከአንድ ወር በፊት ለፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት የወኪሎቹን ዝርዝር ይልካሉ፡፡
5. ክልሎች የምክር ቤት አባላትን በቀጥታ በሕዝብ ለማስመረጥ ከወሰኑ ምርጫውን አግባብ ባላቸው የምርጫ ሕጎች መሠረት ያከናውናሉ፡፡

[18] በ14/3(2000) አ.556/2000 አንቀጽ 11(2) ተሻረ፡፡

6. በምክር ቤቱ የሚወከለው ሕዝብ የራሱ የዞን ወይም የወረዳ መስተዳድር ያለው እንደሆነ ተወካዩ የሚመረጥበት አግባብ ምክር ቤቶቹን ያሳተፈ መሆን ስላለበት ሥርዓቱ በክልል ምክር ቤቶች ሊመቻች ይገባል፡፡

48.<u>የምክር ቤቱ አባላት መብት</u>

1. ማንኛውም የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል በማናቸውም የምክር ቤቱ ስብሰባ ላይ በሚሰጠው አስተያየት ወይም ድምጽ ምክንያት አይከሰስም፣ አስተዳደራዊ እርምጃ አይወሰድበትም።
2. ማንኛውም የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባል ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ በስተቀር ያለ ምክር ቤቱ ፈቃድ አይያዝም፣ በወንጀልም አይከሰስም፡፡

49.<u>የዲሲፕሊን እርምጃ ስለመውሰድ</u>

አንድ የምክር ቤት አባል የወከለውን ብሔር ብሔረሰብ ሕዝብ በብቃት ሊወክል አልቻለም የሚያሰኝ የዲሲፕሊን ጉድለት ከፈጸመ ምክር ቤቱ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የዲሲፕሊን እርምጃ ሊወሰድበት ይችላል፡፡

50.<u>ከምክር ቤት አባልነት ስለመነሣት</u>

ማንኛውም የፌዴሬሽኑ ምክር ቤት አባል ከፈቃዱ ውጪ ከአባልነት ሊነሣ የሚችለው ከዚህ ቀጥሎ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ብቻ ነው፣

ሀ/ በክልል ምክር ቤት የተመረጠ አባል ሲሆን የመረጠው ምክር ቤት እንዲነሣ የወሰነ እንደሆነ፣

ለ/ በቀጥታ በሕዝብ የተመረጠ አባል ሲሆን ከመራጩ ሕዝብ አሥራ አምስት በመቶ (15%) በላይ ሕዝብ የምርጫ ቦርድ በሚያወጣው ደንብ መሠረት የይነሣልን ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ፣

ሐ/ የምክር ቤቱ አባል በሚያሳየው የሥነ ምግባር ጉድለት ምክንያት የወከለውን ብሔር፣ ብሔረሰብ ሕዝብ በብቃት ሊወክል አልቻለም በማለት በሁለት ሶስተኛ ድምጽ ሲወስን።

51.<u>ምትክ አባልን ስለመላክ</u>

1. አንድ የምክር ቤት አባል በሞት ወይም በአንቀጽ 50 በተመለከቱት ምክንያቶች ወይም በራሱ ፈቃድ ከአባልነት የተነሣ እንደሆነ ምክር ቤቱ ጉዳዩን ለሚመለከተው ክልል ያሳውቃል፣
2. የክልል ምክር ቤቱም ውሣኔው በደረሰው በአጭር ጊዜ ውስጥ ምትክ ተወካዩን በራሱ በመምረጥ ወይም በቀጥታ በሕዝብ እንዲመረጥ በማድረግ ይልካል።

## ክፍል ሰባት

## ስለኮሚቴዎች

### 52.ኮሚቴዎችን ስለማቋቋም

1. ምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባሩን በብቃት ለመወጣት የምክር ቤቱ አባላት የሚገኙባቸው ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎችን ያቋቁማል፣ የሥራ ሃላፊነታቸውንም ይወስናል፣
2. እያንዳንዱ ኮሚቴ ሰብሳቢ፣ ምክትል ሰብሳቢና ፀሐፊ ይኖረዋል፣
3. ምክር ቤቱ ከእያንዳንዱ ቋሚ ኮሚቴ ውስጥ ሶስት አባላት በምክር ቤቱ በቋሚነት እንዲሠሩ ማድረግ ይችላል፣
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ምክር ቤቱ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው ከእያንዳንዱ ኮሚቴ በቋሚነት የሚሰሩ አባላት ቁጥር እንዲጨምር ማድረግ ይችላል፡፡

### 53.ስለኮሚቴ አመራሮች

1. **የኮሚቴ ሰብሳቢ፣**

ሀ/ የኮሚቴውን ስብሰባ የመጥራትና የመምራት፣

ለ/ ለኮሚቴው የሚቀርቡትን ጉዳዮች በሥርዓት አቀናብሮ ለኮሚቴው አባላት እንዲደርሱ የማድረግ፣

ሐ/ ምልአተ ጉባዔ መኖሩን የማረጋገጥ፣

መ/ የኮሚቴ ውሣኔዎች ወደሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፉ የማድረግ፣

ሠ/ የኮሚቴውን የሥራ ክንውን ሪፖርት በየወቅቱ ለአፈጉባዔ የማቅረብ ሃላፊነት ይኖረዋል።

### 54.የኮሚቴ ምክትል ሰብሳቢ

ሀ/ የኮሚቴ ሰብሳቢ ሳይኖር ሰብሳቢውን ተክቶ የመስራት፣

ለ/ በኮሚቴው ሰብሳቢ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት የመፈጸም ኃላፊነት ይኖረዋል።

### 55.የኮሚቴው ፀሐፊ

የኮሚቴው ፀሐፊ የኮሚቴውን ቃለ ጉባዔዎች ይይዛል፤ ሰነዶች በቅደም ተከተል ተመዝግበው መቀመጣቸውን የማረጋገጥና ሌሎች በኮሚቴው ወይም በሰብሳቢው የሚሰጡትን ተግባራት የማከናወን ኃላፊነት ይኖረዋል።

### 56.ምልዓተ ጉባዔ

1. ከኮሚቴው አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባኤ ይኖራል።

2. ምክር ቤቱ ሌላ ደንብ ካላወጣ በቀር የኮሚቴ ውሣኔ የሚተላለፈው በአብላጫ ድምጽ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስምንት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 57.ስለ በጀት

1. የምክር ቤቱ በጀት፣

   ሀ/ ከመንግሥት ከሚመደብ በጀት፣

   ለ/ ከስጦታና እርዳታ፣

   ሐ/ ከማንኛውም ሌላ ሕጋዊ ምንጭ

   የተውጣጣ ይሆናል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ገቢ በምክር ቤቱ የባንክ ሂሣብ ተቀምጦ የምክር ቤቱን ሥራ ለማከናወን ብቻ ይውላል፡፡

3. ምክር ቤቱ የበጀት አጠቃቀሙን የሚያሣይ ትክክለኛ የሂሣብ ሰነድ መያዝ ይኖርበታል።

4. የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና የገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራል።

### 58.የውሣኔው የመጨረሻነት ባሕርይና የአስገዳጅነት ኃይል

1. ምክር ቤቱ በቀረበለት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።
2. ጉዳዩ የሚመለከታቸው ወገኖች ውሣኔውን የማክበርና የመፈጸም ግዴታ ይኖርባቸዋል።

### 59.የሕግ ረቂቅ የማቅረብ ሥልጣን

ምክር ቤቱ በሥልጣኑ ክልል በሆኑ ጉዳዮች ላይ የሕግ ረቂቅ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ ሥልጣን ይኖረዋል።

### 60.ደንብ የማውጣት ሥልጣን

ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባራት ለማከናወን ተገቢ ሆኖ ሲያገኘው ደንብ ለማውጣት ይችላል፡፡

### 61.የተሻሩ ሕጎች

1. አዋጅ ቁጥር 13/1988 በዚህ አዋጅ በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።
2. ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ሕጎች፤ ደንቦች፤ መመሪያዎችና ውሣኔዎች በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም።

62.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ 29 ቀን 1993 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 29 ቀን 1993 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

# አዋጅ ቁጥር 556/2000

## የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ

የፌዴሬሽን ምክር ቤት የፌዴራሉ መንግሥት አባል ክልሎች፣ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መርጠው በሚልኳቸው አባላት የተመሠረተ በመሆኑ፣

ምክር ቤቱ በሕገመንግሥቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በአግባቡ እንዲያከናውንና ኃላፊነቱን እንዲወጣ እንዲሁም አፈ-ጉባኤው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 66/2/ የምክር ቤቱን የአስተዳደር ሥራዎች አቀናጅቶ ለመምራት እንዲችል የምክር ቤቱን ጽሕፈት ቤት ማቋቋም በማስፈለጉ፣

የሚቋቋመው ጽሕፈት ቤት ምክር ቤቱንና የሕገ መንግሥት አጣሪ ጉባዔውን በጋራ እንዲያገለግል አድርጐ ማቋቋምና ሁለቱም አካላት ኃላፊነታቸውን በብቃት እንዲወጡ የሚያስችል የራሱ አደረጃጀት፣ አሠራርና በቂ የሰው ኃይል ሊኖረው የሚገባ መሆኑን በማመን፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 /1/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 556/2000" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር

   1. "ምክር ቤት" ማለት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 53 መሠረት የተቋቋመው የፌዴራሉ መንግሥት የፌዴሬሽን ምክር ቤት ነው፡፡
   2. "አፈ-ጉባዔ" እና "ምክትል አፈ-ጉባዔ" ማለት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 62 /11/ መሠረት በፌዴሬሽን ምክር ቤት የሚመረጡ አፈ-ጉባዔና ምክትል አፈ-ጉባዔ ናቸው፡፡
   3. "አጣሪ ጉባዔ" ማለት በሕገመንግሥቱ አንቀጽ 82 መሠረት የተቋቋመ የፌዴራሉ መንግሥት የሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ማለት ነው።
   4. "ኮሚቴዎች" ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 62 /10/ መሠረት በምክር ቤቱ የሚቋቋሙ ቋሚና ጊዜያዊ ኮሚቴዎች ናቸው፡፡

5. "አስተባባሪ ኮሚቴ" ማለት አፈ-ጉባዔው፣ ምክትል አፈ-ጉባዔው፣ የቋሚ ኮሚቴዎች ሰብሳቢዎች፣ ምክትል ሰብሳቢዎችና የንዑስ ቋሚ ኮሚቴዎች ተወካዮች ያሉበት በምክር ቤቱ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፡፡

3. <u>መቋቋም</u>

1. የፌዴሬሽን ምክር ቤት ጽሕፈት ቤት /ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤቱ" ተብሎ የሚጠራ/ ራሱን የቻለ ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነቱ ለአፈ-ጉባዔው ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>ስለምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት</u>

4. <u>የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ጽሕፈት ቤቱ አፈ-ጉባዔው በሚሰጠው አመራር መሠረት፦

1. ለምክር ቤቱና ምክር ቤቱ ለሚያቋቁማቸው ኮሚቴዎች፣ ለአፈ-ጉባዔዎች፣ ለምክር ቤቱና ለአጣሪ ጉባኤ አባላት አጠቃላይ አስተዳደራዊ፣ የጽሕፈት፣ የመስተንግዶና የመረጃ አገልግሎት ይሰጣል፣
2. በአፈ-ጉባዔው ወይም በምክትል አፈ-ጉባዔው ወይም በአጣሪ ጉባኤው ሰብሳቢ ውሳኔመሠረት በወቅቱ ለአባላት የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣ አጀንዳዎችንና ተፈላጊ ሰነዶችንም ያሰራጫል፤
3. የምክር ቤቱና የአፈ-ጉባዔዎች እንግዶች አስፈላጊውን የመስተንግዶ አገልግሎት እንዲያገኙ ያደርጋል፤
4. የምክር ቤቱ፣ የአጣሪ ጉባኤውና የጽሕፈት ቤቱ፦
   ሀ/ ቃለ-ጉባኤዎች፣ ውሳኔዎች፣ አቋሞች፣ ሰነዶችና መዛግብቶች፣ እና
   ለ/ አስፈላጊ የሆኑ መጽሐፍት ጥራዞች ጥናታዊ ጽሑፎችና መረጃዎች
   በአግባቡ ተሰብስበው ተመዝግበውና ተደራጅተው አገልግሎት እንዲሰጡና እንዲጠበቁ ያደርጋል።
5. የምክር ቤቱን የአጣሪ ጉባኤውና የጽሕፈት ቤቱን አቋም አሰራርና ተልእኮ የሚመለከቱ ጉዳዮችን የያዙ መጽሔቶች ጋዜጦችና በራሪ ጽሑፎች አዘጋጅቶ እንዲታተሙና እንዲሰራጩ ያደርጋል፤
6. በምክር ቤቱና በአጣሪ ጉባኤው ሥልጣንና ተግባር አሠራር አደረጃጀትና አግባብነት ባላቸው ሕጎች ዙሪያ ጥናትና ምርምር እንዲያደርግ ሲታዘዝ ጥናት ያካሂዳል። ውጤቱንም ከሙያዊ አስተያየት ጋር ያቀርባል፣

7. የክልሎችና የፌዴራል መንግሥት የጋራ ተብለው የተመደቡና የተሰበሰቡ ገቢዎች በሁለቱ መካከል የሚከፋፈሉበትን እንዲሁም የፌዴራሉ መንግሥት ለክልሎች ድጎማ የሚሰጥበትን በየጊዜው እየተሻሻለ የሚሄድ ቀመር የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት አዘጋጅቶ ለኮሚቴው ያቀርባል፤

8. የሕገመንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ ሕገ መንግሥቱን በመተርጎም በሚሰጠው የውሳኔ ሀሳብ ላይ ምክር ቤቱ ተጨማሪ የባለሙያ አስተያየት ሲጠይቅ ወይም የሕገመንግሥት ትርጉም አያስፈልግም በማለት በሰጠው ውሳኔ ላይ ይግባኝ ሲቀርብ ቋሚ ኮሚቴው በሚያዘው መሠረት ጥናት አድርጎ ሙያዊ አስተያየት ያቀርባል፤

9. ሕዝቡ ስለ ሕገመንግሥቱና ስለምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት እንዲያውቅ ከሚመለከተው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ጋር በመሆን በተለያዩ መንገዶችና ዘዴዎች የግንዛቤ ማስጨበጥ ሥራ እንዲሰራ ያደርጋል፣

10. አንድ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመፍጠር የሚያግዙና ሕግ ሊወጣላቸው የሚገቡ የፍትሐብሔር ጉዳዮችን ቋሚ ኮሚቴው በሚሰጠው አቅጣጫ መሠረት ያጠናል፣ ይለያል፣ ለኮሚቴ ያቀርባል፣

11. በሚሰጠው መመሪያ መሠረት የኢትዮጵያን ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የማንነት ጥናት ያካሂዳል። የጥናቱንም ውጤት ለሚመለከተው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ ያቀርባል፣

12. በክልሎችና በሕዝቦች መካከል ያሉ አለመግባባቶች እንዲጠኑ ሲታዘዝ የዳሰሳ፣ የትንተናና የመከላከያ ስትራቴጂ በማጥናት የጥናቱን ውጤት ለኮሚቴው ያቀርባል፤

13. የምክር ቤቱ የአገር ውስጥና የውጭ ግንኙነት የተሳካና የተቃና እንዲሆን አስፈላጊውን እገዛ ያደርጋል፣

14. በክልሎች መካከል በተከሰተ አለመግባባት፣ በብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የመብት ጥያቄ መነሻነት ለምክር ቤቱ የቀረቡ አቤቱታዎች ሲመሩለት እና በሚሰጠው መመሪያ መሠረት መርምሮና አጣርቶ ለሚመለከተው የምክር ቤቱ ቋሚ ኮሚቴ አስተያየት ያቀርባል፣

15. ምክር ቤቱ ያሳለፋቸውን ውሳኔዎች አፈፃፀምና ያስገኙት ውጤት በተመለከተ በአፈ-ጉባዔው ሲታዘዝ ክትትልና ግምገማ በማድረግ ሙያዊ አስተያየት ያቀርባል፤

16.የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፣

17.በምክር ቤቱና በአፈ-ጉባዔው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

5. <u>**የጽሕፈት ቤቱ አቋም**</u>

የጽሕፈት ቤቱ:-

1. የምክር ቤት አባል ያልሆነና ባለሙያ በአፈጉባኤው አቅራቢነት በምክር ቤቱ አስተባባሪ ኮሚቴ የሚሾም፣
2. ብዛታቸው እንደሥራው አስፈላጊነት የሚወሰንና በአፈ-ጉባዔው የሚመደቡ የመምሪያ ኃላፊዎች፤
3. አስፈላጊው ሠራተኞች፤
4. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ የተጠቀሱት የጽሕፈት ቤቱ የመምሪያ ኃላፊዎች በፌዴራል መንግሥት ሠራተኞች አዋጅ አይካተቱም።

6. <u>**የጽሕፈት ቤቱ የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ ድርጅታዊ መዋቅርና የደመወዝ ስኬል**</u>

1. የጽሕፈት ቤቱ የሠራተኞች አስተዳደር ደንብ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል ተዘጋጅቶ በምክር ቤቱ ሲፀድቅ ሥራ ላይ ይውላል፡፡
2. የጽሕፈት ቤቱ ድርጅታዊ መዋቅርና የደመወዝ ስኬል የመንግሥትን የኢኮኖሚ አቅም ባገናዘበ መልኩ ተዘጋጅቶ ለምክር ቤቱ አስተባባሪ ኮሚቴ ቀርቦ ከታየ በኋላ ይፀድቃል፡፡
3. ጽሕፈት ቤቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /2/ መሠረት መዋቅሩና የደመወዝ ስኬሉ ሲፀድቅና ሲፈቀድ ሥራ ላይ ያውላል።

7. <u>**የጽሕፈት ቤት ኃላፊው ሥልጣንና ተግባር**</u>

1. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ከአፈ-ጉባኤው በሚሰጠው አመራርና የጽሕፈት ቤቱን የአስተዳደር ደንብ በመከተል የጽሕፈት ቤቱን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ፡-

   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 የተመለከቱትን የጽሕፈት ቤቱን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፣

   ለ/ የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ለማጠናከርና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር በወጣው አዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 45 እንደተመለከተው የፌዴራል

ሲቪል ሰርቪስ ሕግ አጠቃላይ መርሆዎችን መሠረት በማድረግና በጽሕፈት ቤቱ የአስተዳደር ደንብ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች ይቀጥራል፡ ያስተዳድራል፣

ሐ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 /2/ የተመለከተውን የጽሕፈት ቤቱን ድርጅታዊ መዋቅርና የደመወዝ ስኬል ለአስተባባሪ ኮሚቴ ያቀርባል። በአስተባባሪ ኮሚቴው ታይቶ ሲፀድቅና ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

መ/ የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራም አዘጋጅቶ ለአፈ-ጉባኤው ያቀርባል ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

ሠ/ ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደለት በጀትና ባዘጋጀው የሥራ ፕሮግራም መሠረት የፋይናንስ ሕግን ተከትሎ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፣

ረ/ ጽሕፈት ቤቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ጽሕፈት ቤቱን ይወክላል፣

ሰ/ የጽሕፈት ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴ አፈፃፀምና የሂሣብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለአፈ-ጉባኤ ያቀርባል፣

ሸ/ ከአፈ-ጉባኤውና ከምክትል አፈ-ጉባኤው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

3. ኃላፊው ለጽሕፈት ቤቱ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣኑና ተግባሩ በከፊል ለጽሕፈት ቤቱ የበታች ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል። ሆኖም እርሱ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ እንዲሰራ የሚወክለው ኃላፊ ከሰላሳ ቀናት በላይ የሚሠራ ከሆነ ውክልናው በቅድሚያ ለአፈ-ጉባዔው ቀርቦ መጽደቅ ይኖርበታል።

8. <u>በጀት</u>

ጽሕፈት ቤቱ ለምክር ቤቱ የተመደበውን አመታዊ በጀት ያስተዳድራል በአግባቡም ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል።

9. <u>የሂሣብ መዛግብት</u>

1. ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሂሣብ መዛግብት ይኖሩታል።
2. የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ። ሆኖም አፈ-ጉባዔው በማናቸውም አስፈላጊ ጊዜና ሰዓት የሂሣብ መዛግብት ሰነዶች በከፊልም ሆነ በሙሉ በዋናው ኦዲተር እንዲመረመሩ ሊያዝ ይችላል፡፡

## ክፍል ሦስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

10. መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

አስተባባሪ ኮሚቴው ይህንን አዋጅና ምክር ቤቱ የሚያወጣውን ደንብ ለማስፈፀም የተለያዩ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

11. የተሻሩና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች

1. ይህን አዋጅ የሚቃረኑ ማናቸውም ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎችና የአሠራር ልምዶች በዚህ አዋጅ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም።
2. የአዋጅ ቁጥር 250/1993 አንቀጽ 5፣ 14፣ 15፣ እና 16 እንዲሁም የአዋጅ ቁጥር 251/1993 አንቀጽ 40 እና 44 ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል።

12. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ታህሣሥ 22 ቀን 2000 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ**

**ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 798/2005

## የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕገ መንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔን ለማጠናከርና ሥልጣንና ተግባሩን ለመዘርዘር በድጋሚ የወጣ አዋጅ

የአገሪቱ የህጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በተሟላ መንገድ ስራ ላይ ማዋል በአገሪቷ ለተጀመረው ዲሞክራሲያዊ ስርዓት፣ ልማትና ሰላም ቀጣይነት አስተማማኝ ዋስትና እንደሚሆን የታመነበት በመሆኑ፤

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥትን ለመተርጎም ሥልጣን ለተሰጠው ለፌደሬሽን ምክር ቤት ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን እያጣራ እንዲያቀርብ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 82 መሰረት የተቋቋመ በመሆኑ፣

አጣሪ ጉባዔው በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84 መሰረት ሕገ መንግሥታዊ ጉዳዮችን የማጣራት ሥልጣን የተሰጠው በመሆኑና ለሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳዮች የተቀላጠፈና ውጤታማ ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የተሻለ አሰራር እና አደረጃጀት እንዲኖረው በማስፈለጉ፤

አጣሪ ጉባዔው ሕገ መንግስታዊ ነጻነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ተግባራቱን በብቃት እንዲወጣ የራሱ ድጋፍ ሰጪ ፅህፈት ቤት እንዲኖረው በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አዋጅ ቁጥር 798/2005" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "ሕገ መንግሥት" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ነው፤

2. “የፌደሬሽን ምክር ቤት” ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 53 መሰረት የተቋቋመው የፌደሬሽን ምክር ቤት ነው፤

3. “የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት” ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 53 መሰረት የተቋቋመው የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፤

4. “አጣሪ ጉባዔ” ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 82 (1) መሠረት የተቋቋመው የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ነው፤

5. “ክልል” ማለት በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 47 (1) የተጠቀሱት የክልል መንግስታት ሲሆኑ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች የአስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

6. “የመንግሥት አካል” ማለት የፌደራሉም ሆነ የክልል ሕግ አውጪ፣ ሕግ አስፈጻሚና ሕግ ተርጓሚ አካል ነው፤

7. “ንዑስ አጣሪ ኮሚቴ” ማለት ከአጣሪ ጉባዔ አባላት መካከል ከሶስት የማያንሱ አባላትን ያካተተ ኮሚቴ ነው፤

8. “ፅህፈት ቤት” ማለት የአጣሪ ጉባዔው ፅህፈት ቤት ነው፤

9. “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

10. “የመጨረሻ ውሳኔ” ማለት ታይቶ ያለቀና ይግባኝ የሌለው ውሳኔ ነው፡፡

11. ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ያካትታል፡፡

## ክፍል ሁለት

## ሕገ መንግሥትን ስለመተርጎም

3. መሠረቱ

1. አጣሪ ጉባዔው ማንኛውም ሕግ፣ ልማዳዊ አሰራር ወይም የመንግስት አካል ውሳኔ ወይም የባለስልጣን ውሳኔ ከሕገ መንግሥቱ ጋር ይቃረናል የሚል ጥያቄ በጽሑፍ ሲቀርብለት ያጣራል፡፡ በሚያደርገው ማጣራት መሠረት ሕገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለፌደሬሽን ምክር ቤት በጉዳዩ ላይ የውሳኔ ሃሳብ ያቀርባል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳይ ለአጣሪ ጉባዔ ሊቀርብ የሚችለው፡-

   ሀ/ በፍርድ ቤት ሊወሰን የሚችል ከሆነ ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ቀርቦ ሲታይ፤

ለ/ በአስተዳደር አካል ሊወሰን የሚችል ከሆነ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን በየደረጃው ስልጣን ላለው አስፈጻሚ አካል ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ ሲያገኝ፤

ሐ/ በፍርድ ሊወሰን የማይችል በማንኛውም ጉዳይ ላይ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አንድ ሦስተኛ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ በፌደራል ወይም በክልል ምክር ቤት አባላት ወይም በፌደራሉም ሆነ በክልል አስፈጻሚ አካላት ለአጣሪ ጉባዔ ሊቀርብ ይችላል፡፡

4. <u>በፍርድ ቤት በተያዙ ጉዳዮች የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ሊያቀርቡ ስለሚችሉ ሰዎች</u>

1. በፍርድ ቤት በተያዙ ጉዳዮች የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የተነሳ እንደሆነ ጥያቄው ጉዳዩን በያዘው ፍርድ ቤት ወይም በባለጉዳዩ ለአጣሪ ጉባዔው ሊቀርብ ይችላል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለጉዳዩ ጥያቄውን ለአጣሪ ጉባዔ ከማቅረቡ በፊት ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄውን ለአጣሪ ጉባዔው እንዲልክለት ማቅረብ ይኖርበታል።
3. ጉዳዩን የያዘው ፍርድ ቤት የትርጉም ጥያቄ ለአጣሪ ጉባዔው የሚልከው ጉዳዩን ለመወሰን ሕገ መንግሥቱን መተርጎም ያስፈልጋል ብሎ ሲያምን ነው፡፡
4. ፍርድ ቤቱ ለአጣሪ ጉባዔው የሚልከው የሕገ መንግሥት ትርጉም ለመስጠት አስፈላጊ የሆነውን ነጥብ ነው።
5. ጥያቄው የቀረበለት ፍርድ ቤት ጥያቄውን ያልተቀበለ እንደሆነ ባለጉዳዩ ውሳኔውን እንዳወቀ በ 90 ቀናት ውስጥ ለአጣሪ ጉባዔው ማቅረብ ይኖርበታል።
6. ባለጉዳዩ ለአጣሪ ጉባዔው የሚያቀርበው ጥያቄ የሕገ መንግሥት ትርጉም ለመስጠት አስፈላጊ የሆነውን ነጥብ ነው።

5. <u>ከፍርድ ቤት ውጪ ስለሚቀርብ የሕገመንግሥት ትርጉም ጥያቄ</u>

1. በማንኛውም የመንግሥት አካል ወይም ባለሥልጣን በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ በሕገ መንግሥቱ የተደነገገው መሠረታዊ መብቴና ነፃነቴ ተጥሷል የሚል ሰው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ለአጣሪ ጉባዔው ሊያቀርብ ይችላል።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ለአጣሪ ጉባዔው የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ የሚቀርበው የመብት መጣስ አቤቱታ ጉዳዩን አይቶ ለመወሰን በየደረጃው ስልጣን ላለው የመንግሥት አካል ቀርቦ የመጨረሻ ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ ነው።
3. በፌደራሉ መንግስትም ሆነ በክልል ሕግ አውጪ አካላት የሚወጡ ሕጎች ከሕገ መንግሥቱ ጋር ይቃረናሉ የሚል ጥያቄ ሲነሳ ጉዳዩ የሚመለከተው ፍርድ ቤት ወይም ባለጉዳይ ለአጣሪ ጉባዔው ሊያቀርብ ይችላል፡፡

6. <u>ጉዳይን ባለበት ደረጃ ስለማቆየት</u>

አጣሪ ጉባዔው ከፍርድ ቤት የተላከለትን ወይም ከባለጉዳዩ የቀረበለትን የትርጉም ጥያቄ መርምሮ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ በፍርድ ቤት ክርክር ላይ ያለ ጉዳይ በእንጥልጥል እንዲቆይ ሊያዝ ይችላል፡፡

7. <u>የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቀራረብ</u>

1. ለአጣሪ ጉባዔው የሚቀርብ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ አቀራረብ በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ የአቤቱታ አቀራረብ መመሪያ መሰረት ይሆናል፡፡
2. የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ በውክልና ሊቀርብ ይችላል።

8. <u>ጉዳዮችን ስለመምራት</u>

የአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢ በቀረቡ ጉዳዮች ላይ የሙያ አስተያየት እንዲዘጋጅ ለንዑስ አጣሪ ኮሚቴ አባላት ወይም ለፅህፈት ቤቱ ባለሙያዎች በቅድሚያ ይመራል።

9. <u>የሙያ አስተያየት ስለማሰባሰብ</u>

1. አጣሪ ጉባዔው በቀረበለት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ላይ ውሳኔ ከመስጠቱ ወይም ለፌደሬሽን ምክር ቤት የውሳኔ ሀሳብ ከማቅረቡ በፊት አግባብነት አላቸው ብሎ የሚያምንባቸው ተቋማት ወይም ባለሙያዎች ቀርበው አስተያየት እንዲሰጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡
2. አጣሪ ጉባዔው የሕገ መንግሥት ጉዳዮችን ለማጣራት አስፈላጊ ነው ብሎ ያመነበትን ማንኛውንም አይነት ማስረጃ አስቀርቦ ሊመረምር ወይም ባለሙያ ጠርቶ ሊጠይቅ ይችላል።
3. ማንኛውንም ማስረጃ እንዲሰጥ በአጣሪ ጉባዔው የተጠየቀ ሰው የተጠየቀውን ማስረጃ ወዲያውኑ የመስጠት ግዴታ አለበት።

10. <u>የጉዳይ አቀራረብና ውይይት ስለሚመራበት ሁኔታ</u>

1. ለአጣሪ ጉባዔው የቀረቡ ጉዳዮች የተለየ ሁኔታ በመኖሩ ቀድሞ እንዲታዩ በጉባዔው ሰብሳቢ ካልተወሰነ በቀር እንደ አቀራረባቸው ቅደም ተከተል ማጣራት ይደረግባቸዋል።
2. ውይይቱ የሚመራበትና ውሳኔ የሚሰጥበት ወይም የውሳኔ ሀሳብ የሚቀርብበት ሥነ ሥርዓት አጣሪ ጉባዔው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።
3. አንድ ጉዳይ በሚታይበት ጊዜ በበቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ለተደጋጋሚ ቀጠሮ መተላለፍ የለበትም፡፡
4. አጣሪ ጉባዔው የያዘውን ጉዳይ በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 12 (1) መሠረት ለሕዝብ ግልፅ በሆነ መንገድ ሊያይ ይችላል። ዝርዝር ሁኔታው አጣሪ ጉባዔው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

11.<u>ስለ አጣሪ ጉባዔው ስብሰባና የውሳኔ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት</u>

1. ከአጣሪ ጉባዔው አባላት ሁለት ሦስተኛው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል።
2. አጣሪ ጉባዔው በቀረበለት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ወይም የሚደርስበት የውሳኔ ሃሣብ በአብላጫ ድምፅ ይሆናል፡፡
3. የተሰጠው ድምፅ በሁለቱም ወገን እኩል በሚሆንበት ጊዜ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ወሳኝ ይሆናል።
4. አጣሪ ጉባዔው የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ወይም የሚያቀርባቸው የውሳኔ ሃሳቦች በስብሰባው ላይ የተገኙትን አባላት፣ የአቤቱታ አቅራቢዎች ወይም ወኪሎቻቸው እንዲሁም አስተያየት የሰጡ ሰዎች ሙሉ ስምና የጉዳዩን ዝርዝር፣ የተሰጡ አስተያየቶችን እና ሌሎች አጣሪ ጉባዔው በሚያወጣው መመሪያ የሚወሰኑ ጉዳዮችን መያዝ አለባቸው፡፡
5. በአጣሪ ጉባዔው የተሰጡ ውሳኔዎች ወይም የቀረቡ የውሳኔ ሃሳቦች በስብሰባው ላይ በተገኙ የአጣሪ ጉባዔው አባላት መፈረም ይኖርባቸዋል፡፡

12.<u>ውሳኔና የውሳኔ ሃሣብ</u>

1. አጣሪ ጉባዔው የቀረበለትን የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ከመረመረ በኋላ፡-

   ሀ/ ሕገ መንግሥቱን መተርጎም አስፈላጊ ሆኖ ካላገኘው የቀረበለትን ጥያቄ ውድቅ በማድረግ ውሳኔውን ለአቤቱታ አቅራቢው በጽሁፍ ያሳውቃል፤

   ለ/ ሕገ መንግስት መተርጎም ያስፈልጋል ብሎ ሲያምን የውሳኔ ሀሳቡንና

ከጉዳዩ ጋር የተያያዙ መረጃዎችና ሰነዶችን አያይዞ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ይልካል፡፡

2. የአጣሪ ጉባዔው ውሳኔ ወይም የውሳኔ ሃሣብ የቀረበውን ጉዳይ ዝርዝር መግለጫ፣ የሕገ መንግሥት ትርጉም ያስፈልጋል ወይም አያስፈልግም ያለበትን ምክንያትና የደረሰበትን መደምደሚያ በግልጽ የሚያሳይ መሆን ይኖርበታል።

3. አጣሪ ጉባዔው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1)(ሀ) መሠረት የሰጠውን ውሳኔ ለባለጉዳዩ ለማሳወቅ እንዲሁም በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1)(ለ) መሠረት የደረሰበትን የውሳኔ ሃሣብ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ለመላክ የሚያስፈልገው ጊዜ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

13.<u>ለባለ ጉዳይ ስለሚሰጥ የውሳኔ ግልባጭ</u>

አጣሪ ጉባዔው የሕገመንግስት ትርጉም አያስፈልግም በማለት በሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ባለጉዳይ የውሳኔው ግልባጭ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የፅህፈት ቤቱ ሃላፊ የተዘጋጀውን ውሳኔ ግልባጭ እንዲሰጠው ያደርጋል፡፡ የውሳኔ ግልባጩ ትክክለኛነት አግባብ ባለው የፅህፈት ቤቱ የስራ ሃላፊ መረጋገጥ ይኖርበታል።

14.<u>ስለ ክፍያ</u>

ለአጣሪ ጉባዔው የሚቀርብ የሕገ መንግሥት ትርጉም ጥያቄ ከክፍያ ነጻ ነው፡

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>የአጣሪ ጉባዔው አደረጃጀት</u>

<u>ምዕራፍ አንድ</u>

<u>ስለ አጣሪ ጉባዔው አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር</u>

15.<u>የአጣሪ ጉባዔው አደረጃጀት</u>

አጣሪ ጉባዔው የሚከተሉት አስራ አንድ አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት........................ ሰብሳቢ፤

ለ/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ............ ም/ሰብሳቢ፤

ሐ/ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅራቢነት በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚሾሙ በሙያ ብቃታቸውና በስነምግባራቸው የተመሰከረላቸው ስድስት የሕግ ባለሙያዎች ................................................................. አባላት፤

መ/ የፌደሬሽን ምክር ቤት ከአባላቱ መካከል የሚወክላቸው ሶስት ሰዎች.. አባላት፡፡

## 16.የአጣሪ ጉባዔው ስልጣንና ተግባር

አጣሪ ጉባዔው የሚከተሉት ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል:-

1. በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 84 (1) መሠረት ሕገመንግሥታዊ ጉዳዮችን በማጣራት ሕገመንግስቱን መተርጐም አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በጉዳዩ ላይ የሰጠውን የሕገመንግስት ትርጉም የውሳኔ ሃሳብ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፤ ጉዳዩ የሕገመንግስት ትርጉም የማያስፈልገው ሆኖ ባገኘው ጊዜ ሕገመንግስቱን መተርጐም አስፈላጊ አይደለም የሚል ውሳኔ ይሰጣል፤
2. የፅህፈት ቤቱ ሃላፊ የሚያቀርበውን የፅህፈት ቤቱን መዋቅር እና የአሰራር ስርዓት ያፀድቃል፣ ተግባራዊነቱን ይከታተላል፤
3. የአጣሪ ጉባዔውን በጀት አዘጋጅቶ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ያስፈፅማል፤
4. የፅህፈት ቤት ሃላፊውንና ሌሎች የስራ ሃላፊዎችን ይሰይማል፣ ያስተዳድራል፤
5. የአጣሪ ጉባዔውን እና የፅህፈት ቤቱን ዓመታዊ የስራ ክንውን እና የፋይናንስ እንቅስቃሴ ሪፖርቶችን ለፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፤
6. የሚመራበትን ስነስርዓት አዘጋጅቶ ለፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤
7. ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል ይከሰሳል፣ ንብረት በባለቤትነት ወይም በሌላ መንገድ ሊይዝ ይችላል፣
8. ከሕገ መንግሥት ትርጉም ጋር በተያያዘ በፌደሬሽን ምክር ቤት የሚሰጡትን ተጨማሪ ስራዎች ያከናውናል፡፡

## 17.የአጣሪ ጉባዔው አባላት የስራ ዘመን

1. የአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ የስራ ዘመን እንደቅደምተከተሉ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትነት እና ምክትል ፕሬዚዳንትነት የሚያገለግሉበት የስራ ዘመን ይሆናል፡፡
2. በፌደሬሽን ምክር ቤት የሚወክሉ የአጣሪ ጉባዔው አባላት የስራ ዘመን የፌደሬሽን ምክር ቤት የስራ ዘመን ይሆናል።
3. በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚሾሙ የአጣሪ ጉባዔው አባላት የስራ ዘመን ስድስት ዓመት ይሆናል።

4. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) እና (3) ድንጋጌዎች ቢኖሩም በፌደሬሽን ምክር ቤት የሚወከሉ አባላት እና በሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት የሚሾሙ የአጣሪ ጉባዔው አባላት በድጋሚ የአጣሪ ጉባዔው አባል ሆነው ሊመረጡ ይችላሉ።

18.<u>የአጣሪ ጉባዔው አባላት የአገልግሎት ክፍያ</u>

1. የአጣሪ ጉባዔው አባላት በጉባዔው ስብሰባ ላይ ለተገኙባቸው ቀናት እና በአባልነታቸው ለሚሰጡት ተጨማሪ አገልግሎት ተመጣጣኝ የውሎና የትራንስፖርት አበል ይከፈላቸዋል። ዝርዝሩ አጣሪ ጉባዔው በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ ቢኖርም በንዑስ አጣሪ ኮሚቴው ውስጥ እንዲሰሩ የተሰየሙ የአጣሪ ጉባዔው አባላት በጉባዔው ስብሰባ ላይ ለተገኙባቸው ቀናትና ከንዑስ አጣሪ ኮሚቴው ውጪ በአጣሪ ጉባዔ አባልነታቸው ለሚሰጡት አገልግሎት የውሎ እና የትራንስፖርት አበል ተከፋይ አይሆኑም፡፡

19.<u>የአጣሪ ጉባዔው አባላት ከሃላፊነት  ስለሚነሱበት</u>

1. የአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ እንደቅደም ተከተሉ ከፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንትነት እና ምክትል ፕሬዚዳንትነት ሹመት ካልተነሱ በስተቀር ከሃላፊነታቸው አይነሱም።
2. ከአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ በስተቀር ማንኛውም የአጣሪ ጉባዔው አባል የስራ ዘመኑ ከማለቁ በፊት በወከለው ወይም በሾመው አካል ከሃላፊነቱ ሊነሳ ይችላል፡፡
3. ከአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ በስተቀር ማንኛውም የአጣሪ ጉባዔው አባል በሚከተሉት ምክንያቶች ከሃላፊነቱ ሊነሳ ይችላል:-

   ሀ/ በፈቃዱ ከሃላፊነቱ ለመነሳት ለወከለው ወይም ለሾመው አካል ጥያቄ ሲያቀርብ፣

   ለ/ የዲሲፕሊን ጥፋት መፈጸሙ ወይም ጉልህ የሆነ የሥራ ችሎታና ቅልጥፍና ያነሰው መሆኑ በአጣሪ ጉባዔው እና በወከለው ወይም በሾመው አካል ሲረጋገጥ፡፡

20.<u>የአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>

1. የአጣሪ ጉባዔው ሰበሳቢ ጉባዔውን የመምራት፣ የአባላቱን ተግባራት የማቀናጀት፣ የጉባዔው ስራዎች ውጤታማና ቀልጣፋ እንዲሆኑ አስፈላጊውን እርምጃ  የመውሰድ ስልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡፡

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢ፡-

ሀ/ የአጣሪ ጉባዔውን ስብሰባ ይጠራል፤ በጉባዔው መመሪያ መሰረት ስብሰባውን ይመራል፤

ለ/ ለአጣሪ ጉባዔው በቀጥታ ወይም በንዑስ አጣሪ ኮሚቴ አማካኝነት የቀረቡለትን ጉዳዮች በአግባቡ ለአባላት መድረሳቸውን ያረጋግጣል፤

ሐ/ ከንዑስ አጣሪ ኮሚቴ የቀረበ ጉዳይ ከአጣሪ ጉባዔ አባላት መካከል እንደአስፈላጊነቱ በጉዳዩ ላይ አስተያየት እንዲቀርብ ወይም ረቂቅ የውሳኔ ሃሳብ እንዲዘጋጅ ሊያደርግ ይችላል፤

መ/ የአጣሪ ጉባዔውን መመሪያዎችና ሥነ ሥርዓት ያከብራል፤ ያስከብራል፤

ሠ/ የፅህፈት ቤቱን መዋቅር እና የደመወዝስኬል ለአጣሪ ጉባዔው በማቅረብ ያጸድቃል፤

ረ/ የአጣሪ ጉባዔውን አባላትና የፅህፈት ቤቱን ሠራተኞች ጥቅማ ጥቅም ለአጣሪ ጉባዔው በማቅረብ ያጸድቃል፤

ሰ/ የፅህፈት ቤቱን ሃላፊ ለአጣሪ ጉባዔው አቅርቦ እንዲመደብ ያደርጋል፤

ሸ/ ብዛታቸው እንደስራው አስፈላጊነት የሚወሰን የፅህፈት ቤቱ ዳይሬክተሮችን ይመድባል፤

ቀ/ የአጣሪ ጉባዔው አባላት መጓደል ሲያጋጥም በዚህ አዋጅ መሰረት ከጉባዔው ሃላፊነት በተነሳ አባል ምትክ ተተኪ አባል እንዲሾም ወይም እንዲወከል ለሚመለከተው አካል ጥያቄ ያቀርባል፤

በ/ ፅህፈት ቤቱን በበላይነት ይመራል፣ ይቆጣጠራል፤

ተ/ የአጣሪ ጉባዔውን ውሳኔዎች ለሚመለከታቸው አካላት እንዲተላለፉ ያደርጋል፤

ቸ/ የአጣሪ ጉባዔውን ዓመታዊ የስራ ክንውን ሪፖርት ለፌደሬሽን ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

21.<u>የአጣሪ ጉባዔው ምክትል ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>

1. የአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢ በማይኖርበት ጊዜ ምክትል ሰብሳቢው ተክቶ ሃላፊነቶቹን ያስፈጽማል፡፡
2. የአጣሪ ጉባዔው ምክትል ሰብሳቢ በሰብሳቢው ወይም በአጣሪ ጉባዔው ተለይተው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

3. የአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢና ምክትል ሰብሳቢ በማይኖሩበት ጊዜ ለጊዜው አጣሪ ጉባዔውን የሚመራ የጉባዔው አባል በፌደሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባዔ ይሰየማል፡፡

## 22.<u>የአጣሪ ጉባዔው አባላት ተግባርና ሃላፊነት</u>

ማንኛውም የአጣሪ ጉባዔው አባል፡-

1. በበቂ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር አጣሪ ጉባዔው በሚጠራው ማንኛውም ስብሰባ ላይ መገኘት ይኖርበታል፤
2. በበቂ ምክንያት ስብሰባ ላይ የማይገኝ ከሆነ ይህንኑ ለአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢ አስቀድሞ ማሳወቅ አለበት፤
3. በአጣሪ ጉባዔው ስብሰባ በአጀንዳነት በተያዘ ጉዳይ ላይ በተሟላ ዝግጅት መሳተፍ እንዲሁም ሃላፊነቱን ለመወጣት ተገቢውን ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፤
4. ሕገመንግስቱን በማክበርና በማስከበር በገለልተኛነት እና በነፃ ህሊና ሃላፊነቱን መወጣት አለበት፤
5. የአጣሪ ጉባዔውን መልካም ስምና ክብር የመጠበቅና የማስጠበቅ ሃላፊነት አለበት፤
6. የአጣሪ ጉባዔውን መመሪያና ስነ ስርዓት ማክበር ይኖርበታል።

## 23.<u>የአጣሪ ጉባዔው ስብሰባ</u>

1. አጣሪ ጉባዔው በየወሩ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
2. የአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢ እንደ አስፈላጊነቱ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) ከተጠቀሰው ባነሰ ጊዜ ውስጥ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡
3. የአጣሪ ጉባዔው ስብሰባ የሚደረገው በአዲስ አበባ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱም በተመረጠ ክልል ሊደረግ ይችላል፡፡

## 24.<u>የንዑስ አጣሪ ኮሚቴ መቋቋም</u>

1. ተጠሪነቱ ለአጣሪ ጉባዔው የሆነ (ከዚህ በኋላ "ንዑስ አጣሪ ኮሚቴ" ተብሎ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ንዑስ አጣሪ ኮሚቴው በአጣሪ ጉባዔው የሚሰየሙ በአጣሪ ጉባዔው ውስጥ በቋሚነት የሚሰሩ የንዑስ አጣሪ ኮሚቴውን ሰብሳቢ ጨምሮ ቢያንስ ሦስት አባላት ይኖሩታል፡፡

## 25.<u>የንዑስ አጣሪ ኮሚቴው ተግባርና ሃላፊነት</u>

ንዑስ አጣሪ ኮሚቴው የሚከተለው ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል፡-

1. አጣሪ ጉባዔው በሚሰጠው መመሪያ መሰረት የሕገ መንግሥት ትርጉም ጉዳዮችን ለውሳኔ አሰጣጥ በሚያመች መልክ ያደራጃል፤
2. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የሕገ መንግሥት ትርጉም የሚያስፈልጋቸውና የማያስፈልጋቸው ጉዳዮችን፣ ለውሳኔ የሚረዱ ጭብጦችን፣ አግባብነት ያላቸው ሕጎችን፣ ውሳኔዎችን እና አስፈላጊ በሆነ መጠን አግባብነት ያላቸው ተሞክሮዎችን በመለየት በጥናት ከተደገፈ ማብራሪያ ጋር ለአጣሪ ጉባዔው ያቀርባል፡፡

26. <u>የንዑስ አጣሪ ኮሚቴው አባላት የስራ ሁኔታና የአገልግሎት ክፍያ</u>

1. የንዑስ አጣሪ ኮሚቴው አባላት የስራ ሁኔታ በጋራ ቅጥር መርህ ላይ ተመስርቶ ተቀጣሪ ወይም ተጂሚ ከሆኑ አሰሪያቸውና አጣሪ ጉባዔው በሚያደርጉት ስምምነት መሰረት ይወሰናል ፡፡
2. በንዑስ አጣሪ ኮሚቴው ውስጥ በቋሚነት እንዲሰሩ የተሰየሙ የአጣሪ ጉባዔው አባላት ለሚሰጡት አገልግሎት ለተሰየሙበት የስራ መደብ የተወሰነው ደመወዝ እና ጥቅማጥቅም ይከፈላቸዋል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የፅህፈት ቤቱ አደረጃጀት፣ ስልጣንና ተግባር</u>

27. <u>የፅህፈት ቤቱ መቋቋም</u>

1. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ፅህፈት ቤት (ከዚህ በኋላ "ፅህፈት ቤቱ" ተብሎ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል ፡፡
2. ፅህፈት ቤቱ፡-
   ሀ/ በአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢ አቅራቢነት በአጣሪ ጉባዔው የሚሾም ሃላፊ፤
   ለ/ ብዛታቸው እንደስራው አስፈላጊነት የሚወሰን ዳይሬክተሮች፤ እና
   ሐ/ አስፈላጊው ሰራተኞች፤
   ይኖሩታል፡፡
3. የፅህፈት ቤቱ ዋና መስሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በክልል ከተሞች ቅርንጫፎች ይኖሩታል፡፡

28. <u>የፅህፈት ቤቱ ስልጣንና ተግባር</u>

ፅህፈት ቤቱ ከአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢ በሚሰጠው አመራር መሰረት፡-

1. ለአጣሪ ጉባዔው አባላት አጠቃላይ አስተዳደራዊ አገልግሎት ይሰጣል፤
2. ለአጣሪ ጉባዔው አባላት የምርምርና ጥናት አገልግሎት ይሰጣል፤

3. ለአጣሪ ጉባዔው አባላት የስብሰባ ጥሪ ያስተላልፋል፣ አጀንዳዎችንና ተፈላጊ ሰነዶችን ያሰራጫል፤

4. በአጣሪ ጉባዔው ስብሰባ ላይ የተጠሩ አባላት ወይም ባለጉዳዮች የአጣሪ ጉባዔውን የስራ ቋንቋ የማያውቁ በሆነ ጊዜ የትርጉም አገልግሎት እንዲሰጥ ያደርጋል፤

5. የአጣሪ ጉባዔውና የፅህፈት ቤቱ ቃለ ጉባዔ፣ ውሳኔዎችና ሌሎች ሰነዶች ተመዝግበውና ተደራጅተው እንዲጠበቁ ያደርጋል፤

6. አጣሪ ጉባዔው የሚያወጣቸውን መፅሔትና ሌሎች ፅሑፎች እንዲሁም ዓመታዊ ሪፖርቶችን አዘጋጅቶ እንዲታተሙና እንዲሰራጩ ያደርጋል፤

7. በሚመለከተው የስራ ክፍል አማካኝነት በየጊዜው ስለ አጣሪ ጉባዔው አሰራርና ውሳኔዎች መግለጫ ይሰጣል ወይም እንዲሰጥ ያደርጋል፤

8. ባለጉዳዮች ተገቢውን መስተንግዶ እንዲያገኙ ያደርጋል፤

9. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ህብረተሰቡ ስለህገመንግስቱ፣ ስለህገመንግስት ትርጉም እና ሌሎች ተዛማጅነት ስላላቸው ጉዳዮች እንዲያውቅ በተለያዩ መንገዶችና ዘዴዎች የግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ ይሰራል ወይም እንዲሰራ ያደርጋል፤

10. የሕገመንግስት ትርጉም አቤቱታ ለሚያዘጋጁ ባለሙያዎች ስለአቤቱታ አቀራረብ ስልጠና ይሰጣል፤

11. የአጣሪ ጉባዔውን የውስጥና የውጭ ግንኙነት ያደርጋል፣

12. ለአጣሪ ጉባዔው ስራ ስኬታማነት የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

## 29. <u>የፅህፈት ቤቱ ሃላፊ ስልጣንና ተግባር</u>

የፅህፈት ቤቱ ሃላፊ፡-

1. የፅህፈት ቤቱን ሥራ ያቅዳል፣ ይመራል፣ ያደራጃል፣ ይቆጣጠራል፤

2. አጣሪ ጉባዔው በአስተዳደራዊ ጉዳዮች የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ተፈጻሚ መሆናቸውን ይከታተላል፤

3. የአጣሪ ጉባዔውንና ፅህፈት ቤቱን በጀት ያዘጋጃል፣ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

4. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 28 የተመለከቱትን የፅህፈት ቤቱን ስልጣንና ተግባራት ስራ ላይ ያውላል፤

5. ፅህፈት ቤቱ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ፅህፈት ቤቱን ይወክላል፤

6. በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህጎች መሰረት የፅህፈት ቤቱን ሰራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤

7. የፅህፈት ቤቱን መዋቅር እና የደመወዝ ስኬል አጥንቶ ለአጣሪ ጉባዔው በማቅረብ ሲወሰን ተግባራዊ ያደርጋል፤

8. የፅህፈት ቤቱን ዓመታዊ የሥራ እቅድ አዘጋጅቶ ለአጣሪ ለጉባዔው ሰብሳቢ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

9. ለፅህፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ እቅድ መሰረት የፋይናንስ ሕግን ተከትሎ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

10. የፅህፈት ቤቱን የስራ እንቅስቃሴና የሒሳብ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለአጣሪ ጉባዔው ሰብሳቢ ያቀርባል፤

11. በአጣሪ ጉባዔውና በሰብሳቢው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

30. <u>የፅህፈት ቤቱ አስተዳደር</u>

1. የፅህፈት ቤቱ የሰራተኞች አስተዳደር ደንብ የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህግን መሰረታዊ መርሆዎች በመከተል ተዘጋጅቶ በአጣሪ ጉባዔው ሲፀድቅ ስራ ላይ ይውላል፡፡

2. የፅህፈት ቤቱ መዋቅርና የደመወዝ ስኬል የመንግስትን የኢኮኖሚ አቅም ባገናዘበ መልኩ ተዘጋጅቶ በአጣሪ ጉባዔው ሲፀድቅ ስራ ላይ ይውላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

31. <u>ስለ አጣሪ ጉባዔው በጀት</u>

1. የአጣሪ ጉባዔው በጀት በመንግሥት ይመደባል።

2. የአጣሪ ጉባዔው ዓመታዊ በጀት በፅህፈት ቤቱ አማካኝነት ተዘጋጅቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይቀርባል፣ ሲፀድቅም ስራ ላይ ይውላል፡፡

3. አጣሪ ጉባዔው የበጀት አጠቃቀሙን የሚያሳይ የሂሳብ ሰነድ በፅህፈት ቤቱ አማካኝነት ይይዛል።

4. የአጣሪ ጉባዔው የሂሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

32. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው አጣሪ ጉባዔው የሚሰጠውን ትዕዛዝ የመፈጸም ወይም የማስፈፀም ግዴታ አለበት፡፡

33. <u>መመሪያ የማውጣት ስልጣን</u>

አጣሪ ጉባዔው ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

34.<u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጐች</u>

1. የፌደራሉ የሕገመንግስት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ አዋጅ ቁጥር 250/1993 በዚህ አዋጅ ተሽሯል።
2. የአዋጅ ቁጥር 556/2000 አንቀፅ 4 ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) እንዲሁም በአንቀጽ 4 ከንዑስ አንቀፅ (4) እስከ (6) የተደነገጉት ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡
3. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም ልማዳዊ አሠራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

35.<u>በቀድሞ ሕጎች መሰረት ተገኝተው ስለነበሩ መብቶች</u>

ግልፅ የሆነ ተቃራኒ ድንጋጌ ከሌለ በስተቀር ይህ አዋጅ ከመጽናቱ በፊት የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎችን ለማስገኘት ይህ አዋጅ የሚጠይቃቸው መመዘኛዎች ከድሮው የተለዩ ቢሆኑም እንኳን በቀድሞው ሕግ መሰረት ተገኝተው የነበሩት ሕጋዊ ሁኔታዎች ጸንተው ይቀጥላሉ፡፡

36.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 24 ቀን 2005 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደ ጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዝደንት**

## ሐ/ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ተጠሪ የሆኑ ተቋማት

## አዋጅ ቁጥር 210/1992

## የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

ከኢትዮጵያ ብሔሮች፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች መሠረታዊ ዓላማዎች አንዱ የሆነውን በሕግ የበላይነት ላይ የተመሰረተ አንድ የፖለቲካ ማኅበረሰብ በጋራ የመገንባት ዓላማ ከግብ የሚደርሰው የግለሰብ፣ የብሔር/ብሔረሰብ እና የሕዝብ መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች መከበራቸው ሲረጋገጥ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መስፈን እንዲሁም ለኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ዕድገቱ መደራጀት ባካሔደው ረጅም ትግል በከፈለው መስዋዕትነት፤ ሰብአዊ መብቶች ለማናቸውም ዓይነት የተፅዕኖ መዳፍ ሳይጋለጡ በእውን የሚከበሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የሕዝቦች መብቶችና ነፃነቶች የተከበሩ መሆናቸው በመረጋገጡና በማንኛውም ደረጃ የሚገኙ የፌዴራልና የክልልመንግሥታት አካላትና ባለሥልጣኖቻቸው እነዚህን የማክበርና የማስከበር ኃላፊነትና ግዴታም እንዳለባቸው በመደንገጉ፤ መብቶቹንና ነፃነቶቹን በማስከበሩ ረገድ የላቀ ድርሻ ይኖራቸዋል ከሚባሉት አካላት አንዱ የሆነውን የሰብአዊ መብት ኮሚሽንን ማቋቋምና ሥልጣኑንና ተግባሩንም ከሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች ጋር በሚስማማ መልክ በሕግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 (1) እና (14) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 210/1992" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካላሰጠው በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፤

   1. "ተሿሚ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በም/ቤቱ የሚሾም የሰብአዊ መብት ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነር፣ የሕጻናትና የሴቶችን ጉዳይ የሚከታተል ኮሚሽነር፣ ወይም በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ የሚገኙ ኮሚሽነሮች ማለት ነው፤

2. “ሠራተኛ” ማለት ከተሿሚዎቹ ውጭ ያሉ የኮሚሽኑ መምሪያ ኃላፊዎችን፣ ባለሙያዎችንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን ያካትታል፤
3. “ቤተዘመድ” ማለት በኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ መሠረት የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ሰው ነው፤
4. "ምክርቤት" ማለት የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፣
5. “ሰብዓዊ መብት” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት እና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ ስምምነቶች ዕውቅና የተሰጣቸውን መሠረታዊ መብቶችንና ነፃነቶችን ያጠቃልላል፤
6. “ሰው” ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
7. “ክልል” ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) ላይ የመተለከቱት ማለት ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድርንና የድሬዳዋ አስተዳደርንም ይጨምራል፤
8. “መንግሥት” ማለት የፌዴራል ወይም የክልል መንግሥት ነው፤
9. “ሦስተኛ ወገን” ማለት አንድን ግለሰብ ወይም ቡድን የሚወክል የሕዝብ ተመራጭ ወይም ማህበር ወይም መንግሥታዊ ያልሆነ ድርጅት ማለት ነው፤
10.“መርማሪ” ማለት የምርመራ ስራ እንዲያካሂድ በዋና ኮሚሽነሩ የተመደበ ሠራተኛ ነው፡፡

3. <u>**መቋቋም**</u>

1. የኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ “ኮሚሽኑ” እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለም/ቤቱ ነው።

4. <u>**የተፈፃሚነቱ ወሰን**</u>

1. ይህ አዋጅ በማንኛውም ክልል ውስጥ በሚፈጸሙ የሰብአዊ መብቶች መጣስ ጉዳዮችም ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።
2. በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

5. <u>**ዓላማ**</u>

የኮሚሽኑ ዓላማ ሕዝቡ ስለሰብአዊ መብቶች ግንዛቤ እንዲኖረው ማስተማር፣ መብቶቹ እንዳይጣሱ መጠበቅ፣ መብቶቹ ሳይሸራረፉ ሥራ ላይ እንዲውሉ እና ተጥሰው ሲገኙ አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይሆናል፡፡

6. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ኮሚሽኑ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፤

1. በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት ውስጥ የተደነገጉት ሰብአዊ መብቶች በማንኛውም ዜጋ፣ በመንግሥት አካላት፣ በፖለቲካ ድርጅቶች፣ በሌሎች ማኅበራት እንዲሁም በባለሥልጣኖቻቸው መከበራቸውን ማረጋገጥ፤
2. በመንግሥት የሚወጡ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ እንዲሁም ትዕዛዞች በሕገ መንግሥቱ ከተረጋገጡ የዜጎች ሰብአዊ መብቶች ጋር የማይቃረኑ መሆናቸውን ማረጋገጥ፤
3. ኅብረተሰቡ ስለሰብአዊ መብት በቂ ዕውቀት ኖሮት መብቱን የማክበርና የማስከበር ባህል እንዲያዳብር መገናኛ ብዙኃንና የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ማስተማር፤
4. የሰብአዊ መብት መጣስ ቅሬታዎች ሲቀርቡለት ወይም በራሱ አነሳሽነት ምርመራ ማካሔድ፤
5. ነባር ሕጎች እንዲሻሻሉና አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ ማሰባሰብ፤
6. በሰብአዊ መብት ጉዳዮች ላይ የምክር አገልግሎት መስጠት፤
7. ለዓለም አቀፍ አካላት በሚቀርቡ የሰብአዊ መብት ሪፖርቶች ላይ አስተያየት መስጠት፣
8. ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሠነዶችን በሀገር ውስጥ ቋንቋዎች መተርጎምና ማሰራጨት፤
9. በዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስብሰባዎች፤ ኮንፈረንሶች ወይም ሲምፖዚየሞች ላይ መሳተፍ፤
10. የንብረት ባለቤት መሆን፤ ውል መዋዋል፤ በስሙ መክሰስና መከሰስ፤
11. ዓላማውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባሮችን ማከናወን፤

7. <u>የሥልጣን ገደብ</u>

ኮሚሽኑ በም/ቤቱ ወይም በፌዴሬሽን ም/ቤት ወይም በክልል ም/ቤቶች ወይም በማንኛውም ፍ/ቤት በየትኛውም ደረጃ በመታየት ላይ ካሉ ጉዳዮች በስተቀር የሰብአዊ መብት መጣስን አስመልክቶ በማንኛውም ሰው ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን ሁሉ ተቀብለው የመመርመር ሙሉ ሥልጣን ይኖረዋል።

8. <u>የኮሚሽኑ አቋም</u>

ኮሚሽኑ፤

1. የኮሚሽነሮች ጉባዔ፤
2. ሀ/ አንድ ዋና ኮሚሽነር፤

   ለ/ አንድ ምክትል ዋና ኮሚሽነር፤

   ሐ/ የሕፃናትና የሴቶች ጉዳዮችን የሚመራ ኮሚሽነር፤

   መ/ ሌሎች ኮሚሽነሮች፤ እና

   ሠ/ አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል።

9. **<u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>**

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ምክር ቤቱ በሚወስነው በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

10. **<u>አሿሿም</u>**

1. ዋና ኮሚሽነር፣ ምክትል ዋና ኮሚሽነርና ሌሎች ኮሚሽነሮች በም/ቤቱ ይሾማሉ።
2. የዋና ኮሚሽነር፣ የምክትል ኮሚሽነርና የኮሚሽነሮች አሿሿም የሚከተለውን የአመራረጥ ሥርዓት ይኖረዋል፤

   ሀ/ ተሿሚዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት በሚቋቋመው ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ ይመለመላሉ፤

   ለ/ ዕጩዎቹም በኮሚቴው ሁለት ሦስተኛ ድምጽ የተደገፉ መሆን አለባቸው፤

   ሐ/ ዕጩዎቹ በምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ለምክር ቤቱ ቀርበው ድምጽ የሚሰጥባቸው ይሆናል፤

   መ/ የቀረቡት ዕጩዎች በምክር ቤቱ ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሲደገፉ ይሾማሉ።

11. **<u>የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ ጥንቅር</u>**

የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

1. የምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ .................... ሰብሳቢ፤
2. የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ...... አባል፤
3. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጡ ሰባት አባላት.......አባል፤
4. በም/ቤቱ መቀመጫ ካላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በጋራ ስምምነት የሚመረጡ ሁለት የም/ቤቱ አባላት......................................አባል፤
5. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ......................................አባል፤
6. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተወካይ .....................አባል፤
7. የኢትዮጵያ እስልምና ጉዳዮች ጠቅላይ ጉባኤ ተወካይ..........................አባል፤

8. የኢትዮጵያ ወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ ተወካይ ................................ አባል፤

9. የኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተክርስቲያን ተወካይ ................................ አባል፤

12.<u>ለሹመት የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ሰው ሊሾም ይችላል፤

1. ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት ተገዥ የሆነ፣
2. ለሰብአዊ መብቶች መከበር ተቆርቋሪ የሆነ፤
3. በሕግ ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሙያ የሰለጠነ ወይም በልምድ ሰፊ ዕውቀት ያካበተ፤
4. በታታሪነቱ፤ በታማኝነቱ እና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፤
5. ከደንብ መተላለፍ ውጭ ባለ በሌላ የወንጀል ጥፋት ተከሶ ያልተፈረደበት፤
6. ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፤
7. ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ ጤንነት ያለው እና
8. ዕድሜው ከ35 ዓመት በላይ የሆነ።

13.<u>ተጠሪነት</u>

1. የዋና ኮሚሽነር ተጠሪነት ለምክር ቤቱ ይሆናል፡፡
2. ምክትል ዋና ኮሚሽነርና ሌሎች ኮሚሽነሮች ተጠሪነታቸው ለዋና ኮሚሽነሩ ይሆናል፡፡

14.<u>የሥራ ዘመን</u>

1. የማንኛውም ተሿሚ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው የሥራ ዘመን ካበቃ በኋላ ተሿሚው እንደገና ሊሾም ይችላል፡፡
3. በአንቀጽ 15 መሠረት ሹመቱ ቀሪ የተደረገበት ወይም ከኃላፊነት የተነሳ ሰው እንደገና ካልተሾመ በስተቀር ለስድስት ወር ያህል በሕግ አውጪ፣ በሕግ አስፈፃሚና በዳኝነት አካላት ውስጥ የኃላፊነት ቦታ አይሰጠውም።

15.<u>ተሿሚው ከኃላፊነት የሚነሳበት ምክንያት</u>

1. አንድ ተሿሚ በሚከተሉት ሁኔታዎች ከኃላፊነት እንዲነሳ ሊደረግ ወይም ሹመቱ ቀሪ ሊሆን ይችላል፤

    ሀ/ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ ሲፈልግና የሦስት ወር ማስጠንቀቂያ አስቀድሞ በጽሑፍ ሲሰጥ፣

    ለ/ በሕመም ምክንያት ሥራውን በሚገባ ለማከናወን የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፣

ሐ/ የሰብአዊ መብት መጣስ መፈፀሙ ሲረጋገጥ፣

መ/ በሙስና መሥራቱ ወይም ሕግን የሚጻረር ሌላ ድርጊት መፈፀሙ ሲረጋገጥ፡

ሠ/ ግልፅ የሆነ የሥራ ችሎታ ማነስ መኖሩ ሲረጋገጥ፣

ረ/ የሥራ ዘመኑ ሲያበቃ፡፡

2. አንድ ተሿሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከኃላፊነት ከተነሳበት ወይም ሹመቱ ቀሪ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ በስድስት ወሮች ውስጥ በሌላ ተሿሚ መተካት አለበት፡፡

## 16. ተሿሚው ከኃላፊነት የሚነሳበት ሥነሥርዓት

1. አንድ ተሿሚ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 (1) (ለ-ሠ) በተዘረዘሩት ምክንያቶች መሠረት ሹመቱ ቀሪ እንዲሆን የሚደረገው በአንቀጽ 17 መሠረት በሚቋቋመው ልዩ አጣሪ ጉባዔ ከተመረመረ በኋላ ይሆናል።
2. ም/ቤቱ፣ በልዩ አጣሪ ጉባዔ በአብላጫ ድምጽ ተደግፎ የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ ም/ቤቱ መርምሮ ትክክል መሆኑን ሲያምንበትና በሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሲደገፍ ተሿሚው ከኃላፊነት እንዲነሳ ይደረጋል።

## 17. የልዩ አጣሪ ጉባኤ ጥንቅር

ልዩ አጣሪ ጉባኤ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

1. የምክር ቤቱ ም/አፈ-ጉባዔ ........................................................ ሰብሳቢ
2. የፌዴሬሽን ምክር ቤት ም/አፈ-ጉባዔ................................................ አባል
3. ከምክር ቤቱ መካከል የሚመረጡ ሦስት አባላት ........................... አባል
4. በምክር ቤቱ መቀመጫ ካላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በጋራ ስምምነት የሚመረጥ አንድ የምክር ቤቱ አባል ..................................አባል
5. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ም/ፕሬዚዳንት ................................አባል

## 18. በሌላ ሥራ መሠማራት ስለመከልከሉ

1. ተሿሚው በሥራ ዘመኑ ክፍያን በሚያስገኝ በሌላ የመንግሥትም ሆነ የግል ቅጥር ሥራ ላይ መሠማራት አይፈቀድለትም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ተሿሚው አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የሚፈለግበት የተለየ የሙያ መስክ ከግምት ውስጥ ገብቶ በምክር ቤቱ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## የተሿሚዎች ሥልጣንና ተግባር

19.<u>የዋና ኮሚሽነር ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋና ኮሚሽነሩ የኮሚሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን በዚህ አዋጅ ለኮሚሽኑ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ዋና ኮሚሽነሩ፤

   ሀ/ የኮሚሽነሮች ጉባዔ በሚያጸድቀው መመሪያ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

   ለ/ በኮሚሽነሮቹ ጉባኤ የተመከረበትን ረቂቅ በጀት አዘጋጅቶ ከቀጥታ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፤

   ሐ/ በቂ ምክንያት ሲኖረው አንድን ጉዳይ ከአንድ የምርመራ ክፍል ወይም መርማሪ ወደ ሌላ ክፍል ያዛውራል፤ ወይም በማንኛውም ሥፍራ የተፈጸመ የሰብዓዊ መብት መጣስ ጉዳይን ራሱ ይመረምራል።

   መ/ ተደጋጋሚ የሰብአዊ መብት መጣስ ጉዳዮችን አጥንቶ ከመፍትሔ ሃሳብ ጋር ለምክር ቤቱ ያቀርባል፤

   ሠ/ የፌዴራል መንግሥት፣ የሰብአዊ መብቶችን ጥበቃ አስመልክቶ በሚያዘጋጀው ሪፖርት ላይ አስተያየት ይሰጣል፣

   ረ/ ሰብአዊ መብቶችን የሚመለከቱ ረቂቅ ሕጎችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፤ በሌሎች አካላት በተዘጋጁትም ላይ አስተያየት ይሰጣል፣

   ሰ/ የሰብአዊ መብት ጉዳዮችንና የኮሚሽኑን የሥራ አካሔድ አስመልክቶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፣

   ሸ/ ኮሚሽኑን በመወከል በስብሰባዎች ይካፈላል፤ ከፌዴራልና ከክልል መንግሥታት አካላት እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፣

   ቀ/ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ያደራጃል፤ ያስተባብራል፤ ይከታተላል፤

   በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡
3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) (ለ)፣ (ረ)፣ (ሰ) እና በአንቀጽ 35 (2) ከተጠቀሱት በስተቀር ያሉትን ሌሎች ጉዳየች በሚመለከት ዋና ኮሚሽነሩ ለኮሚሽኑ የሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኮሚሽነሮች ወይም ለሌሎች ኃላፊዎች በውክልና ሊያስሥተላልፍ ይችላል።

20.<u>የምክትል ዋና ኮሚሽነር ሥልጣንና ተግባር</u>

ምክትል ዋና ኮሚሽነሩ፤

1. የኮሚሽኑን ዋና መሥሪያ ቤት ተግባሮች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ኮሚሽነሩን ይረዳል፤
2. ዋና ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ለዋና ኮሚሽነሩ የተሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፤
3. በዋና ኮሚሽነሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

21.**<u>የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ኮሚሽነሮች ሥልጣንና ተግባር</u>**

ኮሚሽነሩ የቅርንጫፍ ጽ/ቤት የበላይ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (7) እና (9) ሥር ከተጠቀሰው በስተቀር በተቋቋመበት ሥፍራ ውስጥ ለኮሚሽኑ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ከማዋል በተጨማሪ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. በቂ ምክንያት ሲኖረው አንድን ጉዳይ ከአንድ የምርመራ ክፍል ወይም ከአንድ መርማሪ ወደ ሌላ የማዛወር ወይም እራሱ ምርመራ የማከናወን፤
2. የሰብአዊ መብት ጉዳዮችን በተመለከተ ለዋናው ኮሚሽነሩ ዝርዝር ሪፖርት የማቅረብ፤
3. በኮሚሽኑ በሚወጣው መመሪያ መሠረት ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱን የመምራት፣ የማደራጀት፣ ባለሙያዎችንና ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞችን የማስተዳደር፤
4. ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀት መሠረት ክፍያዎችን የመፈጸም፤
5. ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቱን በመወከል ከክልል መንግሥት አካላትና በክልሉ ውስጥ ከሚሠሩ መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሥራ ግንኙነት የማድረግ፤
6. በዋና ኮሚሽነሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች የማከናወን።

## <u>ምዕራፍ ሦስት</u>

## <u>የኮሚሽኑ የአሠራር ደንቦች</u>

22.**<u>አቤቱታ የማቅረብ መብት</u>**

1. አቤቱታ የሚቀርበው መብቴ ተጥሶብኛል በሚል ሰው ወይም በሚስት፤ ወይም በባል፤ ወይም በቤተዘመድ ወይም በወኪል ወይም በሦስተኛ ወገን ሊሆን ይችላል፡፡
2. እንደተፈፀመው የሰብአዊ መብት መጣስ ጉዳይ ክብደት ኮሚሽኑ የአመልካቹ ማንነት ሳይገለጽ የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች ሊቀበል ይችላል።

3. በአንቀጽ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ መሠረት አቤቱታ የማቅረብ መብት በጉዳዩ የወንጀል ወይም የፍትሐብሔር ክስ መመስረትን አይከለክልም።

4. ኮሚሽኑ አቤቱታዎችን ተቀብሎ የሚመረምረው ያለምንም ክፍያ ነው።

23.<u>ስለ አቤቱታ አቀራረብ</u>

1. አቤቱታ በቃል ወይም በጽሑፍ ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ ለኮሚሽኑ ሊቀርብ ይችላል።
2. አቤቱታዎች በተቻለ መጠን ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርባቸዋል።
3. አቤቱታ እንደሁኔታው በአማርኛ ወይም በክልል የሥራ ቋንቋ ሊቀርብ ይችላል።

24.<u>ስለምርመራ</u>

1. ኮሚሽኑ የቀረቡለትን አቤቱታዎች መሠረት በማድረግ ምርመራ ሊያካሒድ ይችላል፡፡
2. ኮሚሽኑ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በራሱ አነሳሽነት ምርመራ የማካሔድ ሥልጣን አለው።

25.<u>ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ስለማድረግ</u>

ኮሚሽኑ አስፈላጊ ማጣሪያዎችን ለማካሔድ በቂ በሆነ ጊዜ ውስጥ፣

1. ተመርማሪዎች ለጥያቄ እንዲቀርቡ ወይም መልስ እንዲሰጡ፣
2. ምስክሮች ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ፣
3. ለጉዳዩ ጠቃሚ የሆነ ማስረጃ የያዘ ማንኛውም ሰው እንዲያቀርብ ለማድረግ ይችላል፡፡

26.<u>መፍትሔ ስለመስጠት</u>

1. ኮሚሽኑ የቀረበለትን አቤቱታ በስምምነት ለመጨረስ የተቻለውን ጥረት ያደርጋል፡፡
2. የምርመራውን ውጤት ከነአስተያየቱ ለሚመለከተው አካል የበላይ ኃላፊ እና ለአቤቱታ አቅራቢ በጽሑፍ ያሳውቃል፡፡
3. ኮሚሽኑ በዚህ አንቀጽ መሠረት የሚሰጠው የመፍትሔ ሀሳብ ለተፈጸመው በደል ምክንያት የሆነው ድርጊት ወይም አሠራር እንዲቆም፣ ለበደሉ ምክንያት የሆነው ተፈፃሚነቱ እንዲቀርና የተፈጸመው የፍትሕ መጓደል እንዲታረም ወይም ተገቢ የሆነ ማንኛውም ሌላ እርምጃ እንዲወስድ በግልጽ የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡

4. ለኮሚሽኑ የሚቀርቡ አቤቱታዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ምላሽ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

27.<u>ቅሬታ የማሰማት መብት</u>

1. ማንኛውም አቤቱታ አቅራቢ ወይም ተመርማሪ የኮሚሽኑ የበታች ተሿሚ ወይም ኃላፊ በሰጠው የመፍትሔ ሃሳብ ላይ ቅሬታ ካለው ይኸው በጽሑፍ ከደረሰው ቀን አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በደረጃው ቀጥሎ ለሚገኘው ተሿሚ ወይም ኃላፊ ቅሬታ የማሰማት መብት አለው፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ቅሬታው የቀረበለት ተሿሚ ወይም ኃላፊ የተሰጠውን የመፍትሔ ሃሳብ ማሻሻል፣ ማገድ፣ መሻር፣ ወይም ማፅናት ይችላል፡፡

3. በዋና ኮሚሽነሩ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

28.<u>ጥፋት መፈጸሙን የማስታወቅ ግዴታ</u>

ኮሚሽኑ የምርመራ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ወንጀል መሰራቱን ወይም የአስተዳደር ጥፋት መፈጸሙን ያመነ እንደሆነ ለሚመለከተው አካል ወይም ኃላፊ ወዲያውኑ በጽሑፍ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

29.<u>ስለሥልጣን መደራረብ</u>

1. በኮሚሽኑና በሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ጉዳዮች በሚጋጥሙበት ጊዜ በማንኛቸው እንደሚመረመሩ በሁለቱ የጋራ ምክክር ይወሰናል፡፡

2. አንድን ጉዳይ የትኛው አካል እንዲመረምር በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መወሰን ካልተቻለ አስቀድሞ የቀረበለት አካል ይመረምራል።

## <u>ምዕራፍ አራት</u>

## <u>ስለ ኮሚሽነሮች ጉባኤና ሰለኮሚሽኑ ሠራተኞች አስተዳደር</u>

30.<u>የኮሚሽነሮች ጉባዔ</u>

1. የኮሚሽነሮች ጉባኤ/ከዚህ በኋላ "ጉባኤው" እየተባለ የሚጠራ/ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

ሀ/ ዋና ኮሚሽነር ........................................ ሰብሳቢ

ለ/ ም/ ዋና ኮሚሽነር ..................................ም/ሰብሳቢ

ሐ/ ሌሎች ኮሚሽነሮች ............................. አባሎች

3. ጉባዔው የራሱን ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል ይመርጣል።

4. ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

31.<u>የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር</u>

ጉባዔው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፣

1. ይህንን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል መመሪያዎችንና የውስጥ ደንቦችን ያጸድቃ፤
2. በኮሚሽኑ ረቂቅ በጀት ላይ ይመክራል፤
3. የፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ህግን መሰረታዊ አላማን በመከተል የኮሚሽኑ ሰራተኞች የሚተዳደሩበትን መመርያ ያጸድቃል፣
4. የኮሚሽኑን እና የቅርንጫፍ ኮሚሽን መምሪያ ኃላፊዎችን ይሾማል፤
5. የሚቅርቡለትን የሠራተኛ አስተዳደር አቤቱታዎች መርምሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይስጣል፤
6. በቅርንጫፍ ጽ/ቤት ደረጃ የህፃናትና የሴቶች ጉዳይ መምሪያ ኃላፊዎችን ይሾማል፤
7. የመምርያ ሀላፊዎችን የዲሲፕሊን ጉዳዮችን ይመለከታል፡፡

32.<u>ይግባኝ የማቅረብ መብት</u>

1. ጉባኤው በሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም የኮሚሽኑ መምሪያ ኃላፊ ውሳኔው ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ውስጥ ቅሬታውን ለምክር ቤቱ አፈ-ጉባኤ ማቅረብ ይችላል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

33.<u>በሌሎች ባለሙያዎች ስለመገልገል</u>

ኮሚሽኑ ለተለየ ሥራና ለተወሰነ ጊዜ ተገቢ የሆነውን ክፍያ በመፈፀም ለሥራው የሚያስፈልጉትን የራሱ ያልሆኑ ባለሙያዎችን መድቦ ሊያሠራ ይችላል።

34.<u>ሚስጥር ስለመጠበቅ</u>

በፍ/ቤት ካልታዘዘ ወይም ዋናው ኮሚሽነር ካልፈቀደ በቀር ማንኛውም የኮሚሽኑ ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ወይም በአንቀጽ 33 መሠረት የተመደበ ባለሙያ በሥራው አጋጣሚ ያወቀውን ሚስጢር በማንኛውም ጊዜ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

35.<u>ልዩ መብት</u>

ማንኛውም የኮሚሽኑ፣

1. ተሿሚ ከሆነ ም/ቤቱ፤

2. መርማሪ ከሆነ ዋና ኮሚሽነሩ፤

ሳይፈቅድ ወይም ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፈንጅ ካልተያዘ በስተቀር አይያዝም፡ አይታሰርም።

## ምዕራፍ አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 36.በጀት

1. የኮሚሽኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፣

ሀ/ በመንግሥት የሚመደብ በጀትና ድጎማ፤

ለ/ ከእርዳታ፣ ከስጦታና ከማናቸውም ሌላ ምንጭ፤

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ከተጠቀሱት ምንጮች የሚገኝ ገንዘብ በቅድሚያ የሦስት ወር ድርሻ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ባንኩ በሚወክለው ሌላ ባንክ ተቀማጭ ሆኖ በመንግሥት ፋይናንስ ሕግ መሠረት ለኮሚሽኑ ዓላማዎች ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

### 37.የሂሣብ መዛግብት

1. ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሣብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2. የኮሚሽኑ ሂሣብ ም/ቤቱ በሚሰይመው አካል በየዓመቱ ይመረመራል፡፡

### 38.የመተባበር ግዴታ

ኮሚሽኑ ሥልጣኑንና ተግባሩን ሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል።

### 39.መግለጫ ስለመስጠት

1. ኮሚሽኑ እንደ አስፈላጊነቱ ይፋዊ መግለጫ ይሰጣል፡፡

2. ኮሚሽኑ መደበኛ ሪፖርቶች ማቅረብን ጨምሮ አሠራሩን ለሕዝብ ግልጽ ማድረግ ይኖርበታል።

3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የአገሪቱ ጸጥታና ደኅንነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ለማድረግ ወይም የግለሰቦችን የግል ሕይወት መብት ለመጠበቅ ሲባል በሚስጢር ሊያዙ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ኮሚሽኑ ጥንቃቄ የመውሰድ ግዴታ አለበት፡፡

### 40.በስም ማጥፋት ስላለመጠየቅ

1. በዚህ አዋጅ መሰረት የቀረበ አቤቱታ በስም ማጥፋት አያስጠይቅም።

2. ኮሚሽኑ ስለሚያካሒደው ምርመራ ውጤት ለም/ቤቱ የሚያቀርበው ሪፖርት ወይም ሥራውን በማስመልከት የሚያደርገው ሌላ ዓይነት መጻጻፍ በስም ማጥፋት የሚያስጠይቅ አይሆንም።

41. <u>ስለ ቅጣት</u>

1. ማንኛውም ሰው በኮሚሽኑ መጥሪያ ደርሶት ወይም በሌላ ሁኔታ ተጠርቶ በቂ ምክንያት ሳይኖረው በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ወይም መልስ ካልሰጠ ወይም ሰነድ ለማቅረብ ወይም ለማስመርመር ፈቃደኛ ካልሆነ ከአንድ ወር እስከ ስድስት ወር በሚደርስ እሥራት ወይም ከብር ሁለት መቶ እስከ ብር አንድ ሺ የገንዘብ መቀጫ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።
2. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው ኮሚሽኑ ዘንድ ምስክሮች ሆነው በቀረቡ ወይም ሰነድ ባቀረቡ ሰዎች ላይ ጥቃት ካደረሰ ወይም ለኮሚሽኑ በቀረቡ ሪፖርቶች በተሰጡት አስተያየቶችና ሃሳቦች ላይ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ያለ በቂ ምክንያት እርምጃ ካልወሰደ ወይም እርምጃ የማይወስድበትን ምክንያት ካልገለጸ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም ከብር ስድስት ሺ እስከ ብር አሥር ሺ የገንዘብ መቀጫ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

42. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ለምክር ቤቱ የቀረቡና ውሳኔ ያላገኙ የሰብአዊ መብቶች መጣስ ጉዳዮችን የሚመለከቱ አቤቱታዎች በኮሚሽኑ ይታያሉ።

43. <u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተጠቀሱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

44. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ከሰኔ 27 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 27 ቀን 1992 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 211/1992 ዓ.ም

## የህዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋምን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለፖለቲካ ሥልጣን ባለቤትነት እንዲሁም ለሕግ ልዕልና እውነት ባካሄደው ረጅም ትግል የከፈለው መስዋዕትነት በዜጎች ላይ በዘፈቀደ የሚፈጸሙ የአስተዳደር በደሎች የሚቀጩበትን ወይም የሚታረሙበትን ቀልጣፋ አሠራር በመዘርጋት ለሰናይ መስተዳድር መሠረት የመጣልን ወቅታዊ እርምጃ የሚጠይቅ በመሆኑ፣

የመንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሚያከናውኗቸው ተግባሮች ከዜጎች የዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር ያላቸው ቁርኝትና ከመብታቸው ጋር በተሳሰረ ሁኔታ የሚኖራቸው የወሳኝነት ሥልጣን ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየሰፋ በመምጣቱ፣

በዚህ ሂደት የመንግሥት አስፈጻሚ አካላትና ባለሥልጣኖቻቸው የሚሰጧቸውን ፍትሀዊነት የጎደላቸው ውሳኔዎችና ትዕዛዞች በወቅቱ ማረም ወይም እንዳይደርሱ መከላከል አስፈላጊ በመሆኑ፣

አስተዳደራዊ ጥፋት የተፈጸመባቸው ዜጎች ተጎድተው እንዳይቀሩ በቀላሉ ቅሬታቸውን የሚያሰሙበትና መፍትሄ የሚሹበት ተቋም የማግኘት ፍላጎታቸው መሟላት ያለበት በመሆኑ፣

ሕግ አውጪው በሕዝብ ተወካይነቱ ሕግ አስፈጻሚው አካል ተግባሩን በሕግ መሰረት የሚያከናውንና የሚሰጣቸው አስተዳደራዊ ውሳኔዎች የዜጎችን መብቶች የማይጋፉ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፣

ይህንኑ መርህ ለማጎልበትና ስለሕግ አውጪው ሆኖ አስተዳደራዊ በደል እንዳይደርስ የመቆጣጠሪያ መሣሪያ በመሆን ከሚያገለግሉት ተቋሞች መካከል አንዱ የሆነውን የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋምን ማቋቋምና ሥልጣኑንና ተግባሩን በሕግ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 55 (1) እና (15) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ምዕራፍ አንድ

### ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 211/1992" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስ፡-

1. "ተሿሚ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በምክር ቤቱ የሚሾም ዋና ዕንባ ጠባቂ፡ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ ወይም በቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ደረጃ የሚገኝ ወይም የህጻናትንና የሴቶችን ጉዳይ የሚከታተል ዕንባ ጠባቂ ማለት ነው።
2. "ሠራተኛ" ማለት የተቋሙ መምሪያ ኃላፊዎችን፣ ባለሙያዎችንና ድጋፍ ሰጭ ሠራተኞችን ይጨምራል፤
3. "ቤተዘመድ" ማለት በኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ መሠረት የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው ሰው ነው፤
4. "ምክር ቤት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲምክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፤
5. "የአስተዳደር ጥፋት" ማለት ማናቸውንም የአስተዳደር ሕግን ወይም የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕግን ወይም ሌሎች አስተዳደር ነክ ሕጎችን በመጻረር በመንግሥት አስፈጻሚ አካላት የሚፈጸሙ ድርጊቶችን ወይም የሚሰጡ ውሳኔዎችን ይጨምራል፣
6. "ባለሥልጣን" ማለት የሕዝብ ተመራጭ ወይም የመንግሥት አስፈጻሚ አካል ተሿሚ ወይም ኃላፊ ነው፣
7. "ሰው" ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣
8. "ክልል" ማለት ኢትየጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47 (1) ላይ የተመለከቱት ማለት ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል የአዲስ አበባ ከተማ መስተዳድርንና የድሬዳዋ አስተዳደርን ይጨምራል፤
9. "መንግስት" ማለት የፌዴራል ወይም የክልል መንግስት ነው፣
10. "የመንግስት የልማታ ድርጅት" በመንግስተ ባለቤትንት ባለቤትነት ሥር የሚገኝ የማምረቻ፣ የማከፋፈያ፣ አገልግሎት ሰጭ ወይም ሌላ ዓይነት ድርጅት ነው፤
11. "የመንግስት መ/ቤት" ማለት ሚኒስቴር፤ ኮሚሽን፤ ባለስልጣን፣ ኤጀንሲ፣ ኢንስቲትዩት ወይም ማናቸውም ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፤
12. "መርማሪ" ማለት የምርመራ ሥራ እንዲያካሂድ በዋና ዕንባ ጠባቂ የተመደበ ሰራተኛ ነው፤

13.“አስፈጻሚ አካል” ማለት የመንግሥት መሥሪያ ቤትን፣ ወይም የመንግስት የልማት ድርጅትን እንዲሁም በዳኝነት ሰጪ ወይም በህግ አውጪው አካል ውስጥ የአስተዳደር ወይም የአስተዳደር ነክ አገልግሎት የሚሰጥ አካልን ይጨምራል፣

14.“ህግ” ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስትን፣ የክልል ህገ መንግስትን፤ የፌዴራል ወይም የክልል ሕጎችንና ደንቦችን ይጨምራል፡፡

3. <u>መቋቋም</u>

1. የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም (ከዚህ በኋላ “ተቋሙ“እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።
2. ተቋሙ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ይሆናል፡፡

4. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

1. በዚህ አዋጅ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ይጨምራል፡፡
2. ይህ አዋጅ በክልል መንግሥት አስፈጻሚ አካላትና ባለሥልጣኖቻቸው በሚፈጸሙ የአስተዳደር ጥፋቶችም ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል።

5. <u>ዓላማ</u>

የተቋሙ ዓላማ በሕግ የተደነገጉ የዜጎች መብቶች እና ጥቅሞች በአስፈጻሚው አካላት መከበራቸውን በማረጋገጥ፣ የሕግ የበላይነትን መሠረት ያደረገ ጥራት፣ ቅልጥፍናና ግልጽነት ያለው መልካም የመንግሥት አስተዳደር እንዲሰፍን ማድረግ ይሆናል፡፡

6. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ተቋሙ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታ፤

1. አስፈጻሚ አካላት የሚያወጧቸው አስተዳደራዊ መመሪያዎች፣ የሚሰጧቸው ውሳኔዎችና አሠራሮቻቸው የዜጎችን ሕገ-መንግሥታዊ መብቶችንና ሕጎችን የማይቃረኑ መሆናቸውን መቆጣጠር፤
2. አስተዳደራዊ ጥፋትን አስመልክቶ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመቀበልና የመመርመር፤
3. አስፈጻሚው አካል ሥራውን በሕግ መሠረት የሚያከናውን መሆኑን ለማረጋገጥና አስተዳደራዊ ጥፋቶች እንዳይፈጸሙ ለመከላከል ቁጥጥር የማድረግ፤

4. አስተዳደራዊ ጥፋት መፈፀሙን ያመነበት ከሆነ የመፍትሄ ሃሳብ የመሻት፣
5. አስተዳደራዊ ጥፋቶች የሚሻሻሉበትን ሁኔታ የማጥናትና ሃሳብ የማቅረብ፤
6. የተሻለ የመንግሥት አስተዳደርን ለማስገኘት ነባር ሕጎች ወይም አሠራሮች ወይም መመሪያዎች እንዲሻሻሉ፤ አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም ፖሊሲዎች እንዲቀየሱ የማሳሰብ፤
7. ከዓላማው ጋር የሚጣጣሙ ሌሎች ተግባሮችን የማከናወን፡፡

7. <u>የሥልጣን ገደብ</u>

ተቋሙ፡-

1. በሕዝብ ምርጫ የተቋቋሙ ምክር ቤቶች በሕግ አውጭነታቸው የሚሰጧቸው ወሳኔዎችን ወይም፣
2. በማንኛውም ፍርድ ቤት በየትኛውም ደረጃ በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችን ወይም፣
3. በዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በመታየት ላይ ያሉ ጉዳዮችን ወይም፣
4. በፀጥታ ኃይሎችና በመከላከያ ሠራዊት ክፍሎች የሚሰጡ የጸጥታ ወይም የሀገር መከላከል ጉዳዮችን በሚመለከት የሚሰጡ ውሳኔዎችን፣

የመመርመር ሥልጣን የለውም።

8. <u>የተቋሙ አቋም</u>

ተቋሙ፡-

1. የዕንባ ጠባቂ ጉባዔ፣
2. ሀ/ አንድ ዋና ዕንባ ጠባቂ፣
   ለ/ አንድ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ፣
   ሐ/ የሕፃናትና የሴቶችን ጉዳይ የሚመራ ዕንባ ጠባቂ፤
   መ/ የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ዕንባ ጠባቂዎች፤ እና
   ሠ/ አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

9. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የተቋሙ ዋና መ/ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ምክር ቤቱ በሚወስነው በማናቸውም ሥፍራ ቅርጫፍ ጽ/ቤት ሊኖረው ይችላል፡፡

10. <u>አሿሿም</u>

1. ዋና ዕንባ ጠባቂ፣ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂና ሌሎች ዕንባ ጠባቂዎች በምክር ቤቱ ይሾማሉ።

2. የዋና ዕንባ ጠባቂ፣ የምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂና የሌሎች ዕንባ ጠባቂዎች አሿሿም የሚከተለው የአመራረጥ ሥርዓት ይኖረዋል፣

ሀ/ ተሿሚዎች በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 መሠረት በሚቋቋመው እጩ አቅራቢ ኮሚቴ ይመለመላሉ፤

ለ/ ዕጩዎቹም በኮሚቴው ሁለት ሦስተኛ ድምፅ የተደገፉ መሆን አለባቸው፤

ሐ/ ዕጩዎቹ በምክር ቤቱ አፈ-ጉባዔ ለምክር ቤቱ ቀርበው ድምጽ የሚሰጥባቸው ይሆናል፤

መ/ የቀረቡት ዕጩዎች በምክር ቤቱ ሁለት ሦስተኛ ድምጽ ሲደገፉ ይሾማሉ።

## 11.<u>የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ ጥንቅር</u>

የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

1. የምክር ቤተ አፈጉባዔ ............................... ሰብሳቢ፤
2. የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈጉባዔ .................. አባል፤
3. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጡ አምስት አባላት ............አባል፤
4. በምክር ቤቱ መቀመጫ ካላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች መካከል በጋራ ስምምነት የሚመረጡ ሁለት የምክር ቤት አባላት .......................... አባል፤
5. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት .................................... " ፤

## 12.<u>ለሹመት የሚያበቁ መመዘኛዎች</u>

ከዚህ በታች የተመለከቱትን መመዘኛዎች የሚያሟላ ሰው በዕንባ ጠባቂነት ሊሾም ይችላል፣

1. ለኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት ተገዥ የሆነ፣
2. በሕግ ወይም በአስተዳደር ወይም አግባብ ባለው ሌላ ሙያ የሰለጠነ ወይም በልምድ በቂ ዕውቀት ያካበተ፤
3. በታታሪነቱ፣ በታማኝነቱ እና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፣
4. ከደንብ መተላለፍ ውጪ ባለ በሌላ የወንጀል ጥፋት ተከሶ ያልተፈረደበት፣
5. ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፣
6. ሥራውን ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ ጤንነት ያለው፣ እና ዕድሜው ከ35 ዓመት በላይ የሆነ።

## 13.<u>ተጠሪነት</u>

1. ዋና ዕንባ ጠባቂ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ይሆናል፡፡

2. ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂውና ሌሎች ዕንባ ጠባቂዎች ተጠሪነታቸው ለዋናው ዕንባ ጠባቂ ይሆናል፡፡

14.<u>የሥራ ዘመን</u>

1. የማንኛወም ተሿሚ የሥራ ዘመን አምስት አመት ይሆናል።
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው የሥራ ዘመን ካበቃ በኋላ ተሿሚው እንደገና ሊሾም ይችላል፡፡
3. በአንቀጽ 15 (1) መሠረት ሹመቱ ቀሪ የተደረገበት ወይም ከኃላፊነት የተነሳ ሰው እንደገና ካልተሾመ በስተቀር ለስድስት ወር ያህል በሕግ አውጪነት፤ በሕግ አስፈጻሚ ወይም በዳኝነት አካላት ውስጥ የኃላፊነት ቦታ አይሰጠውም፡፡

15.<u>ተሿሚው ከኃላፊነት የሚነሳበት ምክንያት</u>

1. አንድ ተሿሚ በሚከተሉት ሁኔታዎች ከኃላፊነት እንዲነሳ ወይም ሹመቱ ቀሪ እንዲሆን ሊደረግ ይችላል፤

   ሀ/ ሥራውን በገዛ ፈቃዱ ለመልቀቅ ሲፈልግና አስቀድሞ የሦስት ወር ማስጠንቀቂያ በጽሑፍ ሲሰጥ ፡ ወይም

   ለ/ በህመም ምክንያት ሥራውን በሚገባ ለማከናወን የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፤ ወይም

   ሐ/ በሙስና መሥራቱ ወይም ሕግን የሚጻረር ሌላ ድርጊት መፈጸሙ ሲረጋገጥ፤ ወይም

   መ/ ግልጽ የሆነ የሥራ ችሎታ ማነስ መኖሩ ሲረጋገጥ፣ ወይም

   ሠ/ የሥራ ዘመኑ ሲያበቃ፡፡

2. አንድ ተሿሚ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ከኃላፊነት ከተነሳበት ወይም ሹመቱ ቀሪ ከሆነበት ጊዜ አንስቶ በስድስት ወሮች ውስጥ በሌላ ተሿሚ መተካት ይኖርበታል።

16.<u>ተሿሚው ከኃላፊነት የሚነሳበት ሥነ ሥርዓት</u>

1. አንድ ተሿሚ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 15 (1) ከ(ለ)-(መ) በተዘረዘሩት ምክንያቶች መሠረት ሹመቱ ቀሪ እንዲሆን የሚደረገው ጉዳዩ በአንቀጽ 17 መሠረት በሚቋቋመው ልዩ አጣሪ ጉባዔ ከተመረመረ በኋላ ይሆናል፡፡
2. ምክር ቤቱ በልዩ አጣሪ ጉባዔው አብላጫ ድምጽ ተደግፎ የቀረበለትን የውሳኔ ሃሳብ መርምሮ ሲያምንበትና በሁለት ሦስተኛ ድምፅ ሲደግፈው ተሿሚው ከኃላፊነት እንዲነሳ ይደረጋል።

17.<u>የልዩ አጣሪ ጉባዔው ጥንቅር</u>

ልዩ አጣሪ ጉባኤው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፤

1. የምክር ቤቱ ምክትል አፈ ጉባኤ ............................................... ሰብሳቢ፤
2. የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ ............................................... አባል፤
3. ከምክር ቤቱ አባላት መካከል የሚመረጡ ሦስት አባላት .................አባል፤
4. በምክር ቤቱ መቀመጫ ካላቸው ተቃዋሚ ፓርቲዎች በጋራ ስምምነት የሚመረጥ አንድ የም/ቤቱ አባል ............................................... አባል፤
5. የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት .................. አባል ፡፡

18.<u>በሌላ ሥራ መሰማራት ስለመከልከሉ</u>

1. ተሿሚው በሥራ ዘመኑ ክፍያን በሚያስገኝ በሌላ የመንግሥትም ሆነ የግል ቅጥር ሥራ ላይ እንዲሠማራ አይፈቀድለትም፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተው ቢኖርም ተሿሚው አስተዋጽኦ እንዲያደርግ የሚፈልግበት የተለየ የሙያ መስክ ከግምት ውስጥ ገብቶ በምክር ቤቱ ሊፈቀድለት ይችላል፡፡

## <u>ምዕራፍ ሁለት</u>

## <u>የተሿሚዎች ሥልጣንና ተግባሮች</u>

19.<u>የዋና ዕንባ ጠባቂው ሥልጣንና ተግባር</u>

1. ዋናው ዕንባ ጠባቂ የበላይ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ ለተቋሙ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ያውላል።
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዕንባ ጠባቂ፤

   ሀ/ የተቋሙ የዕንባ ጠባቂዎች ጉባዔ በሚያጸድቀው መመሪያ መሠረት ሠራተኞችን ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፣

   ለ/ የተቋሙን በጀት አዘጋጅቶ በቀጥታ ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላል፣

   ሐ/ በቂ ምክንያት ሲኖረው አንድ ጉዳይ ከአንድ የምርመራ ክፍል ወይም መርማሪ ወደ ሌላ የምርመራ ክፍል ወይም መርማሪ ያዛውራል፤ ወይም በማንኛውም ሥፍራ የተፈጸመ አስተዳደራዊ ጥፋትን በራሱ ይመረምራል፡

   መ/ ተደጋጋሚ የአስጸዳደር ጥፋቶችን አጥንቶ ከመፍትሄ ሃሳብ ጋር ለምክር ቤቱ ያቀርባል፣

   ሠ/ አስተዳደራዊ ጉዳዮችን የሚመለከቱ ረቂቅ ሕጎችን አዘጋጅቶ ያቀርባል፣

በሌሎች አካላት በተዘጋጁ ላይ አስተያየት ይሰጣል፣

ረ/ አስተዳደራዊ ጥፋቶችንና የተቋሙን ሥራ አካሄድ አስመልክቶ ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል፣

ሰ/ ተቋሙን በመወከል በስብሰባዎች ይካፈላል፤ ከፌዴራልና ከክልል መንግሥታት አካላት እንዲሁም መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሥራ ግንኙነት ያደርጋል፣

ሸ/ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ያደራጃል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣

ቀ/ በምክር ቤቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) (ለ)፣ (ሠ)፣ (ረ) እና በአንቀጽ 35(2) ከተጠቀሱት በስተቀር ሌሎች ጉዳዮችን በሚመለከት ዋና ዕምባ ጠባቂው ለተቋሙ የስራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠንና ስልጣንና ተግባሩን በከፊል ለዕንባ ጠባቂዎች ወይም ለሌሎች ኃላፊዎች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

20.<u>የምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ ሥልጣንና ተግባር</u>

ከዋና እንባ ጠባቂው በሚሰጠው መመርያ መሰረት፤

1. የተቋሙን ዋና መስርያ ቤት ተግባራትን በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራትና በማስተባበር ዋና ዕንባ ጠባቂውን ይረዳል፡፡
2. ዋና እንባ ጠባቂው በማይኖርበት ጊዜ ለዋናው እንባ ጠባቂ የተሰጡትን ሥራዎች ያከናውናል፡፡
3. በዋናው እንባ ጠባቂ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

21.<u>የቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች የእንባ ጠባቂዎች ሥልጣንና ተግባር</u>

ዕንባ ጠባቂው የቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 6 በተቋቋመበት ሥፍራ ውስጥ ለተቋሙ የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር በስራ ላይ ከማዋል በተጨማሪ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. የመንግስት የአስተዳደር ህጎች እና ሌሎች ህጎች፤ ደንቦችና መመርያዎች መከበራቸውን የማረጋገጥ፤
2. በቂ ምክንያት ሲኖር አንድ የአስተዳደር ጉዳይ ከአንድ የምርመራ ክፍል ወይም ከአንድ መርማሪ ወደ ሌላ የማዛወር ወይም እራሱ ምርመራ የማካሄድ፤
3. አስተዳደራዊ ጥፋቶችን በተመለከተ ለዋናው እንባ ጠባቂውና በተቋቋመበት ሥፍራ ለሚገኝ ክልል መንግስት ዝርዝር ሪፖርት የማቅረብ፣
4. ከመልካም አስተዳደር መርህ ጋር የማይጣጣሙ ህጎችና የአሰራር ልምዶች እንዲሻሻሉ ሃሳብ የማቅረብ፤

5. በተቋሙ በሚወጣው መመርያ መሰረት ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን የመምራት፣
6. ለቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ በተፈቀደው በጀት መሰረት ክፍያዎች የመፈጸም፣
7. ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን በመወከል ከክልል መንግስት አካላትና በተቋቋመበት ሥፍራ ወስጥ ከሚሰሩ መንግስታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች ጋር የሥራ ግንኙነት የማድረግ፣
8. በዋና ዕንባ ጠባቂው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች የማከናወን፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## የተቋሙ የአሠራር ደንቦች

### 22.አቤቱታ የማቅረብ መብት

1. አቤቱታ የሚቀርበው መብቴ ተጥሶብኛል በሚል ሰው፣ ወይም በሚስት ወይም በባል ወይም በቤተዘመድ ወይም በወኪል ወይም በሦስተኛ ወገን ሊሆን ይችላል፡፡
2. እንደተፈጸመው የአስተዳደር ጥፋት ክብደት ተቋሙ የአመልካቹ ማንነት ሳይገለጽ የሚቀርቡለትን አቤቱታዎች ሊቀበል ይችላል።
3. ማንኛውም ሰው ስለደረሰበት የአስተዳደር ጥፋት ለተቋሙ አቤቱታ ከማቅረቡ በፊት አግባብነት ላላቸው አካላት ደረጃውን ጠብቆ ቅሬታውን ማሰማት ይኖርበታል፡፡
4. በአንቀጽ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በዚህ አዋጅ መሠረት አቤቱታ የማቅረብ መብት በጉዳዩ የወንጀል ወይም የፍትሐብሔር ክስ መመስረትን አይከለክልም።
5. ተቋሙ አቤቱታዎችን ተቀብሎ የሚመረምረው ያለምንም ክፍያ ነው፡፡

### 23.ስለአቤቱታ አቀራረብ

1. አቤቱታ በቃል ወይም በጽሑፍ ወይም በማንኛውም ሌላ መንገድ ለተቋሙ ሊቀርብ ይችላል፡፡
2. አቤቱታዎች በተቻለ መጠን ከደጋፊ ማስረጃዎች ጋር መቅረብ ይኖርባቸዋል።
3. አቤቱታ እንደሁኔታው በአማርኛ ወይም በክልሉ የሥራ ቋንቋ ሊቀርብ ይችላል።

### 24.ስለምርመራ

1. ተቋሙ የቀረቡለትን አቤቱታዎች መሠረት በማድረግ ምርመራ ሊያካሂድ ይችላል፡፡

2. ተቋሙ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው በራሱ አነሳሽነት ምርመራ የማካሄድ ሥልጣን አለው፡፡

## 25. ማስረጃዎች እንዲቀርቡ ስለማድረግ

ተቋሙ አስፈላጊ ማጣሪያዎችን ለማካሄድ በቂ በሆነ ጊዜ ውስጥ፣

1. ተመርማሪዎች ለጥያቄ እንዲቀርቡ ወይም መልስ እንዲሰጡ፣
2. ምስክሮች ቀርበው ቃላቸውን እንዲሰጡ፤
3. ለጉዳዩ ጠቃሚ የሆነ ማስረጃ የያዘ ማንኛውም ሰው ይህንን ማስረጃ እንዲያቀርብ፤

ለማድረግ ይችላል፡፡

## 26. መፍትሄ ስለመስጠት

1. ተቋሙ የቀረበለትን አቤቱታ በስምምነት ለመጨረስ የተቻለውን ሁሉ ማድረግ አለበት።
2. የምርመራውን ውጤት ከነአስተያየቱ ለሚመለከተው አካል የበላይ ኃላፊ እና ለአቤቱታ አቅራቢው በጽሑፍ ያሳውቃል።
3. ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሠረት የሚሰጠው አስተያየት ለተፈጸመው የአስተዳደር ጥፋት ምክንያት የሆነው ድርጊት ወይም አሠራር እንዲቆም ወይም ለጥፋቱ ምክንያት የሆነው መመሪያ ተፈጻሚነቱ ቀሪ እንዲሆንና የተፈጸመው የአስተዳደር ጥፋት እንዲታረም ወይም ተገቢ የሆነ ማንኛውም ሌላ እርምጃ እንዲወሰድ በግልጽ የሚያመለክት መሆን ይኖርበታል።
4. ለተቋሙ የሚቀርቡ አቤቱታዎች በአጭር ጊዜ ውስጥ ምላሽ ማግኘት ይኖርባቸዋል።

## 27. ቅሬታ የማሰማት መብት

1. ማንኛውም አቤቱታ አቅራቢ ወይም ተመርማሪ የተቋሙ የበታች ተሿሚ ወይም ኃላፊ በሰጠው የመፍትሔ ሃሳብ ቅሬታ ያለው ከሆነ የመፍትሔ ሀሳቡ በፅሑፍ ከደረሰው ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ በደረጃው ቀጥሎ ለሚገኘው የተቋሙ ተሿሚ ወይም ኃላፊ ቅሬታውን የማሰማት መብት አለው።

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት ቅሬታው የቀረበለት ተሿሚ ወይም ኃላፊ የተሰጠውን የመፍትሄ ሃሳብ ማሻሻል፣ ማገድ፣ መሻር ወይም ማፅናት ይችላል፡፡

3. በዋና ዕንባ ጠባቂው የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል።

28. <u>ጥፋት መፈጸሙን የማስታወቅ ግዴታ</u>

ተቋሙ የምርመራ ሥራውን በሚያከናውንበት ጊዜ ወንጀል መሠራቱን ያመነ እንደሆነ ለሚመለከተው አካል ወይም ኃላፊ ወዲያውኑ በጽሑፍ የማስታወቅ ግዴታ አለበት፡፡

29. <u>ስለ ሥልጣን መደራረብ</u>

1. በተቋሙና በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብት ኮሚሽን ሥልጣን ሥር የሚወድቁ ጉዳዮች በሚያጋጥሙበት ጊዜ በማንኛቸው እንደሚመረመሩ በሁለቱ የጋራ ምክክር ይወሰናል።

2. አንድን ጉዳይ የትኛው አካል እንደሚመረምር በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት መወሰን ካልተቻለ አስቀድሞ የቀረበለት አካል ይመረምራል።

<u>ምዕራፍ አራት</u>

<u>ስለተቋሙ ዕንባ ጠባቂዎች ጉባዔና ስለተቋሙ ሠራተኞች አስተዳደር</u>

30. <u>የተቋሙ ዕንባ ጠባቂዎች ጉባዔ</u>

1. የተቋሙ ዕንባ ጠባቂዎች ጉባኤ (ከዚህ በኋላ "ጉባዔው" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል።

2. ጉባዔው የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡

ሀ/ ዋና ዕንባ ጠባቂ .................................. ሰብሳቢ

ለ/ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ ................. ም/ሰብሳቢ

ሐ/ ሌሎች ዕንባ ጠባቂዎች ...................... አባላት።

3. ጉባዔው የራሱን ፀሐፊ ከአባላቱ መካከል ይመርጣል።

4. ጉባዔው የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥነሥርዓት ደንቦች ሊያወጣ ይችላል፡፡

31. <u>የጉባዔው ስልጣንና ተግባር</u>

ጉባዔው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፡

1. ይህን አዋጅ ሥራ ላይ ለማዋል መመሪያዎችንና የውስጥ ደንቦችን ያጸድቃል፣

2. በተቋሙ ረቂቅ በጀት ላይ ይመክራል።

3. የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕግን መሠረታዊ ዓላማ በመከተል የተቋሙ ሠራተኞች የሚተዳደሩበትን መመርያ ያጸድቃል፣

4. መምሪያ ኃላፊዎችን ይሾማል፣

5. የሚቀርቡለትን የሠራተኛ አስተዳደር ጉዳዮች፣ ጥያቄዎች ወይም አቤቱታዎች መርምሮ በአጭር ጊዜ ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ ይሰጣል፡

6. የመምሪያ ኃላፊዎችን የዲሲፕሊን ጉዳዮች ያያል።

32. <u>ይግባኝ የማቅረብ መብት</u>

1. ጉባዔው በሚሰጠው የአስተዳደር ውሳኔ ቅር የተሰኘ የተቋሙ መምሪያ ኃላፊ ውሳኔው ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን ለምክር ቤቱ አፈ ጉባዔ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

33. <u>በሌሎች ባለሙያዎች ስለመገልገል</u>

ተቋሙ ለተለየ ሥራና ለተወሰነ ጊዜ ተገቢ የሆነውን ክፍያ በመፈጸም ለሥራ የሚያስፈልጉትን የራሱ ያልሆኑ ባለሙያዎችን መድቦ ሊያሠራ ይችላል፡፡

34. <u>ሚስጥር ስለመጠበቅ</u>

በፍርድ ቤት ካልታዘዘ ወይም በዋናው ዕንባ ጠባቂ ካልተፈደቀ በስተቀር ማንኛውም የተቋሙ ተሿሚ ወይም ሠራተኛ ወይም በአንቀጽ 33 መሠረት የተመደበ ባለሙያ በሥራው አጋጣሚ ያወቀውን ምስጢር በማንኛውም ጊዜ የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

35. <u>ልዩ መብት</u>

ማንኛውም የተቋሙ፡-

1. ተሿሚ ከሆነ ምክር ቤቱ፣

2. መርማሪ ከሆነ ዋና እንባ ጠባቂው፣ ሳይፈቀድ ወይም ከባድ ወንጀል ሲፈጽም እጅ ከፍንጅ ካልተያዘ አይያዝም፣ አይታሰርም፡፡

## <u>ምዕራፍ አምስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

36. <u>በጀት</u>

1. የተቋሙ በጀት ከሚከተሉት የተውጣጣ ይሆናል፤

ሀ/ በመንግሥት በሚመደብ በጀትና ድጎማ፤

ለ/ ከዕርዳታ፤ ከስጦታና ከማናቸውም ሌላ ምንጭ፡፡

2. ለተቋሙ ከተፈቀደው በጀት ውስጥ የየሦስት ወሩ ድርሻ የሆነ የሥራ ማስኬጃ በቅድሚያ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ወይም ባንኩ በሚወክለው ሌላ ባንክ ተቀማጭ ሆኖ በመንግሥት የፋይናንስ ሕግ መሠረት ለተቋሙ ዓላማዎች ማስፈጸሚያ ይውላል፡፡

37.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ተቋሙ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሒሳብ መዛግብት ይይዛል፡፡
2. የተቋሙ ሂሳብ ምክር ቤቱ በሚሰይመው አካል በየዓመቱ ይመረመራል።

38.<u>የመተባበርግዴታ</u>

ተቋሙ ሥልጣንና ተግባሩን ሥራ ላይ ለማዋል እንዲችል ማንኛውም ሰው አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት ይኖርበታል።

39.<u>መግለጫ ስለመስጠት</u>

1. ተቋሙ እንደአስፈላጊነቱ ይፋዊ መግለጫ ይሰጣል፡፡
2. ተቋሙ መደበኛ ሪፖርቶች ማቅረብን ጨምሮ አሠራሩን በሙሉ ለሕዝብ ግልጽ ማድረግ ይኖርበታል።
3. በዚህ አንቀጽ በንዑስ አንቀጽ (2) የተደነገገው ቢኖርም የአገሪቱ ጸጥታና ደኅንነት አደጋ ላይ እንዳይወድቅ ለማድረግ ወይም የግለሰቦችን የግል ሕይወት ሙብት ለመጠበቅ ሲባል በምስጢር ሊያዙ በሚገባቸው ጉዳዮች ላይ ተቋሙ ጥንቃቄ የመውሰድ ግዴታ አለበት።

40.<u>በስም ማጥፋት ስላለመጠየቅ</u>

1. በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበ አቤቱታ በስም ማጥፋት አያስጠይቅም።
2. ተቋሙ ስለሚያካሂደው ምርመራ ውጤት ምክር ቤቱ የሚያቀርበው ሪፖርት ወይም ሥራውን በማስመልከት የሚያደርገው ሌላ ዓይነት መጸጻፍ በስም ማጥፋት የሚያስጠይቅ አይሆንም።

41.<u>ስለ ቅጣት</u>

1. ማንኛውም ሰው በተቋሙ መጥሪያ ደርሶት ወይም በሌላ ሁኔታ ተጠርቶ በቂ ምክንያት ሳይኖረው በተወሰነ ጊዜ ውስጥ ካልቀረበ ወይም መልስ ካልሰጠ ወይም ሰነዶች ለማቅረብ ወይም ለማስመርመር ፈቃደኛ ካልሆነ ከአንድ ወር እስከ ስድስት ወር በሚደርስ እሥራት ወይም ከብር ሁለት መቶ እስከ ብር አንድ ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

2. በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ የበለጠ የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፤ ምሥክሮች ሆነው በቀረቡ ወይም ሰነድ ባቀረቡት ሰዎች ላይ ጥቃት ካደረሰ ወይም በተቋሙ በቀረቡ ሪፖርቶች፤ በተሰጡት የማሻሻያ አስተያየቶችና ሀሳቦች ላይ በሦስት ወር ጊዜ ውስጥ ያለበቂ ምክንያት እርምጃ ካልወሰደ ወይም እርምጃ የማይወስድበትን ምክንያት ካልገለጸ ከሦስት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ እሥራት ወይም ከብር ስድስት ሺ እስከ ብር አሥር ሺ በሚደርስ የገንዘብ መቀጫ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

42.<u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች</u>

ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በምክር ቤቱ መታየት የተጀመሩ የአስተዳደር ጥፋቶችን የሚመለከቱ አቤቱታዎች በተቋሙ ይታያሉ።

43.<u>ተፈጻሚነት ስለማይኖራቸው ሕጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም።

44.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ ከሰኔ 27 ቀን 1992 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሰኔ 27 ቀን 1992 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 449/1997

## የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ

የሕዝብ ቆጠራ ውጤት የሕዝቡን ኑሮ ለማሻሻል ለሚደረገው ሕገ መንግሥታዊ አደረጃጀትና ለፖለቲካዊ ሥርዓቱ ዝግጅት አስፈላጊ ስለሆነ፣

ትክክለኛውን የሕዝብ ብዛት ማወቅ በሀገር አቀፍ ወይም በተወሰነ የክልል አስተዳደር እርከን ደረጃ ለሚደረጉ ምርጫዎች አፈጻጸም አስተማማኝ መሠረት በመሆኑ፣

የተግባሩን አስፈላጊነት፣ ስፋት እና ውስብስብነት በማገናዘብ የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን እንደሚቋቋም በሕገ መንግሥቱ የተደነገገውን በሥራ ላይ ለማዋል ዝርዝር ሕግ ማውጣት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽንን ለማቋቋም ቀደም ሲል የወጣው አዋጅ ቁጥር 180/1991 በተግባር ሲታይ የሥራ ድግግሞሽን የሚፈጥር ሆኖ በመገኘቱ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ 103 እና አንቀጽ 55(1) መሠረት ከዚህ እንደሚከተለው ታውጇል፡፡

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽንን እንደገና ለማቋቋም የወጣ አዋጅ ቁጥር 449/1997" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "የሕዝብ ቆጠራ" ወይም "ቆጠራ" ማለት በሀገር አቀፍ፣ በክልል ወይም በተወሰነ የክልል አስተዳደር እርከን ስለሚገኘው ጠቅላላ የሕዝብ ብዛት፣ የጾታ፣ የእድሜ፣ የጋብቻ፣ የትምህርት ደረጃ፣ የሰው ኃይል፣ የሥራ ዓይነት፣ የሥራ መስክ፣ የልደት፣ የሞት፣ የፍልሰትና ሌሎች ተመሳሳይ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ መረጃዎችን የመሰብሰብ፣ የማጠናቀር፣ የመገምገምና የማሰራጨት ተግባር ነው፣
   2. "የቆጠራ ካርታ ሥራ" ማለት ማንኛውም ሰው ሳይቆጠር እንዳይቀር እንደዚሁም ከአንድ ጊዜ በላይ እንዳይቆጠር ለማድረግ የቆጠራው ክንዋኔ ከመጀመሩ በፊት የቆጠራ ቦታና የመቆጣጠሪያ ቦታ ካርታዎች ማዘጋጀት ነው፣
   3. "ምክር ቤት" የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብተወካዮች ምክር ቤት ነው፣
   4. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፣
   5. "ባለስልጣን" ማለት የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ባለሥልጣን ነው፣

3. <u>ስለመቋቋም</u>

1. የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን (ከዚህ በኋላ "ኮሚሽኑ" እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፣
2. ኮሚሽኑ ተጠሪነቱ ለምክር ቤቱ ይሆናል።

4. <u>ዓላማዎች</u>

የኮሚሽኑ አላማ ለአስተዳደራዊ ጉዳዮችና ለምርጫዎች፣ ለዕቅድ ዝግጅት፣ ለዕቅድ አፈጻጸም፣ ክትትልና ግምገማ እንዲሁም ለምርምር የሚጠቅሙ ሕዝብን የሚመለከቱ መረጃዎችን በቆጠራ መሰብሰብ፣ ማጠናቀር፣ መገምገምና ማሰራጨት፣ ይሆናል።

5. <u>የኮሚሽኑ አወቃቀር</u>

1. በሕገ-መንግሥቱ አንቀጽ 103 ንዑስ አንቀጽ (2) በተደነገገው መሠረት የኮሚሽኑ አባላት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በምክር ቤቱ ይሾማሉ፣
2. የኮሚሽኑ ሰብሳቢ የሚሆነው አባል የሚኒስትር ወይም ከዚያ በላይ ደረጃ ያለው የፌዴራል መንግሥት ሹም ሆኖ በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በምክር ቤቱ ተለይቶ ይሰየማል፣
3. የባለሥልጣኑ መሥሪያ ቤት የኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡ ባለሥልጣኑ ለሕዝብ ቆጠራ ጉዳይ ብቻ ተጠሪነቱ ለኮሚሽኑ ይሆናል፣
4. የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስኪያጅ የኮሚሽኑ አባልና ዋና ፀሐፊ ሆኖ ይሠራል።

6. <u>የኮሚሽኑ አባላት ስብጥር</u>

ኮሚሽኑ ለሕዝብ ቆጠራ ጉዳይ አግባብነት ካላቸው የፌዴራል ሚኒስቴር ሚኒስትሮች፣ ከምርጫ ቦርድ፣ ከፌዴሬሽን ምክር ቤት፣ ከዘጠኙ ክልሎች፣ ከአዲስ አበባና ከድሬዳዋ መስተዳድሮች የተውጣጡ አባላት ይኖሩታል፣

7. <u>የኮሚሽኑ ሥልጣንና ተግባር</u>

ኮሚሽኑ፡-

1. የሕዝብ ቆጠራ እንዲካሄድ በማድረግ የአገሪቱ የሕዝብ ብዛት በአገር አቀፍ፣ በክልል፣ በዞን፣ በወረዳ፣ በከተማ እንዲሁም በከተማና በገጠር ቀበሌዎች ተለይቶ በጾታና በዕድሜ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣
2. የቆጠራ ካርታ ሥራ እና የሕዝብ ቆጠራን በሚመለከት መመሪያ ያወጣል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣
3. ስለቆጠራ ካርታ ሥራ እንዲሁም ስለቆጠራ ምንነት ሕዝቡን ያሳውቃል፣

4. በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በክልል፣ በወረዳና አስፈላጊ ሆነው በሚያገኛቸው ተጨማሪ የአስተዳደር እርከኖች ደረጃ ሌሎች ኮሚሽኖችን በቆጠራ ማካሄጃ ወቅት ያቋቁማል፡ እንዲሁም ሥልጣንና ተግባራቸውን የአባላቱን አሰያየምና የስብሰባ ሥነ-ሥርዓታቸውን ይወስናል፣
5. ከፌዴሬሽን ምክር ቤት በሚቀርበው የብሔረሰቦች ዝርዝር መሠረት እና በሕዝብ ቆጠራ አማካኝነት የብሔረሰቦች ብዛትና ስርጭት እንዲታወቅ ያደርጋል፣
6. በየክልሉ በሚገኙት ዞኖች፣ ወረዳዎች፣ ከተማዎች እና የከተማና የገጠር ቀበሌዎች ውስጥ ያለው የእያንዳንዱ ብሔረሰብ የሕዝብ ቁጥር በጾታና በዕድሜ ተከፋፍሎ በገጠርና በከተማ ተለይቶ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣
7. በዚህ አዋጅ መሠረት በሚካሄደው ቆጠራ አፈፃፀም ሂደት በስፋቱና በዓይነቱ የቆጠራውን ውጤት ሊያዛባ የሚችል ግድፈት ስለመከሰቱ በቂ መረጃ ካገኘ ለምክር ቤቱ በማሳወቅ ውጤቱን ይሠርዛል፣ እንደገና ቆጠራ እንዲካሄድ ያዛል፣
8. የቆጠራ ውጤቶችን ያረጋግጣል፤ ለምክር ቤቱ ያቀርባል እንዲሁም ምክር ቤቱ ሲቀበለው ለሕዝብ በይፋ እንዲገለጽና በተለያዩ መንገዶችም እንዲሰራጭ ያደርጋል፣
9. የሕዝብ ቆጠራ በጀት ለመክር ቤቱ አቅርቦ ያስፈቅዳል፣ በትክክል በሥራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፡፡
10. ስለ ሥራ አፈፃፀሙ በየጊዜው ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባል።

8. <u>የኮሚሽኑ ስብሰባ</u>

1. ኮሚሽኑ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፣
2. ከኮሚሽኑ አባላት ውስጥ ከግማሽ በላይ የሚሆኑ በስብሰባ ላይ ሲገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፣
3. የኮሚሽኑ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ይሰጣሉ፣ ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል፣
4. የዚህ አንቀጽ ሌሎች ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው፣ ኮሚሽኑ የራሱን የስብሰባ ስነ-ስርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

9. <u>የኮሚሽኑ ሰብሳቢ ስልጣንና ተግባር</u>

የኮሚሽኑ ሰብሳቢ፣

1. የኮሚሽኑን ስብሰባ ይጠራል፣ ይመራል፣
2. የኮሚሽኑ ውሳኔዎች በስራ ላይ መዋላቸውን ያረጋግጣል፣

3. የህዝብ ቆጠራ ስራን በሚመለከት የኮሚሽኑን ጽህፈት ቤታ የስራ እንቅቃሴ በበላይነት ይቆጣጠራል፡፡

10. <u>የኮሚሽኑ ጽህፈት ቤት ስልጣንና ተግባር</u>

ጽህፈት ቤቱ የሚከተሉት ስልጣንና ተግባር ይኖሩታል

1. የቆጠራ ካርታ ስራ የማከናወን፣
2. የቆጠራ ዕቅድ አዘጋጅቶ ለኮሚሽኑ የማቅረብ፣
3. የቆጠራ ሥራ የማካሄድ፣ ለዚሁም አፈፃፀም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 7 (4) መሠረት የሚቋቋሙትን ሌሎች ኮሚሽኖች እንቅስቃሴ የመምራት የማስተባበርና የመቆጣጠር፣
4. ለቆጠራ አፈፃፀም የሚያስፈልጉ መጠይቆች፣ መመሪያዎችና ልዩ ልዩ ቅጾች እንዲሁም ቁሳቁሶች የማዘጋጀትና የማሠራጨት፣
5. ሕዝብን የሚመለከቱ መረጃዎችን ለመሰብሰብ አግባብ ያላቸውን ሰነዶችና መዛግብት የመመርመር፣ ምርመራውንም ለማከናወን ተገቢ በሆነ ጊዜ ወደ ማንኛውም ሰው ቤት ወይም ቅጥር ግቢ የመግባት፣
6. ለቆጠራ አፈፃፀም የማያስፈልገውን የሰው ኃይል የማሰልጠን፣
7. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 7 ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) መሠረት የቆጠራ ካርታ ሥራ ወይም ቆጠራ ለማካሄድ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው ለመንግስት አቅርቦ ሲፈቀድ በማንኛውም የመንግስት መስርያ ቤት ሰራተኞች ንብረት እና አገልግሎት የመጠቀም፣
8. የተሰበሰበውን የቆጠራ መረጃ ማደራጀት፣ መተንተንና ሪፖርቱን አዘጋጅቶ እንዲፀድቅ ለኮሚሽኑ የማቅረብ፣
9. በየጊዜው የሚደረገውን ቆጠራ አፈፃፀም የመገምገም እንዳስፈላጊነቱም የአሠራር ማሻሻያ ጥናቶች እንዲካሄዱ የማድረግ፣
10. በኮሚሽኑ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት ሌሎች አግባብ ያላቸውን ተግባሮች የማከናወን፡፡

11. <u>በጀት</u>

ኮሚሽኑ፣

1. በምክር ቤቱ በሚጸድቀው መሠረት ለቆጠራ የካፒታል በጀት ከመንግሥት ይመደብለታል፣
2. ለቆጠራ ማካሄጃ ከውጭ ዕርዳታ ሊጠይቅ ይችላል።

12. <u>ግዴታ</u>

1. ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ለቆጠራው ሥራ የመተባበር ግዴታ አለበት፣
2. በዚህ አዋጅ መሠረት ለቆጠራ መረጃ እንዲሰጥ የተጠየቀ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት ከኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን መታወቂያ ለሚያሳይ መረጃ ሰብሳቢ ወይም ተቆጣጣሪ ትክክለኛውን መረጃ የመስጠት ግዴታ አለበት፣
3. ማንኛውም የቤት ወይም የቅጥር ግቢ ባለንብረት፣ ባለ ይዞታ ወይም ጠባቂ ከኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት የተሰጠውን መታወቂያ ለሚያሳይ የቆጠራ መረጃ ሰብሳቢ ወይም ተቆጣጣሪ ወደተባለው ንብረት እንዲገባ የመፍቀድ ግዴታ አለበት።

13.<u>የመረጃዎች ሚስጥራዊነት</u>

በፍርድ ቤት ቤት በማስረጃነት እንዲያቀርብ ካልታዘዘ በስተቀር የኮሚሽኑ ጽሕፈት ቤት የሰበሰባቸውን ያልተጠቃለሉ የቆጠራ መረጃዎች በምሥጢር ይጠብቃል።

14.<u>ቅጣት</u>

በወንጀለኛ መቅጫ ህግ መሰረት የበለጠ ቅጣት የሚስከትል ካልሆነ በስተቀር ማንኛውም ሰው፣

1. የቆጠራ መረጃ ለመስጠት ፈቃደኛ ያልሆነ እንደሆነ እስከ ስድስት ወራት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል፡፡ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው የሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ሲሆን ከብር 2000 (ከብር ሁለት ሺ) በማይበልጥ ገንዘብ ይቀጣል፣
2. ይህንኑ በሚመለከት ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ ወይም በዚህ አዋጅ አንቀጽ 10 ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ወደተመለከተው ንብረት ገብቶ የቆጠራ መረጃ የማግኘት ሥራን ያሰናከለ እንደሆነ ጥፋተኛ ሆኖ ሲገኝ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ እሥራት ይቀጣል። ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘው በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ሲሆን ከብር 5000 (ከብር አምስት ሺህ ) በማይበልጥ ገንዘብ ይቀጣል።

15.<u>የተሻሩ እና ተፈጻሚ የማይሆኑ ህጎች</u>

1. የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 180/1991
2. ይህን አዋጅ የሚቃረን ማናቸውም ሌላ ሕግ፣ ደንብ፣ መመሪያ ወይም የአሠራር ልምድ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

16.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

ኮሚሽኑ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉትን ደንቦችና መመሪያዎች ለማውጣት ይችላል።

17.<u>**የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ**</u>

በአዋጅ ቁጥር 180/1991 መሠረት ተቋቁሞ የነበረው የሕዝብ ቆጠራ ኮሚሽን ጽህፈት ቤት መብትና ግዴታዎች ለባለሥልጣኑ ተላልፈዋል፡፡

18.<u>**ደንቡ የሚፀናበት ግዜ**</u>

ይህ አዋጅ ከግንቦት 18 ቀን 1997 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ ግንቦት 18 ቀን 1997 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 858/2006 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ

የብሮድካስት አገልግሎት ቴክኖሎጂ ከጊዜ ወደ ጊዜ እያደገና እየተሻሻለ በመምጣቱ ይህንኑ በአግባቡ ተጠቅሞ የሕዝቡን ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ ያለውን የብሮድካስት አገልግሎት አደረጃጀትና አሠራር ማሻሻል በማስፈለጉ፤

የሀገሪቱን ልማት፣ ሠላምና ዲሞክራሲ እና የሕዝባችን በእኩልነትና በመፈቃቀድ ላይ የተመሠረተ ዲሞክራሲያዊ አንድነት አጠናክሮ ለማስቀጠል የብሮድካስት አገልግሎት ሚና ከፍተኛ መሆኑን በመገንዘብ፤

የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን መንግሥትና ሕዝብን በማገናኘት የሕዝቡን የልማት ተሳታፊነትና የጋራ ተጠቃሚነት ለማረጋገጥ የሚጠበቅበትን ሚና በአግባቡ መወጣት እንዲችል እና በህብረተሰቡ መካከል ሐሳቦችና አመለካከቶች በሕገመንግሥቱ በተደነገገው መሠረት በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ የተቋምና የአሠራር ነፃነት እንዲሁም የተሻለ የሕግ ጥበቃ እንዲኖረው ማድረግ በማስፈለጉ፤

የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽንን በማቋቋም ተቋሙ የሚሰጠው አገልግሎት የበለጠ ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለውና ተወዳዳሪ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 858/2006" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

   1. "ሠራተኛ" ማለት የኮርፖሬሽኑ ጋዜጠኞች፣ የቴክኒክ ባለሙያዎች፣ ድጋፍ ሰጪ ሠራተኞች፣ ዳይሬክተሮችና በተዋረድ ያሉ የሥራ ኃላፊዎችን ያካትታል፤
   2. "ብሮድካስቲንግ" ማለት ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማሳወቅ ወይም ለማዝናናት በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በኢንተርኔት እና በተለያዩ የኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች አማካኝነት የሚከናወን የድምጽ እና የምስልና የድምጽ ስርጭት ነው፤

3. "ቦርድ" ማለት በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሾሙ አባላትን የያዘ ኮርፖሬሽኑን በበላይነት የሚመራ አካል ነው፤
4. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤
5. "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤
6. "ፕሮግራም" ማለት በድምጽ ወይም በምስል ወይም በሁለቱ ተቀነባብሮ ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት ወይም ሁሉንም አካቶ የሚቀርብ ስርጭት ነው፤
7. ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትንም ያካትታል።

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን

3. **መቋቋም**

1. የኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ከዚህ በኋላ "ኮርፖሬሽን" እየተባለ የሚጠራ የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ ህዝባዊ አገልግሎት የሚሰጥ የመንግስት ተቋም ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ኮርፖሬሽኑ ተጠሪነቱ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፡፡

4. **ዋና መሥሪያ ቤት**

የኮርፖሬሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በመላ አገሪቱ እና በውጭ አገራት በተለያዩ ሥፍራዎች ቅርንጫፎች እና ወኪሎች ሊኖሩት ይችላል፡፡

5. **የኮርፖሬሽኑ ዓላማ**

የኮርፖሬሽኑ ዓላማዎች፦

1. በመገናኛ ብዙኀንና በሌሎች አግባብ ባላቸው ሕጎችና ፖሊሲዎች መሠረት በአገር ውስጥና በውጭ አገር ስለሚፈጸሙ አበይትና ወቅታዊ ጉዳዮች እንዲሁም ትምህርታዊና አዝናኝ ዝግጅቶችን በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በድህረ-ገጽ በማቅረብ፤ ከሕዝቡም በግብረ-መልስ ሥርዓት ወይም በቀጥታ የሚገኘውን ግብዓት በመጠቀም ሕዝቡ በአገሪቱ በሚካሄዱ ሁለንተናዊ ጉዳዮች ላይ ግንዛቤ ኖሮት በአገር ልማት ንቁ ተሳታፊ እንዲሆን ማድረግ፤

2. ብሔራዊ መግባባት በመፍጠር አገራዊ ማንነትን፣ ብዝሃነትን፣ መቻቻልንና ዲሞክራሲያዊ አንድነትን ለመጠበቅና ለማጎልበት የሚደረገውን አገራዊ ጥረት ማገዝ ይሆናል፡፡

6. **<u>የኮርፖሬሽኑ ሥልጣንና ተግባር</u>**

ኮርፖሬሽኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. ለሕዝብ ጠቃሚና አስፈላጊ የሆኑ ዜናዎችና መዋዕለ-ዜናዎችን ማሰባሰብ፣ ማዘጋጀትና በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥንና በድህረ-ገጽ በልዩ ልዩ የአገር ውስጥና የውጭ ቋንቋዎች በማሠራጨት ለተገልጋዩ የማድረስ፣
2. ለልማት፣ ለመልካም አስተዳደርና ዲሞክራሲ ግንባታ ህብረተሰቡን የሚያነሳሱ ትምህርታዊና አሳዋቂ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፣ የመንግስትን ፖሊሲዎችና ሕጎች ለሕዝብ የማስተዋወቅ፤
3. ሕዝቡ ስለ ሰብአዊና ዲሞክራሲያዊ መብቶች ያለው ግንዛቤ እንዲዳብር የሚረዱ ፕሮግራሞችን የማቅረብ፤
4. ነጻ የህዝብ አስተያየቶችንና ጥቆማዎችን ተቀብሎ የማስተላለፍ፤
5. የሕዝቡን ዕውቀትና ፈጠራ የሚያዳብሩና የመዝናናት ፍላጎቱን የሚያረኩ ልዩ ልዩ ኘሮግራምችን የማቅረብ፤
6. በአገር ውስጥና ከውጭ ካሉ ተመሳሳይ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት የመመሥረት፤
7. ለክልል ብዙሃን መገናኛ ድርጅቶች የቴክኒክና ሥልጠና ድጋፍ የመስጠት፤
8. ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ የመወሰንና የመሰብሰብ፣ እንደ አስፈላጊነቱ በከፊል ወይም በሙሉ ከክፍያ ነጻ የማድረግ፤
9. የንብረት ባለቤት መሆን፣ ውል የመዋዋል፣ በስሙ የመክሰስና የመከሰስ፤
10. ዓላማውን ከግብ ለማድረስ ሌሎች ተዛማጅ ተግባራትን የማከናወን፡፡

7. **<u>የኮርፖሬሽኑ አቋም</u>**

ኮርፖሬሽኑ

1. ቦርድ፣
2. ዋና ሥራ አስፈጻሚ እና አስፈላጊ የሆኑ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች፤
3. አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞች፤

ይኖሩታል።

8. **<u>ስለቦርዱ</u>**

1. ቦርዱ አንድ ሰብሳቢ፣ አንድ ጸሐፊና ሰባት አባላት ያሉት ሆኖ የአባላቱ ቁጥር እንደ አስፈላጊነቱ ሊጨምር ይችላል፡፡

2. የቦርዱ ሰብሳቢና አባላት አግባብነት ካላቸው ተቋማትና ከልዩ ልዩ የህብረተሰብ ክፍሎች ተውጣጥተው በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማሉ።
3. የቦርዱ ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፡፡
4. የቦርዱ የሥራ ዘመን አምስት ዓመት ይሆናል፡፡
5. ዋና ስራ አስፈጻሚው የቦርዱ ጸሐፊና አባል ይሆናል፡፡
6. ቦርዱ የራሱ የአሠራር መመሪያ ያወጣል።

9. <u>የቦርዱ ሥልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. መገናኛ ብዙሃንን በሚመለከቱ የመንግሥት ፖሊሲዎች እና ሕጎች በኮርፖሬሽኑ ተግባራዊ መሆናቸውን የማረጋገጥ፤
2. በህዝብ መታወቅ ያለባቸው የመንግሥት ፖሊሲዎችና ሕጎች በወቅቱ መተላለፋቸውን የማረጋገጥ፤
3. ኮርፖሬሽኑ በሚሰጠው አገልግሎት ሕዝቡ ተጠቃሚ መሆኑን የመገምገም ይበልጥ ተጠቃሚ ስለሚሆንበት ሁኔታ ሐሳብ የማቅረብ፤
4. የተለያየ አመለካከት ያላቸው የፖለቲካ ድርጅቶችና የኅብረተሰብ ክፍሎች ሚዛናዊ የሆነ የሬዲዮና የቴሌቪዥን ፍትሐዊ አገልግሎት ማግኘታቸውን የማረጋገጥ፤
5. በሬዲዮ፣ በቴሌቪዥን፣ በኢንተርኔትና በሌሎች በኤሌክትሮኒክስ መሳሪያዎች የሚተላለፈውን ፕሮግራም ይዘት የመገምገም፣ ስለሚሻሻልበትም ሁኔታ ሐሳብ የማቅረብ፤
6. ከአድማጮና ከተመልካች በኮርፖሬሽኑ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የመመርመር፣ ተገቢውን ውሳኔ የመስጠት፤
7. የኮርፖሬሽኑን ሠራተኞች የቅጥር መመሪያ የማውጣት፣ ደመወዝ፣ አበልና ሌሎች ጥቅማጥቅሞቻቸው ላይ የመወሰን፣
8. ኮርፖሬሽኑ የሚጠናከርበትንና አሠራሩ የሚሻሻልበትን መንገድ የመቀየስ፤
9. የኮርፖሬሽኑን ዓመታዊ የሥራ ዕቅድና በጀት እንዲሁም የሥራ እቅስቃሴ ሪፖርት ገምግሞ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ፤
10. ኮርፖሬሽኑን በሚመለከቱ ሌሎች የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ የመምከር፤ የመወሰን፡፡

10. <u>የቦርዱ ስብሰባዎች</u>

1. ቦርዱ ቢያንስ በወር አንድ ጊዜ መደበኛ ስብሰባ ያደርጋል፡፡
2. አስቸኳይ ሁኔታ ሲያጋጥም በቦርዱ ሰብሳቢ ወይም ከቦርዱ አባላት መካከል ቢያንስ አንድ ሶስተኛው አባላት ከጠየቁ በማናቸውም ጊዜ ሊሰበሰብ ይችላል፡፡
3. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡
4. ቦርዱ ውሳኔ የሚያሳልፈው በድምጽ ብልጫ ይሆናል፣ ሆኖም ድምጽ እኩል ለእኩል የተከፈለ እንደሆነ ሰብሳቢው ያለበት ወገን ሐሳብ የቦርዱ ውሳኔ ሆኖ ያልፋል።
5. ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

11.<u>ስለኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ</u>

1. ዋና ሥራ አስፈጻሚው በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማል።
2. ዋና ሥራ አስፈጻሚው የኮርፖሬሽኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የኮርፖሬሽኑን ሥራ ይመራል፤ ያስተዳድራል።
3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ሥራ አስፈጻሚው፡-

   ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ለኮርፖሬሽኑ የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ሥራ ላይ ያውላል፣

   ለ/ የፕሮግራሞች ይዘት አቅጣጫን ያቅዳል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፤

   ሐ/ የኮርፖሬሽኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

   መ/ የኮርፖሬሽኑን ዓመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት እንዲሁም የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣

   ሠ/ ለኮርፖሬሽኑ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

   ረ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ኮርፖሬሽኑን ይወክላል፤

   ሰ/ ከቦርዱ የሚሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል።
4. ዋና ሥራ አስፈጻሚው ለኮርፖሬሽኑ የሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለኮርፖሬሽኑ የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች

በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፤ ሆኖም እርሱን ተክቶ የሚሠራው ከሠላሳ ቀናት ለሚበልጥ ጊዜ የሚሠራ ከሆነ ውክልናው አስቀድሞ ለቦርዱ ቀርቦ መፈቀድ ይኖርበታል፡፡

12.<u>ስለ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች</u>

1. የኮርፖሬሽኑ ምክትል ዋና ሥራ አስፈጻሚዎች በዋና ሥራ አስፈጻሚው አቅራቢነት በቦርዱ ይሾማሉ።
2. እያንዳንዱ ምክትል ዋና ስራ አስፈጻሚ ከዋናው ሥራ አስፈጻሚ በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በሥሩ የተመደበለትን ዘርፍ ሥራ ይመራል፣ ያስተባብራል፣ እንዲሁም ከዋና አስፈጻሚው የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

13.<u>ሪፖርት ስለማቅረብ</u>

ኮርፖሬሽኑ በሥልጣን ክልሉ ስለሚያከናውናቸው ተግባራት በየጊዜው ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል።

14.<u>የኮርፖሬሽኑ በጀት</u>

የኮርፖሬሽኑ በጀት ከሚከተሉት ምንጮች የተውጣጣ ይሆናል፦

1. በዚህ አዋጅ መሠረት ከሚሰበሰብ ገቢ፤
2. ለኮርፖሬሽኑ ዓላማ መሳካት ሲባል መንግሥት ከሚያደርግለት ድጋፍ፤
3. ከሌሎች ምንጮች፡፡

15.<u>ስለ ኮርፖሬሽኑ የግዢና የፋይናንስ ሥርዓት</u>

የኮርፖሬሽኑ የግዢና የፋይናንስ ሥርዓት በመንግሥት የልማት ድርጅቶች የግዢና የፋይናንስ ሥርዓት መሠረት ይሆናል፡፡

16.<u>የሂሳብ መዛግብት</u>

1. ኮርፖሬሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሳብ መዛግብትና የገንዘብ ሰነዶች ይይዛል፡፡
2. የኮርፖሬሽኑ የሂሳብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

<u>ክፍል ሦስት</u>

<u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

17.<u>ስለኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች አስተዳደር</u>

የኮርፖሬሽኑ ሠራተኞች አስተዳደር የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ይመራል፡፡

18.<u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል፡፡
2. ቦርዱ ለዚህ አዋጅ ማስፈጸሚያና ለተለያዩ የኮርፖሬሽኑ አሠራሮች የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

19.<u>የመብትና ግዴታዎች መተላለፍ</u>

የኢትዮጵይ ሬድዮና ቴሌቪዥን ድርጅት መብቶችና ግዴታዎች በዚህ አዋጅ ለኮርፖሬሽኑ ተላልፈዋል፡፡

20.<u>የተሻሩ ሕጎች</u>

የሚከተሉት ሕጎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡-

1. የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 114/1987 (እንደተሻሻለ)፤
2. የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት አዋጅ ቁጥር 15/1967፤ እና
3. የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት ደንብ ቁጥር 20/1967፡፡

21.<u>የመሸጋገርያ ድንጋጌዎች</u>

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 20 የተደነገገው ቢኖርም የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 114/1987 አንቀጽ 5(6) እና (9)፣ በኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት አዋጅ ቁጥር 15/1967 የቴሌቪዥን ምዝገባና ፈቃድን የተመለከቱ ድንጋጌዎች እና የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት ደንብ ቁጥር 20/1967 በሥራቸው የተዘረዘሩትን ተግባራት በሕግ ሥልጣን የሚሰጠው አካል እስከሚረከብ ድረስ ተፈጻሚነታቸው ይቀጥላል።

22.<u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥቅምት 29 ቀን 2007 ዓ.ም**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 982/2008

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን እንደገና ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር መንግሥት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ በማግኘት ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያለው በመሆኑ፤

በልዩ ልዩ የልማትና አስተዳደር መስኮች የተሰማሩ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የገንዘብ አስተዳደር ተገቢውን የሂሣብ አያያዝ ሥርዓት የተከተለ የገቢ አሰባሰባቸው የወጪ አፈቃቀዳቸውና የንብረት አስተዳደራቸው የመንግሥት ሕግንና መመሪያን ተከትሎ የተፈጸመ መሆኑንና ዕቅድና ፕሮግራማቸውንም በቅልጥፍና እና ኢኮኖሚያዊ በሆነ መንገድ በማከናወን የሚጠበቅባቸውን ግብ ማሟላታቸውን ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፤

በመንግሥት መዋቅር ውስጥ በሚገኙ ልዩ ልዩ የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ውስጥ ተጠያቂነትን፣ ግልጽነትን እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ኦዲት ዓይነተኛ መሣሪያ በመሆኑ፤

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የኢኮኖሚ ፖሊሲን በሚገባ ተግባራዊ ማድረግ ይቻል ዘንድ በፌደራላዊ መንግሥት ይዞታ ሥር የሚገኙ የአስተዳደር፣ የልማትና የአገልግሎት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች በብቃት ለመቆጣጠር በተጠናከረና ዘመናዊ በሆነ የኦዲት ተግባር መታገዝ ያለበት በመሆኑ፤

ለዚህ የፌዴራል ዋና ኦዲተሩንና የመ/ቤቱን የሙያ ነፃነት፣ አሠራርና አደረጃጀት ይበልጥ ማሻሻልና ማጠናከር በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ መንግስት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ ቁጥር 982/2008" ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

   በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

1. "ምክር ቤት" ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፤
2. "የፌዴራል ዋናው ኦዲተር" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 101 ንዑስ አንቀፅ (1) እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ 6 መሠረት የተሾመ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ዋናው ኦዲተር ነው፤
3. "መስሪያ ቤቱ" ማለት የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ነው፤
4. "የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤት" ማለት ሚኒስቴር፣ ኮሚሽን፣ ባለሥልጣን፣ ተቋም፣ ኤጀንሲ ወይም ማናቸውም ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፤
5. "ድርጅት" ማለት ማናቸውም በሙሉ ወይም በከፊል የፌዴራል መንግሥት የሆነ የማምረቻ፣ የማከፋፈያ፣ የአገልግሎት ሰጭ ወይም ሌላ የንግድ ድርጅት ነው፣
6. "የለጋሾችና አበዳሪዎች ሂሣብ" ማለት የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤት ወይም ድርጅት በዓይነት ወይም በጥሬ ገንዘብ ከለጋሹና ከአበዳሪዉ የተቀበለው ስጦታ፣ እርዳታ ወይም የብድር ሂሳብ ነው፤
7. "ሚኒስቴር" ማለት የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ነው፣
8. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተው ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፣
9. "ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ነው፣
10. በወንድ ጾታ የተገለጸው ማንኛውም ድንጋጌ የሴትንም ፆታ ይጨምራል።

3. <u>የፌዴራል ዋና ኦዲትር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002 ስለማሻሻል</u>

1. የፌዴራል ዋና ኦዲትር መሥሪያ ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 669/2002ን ለማሻሻል የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ከዚህ በኋላ "መሥሪያ ቤት"
2. እየተባለ የሚጠራ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 101(4) በተመለከተዉ መሠረት የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌዴራል መንግሥት አካል ሆኖ እንደገና ተቋቁሟል፣
3. የፌዴራል ዋና ኦዲተር ዋና መስሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ ለሥራው አስፈላጊ በሆነ ቦታ ሁሉ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤት ይኖረዋል።

4. <u>የመስሪያ ቤቱ ዓላማዎች</u>

መሥሪያ ቤቱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል:-

1. የፌዴራል መንግሥት ዕቅዶችና በጀት በሚገባ ለመምራትና ለማስተዳደር የሚያስፈልገውን አስተማማኝ መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የኦዲት ሥርዓትን ማጠናከር፤
2. የፌዴራል መንግሥት ገንዘብና ንብረት በወጡት ሕጎችና ደንቦች መሠረት መሰብሰቡን፣ መጠበቁን እና በአግባቡ ሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ እና የደረሰበትን ውጤት ለምክር ቤቱ ሪፖርት ማቅረብ፤
3. የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶች ላይ የፋይናንስ፣ የክዋኔ የአካባቢ ጥበቃ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ፣ የቁጥጥር ኦዲቶች፣ ልዩ ኦዲቶች እና ሌሎች ኦዲቶችን ማካሄድ፣
4. አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝና የኦዲት ሙያ እንዲያድግ እና እንዲጠናከር ጥረት ማድረግ፣
5. በሂሣብ አያያዝና በኦዲት ሙያ ላይ ለተሠማሩት የክልል እና የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ሙያዊ እገዛና ምክር መስጠት፤
6. የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች ሂሣብ የሚመረመርበትን የኦዲት ደረጃ (ስታንዳርድ) ማውጣትና ተግባራዊ መሆኑን መከታተል፣

## ክፍል ሁለት

## የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ስልጣንና ተግባር

### 5. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ስልጣንና ተግባር

የፌደራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት በሕግ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን የሚያስፈልገው ሥልጣን ሁሉ ይኖረዋል። በዚህ አጠቃላይ ድንጋጌ ሳይወሰን የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት:-

1. የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶችን ሂሣብ ኦዲት ያደርጋል፤ያስደርጋል፤
2. የፌደራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶች እና ድርጅቶችን የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሥርዓት፣ አጠቃቀምና አስተዳደር ኦዲት ያደርጋል፤ ያስደርጋል፤
3. የፌዴራል መንግሥት መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች ያስገኙት ውጤት ሕጉን የተከተለ፣ ኢኮኖሚያዊ በሆነ አሠራር የተፈጸመ መሆኑንና ተፈላጊውን ግብ መምታቱን ለማረጋገጥ እንደአስፈላጊነቱ የክዋኔ ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤
4. የመንግሥትንና የሕዝብን ጥቅም ለማስጠበቅ ሲባል የግል ወይም የሕዝባዊ ድርጅቶችን ኦዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤

5. ለፌዴራል መንግሥቱ መሥሪያ ቤቶችና ድርጅቶች የተለገሱ እርዳታዎችን ወይም ስጦታዎችን፣ እንዲሁም ብድርን አዲት ያደርጋል፣ ያስደርጋል፤

6. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጾች (1)፡ (2)፡ (3)፡ (4) እና (5) በተመለከተው መሠረት ያከናወነውን የኦዲት ውጤት እንደነገሩ ሁኔታ ለመሥሪያ ቤቱ ወይም ለድርጅቱ የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል። የፌዴራል ዋና ኦዲተሩ የምርመራው ውጤት ወንጀል መፈጸሙን የሚያሳይ ሆኖ ሲገኝ ለሚመለከተው አካል ወዲያውኑ ያሳውቃል፤

7. ጉዳዩ ከሚመለከታቸው መሥሪያ ቤቶች ጋር በመመካከር የሂሣብና የንብረት ኦዲት ሥርዓትና ደረጃን የሚመለከቱ መመሪያዎችን ያወጣል፤

8. አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው የማናቸውም ፌደራል መሥሪያ ቤት የውስጥ ኦዲተሮች የመሥሪያ ቤታቸውን ሂሣብና ንብረት በመመርመር ውጤቱን እንዲገልጹለት ሊያደርግ ይችላል፤

9. ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር እንደአስፈላጊነቱ ለውስጥ ኦዲተሮች ስልጠና ይሰጣል፤

10. አንድ ሂሣብ ወንጀል ባለበት ሁኔታና ታማኝነት በጎደለው አኳኋን መያዙን ለማመን ምክንያት ያለው እንደሆነ ይህንን ሂሣብ የሚመለከቱ ጽሑፎች፣ መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች ላይ ያሽጋል፤

11. የገንዘብና የኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር ስለገንዘብ አጠባበቅ የሂሣብ አያያዝና የንብረት አስተዳደር በተመለከተ በሚያዘጋጀው መመሪያዎች ላይ አስፈላጊውን ምክር ይሰጣል፤

12. ከሌሎች ጉዳዩ ከሚመለከታቸው የፌዴራል መንግሥትና የክልል መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር የሂሣብ አያያዝ እና የኦዲት ሙያ ትክክለኛውን ፈር ይዞ እንዲዳብር ጥረት ያደርጋል፤

13. ከክልል የኦዲት መ/ቤቶች እና ቁጥጥር ቢሮዎች ጋር የኦዲት ተግባር የሚዳብርበትን ሁኔታ በተመለከተ የቅርብ የሥራ ግንኙነትና ትብብር ያደርጋል፤

14. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2)፣ (3)፣ (5)፣ (6) እና (7) መሠረት የብቃት ማረጋገጫ የተሰጣቸውን ኦዲተሮች በመመልመል ኦዲት ሲያስደርግ ኦዲቱ ደረጃውን የጠበቀ ስለመሆኑ የመቆጣጠርና የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት። ዝርዝር አፈተጻጸሙን በተመለከተ የፌደራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት መመሪያ ያወጣል፤

15. የኦዲት ሙያተኞች ማሰልጠኛ ማዕከል ያደራጃል፡፡

## ክፍል ሦስት

6. **የፌዴራል ዋና ኦዲተር አሿሿምና ተጠሪነት**

   1. የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤትን የሚመራ ዋና ኦዲተር በጠቅላይ ሚኒስትሩ አቅራቢነት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሾማል፤
   2. የፌዴራል ዋና ኦዲተር ተጠሪነት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይሆናል፡፡ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሥራ ላይ በማይሆንበት ጊዜ ተጠሪነቱ ለፌዴራል ሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ይሆናል።

7. **ስለምክትል ዋና ኦዲተሮች አሿሿም**

የፌደራል ዋና ኦዲተርን የሚረዱ በጠቅላይ ሚኒስቴሩ አቅራቢነት በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚሾሙ አራት የፌደራል ምክትል ዋና ኦዲተሮች ይኖራሉ፡፡ እነዚህም የሬጉላሪቲ ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት፣ የኦዲት ጥራት፣ ምርምርና ስልጠና እና የድጋፍ አገልግሎቶች ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተሮች ናቸዉ፡፡

8. **ለሹመት የሚያበቁ መመዘኛዎች**

ለሹመት የሚያበቁ መመዘኛዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

   1. ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ፣
   2. ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ተገዥ የሆነ፣
   3. በኦዲት ሥራ ወይም አግባብነት ባለው ሌላ ሙያ የሰለጠነ እና በመንግሥት የኦዲት ሥራ ሰፊ እውቀትና ልምድ ያለው፣
   4. በታታሪነቱ፣ በታማኝነቱ እና በሥነ ምግባሩ መልካም ስም ያተረፈ፣
   5. በወንጀል ጥፋት ተከሶ ያልተፈረደበት፣
   6. ሥራዉን ለመሥራት የሚያስችል የተሟላ ጤንነት ያለው፣
   7. ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ገለልተኛ የሆነ።

9. **ተመድቦ ስለመስራት**

ተሿሚዎቹ በሥራ ዘመናቸው ማብቂያ ላይ እድሜያቸው ለጡረታ ያልደረሰ ከሆነ በመንግሥት መሥሪያ ቤቶች ወይም ድርጅቶ ውስጥ ተመድበው እንዲሰሩ ሁኔታዎች ይመቻቹላቸዋል።

10. **የስራ ዘመን**

   1. የዋና ኦዲተሩና ምክትሎቹ የሥራ ዘመን ስድስት ዓመት ይሆናል፤
   2. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለጸው የሥራ ዘመን ካበቃ በኋላ የዋና ኦዲተሩና ምክትሎቹ እንደገና ሊሾሙ ይችላሉ።

11. **ተሿሚዎች ከኃላፊነት የሚነሱበት ሁኔታ**

ዋና ኦዲተርና ምክትል ዋና ኦዲተሮች በሚከተሉት ሁኔታዎች ከኃላፊነት እንዲነሱ ሊደረግ ይችላል፦

1. በሕመም ምክንያት ሥራውን በሚገባ ለማከናወን የማይችል መሆኑ ሲረጋገጥ፤
2. ግልፅ የሆነ የሥራ ችሎታ ማነስ መኖሩ ሲረጋገጥ፤
3. በሥራው ላይ በሚያሳየው ቸልተኝነት ጥፋተኛ ሲሆን ወይም ምግባረ ብልሹ ሆኖ ሲገኝ፤
4. ሙስና መሥራቱ ወይም ህግን የሚፃረር ሌላ ድርጊት መፈጸሙ ሲረጋገጥ፤
5. የጡረታ ዕድሜ ላይ ሲደርስ፤
6. የሥራ ዘመኑ ሲያበቃ፤
7. ቀጣይነት ባለው የጤና ጉድለት ወይም በሌላ ምክንያት በገዛ ፍቃዱ ሥራውን ለመልቀቅ በጽሁፍ ሲጠይቅ፤
8. ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 4 እና 7 ያሉት ተፈጻሚ የሚሆኑት ከምክር ቤቱ አባላት መካከል በሚቋቋም ኮሚቴ ተጣርቶ ሲረጋገጥና ለምክር ቤቱ ቀርቦ በሁለት ሶስተኛ ድምፅ የምክር ቤቱን ውሳኔ ሲያገኝ ይሆናል።

12.<u>ክፍት ቦታ</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 11 ውስጥ በተገለጹትና በሞት ምክንያት የፌዴራል ዋና ኦዲተር በሌለ ጊዜ የሬጉላሪቲ ኦዲት፣ የክዋኔ ኦዲት እና የኦዲት ጥራትና ምርምርና ስልጠና ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተሮች በቅደም ትክተል ከሦስት ወር ላልበለጠ ጊዜ ተክቶ ይሠራሉ፣
2. የኦዲት ዘርፎችን የሚመሩ ምክትል ዋና ኦዲተሮች በሌሉ ጊዜ የድጋፍ አገልግሎቶች ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተር በንዑስ አንቀጽ 1 ለተጠቀሰው ጊዜ የፌዴራል ዋና ኦዲተሩን ተክቶ ይሠራል፤
3. የፌዴራል ዋና ኦዲተርና የምክትል ዋና ኦዲተሮች ቦታ በተመሣሣይ ጊዜ ክፍት የሆነ እንደሆነ የምክር ቤቱ አፈጉባዔ ከኦዲት ዳይሬክተሮች አንዱን በንዑስ አንቀጽ 1 ለተጠቀሰው ጊዜ መድቦ ሊያሠራ ይችላል፡፡

## <u>ክፍል አራት</u>

## <u>የፌዴራል ዋና ኦዲተርና የፌዴራል ምክትል ዋና ኦዲተሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

13.<u>የፌዴራል ዋና ኦዲተር ሥልጣንና ተግባር</u>

የፌዴራል ዋና ኦዲተር የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት የበላይ ኃላፊ በመሆን በዚህ አዋጅ አንቀፅ 5 ለመሥሪያ ቤቱ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በሥራ ላይ ከማዋል በተጨማሪ ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

1. በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2)፣ (3)፣ (4)፣ (5) እና (6) መሠረት ስለሚከናወነው ምርመራና ስለመሥሪያ ቤቱ ሥራዎች አጠቃላይ ዓመታዊ ሪፖርት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል። ምክር ቤቱ በሥራ ላይ በማይሆንበት ጊዜ ለፌዴራል ሪፐብሊኩ ፕሬዚዳንት ያቀርባል፤
2. የገንዘብና ኢኮኖሚ ትብብር ሚኒስቴር የፌዴራል መንግሥት ያለፈውን በጀት ዓመት ገቢና ሂሳብ፣ ሀብትና ዕዳ እንዲሁም የመንግሥት ገንዘብ ነክ የሆኑ መረጃዎችን የሂሣብ መግጫዎች የበጀት ዓመት እንደተጠናቀቀ በስድስት ወር ውስጥ ዘግቶ ለምርመራ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር ይልካል።
3. ዋና ኦዲተሩም የሒሳብ ዘገባው በደረሰው በ4 ወር ጊዜ ውስጥ ምርምራ በማድረግ ሪፖርቱን ከነአስተያየቱ ለሚኒስቴሩ ይልካል፤ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያቀርበው ዓመታዊ ሪፖርት ውስጥ ሪፖርቱ እንዲካተት ያደርጋል፤
4. በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ንዑስ አንቀጽ 7 መሠረት ጉጤቱን እንዲያውቁ የተደረጉት አካላት የሰጡት አስተያየትና ያቀረቡት ተቃውሞ አጥጋቢ ያለመሆኑን የገመተ እንደሆነ ይህን በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተጠቀሰው ሪፖርት ውስጥ ያስገባል፤
5. ተግባሩን በሚገባ ለማከናወን በሚያስችል አኳኋን መሥሪያ ቤቱን ያደራጃል፤
6. የመሥሪያ ቤቱን በጀት አዘጋጅቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤
7. የመ/ቤቱን መዋቅርና የደመወዝ ስኬል በማዘጋጀትና በሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት በማፀደቅ የሠራተኞችን ደመወዝና የጥቅማ ጥቅሞቻቸውን ክፍያ ይፈጽማል፤ ዝርዝር አፈጻጸሙን በተመለከተ ምክር ቤቱ ደንብ ያወጣል።
8. በፌዴራል ፐብሊክ ሠርቪስ ህግና ደንብ ውስጥ የተመለከቱትን መሠረታዊ ዓላማዎች ጠብቆ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ መሠረት ለመስሪያ ቤቱ አስፈላጊ የሆኑ የሠራተኞችን ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፤
9. ለሥራው አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በቂ መመሪያ በመስጠትና በመቆጣጠር የኦዲት ሥራ እንደአግባቡ በግል ኦዲተሮች ወይም በሌሎች ባለሙያዎች እንዲከናወን ይወክላል፤
10. በሀገሪቱ የመንግሥት ኦዲት በአነስተኛ ወጪ የሚካሄድበትንና በርካታ ክልሎችንና መስሪያ ቤቶችን ሊያሳትፉ የሚችሉ ተሸጋጋሪ ኦዲቶችን ከሚመለከተዉ ጋር በመመካከር ያከናውናል።

14. <u>የፌዴራል ምክትል ዋና ኦዲተሮች ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የሬጉላሪቲ ኦዲት ሥራዎች ዘርፍ ምክትል ዋና ሥልጣን እና ተግባር፦

ሀ/ የመሥሪያ ቤቱን የሬጉላሪቲ ኦዲት ሥራዎች በማቀድ፣ በማደራጀት፤ በመምራት በማስተባበር እና በመቆጣጠር የፌዴራል ዋና ኦዲተሩን ይረዳል፤

ለ/ ለምክር ቤቱ በሚቀርቡት የመንግሥት ሂሣብ ዘገባ (የተጠቃለለ ፈንድ ሂሣብ) የመሥሪያ ቤቱን ሥራዎች የሚያመለክት ዓመታዊ ዘገባና ልዩ ዘገባዎች ከመፈረም በስተቀር የፌደራል ዋና ኦዲተር በሌለ ጊዜ ተክቶት ተግባራቱን ያከናውናል፣

ሐ/ በፌዴራል ዋናው ኦዲተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

2. የክዋኔ ኦዲት ሥራዎች ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተር ሥልጣን እና ተግባር፦

ሀ/ የመሥሪያ ቤቱን የክዋኔ ኦዲት ሥራዎች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት፣ በማስተባበር እና በመቆጣጠር የፌዴራል ዋና ኦዲተሩን ይረዳል፤

ለ/ ለምክር ቤቱ በሚቀርቡት የመንግሥት ሂሣብ ዘገባ (የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ)፣ የመሥሪያ ቤቱን ሥራዎች የሚያመለክት ዓመታዊ ዘገባና ልዩ ዘገባዎች ከመፈረም በስተቀር የፌዴራል ዋና ኦዲተር በሌለ ጊዜ ተክቶት ተግባራቱን ያከናውናል፤

ሐ/ በፌዴራል ዋናው ኦዲተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

3. የኦዲት ጥራት፣ ምርምርና ሥልጠና ሥራዎች ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተር ሥልጣን እና ተግባር፦

ሀ/ የመሥሪያ ቤቱን የኦዲት ጥራት፣ ምርምርና ሥልጠና ሥራዎች በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት፣ በማስተባበር እና በመቆጣጠር የፌዴራል ዋና ኦዲተሩን ይረዳል፣

ለ/ ለምክር ቤቱ በሚቀርቡት የመንግሥት ሂሣብ ዘገባ (የተጠቃለለ ፈንድ ሂሳብ)፣ የመሥሪያ ቤቱን ሥራዎች የሚያመለክት ዓመታዊ ዘገባና ልዩ ዘገባዎች ከመፈረም በስተቀር የፌዴራል ዋና ኦዲተር በሌለ ጊዜ ተክቶ ተግባራቱን ያከናውናል፣

ሐ/ በፌዴራል ዋናው ኦዲተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

4. የድጋፍ አገልግሎቶች ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተር ሥልጣንና ተግባር፦

ሀ/ የመሥሪያ ቤቱን የድጋፍ አገልግሎቶች ዘርፍ ስራን በማቀድ፣ በማደራጀት፣ በመምራት፣ በማስተባበር እና በመቆጣጠር የፌዴራል ዋና ኦዲተሩን ይረዳል፣

ለ/ ለምክር ቤቱ በሚቀርቡት የመንግሥት (ሂሣብ ዘገባ የተጠቃለለ ፈንድ)፣ የመሥሪያ ቤቱን ሥራዎች የሚያመለክት ዓመታዊ ዘገባና ልዩ ዘገባዎች ላይ

ከመፈረም በስተቀር ዋና ኦዲተሩ እና የኦዲት ሰራዎች ዘርፍ ምክትል ዋና ኦዲተሮች በሌሉ ጊዜ በመተካት ተግባራቱን ያከናውናል፣

ሐ/ በፌዴራል ዋናው ኦዲተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል።

## ክፍል አምስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 15.በጀትና ሂሳብ ምርመራ

1. ለፌዴራል ዋና ኦዲትር መሥሪያ ቤት ከተፈቀደው በጀት ውስጥ የየሶስት ወር ድርሻ የሆነው የሥራ ማስኬጃ በፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት ስም በተከፈተው የባንክ ሂሣብ ውስጥ በአንድ ጊዜ በቅድሚያ እንዲቀመጥ ይደረጋል።
2. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መስሪያ ቤት ሂሳብ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ምክር ቤቱ በስራ ላይ በማይሆንበት ጊዜ በፌዴራል ሪፐብሊኩ ፕሬዝዳንት በሚሰየም ገለልተኛ ኦዲተር ይመረመራል፡፡

### 16.ስለኦዲት ስርዓት ወሰን እና የጊዜ ገደብ

1. የፌዴራል ዋና ኦዲተር አንድን ሂሳብ ኦዲት ሲያደርግ እንደነገሩ ሁኔታ አንድ በአንድ፣ በዝርዝር ወይም በአልፎ አልፎ የኦዲት ዘዴ ሊመረምር ይችላል፡፡ ቢሆንም በዚህ አዋጅ አንቀፅ (13) ንዑስ አንቀፅ (1) እና (2) መሰረት ሂሳቦችን ኦዲት አድርጎ በሚያቀርበው ዘገባ ውስጥ ለእያንዳንዱ ሂሳብ ያመራመሩን ሁኔታና ጥልቀት መግለፅ አለበት፡፡
2. የፌዴራል ዋና ኦዲተር የሚያደርጋቸው ምርመራዎች ከሚመረመረው የበጀት ዓመት ወደ ኋላ ከሁለት በጀት ዓመታት ማለፍ የለባቸውም፡፡ ነገር ግን በእርሱ ግምት ወንጀል መፈጸሙን ያመነ እንደሆነ ከተባሉት ሁለት የበጀት ዓመት ወደ ኋላ አልፎ ሊመረምር ይችላል፡፡
3. የፌዴራል ዋና ኦዲተር የሂሳብ ምርመራ ሲያደርግ በዓለም አቀፍ የመንግስት የኦዲት ደረጃዎች መሰረት ይሆናል፡፡

### 17.የተመርማሪዎች ግዴታ

1. የፌዴራል ዋና ኦዲተር፣ የመስሪያ ቤቱ ኦዲተሮች ወይም የፌዴራል ዋና ኦዲተር ወኪሎች ለምርመራ ጠቃሚና አስፈላጊ የሚመስሏቸውን መጻሕፍት፣ መዘክሮች፣መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች የጽሑፍና የቃል መረጃዎች ሁሉ ሲጠይቁ የተጠየቀው ግለሰብ፣ ሠራተኛ ወይም ባለስልጣን በትክክልና በተሟላ አኳኋን ወዲያውኑ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

2. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መሥሪያ ቤት እንዲቆጣጠራቸው በዚህ አዋጅ ሥልጣን የተሰጠው አካላትን ገንዘብ ወይም ንብረት የተረከበ፣ ወጪ ያደረገ፣ የከፈለ ወይም ለሂሳቡ ኃላፊ የሆነ ማኛውም ሰው ሲጠየቅ ሂሳቡን ኦዲት የማስደረግ ግዴታ አለበት፡፡

3. ተመርማሪ መስሪያ ቤቶች በፌዴራል ዋና ኦዲተር በተላኩ ሪፖርቶች በተገለፁ ግኝቶች ላይ ተገቢውን የእርምት እርምጃ እንዲወስዱ በተሰጡ የማሻሻያ ሃሳቦችና አስተያየቶች መሰረት ከ15 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ አለባቸው፡፡ የወሰዱትን እርምጃ እና ለመውሰድ ካልቻሉ ምክንያቱን በመግለፅ ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር መስሪያ ቤት ከላይ በተጠቀሰው ጊዜ ገደብ ውስጥ ማሳወቅ አለባቸው፡፡

4. የፌዴራል ዋና ኦዲተር ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በሚያቀርበው ሪፖርት ውስጥ ድክመት የታየባቸው መስሪያ ቤቶች ኃላፊዎች በታዩት ድክመቶች ላይ አስፈላጊውን የማስተካካያ እርምጃ ወስደው ይህንኑ ለምክር ቤቱና ለፌዴራል ዋናው ኦዲተር የማሳወቅ ግዴታ አለባቸው፡፡

5. ማንኛውም ተመርማሪ የፌዴራል ዋና ኦዲተር ተግባርና ኃላፊነቱን ለመወጣት ይቻለው ዘንድ የመደበው ኦዲተር ስራውን ለማካሄድ የሚያስችለውን ቢሮ አዘጋጅቶ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 18. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

መስሪያ ቤቱ ስልጣኑንና ተግባሩን ስራ ላይ ለማዋል እንዲችል ማንኛውም መስሪያ ቤት እና ሰው አስፈላጊውን ድጋፍ የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

## 19. <u>የኦዲት ባለሙያዎች የሙያ ሰነ-ምግባርና የሙያ ከለላ</u>

1. የመ/ቤቱ ኦዲተሮች ዋና ኦዲተሩ የሚያወጣውን የሙያ ሥነ-ምግባር አክብረው የመስራት ግዴታ አለባቸው፡፡

2. ዋና ኦዲተሩ፣ ምክትል ዋና ኦዲተሮችና ኦዲተሮች የሀገሪቱን ህግና የሙያ ስነ-ምግባር እና ዓለም አቀፍ መንግስት ኦዲት ደረጃዎችን አክብረው በሚያከናውኑት የኦዲት ስራዎች ምክንያት አይከሰሱም፡፡

3. ለሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ስራ ተዘጋጅተው በዋና ኦዲተሩ የሚቀርቡ ሪፖርቶች እንደ ሕዝብ ተወካዮች ሪፖርቶች አካል ሆነው ይቆጠራሉ፡፡ በእነኚህ ሪፖርቶች መነሻነት በዋና ኦዲተር ላይ ምንም ዓይነት የፍትሐ ብሔርም ሆነ የወንጀል ክሶች አይመሠረቱም፡፡

## 20. <u>የማሳወቅ ግዴታ</u>

1. የፌዴራሉ ዋና ኦዲተር ኦዲት ሲያከናውን በጉዳዩ ላይ ወንጀል መሰራቱን ያመነ እንደሆነ ይህንኑ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ ለጠቅላይ አቃቤ ህግ እና ለሌሎች ጉዳዩ ለሚመለከተው ኦዲት ተደራጊ መስሪያ ቤት ወይም ድርጅት የበላይ ኃላፊ ያሳውቃል፡፡
2. የሚከተሉት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙ ሳይዘገይ ለፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ሊገለጽለት ይገባል፤
   ሀ/ የፌዴራሉ መንግስት ባለስልጣኖች በጀት እያያዝን ወይም ከመንግስት ደረሰኝና ክፍያ ጋር የተያያዙ ጠቅላላ ደንቦችን ወይም መመሪያዎችን ሲያወጡ ወይም ሲተረጉሙ፤
   ለ/ የፌዴራል መንግስቱን የሚመለከቱ ስምምነቶች ሲመሰረቱ፣ መሰረታዊ ለውጥ ሲደረግባቸው ወይም ሲቋረጡ፣
   ሐ/ በክልል መንግስት እና ከፌዴራል አስተዳደር ውጭ ባሉ አካላት ወይም በክልል ባለስልጣናት መካከል የፌዴራል መንግስቱን የበጀት አስተዳደር የሚመለከቱ ስምምነቶች ሲፈፀሙ፤
   መ/ የፌዴራሉ መንግስት ባለስልጣናት በፋይናንስ አሰተዳደር ሥርዓቱ ላይ መሠረታዊ ለውጥ ሊያስከትሉ የሚችሉ ድርጅታዊ ወይም ሌሎች እርምጃዎችን በሥራ ላይ ለማዋል ሲያቅዱ፡፡

21. <u>ጥፋትና ቅጣት</u>

1. ማንኛውም ሰው፡-
   ሀ/ የፌዴራል ዋናዉ ኦዲተር በቀጥታ ወይም በኦዲተሮቹ ወይም በወኪሎቹ አማካኝነት ለምርመራ እንዲቀርብለት የሚጠይቀዉን መጻሕፍት፣ መዘክሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሊሎች የጽሑፍ ወይም የቃል መረጃዎች ያላቀረበ፣ ወይም
   ለ/ ለፌዴራል ዋናዉ ኦዲተሩ፣ ለመሰሪያ ቤቱ ኦዲተሮች ወይም ለወኪሎች ሀሰተኛ መሆኑ እያወቀ ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ ወይም እዉነተኛ መሆኑን ለማመን ምክንያት ሳይኖረዉ መረጃ የሰጠ፣ ወይም
   ሐ/ የፌዴራል ዋናዉ ኦዲተር ስራ በሚገባ እንዳይከናወን ያሰናከለ፣ ወይም
   መ/ ያለበቂ ምክንያት በፌዴራል ዋናዉ ኦዲተሩ በቀረቡ ኦዲት ሪፖርቶች በተሰጡ የማሻሻያ አስተየየቶችና ሐሳቦች ላይ በወቅቱ ርምጃ ያልወሰደ፣ ወይም በዚህ አዋጅ በተደነገገዉ መሰረት መፈጸም ሲኖርበት ለመፈጸም ፈቃደኛ ሆኖ ያልተገኘ፣

እንደሆነ ከአምት እስከ ሰባት አመት በሚደርስ እሰራት ወይም ከብር 10,000 እሰከ ብር 30,000 (አስር ሺ ብር እስከ ሰላሰ ሺ ብር) የገንዘበ መቀጫ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

2. ማንኛዉም ኦዲተር፡-

ሀ/ የስራ ግዴታዉን ለመፈጸም ወይም በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የሚገባውን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የማይገባውን ለማድረግ ስጦታን፣ ገንዘብ ወይም ሌላ ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ የተስፋ ቃል የተቀበለ ወይም የቀረበለትን የወሰደ፤ ወይም

ለ/ ለሚያደርገው የሂሣብ ምርመራ ተመርማሪው ያቀረበለት ሰነድ ሐሰተኛ መሆኑን እያወቀ እንደትክክለኛ ሰነድ ከያዘለት ወይም ትክክለኛነቱን እያወቀ ሊይዝለት የሚገባውን በሰነድ ሳይቀበለው የቀረ፣ ወይም

ሐ/ የፌዴራል መንግሥት ገንዘብ ያጭበረበረ ወይም ሌላ ሰው እንዲያጭበረብር ሁኔታዎችን በማመቻቸት የተባበረ ወይም ያሴረ፣ ወይም

መ/ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለራሱ ለማገኘት ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት ወይም ሌላ ሰውን ለመጉዳት በማሰብ፣ በተመርማሪው የቀረበለትን መጽሐፍት፣ መዘከሮች፣ መዝገቦች፣ ሰነዶችና ሌሎች ማናቸውንም መረጃዎች እንዲጠፉ ያደረገ ወይም ወደ ሐሰት የለወጠ ወይም እንዲለወጡ ያደረገ፤

አንደሆነ ከአምስት እስከ አሥር ዓመት በሚደርስ እሥራት እና ከብር 10,000 እስከ ብር 40,000 (ከብር አሥር ሺህ እስከ ብር አርባ ሺ) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል፡፡

22. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

1. የሕዝብ ተወካዮች ም/ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም አስፈላጊ የሆነ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፤

2. የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤት ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

23. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የማይኖራቸዉ ህጎች</u>

1. የፌዴራል ዋናው ኦዲተር መሥሪያ ቤትን ለማቋቋም የወጣው አዋጅ ቁጥር 669/2002 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

2. ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር በዚህ አዋጅ በተጠቀሱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖራቸውም፡፡

24. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

**አዲስ አበባ መስከረም 11 ቀን 2008 ዓ.ም.**

**ዶ/ር ሙላቱ ተሾመ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

መ/ <u>የሪፐብሊኩ ፕሬዝዳንት</u>

## <u>አዋጅ ቁጥር 131/1991</u>

## <u>የፕሬዚዳንቱ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ</u>

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት ጽ/ቤትን ማቋቋም አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55 ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

1. <u>አጭር ርዕስ</u>

   ይህ አዋጅ "የፕሬዚዳንቱ ጽሕፈት ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 131/1991" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. <u>ትርጓሜ</u>

   በዚህ አዋጅ ውስጥ "ፕሬዚዳንት" ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ርዕስ ብሔር ነው::

3. <u>መቋቋም</u>

   1. የፕሬዚዳንቱ ጽሕፈት ቤት (ከዚህ በኋላ "ጽሕፈት ቤቱ" ተብሎ የሚጠራ) እራሱን የቻለና ሕጋዊ ሰውነት ያለው አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል::
   2. የጽሕፈት ቤቱ ተጠሪነት ለፕሬዚዳንቱ ይሆናል፡፡

4. <u>የጽሕፈት ቤቱ ሥልጣንና ተግባር</u>

   ጽሕፈት ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

   1. በሕገ-መንግሥቱና በሌሎች ሕጎች መሠረት ለፕሬዚዳንቱ ለተሰጡ ሥልጣንና ተግባሮች አፈጻጸም ቀልጣፋ የአሠራር ሥርዓት መዘርጋት፤
   2. በሀገሪቱ ውስጥ እንዲሁም በዓለም አቀፍና አህጉራዊ ደረጃ ስለሚካሄዱ አበይት ፖለቲካዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ እንቅስቃሴዎች አግባብ ካላቸው ጋር በመተባበር ወቅታዊ መረጃ ማሰባሰብ፤ አጠናቅሮ ማቅረብ፤
   3. ፕሬዚዳንቱ በቴሌቪዥንና በሬድዮ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች በተወሰነ ወቅት የሚያስተላልፉትን ሀገራዊ መልዕክት፣ በሕዝብ ተወካዮችና በፌዴሬሽን ምክር ቤቶች ዓመታዊ የጋራ ስብሰባ እንዲሁም በልዩ ልዩ የሀገር ውስጥና ዓለም አቀፍ ጉባዔዎች ላይ የሚያሰሙትን ንግግር ረቂቅ አዘጋጅቶ ማቅረብ፤
   4. ለፕሬዝዳንቱ የሚቀርቡ ሕግ ነክ ጉዳዮችን እየመረመረ ተገቢውን የውሣኔ ሃሣብ ማቅረብ፤

5. ለፕሬዚዳንቱና ለቤተሰባቸው ደህንነት ተገቢው ጥበቃ መደረጉን ማረጋገጥ፤ የመኖሪያ ቤታቸውን አስተዳደራዊ ጉዳይ ማካሄድና መከታተል፤
6. ፕሬዚዳንቱ የኅብረተሰቡን ልዩ ልዩ ክፍል ተጠሪዎችና ሌሎችንም እንደ አግባብነቱ ተቀብለው የሚያነጋግሩበትን ሁኔታ ማስተባበር፤
7. የውጭ ሀገር ርዕሳነ ብሔራት ኢትዮጵያን ለመጐብኘት ሲመጡ አግባብ ካላቸው ጋር በመተባበር፤ ለጉብኝቱ ውጤታማነትና ሁለገብ ስኬታማነት አመች ሁኔታ መፍጠር፤ አፈጻጸሙንም መከታተል፤
8. የውጭ ሀገር አምባሳደሮች የሹመት ደብዳቤያቸውን ለፕሬዘዳንቱ የሚያቀርቡበትን እና በሥራ ጊዜያቸው ፍጻሜ ላይ ፕሬዚዳንቱን የሚሰናበቱበትን ሥነ-ሥርዓት አግባብ ካላቸው ጋር በመመካከር ማስፈጸም፤
9. ፕሬዚዳንቱ የውጭ ሀገር እንግዶችን በኦፊሴል ተቀብለው ሲያነጋግሩ የውይይቱን ቃለ ጉበኤ መያዝ፤ ይኸንኑም በሥርዓት ማደራጀትና በሚገባ ጠብቆ ማቆየት፤
10. የሀገሪቱ አምባሳደሮችና ሌሎች መልዕክተኞች ሹመት እንዲሁም በሕግ መሠረት ከፍተኛ የውትድርና ማዕረግ፤ ኒሻን፤ ሜዳይና ሽልማት በፒሬዘዳንቱ የሚሰጥበትን ሥነ-ሥርዓት አግባብ ካላቸው ጋር በመተባበር ማስፈጸም፤
11. ለፕሬዚዳንቱ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን እየመረመረ ወደ የሚመለከታቸው አካላት የሚመሩበትን ሁኔታ ማመቻቸት፤
12. በፕሬዚዳንቱ የበላይ ጠባቂነት ከሚመሩ አካላት ጋር የቅርብ ግንኙነት መፍጠር፤ የሥራ እንቅስቃሴያቸው ስለሚገኝበት ሁኔታ በየጊዜው ክትትል ማድረግ፤
13. ፕሬዚዳንቱ በኦፊሴል ጉብኝት ወይም በሌላ ሁኔታ ወደ ውጭ ሀገር ስለሚያደርጉት ጉዞ አግባብ ካላቸው ጋር በመተባበር አስፈላጊውን ሁሉ ማከናወን፤
14. ፕሬዚዳንቱ በሀገር ውስጥ ለሚያደርጉት የሥራ ጉብኝት ከሚመለከታቸው ጋር በመመካከር ሁለገብ ፕሮግራም መንደፍ፤
15. በፕሬዚዳንቱ ለሚሰጡ የማበረታቻ ሽልማቶች እና የበጐ አድራጐት ችሮታዎች አፈጻጸም ሁኔታዎችን ማመቻቸት፤
16. የንብረት ባለቤት መሆን፤ ውል መዋዋል፤ በስሙ መክሰስና መከሰስ፤
17. ኃላፊነቱን ለመወጣት የሚረዱ ሌሎች አግባብ ያላቸው ተግባሮችን ማከናወን፡፡

5. <u>የጽሕፈት ቤቱ አቋም</u>

ጽሕፈት ቤቱ፤

1. በመንግሥት የሚሾሙ፤

ሀ/ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ፤

ለ/ የፕሬዚዳንቱ ልዩ ረዳት፣

ሐ/ የፕሬዚዳንቱ ልዩ አማካሪ፤

መ/ የፕሬዚዳንቱ ልዩ ጥበቃ ሹም፤ እና

2. አስፈላጊው ሠራተኞች ይኖሩታል ።

6. <u>የጽሕፈት ቤት ኃላፊው ሥልጣንና ተግባር</u>

1. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ከፕሬዚዳንቱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የጽሕፈት ቤቱን የዕለት ተዕለት ሥራዎች የበላይ ሆኖ ይመራል፤ ያስተዳድራል፤

2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ፤

ሀ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 ከተመለከቱት የጽ/ቤቱ ሥልጣንና ተግባሮች መካከል በውስጥ መመሪያ ተለይተው የሚሰጡትን ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 (1) የተጠቀሱትን ሌሎች የጽሕፈት ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች የሥራ እንቅስቃሴ ያስተባብራል፡

ሐ/ የጽሕፈት ቤቱን ሠራተኞች የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጐችን መሠረታዊ መርሆዎች በመከተል ይቀጥራል ፡ ያስተዳድራል ፤

መ/ የጽሕፈት ቤቱን ዓመታዊ በጀትና የሥራ ፕሮግራም ያዘጋጃል ሲፈቀድም ተግባራዊ ያደርጋል፤

ሠ/ ለጽሕፈት ቤቱ በተፈቀደው በጀትና የሥራ ፕሮግራም መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ረ/ ጽሕፈት ቤቱ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ጽ/ቤቱን ይወክላል፤

ሰ/ የጽሕፈት ቤቱን የሥራ እንቅስቃሴና የሂሣብ ሪፖርት ያዘጋጃል።

ሸ/ ከፕሬዚዳንቱ የሚሰጡትን ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮች ያከናውናል።

3. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ ለሥራ ቅልጥፍና ባስፈለገ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል፤ ለርሱ ተጠሪ ለሆኑ የጽሕፈት ቤቱ የበታች ኃላፊዎችና ሌሎች ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

4. የጽሕፈት ቤቱ ኃላፊ በማይኖርበት ጊዜ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5(1) ከተጠቀሱት ሌሎች የበላይ ኃላፊዎች አንዱ፤ ከፕሬዚዳንቱ በሚሰጥ ውሣኔ መሠረት ተክቶት ሊሠራ ይችላል፡፡

7. **<u>የጽሕፈት ቤቱ በጀት</u>**

የጽሕፈት ቤቱ በጀት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይጸድቃል፡፡

8. **<u>የሂሣብ መዛግብት</u>**

1. ጽሕፈት ቤቱ የተሟሉና ትክክለኛ የሆኑ የሂሣብ መዛግብት ይይዛል።
2. የጽሕፈት ቤቱ የሂሣብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሠነዶች በዋናው ኦዲተር በየዓመቱ ይመረመራሉ፡፡

9. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ ከህዳር 1 ቀን 1991 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 1 ቀን 1991 ዓ.ም**

**ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## ክፍል አራት

## መገናኛ ብዙሃን

## አዋጅ ቁጥር 15/1967

## የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅትን ሥልጣን ለመወሰን የወጣ አዋጅ[19]

## "ኢትዮጵያ ትቅደም"

የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት በትዕዛዝ ቁጥር 50/1960 ዓ.ም የተቋቋመ መሆኑን በመመልከት፣

ይኸው ድርጅት ትምህርት፤ጠቅላላ ዕውቀትንና ዜናን ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በበለጠ ለማዳረስ እንዲችል ተገቢው ሥልጣን እንዲኖረው ማድረግ የሚያስፈልግ መሆኑን በማመን፤

የጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግንና የሊቀ መንበሩን ሥልጣን ለመወሰን ባወጣው አዋጅ ቁጥር 2/1967 ዓ.ም በአንቀጽ 6 መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጅዋል፡፡

1. **አጭር ርዕስ፤**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት አዋጅ ቁጥር 15/1967 ዓ.ም" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

2.

3. **የድርጅቱ ሥልጣን፤**

   ድርጅቱ፣

   1. የቴሌቪዥን ባለቤትነትን ወይም ይዞታን ለመመዝገብና ይህንኑ የሚመለከት ፈቃድ ለመስጠት፤
   2. ሀ/ ማናቸውም ነጋዴ የሚሸጠውን ወይም በሌላ አኳኋን ንብረትነቱን ወይም ይዞታውን የሚያስተላልፈውን ቴሌቪዥን እንዲሁም፤

      ለ/ ማናቸውም አዳሽ ለማደስ የተቀበለውን ቴሌቪዥን በመዝገብ እንዲይዝ ለማድረግ፤
   3. ማናቸውም ነጋዴና አዳሽ ለመመዝገብ፤
   4. ለሚሰጠው ፈቃድና በቴሌቪዥንና በራዲዮ ፕሮግራም ውስጥ ለሚሸጠው ጊዜ የአገልግሎት ዋጋ ለመወሰንና ለመሰብሰብ፤

[19] በ20/79(2006) ኢ.858 ይህን አዋጅ ከሻረ በኃላ አንቀፅ 21 የቴሌቭዥን ምዝገባና ፈቃድን የተመለከቱ ድንጋጌዎች ተፈፃሚነታቸው እንደሚቀጥል በተደነገገው መሰረት ገባ ነው፡፡

5. ለሥራው በማያስፈልገው መጠን ገንዘብ ለመበደርና ለዚሁም የሚንቀሳቀስና የማይንቀሳቀስ ንብረቱን ለማስያዝ፤ ሥልጣን አለው፡፡

4. ፈቃድ የሌለውን ቴሌቪዥን ስለመያዝ፤

1. ማናቸውም ሥልጣን የተሰጠው ሠራተኛ ጽኑ የሆነ ፈቃድ የሌለውን ቴሌቪዥን የያዘ ሰው ሲያገኝ ደረሰኝ ሰጥቶ ሌቴቪዥኑን ለጊዜው ይይዝበታል፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ቴሌቪዥኑ የተያዘበት ሰው ለዚሁ ቴሌቪዥን ጽኑ የሆነ ፈቃድ ይዞ ሲቀርብ ቴሌቪዥኑ ይመለስለታል፡፡

3. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት ስለተያዘ ቴሌቪዥን ድርጅቱ በቂ ማስታወቂያ ከሰጠ በኋላ እስከ ሶስት /3/ ወር ይገባኛል ባይ ያልቀረበ እንደሆነ ቴለቪዥኑ በሐራጅ ተሽጦ ከሽያጩ ዋጋ የቴሌቪዥኑ የፈቃድ አገልግሎት ዋጋና ሌላም ተገቢ ወጪ ለድርጅቱ ይከፈላል፡፡

5. ምርመራ የማድረግ ሥልጣን፤

ሥልጣን የተሰጠው ሠራተኛ ተገቢ በሆነ በማናቸውም ጊዜ በዚህ አዋጅ መሠረት፤

1. እንዲያዝ የታዘዘው መዝገብ መያዝ አለመያዙን ለመመርመርና፤

2. ፈቃድ እንዲኖረው ይገባል ብሎ የሚያስበውን ሰው ፈቃዱን ለምርመራ እንዲያቀርብ ለመጠየቅ ይችላል፡፡

6. ስለፈቃድ መታደስ፤

በዚህ አዋጅ መሠረት የተሰጠው ፈቃድ በየዓመቱ ይታደሳል፡፡

7. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ፤

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ጥር 8 ቀን 1967 ዓ.ም**

**ጊዜያዊ ወታደራዊ አስተዳደር ደርግ**

## የሕግ ክፍል ማስታወቂያ ቁጥር 20/1967 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት ደንብ[20]

## "ኢትዮጵያ ትቅደም"

1. **አውጪው ባለሥልጣን፣**

የማስታወቂያ ሚኒስትር በኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት አዋጅ ቁጥር 15/1967 (ከዚህ ቀጥሎ "አዋጅ" እየተባለ በሚጠራው) በአንቀጽ 3 እና 9 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን ደንብ አውጥቶአል፡፡

2. **አጭር ርዕስ፣**

ይህ ደንብ "የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት ደንብ ቁጥር 20/1967 ዓ.ም" ተብሎ ጠቀስ ይቻላል፡፡

3. **ትርጓሜ፣**

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልሰጠው በቀር፣ በዚህ ደንብ ውስጥ፣

1. "ሰው"፣ "ቴሌቪዥን"፣ "ነጋዴ"፣ "አዳሽ"፣ "ሥልጣን የተሰጠው ሠራተኛ" እና "ድርጅት" በአዋጁ የተሰጣቸው ትርጓሜ ይኖራቸል፡፡
2. "መዝጋቢ ባልሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ ራዲዮና ቴሌቪዥን አገልግሎት ድርጅት ወይም በዚህ ደንብ በአንቀጽ 4 እና 5 የተመለከቱትን ተግባሮችተ እንዲፈጽም ድርጅቱ የሚወክለው ሚኒስቴር ወይም ሌላ የመንግሥት መሥሪያ ቤት ነው፡፡

4. **ምዝገባ፣**

ነጋዴ፣ አዳሽ፣ የቴሌቪዥን ባለቤት ወይም ባለይዞታ የሆነ ማንኛውም ሰው ይህ ደንብ ከወጣበት ቀን አንስቶ በ90 ቀን ውስጥ መዝጋቢ ባለሥልጣን ዘንድ እየቀረበ መመዝገብ አለበት፡፡

5. **ስለምዝገባ ፈቃድና የአገልግሎት ዋጋ፣**

1. መዝጋቢው ባለሥልጣን ማንኛውም ነጋዴ ወይም አዳሽ ሲመዘገብ፣ እንደነገሩ ሁኔታ በዚህ ደንብ በሠንጠረዥ ሀ ወይም ለ የተመለከተውን የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡
2. መዝጋቢው ባለሥልጣን ማንኛውም የቴለቪዥን ባለቤት ወይም ባለይዞታ ሲመዘገብ በዚህ ደንብ በሠንጠረዥ ሐ የተመለከተውን ፈቃድ ይሰጠዋል፡፡

[20] በ20/79(2006) አ.79 አንቀፅ 21 መሰረት ተፈፃሚነቱ እንደሚቀጥል የተደነገገ በመሆኑ የገባ ነው፡፡

3. ማንኛውም የቴሌቪዥን ባለቤት ወይም ባለይዞታ ፈቃድ ስሰጠው ሃምሳ (50) ብር የአገልግሎት ዋጋ በየዓመቱ ለመዝጋቢው ባለሥልጣን ይከፍላል፡፡

6. <u>መዝገብ ስለመያዝና ስለምርመራ፤</u>

1. ማንኛውም ነጋዴ፣ --

ሀ. በእጁ የሚገኙትን ቴሌቪዥኖች ብዛት፣ ዓይነትና የመለያ ቁጥር፣ እንዲሁም

ለ. ያደረገውን የቴሌቪዥን ሽያጭ ወይም ኪራይ ብዛት፣ የቴሌቪዥኑን ዓይነት፣ መለያ ቁጥርና የገዢውን ወይም የተከራዩን ስምና አድራሻ ጭምር በመዝገብ መያዝ አለበት፡፡

2. ማንኛውም አዳሽ ለማደስ የተረከባቸውን ቴሌቪዥኖች ብዛት፣ ዓይነት፣ መለያ ቁጥርና፣ እንዲሁም የደንበኛውን ስምና አድራሻ በመዝገብ መያዝ አለበት፣

3. ማንኛውም ነጋዴ ወይም አዳሽ ማንኛውም ሥልጣን የተሰጠው ሠራተኛ ሲጠይቀው ለምርመራ ወይም ለቅጂ መዝገቡን የማቅረብ ግዴት አለበት፡፡

4. ማንኛውም የቴሌቪዥን ባለቤት ወይም ባለይዞታ ማንኛውም ምልጣን የተሰጠው ሠራተኛ ሲጠይቀው ፈቃዱን ለምርመራ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

7. <u>ያለፈቃድ በቴሌቪዥን መጠቀም ስለመከልከሉ፤</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ካልያዘ በቀር በቴሌቪዥን መጠቀም አይችልም፡፡

8. <u>ደንብ ስለመተላለፍ፤</u>

ይህን ደንብ የጣሰ ወይም ያልፈጸመ ሰው በአዋጁ አንቀጽ 10 መሠረት ይቀጣል፡፡

9. <u>ደንቡ ስለሚጸናበት ጊዜ፤</u>

ይህ ደንብ ከመስከረም 3 ቀን 1968 ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ነሐሴ 19 ቀን 1967 ዓ.ም**

**ሻለቃ ያዕቆብ ገብረ እግዚአብሔር**

**የማስታወቂያ ሚኒስትር**

## ሠንጠረዥ ሀ

## የቴሌቪዥን ነጋዴ ምዝገባ የምስክር ወረቀት

ጉርድ ፎቶግራፍ

የሴሪ ቁጥር ……………………………

የምስክር ወቀት ቁጥር ………………..

የደረሰኝ ቁጥር ………………………..

1. የነጋዴው ስም ……………………….. 2. አድራሻ ………………..

3. የፖ.ግ.ቁጥር ………………………….. 4. ስልክ ……………………

5. ዜግነት ……………………………….. 6. የሥራ ዓይነት ……………..

7. የንግድ ፈቃድ ቁጥር …………………………

የተመዘገበበት ቀን ………………………….

ፊርማ ………………………….

ማኅተም ……………………….

## ሠንጠረዥ ለ.

## የቴሌቪዥን አዳሽ የምዝገባ ምስክር ወረቀት

ጉርድ ፎቶግራፍ

የሴሪ ቁጥር ……………………………

የፈቃድ ቁጥር ……………………………

የደረሰኝ ቁጥር ……………………………

1. የአዳሹ ስም ……………………………  2. አድራሻ …………………

3. የፓ.ግ.ቁጥር ……………………………  4. ስልክ ……………………

5. ዜግነት ……………………………  6. የሥራ ዓይነት ……………

7. የንግድ ፈቃድ ቁጥር ……………………………

የተመዘገበበት ቀን ……………………………

ፊርማ ……………………………

ማኅተም ……………………………

## ሠንጠረዥ ሐ.

## የቴሌቪዥን ባለቤት ወይም ባለይዞታ የምስክር ወረቀት

ጉርድ ፎቶግራፍ

የሴሪ ቁጥር ……………………………

የፈቃድ ቁጥር ..............................

የደረሰኝ ቁጥር ..............................

1.የባለቤት ወይም ባለይዞታ ስም ............................ 2. አድራሻ ..............

ሀ. መኖሪያ ...................

ለ. የሥራ ቦታ ..............

3.ዜግነት ...........................................ገ.ግ.ቁ ሀ. መኖሪያ ........

ለ. የሥራ ቦታ ------------------

ስልክ ሀ. መኖሪያ ............

ለ. የሥራ ቦታ .................

4.ሥራ ...................................................................................................

5.የመታወቂያ ካርድ ቁጥር ..........................................................................

የቴሌቪዥን መለያ ................................................................................

| <u>ዓይነት</u> | <u>መጠን</u> | <u>የመለያ ቁጥር</u> |
|---|---|---|
| ........................... | .......................... | ......................... |

ቀን .....................

ፊርማ .....................

ማኅተም ....................

ማሳሰቢያ፡- ይህ የፈቃድ ወረቀት የሚያገለግለው ለ19........ ዓ.ም ብቻ ነው፡፡

**ዕድሳት**

| | | |
|---|---|---|
| -------------------------- | -------------------------- | -------------------------- |
| -------------------------- | -------------------------- | -------------------------- |

## አዋጅ ቁጥር 114/1987 ዓ.ም

## የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ[21]

በመንግሥት ባለቤትነት ያሉ የመገናኛ ብዙሃን በኅብረተሰቡ መካከል ሐሳቦችና አመለካከቶች ሕገ መንግሥቱ በደነገገው መሠረት በነፃ መንሸራሸራቸውን ለማረጋገጥ የተቋምና የአሠራር ነፃነት እንዲሁም የሕግ ጥበቃ እንዲኖረው ማድረግ ስለሚያስፈልግ፡፡

የኢትዮጵያ የሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅትን በአዲስ መልክ በማዋቀር የድርጅቱ የሥራ ዕድገትና ቅልጥፍና በተሻለ መንገድ እንዲራመድ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

በሕገመንግሥት ጉባኤ የመሸጋገሪያ ውሳኔ መሠረት የሚከተለው ታውጇዋል፡፡

1. **አጭር ርዕስ፣**

   ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ሬዲዮና ቴሌቪዥን ድርጅት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 114/1987" ተብሎ ሊጠቀስ ይቻላል፡፡

5. **የድርጅቱ ሥልጣንና ተግባር፣**

   6. ለሥራው አፈጻጸም አስፈላጊ የሆኑትን የሬዲዮና የቴሌቪዥን ማስተላለፊያ፣ መሸጋገሪያና ሌሎችንም ለተመሳሳይ አገልግሎት የሚውሉ መግሪያዎች በተገቢ ሥፍራዎች ያቋቁማል፣ ያስተዳድራል፣

   9. የሬዲዮና የቴሌቪዥን አገልግሎት የሚስፋፋበትንና በተስማሚ ቴክኖሎጂ የሚደራጁበትን ሁኔታ በማጥናት ሐሳብ ያቀርባል፣ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፣

15. **አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ፣**

   ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ የካቲት 22 ቀን 1987 ዓ.ም**

**መለስ ዜናዊ**

**የኢትዮጵያ የሽግግር መንግሥት ፕሬዚዳንት**

[21] በ20/79(2006) አ.858 ይህን አዋጅ ከሻረ በኃላ አንቀፅ 21 የአዋጁ አንቀፅ 5 (5) እና (9) ተፈፃሚነታቸው እንደሚቀጥል በተደነገገው መሰረት ገባ ነው ::

## አዋጅ ቁጥር 533/1998

## ስለብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ

የብሮድካስት አገልግሎት ኢንፎርሜሽን፣ ትምህርትና የመዝናኛ ፕሮግራም ለሕዝብ በማቅረብ ለአንድ አገር ፖለቲካዊ፣ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ከፍተኛ ሚና የሚጫወት በመሆኑ፤

የብሮድካስት አገልግሎት በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጡ ሀግብን በነፃ የመግለጽ፣ መረጃ የማግኘት፣ የመምረጥ፣ የመመረጥና የመሳሰሉትን መሠረታዊ መብቶችና ነፃነቶች ተግባራዊ ለማድረግ ከፍተኛ ሚና ስለሚጫወት፤

ውስን የአገር ሀብት የሆነውን የራዲዮ ሞገድ በአግባቡ እና ፍትሐዊ በሆነ መንገድ ጥቅም ላይ መዋሉን ማረገጥ በማስፈለጉ፤

የብሮድካስት አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ ሚሰማሩ ሰዎችን መብተና ግዴታ በግልፅ መወሰን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

እነዚህን አላማዎች ከግብ ለማድረስ በሥራ ላይ ያለውን የብሮድካስተ ሕግ በተሻሻለ ሕግ መተካተ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55/1/ መሠረት የሚከተለው ታዉጇል፡፡

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ "የብሮድካስት አገልግሎት አዋጅ ቁጥር 533/1998" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ዉስጥ፤

   1. "የራዲዮ ሞገድ" ማለት በዓለም የቴሌኮሙኒኬሽን ማኅበር የሬዲዮ ደንብ መሠረት ለብሮድካስት አገልግሎት የተመደበ የራዲዮ ሞገድ ነዉ፤
   2. "የብሮድካስት አገልግሎት" ማለት ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማሳዉቅ ወይም ለማዝናናት የሚከናወን የሬዲዮ ወይም የቴሌቪዥን ሥርጭት አገልግሎት ነዉ፤
   3. "ባለፍቃድ" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ የተሰጠወቱ ሰዉ ሲሆን ይህ አዋጅ ከመወጣቱ በፊት ጀምሮ በሕጋዊ መንገድ የብሮድካስት አገልግሎት በመስጠት ላይ ያለ ሰዉንም ይጨምራል፤

4. "ፕሮግራም" ማለት በድምጽ ወይም በምስል ወይም በሁለቱ ተቀነባብሮ ለማሳወቅ፣ ለማስተማር ወይም ለማዝናናት ወይም ሁሉንም አካቶ የሚቀርብ የፕሮግራም ሥርጭት ነው፤

5. "ማስታወቂያ" ማለት ዕቃዎችና አገልግሎቶች እንዲታወቁና እንዲሸጡ የሚተላለፍ መልዕክት ነው፤

6. "የምርጫ ወቅት ማስታወቂያ" ማለት አንድ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ዕጩ ተወዳዳሪ እራሱንና ፍላጎቱን ለማስተዋወቅ ገንዘብ በመክፈል ወይም ለመክፈል ቃል በመግባት በሬዲዮ ወይም በቴሌቪዥን የሚያስነግረዉ ማስታወቂያ ነው፤

7. "በስፖንሰር የሚቀርብ ፕሮግራም" ማለት ፕሮግራሙን ለማሰራጨት ገንዘብ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተከፈለበት ወይም የክፍያ ቃል የተገባበት ፕሮግራም ነው፤

8. "የምርጫ ወቅት" ማለት የምርጫ ዉድድር በይፋ ከተጀመረበት ቀን ጀምሮ ድምጽ መስጠት ከሚጀመርበት ቀን 48 ሰዓት በፊት ድረስ ያለው ጊዜ ነው፤

9. "የመንግሥት ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማግወቅና ለማዝናናት በአገር አቀፍ ወይም በክልል የሚቋቋም ተጠሪነቱም ለፌደራል የሕዝብ ተወካዮች ወይም ለየክልል ምክር ቤቶች የሆነ በሙሉ ወይም በከፊል የመንግሥት በጀት የተመደበለት የሬዲዮ ወይም የቴሌቭዥን አገልግሎት ነው፤

10. "የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት ትርፍን መሠረት ያደረገ፣ ሕዝብን ለማስተማር፣ ለማግወቅና ለማዝናናት ሕጋዊ ሰዉነት ባለዉ አካል የተቋቋመ የሬዲዮ ወይም የቴሌቭዥን አገልዐገለብት ነዉ፤

11. "ማኀበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት" ማለት በአንድ በተወሰነ አካባቢ በሚኖሩ ወይም የጋራ ፍላጎት በሚያገናኛቸው የህብረተሰብ ክፍሎች በፍላጎት የተቋቋመና በማህበረሰቡ የሚተዳደር እና የሚመራ ለትርፍ ያልቆመ የሬዲዮ ወይም የቴሌቭዥን አገልግሎት ነው፤

12. "የፖለቲካ ድርጅት" ማለት በሕጋዊ መንገድ ፖለቲካ ፕሮግራሙን የሚያራምድ ቡድን ነው፤

13. "አመልካች" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ 19(3) የተጠቀሰውን የማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ለባለሥልጣኑ ያቀረበ ሰው ነው፤

14. "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 47(1) የተመለከተዉ ማንኛዉም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተሞች አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

15. "አገር አቀፍ ስርጭት" ማለት ከአንድ ክልል በላይ የሚሸፍን የብሮድካስተ አገልግሎት ነው፤

16. "ክልላዊ ስርጭት" ማለት ስርጭቱ በአንድ ክልል ብቻ የተወሰነ የብሮድካስተ አገልግሎት ነው፤

17. "አካባቢያዊ ስርጭት" ማለት ስርጭቱ በአንድ ወረዳ ወይም ማዘጋጃ ቤተ ብቻ የተወሰነ የብሮድካስት አገልግሎት ነዉ፤

18. "አገራዊ ፕሮግራም" ማለት በኢትዮጵያ ውስጥ በኢትዮጵያዊያን የተዘጋጀ ፕሮግራም ነው፤

19. "ሚኒስቴር እና "ሚኒስትር" ማለት እንደቅደም ተከተሉ የማስታወቂያ ሚኒስቴር እና ሚኒስተር ነዉ፤[22]

20. "ኢንስፔክተር" ማለት ባለፈቃዶች ይህን አዋጅና በአዋጁ መሠረተ የወጡ ደንቦችና መመሪያዎችን አክብረው መሥራታቸውን የሚቆጣጠር በባለሥልጣኑ የሚመደብ ሠራተኛ ነው፤

21. "ሰዉ" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ ሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በኢትዮጵያ ውስጥ በተቋቋሙ በመንግሥት፣ በንግድ እና በማኅበረሰብ የብሮድካስት አገልግሎቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ሁለት</u>

## <u>የኢትዮጵያ የብሮድካስት ባለሥልጣን</u>

4. <u>መቋቋም</u>

1. የኢትዮጵያ የብሮድካስት ባለስልጣን (ከዚህ በኋላ "ባለሥልጣን" እየተባለ የሚጠራ) የሕግ ሰውነት ያለው ራሱን የቻለ የፌደራል መሥሪያ ቤት ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ተጠሪነቱ ለሚኒስቴሩ ይሆናል፡፡

5. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

22

የባለሥልጣኑ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ እንደአስፈላጊነቱ በአገሪቱ በማናቸውም ሥፍራ ቅርንጫፍ ሲኖረው ይችላል፡፡

6. <u>ዓላማ</u>

የባለሥልጣኑ ዓላማ ለፖለቲካዊ፣ ለማኅበራዊና ለኢኮኖሚያዊ ዕድገት አስተዋጽኦ የሚያደርግ፣ ጥራቱ የተጠበቀ፣ ቀልጣፋና አስተማማኝ የብሮድካስት አገልግሎት እንዲስፋፋ ማድረግና መቆጣጠር ይሆናል፡፡

7. <u>ሥልጣንና ተግባር</u>

ባለሥልጣኑ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. የብሮድካስት አገልግሎት ለአገሪቱ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ ዕድገት ተገቢውን አስተዋጽኦ ሲያበረክት በሚችል መልኩ መካሄዱን ያረጋግጣል፤
2. ለብሮድካስት አገልግሎቶች ፈቃድ ይሰል፣ ያግዳል፣ ይሰርዛል፤
3. ብሮድካስት ጣቢያ የሚቋቋምበትን ሥፍራና የሽፋን ክልል ከሌሎች የሬዲዮ ኮሙኒኬሽን አገልግሎቶች ጋር አለመጋጨቱን አረጋግጦ ይወስናል፤
4. ለብሮድካስት አገልግሎት የሚውሉትን መግሪያዎች ዓይነትና እንዲሁም የማሠራጫ መግሪያውን ጉልበት ይወስናል፤
5. ሕገወጥ ሥርጭትን በሚመለከት ቁጥጥር ያደርጋል፤
6. ለብሮድካስት አገልግሎት በሚመለከተው አካል የተመደበውን የሬዲዮ ሞገድ ዕቅት ያዘጋጃል፣ ይፈቅዳል፣ ይቆጣጠራል፣ ያከራያል፤
7. ስለብሮድካስት አገልግሎት ዕድገትና መሻሻል ጥናት ያደርጋል፣ አገልግሎቱን የሚመለከቱ መረጃዎችን አጠናቅሮ ይይዛል፤
8. ለተለያዩ የብሮድካስት አገልግሎቶች የቴክኒክ ደረጃዎች ያወጣል፤
9. የብሮድካስት መግሪያዎችን ደረጃ ያወጣል፤ ለመግሪያዎቹ አስመጪዎች የማረጋገጫ ሰርቲፊኬት ይሰጣል፣ አሰራራቸዉንም ይቆጣጠራል፤
10. በብሮድካስት አገልግሎት በሚነሱ ቅሬታዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤
11. አግባብ ያላቸው ሕጎችና የመንግሥት መመሪያዎች እንደተጠበቁ ሆነው የብሮድካስት አገልግሎትን በሚመለከት መንግሥትን በመወከል በዓለም አቀፍ ስብሰባዎች ይሳተፋል፤
12. የብሮድካስት አገልግሎትን በሚመለከት አገሪቱ የተቀበለቻቸውን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች አፈጻጸም ይከተላል፤
13. የብሮድካስት አገልግሎት የፈቃድ ክፍያዎችን ተመን ይፈፅማል፤
14. በሚመለከተው አካል ለሚመደበው የሬዲዮ ሞገድ ተገቢውን ክፍያ ይፈጽማል፤

15. የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሰሳል፣ ይከሰሳል፤

16. ዓላማውን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስፈልጉ ሌሎች ተዛማጅ ተግባሮችን ያከናዉናል፡፡

8. <u>የባለሥልጣኑ አቋም</u>

ባለሥልጣኑ፣

1. ቦርት፣
2. ዋና ዳይሬክተር፣
3. ምክትል ዋና ዳይሬክተር፣ እና
4. አስፈላጊ ሠራተኞች፣

ይኖሩታል፡፡

9. <u>ስለ ባርድ አባላት</u>

1. ቦርዱ በመንግሥት የሚወሰንያላቸው አባላት ይኖሩታል፡፡
2. የቦርዱ አባላት ከተለያዩ ተቋማትና ኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ሆነው በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግስት የሚመደቡ ይሆናሉ።
3. የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር የቦርዱ አባል እና ፀሀፊ ይሆናል፡፡
4. የቦርዱ ተጠሪነት ለማስታወቂያ ሚኒስቴር ይሆናል፡፡

10. <u>የቦርዱ ስልጣንና ተግባር</u>

ቦርዱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል፤

1. የዚህን አዋጅ አፈጻጸምና የባለሥልጣኑን ሥራዎች በበላይነተ ይቆጣጠራል፣
2. የባለሥልጣኑን አመታዊ የሥራ ፕሮግራምና በጀት እንዲሁም የሥራ እንቅስቃሴ ሪፖርተ ይገመግማል፤
3. ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚወጡ መመሪያዎችን መርምሮ እንዲፀድቁ ለሚኒስቴሩ ያቀርባል፤
4. አመልካቾችና ባለፈቃዶች የሚያቀርቧቸዉን አቤቱታዎች መርምሮ ይወስናል፤ ባለፈቃዶችን አስመልክቶ ከሕዝቡ በቀረቡ ቅሬታዎች በተሰጡ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ አቤቱታዎችን መርምሮ ይወስናል፤
5. የዚህን አዋጅ አፋጻጸም በሚመለከት በሚቀርቡለት የፖሊሲ ጉዳዮች ላይ ይመክራሉ እንደአግባቡ ይወሰናል፡፡

11. <u>የቦርዱ ስብሰባ</u>

1. ቦርዱ በወር አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ ሆኖም በሰብሳቢዉ ጥሪ በማናቸውም ጊዜ ሲሰበሰብ ይችላል፡፡

2. በቦርዱ ስብሰባ ላይ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት አባላት ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

3. የቦርዱ ውሳኔዎች በድምጽ ብልጫ ያልፋሉ፤ ሆኖም ድምጹ እኩል በእኩል ከተከፈለ ሰብሳቢው ወሳኝ ድምጽ ይኖረዋል።

4. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ቦርዱ የራሱን የስብሰባ ሥነ ሥርዓት ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

12. <u>ስለባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር</u>

1. ባለሥልጣኑ ዋና ዳይሬክተር በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማል።

2. ዋናው ዳይሬክተር የባለሥልጣኑ ዋና ሥራ አስፈጻሚ በመሆን ከቦርዱ በሚሰጠው አጠቃላይ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሥራዎች ይመራል፣ ያስተዳድራል፡፡

3. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ዋናው ዳይሬክተር፣

ሀ/ አዋጅ አንቀጽ 7 የተመለከቱትን የባለሥልጣኑን ሥልጣንና ተግባራት በሥራ ላይ ያዉላል፡

ለ/ የፌዴራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎችን መሠረታዊ መርሆዎች ተከትሎ በመንግሥት በሚጸድቅ መመሪያ መሠረት የባለሥልጣኑን ሠራተኞች ይቀጥራል፣ ያስተዳድራል፣

ሐ/ የባለሥልጣኑን የሥራ ፕሮግራምና በጀት አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፣ አግባብ ባለው አካል ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያዉላል፤

መ/ ለባለሥልጣኑ በተፈቀደው የሥራ ፕሮግራምና በጀት መሠረተ ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ/ ከሦስተኛ ወገኖች ጋር በሚደረጉ ግንኙነቶች ሁሉ ባለሥልጣኑን ይወክላል፤

ረ/ የባለሥልጣኑን የሥራ እንቅስቃሴና የሂግብ ሪፖርተ አዘጋጅቶ ለቦርዱ ያቀርባል፤

ሰ/ በቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

4. ዋናው ዳይሬክተር ለባለሥልጣኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልገው መጠን ሥልጣንና ተግባሩን በከፊል ለባለሥልጣኑ ሌሎች ኃላፊዎችና ሠራተኞች ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

13.<u>ስለባለሥልጣኑ ምክትል ዋና ዳይሬክተር</u>

1. ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ በሚኒስትሩ አቅራቢነት በመንግሥት ይሾማል።

2. ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ከዋናው ዳይሬክተር በሚሰጠው መመሪያ መሠረት፣

ሀ/ በሥሩ የተመደበለትን የሥራ ዘርፍ ይመራል፡ ያስተባብራል፤

ለ/ በዋና ዳይሬክተሩ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል።

14.<u>በጀት</u>

የባለሥልጣኑ በጀት በመንግስት የሚመደብ ይሆናል፡፡

15.<u>ስለሂሳብ መዝገብ</u>

1. ባለስልጣኑ የተሟላና ትክክለኛ የሆኑ የሂግብ መዛግብት ይይዛል፡፡

2. የባለሥልጣኑ የሂግብ መዛግብትና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በዋናው ኦዲተር ወይም ዋናዉ ኦዲተር በሚሰይመዉ ኦዳተር በየአመቱ ይመረምራሉ፡፡

## <u>ክፍል ሦስት</u>

## <u>የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ</u>

16. <u>የብሮድካስት አገልግሎት ዓይነቶች</u>

1. የብሮድካስት አገልግሎት ዓይነቶች የመንግሥት፣ የንግድና የማኅበረሰብ ይሆናሉ።

2. ማንኛዉም መንግስት የብሮድካስት አገልግሎት፣

ሀ/ የመንግሥት ፖሊሲዎችንና ስትራቴጅዎችን እንዲሁም የልማት፣ የዲሞክራሲና የመልካም አስተዳደር እንቅስቃሴዎችን በማቅረብ የሕዝቡን ተግትፎ ያዳብራል በራል፣

ለ/ ሕዝቡን የሚያሳውቁ፣ የሚያስተምሩና የሚያዝናኑ ፕሮግራሞችን ያቀርባል፤

ሐ/ በእኩልነት ላይ የተመሠረተ የሕዝቦችን አንድነት የሚያንፀባርቁ ፕሮግራሞችን ያቀርባል፤

መ/ የሕዝቡን ባህልና ዓበባዊ እሴቶች ያስተዋዉቃል፣ ያጎለብታል፤

ሠ/ በአገሪቱ ሕገ መንግሥትና የምርጫ ሕግ መሠረተ የሚንቀግቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችን በፍትሃዊነተ ያገለግላል፡፡

3. ማንኛዉም የንግድ ብሮድካስት አገልግሎት ለተርፍ ዓላማ የተቋቋመ ቢሆንም፣

ሀ/ ፈቃድ በወሰደበት አካባቢ የሚገኘውን ኅብረተሰብ በእኩልነት ያስተናግዳል፤

ለ/ ፈቃድ ለወሰደበት አካባቢ አገልግሎቱን ያደርሳል፤

ሐ/ በፕሮግራሙ ዉስጥ አካባቢያዊና አገራዊ ዜናዎችን ያካትታል፡፡

መ/ በባለስልጣኑ የተሰጠውን ፈቃድ እንደአግባብነቱ ለንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም ለክልል ንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ በማቅረብ ማስመዝገብ አለበት፡፡

4. ማንኛዉም ማኀበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት፣

ሀ/ ማኀበረሰቡን የልማት፣ የትምህርትና የመልካም አስተዳደር ፍላጎቶች መሠረት አድርጎ ይሰራል፤

ለ/ ማኀበረሰቡን ቋንቋ፣ ባህልና ጥበባዊ እሴቶች ያስተዋጡቃል፣ ያገለብታል፤

ሐ/ በፕሮግራም ዝግጅት የማኀበረሰቡን አባላተ ያላተፋል፤

መ/ ሌሎች ለማሰራጨት ያልቻሉትን የማኀበረሰቡን የጋራ ፕሮግራሞች ጉዳዮች የሚመለከቱ ፕሮግራሞችን ያሰራጫል፤

ሠ/ ከተለያዩ ምንጮች የሚገኙ ገቢዎችን ለማሰራጫ ጣቢያው አገልግሎት ያዉላል፡

ረ/ ለማኀበረሰቡ ጠቀሜታ ያላቸውንና ማኀበረሰቡን መሠረት ያደረጉ አስፈላጊ መረጃዎችንና የመዝናኛ ፕሮግራሞችን በማዘጋጀት የማኀበረሰቡን የመረጃ ባህልና እውቀት ያዳብራል።

## 17. <u>የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይነቶች</u>

1. የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይነቶች የሚከተሉት ይሆናሉ፡-

ሀ/ ከምድር ወደ አየር ነፃ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት፣

ለ/ ከምድር ወደ አየር ነፃ የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት፣

ሐ/ በሳተላይት አማካይነት የሚሰራጭ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት፣

መ/ በሳተላይት አማካይነት የሚሠራጭ የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት፣

ሠ/ በሳተላይት አማካይነት በክፍያ ለደንበኞች የማድረስ ብሮድካስት አገልግሎት፣

ረ/ የውጪ ፕሮግራሞችን በመቀበል ለደንበኞች በክፍያ የማድረስ ብሮድካስት አገልግሎት፣

ሰ/ በኬብል አማካይነት የቴሌቪዥን ፕሮግራም ለክፍያ ለደንበኞች የማድረስ ብሮድካስት አገልግሎት፤

ሸ/ ሌሎች ባለሥልጣኑ የሚወስናቸው የፈቃድ ዓይነቶች፡፡

## 18. <u>የፈቃድ አስፈላጊነት</u>

1. ማንኛውም ሰው ከባለሥልጣኑ የብሮድካስት ፈቃድ ሳይሰጠው ባብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ላይ መሠማራት አይችልም።

2. አንድ ባለፈቃድ በአንድ ፈቃድ ከአንድ ማሰራጫ ጣቢያ በላይ ማቋቋም አይችልም።

19. <u>አመልካቾችን ስለመመዝገብ</u>

1. ባለሥልጣኑ አመልካቾችን ሰፊ ስርጭት ባለው ጋዜጣ ወይም በሌሎች መገናኛ ብዙኃን በሚገለጽ ማስታወቂያ ይጋብዛል፡፡
2. ማስታወቂያዉ ለመፍቀድ ታሰበጡን የብሮድካስት አገልግሎት አይነት፣ አገልግሎቱ የሚሸፍነውን አካባቢ፣ ዝግጁ የሆነውን የሬዲዮ ሞገድ፣ የማመልከቻ ማቅረቢያጡን ጊዜና ቦታ፣ የፈቃዱን ክፍያና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡
3. በብሮድካስት አገልግሎት ሥራ ላይ ለመሠማራት የሚፈልግ ሰው በዚህ አንቀጽ መሠረት በሚወጣዉ ማስታወቂያ በሚጠቅሰዉ ጊዜ ውስጥ በባለሥልጣኑ የተዘጋጀውን የፈቃድ ማመልከቻ ቅጽ ሞልቶ ማቅረብ አለበት፡፡
4. በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ 1-3 የተደነገገዉ ቢኖርም የመንግሥት እና የማህበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት አመልካች በማናቸጡም ጊዜ ለባሥልጣኑ የፈቃድ ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡

20. <u>ተቀባይነት ስለሌለዉ ማመልከቻ</u>

ማንኛዉም ፍቃት እንዲሰጠጡ ማመልከቻ ያቀረበ ሰዉ.

1. የፋይናንስ አቅሙንና ምንጩን ለማረጋገጥ ሚያስችል ሕጋዊ ማስረጃ ካላቀረበ፣
2. ዝርዝር የፕሮጀክት ጥናት ሰነድ ካላቀረበ፣ ወይም
3. በአንቀጽ 23 መሠረት ፈቃድ የማይሰጠጡ አካል ከሆነ፣

በዝርዝር ማጣራት ሳያስፈልግ ማመልከቻጡ ውድቅ ይሆናል፡፡

21. <u>የፍቃድ መስፈርት</u>

1. ባለሥልጣኑ የአመልካቾችን ብዛት ለመመዘን የሚያስችለው ዝርዝር መስፈርት ያወጣል።
2. በባለሥልጣኑ የሚዘጋጀው መስፈርት የሚከተሉትን ያካተተ ይሆናል፤

ሀ/ አገልግሎቱን ለመስጠት የአመልካቹ የፋይናንስ አቅም ተአማኒነትና ብቃት፤

ለ/ በአመልካቹ ፕሮጀክት የተዘረዘሩ መግሪያዎችና ቴክኖሎጂዎች አገልግሎቱን ለመስጠት ያላቸው ብቃት፤

ሐ/ አመልካቹ አገልግሎቱን ለመስጠት ያለዉ ድርጅታዊ ብቃት፣ እዉቀትና የሥራ ልምድ፣

መ/ በአመልካቹ የቀረበዉ የፕሮግራም ይዘትና በፕሮግራሙ የተካተቱ ማኅበራዊ ፍላጎቶች፣

ሠ/ ለአገልግሎቱ የተመደበዉ የስርጭት ጊዜ፡፡

22. <u>የዉሳኔ አሰጣጥ</u>

1. ባለሥልጣኑ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 19(3) መሠረት የቀረበለትን ማመልከቻ በአንቀጽ 20 እና 21 መሠረተ ከመረመረ በኋላ ውሳኔ ይሰጣል፡፡
2. ባለሥልጣኑ ፈቃድ እንዳይሰጥ ሲወስን፣ ፈቃድ ማጁለጥበትን ምክንያት ለአመልካቹ ማሳወቅ አለበተ፡፡
3. ፈቃድ የተከለከለ አመልካች ወግኔ ከተሰጠበት ጊዜ አንስቶ በ14 ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለቦርዱ ሲያቀርብ ይችላል፡፡ ቦርዱም አቤቱታዉ በደረሰው በ20 ቀናት ውስጥ ውግኔ መስጠት አለበት፡፡
4. የፈቃድ ማመልከቻወዉ ተቀባይነት ያገኘ አመልካች ፈቃዱ በሥራ ላይ ስለሚወልበት ሁነታ በባለሥልጣነቹ የተዘጋጅዉን የፈቃድ ስምምነት በመፈረምና ተገቢዉን የፈቃድ ክፍያ በመፈጸም የፈቃድ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

23. <u>ፈቃድ የማይሰጣቸዉ አካላት</u>

የሚከተሉት አካላት የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ አይሰጣቸጡም፣

1. ለግለሰብ እና በሕግ የሰወነት መብት ያልተሰጠው አካል፤
2. በትውልድ ኢትዮጵያዊ የሆኑ የውጭ አገር ዜጎችን በተመለከተ በሌሎች ሕጎች የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ፣

   ሀ/ ኢትዮጵያ ውስጥ ያልተቋቋመ፣ ወይም

   ለ/ በካፒታሉ ወይም በአመራሩ የዉጭ አገር ዜጎች ድርሻ ያለበት፣

   ድርጅት፣
3. የፖለቲካ ድርጅት ወይም የፖለቲካ ድርጅት ባለአክሲዮን የሆነበት ወይም የፖለቲካ ድርጅት በላይ አመራር አባል ባለአክሲዮን ወይም በማንኛዉም ደረጃ የአመራር አባል የሆነበት ድርጅተ፤
4. የሐይማኖት ድርጅት፤
5. የድርጅቱ ባለቤት ወይም ከድርጅቱ ባለቤቶች ወይም ከአመራር አባላቱ ውስጥ በከባድ ወንጀል ተከሶ የተፈረደበት ወይም በፍርድ ቤት ውሳኔ ከሲቪል ወይም

ከፖለቲካ መብቶቹ የጠቶ ወይም ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል የሕግ ችሎታውን ያጣ ሰው ከሆነ፤

6. የካፒታሉ 50 በመት በላይ የሚሆነው የህትመት ፕሬስ ወይም የዜና አገልግሎት ሥራ በሚሠራ ድርጅት ወይም በእንደዚህ ዓይነት ድርጅት ካፒታል ውስጥ ከ20 በመቶ በላይ ድርሻ ባለው ሰው የተያዘ ድርጅት
7. የቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ወይም ከአንድ በላይ የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ያለው ሆኖ ለቴሌቪዥን ብሮድካስት አገልግሎት ሌላ ፈቃድ የሚጠይቅ ድርጅት፤
8. በተመሳሳይ የፈቃት ክልል የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ያለው ወይም በተለያዩ የፈቃድ ክልሎች ሁለት የሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ያለው ሆኖ ለሬዲዮ ብሮድካስት አገልግሎት ሌላ ፈቃድ የሚጠይቅ ድርጅት፡፡

24. <u>የብሮድካስት ፈቃድ ዘመን</u>

የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃዶች ጸንተው የሚቆዩበት ጊዜ እንደሚከተለው ይሆናል፤

1. በአገር አቀፍ ደረጃ የሚሠራጯቸው ሲሆን ለሬዲዮ 8 ዓመት፣ ለቴሌቪዥን 10 ዓመት፤
2. የሥርጭት ሽፋኑ በክልል ደረጃ የተወሰነ ሲሆን ለሬዲዮ 10 ዓመት፤ ለቴሌቪዥን 12 ዓመት
3. የሥርጭት ሽፋኑ በአካባቢ ደረጃ የተወሰነ ሲሆን ለሬዲዮ 12 ዓመት፤ ለቴሌቪዥን 14 ዓመት
4. የሥርጭት ሽፋኑ በድሬዳዋ የተወሰነ ከሆነ 10 ዓመት፣ ለቴሌቪዥን 12 ዓመት፤
5. የሥርጭት ሽፋኑ በአዲስ አበባና አካባቢዋ የተወሰነ ከሆነ ለሬዲዮ 6 ዓመት፣ ለቴሊቪዥን 8 ዓመት፤
6. ማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ከሆነ 5 ዓመት፤
7. የአጭር ጊዜ የማኅበረሰብ ብሮድካስት አገልግሎት ከሆነ ከ1 ዓመት ያልበለጠ፡፡

25. <u>ፈቃድ ስለማደስ</u>

1. የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የፈቃድ ጊዜ ገደቡ ሳያልቅ ከ1 አመት ባልበለጠና ከ6 ወራት ባላነሰ ጊዜ ውስጥ ባለሥልጣኑ ያዘጋጀውን የፈቃድ ማደሻ ቅጽ ሞልቶ የሰድሳት ማመልከቻውን ማቅረብ አለበት፡፡

2. ባለሥልጣኑ ፈቃዱን ከማደሱ በፊት የሬዲዮ ሞገዱ ለሌላ ተግባር አለመፈለጉን ማረጋገጥ አለበተ፡፡

3. ባለፈቃዱ በፈቃድ ዘመኑ የሰጠው አገልግሎት በተገልጋዩ ኅብረተሰብ ተቀባይነትን ያትኘና የተደጋጋሚ ቅሬታዎች ሪኮርድ የሌለበት መሆኑን ባለሥልጣኑ ማረጋገጥ አለበት፡፡

4. የታደሰ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ጸንቶ የሚቆይበት ጊዜ በባሰሥልጣኑ ይወሰናል፡፡

26. <u>የማስፋፊያ ፈቃድ</u>

1. የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ተጨማሪ ስርጭትን ለማካሄድ፣ የጣቢያዉን አቅም ለማሳደግ ወይም የቴክኖሎጂ ለውጥ ለማድረግና የማሠራጫ መሳሪያዉን አቅም ለማሳደግ ከፈለገ ከባለሥልጣኑ የማስፋፊያ ፈቃት ማግኘት አለበት፡፡

2. የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አገልግሎተ ከሚሰጥበተ አካባቢ ውጭ ሌሎች አካባቢዎችን ለማዳረስ አዲስ የሬዲዮ ሞገድ ሲጠየቅ፣ ባለሥልጣኑ የማስፋፊያ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት፣

ሀ/ ፈቃድ የተጠየቀበት ተጨማሪ የሬዲዮ ሞገድ በሌላ የብሮድካስት አገልግሎት

አለመያዙን፣ እና

ለ/ ፈቃድ የተጠየቀበትን አካባቢ የሕብረተሰብ ፍላጎት፣

ማረጋገጥ አለበት፡፡

3. የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ቀደም ብሎ ፈቃድ በወሰደበት የሬዲዮ ሞገድ የቴክኖሎጂ ማስፋፊያ ፈቃት ሲጠይቅ፣ የብሮድካስት አገልግሎቱን ለማስፋፋት የቀረቡት መግሪያዎች ከታቀደው የአገልግሎት ማስፋፊያ ዕቅድ ጋር መጣጣማቸውን ባለሥልጣኑ ማረጋገጥ አለበት፡፡

27. <u>የፈቃድና አመታዊ ክፍያ</u>

1. ማንኛዉም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃት ባለሥልጣኑ በየጊዜው እያጠና በሚወስነው መሠረት የፈቃድ ክፍያ፣ ዓመታዊ ክፍያና የፈቃድ ማደሻ ክፍያ መክፈል አለበት፡፡

2. አመታዊ ክፍያው የመንግሥት የበጀት ዓመተ በተጠናቀቀ በ60 ቀናተ ዉስጥ ካልተከፈለ ለዘገየበት ለያንዳንዱ ወር 5 በመቶ መቀጫ እየታከለበተ

ይከፈላል፡፡ ሆኖም የመቀጫዉ ጠቅላላ ድምር ከዋናው ክፍያ 50 በመቶ ሊበልጥ አይችልም፡፡

28. ፈቃድን ስለማገድ

1. የዚህ አዋጅ አንቀጽ 29 እንደተጠበቀ ሆኖ ማናቸውም የብሮድካስተ አገልግሎት ባሰፈቃድ በዚህ አዋጅ የተመለከቱተን ድንጋጌዎች ከጣሰ ባሰሥልጣኑ ፈቃዱን ሊያግድ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የሚደረግ እገዳ በጽሑፍ ሆኖ እገዳው የተደረገበት ምክንያትና ተፈጻሚ የሚሆንበት ቀን ተገልጾ ለባለፈቃዱ እንዲደርሰዉ መደረግ አለበት፡፤፡
3. በተሰጠዉ እገዳ ቅር ተሰኘ የብሮድካስት አገልግሎተ ባለፈቃድ የእግዱ ትዕዛዝ በደረሰዉ በ14 ቀናተ ውስጥ ቅሬታዉን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ለቦርዱ አቤቱታዉ በደረሰዉ በ30 ቀናተ ውስጥ ጡግኔ መስጠት አለበት፡፡

29. የብሮድካሰት ፈቃድን ስለመሰረዝ

1. የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ በባለሥልጣኑ ሲሠረዝ ይችላል፤
   ሀ/ ባለፈቃዱ ፈቃድ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በአንድ ዓመተ ጊዜ ውስጥ ሥርጭቱን ያልጀመረ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
   ለ/ ባለፈቃዱ ፈቃዱን ያገኘዉ በተጭበረበረ መንገድ መሆኑ ሲረጋገጥ፤
   ሐ/ የሥርጭት ጣቢያው ያለበቂ ምክንያት ሥርጭቱን ከአንድ ወር በላይ ሲያቋርጥ፤
   መ/ ጣቢያው በፍርድ ቤት ትዕዛዝ እንዲዘጋ ሲወሰን፤
   ሠ/ ባለፈቃዱ በራሱ አነሳሽነት ሥራውን ሲያቆም፤
   ረ/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 30(4) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተጥሰጡ ሲገኙ፤
   ሰ/ ባለፈቀዱ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 27 የተጣለበትን ግዴታ ያልተወጣ እንደሆነ።
2. በባለሥልጣኑ ውግኔ ቅር የተሰኘ ብሮትካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ውግኔው በደረ ሰው በ14 ቀናት ውስጥ አቤቱታውን ለቦርዱ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ ቦርዱም አቤቱዉ በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ ውግኔ መስጠት አለበት፡፡
3. የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1(ሀ) በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ሥርጭቱን ለመጀመር ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ያገጠመዉ መሆኑ በባለሥልጣኑ ተቀባይነት ካገኘ ሥሮጭቱን ለመጀመር የሚያስችል ከስድስት ወር የማይበልጥ ተጨማሪ ጊዜ ሊጨመርለት ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## በብሮድካስት አገልግሎት ባለፍቃዶች ስለሚሰራጩ ፕሮግራሞች

### 30. ጠቅላላ

1. ማንኛውም ለሥርጭት የሚቀርብ ፕሮግራም የተለያዩ አመለካከቶችን በማንጸባረቅ ሕብረተሰቡን እንዲያገለግል ሚዛናዊ ሆኖ መቅረብ አለበት፡፡
2. ማንኛውም ለሥርጭት የሚቀርብ ፕሮግራም ይዘቱና ምንጩ ተክክለኛ መሆኑ መረጋገጥ አለበት፡፡
3. ማንኛውም ዜና ከአድልዎ የጸዳ፣ ትክክለኛና ሚዛናዊ መሆን አለበት፡፡
4. ማንኛውም ለሥርጭት የሚቀርብ ፕሮግራም
   ሀ/ የሰዉ ልጆችን ሰብዕናና ነፃነት ወይም ሥነ ምግባርን የሚፃረር ወይም የሌሎችን እምነት የሚያንኳስስ፣
   ለ/ በመንግሥት ፀጥታ ወይም በሕገመንግሥቱ መሠረተ በተቋቋመው የመንግሥተ አስተዳደር ወይም በአገር መከላከያ ኃይል ላይ የወንጀል ድርጊት የሚፈጽም፣
   ሐ/ የግለሰብን፣ የብሔር ብሔረሰብን፣ የሕዝብን ወይም የድርጅተን ስም የሚያጠፋ ወይም በሐሰት የሚወነጅል፣
   መ/ ብሔረሰብን ከብሔረሰብ የሚያጋጭ ወይም በሕዝቦች መካከል የርስ በርስ ግጭት የሚያነሳሳ፣ ወይም
   ሠ/ ጦርነት የሚቀሰቅስ፣
   መሆን የለበትም፡፡

### 31. የልጆችን ደህንነት ስለመጠበቅ

1. የልጆችን አመለካከት፣ ስሜትና አስተሳሰብ ሊጎዱ የሚችሉና ወደ አልተፈለገ አቅጣጫ እንዲያዘነብሉ የሚገፋፉ የሬዲዮና የቴሌቭዥን ሥርጭተችን ልጆች ሊመለከቱና ሊያዳምጡ በሚችሉበት ሰዓት ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡
2. ከምሽቱ 5 ሰዓት እስከ ንጋቱ አስራ አንድ ሰዓት ድረስ ልጆች የሬዲዮና የቴሌቭዥን ስርጭተችን ሊያዳምጡና ሊመለከቱ አይችሉም ብሎ መገመት ይቻላል፡፡

32. <u>ስለአገራዊ፣ ክልላዊና አከባቢያዊ የሥርጭት ፕሮግራም</u>

1. ማንኛዉም አገር አቀፍ ስርጭት ከሳምንታዊ ስርጭት ጊዜዉ ቢያንስ 60 በመቶ ለአገራዊ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡
2. ማንኛዉም ክልላዊ ስርጭት ከሳምንታዊ የስርጭት ጊዜዉ ቢያንስ 60 በመቶዉ ክልሉን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡
3. ማንኛዉም አካባቢያዊ ስርጭት ከሳምንታዊ የስርጭት ጊዜዉ ቢያንስ 60 በመቶዉ አካባቢውን ለሚመለከቱ ፕሮግራሞች ማዋል አለበት፡፡

33. <u>ማስታወቂያ</u>

1. ማስታወቂያ ከሌሎች ፕሮግራሞች የተለየ መሆኑ በግልጽ እንዲታወቅ ሆኖ መተላለፍ አለበት፡፡ በሌሎች ፕሮግራሞች ይዘት ላይ ተጽዕኖ ማድረግም የለበትም፡፡
2. የንግድ ማስታወቂያ እዉነተኛ፣ የማያሳስትና ሕጋዊ የንግድ እንቅስቃሴን የሚያመለክት መሆን አለበት፡፡
3. የሌላውን ምርት ወይም አገልግሎት በማጥላላት ወይም በማንኳሰስ ማስታወቂያ ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡
4. የሥርጭት ጊዜው ከ20 ደቂቃ በማይበልጥ በማናቸውም ፕሮግራም ወይም በሕዓናት ፕሮግራም ጣልቃ ማስታወቂያ ማስተላለፍ የተከለከለ ነው፡፡

34. <u>የተከለከሉ ማስታወቂያዎች</u>

የሚከተሉት ማስታወቂያዎች በማናቸዉም የብሮድካስተ አገልግሎተ እንዳይተላለፉ ተከልክሏል፤

1. የሥርዓተ ፆታ እኩልነትን፣ የሴቶች ሰብአዊ መብትና ክብርን የሚያንኳስሱና የሚጋፉ ማናቸውም ማስታወቂያዎች
2. የሲጋራና ሲጋራ ነክ ማስታወቂያዎች፤
3. የአደንዛዥነት ባህርይ ያላቸው ዕጾችን የሚመለከቱ ማስታወቂያዎች፤
4. የአልኮል መጠናቸው ከ12 በመቶ በላይ ሆኑ መጠጦችን የሚመለከቱ ማስታወቂያዎች፤
5. ማናቸውም ያለ ሐኪም ትዕዛዝ ሊሰጡ የማይችሉ መድኃኒቶችን በቀጥታ ተጠቃሚ እንዲገዛ የሚገፋፉ ማስታወቂያዎች፣
6. ለሎች በሕግ የሚከለከሉ ማስታወቂያዎች፡፡

35. <u>ስለማስታወቂያ የሚመደብ ጊዜ</u>

ማስታወቂያ ጣቢያ ካልሆነ በቀር በማናቸውም የሥርጭት ጣቢያ ለማስታወቂያ የሚመደብ ጊዜ ከየዕለቱ ወይም ከአንድ ከተለየ ፕሮግራም የሥርጭት ጊዜ ውስጥ ከ20 በመቶ መብለጥ የለበትም፡፡

36. <u>በስፖንሰር ስለሚቀርብ ፕሮግራም</u>

1. በስፖንሰር የሚቀርብ ፕሮግራም ይዘትና የጊዜ ሠሌዳ በስፖንሰሩ ተፅዕኖ ሥር መውደቅ የለበትም፡፡ በተለይም በፕሮግራሙ ይዘት ዉስጥ የስፖንሰሩ ምርት ወይም አገልግሎት እንዲሸጥ ወይም እንዲከራይ መቀስቀስ የለበትም፡፡
2. ማስታወቂያ እንዳይነገርላቸዉ በሕግ የተከለከሉ ምርቶችን የሚያመርቱ ወይም የሚሸጡ ወይም አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ ሰዎች ስፖንሰር ሊሆኑ አይችሉም።
3. በስፖንሰሩና በጣቢያው መካከል ስምምነት ካልተደረገ በቀር ስፖንሰር በተደረጉ ፕሮግራሞች ጣልቃ ሌሎች የንግድ ማስታወቂያዎች እንዲገቡ አይፈቀድም።
4. በስፖንሰር በሚቀርብ ፕሮግራም የስፖንሰር አድራጊው ስም ቢያንስ በፕሮግራሙ መጀመሪያና መጨረሻ ላይ መገለጽ አለበት፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የባለፍቃድ ግዴታዎች</u>

37. <u>ተጠሪን ስለማሳወቅ</u>

1. የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ለሚያሰራጨዉ ፕሮግራም ኃላፊ አድርጎ የሚመደበዉን ሰው ባለሥልጣኑ ማስታወቅ አለበት፡፡ በኃላፊነት የተመደቡት ሰዎች ከአንድ በላይ ከሆኑ የእያንዳንዱ ሰው ኃላፊነት ድርሻ በግልጽ ተለይቶ መታወቅ አለበት፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ የባለፈቃዱን ኃላፊነት አያስቀረዉም፡፡

38. <u>ፕሮግራም ቀርጾ ስለመያዝ</u>

1. የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ዜናን ጨምሮ ያሰራጨውን ፕሮግራም ለ30 ቀናት ቀርጾ ማስቀመጥ አለበት፡፡ በፕሮግራሙ ዉስጥ ቀደም ሲል የተቀረፀ ፕሮግራም ወይም ፊልም ተካተቶ ከሆነ አብሮ መቀመጥና በተፈለገ ጊዜ ሊገኝ መቻሉ መረጋገጥ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተመለከተጡ የጊዜ ገደብ ከማለቁ በፊት በተላለፈዉ ፕሮግራም ላይ ቅሬታ ከቀረበ ቅሬታዉ አግባብ ባለው ሕግ ውግኔ እስከሚያገኝ ድረስ ሪከርዱ ተይዞ ይቆያል፡፡

3. ለቁጥጥር ወይም የቀረበ ቅሬታን ለመመርመር አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ባለፈቃዱ የያዘውን ፕሮግራም ቅጅ በራሱ ወጭ ለባለሥልጣኑ ወይም በሕግ መሠረት ጉዳዩን ለሚመለከተው አካል የማቅረብ አለበት፡፡

39. <u>መረጃን ስለመስጠት</u>

ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ በእያንዳንዱ ሥርጭት መጀመሪያና መጨረሻ ላይ ሥርጭት ጣቢያውን ስም መግለጽ አለበት፡፡ የፕሮግራሙ አዘጋጅም በፕሮግራሙ መጀመሪያ ወይም መጨረሻ በስም መጠቀስ አለበት፡፡

40. <u>ቁጥጥር እንዲደረግ ስለመፍቀድ</u>

ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ የማሠራጫ ጣቢያውን በዚህ አዋጅ አንቀጽ 44 መሠረት ለሚደረግ ቁጥጥር ክፍት የማድረግና የሚጠየቁ ሰነዶችንም የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡

41. <u>አስቸኳይ መንግስታዊ ማስታወቂያን ስለማስተላለፍ</u>

1. ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቱን አደጋ ላይ የሚጥል ሁኔታ በመከሰቱ፣ የተፈጥሮ አደጋ በማጋጠሙ ወይም የሕዝብን ጤንነት አደጋ ላይ ሚጥል በሽታ በመከሰቱ ምክንያት የፌዴራል መንግሥት ወይም ማንኛዉም ክልል የሚሰጣቸዉን አስቸኳይ መግለጫዎች ያለክፍያ ማስተላለፍ አለበት፡፡

2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) የተመለከተዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ሌሎች መንግሥታዊ ማስታወቂያዎች በሚተላለፉበት ጊዜ የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃዱ ክፍያ የመጠየቅ መብቱ የተጠበቀ ይሆናል፡፡

42. <u>መልስ የመስጠትን መብት ስለማስከበር</u>

1. ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ ባስተላለፈዉ ፕሮግራም መብቱ ተነክቷል ወይም በአግባቡ አልቀረበም ለሚል ሰው ስለጉዳዩ መልስ ለመስጠት ያለውን መብት ማክበር አለበት፡፡

2. ባለፈቃዱ መልስ ሰጭዉ የሚሰጠውን መልስ በተመጣጣኝና በተመግግይ ጊዜ በግልፅ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት፡፡

43. <u>የምርጫ ጊዜ መግለጫዎችን ስለማስራጨት</u>

1. ማንኛውም የብሮድካስት አገልግሎት ባለፈቃድ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተመዝግበዉ የሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ድርጅቶችና የምርጫ ዕጩ ተወዳዳሪዎች በምርጫ ወቅት ዓላማቸዉንና ፕሮግራሞቻቸዉን ለሕዝብ እንዲያስተዋዉቁ ወይም መግለጫ እንዲያስተላልፉ ነፃ የአየር ጊዜ መመደብ አለበት፡፡ አፈጻጸሙ ሚኒስቴሩ በሚጸዉ መመሪያ ይወሰናል፡፡
2. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም ፖለቲካ ድርጅት ወይም ዕጩ ተወዳዳሪ የምርጫ ወቅትር ማስታወቂያ ማስተላለፍ ይችላል፡፡
3. ለምርጫ ዉድድር ማስታወቂያ የሚጠየቀዉ ክፍያ ለንግድ ማስታወቂያ ከሚጠየቀዉ ክፍያ ሊበልጥ አይችልም።
4. የሥርጭት ጊዜ የተሰጠዉ የፖለቲካ ድርጅት ወይም ዕጩ ተወዳዳሪ ለተሠራጨዉ ፕሮግራም ወይም መግለጫ ሕጋዊነት ኃላፊ ይሆናል፡፡

## <u>ክፍል ስድስት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### 44. <u>ቁጥጥር የማድረግ ስልጣን</u>

1. ባለሥልጣኑ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎችና በዚህ አዋጅ መሠረት የሰጣቸው ውሳኔዎች መከበራቸዉን ለማረጋገጥ ኢንስፔክተሮችን ለመመደብ ይችላል፡፡
2. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመደበ ኢንስፒክተር የብሮድካስት አገልግሎት በሚያካሂድ ድርጅት ውስጥ በሥራ ሰዓት ለመግባትና ቁጥጥር ለማድረግ ይችላል፡፡
3. ኢንስፒክተሩ ቁጥጥር ሲያደርግ ማንኛውንም የብሮድካስት መግሪያ ለመመርመር፣ አግባብ ያላቸውን ሰነዶች ለማየትና ቅጅዉ እንዲሰጠዉ ለመጠየቅ ይችላል፡፡
4. ኢንስፒክተሩ ቀጥጥር ወደሚያደርግበት ሥፍራ ለመግባት የመታወቂያ ወረቀቱን ማሳየት አለበተ፡፡

### 45. <u>ቅጣት</u>

በወንጀል ሕግ የበለጠ ቅጣት የሚያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር፣

1. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 18 በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ሰዉ ከብር 50000 በማያንስና ከብር 100000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤

2. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 30 ንዑስ አንቀጽ (1)፣(2) ወይም (3) በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ባለፈቃድ ከብር 100000 በማያንስና ከብር 50000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
3. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 31 በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ባለፈቃድ 10000 በማያንስና ከብር 25000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
4. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 33(2) ወይም አንቀጽ 34 በመተላለፍ ጥፋት የፈጸመ ባለፈቃድ ከብር 20000 በማያንስና ከብር 30000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
5. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 33 ንዑስ አንቀጽ (1)፣ (2) ወይን (4)፣ አንቀጽ 35 ወይም 36 በመተላለፍ ጥፋተ የፈጸመ ባለፈቃድ ለመጀመሪያ ጊዜ ከባለሥልጣኑ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይለጠዋል፤ ድጋሚ ጥፋት ከፈጸመ ከብር 5000 በማያንስና ከብር 10000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
6. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 37 ወይን 39 በመተላለፍ ጥፋተ የፈጸመ ባለፈቃድ ለመጀመሪያ ጊዜ ከባለሥልጣኑ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ይለጠዋል፤ ድጋሚ ጥፋት ከፈጸመ ከብር 5000 በማያንስና ከብር 15000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፤
7. የዚህን አዋጅ አንቀጽ 39 ወይን 43 በመተላለፍ ጥፋተ የፈጸመ ባለፈቃድ ከፈጸመ ከብር 20000 በማያንስና ከብር 50000 በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፣

46. <u>ስለዉርስ</u>

የዚህን አዋጅ አንቀጽ 30(4) የተመለከተዉን ድንጋጌ በመተላለፍ አግባብነት ባለዉ የወንጀል ህግ ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰዉ ከዋናዉ ቅጣት በተጨማሪ አግባብነት በብሮድካስተ አገልግሎት ያዋለዉ ንብረት ይወረሳል፡፡

47. <u>ደንብና መመሪያ የማዉጣት ስልጣን</u>

ይህን አዋጅ በሚገባ ሥራ ላይ ለማዋል አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን የሚኒስትሮች ምክር ቤት፣ መመሪያዎችን ሚኒስትሩ ማዉጣት ይችላሉ፡፡

48. <u>የተሻረ ህግ</u>

የብሮድካስት አዋጅ ቁጥር 178/1991 በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

49. <u>ሌሎች ሕጎች ተፈፃሚነት</u>

1. የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ አግባብነት ያላቸዉ የሀገሪቱ የፕሬስ አዋጅ ድንጋጌዎች አግባብ ያላቸው ድንጋጌዎች በብሮድካስት አገልግሎት ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡
2. የዚህን አዋጅ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛዉም ሕግ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱ ጉዳዮችን በሚመለከት ተፈጻሚነተ አይኖረጡም፡፡

50. **<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ 16 ቀን 1998**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

## አዋጅ ቁጥር 590/2000

## የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት ሀሳብን በነጻ የመግለፅና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት የተረጋገጠ በመሆኑ፣

መገናኛ ብዙሃን በነፃነት ለመንቀሳቀስ ይችሉ ዘንድ የቅድሚያ ምርመራ ገደብ እንዳይጣልባቸው ሕገ መንግሥቱ ዋስትና የሰጠ መሆኑን በአጽንኦት በመገንዘብ፤ የወጣቶች ደህንነት፣ የሰውን ክብርና መልካም ስም፣ ብሔራዊ ደህንነትን፣ የህዝብ ሰላምና ፀጥታን እንዲሁም ሌሎች ተነጻጻሪ መብቶችና ጥቅሞችን ለማስጠበቅ ሲባል በግልጽ በሚደነገጉ ሕጎች ብቻ ሃሳብን በነፃ በመግለፅና በመገናኛ ብዙሃን ነፃነት ላይ ገደቦች እንዲጣሉ የሚያዘውን ህገ መንግስታዊ መርህ በማረጋገጥ፣ በዜጎች መሀከል በሚደረገው ነፃ የሀሳብና የመረጃ ልውውጥ እንዲሁም በመገናኛ ብዙሃን የአሰራር ነፃነት ላይ መሰናክል የነበሩ ተቋማዊ እና መዋቅራዊ ችግሮችን በማስወገድ በነፃ ሀሳብን የመግለፅና የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን አስመልክቶ ያዳበርናቸውን አዎንታዊ እና ገንቢ ልምዶች የመጠ በቅና ይበልጥ የማጠናከርን አስፈላጊነት በመረዳት፣ በሀገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአትን ለመገንባት የሚደረገው ጥረት ስኬታማ የሚሆነው መተኪያ የሌለው ታላቅ ሚና መጫወት የሚችል ራሱን በከፍተኛ ስነምግባር በማነፅ በከፍተኛ ሙያዊ ብቃት የሚንቀሳቀስ ነፃና ፈርጀ ብዙ የመገናኛ ብዙሃን ሲኖር ብቻ መሆኑን በመገንዘብ፣

መገናኛ ብዙሀን በህገ መንግስቱ ለተረጋገጡ መሰረታዊ ነፃነቶችና መብቶች መከበር እንዲሁም ለሰላም፣ ለእኩልነት፣ ለፍትህና ለዴሞክራሲ የቆሙ መሆኑን በመረዳት። መገናኛ ብዙሃን አጋላጭ የሆኑትን ጨምሮ መረጃዎችን የመሰብሰብና የማሰራጨት መብት ያላቸው መሆኑን በመገንዘብ፣ በህዝቦች መካከል ነጻ የሃሳብና የመረጃ ልውውጥን የሚያመቻችና ዜጎች በነጻ መረጃና አስተያየትን ለመሰብሰብ፣ ለመቀበልና ለማስተላለፍ ያላቸውን መብት ሙሉ በሙሉ እንዲያረጋግጡ የሚያስችላቸው ጤናማ የመረጃ ስርዓት ያልተገደበ ዲሞክራሲያዊ የህዝብ ውይይት መድረክ በመሆን ለሚያገለግል ነጻ የመገናኛ ብዙኃን ህልውና እጅግ አስፈላጊ መሆኑን በመገንዘብ፣

የመንግስት ግልፅ አሰራር በተለይም የማንኛውም ግለሰብ በመንግስት አካላት እጅ የሚገኙ መረጃዎችን የማግኘት መብት ለዴሞክራስያዊ ህብረተሰብ ያለውን መሰረታዊ ጠቀሜታ በመረዳት፣

በህገ መንግስቱ የተረጋገጡትን የመንግስታዊ አሰራርና የተጠያቂነትን እሴቶች ለማዳበርና ይበልጥ ለማጠናከር እንዲሁም የህዝብ ጥቅምን የሚመለከቱ ጉዳዮች ይፋ

ወጥተው ህዝብ እንዲወያይባቸው ለማድረግ ይቻል ዘንድ፤ የመንግስት ኃላፊዎች ለግለሰቦችና ለመገናኛ ብዙሃን መረጃዎችን የማቅረብ ግዴታ በህግ እንዲጣልባቸው ለማድረግ፣

በስራ ላይ ያለውን የፕሬስ አዋጅ በማሻሻል በኢትዮጵያ በመካሄድ ላይ ከሚገኘው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ጋር በሚጣጣም አዲስ መተካቱ አስፈላጊ መሆኑን በመረዳት፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ 55(1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

   ይህ አዋጅ " የመገናኛ ብዙሃንና የመረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 ዓ ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. **ትርጓሜ**

   የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው አልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፦

   1. የመገናኛ ብዙሃን ማለት በየጊዜው የሚወጡ ህትመቶችንና ብሮድካስቶችን የሚያካትት የህትመት ሥራ ነው።
   2. የህትመት ሥራ ማለት መገናኛ ብዙሃንንና እንዲሁም ለህዝብ እንዲደርሱ ታስበው የሚሰራጩ የሙዚቃ ስራዎችን፣ የኦዲዮ፣ የቪዥዋል ወይም የኦዲዮቪዥዋል ሥራዎችን፣ ስዕሎችን፣ ተውኔቶችን፣ ካርቱኖችን፣ መጽሀፍትን፣ በራሪ ጽሁፎችን፣ ፊልሞችን ፣ ፖስተሮችን፣ የንግድ ማስታወቂያዎችን፣ የዜና አገልግሎትንና ማንኛውም አይነት ሌሎች ህትመቶችን የሚያካትት ሲሆን፣

      ሀ/ በህግ አውጪ፣ በዳኝነትና በሕግ አስፈፃሚ አካላት ታትመው የሚወጡ ይፋዊ መግለጫዎችን፣ ማስታወቂያዎችን፣ ቃለ ጉባኤዎችን፣ ሪፖርቶችን ወይም ውሳኔዎችን፣ ወይም

      ለ/ለንግድና ለትራንስፖርት፣ ለቤት ውስጥ አገልግሎትና ለማህበራዊ ጉዳዮች ታስበው የሚታተሙ ፎርሞችን የዋጋ ሰንጠረዦችን፤ የንግድና የቤተሰብ ማስታወቂያዎችን፣ ፓስት ካርዶችን፣ ተባዝተው የሚሸጡ ስእሎችን፣ የንግድና አስተዳደር አመታዊ ሪፖርቶችን ወይም የምርጫ ሰነዶችን፣ አያካትትም።

3. በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ማለት አንድ ቋሚ ስያሜ በመያዝ በተወሰነ የጊዜ ክፍተት ሳይቋረጥ በተከታታይ እንዲወጣ ታቅዶ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚታተም፤አጠቃላይ ስርጭት ያለውና በጠቅላላው ህብረተሰብ ወይም በአንድ በተወሰነ የህዝብ ክፍል እንዲነበብ ታስቦ የሚሰራጭ ጋዜጦችንና መፅሄቶችን የሚያካትት የሕትመት ሥራ ነው።

4. ብሮድካስተር ማለት የግል ወይም የመንግስትን ውስጣዊ ግንኙነቶችን የማያካትትና ምድር ለምድር አስተላላፊ ትራንስሚተሮችን፣ ኬብሎችንና ሳተላይትን በመሰሉ ማሰራጫዎች አማካይነት በሬድዮ ወይም በቴሌቪዥን የብሮድከስት መልእክት መቀበያዎች ወይም በሌላ ኤሌክትሮኒክስ መቀበያዎች አማካይነት በክፍያ ወይም ያለክፍያ የብሮድከስት ፕሮግራሞችን በአንድ ጊዜ ህዝብ እንዲያደምጣቸው እና እንዲመለከታቸው ወይም እንዲሰማቸው የሚያሰራጭ ሰው ማለት ነው።

5. የመንግስት አካል ማለት በፌደራል ወይም በክልል ሕገ መንግስት ወይም በሌላ ሕግ መሰረት የተቋቋመ ወይም በፌደራል ወይም በክልል መንግስታት መዋቅር ውስጥ በየትኛውም እርከን ላይ የሚገኝ ወይም በፌዴራል ወይም በክልል መንግስታት የባለቤትነት ይዞታ ስር የሚገኝ ወይም ዋነኛ የፋይናንስ ምንጩን በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ከነዚሁ አካላት የሚያገኝ ወይም ተጠሪነቱ ለፌደራል ወይም ለክልል መንግስት የሆነ ማንኛውም አካል ማለት ነው ።

6. መረጃ ማለት በማናቸውም አይነት ቅርፅ የተቀናበረ ማንኛውም ሰነድ ማለት ነው።

7. ሰነድ ማለት በማንኛውም አካል በማንኛውም ጊዜ የተፈጠረ ወይም የተዘጋጀ ቢሆንም በመንግስት አካል ይዞታና ቁጥጥር ስር የሚገኝ፣

   ሀ/ ማንኛውንም መዝገብ፣ ፋይል፣ በእጅ ወይም በማሽን የተጻፈ ረቂቅ፣

   ለ/ ማንኛውንም ማይክሮ ፊልም፣ ማይክሮፊች እና በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ የወጣ የመዝገብ ግልባጭ፣

   ሐ/ የጎሉ ባይሆኑም፣ ማንኛውም በነዚህ ማይክሮፊልሞች ውስጥ ያሉ ምስሎች ቅጅ ፣

   መ/ በኮምፒዩተር ወይም በሌላ በማንኛውም መሳሪያ በመታገዝ የሚታዩ፣ የሚነበቡ፣ የሚደመጡ ወይም የሚታወቁ መረጃዎችን ወይም

   ሠ/ በማንኛውም አይነት ቅርፅ ወይም የማስተሳሰሪያ ዘዴ የሚገኝ፣ የአመንጪው ወይም የአዘጋጁ አካል ማንነት እና የተዘጋጀበት ወይም

የመነጨበት ጊዜ ልዩነት ሳይኖረው በመንግስት አካል ይዞታና ቁጥጥር ስር የሚገኝ ማንኛውንም መረጃ ያካትታል።

8. የግለሰብ መረጃ ማለት ተለይቶ የሚታወቅ ግለሰብን የሚመለከት ሆኖ፡-

ሀ/ የግለሰቡን የህክምና፣ የትምህርት ወይም የአካዳሚክ፣ የስራ አገልግሎት፣ የሙያ፣ የወንጀል ታሪኩን የሚመለከት መረጃንና ግለሰቡ ያደረጋቸውን የንግድ ግንኙነቶች የሚመለከት መረጃዎችን ወይም

ለ/ የግለሰቡን ዘር፣ ብሔር፣ ማህበራዊ ምንጩን፣ እድሜ፣ እርግዝና፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ የቆዳ ቀለሙን፣ የፍትወት ዝንባሌውን፣ አከላዊና አእምሮአዊ ጤንነቱን፣ የጤና ብቃቱንና ጉድለቶቹን፣ ሀይማኖቱን፣ እምነቱን፣ ህሊናውን፣ ባህሉን፣ ቋንቋውን፣ ልደቱን የሚመለከት መረጃን፣ ወይም

ሐ/ የግለሰቡን የመለያ ቁጥሮች፣ ምልክቶች ወይም መለያዎች፣ አድራሻውን፣ አሻራውን ወይም የደሙን አይነት የሚመለከት መረጃን፣ ወይም

መ/ ስለሌላ ግለሰብ ወይም ግለሰብ የማእረግ እድገት፣ ሽልማት ወይም የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኝ በቀረበ ሀሳብ ላይ በሰጣቸው አስተያየቶች፣ አመለካከቶች ወይም አማራጭ ሀሳቦች ውስጥ የማይካተቱ የግል አስተያየቶቹን፣ ሀሳቦቹን ወይም ምርጫዎቹን የሚመለከቱ መረጃዎችን፣ ወይም

ሠ/ የአስተያየት ሰጭው ስም የተወገደበትና ግለሰቡን የሚመለከቱ ወይም ግለሰቡ የገንዘብ ድጋፍ፣ ሽልማት ወይም የማእረግ እድገት እንዲያገኝ በቀረበ ሀሳብ ላይ ግለሰብ የሰጣቸው የግል አስተያየቶች፣ አመለካከቶች ወይም አማራጭ ሀሳቦችን የያዘ መረጃን፣ ወይም

ረ/ ሌላ ሰው ስለግለሰቡ ያለውን አመለካከት ወይም የሰጠውን አስተያየት የያዛ መረጃን፣ ወይም

ሰ/ ግለሰቡን በሚመለከቱ ግላዊ መረጃዎች ጋር የተያዘውን ወይም መግለፁ በራሱ ግለሰባዊ መረጃን የመግለጽ ውጤትን ሊያስከትል የሚችል የግለሰብን ስም የያዘ መረጃን፣ የሚያካትት ሲሆን በምንም ሁኔታ ከሞተ 20 ዓመት የሞላው ግለሰብን የሚመለከት መረጃን ግን አያካትትም።

9. ሶስተኛ ወገን ማለት ከመረጃ ጠያቂው ውጪ ወይም መረጃውን ከተጠየቀው የመንግስት አካል ውጭ የሆነ ማንኛውም ሰው ወይም ማንኛውም የመንግሥት አካል ማለት ሲሆን፣ የውጪ ሀገር መንግሥትን፣ መንግሥታዊ አካልን፣ ድርጅትን ወይም አለም አቀፍ ድርጅት ወይም አካልን ያካትታል፡፡

10.የጠላትና የአማጺያን እንቅስቃሴዎች ማለት፡

ሀ/ በሀገሪቱ ላይ የተቃጣ የወራሪ ድርጊት፣

ለ/ በሀገሪቱ ወይም በህዝቡ ወይም በሀገሪቱ ስትራቴጂካዊ ጥቅሞች ላይ ያነጣጠሩ የውስጥ ወይም የውጪ የአሻጥር ወይም የሽብር ተግባራት፣

ሐ/ ህገ መንግሰታዊ ስርዓቱን በኃይል ወይም በአመጽ መለወጥን ዓላማው ያደረገ እንቅስቃሴ፣ ወይም

መ/ ማንኛውም የውጭ ሀገር የስለላ ተግባራት ወይም የጠላት እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡

11. ዋና አዘጋጅ ማለት በአንቀፅ 6 በተደነገገው መሰረት ሙሉ የኤዲቶሪያል ስልጣን ያለው ሰው ነው።

12. አሳታሚ ማለት መገናኛ ብዙኃኑን የሚወክል ወይም መገናኛ ብዙኃኑ ባለቤት የሆነ፣ በድርጅቱ ውስጥ የጎላ የባለንብረትነት ጥቅም ያለው ወይም የድርጅቱን የሥራ አስተዳደር የሚመራ ማንኛውም ሰው ነው።

13. አታሚ ማለት የህትመት ስራዎችን ለማተም በአሳታሚው የተሾመ ወይም ከአሳታሚው ጋር የተዋዋለ ማንኛውም ሰው ነው።

14.አከፋፋይ ማለት የህትመት ሥራዎችን በጅምላ ለማከፋፈል ወይም ለማሰራጨት በአሳታሚው የተሾመ ወይም ከአሳታሚው ጋር የተዋዋለ ሰው ነው።

15. አስመጪ ማለት የመገናኛ ብዙሃን ውጤቶችን ሀገር ውስጥ ለማሰራጨት በማሰብ ወደ ሀገር የሚያስገባ ወይም በሀገር ውስጥ የሚሰራጩ የውጭ ህትመቶች ወኪል የሆነ ማንኛውም ሰው ነው።

16.የህዝብ እንባ ጠባቂ ማለት በአዋጅ ቁጥር 211/1992 ዓ.ም መሠረት የተቋቋመ የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ነው፡፡

17.ክልል ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም ሲባል አዲስ አበባንና ድሬዳዋን ይጨምራል።

18. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ማለት የህዝብ ግንኙነት ስራን ለማከናወን በመንግስት አካል የተመደበ ወይም የተሾመ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊ ወይም ሌላ ኃላፊ ማለት ነው።

19.ሰው ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በህግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

3. **ስለፆታ አገላለፅ**

በግልጽ የተደነገገ ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል።

4. **መገናኛ ብዙኃን ነፃ ስለመሆናቸው**

   1. የመገናኛ ብዙሃን ነፃነት በሕገ መንግሥቱ ዕውቅና አግኝቷል። ቅድመ ምርመራ በማንኛውም መልኩ የተከለከለ ነው
   2. በመገናኛ ብዙሃን ነፃነት ላይ ገደቦች የሚጣሉት ሕገ መንግስቱን መሠረት በማድረግ በሚወጡ ሕጎች ብቻ ይሆናል፡፡
   3. ማንኛቸውም የመንግስት አካል የመገናኛ ብዙሃን ማህበራዊ ተግባራቸውን ለመወጣት

      ሀ/ ዜና ወይም መረጃን የመሰብሰብ፣ የመቀበልና የማሰራጨት፣

      ለ/ በልዩ ልዩ ጉዳዮች ላይ አስተያየት ወይም ትችት የማቅረብ፣ ወይም

      ሐ/ የተለያዩ ሌሎች ዘዴዎችን በመጠቀም የሕዝብን አስተያየት በመቅረጽ ሂደት የመሳተፍ፣

      መብታቸውን ማክበር ይኖርበታል።
   4. በንኡስ አንቀጽ /2/ መሰረት በግልፅ የተደነገጉ ህጎች ከሌሉ በስተቀር የመገናኛ ብዙሃን ነፃነትን የሚያስተጓጉሉ ማናቸውም አስተዳደራዊ ርምጃዎች ተከልክለዋል።

5. **የማሳተም እና የመደራጀት መብት**

   1. በአንቀፅ 7 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛውም ዜግነቱ ኢትዮጵያዊ የሆነ ሰው የመገናኛ ብዙሃን ስራ የመስራት መብት አለው።
   2. ጋዜጠኞች በመረጡት የሙያ ማህበር ራሳቸውን የማደራጀት መብት አላቸው፡፡

## ክፍል ሁለት

## በመገናኛ ብዙኃን ሥራ የመሰማራት መብት

6. **ዋና አዘጋጅ**

   1. በመገናኛ ብዙኃን ዋና አዘጋጅነት የሚሾም ሰው ሥልጣን የሚታተሙትን ህትመቶች ይዘት የመቆጣጠርና ማንኛውም ነገር ያለፍቃዱ እንዳይታተም ማድረግን ያካትታል። ይህን ሥልጣን የሚገድቡ ማናቸውም አሰራሮች ወይም ስምምነቶች በህግ ፊት ድድቅና ፈራሽ ናቸው።

2. የመገናኛ ብዙሃኑ ዋና አዘጋጅ በማንኛውም ምክንያት የተሟላ የህግ ችሎታ የሌለው ከሆነ የተሟላ የህግ ችሎታ ያለው ሃላፊ አዘጋጅ መሾም ይኖርበታል።

3. በንኡስ አንቀፅ 2 መሰረት ለሃላፊነት የተሾመው ዋና አዘጋጅ ለመገናኛ ብዙሃኑ ውጤት ይዘቶች ሙሉ የህግ ተጠያቂነት ያለበት ሲሆን በንዑስ አንቀፅ 1 የተደነገገው ቢኖርም ማንኛውም ነገር ያለፍቃዱ ታትሞ እንዳይወጣ የማድረግ ስልጣን አለው፡፡

7. <u>የመገናኛ ብዙሃን ባለቤትነት</u>

1. ለአገር አቀፍ ወይም ቁጥሩ ከአንድ መቶ ሺ በላይ የሆነ የተመዘገበ ነዋሪ ለሚገኝበት አካባቢ ወይም ክልል የብሮድካስት ፈቃድ ከያዘ ኩባንያ ጠቅላላ ካፒታል ወይም አክስዮን ውስጥ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ማንኛውም ሰው ተመሳሳይ ፈቃድ በያዘ እና በተመሳሳይ ወይም በተደራራቢ የገበያ አካባቢ የብሮድካስት አገልግሎት ከሚሰጥ ሌላ ኩባንያ ጠቅላላ ካፒታል ወይም አክስዮን ላይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር ሊኖረው አይችልም።

2. ለአገር አቀፍ ወይም ቁጥሩ ከአንድ መቶ ሺ በላይ የሆነ የተመዘገበ ነዋሪ ካለበት አካባቢ ወይም ሰፍራ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ በያዘ ኩባንያ ካፒታል ወይም አክስዮን ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ማንኛውም ሰው በዚሁ አካባቢ ወይም በተደራራቢ የገበያ አካባቢ የሚሰራጭ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ስራን ከሚሰራ ሌላ ማንኛውም ኩባንያ ጠቅላላ ካፒታል ወይም አክስዮን ላይ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር ሊኖረው አይችልም።

3. በንዑስ አንቀጽ 1 እና 2 የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በየጊዜው የሚወጣ ሕትመት ስራን የሚሰራ ኩባንያ ካፒታል ወይም አክስዮን ይይ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ማንኛውም ሰው በተመሳሳይ ቋንቋ በሚታተምና በተመሳሳይ ወይም በተደራራቢ ገበያ የሚሰራጭ የህትመት ሥራን ከሚሰራ ሌላ ኩባንያ ካፒታል ወይም አክስዩን ላይ ውጤታማ ቁጥጥር ሊኖረው አይችልም።

4. ከንዑስ አንቀጽ 1 እስከ 3 ባሉት ድንጋጌዎች የተመለከተውን የአክሲዮን ውጤታማ ቁጥጥር የሚወስንበትና የመለኪያ ቅኝቱ የሚያከናውንበት ሥነ ሥርዓት በሕግ ተደንግጎ እስኪወጣ ድረስ ሌላ ተቃራኒ ማስረጃ ካላቀረበ በስተቀር ማንኛውንም ኩባንያ ወይም ድርጅት አክሲዮኖች ወይም ካፒታል

በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋዘሪ ከ15 በመቶ በላይ የያዘ ማንኛውም ሰው ውጤታማ ቁጥጥር እንዳለው ይገመታል።

5. ለአንቀጽ 5 /1/ አፈፃፀም ሲባል አንድ ኩባንያ ኢትዮያዊ ኩባንያ ነው የሚባለው የኩባንያው የካፒታል ምንጭ ሙሉ በሙሉ ከሀገር ውስጥ የሆነ እና የአክስዮኑ ባለድርሻዎች በሙሉ ኢትዮጵያዊ ዜግነት ያላቸው እንደሆነ ሲሆን የውጭ አገር ሰዎች የአክስዮኑ ባለድርሻዎች የሆኑበት ድርጅት አክሲዮን የያዘበትን ኩባንያ አያካትትም።በተመሳሳይ አንድ ማህበር የሀገር ውስጥ ማህበር ነው የሚባለው በበጎ አድራጎት ድርጅቶችና ማህበራት ሕግ መሰረት እንደ አገር በቀል ማህበር ሲመዘገብ ነው፡፡
6. በሕግ የሰውነት መብት ከተሰጠው አካል ወይም ድርጅት በስተቀር ማንኛውም ሰው የብሮድካስት አገልግሎት ስራን፣ በየጊዜው የሚወጡ ሕትመቶችን ወይም የዜና አገልግሎት ስራን ለመስራት አይችልም ።
7. ሀገር ውስጥ ለማሰራጨት ሲባል ወደ ኢትዮጵያ የሚገባና ዋነኛ አትኩሮቱ በሀገር ውስጥ ጉዳዮች ላይ የሆነ ማንኛውም የውጭ ሀገር የመገናኛ ብዙሃን ላይ የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

8. <u>አከፋፋዮች</u>

በየጊዜው የሚወጡ ህትመቶችን የማከፋፈል ስራ የሚሰሩ ድርጅቶች የህትመቶቹን ይዘት መሰረት በማድረግ የአገልግሎትም ሆነ የክፍያ ልዩነት ማድረግ የለባቸውም፡፡

9. <u>የምዝገባ የምስክር ወረቀት</u>

1. ማንኛውም በየጊዜው የሚወጣ የህትመት ወይም የዜና አገልግሎት ስራ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚያገኘው ስርጭቱ ከአንድ ክልል በላይ ከሆነ ከማስታወቂያ ሚኒስቴር ሲሆን ስርጭቱ በአንድ ክልል ውስጥ የተወሰነ ከሆነ የምዝገባ ምስክር ወረቀት የሚያገኘው ከክልሉ ማስታወቂያ ቢሮ ይሆናል።
2. ማንኛውም አካል፣ ድርጅት ወይም መንግሥታዊ አካል ዓላማውን ለማራመድ ወይም ለማከናወን በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ማሳተም ካስፈለገው በንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት እንደተመዘገበ ይቆጠራል፡፡
3. የምዝገባ ማመልከቻ የሚከተለውን ዝርዝር መያዝ አለበት

   ሀ/ የአሳታሚውን ድርጅት ስምና አድራሻ

   ለ/ በየጊዜው የሚወጣው ህትመትወይም የዜና አገልግሎት ድርጅቱ ስም

እንዲሁም ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች ካሉ አድራሻቸውን፣ እና

ሐ/ በአሳታሚው ወይም በዜና አገልግሎት ድርጅቱ ከ2 በመቶ የበለጠ የአክስዮን ድርሻ ያላቸውን ሰዎች ስም አድራሻና የአክስዮን ድርሻቸውን መጠን ፤

4. አስቀድሞ ከተመዘገበ በየጊዜው ከሚወጣ ህተመት ጋር አንድ አይነተ ወይም ተመሳሳይ በሆነ ስም ወይም አርማ ሌላ በየጊዜው የሚወጣ ህተመት አሳትሞ ለማውጣት የምዝገባ ሰርተፊኬት ጥያቄ የቀረበ ከሆነና የሁለቱ ህትመቶች መመሳሰል የሚያሳስት ከሆነ በየጊዜው የሚወጣው ህተመት በሌላ ስያሜ ወይም አርማ እንዲመዘገብ ይደረጋል፡፡

5. የማስታወቂያ ሚኒስቴር ወይም የክልሉ ማስታወቂያ ቢሮ ማመልከቻ በቀረበለት በ30 ቀናት ውስጥ የምዝገባ የምስክር ወረቀት ካልሰጠ ወይም ያልሰጠበትን ምክንያት በጽሁፍ ለአመልካቹ ካላሳወቀ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም የዜና አገልግሎት እንደተመዘገበ ይቆጠራል።

6. በንዑስ አንቀፅ 3 በተዘረዘሩት ሁኔታዎች ላይ በየጊዜው የሚወጣ ሕትመት አሳታሚ ወይም የዜና አገልግሎት ድርጅት ለውጡ በተከሰተ በ15 ቀናት ውስጥ ለመዝጋቢው የተደረገውን ለውጥ ማሳተቅ አለበት፡፡

7. የምዝገባ በርተፊኬት ሊሰረዝ የሚችለው፣

ሀ/ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም የዜና አገልግሎት ስራ ሲሆን አሳታሚው ወይም ድርጅቱ ስራውን ማቆሙን በጽሁፍ ሲያሳውቅ ወይም

ለ/ በየጊዜው ለሚወጣ ሕትመት ወይም የዜና አገልግሎት ስራ የምዝገባ የምስክር ወረቀት የተሰጠው ሰው ከተመዘገበበት ጊዜ ጀምሮ ባለው አንድ አመት ጊዜ ውስጥ ህትመቱን ማውጣት ያልጀመረ ወይም የዜና አገልግሎት ስራውን ያልጀመረ እንደሆነ ነው።

8. የንዑስ አንቀፅ 7 ድንጋጌ እንደአግባቡ በንዑስ አንቀፅ 2 ላይም ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

10. <u>በህትመት ላይ የሚገፁ ነገሮች እና ያለ ክፍያ የሚሰጡ ቅጅዎች</u>

1. ማንኛውም አይነት በየጊዜው የሚወጣ ህትመት በያንዳንዱ እትም ላይ የአሳታሚውን፣የአታሚውን፣ የዋና አዘጋጁን ሰምና አድራሻ፣ የህትመቱን ቅፅ፣ ቁጥር፣ ህትመቱ የሚወጣበትን ጊዜ እና ታትሞ የወጣበትን ቀን፣ ወርና አመተ ምህረት በግልጽ በሚታይ ቦታ ላይ ማስፈር አለበት፡፡

2. ማንኛውም ብሮድካስተር በያንዳንዱ ፕሮግራም መጀመሪያና ማብቂያ ላይ የጣብያውን ስምና ፕሮግራም፣ የፕሮግራሙን መሪ መግለፅ ይኖርበታል፡፡
3. ማንኛውም በአዲስ አበባ የሚሰራጭ ወይም አገር አቀፍ ስርጭት ያለው በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ታትሞ በወጣ ከሀያ አራት ሰአት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱን እተም ሁለተ ቅጂዎች ያለክፍያ ለብሄራዊ ቤተ መዛግብትና ቤተ መፃህፍት ኤጀንሲ መስጠት አለበት፡፡
4. በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ስርጭት በአንድ ክልል ብቻ የተወሰነ ከሆነ ታትሞ በወጣ ከሀያ አራት ሰዓት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የእያንዳንዱን እትምን ቅጂዎች ያለክፍያ ለክልሉ ቤተ መዘክር እና ማስታወቂያ ቢሮ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል ሶስት

## መረጃ የማግኘት መብት

### 11.ዓላማ

በዚህ ክፍል የተደነገጉ ድንጋጌዎች፣

1. ተነፃፃሪ የህዝብና የግለሰብ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ የወጡ ተገቢ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆኖ ከማንኛውም መንግስታዊ አካል ዜጎች መረጃን ለመጠየቅ፣ ለማግኘት እና ለማስተላለፍ ያላቸውን መብት ተፈፃሚ የማድረግ፣
2. መረጃ ፈላጊዎች መረጃዎችን በተቻለ መጠን በፍጥነትና በዝቅተኛ ውጪ ሳይደክሙ የሚያገኙበትን አሰራርና ስነ ስረአት በመመስረት መብቱን ተፈፃሚ የማድረግ፣ እና
3. የህዝብ ተሳትፎን የስልጣን ባለቤትነትን የማረጋገጥ እና እንዲሁም የአሰራር ተጠያቂነትና ውጤታማነት የሰፈነበት የመንግስት አሰራርንና መልካም አስተዳደርን የማጠናከር፣

አላማ አላቸው።

### 12.መረጃ ጠይቆ የማግኘት መብት

1. በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር ማንኛውም ሰው ከማንኛውም መንግስታዊ አካል መረጃን የመጠየቅ፣ የማግኘትና የማስተላለፍ መብት አለው፡፡
2. በንዑስ አንቀፅ 1 የተመለከተው መብት መረጃውን ወይም የመረጃውን ምንጭ የያዘ ሰነድ በማንኛውም መንግስታዊ አካል እጅ የሚገኝ መሆን አለመሆኑን በመጠየቅ የማወቅ መብትንና በመንግሥታዊ አካል እጅ የሚገኘውን ሰነድ፣

ሀ/ የመመልከት ወይም ማስታወሻዎችን የመውሰድ ወይም ጥቅሶችን የመገልበጥ፣

ለ/ ጉዳዩ በሚመለከተው መንግስታዊ አካል የተረጋገጠ ትክክለኛ ግልባጭ የመውሰድ፣ ወይም

ሐ/ በዲስኬቶች፣ በፍሎፒዎች ፣ በሌላ በማንኛውም አይነት የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ አማካይነት የመውሰድ ወይም ሰነዱ በኮምፒዩተር ወይም በሌላ መሳሪያ የሚገኝ ከሆነ ከዚሁ መሳሪያ ታትመው የወጡ ቅጂዎችን የመውሰድ፣ መብትን ያካትታል።

3. ይህ አዋጅ የመንግስት አካላት በአዋጁ ከተደነገጉት ስርአቶች ውጭ መረጃን የመስጠት ስልጣናቸውን እንደሚገድብ ተደርጎ መተርጎም አይኖርበትም።

## 13. አትሞ የማውጣት ግዴታ

1. ማንኛውም መንግስታዊ አካል፡

ሀ/ ስለመስሪያ ቤቱ መዋቅር፣አደረጃጀት፣ ስለ ዋና ተግባራቱና ኃላፊነቱ፣

ለ/ የኃላፊዎቹን ስልጣንና ኃላፊነት እንዲሁም በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተፈጻሚ ስለሚሆነው ሥነ ሥርአት፣

ሐ/ ለሕዝብ ስለሚሰጣቸው አገልግሎቶች ዝርዝር፣

መ/ ለተገልጋዩ ሕዝብ ስለተበጀው የቅሬታ አሰማምሥርዓትና ከሕዝብ ዘወትር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች የመሥሪያ ቤቱን ምላሽ የሚያሳዩ አጭር ዘገባዎችን፣

ሠ/ በእጁ ስለሚገኙ መዝገቦች አይነትና በመዝገቦቹ ውስጥ ስለሚገኙ መረጃዎች ይዘት አጭር ማብራሪያ እንዲሁም መረጃ ለማግኘት የሚፈልጉ ሰዎች የመረጃ ጥያቄዎች አቀራረብ ሥነ ስርአት ዝርዝር ማብራሪያዎችን፣

ረ/ የመሥሪያ ቤቱ መተዳደሪያ ደንብ ፣የመስሪያ ቤቱ ልዩ ልዩ አካላት ሥራዎች የሚመሩባቸውን ደንቦች፣ ፖሊሲዎች፣መመሪያዎች፣ ማንዋሎች እንዲሁም የተሻሻሉ ወይም የተሻሩ መመሪያዎች የሚገኙባቸውን መዝገቦች ዝርዝር፣

ሰ/ የድርጅቱ ሰራተኞች የሚሰሩባቸው መመሪያዎች፣ ደንቦች፣ ማብራሪያዎችና ሌሎች ሰነዶች፣

ሸ/ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ስም እና አድራሻ፣ እና

ቀ/ ሌሎች ዝርዝሮችን፣ አትሞ ያወጣል።

2. አስፈላጊ የሆነ ለውጥ ሲኖር የተለወጡ ነገሮች የታከሉበትን እና በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው ህትመት ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ በማውጣት ለማንኛውም ጠያቂ ወዲያውኑ የሕትመቱን ቅጂ መስጠት ወይም እንዲመ ለከት ማድረግ አለበት፡፡ ሆኖም እያንዳንዱ የመንግስት አካል በእነዚህ ህትመቶቹ ውስጥ በዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት የተከለከሉ መረጃዎችን በግመ ለከቱ ደንጋጌዎች መሰረት መገለፅ የሌለባቸውን ነገሮች ማካተት የለበትም፡፡

3. ማንኛውም የመንግስት አካል፡

ሀ/ የህዝብን ጥቅም የሚመለከቱ ጠቃሚ ፖሊሲዎችና ውሳኔዎችን ይፋ በሚያደርግበት ጊዜ ከውሳኔዎቹ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን በሙሉ አትም ማውጣት አለበት፡፡

ለ/ የአስተዳደራዊ፣ የዳኝነትም ሆነ የዳኝነት ነክ ውሳኔዎችን ሲሰጥ የሃሳብ ልዩነት ካለም ከነልዩነቱ ለማንኛውም መረጃ የሕትመቱን ቅጂ መሰጠት ወይም እንዲመለከተው ማድረግ አለበት፡፡

ሐ/ በግልጽነትና ተጠያቂነት መርሆዎች መሰረት ማንኛውንም አይነት ፕሮጀክት ተግባራዊ ከማድረጉ በፊት ለጠቅላላው ሕዝብ ወይም ጥቅማቸው ለተነካባቸው ወይም ሊነካባቸው ለሚችሉ ወገኖች ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዙ ፍሬ ነገሮችን አትሞ ማውጣት ወይም ማሳወቅ ይኖርበታል።

## 14. መረጃ ለማግኘት ስለሚቀርቡ ጥያቄዎች

1. መረጃ ለማግኘት የፈለግ ማንኛውም ሰው፣ የሚፈልገውን መረጃ ለይቶ በመግለጽ ጥያቄውን በጽሁፍ ወይም ሊነበብ በሚቻል የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ አማካይነት ለዚህ ዓላማ በየመሥሪያ ቤቱ የተዘጋጀውን የመጠየቂያ ፎርም በመሙላት ለሚመለከተው የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ ማቅረብ አለበት፡፡ መረጃ ጠያቂው ማንበብና መጻፍ የማይችል ከሆነ ወይም በአካል ጉዳት ምክንያት ጥያቄውን በጽሑፍ ማቅረብ ካልቻለ የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው በተዘጋጀው ፎርም ላይ በመሙላት መተባበር አለበት፡፡

2. የመረጃ ጥያቄ ያቀረበ ማንኛውም መረጃ ፈላጊ መረጃውን የፈለገበትን ምክንያት መጠየቅ የለበትም፡፡

3. በንኡስ አንቀፅ 1 መሠረት የመረጃ ጥያቄ የደረሰው የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ በተቻለ ፍጥነት ሆኖም በማንኛውም ሁኔታ ከ30 የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተጠየቀውን መረጃ በክፍያ ለአመልካቹ መስጠት ወይም በዚህ አዋጅ ከልከላን በተመለከተ የተደነገጉትን ምክንያቶች

በመጥቀስ የመረጃ ጥያቄውን ያልተቀበለው መሆኑንና ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑን በመለፅ ምላሹን በፅሁፍ መስጠት አለበት፡፡

4. የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው አመልካቹ የተተመነውን ክፍያ በመክፈል መረጃውን እንዲወስድ ከተወሰነ ለመረጃ ጠያቂው የክፍያውን መጠንና የአከፋፈሉን ሁኔታ ዘርዝሮ በጹሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ማስታወቂያው በተላከበትና ክፍያው በተፈጸመበት ቀን መካከል ያለው ጊዜ በላይኛው ንዑስ አንቀጽ በተመለከተው 30 የሥራ ቀን ጊዜ ውስጥ አይካተትም፡፡
5. በንዑስ አንቀጽ 3 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ለመረጃ ጥያቄው ምላሽ አለመስጠት ጥያቄውን እንዳለመቀበል ተደርጎ ይወሰዳል።
6. የመንግስት አካልን የሰውና የቁሳቁስ ኃይል ያለአግባብ እንዲባክን ወይም መደበኛ ተግባሩን የሚያስት ወይም ለመዝገቡ የጥበቃ ደህንነት አስጊ ካልሆነ በስተቀር መረጃው መሰጠት ያለበት ጠያቂው ይሰጠኝ ባለበት አይነት ፎርም ነው፡፡
7. ማንኛውም የመስሪያ ቤቱ ሃላፊ ወይም ሰራተኛ በህዝብ ግንኙነት ኃላፊው የመረጃ ጥያቄ ሲቀርብለት የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡
8. በመስሪያ ቤቱ ሰነድ ውስጥ የሚገኝ መረጃን ለማግኘት ጥያቄ የቀረበለት የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ፣ በንዑስ አንቀፅ 3 የተመለከተውን የሰሳሳ ቀን ጊዜ ለተጨማሪ 30 የስራ ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝም የሚችለው፣

   ሀ/ መስሪያ ቤቱ በበርካታ ተመሳሳይ የመረጃ ጥያቄዎች የተጥለቀለቀ ከሆነ እና የተጠየቀውን መረጃ በተወሰነው ጊዜ ውስጥ ለመስጠት የማይቻል ከሆነ፣

   ለ/ መረጃውን በተወሰነው ጊዜ ለመስጠት በርካታ ሰነዶችን ማገላበጥ የሚያስፈልግ በመሆኑ ምክንያት የመንግስት አካሉ የሰው ኃይልና የቁሳቁስ አጠቃቀም የሚያዛባ ከሆነ፣

   ሐ/ የተጠየቀውን መረጃ የማሰባሰቡና ወይም የማጠናቀሩ ሥራ በተለያዩ ከተሞች ውስጥ ከሚገኙ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች የሚገኙ በርካታ መዛግብትን መመልከትን የሚጠይቅ ከሆነ፣

   መ/ የተፈለገውን መረጃ ለመስጠት ከመንግስት አካሉ ልዩ ልዩ አካሎች ወይም ክፍሎች ወይም ከሌሎች መንግስታዊ አካላት ጋር መመካከሩ ተገቢ ወይም አስፈላጊ ከሆነ እና በዚህ የተነሳ መረጃውን በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ለመስጠት የማይቻል ከሆነ፣ ወይም

ሠ/ ጠያቂው ራሱ ጊዜው ቢራዘም ፈቃደኛ መሆኑን በጽሑፍ የገለጸ ከሆነ፣

ነው።

9. በንዑስ አንቀፅ 3 የተመለከተው ቢኖርም ማንኛውም የመንግሥት አካል አጣዳፊ ለሆነ ጉዳይ የመረጃ ጥያቄ ሲቀርብለት እጅግ ቢዘገይ ከአስር የስራ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

10. በመንግሥታዊ አካላት አጣዳፊ ወይም አስቸኳይ ተብለው በመመሪያ የሚወሰኑ ሌሎች ጉዳዮች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ አጣዳፊ ወይም አስቸኳይ ጉዳይ እንዳለ የሚቆጠረው

ሀ/ የተጠየቀው መረጃ ባስቸኳይ ካልተሰጠ በሰው ሕይወት ወይም አካላዊ ደህንነት ላይ የቅርብ ጊዜ አደጋን ሊያስከትል ይችላል የሚያሰኝ ተጨባጭ ምክንያት መኖሩን የሚያሳይ ማመልከቻ ያቀረበ እንደሆነ፣ ወይም

ለ/ መረጃን ለህዝብ ማሰራጨት ዋነኛ ተግባሩ በሆነ አመልካች በመንግስት አካል ተከናውኗል የሚባልና ህዝብ በአስቸኳይ ሊያውቀው ይገባል የሚያሰኝ ተጨባጭ ምክንያታዊ መነሻ ያለው ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ፣

ነው።

11. የህዝብ ግንኙነት ሃላፊው ከላይ በንኡስ አንቀፅ 10 /ሀ/እና /ለ/ መሰረት የቀረበው የመረጃ ጥያቄ አጣዳፊ አይደለም ብሎ ካመነ አመልካቹ አስተዳደራዊ ይግባኝ ሊያቀርብ የሚችል መሆኑን በመገለፅ ምላሹን በንኡስ አንቀፅ 9 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መስጠት ያለበት ሲሆን፣ ፍርድ ቤት በዚህ መሰረት ምላሽ የተሰጠበትን ጉዳይ በይግባኝ ሊመረምር አይችልም።

12. በዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀፅ 4 መሰረት መረጃ ለማግኘት የሚከፈለው ክፍያ መረጃውን የያዘውን ሰነድ ለመፈለግ፣ለማሰባሰብና ለማባዛት ከሚያስፈልገው ወጪ መብለጥ የሌለበት ሲሆን የግል መረጃን ለማግኘት ጥያቄ የሚያቀርቡ አመልካቾች ወይም የመክፈል አቅም የሌላቸው ጠያቂዎች እንዲከፍሉ መደረግ የለባቸውም፡፡

15. <u>የማይፈቀዱ መረጃዎች</u>

1. በዚህ አዋጅ አንቀፅ 12 የተመለከተው መረጃ የማግኘት መብት በዚህ ክፍል ስር በተደነገጉ ገደቦች ካልሆነ በስተቀር መረጃ እንዳይገለፅ በሚከለክሉ ማንኛቸውም የህግ ክልከላዎች ሊገደብ አይችልም።

2. በዚህ ክፍል ስር በተደነገጉ የማይገለፁ መረጃዎች ውስጥ የማይሸፈን ማንኛውም መረጃ በአስተዳደራዊ ውሳኔ ምስጢር ነው ተብሎ በመፈረጁ ብቻ በዚህ አዋጅ የተረጋገጠውን መረጃ የማግኘት መብት አፈፃፀም ሊያስቀር አይችልም።

16. <u>ሶስተኛ ወገንን የሚመለከቱ የግል መረጃዎች</u>

ማንኛውም የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ፡

1. ከሞተ 20 ዓመት ያልሞላውን ሰው ጨምሮ የሦስተኛ ወገንን የግል ሕይወት የሚመለከቱ መረጃዎች ያለበቂ ምክንያት እንዲገለፁ የሚያደርግ ከሆነ የቀረበውን የመረጃ ጥያቄ ውድቅ ለማድረግ ይችላል፡፡

2. በንዑስ አንቀፅ 1 መሠረት ሦስተኛ ወገንን የሚመለከተውን መረጃ ለመከልከል የማይቻለው፡

ሀ/ በአንቀፅ 19 መሰረት ሦስተኛው ወገን የመረጃውን መገለፅ ያልተቃወመ ከሆነ ወይም መረጃውን ለጠየቀው ሰው እንዲገለፅ ፈቃደኝነቱን በጽሁፍ የገለጸ ከሆነ፣

ለ/ መረጃውን የሰጠው ሶስተኛ ወገን መረጃውን በተቀበለው የመንግሥት አካል ወይም በርሱ ስም መረጃውን በተቀበለው ሌላ ወገን አማካይነት የሚሰጠው መረጃ ለሕዝብ ግልጽ የሚደረግ መሆኑን ወይም ግልፅ ሊደረግ የሚችል መሆኑን አስቀድሞ እንዲያውቀው ተደርጎ ከሆነ፣

ሐ/ መረጃው አስቀድሞ ለሕዝብ ግልጽ ተደርጎ ከሆነ ፣

መ/ መረጃው የግለሰብን የአእምሮና የአካል ጤንነት ወይም ደህንነት የሚመለከት ከሆነና መረጃው የሚመለከተው ሰው በመረጃ ጠያቂው ሞግዚትነት ስር የሚተዳደር ከሆነ፣ አስራ ስምንት አመት ያልሞላው ከሆነ ወይም የጥያቄውን ፀባይ ለመረዳት የማይችል ከሆነና መረጃውን መስጠቱ ለሦስተኛው ወገን ጥቅም አስፈላጊ ከሆነ፣

ሠ/ መረጃው በህይወት የሌለ የሦስተኛ ወገንን የሚመለከት ከሆነና የሟቹ የቅርብ የሥጋ ዘመድ በሆነ ሰው መረጃው እንዲገለጽ ከተጠየቀ ወይም የሟቹን የስጋ ዘመድ የጽሁፍ ፍቃድ በያዘ ሰው አማካይነት መረጃው እንዲገለጽ ጥያቄ የቀረበ ከሆነ ወይም፣

ረ/ የተጠየቀው መረጃ በመንግሥት መሥሪያ ቤት የሚሰራን ወይም ይሰራ የነበረን ሰው የሥራ ኃላፊነትና ደረጃን ጨምሮ ማዕረጉን፣ የሥራአድራሻውን፣ የመሥሪያ ቤት ስልክና ተመሳሳይ ዝርዝር አድራሻውን፣ የሥራ መደቡን፣ ደመወዙንና ሌሎች ክፍያዎቹን፣ ወይም የግለሰቡን የሥራ ኃላፊነቶችና፣

በሥራው ላይ ያከናወናቸውን ተግባሮች ወይም ግለሰቡ ራሱ በሞላው መዝገብ ላይ ያሰፈረውን ስሙን የሚመለከት ከሆነ፣ ነው።

17. <u>የሦስተኛ ወገንን የንግድ መረጃዎች ስለመጠየቅ</u>

1. የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው የተጠየቀው መረጃ፡

ሀ/ የሦስተኛ ወገን የንግድ ምስጢር የያዘ ከሆነ፣

ለ/ የንግድ ምስጢር ባይሆንም የሦስተኛ ወገንን የፋይናንስ፣ የንግድ፣ የሳይንሳዊ ወይም ቴክኒካዊ መረጃዎችን የሚመለከት ከሆነና የመረጃዎቹ መገለጽ በሦስተኛው ወገን የፋይናንስና የንግድ ጥቅሞች ላይ ጉዳትን የማስከተል ውጤት የሚኖረው ከሆነ ፣ወይም

ሐ/ ሌላ እንደማይገለጽበት በማመን በሦስተኛው ወገን በእምነት የተሰጠ መረጃን የያዘ ከሆነና የመረጃው መገለፅ በውል ወይምበሌሎች ድርድሮች ሦስተኛውን ወገን ተገቢ ላልሆነ ጉዳት ሊያጋልጠው ይችላል ወይም ሶስተኛውን ወገን በንግድ ውድድር ሊጎዳው ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት ያለ ከሆነ፣

የመረጃ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ አለበት።

2. በንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት አንድ መረጃ ሊከለከል የማይችለው መረጃው፡

ሀ/ ለሕዝብ ግልጽ እንዲሆን ተደርጎ ከሆነ፣

ለ/ ሶስተኛው ወገን በአንቀጽ 19 መሠረት ፈቃደኛነቱን የገለፀ ከሆነ ወይም ሦስተኛው ወገን በሌላ አኳኋን መረጃው ለጠያቂው እንዲሰጥ በፅሁፍ የፈቀደ እንደሆነ፣ ወይም

ሐ/ በሦስተኛው ወገን በራሱ ወይም በሌላ በሦስተኛ ወገን ስም ማንኛውም የተመረተ ነገርን ወይም የአካባቢ ደህንነትን አስመልክቶ የተከናወነ ሙከራ ወይም የምርምር ሥራን የሚመለከት ከሆነና የመረጃው መገለፅ በሕዝብ ደህንነት ወይም በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋን ለማሳወቅ አስፈላጊ የሆነ እንደሆነ፣ ነው።

3. በንዑስ አንቀጽ 2 የተመለከተው መረጃ የሙከራ ወይም የምርመራ ዘዴዎችን ለማዳበር የተደረጉ ቅድመ ሙከራዎችን ወይም ሌሎች ምርመራዎችን የሚመለከቱ መረጃዎችን አያካትትም።

18. <u>በእምነት የተሰጠ የሦስተኛ ወገን መረጃን ስለመጠበቅ</u>

1. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው የተጠየቀው መረጃ፡

ሀ/ የመንግስት አካል መገለጽ የሌለበት መረጃ ልውውጥን በሚመለከት ያደረገውን የውል ግዴታ እንዲያፈርስ በማድረግ በተዋዋዩ ወገን ክስ ሊያስመሰርትበት የሚችል ከሆነ ወይም፣

ለ/ ሦስተኛ ወገን አይገለጽም ብሎ በማመን የሰጠውን መረጃ የሚመለከት ሆኖ የመረጃው መገለጽ ወደፊት ከተመሳሳይ ምንጭ የሚገኙ ተመሳሳይ መረጃዎችን መቀበልን ሊያስተጓጉል የሚችል ከሆነ እና የመንግሥት አካል ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መረጃዎቹን በየጊዜው መቀበል ያለበት ከሆነ፣ የመረጃ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ ይኖርበታል።

2. የንዑስ አንቀጽ 1 /ሀ/ ድንጋጌ ቢኖርም ሶስተኛው ወገን መረጃው ለመረጃ ጠያቂው እንዲሰጥ በጽሁፍ ከፈቀደ የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው መረጃውን መስጠት ይኖርበታል።

19.<u>ሦስተኛ ወገንን ስለማሳወቅ እና ጣልቃ ስለማስገባት</u>

የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው በዚህ አዋጅ መሠረት የቀረበለት የመረጃ ጥያቄ ሦስተኛ ወገንን የሚመለከት ከሆነና መረጃውን ለጠያቂው ለመስጠት ካሰበ ጥያቄው በደረሰው በ15 ቀናት ውስጥ መረጃውን የጠየቀውን ሰው ስም፣ የተጠየቀውን መረጃ ይዘት፣ እንዲሁም መረጃው መገለጽ ይኖርበታል የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር መረጃው የሚመለከተው ሦስተኛ ወገን ተቃውሞ ካለው ይህንኑ ማስታወቂያው በወጣ በ15 ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ በተጠየቀው መሰረት ተቃውሞ አለማቅረብ የዚህ አዋጅ አንቀፅ 16 (2) (እና አንቀፅ 17/2/ /ለ/ ድንጋጌዎች ውጤትን ያስከተላል።

20.<u>የግለሰቦች እና የንብረት ደህንነትን ስለመጠበቅ የሕዝብ ግንኙት ኃላፊው የተጠየቀው መረጃ ቢገለፅ፡</u>

1. የግለሰብን ሕይወት ወይም አካላዊ ደህንነት ለጉዳት ሊያጋልጥ ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት ካለ፣
2. የሕንፃን፣ ወይም የኮምፒዩተርና የሌላ መገናኛ መግሪያን፣ ወይም የሕዝብ የማመሳለሻ አገልግሎትን ወይም የሌላ ማንኛውንም አይነት የንብረት መዋቅርን ወይም አሰራርን ደህንነት ሊያሰናክል ወይም ሊያደናቅፍ የሚችል፣ ከሆነ ወይም
3. በምስክሮች ጥበቃ ፕሮግራም የሚሸፈን ግለሰብን ወይም የጠቅላላውን ሕዝብ ወይም የአንድ የተወሰነ የሕዝብ ክፍልን ደኅንነት ለመጠበቅ የተበጁ ስልቶችን፣ እቅዶችንና አሠራሮችን ሊያደናቅፍ ወይም ሊያሰናክል የሚችል ከሆነ፣

መረጃውን መግለጽ የለበትም።

21.<u>የሕገ አስከባሪና የፍርድ ምርመራ ስራዎች ጠበቃ</u>

1. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው እንዲሰጥ የተጠየቀው መረጃ ወይም መኖሩ ወይም አለመኖሩን እንዲያረጋገጥ የተጠየቀው መረጃ ፤ የተፈጸመን ወይም ሊፈጸም የሚችል የሕግ ጥሰትን መመርመርያ፣ መከታተያ፣ መግቻ ወይም መከላከያ ዘዴዎችን፣ ቴክኒኮችን፣ የአሠራር ሥነ-ሥርአቶችን ወይም የተግባር መመሪያዎችን የሚመለከት ከሆነና የመረጃው መገለፅ ለወንጀል አፈጻጸም ምቹ ሁኔታን በመፍጠር ውጤታማነታቸውን ሊያሰናክል ወይም ከህግ ማምለጥን ሊያስከትል ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት ካለ የመረጃ ጥያቄውን ሊከለክል ይችላል።
2. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው የተጠየቀው መረጃ የሚመለከተው የወንጀል ተጠርጣሪ ክስ ገና በዝግጅት ላይ ያለ ከሆነ ወይም ዝግጅቱ ቢጠናቀቅም ክሱ ገና ያልተጀመረ ከሆነ ወይም ክሱ በመታየት ላይ ያለ ከሆነና የተጠየቀው መረጃ መገለፅ ወይም መረጃው መኖሩን ወይም አለመኖሩን ማረጋገጥ፣

   ሀ/ ክሱን ሊያሰናክል ይችላል፣

   ለ/ በክሱ አሰማም ሂደት ላይ የፍትሕ መጨናገፍን ሊያስከትል ይችላል። ወይም

   ሐ/ የፍርድ ሂደቱን ሚዛናዊነት ወይም ገለልተኝነት ሊያዛባ ይችላል። የሚል ምክንያታዊ ግምት ካለ የተጠየቀውን መረጃ መግለጽ አይኖርበትም።
3. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው የተጠየቀው ሰነድ በቁጥጥር ሥር ስላሉ ወይም በሕግ ጥበቃ ሥር ስላሉ ሰዎች አጠቃላይ የጥበቃ ሁኔታ የሚመለከቱ መረጃዎችን ብቻ የያዘ ከሆነ የመረጃ ጥያቄውን በንዑስ 1 አንቀጽ መሰረት ውድቅ ሊያደረግ አይችልም።

22.<u> በፍርድ ምርመራ ጠበቃ ስለሚደረግላቸው መረጃዎች</u>

የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው በክስ ክርክር ላይ ተከራካሪ የሆነው ወገን ለሌላኛው ወገን እንዲገልጽ በህግ የማይገደድባቸውን መረጃዎች ለማግኘት የቀረቡ ጥያቄዎችን የዚህ ልዩ መብት ተጠቃሚ የሆነው ሰው በመብቱ አልጠቀምበትም ካላለ በስተቀር መፍቀድ የለበትም፡፡

23.<u>ስለመከላከያ፣ ደዕንነትና አለም አቀፍ ግንኙነቶች</u>

1. የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው እንዲሰጥ የተጠየቀው ወይም መኖር አለመኖሩ እንዲያጋገጥ የተጠየቀው መረጃ መገለጽ የሀገሪቱን መከላከያ፣የሀገርን ፀጥታና

ደህንነት ወይም አለምአቀፋዊ ግንኙነትን ሊጎዳ የሚችል ከሆነ ጥያቄውን ውድቅ ማድረግ አለበት፡፡

2. የንዑስ አንቀፅ 1 አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከተው መረጃ፡

ሀ/ የጠላትን እንቅስቃሴ ወይም ፀብ አጫሪ ተግባር ለመቋቋም ከሚደረግ ዝግጅት ወይም አማፂዎችን ከመከታተል፣ ከመከላከል፣ ወይም ከመግታት ጋር የተያያዙ ግዳጆች ወይም ወታደራዊ ልምምዶች ወይም ወታደራዊ ታክቲኮች ወይም ስትራቴጂዎች ጋር የተያያዙ መረጃዎችን፣

ለ/ የአማፂያንን ወይም የጠላትን እንቅስቃሴዎች ለመከታተል፣ ለመከላከል፣ ወይም ለመምታት ወይም ለመደምሰስ ወይም ለመግታት የሚያገለግሉ የጦር መግሪያዎችን ወይም ሌሎች አይነት መሳሪያዎችን ወይም ለጦር መሳሪያነት ወይም ለተመሳሳይ ትግባር እንዲያገለግሉ ታስበው የተነደፉ፣ የተበጁ፣ የዳበሩ፣የተመረቱ ማንኛቸውንም ነገሮች ብዛት፣ አይነት፣ አቅም፣ ጉልበት፣ ደካማ ጐን፣ አሠራር ፣ ብቃት፣ እንቅስቃሴ ወይም አጠቃቀምን የሚመለከቱ መረጃዎችን፣

ሐ/ የማንኛውንም ሠራዊት ወይም የሠራዊት ክፍል ወይም የአባላቱን ወይም የአማጽያንን ወይም የጠላትን እንቅስቃሴዎች የመከታተል፣ የመቆጣጠር፣ ወይም የመግታት ኃላፊነት የተጣለበትን የማንኛውንም ሰው፣ ባህሪይ፣ ብቃት፣ ደካማ ጐን፣ ተግባራት፣ እምቅ ችሎታ፣ ስምሪት ወይም እንቅስቃሴ የሚመለከት መረጃን፣

መ/ ከላይ በፊደል 2 /ሀ/፣/ለ/፣ /ሐ/ እና /ረ/ የተመለከቱ መረጃዎችን መሰብሰብያ፣ መገምገምያና መያዣ ዘዴዎችን ወይም ለዚሁ አገልግሎት የሚውሉ ሳይንሳዊ ወይም ቴክኒካዊ መሳሪያዎችን፣

ሠ/ ከላይ በፊደል/ሀ/ የተመለከቱ መረጃዎች ምንጭ የሆኑ የምስጢር መረጃ አቀባዮችን እና የማንኛውም ሌላ የመረጃ ምንጭን ማንነት የሚመለከቱ መረጃዎችን፣

ረ/ የሀገር መከላከያን ወይም ከላይ በፊደል /ሀ/ የተመለከቱ መረጃዎችን ወይም የሌላ ሀገር መንግስትን ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅቶችን የሚመለከት ወይም ከላይ የተመለከቱ በሀገሪቱ ወይም በሀገሪቷ ስም በዓለም አቀፋዊ ምክክሮችና ውይይቶች ላይ ጥቅም ላይ የሚውልን የፀጥታ መረጃ (ኢንተለጀንስን) የሚመለከት መረጃን፣

ሰ/ በአለም አቀፍ ስምምነት ወይም ድርድር መሰረት ጉዳዩ በምስጢር እንዲጠበቅለት ለሚፈልግ አለም አቀፍ ድርጅት ወይም ሌላ መንግስት በሀገሪቱ ወይም በሀገሪቷ ስም የተሰጠ መረጃ፣

ሸ/ በአለም አቀፍ ስምምነት ወይም በአለም አቀፍ ልማዳዊ መሰረት በምስጢር መጠበቅ ያለበትን መረጃ፣

ቀ/ በሀገሪቱ ወይም በሌላ መንግስት ወይም አለም አቀፋዊ ድርጅት እየተደረጉ ባሉ ወይም ወደፊት በሚደረጉ አለም አቀፍ ድርድሮች ላይ በመንግስት ወይም በሌላ የውጭ ሀገር መንግስት ወይም አለም አቀፋዊ ድርጅት የተያዙ ወይም የሚያዙ አቋሞችን፣ ወይም

በ/ ከሌላ መንግስት ወይም አለም አቀፍ ድርጅት ጋር የተደረጉ ዲፕሎማሲያዊ የመልእክት ልውውጦችን ወይም ከሀገሪቱ ዲፕሎማቲክ ሚስዮን ወይምቆንስላ ፅ/ቤቶች ጋር የተደረጉ ይፋዊ የመልእክት ልውውጦችን የሚመለከቱ መረጃዎችን፣ የያዘ ሰነድን ይጨምራል።

24. <u>የሚኒስተሮች ምክር ቤት ሰነዶች</u>

የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለህዝብ በይፋ እንዲገለፁ ከወሰናቸው መረጃዎች በስተቀር የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰነድ ውስጥ የሚገኝ መረጃን ለማግኘት ወይም የመረጃውን መኖር ወይም አለመኖር ለማረጋገጥ የቀረበ ማንኛውንም ጥያቄ መቀበል የለበትም፡፡ የዚህ አንቀጽ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ለአንቀፁ አፈፃፀም አንድ ሰነድ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ሰነድ ነው የሚባለው፡

1. ለሚኒስትሮች ምክር ቤት የተመራ ማንኛውም ሰነድ ወይም ለሚኒስትሮች ምክር ቤት መቅረብ የሚገባው በመሆኑ በመንግስት አካል የበላይ ኃላፊ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እንዲመራ የተደረገ ሰነድ ከሆነ፣
2. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይፋዊ ሰነድ ከሆነ፣
3. በንዑስ አንቀጽ 1 ወይም 2 የተመለከቱት ሰነዶች ግልባጭ ወይም ቅጅ ከሆነ ወይም ከነዚህ ሰነዶች የተወሰዱ ጥቅሶችን የያዘ ከሆነ፣ ወይም
4. ቢገለጽ የሚኒስትሮች ምክር ቤት በይፋ ካሳተማቸው ውሳኔዎቹ ውጭ ያሉ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ወይም የኮሚቴዎቹን ውሳኔዎች ወይም ውይይቶች እንዲታወቁ የሚያደርግ ከሆነ፣

ነው።

## 25. የሀገሪቷን የኢኮኖሚ ጥቅሞችና የፋይናንስ ደኅንነት እንዲሁም የመንግሥት ድርጅቶችን የንግድ እንቅስቃሴ ስለሚመለከቱ መረጃዎች

1. የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው እንዲሰጥ የተጠየቀው መረጃ ወይም መኖር ወይም አለመኖሩ እንዲረጋገጥ የተጠየቀው መረጃ ቢሰጥ ወይም ቢገለጽ የሀገሪቱን ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ወይም የፋይናንስ ደህንነት ጉዳት ላይ ሊጥል የሚችል ከሆነ ወይም መንግሥት የሀገሪቱን ኢኮኖሚ ለማስተዳደር ያለውን አቅም ሊያዳክም የሚችል ከሆነ መረጃውን ለመከልከል ይችላል።
2. የንዑስ አንቀጽ 1 አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ አንቀጽ 1 የተመለከቱት መረጃዎች፡
   ሀ/ በሥራ ላይ ባለው ገንዘብ፣በቅንስናሽ ሳንቲሞች፣ በህጋዊ ጨረታ፣ በውጭ ምንዛሬ ተመን ወይም በውጭ ኢንቨስትመንት ላይ ተጽእኖ ሊያስከትል የሚችል የፖሊሲ ለውጥ የማድረግ ወይም ያለማድረግ ውጥንን፣
   ለ/ በስራ ላይ ያለው የብድር ወይም የወለድ ክፍያ፣ የቀረጥ፣የኤክሳይዝ፣ የግብር ወይም ማናቸውም ሌላ የገቢ ምንጮችን የመለወጥን ወይም እንዳለ የማቆየት ውሳኔ ውጥኖችን ወይም የመንግስት ብድርን፣የሸቀጦች ወይም የአገልግሎቶች ዋጋን፣ ኪራዮችን የደመወዝ ወይም የቀን ክፍያዎችን ወይም ሌሎች ገቢዎችን የሚመለከቱ ቁጥሮችን ለመለወጥ ወይም እንዳለ የመቆየት ውሳኔ ውጥኖችን ወይም
   ሐ/ የሚንቀሳቀሱ ወይም የማይንቀሳቀሱ ንብረቶችን ሽያጭ ወይም ይዞታን የሚመለከቱ ውጥኖችን ወይም ዓለም አቀፍ የንግድ ስምምነቶችን፣ ያካትታሉ።
3. የንኡስ አንቀጽ 2 /ሐ/ አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ አንቀፁ የተመለከተው መረጃ በዚህ አዋጅ የመንግስት አካል ትርጓሜ ውስጥ ለማይካተት ማንኛውም ሰው የመንግስት አካልን የአክስዩን ድርሻ ወይም ጥቅም ለማስተላለፍ የተደረገ ስምምነትን ወይም የተወጠነ ስምምነትን ያካትታል።
4. የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው መረጃው አስቀድሞ ለሕዝብ ይፋ ካልተደረገ ወይም መረጃው የሚመለከተው ወይም የመረጃው ባለቤት የሆነ ሌላ የመንግስት አካል መረጃው እንዲገለጽ በጽሁፍ ካለፈቀደ ወይም በመንግስት አካል ወይም በመንግስት አካል ስም የተደረጉ የምርት ወይም የአካባቢ ሙከራ ውጤቶችን ወይም ምርመራዎችን የሚመለከት መረጃ ሆኖ ቢገለፅ

በሕዝብ ደህንነት ወይም በአካባቢ ደህንነት ላይ ሊደርስ የሚችል ከባድ አደጋን የሚያጋልጥ ካልሆነ በስተቀር የተጠየቀው መረጃ፦

ሀ/ የመንግሥትን ወይም የመንግሥት አካላትን የንግድ ምስጢሮች የያዘ ከሆነ፣

ለ/ ከንግድ ምስጢሮች ባይካተቱም መግለጻቸው የመንግሥት ወይም የማንኛውንም መንግሥታዊ አካል ጥቅም ሊጎዳ የሚችል የፋይናንስ፣ የንግድ ወይም የቴክኒክ ወይም የሳይንስ መረጃዎች የያዘ ከሆነ፣ ወይም ማንኛውም የመንግሥት አካል የሚያደርገውን የንግድ ውድድር የሚጎዳ ከሆነ ወይም የመንግሥት አካል ከሌሎች ጋር በሚያደርጋቸው የውል ወይም ሌሎች ድርድሮች ተጠቃሚ እንዳይሆን ሊያደርግ ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት ካለ፣ መረጃውን መከልከል ይኖርበታል።

26. <u>የመንግስት የስራ ሰነዶች</u>

1. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው በመረጃ ፈላጊው የተጠየቀውን ሰነድ የያዘው ሰነድ፡

   ሀ/ በህግ የተሰጠን ኃላፊነት ወይም ግዴታን ለመወጣት፣ የውሳኔ አሰጣጥን ወይም የፖሊሲ ቀረፃን ለማገዝ፣ የቀረቡ ወይም የተዘጋጁ አስተያየቶችን፣ ምክሮችን፣ የውሳኔ ሃሳቦችን ወይም ሪፖርቶችን፣ የስብሰባ ቃለ ጉባኤዎችን ጨምሮ የተደረጉ ምክክሮችን፣ውይይቶችን ወይም ስብሰባዎችን የሚያትቱ ሌሎች ሰነዶችን የያዘ ከሆነ፣

   ለ/ ቢገለፅ ግልጽ የሆነ የሃሳብ ልውውጥን፣ ምክክርን ፣ሪፖርትን፣ የውሳኔ ሃሳብን ወይም ውይይትን በመገደብ በማንኛውም የመንግስት አካል ውስጥ ወይም በተለያዩ የመንግስት አካላት መሀከል የሚደረገውን የምክክር ሂደት ሊያጨናግፍ የሚችል ከሆነ፣ ወይም

   ሐ/ ቢገለፅ በዝግጅት ወይም በውጥን ላይ ያለን ፖሊሲን ያለጊዜው እንዲገለጽ በማድረግ የፖሊሲውን ስኬት የሚያሰናክል ውጤትን ሊያስከትል የሚችል ከሆነ፣

   ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል።

2. የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው የተጠየቀው ሰነድ፡

   ሀ/ የቁጥጥርና የክትትል ሥራ የሚሰሩ የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን የቁጥጥር፣ የኦዲት፣የምርመራ ወይም የፍተሻ ቴክኒኮችንና ሥነ ሥርዓቶችን የመሳሰሉ የውስጥ አሰራሮችንና መመሪያዎችን የያዘ ከሆነና የሰነዱ መገለፅ የመንግስት አካልን የሙከራ፣ የምርመራ ወይም የኦዲት አሰራሮችንና ዘዴዎችን ውጤታማነት ሊያስተጓጉል የሚችል ከሆነ፣

ለ/ ሰነዱ የግምገማ ሰነድን የያዘ ከሆነና መረጃውን ያቀረበው ሰው ማንነት በሰነዱ ላይ የተገለፀ ቢሆንም ባይሆንም የመረጃው መገለፅ መረጃውን ለሰጠው ሰው መረጃው እንደማይገለጽ ወይም የመረጃ ሰጭው ማንነት በምስጢር እንደሚጠበቅ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ የተገባውን ቃል የማፍረስ ውጤት የሚያስከትል ከሆነ፣ ወይም

ሐ/ ሰነዱ ማንኛውንም የመንግስት አካል ኃላፊን ማስታወሻዎች ወይም ፣ የዝግጅት መነሻዎች ወይም ሌሎች ማንኛውም ዓይነት ረቂቆችን የያዘ ከሆነ፣

የቀረበውን ጥያቄ ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

3. በንዑስ አንቀፅ 1 እና 2 የተመለከቱትን መረጃዎች የያዘ ሰነድ በፍርድ ምርመራ ሂደት ሊሰጡ የሚገባቸውን ማብራሪያዎች ወይም ምክንያቶች የያዘ እስከሆነ ድረስ መከልከል የለበትም።

27. <u>በጥቅሉ የቀረቡ፣ የሰው ኃይልና የቁሳቁስ አጠቃቀምን የማያዛቡ፣ ወደፊት ታትመው የሚወጡ መረጃዎችን ለማግኘት ስለማቀርቡ፣የመረጃ ጥያቄዎች</u>

በዚህ አዋጅ በአንቀጽ 12 የተደነገገው ቢኖርም የህዝብ ግንኙነት ኃላፊው፡

1. ጥያቄው በጥቅሉ የቀረበ ከሆነ ወይም ከመጠናቸው ብዛት የተነሳ የተጠየቁትን መረጃዎች የመገልበጡ ወይም የመሰብሰቡ ሥራ የመንግስታዊ አካሉ መደበኛ የሰው ኃይልና የቁሳቁስ አጠቃቀም የሚያዛባ ወይም የመንግስታዊ አካሉን መደበኛ ሥራ የሚያስተጓጉል ከሆነ፣
2. መረጃ ፈላጊው ተቀባይነት ሊያገኝ በሚያስችለው መልክ ያቀረበውን ጥቅል ጥያቄ እንዲያስተካክል የመርዳት ግዴታውን ቢወጣም አመልካቹ በጥቅሉ የቀረበውን ጥያቄ ያላስተካከለ ከሆነ፣
3. መረጃው በአንድ በተወሰነ ጊዜ እንዲታተም የሚያዝ አዋጅ፣ ደንብ ፣መመሪያ ወይም ትዕዛዝ ኖሮ የመረጃ ጥያቄው ከቀረበበት ዕለት ጀምሮ ቀናት ውስጥ መረጃው ሊታተም የሚችል ከሆነ ፣ ወይም
4. ለጠቅላላው ሕዝብ እንዲዳረሱ ታትመው በወጡ ሕትመቶች ውስጥ መረጃው የተካተተ ከሆነ፣

የመረጃ ጥያቄውን ውድቅ ሊያደርገው ይችላል፡፡

28. <u>የሕዝብ ጥቅም ማመዛዘን</u>

የተመለከቱት ድንጋጌዎች ቢኖሩም የህዝብ ግንኙነት ሃላፊው በመረጃው መገለፅ ጥበቃ በተደረገላቸው ጥቅሞች ላይ የሚደርሰው ጉዳት በመረጃው መገለፅ

ሊገኝ ከሚችለው የህዝብ ጥቅም የሚበልጥ ካልሆነ በስተቀር መረጃ ለማግኘት የቀረበ ጥያቄን ውድቅ ማድረግ የለበትም፡፡

29.<u>ተነጥሎ ስለሚሰጥ መረጃ</u>

በዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች መሰረት ሊከለከሉ የሚችሉ ወይም መከልከል ያለባቸውን የሰነዱን ክፍሎች ወይም ገጾች ክልከላው ከማይመለከታቸው ገጾች ነጥለህ ማውጣቱ አስቸጋሪ ካልሆነ በስተቀር ክልከላ ያልተደረገባቸው የሰነዱ ክፍሎች መገለጽ አለባቸው።

30.<u>መረጃ የሚሰጥበት ቋንቋ</u>

ለመንግሥት አካል ያቀረበው የመረጃ ጥያቄ የተፈቀደለት አመልካች የጠየቀው መረጃ፡

1. በመረጠው ቋንቋ የተዘጋጀ ከሆነ መረጃው አመልካቹ በመረጠው ቋንቋ ይሰጠዋል።
2. መረጃው አመልካቹ በመረጠው ቋንቋ ያልተዘጋጀ ከሆነ መረጃው በተዘጋጀበት ቋንቋ ለአመልካቹ መሰጠት አለበት፡፡

31. <u>በመረጃ ክልከላ ላይ ይግባኝ ስለማቅረብ</u>

1. በዚህ ክፍል ሰር ባሉ ድንጋጌዎች መሰረት በሕዝብ ግንኙነት ኃላፊው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ውሳኔው ከተሰጠ ጀምሮ ባሉት 30 ቀናት ውስጥ ለመንግሥታዊ አካሉ የበላይ ኃላፊ አቤቱታውን ለማቅረብ ይችላል፡፡
2. አቤት ባዩ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት አቤቱታውን በጊዜ ለማቅረብ አለመቻሉን በበቂ ሁኔታ ለማስረዳት ከቻለ ቅሬታ ሰሚው አካል በንኡስ አንቀጽ/1 /የተወሰነው ጊዜ ቢያልፍም የቀረበለትን የቅሬታ አቤቱታ ሊቀበል ይችላል፡፡
3. አቤቱታው የቀረበለት መንግስታዊ አካል የበላይ ሃላፊ በአስር ቀናት ውስጥ በአቤቱታው ላይ ውሳኔ መሰጠት አለበት፡፡
4. በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የመረጃ ጥያቄው በሚመለከተው የመንግሥት አካል የበላይ ኃላፊ ውድቅ የተደረገበት ማንኛውም አመልካች ቅሬታውን ውሳኔ በተሰጠው በ30 ቀናት ውስጥ ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ይግባኘ ማቅረብ ይችላል።

32.<u>የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ኃላፊነት</u>

1. የሕዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በዚህ አዋጅ የክፍል ሶስት ድንጋጌዎች ለመጠቀም የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በቀላሉ ሊረዳው በሚችል አኳኋን፡

ሀ/ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች አላማዎች፣

ለ/ በዚህ አዋጅ የሚሸፈኑ የመንግስት አካላት የህዝብ ግንኙነት ሃላፊዎች እና የምክትሎቻቸውን ሙሉ ስምና አድራሻ፣

ሐ/ የእያንዳንዱን የመንግስታዊ አካል አብይ የስራ ፀባይ፣

መ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 12 መሰረት የሚቀርቡ የመረጃ ጥያቄዎች የሚቀርቡበትን ፎርም፣

ሠ/መረጃ ጠያቂዎች በዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት መሰረት ከህዝብ ግንኙነት ሃላፊው የሚደረግላቸውን ትብብር ወይም አገልግሎቶች፣

ረ/ በዚህ አዋጅ መሰረት ከህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ለመረጃ ጠያቂዎች የሚሰጠው እገዛ ወይም አገልግሎት፣

ሸ/ በዚህ አዋጅ በክፍል ሶስት ድንጋጌዎች የተመለከቱ መብቶችና ግዴታዎች ባልተከበሩ ጊዜ በአዋጁ የተበጁ መፍትሄዎችን፣

ቀ/ ስለ አስተዳደራዊ ይግባኞች አቀራረብ፣

በ/ የህዝብ ግንኙነት ወይም የመንግስታዊ አካላት ሃላፊዎችን ውሳኔ በመቃወም ለፍርድ ቤቶች ስለሚቀርቡ የይግባኝ ማመልከቻዎች፣

ተ/ በዚህ ክፍል በመንግስት አካላት ታትመው እንዲወስኑ የታዘዙ መረጃዎችን አይነቶችና እነዚህን መረጃዎች ለማግኘት የሚረዱ ማብራሪያዎችን፣

ቸ/ የመረጃ ክፍያ ስለሚከፈልባቸውና ከክፍያ በሙሉ ወይም በከፊል ነፃ ስለሚደረጉ ጥያቄዎች፣ እና

ነ/ የህዝብ ግንኙነት ሃላፊዎች የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች በተመሳሳይ መንገድ እንዲፈጽሙ ለማድረግ የሚወጡ የአፈፃፀም መመሪያዎችን እና ማብራሪያዎችን፣

የዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት በስራ ላይ ከሚውልበት ቀን ጀምሮ ባሉት 18 ወራት ግዜ ውስጥ በመንግስት ኦፊሲያል ቋንቋዎች አትሞ የማውጣት ሃላፊነት አለበት፡፡

2. የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በዚህ አዋጅ ከተሰጡት ስልጣኖችና ሃላፊነቶች በተጨማሪ አቅም በፈቀደ መጠን፡

ሀ/ በአንቀጽ 36 (1) የተቀበላቸውን ሪፖርቶች መሰረት በማድረግ የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች በመንግስት አካላት መፈፀማቸውን የመከታተልና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት የማቅረብ፣

ለ/ የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች አፈፃፀም አስመልክቶ አሰራሮችን ለማዳበር

እና ለማሻሻል የሚረዱ አጠቃላይና ወይም ዝርዝር የውሳኔ ሀሳቦችን ለመንግስታዊ አካላት የማቅረብ፣

ሐ/መረጃ የማግኘት መብትንና የዚህን ክፍል ድንጋጌዎች ውጤታማ አፈፃፀም አስመልክቶ ለህዝብ ግንኙነት ሀላፊዎች የሚሰጡ ስለጠናዎችን የማዘጋጀት ወይም የማገዝ፣

መ/ በዚህ ክፍል ድንጋጌዎች የሚጠየቁ መስፈርቶችንና ግለሰቦች ያላቸውን መብት ለህዝብ የማሳወቅ፣

ሠ/ በዚህ አዋጅ አንቀፅ 13 መሰረት ታትመው መውጣት ያለባቸውን መረጃዎች በተመለከተ ከስራ ባህሪያቸው የተነሳ በአንድ ህትመት ውስጥ መረጃዎቻቸውን አጣምረው ማውጣት ያለባቸውን የመንግስት አካላት ወይም የህትመት ወጪን መጋራት የሚኖርባቸውን የመንግስት አካላት ወይም ወጪያቸው በሌላ የመንግስት አካል ሊሸፈንላቸው የሚገባ የመንግስት አካላትን የሚመለከቱ ውሳኔዎችን የመስጠት፣

ረ/ የዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት ድንጋጌን አጠቃቀም ግልጽ ለማድረግ የሚያግዙ የማብራሪያ መድብሎችን የማዘጋጀት፣

ሰ/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች ለማሻሻል፣ ለማጠናከር እና ለማዳበር የሚረዱ የመፍትሄ ሃሳቦችን ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የማቅረብ፣ ለዚህ ክፍል ድንጋጌዎች አፈፃፀም የሚያስፈልጉ ሌሎች ተግባራትን የማከናወን፣ ስልጣንና ሃላፊነት አለው ፡፡

3. የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም በዚህ አዋጅ የተሰጡትን ተግባራት ለማከናወን የሚያስችለው የተሟላ ስልጣን ያለው ሲሆን ለስራው የሚያስፈልገውን ተጨማሪ በጀትም ከህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያገኛል።

4. ዋና እንባ ጠባቂው ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አመታዊ ሪፖርት ያቀርባል።

33. <u>አስተዳደራዊ ይግባኝ</u>

1. ዋና እንባ ጠባቂው በአንቀፅ 31(4) መሰረት የቀረቡለትን የይግባኝ ቅሬታዎች ሲመረምር በአንቀፅ 35 መሰረት መገለፅ የሌለባቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ሰርተፊኬት ከተሰጠባቸው ሰነዶች በስተቀር በመንግስት አካላት እጅ የሚገኙ ማንኛቸውንም ሰነዶች አስቀርቦ መመርመር ይችላል፡፡ ዋና እንባ ጠባቂው ይህንን ሲያከናውን በዚህ አዋጅ እንዳይገለፁ ክልከላ የተደረገባቸው መረጃዎች አለመገለፃቸውን የማረጋገጥ ግዴታ አለበት ፡፡

2. ዋና እንባ ጠባቂው በአንቀፅ 31(4) መሰረት በቀረበለት የይግባኝ አቤቱታ ላይ በ 30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

3. ዋና እንባ ጠባቂው አቤቱታውን ውድቅ የማደረግ ወይም መንግሰታዊ አካል የተጠየቀውን መረጃ እንዲሰጥ የመወሰን ወይም መንግሰታዊ አካል በዚህ አዋጅ የተጣለበትን ግዴታዎች እንዲያሟላ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ያገኘውን እርምጃ የመውሰድ ስልጣን አለው ፡፡

## 34. ለፍርድ ቤት ስለሚቀርብ ይግባኝ

1. በዋና እንባ ጠባቂው በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው መረጃው የፌደራል የመንግሰት አካልን የሚመለከት በሆነ ጊዜ ይግባኙን ለፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት፤ መረጃው የክልል የመንግሰት አካልን የሚመለከት በሆነ ጊዜ ደግሞ ለክልል ክፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኙን በሰላሳ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡

2. የይግባኝ አቤቱታው የቀረበለት ፍርድ ቤት በአንቀፅ 35 መሰረት ሰርተፊኬት ከተሰጠባቸው ሰነዶች በስተቀር ማንኛውንም ሰነድ ሊመርመር ይችላል፡፡ በማንኛውም ምክንያት እነዚህ ሰነዶች ለፍርድ ቤት እንዳይቀርቡ ማድረግ አይቻልም።

3. ፍርድ ቤቱ በሚያደርገው የፍርድ ምርመራ፣ በዚህ አዋጅ መሰረት መገለፅ የሌለበትን ማንኛውንም መረጃ መግለፅ የለበትም ፡፡ ፍርድ ቤቱ መረጃዎቹ እንዳይገለፁ ለማድረግ አስፈላጊ ሆኖ ካገኘው አቤቱታ አቅራቢው ወይም ወኪሉ በሌለበት ማስረጃ መቀበልም ሆነ ክርክር መሰማት ይችላል፡፡

4. ፍርድ ቤቱ በቀረበለት ይግባኝ ግይ በሰሳሳ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱ በጉዳዩ ሳይ ከሚሰጠው ውሳኔ በተጨማሪ ወጪና ኪሳራን በተመለከተ ተገቢ ነው ያለውን ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

## 35. ሰርተፊኬት ስለመስጠት

1. እንዲሰጥ የተጠየቀው ወይም መኖር አለመኖሩ እንዲረጋገጥ የተጠየቀው መረጃ ብሄራዊ ፀጥታን፣ መከላከያን ወይም አለምአቀፍ ግንኙነትን የሚመለከት ሲሆን የመንግስት አካላት የበላይ ኃላፊዎች መረጃው በዚህ አዋጅ አንቀፅ 23 ክልክላዎች የሚሸፈንና የማይፈቅድ መረጃ መሆኑንና መረጃው ቢገለፅ በሃገር ደህንነት ላይ እርግጠኛ የሆነ አደጋ ሊከሰት የሚችል መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰርተፊኬት ሊሰጡ ይችላሉ፡፡

2. የዚህ ክፍል ድንጋጌዎች ቢኖሩም የዋና እንባ ጠባቂውም ሆነ ማንኛውም ፍርድ ቤት በንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት ሰርተፊኬቱ የተሰጠው በአግባቡ መሆን አለመሆኑን የመመርመር ስልጣን የላቸውም።

3. በንኡስ አንቀፅ 1 መሰረት በመንግስት አካላት የበላይ ኃላፊ የተሰጠ ሰርተፊኬት ትክክለኛ ቅጅ ከተሰጠ ጀምሮ ባለው በሰላሳ ቀናት ጊዜ ውስጥ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት መላክ አለበት፡፡ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰርተፊኬቱን የማፅደቅ ወይም የመሰረዝ ስልጣን አለው።

36. ሪፖርት የማቅረብ ግድታ

1. የእያንዳንዱ የመንግሥታዊ አካል የሕዝብ ግንኙነት ኃላፊ የዚህን አዋጅ ክፍል ሶሰት ለማስፈፀም ያከናወናቸውን ተግባራት አመታዊ ሪፖርት ከግንቦት 30 በፊት ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም ማቅረብ ይኖርበታል።

2. በንኡስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚዘጋጀው ሪፖርት፣

ሀ/ ለመንግስታዊ አካሉ የቀረቡ የመረጃ ጥያቄዎችን ብዛት፣

ለ/ በከፊልና በሙሉ ተቀባይነት ያገኘ የመረጃ ጥያቄዎች ብዛት፣

ሐ/ በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ውድቅ የተደረጉ የመረጃ ጥያቄዎች ብዛት፣

መ/ በመንግስታዊ አካሉ የተሰጡ የውስጥ ይግባኝ መፍትሄዎችና በነዚህ መፍትሄዎች መሠረት ተቀባይነት ያገኙ የመረጃ ጥያቄዎች ብዛት፣

ሠ/ ለህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የቀረቡ ይግባኞችን ብዛትና የውሳኔዎቹን ውጤቶች፣

ረ/ ፍርድ ቤት የቀረቡ የይግባኝ ጥያቄዎችን ብዛትና የውሳኔዎቹን ውጤቶች፣

ሰ/ ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮችን፣ የሚይዝ ይሆናል፡፡

3. የእያንዳንዱ መንግሰታዊ አካል የበላይ ኃላፊ የፌደራል መንግስታዊ አካል ከሆነ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፣ የክልል የመንግስት አካል ከሆነ ደግሞ ለክልሉ ምክር ቤት እና ለክልል አስተዳደር ምክር ቤት አመታዊ የስራ አፈፃፀም ሪፖርቱን በሚያቀርብበት ጊዜ በንዑስ አንቀፅ 1 የተመለከተውን ሪፖርትም አካቶ ማቅረብ አለበት፡፡

37. ደንብ የማውጣት ስልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት፡

1. ለተለያዩ የመረጃ አይነቶች ተፈፃሚ ስለሚሆነው የክፍያ ተመን ስንጠረዥ፣ ክፍያዎች ስለሚቀነሱበት ወይም መረጃ በነፃ ስለሚሰጥበት ዝርዝር ሁኔታ፣

2. ስለተከለከሉ መረጃዎች አጠባበቅና ምደባ ወይም ምስጢርነታቸው ስለሚቀርበት ሁኔታ፣ እንዲሁም
3. በዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት ውስጥ የተመለከቱ ድንጋጌዎችን አፈጻጸም ለማሟላት የሚያስፈልግ ማንኛቸውንም ጉዳዮች የሚመለከቱ፣ ደንቦችን ያወጣል።

38. <u>ስለ ሰነድ አጠባበቅ</u>

1. የህዝብ እንባ ጠባቂ ተቋም የሚመለከታቸውን ወገኖች በማማከር ስለ ሰነዶች አጠባበቅ፣ አስተዳደርና አወጋገድ የተግባር መመሪያ ያወጣል፣ መመሪያውን ከጊዜው ጋር ለማጣጣምም በየጊዜው አስፈላጊ ማሰተካከያዎችን ያደርጋል።
2. ማንኛውም የመንግስት አካል በእጁ የሚገኙ ሰነዶችን በተግባር መመሪያው መሰረት የመጠበቅ ግዴታ አለበት።
3. ማንኛውም የመንግስት አካል የግል መረጃዎችን ለማስተካከል የሚያስችል በቂ አሰራር የማዘጋጀት ግዴታ አለበት።

39. <u>ልዩ ልዩ ጉዳዮች</u>

1. በዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት ውስጥ የተመለከቱትን ግዴታዎችና ኃላፊነቶች በቅን ልቦና ለመፈፀም በተደረገ ማንኛውም ዓይነት ድርጊት በማንኛውም ሰው ላይ የፍታብሔር ወይም የወንጀል ኃላፊነት አይኖርም።
2. ማንኛውም ሰው የህግ ወይም የስራ ግዴታን በመተላለፍ ጥፋትን ወይም የህዝብ ጤንነትን፣ ደህንነትን ወይም የአካባቢያዊ ደህንነትን ጎጂ የሆነ ከባድ አደጋን የሚመለከት መረጃን በመግለፁ ለህጋዊ ወይም አስተዳደራዊ ቅጣቶች የማይዳርገው፣ መረጃዎቹ በእርግጥም ጥፋትን ወይም የህዝብ ጤንነትን ደህንነትን ወይም አካባቢያዊ ደህንነትን ጎጂ የሆነ ከባድ አደጋን ሊያሳዩ ይችላሉ የሚል ምክንያታዊ እምነት በመያዝ ድርጊቱን በቅን ልቡና የፈፀመው እንደሆነ ብቻ ነው።
3. ለንኡስ አንቀፅ 2 አላማ ከግለሰብ ድርጊት ጋር ተያያዥነት ቢኖረውም ባይኖረውም ጥፋት ማለት የወንጀል ድርጊት፣ የህግ ግዴታን መተላለፍ ፍትህ ማዛባት፣ ሙስና፣ ማጭበርበር፣ በስልጣን ያለአግባብ መጠቀም ወይም ከባድ የስነ ምግባር ጉድለት ማለት ነው።
4. በዚህ ክፍል ውስጥ የተረጋገጡትን መረጃ የማግኘት መብቶች ለመጣስ በማሰብ ሆን ብሎ ማንኛውንም ሰነድ ፣

ሀ/ያጠፋ፣ ያበላሸ ወይም የቀየረ ወይም የደለዘ ወይም፣

ለ/ የደበቀ፣ በተንኮል የከለከለ ወይም ፣

ሐ/ ያፋለሰ ወይም ሃሰተኛ ሰነድ የሰራ፣

ማንኛውም ሰው የወንጀል ጥፋቱ በፍርድ ሲረጋገጥበት በገንዘብ ወይም ከሁለት ዓመት በማይበልጥ እስራት ይቀጣል።

5. የህዝብ ግንኙነት ሃላፊው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 14 መሠረት ማመልከቻው ከመቅረቡ 25 ዓመት አስቀድሞ የሆነን፣ የተፈፀመን ፣ የተከሰተን ወይም የተደረገን ነገር የሚመለከት የመረጃ ጥያቄን ውድቅ ለማድረግ የሚችለው መረጃው በዚህ አዋጅ በአንቀፅ 16፣17፣18 እና 23 ድንጋጌዎች ውስጥ የማይሸፈን የሆነ እንደሆነ ብቻ ነው።

6. ሙስናን ወይም ሌላ ሕገ ወጥ አሰራርን ፣የሥራ አፈጻጸም ብቃት ጉድለትን፣ የግለሰብን ወይም የድርጅትን ቅሌት ለመሸፈን ማንኛውንም ሰነድ በምስጢር እንዲያዝ መወሰን ክልክል ነው።

## ክፍል አራት

## የመገናኛ ብዙኃን መብቶች እና ግዴታዎች

### 40. የእርማት ወይም

1. በመገናኛ ብዙሃን በቀረበ የፍሬ ነገር ዘገባ መልካም ስሙና ክብሩ የተጎዳበት ማንኛውም ሰው ዘገባው በቀረበበት መገናኛ ብዙሃን ላይ የለክፍ መልስ የመስጠት መብት አለው፡፡

   ሀ/ በየጊዜው የሚወጣው ህትመትአዘጋጅ ወየም በአዘጋጁ የተዋከለው ሰው የተላከለትን ምለሽ ዕለታዊ ጋዜጣ ከሆነ በ 3 ቀን ውስጥ ሳምንታዊ ጋዜጣ ከሆን በ 9 ቀን ውስጥ ወየም በሌላ አይነት ህትመት ከሆን በቀጣይ ሕትም የለ እርምት የማውጣት ግዴታ አለበት፡፡

   ለ/ ለመልሱ መነሻ የሆነው ዘገባ የተላለፈው በቴሌቪዥን ወይም በሬዲዮ ፕሮግራም ከሆነ ኃላፊ የሆነው አዘጋጅ ምላሹ ከደረሰበት ቀን ጀምሮ ባሉት 14 ቀናት ውስጥ በቀጣዩ የፕሮግራሙክፍል ወይም በተመሳሳይ ፕሮግራምያለእርማት ምላሹን በነፃ የማስተላለፍ ግዴታ አለበት።

   ሐ/ የሚቀርበው መልስ ከዘገባው ጋር የተያያዘ፣ ና ህጋዊ ይዘት ያለው መሆን ይኖርበታል።

   መ/ ዘገባው የተሰራጨው ምርጫ በሚካሔድበትወቅት ከሆነ በንኡሰ አንቀፅ 1 /ሀ/ እና /ለ/ የተጠቀሰው የጊዜ ገደብ 24 ሰአት፣ 14ቀኑ ገደብ ደግሞ ወደ 38 ሰዓት ዝቅ እንደተደረገ ይቆጠራል፡፡

መ/ ንዑስ አንቀፅ 1(መ) ድንጋጌ ተፈፃሚነት የሚኖረው ምላሹ ለመገናኛ ብዙሀኑ የደረሰው መላሹ የሚወጣበት ህትመት ወይም ፕሮግራም ለመታተም ወይም በአየር ከመለቀቁ ስድስት ቀደም ብሎ ከሆነ ቢቻ ነው፡፡

2. መልስ የመስጠት መብቱን የተነፈገ ማንኛውም ሰው የህትመቱ ወይም ፕሮግራሙ አዘጋጅ ተገዶ መልሱን እንዲያወጣለት ለፍርድ ቤት ማመልከት ይችላል፡፡

3. ማመልከቻው የቀረበለት ፍርድ ቤት ውሳኔውን በ 10 ቀናት ውስጥ መስጠት አለበት፡፡ ሆኖም በምርጫ ወቀተት ከሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻው ከቀረበለት በ 24 ሰዓት ውስጥ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

4. በወንጀል ህግ አንቀጽ 43 መሰረት ኃላፊ የሆነው ሰው መልሱን ለማውጣት ፈቃደኛ አለመሆኑን ከተረዳ ፍርድ ቤቱ ቅጣት ሊወስንበት ይችላል፡፡

5. የዚህ አንቀፅ ድንጋጌዎች በፍታብሔር ህግ 2049 የተመለከቱትን ከተፈፃሚነት አያስቀሩም፡፡

6. ከንኡስ አንቀፅ (1) እስከ (5) የተመለከቱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ቅሬታ የፈጠረው የመገናኛ ብዙሃን ውጤት ከተሰራጨበት ቀን ጀምሮ ባለው ሸስት ወር ጊዜ ውስጥ መልሰ የማውጣት ጥያቄው ለመገናኛ ብዙኀን የቀረበ ከሆነ ብቻ ነው፡፡

7. የዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ማንም ሰው እርሱን የሚመለከቱና በፍሬ ነገር ይዘታቸው ትክክለኛ ያልሆኑ የመገናኛ ብዙኀን ዘገባዎች እንዲታረሙለት ለማድረግ ባለው መብት ላይም

## ክፍል አምስት

## ሕጋዊ እርምጃዎችን ስለመውሰድ

### 41.ስለ ተጠያቂነት

1. በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ለሚፈፀም የወንጀል ድርጊት ወይም የፍታብሔር ጉዳት በወንጀል ህግ አንቀጽ 43 በተደነገገው መሠረት የምትክ ተጠያቂነት ካለበቸው ሰዎች ጋር የመገናኛ ብዙሃን ድርጅቱ በተደራቢነት ተጠያቂ ሊሆን ይችላል።

2. መገናኛ ብዙሃን አማካኝነት ለሚደርስ የስም ማጥፋት ጉዳት የፍታብሔር ክስ ከተመሠረተ እስከ ብር 100,000 /መቶ ሺ.ህ ብር/ የሚደርስ የህሊና የጉዳት ካሳ ሊወስን ይችላል።

3. በዚህ አዋጅ ክፍል አምስት እና ስድስት በተመለከቱ ድንጋጌዎችና በወንጀል ህጉ ድንጋጌዎች መሀከል ግጭት ከተፈጠረ የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

4. የወንጀል ክሱ በይርጋ ቢታገድም ሆነ ውድቅ ቢደረግ እንኳን በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት ለደረሰ ጉዳት የፍትሐብሔር ክስ ሊቀርብ ይችላል።

42.<u>የእገዳ እርምጃዎችን ስለመውሰድ</u>

1. በሌላ ህግ በሌላ ሁኔታ የተደነገገ ቢኖርም በዚህ አንቀፅ ከተደነገገው ውጭ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም መፅሀፍ ሊታገድ አይችልም።

2. እንደነገሩ ሁኔታ የፌደራል ወይም የክልል አቃቤ ህግ በብሄራዊ ደህንነት ላይ ከስርጭት በኋላ በማስቀጣት ሊቀለበስ የማይችል ግልጽና ድርስ የሆነ ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል በየጊዜው የሚወጣ ህገ ወጥ ህትመት ወይም መፅሀፍ ሊሰራጭ መሆኑን ለማመን በቂ ምክንያት ሲኖረው የህትመት ውጤቱ እንዳይሰራጭ ለማዘዝ ይችላል፡፡

3. አቃቤ ሕግ ከነገሩ አጣዳፊነት የተነሳ ጉዳቱን ለመከላከል የፍርድ ቤት የማገጃ ትእዛዝ በፍጥነት ማግኘት ባልቻለ ጊዜ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም መፅሀፍ እንዲታገድ ትእዛዝ መሰጠት ይችላል፡፡ ሆኖም አቃቤ ሕግ አንድን በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም መፅሀፍ ከስርጭት እንዲታገድ ውሳኔ ሲሰጥ ውሳኔው በተሰጠ 48 ሰዓት ውስጥ ለፍርድ ቤት ማስታወቅ አለበት፡፡ ፍርድ ቤቱ የአቃቤ ሕጉ የእገዳ ማስታወቂያ ከደረሰው ጊዜ ጀምሮ በ 24 ሰዓት ውስጥ የእግድ እርምጃውን የሚያፀድቅ መሆን አለመሆኑን በውሳኔ ማሳወቅ አለበት፡፡

4. ፍርድ ቤቱ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም መፅሀፍ እንዲታገድ በአቃቤ ሕግ የተሰጠው ትእዛዝ ሲቀርብለት፡

ሀ/ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም መፅሀፍ ህገወጥና ከፍተኛ ጉዳት የሚያስከትል ሆኖ ካገኘው የአቃቤ ህጉን ትእዛዝ በማፅደቅ አቃቤ ሕጉን የማገድ እርምጃ ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ባለው የሁለት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ክሱን እንዲመሠርት ወይም ሕትመቱ እንዲወረስ ማመልከቻ እንዲያቀርብ ማዘዝ አለበት፡፡ አቃቤ ሕግ በተሰጠው ትእዛዝ መሠረት ካልፈጸመ ፍርድ ቤቱ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም መፅሀፍ እንዲያዝና ስርጭቱም እንዲቋረጥ የሰጠውን ትእዛዝ ያነሳል።

ለ/ በየጊዜው የሚወጣው ህትመት ወይም መፅሀፍ ሕግን የማይተሳለፍና ከፍተኛ ጉዳትን የማያስከትል ሆኖ ካገኘው በአቃቤ ህጉ የተሰጠውን የእገዳ

ትእዛዝ ውድቅ በማድረግ የታገደው ህትመት እንዲለቀቅ ትእዛዝ ሊሰጥ ይችላል፡፡

ፍርድ ቤቱ የሰጠው ትእዛዝ በይግባኝ ሰሚ ፍርድቤት ካልታገደ በስተቀር ትእዛዙ በተሰጠ በ 72 ሰአት ጊዜ ውስጥ ይፈፀማል፡፡

5. በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም መፅሀፍ ላይ የወንጀል ክስ ከተመሰረተ ወይም ውጤቱ እንዲወረስ ማመልከቻ ከቀረበ ፍርድ ቤቱ ሕትመቱ እንዲያዝና እንደ አስፈላጊነቱ ቀጣይ እትሞችን ከማውጣት እንዲታገድ ወይም የህትመት ስራው እንዲወረስ ሊወስን ወይም በንዑስ አንቀጽ 3 መሠረት የህትመቱ ስርጭት እንዲታገድ የሰጠውን ውሳኔ ለመሰረዝ ይችላል፡፡
6. በህትመት አማካይነት ወንጀል ከተፈፀመና በወንጀል ህግ መሰረት ኃላፊ የሚሆነው ሰው ካልተገኘ የግል ተበዳዩ ወይም አቃቤ ህጉ የወንጀል ክስ ከሚመሰረት ህትመቱ እንዲወረስ ለፍርድ ቤቱ ማመልከት ይችላሉ። ለወንጀሉ ኃላፊ ለሚሆነው ሰው በሀገር ውስጥ መጥሪያ ለመስጠት በማይቻልበት ጊዜም በተመሳሳይ ማመልከቻ ማቅረብ ይቻላል፡፡
7. በእገዳው ከሚሸፈነው ጉዳይ ባህሪ ወይም በሌላ በቂ በሆነ ምክንያት የተነሳ አቃቤ ህጉ በንኡስ አንቀፅ 4 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ክሱን ለማቅረብ የማይችል ከሆነ በአቃቤ ሕጉ ጥያቄ ፍርድ ቤቱ የክስ ማቅረብያ ጊዜውን እስከ ሁለት ሳምንት ሊያራዝመው ይችላል፡፡
8. በየጊዜው የሚወጣ ህትመት ወይም መጽሐፍ ስርጭት ላይ የሚሰጥ የእገዳ ትእዛዝ ለትእዛዙ መነሻ የሆነውን አንቀፅ ወይም አንቀፆች፣ የህመቱን ቅፅ በጽሑፉ የወጣበትን እትም መግለፅ አለበት፡፡
9. በየጊዜው በሚወጣ ህትመት እና መፅሀፍ ላይ የሚሰጥ እገዳ ለስርያጭት በተዘጋጁ ህትመቶች ላይ ብቻ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡ የእገዳ ትእዛዙ በፖሊስ አማካይነት ወዲያውኑ መፈፀም አለበት፡፡
10. አቃቤ ህግ በዚህ አንቀጽ የተሰጠውን ስልጣን አግባብ በሌለው መንገድ የተጠቀመበት እንደሆነ በህግ ይጠየቃል፡፡

43. <u>ከመገናኛ ብዙሃን ጋር የተያያዙ ክሶች ስለሚቀርቡበትና ስለሚሰሙበት ሁኔታ</u>

1. በመገናኛ ብዙሃን አማካኝነት የወንጀል ድርጊት በመፈፀም የተጠረጠረ ማንኛውም ሰው ጠቅላይ ዐቃቤ ሕጉ ካልወሰነ በስተቀር በወ/መ/ሕ/ሥ/ሥ 59 (2) እና (3 ድንጋጌዎች መሠረት ለተጨማሪ ምርመራ በእስር እንዲቆይ ሳይደረግ ክሱ በቀጥታ ለፍርድ ቤት መቅረብ አለበት፡፡

2. ክሱን ለመስማት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት የክስ ማመልከቻው በቀረበለት በ15 ቀናት ውስጥ ክሱ እንዲሰማ ማድረግ አለበት፡፡
3. ፍርድ ቤቱ ክሱ ከመሰማቱ ቢያንስ ከአምስት ቀናት በፊት የክሱን ማመልከቻ ግልባጭ ወይም ቅጂ እንዲሁም የቀረቡ ማስረጃዎች ካሉ ለተከሳሹ እንዲደርስ ማድረግ አለበት፡፡
4. ክሱን የሚሰማው ፍርድ ቤት ክሱ መሰማት ከጀመረበት ቀን አንስቶ እጅግ ቢበዛ በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ፍርድ መስጠት ይኖርበታል።
5. ተከሳሹ በአድራሻው ያልተገኘ እንደሆነ ወይም ጥሪው ደርሶት በ 7 ቀናት ውስጥ ካልቀረበ ጉዳዩ በሌለበት ታይቶ እንደሚወሰን ፍርድ ቤት በጋዜጣ መጥሪያ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡
6. ተከሳሹ በሌለበት በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካለው በአንቀጽ 44 መሰረት ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡
7. የወንጀል ክስ ለመመስረት የግል ተበዳይ አቤቱታ ከማያስፈልጋቸውና በሀገ መንግስቱ በተቋቋሙ የህግ አስፈፃሚ ወይም የፍርድ ቤቶች ባለስልጣኖች ላይ ከሚፈፀሙ የስም ማጥፋትና የሀሰት ወንጀል ድርጊቶች በስተቀር በግለሰቦችና በግል ድርጅቶች ላይ በብዙሀን መገናኛ አማካኝነት የሚፈፀሙ የስም ማጥፋትና በሀሰት የመወንጀል ክሶች በራሳቸው በግል ተበዳዮቹ መቅረብ አለባቸው።
8. ፍርድ ቤት በንዑስ አንቀጽ 4 መሰረት የሰጠውን ውሳኔ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ወይም ለክልል ማስታወቂያ ቢሮ እንዲደርሰው ማዘዝ አለበተ፡፡

44. <u>ስለ ይግባኝ</u>

1. በተሰጠው ፍርድ ቅር የተሰኘ ወገን የይግባኝ ማመልከቻውን ፍርዱ በተሰጠ በ 30 ቀናት ውስጥ ለሚመለከተው ፍርድ ቤት ማቅረብ አለበት። ፍርዱንየሰጠው ፍርድ ቤትም አመልካቹ ይግባኝ ለማቅረብ የሚፈልግ መሆኑን ካሳወቀበት ጊዜ ጀምሮ በ 24 ሰዓት ውስጥ የፍርዱን ግልባጭ ለአመልካች መስጠት አለቡት።
2. ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት ይግባኙ በቀረበለት በ 10 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠተ አለበት፡፡

45. <u>ስለ ቅጣት</u>

1. ከአንቀጽ 7(1) እስከ (3) የተደነገገውን የተላለፈ ማንኛውም ሰው ከብር 20000 /ሀያ ሺህ ብር/ ባላነሰ ከብር 200000 /ሁለት መቶ ሺህ ብር/ ባልበለጠ የገንዘብ መቅጮ ይቀጣል።
2. አንቀፅ 6(2)ን በመተላለፍ ሃላፊነት የሚቀበል አዘጋጅ ያልሰየመ ወይም በአንቀፅ 9(6) የተደነገገውን ግዴታ የጣሰ ወይም በአንቀፅ 10 የተመለከቱትን ግዴታዎች ያላሟላ በየጊዜው የሚወጣ ህትመት አሳታሚ ወይም ብሮድካስተር እስከ ብር 15,000 ( አሰራ አምስት ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
3. በአንቀፅ 40 መሰረት በህትመቱ ላይ እንዲያወጣው የተላከለትን መልስ ወይም ማስተካከያ ያላወጣ ዋና አዘጋጅ ወይም የፕሮግራም አዘጋጅ እስከ 10,000.00 ብር /አስር ሺህ ብር/ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል። ጥፋቱ የተፈፀመው በምርጫ ወቅት ከሆነ እስከ ብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ።
4. የአንቀጽ 6(1) ወይም የአንቀፅ 8 ድንጋጌን የተላለፈ ማንኛውም ሰው እስከ ብር 15,000 /አስራ አምስት ሺህ ብር/ በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።
5. በመገናኛ ብዙሃን አማካይነት በተፈፀመ ወንጀል ተከሳሹ ጥፋተኛ መሆኑን ካረጋገጠ የጥፋተኝነት ውሳኔው ታትሞ እንዲወጣ ሲጠየቅ ፍርድ ቤቱ ውሳኔው በህትመቱ ላይ እንዲወጣ ትዕዛዝ መስጠት ይችላል፡፡
6. ፍርድ ቤቱ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበት ወይም ህተመቶቹ እንዲያዙ ትእዛዝ የተሰጠበት የመገናኛ ብዙሃን ውጤት እንዳይሰራጭ ሊያግድ ይችላል፡፡

46.<u>ስለ ይርጋ</u>

1. በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 28/1/ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች በመተላለፍ የሚፈጸሙ የወንጀል ጥፋቶች ህትመተቹ ከተሰራጩበት ወይም ከተላለፉበት ቀን አንስቶ እስከ አንድ ዓመት ባለው ጊዜ ውስጥ ክሶቹ ካልቀረቡ በይርጋ ቀሪ ይሆናሉ።
2. በብሮድካስት አማካይነት ለሚፈፀም ጥፋት ጥፋቱ የተፈፀመበት ፕሮግራም ከተላለፈበት ቀን ጀምሮ ባለው ስድስት ወር ጊዜ ውስጥ የወንጀል ክስ ካልተመሰረተ ክሱ በይርጋ ቀሪ ይሆናል፡፡

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

47. <u>የአፈፃፀም ወሰን</u>

1. ይህ አዋጅ በማንኛውም የሕትመት ስራ ላይ ተፈፃሚ ሊሆን የሚችለው፡

ሀ/ ለሕትመት ስራው በዚህ አዋጅ መሰረት የምዝገባ ምስክር ወረቀት የተሰጠ ከሆነ፡

ለ/ የህትመት ስራው የተባዛ መሆኑን፤ የአሳታሚውን ወይም የአታሚውን ማንነት፣ የታተመበትን አድራሻና ዓመተ ምህረት የሚገልፅ ፅሁፍ ያለበት ከሆነ፣

ብቻ ነው።

2. የህትመት ስራዎች እንደመገናኛ ብዙሃን የሚታዩት ተባዝተው ለስርጭት ወይም ለሽያጭ ሲቀርቡ ወይም ብሮድካስት ሲደረጉ ነው ።

3. በዚህ አዋጅ በሌላ ሁኔታ የተነገረው እንደተጠበቀ ሆኖ ከፅሁፍ ጋር አብሮ የወጣ ባይሆንም ማንኛውም ስዕል እንደሕትመት ስራ ይቆጠራል።

4. በሽያጭ ወይም ያለክፍያ የተሰራጩ ማንኛቸውም ወሲብ ነክ ይዘት ባላቸው ሕትመቶች ላይ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ አይሆንም። ስለእነዚህ የህትመት ስራዎች ስርጭትና ህትመት በሚመለከት ዝርዝሩ በህግ ይወሰናል፡፡

48.<u>የመሸጋገሪ ድንጋጌ</u>

1. ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት ተቋቁሞ የፕሬስ ስራ በማካሄድ ላይ የሚገኝ ማንኛውም ፕሬስ ይህ አዋጅ ከጸናበት ቀን ጀምሮ ባሉት 90 ቀናት ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ 9 በተመለከተው መሰረት መመዝገብና የምዝገባ ምስክር ወረቀት ማግኘት አለበት፡፡

2. አስፈላጊ የሆኑ ሁኔታዎችን ለማዘጋጀት ሲባል የዚህ አዋጅ ክፍል ሶስት ድንጋጌዎች ተፈጻሚ የሚሆኑት አዋጁ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ከሁለት ዓመት በኋላ ሲሆን የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከአንድ አመት ላልበለጠ ጊዜ ሊያራዝመው ይችላል፡፡

49. <u>ከአዋጁ ጋር ስለሚቃረኑ ህጎች</u>

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ደንብ፣ መመሪያ፣ ትእዛዝ ወይም የተለመደ አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ አይሆንም።

50. <u>ስለተሻሩ ሕጎች</u>

የዚህ አዋጅ ክፍል 3 ድንጋጌዎች በስራ ላይ እስከሚውሉበት ጊዜ ድረስ ተፈጻሚ ከሚሆኑት የፕሬስ አዋጅ ቁጥር 34/85 አንቀጽ 8 እና 19 በስተቀር ቀሪዎቹ የአዋጁ ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

51.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ህዳር 25 2001 ዓ.ም**

**ግርማ ወልደጊዮርጊስ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**